Gide Mariam Ejigu
Jan 2014

# መጽሐፍ ቅዱስ

## በምሕጻረ ቃል

(Condensed Bible)

ከትምህርታዊ ትርጉም ጋር
ለፈጣን ጥናትና
ልዩ ግንዛቤ

ክፍል \፩ /Vol 1

ስምንቱ ብሔረ ኦሪት /Pentateuch,
Including Joshua, Judges & Ruth

በ

መጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው /Rev Mekbib Atnaw

ታኅሣሥ \፳፻፭ ዓ/ም /December 2012

www.ethiopianorthodox.org

# መክሥተ አርእስት
## ( Contents )

**ተራ ቁጥር** — **የገጽ ብዛት**


1. ልዩ ማስታወሻ ---------------------------------------- ፪ /II
2. አሪት ዘፍጥረት ---------------------------------------- 1 - 83
3. አሪት ዘፀአት ---------------------------------------- 84 -115
4. አሪት ዘሌዋውያን ----------------------------------------115 - 127
5. አሪት ዘኍልቍ ---------------------------------------- 128 -147
6. አሪት ዘዳግም ---------------------------------------- 148--161
7. መጽሐፈ ኢያሱ ---------------------------------------- 162 -177
9. መጽሐፈ መሳፍንት ---------------------------------------- 178 -202
10. መጽሐፈ ሩት ---------------------------------------- 103 -215



ተኀትመ ዝንቱ መጽሐፍ በወርኀ ታኅሣሥ ፳፻፬ ዓ/ም ( Dec 2011 ) በትዕይንተ አዲስ አበባ አመ ፲፰ ዓመተ በትረ ፓትርያርክናሁ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ፡ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት





www.ethiopianorthodox.org

# ''''''''''' ልዩ ማስታወሻ'''''''''''

ለመንፈሳውያን ኮሌጆች፡ (Seminaries): ለካህናት ማሠልጠኛ፡ ለሰንበት-ት/ቤቶች_ተማሪዎችና_ባጠቃላ_ለጐልማሶች ማስተማሪያ - Adult Education መጽሐፍ እና ለመላላክ ትምህርትም አመቺ ሁኔታን በመፍጠር ኃምሳ አሬት ዓመት ሙሉ በሺህ የሚቆጠሩ መጻሕፍትን በማንበብና በማገናዘብ ዐርባ ሁለት ዓመት የፈጀ ጥናት ተካሂዶበት የተቀበረና የኢት. ኦ. ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ጉባኤ አይቶት ተስማምቶበት የታተመ፡ ራስን በራስ በማስተማር ጭምር የሚረዳ የእጅ መጽሐፍ (Text Book) ነው:: ቅዱሳት መጻሕፍትን በግል ማጥናት- ለሚሹ ምእመናንና ምእመናትም ሁሉ አመቺ-ሁኔታን ለመፍጠር ኃምሳ ዐሬት ዓመት ሙሉ ልዩ፡ ልዩ መጻሕፍትን በማንበና በማገናዘብ ዐርባ ሁለት ዓመት የፈጀ- ጥናት ተካሂዶበት-የተጠናቀቀ፡ ራስን- በራስ ማስተማሪያ (Text Book) ነው ።

_ስለዚህ ይህ መጽሐፍ እንደ አንድ የጥናት አማራጭ ሆኖ ቢወሰድ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማወቅ እንዲረዳና ወደ ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ምልአተ- አእምሮ ፡ የከፍተኛ እውቀት መንደርደሪያና፡ መሸጋገሪያ ድልድይ (ማዕዶት) ይሆን ዘንድ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ በማሳጠር / ባስተዋፅኦ መልክ ከትርጓሜ ጋር የተቀመረ /የተዘጋጀ ነው።

**የቃላት ትርጓሜ:** በመሠረቱ " አሬት " ብርሃን ማለት ነው:: የጥንት ባቢሎናውያን--በብርሃን ያመልኩ ነበርና። በክላውዴዎን ምድር ቀድሞ የአብርሃም ቤተሰብ ይኖርባት የነበረችው ከተማ ኡር ተብላ ትጠራ ነበር ፣ አሬት የሚለው ስም ከዚያ ሲያይዝ የመጣ ነው:: አሪዮ ፣ አሪያሬስ ፣ አሪዮን፣አሪያ የተሰኙትም- ስሞች ከዚሁ ቃል የሠረፁ /የተገኙ ናቸው ።

"ብሉይ ኪዳን"፦ የጥንት ዘመን ቃል ኪዳን ማለት ነው። እግዚአብሔር ብሔር አምላክ ለቀደምት አበው ቃል ኪዳን ገብቶላቸው፣ እነርሱ በሕገ አሬት የተሰጣቸውን ትእዛዝ /መመሪያ ሕግ ሊጠብቁ፣ እርሱም ከክፉ ነገር ሁሉ ሊጠብቃቸውና ከዓለም ማኅበረሰብ መካከል መርጦ ለራሱ የተለየ ሕዝብ ( ቤተ- ሰብ ) አድርጎ- በጸጋ ሊቀበላቸው፣ስምምነት- (ውሉታ ያደረገበት- የጥንት ዘመን ቃል ኪዳን ማዘከሪያና ማጠናከሪያ መጽሐፍ ማ ለት ነው::



# ኦሬት ዘፍጥረት

( መጽሐፈ ሙሴ ቀዳማዊት)

**መግቢያ:** > ኦሬት ዘፍጥረት ( ዘልደት ) ስለ ኽያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት፡ ስለ ሰው ዘር አመጣጥ፡ ኃጢአት ወደ ዓለም እንዴት እንደገባ፡ ስለ ሰው ዘር ሀልውና-/ሥርዓተ ኑሮ አጀማመር ፡ እግዚአብሔር ከሰው ዘርና ከሊሎችም ፍጥረታት ጋር ስላለው ግንኙነት የሚናገር መጽሐፍ ነው። ዋና፡ ዋና ክፍልቹም በሁለት ረድፍ ተመድብው መታየት ይችላሉ፡ ይኸውም ክፍል አንድ፡--> ከምዕራፍ 1 እስከ 11 ስለ ዓለማት አፈጣጠር ፡ ስለ ሰው ዘር ቅድመ ታሪክ ሕገ ልቡናዊ አኗኗር በአዳምና ሔዋን፡ በቃየልና አቤል፡ ይጀምርና ከአዳም እስከ ኖኅ የነበሩትን አበው ታሪክ፡ በኖኅ ዘመን የተስፋፋ ገድብ -የለሽ ኃጢአት ያስከተለውን የጥፋት ውኃ፡ እንዲሁም ከጥፋት ውኃ በኋላ በተነሣው ትውልድ ተጀምሮ ስለነብረው የባብሎን ግንብ፡ ስለቋንቋ መከፋፍፈልና ስለሰው ዘር መበታተን (ዝርወት) ይናገራል።

**ክፍል ሁለት:** > ከምዕራፍ 12 እስከ -50 ከአብርሃም መጠራት ጀምሮ ስለ እስራኤላውያን ቅድመ አያቶች ይናገራል። ከነርሱም መካከል የአብርሃምን፡ የይሳሐንና የያዕቆብን በትረያሬክነት ( የአባቶች አባትነት) አየተረከ፡ እግዚአብሔር በዮሴፍ ላይ ጸጋና በረከትን አሳድሮ ድንቅ ሥራውን በመግለጥ የግብጽ ጠቅላይ ገዢ ለመሆን አብቅቶት፡ በዘመነ ረኀብ እንዴት እንደታደጋቸውና ሲመግባቸው እንደኖረ ያሳያል። ይዕቆብ ዐሥራ ሁለት ነገደ እስራኤል የተባሉ ልጆቹን ሲባርክ ወደፊት የሚገጥማቸውን ክፉውንም ሆነ ደጉን ነገር ሁሉ እንዴት እንደገለጠላቸው ያመለክትና በዮሴፍ ሞት ይደመደማል።

> መጽሐፉ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ሁሉ ጐልቶ የሚታይበት ፍጹም ታሪካዊና ፍጹም ትምህርታዊም ሆኖ በጥሩ ሥነ ጽሑፍ የተገነባ ነው። ስለዚህም አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ ብቻ ተነብቦ የሚታለፍ ሳይሆን እስከ ሕይወት ፍጻሜ ድረስ በልብ ሠርፆ እንዲኖር በስፋትና በጥልቀት መጠናት- የሚገባውና -ልጆች ሁሉ ሊማሩት የሚያስፈልግ ዋና መሠረታዊ የሕይወት መመሪያ ነው።

''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

www.ethiopianorthodox.org

## ፩/1 የዓለም-ሥነ ፍጥረት ሁሉ መጀመሪያ ታሪክ

1 በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ። 2 ምድርም
ቅርጽ የሌላት ባዶ ነበረች። ጨለማ በጥልቁ ላይ ነበር።
የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ይሠፍ ነበር። 3 እግዚአብ
ሔር "ብርሃን ይሁን" - አለ ፡ ብርሃንም ሆነ ። 4 እግዚአብሔር
የፈጠረው ብርሃን መልካም መሆኑን አየ ። 5 ብርሃንንም ከጨለማ
ለይቶ ቀን ብሎ ጠራው፡ ጨለማውን ሌሊት አለው። የብርሃንና-
የጨለማው-ጊዜ አንድ ቀን-ሆነ። (ትርጓሜ ፡ " ብርሃንን ሠራሁ፡ ጨላማንም ፈጠርሁ' ይላል ጌታ እግዚአብሔር ኢ.ሳ 45 ፡ 7) ። ከብርሃን ተፈጥሮ ጋር በማገናዘብ፡ ይህ ጥቅስ ያስፈለገበት ምክንያት ፡ አንዳንድ ተፈላሳፊዎች "ጨለማ የብርሃን መታጣት ነው እንጂ ራሱን የቻለ ፍጥረት አይደለም " ይላሉ። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል ግን ጨለማ ራሱን ችሎ ከኻያ ሁለቱ ፍጥረታት አንዱ ነው።

## የኻያ ሁለቱ ሥነ ፍጥረት ክፍሎች አመዳደብ፡ - ቊ 6 -25

በዕለተ እሑድ የተፈጠሩ፡ ስምንት ናቸው፡- እነርሱም-መሬት፡ ውኃ፡ እሳት፡ ነፋስ፡ ጨለማ፡ ብርሃን፡ ሰማያትና መላእክት። (መላእክት በዕለተ እሑድ ስለመፈጠራቸው መጽሐፈ ኵፋሌ ሞዕራፍ 2፡ 6 -7 ያስረዳል።) ሰኞ--የተፈጠረ፡ አንድ ብቻ ነው።ይኸውም ውኃዎችን ከፍሎ በውኃዎች መካከል ጠፈር እንዲኖር አድርጎ ሰማይ ብሎ ጠራው፡ በምድር ያለውን የውኃ መከማቻ ውቅያኖስ" አለው ።

ማክሰኞ- የተፈጠሩ ፡ 1. አዝርዕት፡ 2. አትክልትና፡ 3. ዕፀዋት /ዛፎች።

ረቡዕ -የተፈጠሩ፡ ሦስት ናቸው፡-1. ፀሐይ፡ 2. ጨረቃና 3. ከዋክብት።

ሐሙስ -_ከውሃ የተፈጠሩ ሦስት ናቸው፡ እነርሱም በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው በባሕርና በውኃ አጠገብ /አካባቢ. የሚኖሩ ፡ 1. በእግር የሚሽከ ረከሩ፡ 2.. በክንፍ የሚበሩ፡ 3 በልብ የሚሳቡ ተሐዋስያን። ዓርብ --ከደረቅ ምድር የተፈጠሩ ዐራት ናቸው፡ እነርሱም፡ 1 በእግር የሚሽረከሩ ፡ 2 በክንፍ የሚበሩ፡ 3. በልብ የሚሳቡ ተሐዋስያን /ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት፡ 4 የፍጥረታት ሁሉ መደምደሚያ ሰው።

(ማስታወሻ፡ጠቈር ብለው የተጻፉት ሕያዋን /Living things ሲሆኑ ነጣ ብለው የተጻፉት ግን ግዑዛን (Non Living things) ናቸው።)



### የሰው ዘር ተፈጥሮና የተሰጠው በረከት (ቊ 25 -30 )

_ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር " ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን አድርገን እንፍጠር' አለ ። ወንድና ሴት አድርጎ ፈጥሮ እንዲህ ሲል ባረካቸው፡-"ብዙ፡ ተባዙ ። ምድርንም ሙሉአት ፡ ግዙዋትም። የባሕር ዓሣዎችን፡ የሰማይ ወፎችን፡ ፡ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱ ፍጥረታትን ሁሉ ግዙዋቸው ። እነሆ ምግብ እንዲሆንላችሁ በውስጡ ዘር ያለውን ፡ ፍሬ የሚያፈራውን ለምለም ተክል /ዛፍን ሁሉ ሰጠኋችሁ። በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው ለሚኖሩ እንስሳት ፡ አራዊትና ለሰማይ ወፎች፡ ለሌሎች ተንቀሳቃሽ ጥረታትም ሁሉ በምድር ላይ የሚበቅል ሐመልማል ሁሉ ምግብ ይሆንላቸው ዘንድ ሰጥቻለሁ"።
31 እግዚአብሔር የፈጠረው ነገር ሁሉ እጅግ መልካም እንደ ሆነ አየ።

## እንደ ድልድይ ሆኖ ብሉይ ኪዳንን ከሐዲስ ኪዳን ጋር የሚያገናኝ ትርጓሜ /Interpretations

To Bring The Old & New Testaments Together

በቊጥር 1 "እግዚአብሔር" የሚለው ስም በነጠላና በብዙ የሚነገር ነው። በነጠላ ሲነገር የእግዚአብሔርን አንድነት ይገልጣል። በብዛት ሲሆን ደግሞ ሦስትነቱን ያሳያል። " ወሶበ እቤ እግዚአብሔር እብል በእንተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ = እግዚአብሔር ብዬ በምጠራበት ጊዜ ስለ አብ ፡ ስለ ወልድ ፡ ስለመንፈስ ዱስም መናገሬ ነው" ሲል ቅ/ ጎርጎሬዎስ እንዳስተማረ (በሃይማኖተ አበው-ትንሣኤ ማሳተሚያ ድርጅት ጥር 30፡ 1967 ዓ /ም ገጽ 420 ይመልከቱ ) ።

በቊ 2 ፡ " ምድር ቅርጽ የሌላት ባዶ ነበረች" የሚለው ቃል ከሰው ሕይወት ጋር በማነጻጸር ሲታይ ፡ እግዚአብሔር በተናገረው በቅዱስ መጽሐፍ ቃል ከመታነፅ በፊት የሚኖረውን የመንፈስ ወይም የአእምሮ ባዶነት ያመለክታል። "እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ! አእምሮዬን በቅዱስ ቃልህ ከማብራትህ በፊት እኔ ራሴ ምንም ቅርጽ እንደሌላት ባዶ ምድር ነበርኩ-"እንዳለ ደራሲ ከዛሬ 500 ዓመት በፊት "ክርስቶስን መምሰል" በሚል ርእስ በጻፈው ቃለ ምክር ወትምህርት።

ከቊጥር 3-4 ስለ ብርሃን ተፈጥሮ የተነገረው ቃል በጠፈረ ሰማይ ላይ የሚያበሩ ፀሐይ፡ ጨረቃና ከዋክብት ከመፈጠራቸው በፊት ይህ ዓለም በብርሃን የተሞላ ሆኖ መፈጠሩን ያሳያል። ለምሳሌ እንጨቱ ከእንጨት ቢፋጭ፡ ድንጋዩ ከድጋይ ቢጋጭ እሳት - ወለድ ብርሃን



www.ethiopianorthodox.org

*ይወጣል። በከርሠ-ምድር ያለው እሳተ ገሞራና የመብረቅ ብልጭታ ሁሉ፡ ከውሃ-የሚመነጭ የኤሌክትሪክ መብራት ኃይል፡ ልዩ ፡ ልዩ ብርሃን የሚያንጸባርቁ የዕንቍ ዓይነቶች አሉ ። ለምሳሌ ቶጳዝዮንና ቢረሌ የተባሉት አዕናቍ የሚያብረቀርቅ_ልዩ ብርሃን ያፈልቃሉ ። መረግድ የሚባለውም ዕንቍ፡ ልዩ አረንጓዴ ብርሃን ይሰጣል -ዘፀ 28 :17 -21። _ከዚህም ሁሉ ጋር ከራሱ ከእግዚአብ ሔር ባሕርይ የሚፈልቅ ልዩ የብርሃን ጐርፍ መኖሩም ተጽፏል- መዝ 139፡ 12+ መጽሐፈ ራእይ 21፡ 23 -24 ) ። እግዚአብ-ሔር ራሱ አማናዊ ብርሃን ተብሎ ይጠራል። ( 1 ዮሐ 1፡ 5 ። ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስም ከእማናዊ ብርሃን የተገኘ አማናዊ ብርሃን ነው ( ዮሐ 1፡ 5 )።*

*በቍ 20 -23 እንደተጻፈ፡ ሕይወት ለመጀመሪያ ጊዜ ከውሃ እንደተገኘች ፡ የክርስትና ሃይማኖትም አዲስ ሕይወት በውኃ ጥምቀት እንዲጀመር የአምላክ ፈቃድ-ሆኗል ። በዕለተ- ዓርብ- ለአዳም ሁለት ታላላቅ ነገሮች ተፈጽመውለታል ። ይህም ማለት ፡ 1ኛ ተፈጥሮባታል;; 2ኛ ከዘለዓለም ፍዳ ነጻ ወጥቶ ወደ ገነት የተመለሰባት ቀን ጌታ በራሱ ቅዱስ ፈቃድ ለቤዛ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ በቀራንዮ የተሰቀልባት ዕለተ ዓርብ ናት።)*

**፪/2. የ<u>ሰባተኛው ዕለት ቅድስና</u>፡** 1--3 እግዚአብሔር አምላክ ሰብባኛውን ቀን ( *ቅዳሜን* ) ከዕለታት ሁሉ ለይቶ ባረከው /ቀደሰው። የዕረፍት ቀንም አደረገው። 6 እግዚአብሔር በምድር ላይ ዝናም ማዝነም ገና አልጀመረም ነበርና። ጉም ከመሬት ወጥታ እየተሳበች የምድርን ገጽ ታጠጣ ነበር። 7 እግዚአብሔር አምላክም ከመሬት አፈር የፈጠረውን ሰው በአፍንጫው እፍ ብሎ የሕይወትን እስትንፋስ አሳደረበት ።ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ ።

<u>እግዚአብሐር ያዘጋጃት የተድላ -ደስታ ገነት ፡</u>

8 –11፡ እግዚአብሔር አምላክም ከዔድን በስተምሥራቅ ገነትን (የአትክልትን ) ቦታ አዘጋጀ። በዚያም ለማየት ደስ የሚያሰኙና ለምግብነትም የሚጠቅሙ ተክሎችንና ዛፎችን ሁሉ አበቀለ ። በነዚያ ዛፎችና ተክሎች መካከል የሕይወት ዛፍና እንዲሁም ክፉና ደጉን ለይቶ የሚያሳውቅ ዛፍ ነበሩ። ገነትንም የሚያጠጣ ወንዝ ከዔደን ፈልቆ ይፈስ ነበር። ያም ወንዝ በዐራት ተከፈለ። 12-14 የመጀመሪያ ወንዝ ፊሶን ( ኤፌሶን ) ተብሎ የሚጠራው ሲሆን፡ የሐዊላን ምድር የሚከብ ነው ። እርሱም ንጹሕ ወርቅና ሽቶ፡ የከበረ ድንጋይ - ሉል የሚገኝበት ነው ። የ2ኛው ወንዝ ስም ግዮን /ዓባይ ሲሆን እርሱም



የኩሽ ምድር የተባለች ኢትዮጵያን ይከባል። 3ኛው ወንዝ ጤግሮስ ከአሶር በስተምሥራቅ የሚፈስ ሲሆን 4ኛውወንዝ ኤፍራጥስ ነው ። 15-17፡ ግዚአብሔር አምላክ ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው "በገነት ከሚገኙት ዛፎችና ተክሎች ፍሬ ሁሉ ትበላለህ። ነገር ግን ክፉና ደጉን ለይቶ ከሚያሳውቅ ዛፍ ፍሬ እንዳትበላ ተጠንቀቅ ። ከዚያ ዛፍ ፍሬ በምትበላበት ቀን በእውነት እንደምትሞት እወቅ" ።

16–18 ደግሞም እግዚአብሔር "ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም ተስማሚ የኑሮ ጓደኛ እንፍጠርለት" አለ ። 18- 19 ከዚያ በፊት ግን እግዚአብሔር የፈጠራቸውን እንስሳትና፡ አራዊት፡ የሰማይ ወፎችንና ሌሎችንም ፍጥረታት ሁሉ ምን ብሎ እንደሚጠራቸው ለማየት ወደ አዳም አመጣቸው፡ አዳም ለያንዳንዱ ፍጥረት መጠሪያ ስም አወጣላቸው። 20--24 ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አምላክ በአዳም ላይ ከበድ እንቅልፍ አመጣበትና ተኝቶ ሳለ፡ ከጎኑ አጥንቶች አንዲቱን አንሥቶ ፡ ሴት አድርጎ ሠራት።አምጥቶም ፡ ለአዳም አስረከበው ። አዳምም "እርሷ -ከእኔ አጥንትና ሥጋ የተገኘች ናትና ሴት ትባል" አለ። ከዚህም የተነሣ ሰው አባቱንና እናቱን ትቶ ከሚስቱ ጋር ይተባበራል። ሁለቱ እንድ ሥጋ፡ አንድ አካል ይሆናሉ። እግዚአብሔር አምላክም የፈጠረውን ሰው ወስዶ በገነት አኖረው። ገነትን እያበጀ በመከባከብ እንዲጠብቃትም አዘዘው። *(መሥራትን የማይወድ ቢኖር አይብላ ( 2 ተሰ 3፡ 10 )።* ........................................

25 አዳምና ሚስቱ ዕራቁታቸውን ነበሩ። ግን አይተፋፈሩም ነበር ።

*(ትርጓሜ፡ቍ-3 የሰንበትን ቀን ስለማክበር የተነገረውን በሚመለከት፡ በትንቢተ ኢሳይያስ እንደተጻፈ የእግዚአብሔር አምልኮት የሚፈጸምበትም ቀን መሆኑን ለመግለጥ፡"ሥጋ -ለባሽ የሆነ ሰው ሁሉ በፊቴ ይሰግድ ዘንድ ወደ እኔ ይመጣል ይላል-ጌታ እግዚአብሔር። በየዕለተ ሰንበቱ- ወደ ቤተ እግዚአብሔር የማይሄዱ ሰዎች በቤት ተቀምጠው ወይም ተኝተው የሚያሳልፉት እያንዳንዱዋ የሰንበት፡ቀን ከዕድሜአቸው ላይ የምትቀነስ መሆኑን በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልእ 36፡ 21-23 የተጻፈው ያስረዳል።)*

***ቍ 6*፡ *ከመሬት ወጥታ እየተሳበች የምድርን ገጽ በማረስረስ ታጠጣ የነበረች ይች ጉም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ምሳሌ ናት። በእኛ ሕይወት አድሮ፡ ፍሬ ምግባር ወሃይማኖት የምናፈራበትን የመንፈስ ልምላሜ የሚሰጠን እርሱ ነውና። የመንፈስ ፍሬ የትባሉትም ፍቅር ፡ የመንፈስ ደስታ፡ ሰላም፡ ትዕግሥት፡ ቸርነት፡ በጐነት ፡ እምነት ፡ የዋሃት*



www.ethiopianorthodox.org

ራስን መግዛት መሆናቸው - በገላ 5፡ 22--23 ትጽፏል።

ቍ 7 በመጽሐፈ ኢዮብ- 33፡ 4- 3 " የእግዚአብሔር መንፈስ ፈጠረኝ፡ ሁሉን ማድረግ የሚችል የአምላክ እስትንፋስ ሕይወትን ሰጠኝ "ተብሎ የተጻፈ ይህኑ የንፍስን ተፈጥሮ- በማስመልከት ነበርና። ስለዚህ ሰው 1ኛ. ሥጋ ፡ 2.ኛ ነፍስ ፡ 3ኛ. መንፈስ ያለው ፍጥረት ሲሆን የሰው መንፈስ የዕውቀቱ ማኅደር የሆነ ልብና አእምሮው ነው (1 ተሰሎንቄ 5፡ 23)፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ገጽ 27 ።

8 -11 ከዔደን ገነት ፈልቆ በዐራት ወንዞች የተከፈለው ውኃ ከአንድ ጌታ መለኮታዊ አንደበት ፈልቆ በዐራት ወንጌላውያን ተጽፎ ፡ በዐራቱ ማዕዝነ ዓለም ሲነገር የሚኖር የክርስቶስ ወንጌል ምሳሌ መሆኑን ቅዳሴ አትናቴዎስ ቍጥር 43- 46 ያሳያል። ) ሰው ክፉና ደጉን ለይቶ ከሚያሳውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳይበላ መከልከሉም ፍጡር ለፈጣሪ መታዘዝ እንዳለበት የሚገልጥ የሕገ ልቡና ምልክት ነው።

ቍ 15 -17 አዳም በገነት ሲኖር ገነትን እይበጀ እንዲከባከባት መታዘዙ ከጥንት ጀምሮ የሥራ ክቡርነት መለኮታዊ መመሪያ የተሰጠበት መሆኑን ያመለክታል። በሐዲስ ኪዳንም "መሥራትን የማይወድ ቢኖር አይብላ"ተብሏል ( 2 ተሰ 3፡ 10 )። ይህን የሥራ መመሪያ ቃል የሚተረጕሙ ተጓዳኝ ታሪክና ምሳሌዎችን "ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ የአብነት ትምህርት ከልዩ የልማት ዕድገት ጋር " በሚል ርእስ በታተመው መጽሐፋችን በአማሪኛ ገጽ 232 እና ገጽ 215 በእንግሊዝኛ፡ ወይም "አምስተኛ ጉባኤ -የአባቶች ቸዋታ" ገጽ 16 -18 "ወደ አባ ስልዋኖስ (Silvanus ) ገዳም ስለመጣው ተግባረ -ፈት መነኮስ በሞል ርእስ የተጻፈውን ይመልከቱ።

**ቍ18፡-** የብቸኝነት_ኑሮ_ከባድና አስከችጋሪ_መሆኑን_የምንለካበት ትርጕማዊ ታሪክና ምሳሌ መነሻ ርእሱ "ዕድሜዎት ስንት ነው ?" በማለት ይጀምራል። ይኸውም በጎጃም አገው ምድር በዳንግላ ከተማ የታወቁ አንድ ምሁር እስከ ኃምሳ ዓመት ዕድሜቸው ድረስ ሚስት ሳያገቡ በብቸንነት ይኖሩ ነበር። ከኃምሳ ዓመት በኋላ ሚስት አግብተው ልጆች መውለድ ጀመሩ። ታዲያ ለምስክርነት ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተጠርተው ሄደው "ዕድሜዎት ስንት ነው"? ተብለው ሲጠየቁ፡ "ከሦስት ዓመት አይበልጥም " አሉ ። "ለምን ይቀልዳሉ ? እውነቱ ይንገሩን" ሲባሉ " እኔ በበኩሌ ዕድሜ ብዬ የማምንበት ሚስት አግብቼ ፡ ልጆች ወልጄ መኖር ከጀመርኩበት ወዲህ ያለውን ጊዜ ብቻ ነው።



ዘአልቦ ብእሲት ይነብር በከ=የለሚስት ብቻኛ የሆነ ሰው ኑሮው ብላሽ ነው" እንዳለ ሲራክ ከዚያ በፊት የነበርኩብት ኃምሳ ዓመት በከንቱ ያለፈ ስለሆነ እንደ ዕድሜ አድርጌ አልቆጥረውም ። አንተ ካመንህበት ግን ሃምሳ ሦስት ዓመት ብለህ ብትጽፍ መብትህ ነው" አሉት ይባላል። "ጋብቻ በሁሉ ዘንድ የከበረ ይሁን" - ዕብ 13፡ 4 )።

_ሴት ከወንድ ዕኩል ሆና የተፈጠረችበት ምሳሌያዊ (Allegorical) ትምህርት-አዘል ትርጓሜ

- ከራስ አጥንቶች ያልተፈጠረችበት ምክንያት በመብት ከባልዋ ባላይ ልሁን እንዳትል ነው፡ ከእግሮች አጥንቶች ያልፈጠረችበትም ምክንያት በመብት በጣም የተዋረደች እንዳትሆን ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር አምላክ ከባልዋ ጋር ዕኩል እንድትሆን ፈቅዶ ( To be equal with him) ከጎን አጥንት አንሥቶ ፈጥሯታል። ባልዋ በክብር እንዲጠብቃት አስፈላጊ መሆኑን ለመግለጥ በክርኑ ሥር ከምትገኝ አጥንት አንሥቶ የፈጠራት ሲሆን፡ ባልዋ ከልብ እንዲወዳትም ፈቅዶ (Near his heart ) በልቡ አጠገብ ከምትገኝ አጥንት አንሥቶ ፈጥሯታል ማለት ነው። ሔውን የተፈጠረች በግራ ጎን ከምትገኝ አጥንት መሆኑንም የመጽሐፍ ቅዱስ መተርጕማን ያትታሉ።

_በሊቁ ቅ/ ቄርሎስ ትርጕም ደግሞ ከዚህ ለየት ያለ ትንታኔ ቀርቧል ፡ ይኸውም ከአዳም- ጎን -አንዲት -አጥንት -በተነሣች -ጊዜ-ሕመም አልተሰማውም፡_ የአካል ጉድለትም ከቶ አልደረሰበትም። ይህም ምልእተ ጸጋ የሆነች የቡርክት ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ነው። ጌታን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ስትወልድ የምጥ ፃዕር አልደረሰባትም፡ ማኅተመ ድንግልናዋም-አልተለወጠምና ማለት ነው ። የጌታ ልደት ከመ ሐፍ ይወፅእ እምገጽ= ላብ ከሰውነት ወጥቶ በፊት ላይ ሲወርድ እንደሚታይ ያህል ነው" ይለዋል ሊቁ ያዕቆብ ዘእልበረዳኢ። ይህም ቢሆን ምሳሌ ዘየሐጽጽ ፡ ፍጹምነት የሌለው ምሳሌ ነው ። የጌታ ልደት- ትርጕሙ- የሰው ኅሊና- ሊደርስበት -የማይችል ምሥጢረ መለኮት ነውና ።

## ሁለት አሸናፊዎች ኃይላት በዓለም ዙሪያ '

1ኛ. የሴቶች አሸናፊነት ( እንስት ይመውዓ ):

2ኛ. የእውነት አሸናፊነት=( ጽድቅ ትመውዕ )

በመጽሐፈ ዕዝራ ካልእ ምዕራፍ. 3 እና 4 ተጽፎ እንደሚገኝ አንድ ጊዜ የ 120 አገሮች መድበለ መንግሥት (Empire) መሪ የነበረ ዳርዮስ



www.ethiopianorthodox.org

ንጉሠ ፋርስ ሦስት ባለሟሊቹን መሸለም ፈልጎ፡ "በዓለም ዙሪያ አሸናፊ የሆነ ምንድን ነው / ማነው?" የሚል ጥያቄ ተነሥቶ በመከራከር ውድድር ውስጥ ገብተው ነበር። ከሦስት ባለሟሎቹ አንዱ "በምድር ላይ አሸናፊ ሆኖ የሚኖር ንጉሥ ብቻ ነው" በማለት አንዳንድ ነገሥታት ድል ያደረጉባቸውን የጦር ሜዳዎች ታሪክ እየጠቀሰ ተንትኖ አስረዳ። 2ኛው ባለሟል: በዓለም ላይ አሸናፊ ሆኖ ኃያላንን ሁሉ እያብረከረከና ከክብር ሲያዋርድ የሚኖር ጠንካራ የሆነ አስካሪ መጠጥ (Alcoholism) መሆኑን በማጠናከር ተናገረ። 3ኛው ባለሟል ዘሩባቤል የተባለው አይሁዳዊ ሲናገር ግን በዓለም ዙሪያ ግንባር ቀደም አሸናፊዎች :አንደኛ ሴቶች ናቸው= አንስት ይመውዓ። ለምሳሌ የ120 አገሮች ሕዝቦች በመራድ፡ በመንቀጥቀጥ የሚያከብሩትን ንጉሠ ነገሥት ዳርዮስን ማንም አይደፍረውም። ሚስቱ ኢጴሚን ግን በፍቅር አሸንፋ በቊጥጥር ሥር በማድረግ ፡ ሲጫወቱ እንኳ አንዳንድ ጊዜ ፊቱን በጥፊ ትመታዋለች። ስለዚህ በዓለም ላይ ያለምንም ጦር መሣሪያ በፍቅር ብቻ አሸናፊዎች ሴቶች ናቸው።

_ሁለተኛ በየትኛውም ዓለም "ጽድቅ ትመውዕ =እውነት ታሸንፋለች። እውነት የሥልጣናት ሁሉ ባለቤት ናት፡ ዕውነት በዘመን ዘለዓለማዊት ናት። እውነት ማለትም ራሱ እግዚአብሔር ነው" ሲል ንግግሩን ደመደመ። በዚሁ ጥበባዊ ንግግር አንደኛነትን አግኝቶ በግንባር ቀደምነት ተሸላሚ ሆነ።

_በመጨረሻም ንጉሥ ዳርዮስ "ምን ላድርግልህ ትወዳለህ ? " ብሎ ሲጠይቀው የዘሩባቤል መልስ " በፋርስና ባቢሎን ተበትነው በስደት የሚኖሩ ሕዝቤን እስራኤልን ነጻ አውጥተህ ወደ ቅድስት አገራቸው ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ አድርግልኝ" የሚል ነበር። ይህም ሐሳቡ ተቀባይነትን አግኝቶ ከሰባ ዓመት የስደት ዘመን በኋላ ወደ አገውራቸው ተመልሰው ዘሩባቤልን አንግሠው በሰላም ኖረዋል።

## ትርጓሜ ( Comments )

እግዚአብሔር አንድን ሕዝብ መታደግ ሲፈቅድ እንደዚህ ያላውን የንግግር ጥበብ በአንዳንድ ሰው አእምሮ ያኖራል። በጦር ሜዳም ቢሆን "ሴት ወንድን ትከባለች" ይላል ኤር 31፡ 22። ስለ ሀገራችን ኃያላት ሴቶች ጀግንነት ደግሞ ጥቂት ብናወሳ ፡ የግራኝ መሐመድን ወረራ እንዲገታ ያደረጉ እቴጌ ሰብለ ወንጌልን፡ በዓድዋ ጦርነት ላይ



ከዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ጎን ሆነው የጀግንነትን ወኔ ከቈራጥነት ጋር ያሳዩትን ፡ እቴጌ ጣይቱን፡ በአምስቱ ዓመት የጣልያን ፋሺስት ወረራ ዘመን በዐርበኝነት ተግባር ተሠልፈው የነበሩ ወ/ሮ- ሸዋረገድሌን በመሐል አገር ሸዋ፡ የትግራይ ተወላጅ ሆነው በላስታ የድ/ች ኃይሉ ሚስት የነበሩትን-ወ/ሮ ሸዋየ /ሸዋነስ አብርሀን ወዘተ በዐርበኛነት ሙያ የሚወዳደራቸው ማን ነበር?

## ፫ /3. ዘርዐ አዳምን ከእግዚአብሔር ቤተሰብነት አለያይቶ የኖረ ፈተና አመጣጥ

1--5 እግዚአብሔር አምላክ ከፈጠራቸው ከምድር አራዊት ሁሉ በተለይ እባብ እጅግ የከፋ-ተንኮለኛ ነበር። እርሱም ወደ መጀመሪያዪቱ ሴት ቀርቦ "በእውነት እግዚአብሔር ከገነት ዛፍ ሁሉ ፍሬ እንዳትበሉ አዟልን?" ሲል ጠየቃት። ሴቲቱም እንዲህ አለችው፡"በገነት ካለው ዛፍ ፍሬ ሁሉ እንበላለን፡ ነገር-ግን ከፋና ደጉን ለይቶ ከሚያሳውቀው-ዛፍ ፍሬ እንዳንበላና፡ቅጠሉንም እንዳንነካ አዞናል፡ ከዚያም ዛፍ ፍሬ ብንበላ እንደምንሞት አስጠንቅቆ ነግሮናል። "እባብም-ሲመልስ፡-"ከዚያ ዛፍ ፍሬ ብትበሉ -ፈጽሞ-አትሞቱም። ዓይኖቻችሁ-ተከፍተው-ክፉና-ደጉን-ለይታችሁ ታውቃላችሁ፡ እንደ- አምላክ- ትሆናላችሁ። እግዚአብሔር ከዚህ ዛፍ ፍሬ- እንዳትበሉ-ያዘዛችሁም ይህን-ስለሚያውቅ ነው"አላት። 6--8-ሴቲቱም-የዛፉን-ልምላሜ ማማርና ለመብላትም የሚያስጐመጅና ጥበብን የሚገልጥ መሆኑን አይታ ከፍሬው ወስዳ--በላች፡ ለባሏም-ሰጠችውና-በላ ። ወዲያው የሁለቱም ዓይኖች ተከፈቱና-ዕራቁታቸውን መሆናቸውን-ስላወቁ፡- የበለስን-ቅጠል- ሰፍተው-ለሰውነታቸው-መሸፈኛ-የሚሆን ሽርጥ /ግልድም ሠሩ። -እግዚአብሔርም በምሽት ጊዜ በአትክልቱ ውስጥ ሲያልፍ ድምፁን ሰምተው-ስለፈሩ በዛፎች መካከል ተደበቁ ( ኤር 21፡ 24 )። እግዚአብሔርም አምላክም አዳምን ጠርቶ "የት ነው ያለኸው?" ሲል ጠየቀ። አዳምም "በአትክልቱ መካከል ስታልፍ ድምፅህን ሰምቼ ራቊቱን ስለሆንሁ ተደበቅሁ" አለው። እግዚአብሔር አምላክም "ራቊትህን መሆንክን ማን ነገረህ? በውኑ እንዳትበላ ካዘዝኩህ -ከዚያ-ዛፍ ፍሬ በላህን?" ሲለው፡አዳም 'ይህች ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት ሰጠችኝና በላሁ" አለ። እግዚአብሔርም ሴቲቱን "ይህ ያደረግሽው ነገር ምንድን ነው/" ሲላት፡ "እባብ አሳተኝና በላሁ" አለች። እግዝዘአብሔርም መጀምሪያ እባብን እንዲህ



www.ethiopianorthodox.org

አለው-" ይህን በማድረግህ አንተ ከአራዊት ሁሉ ተለይተህ የተረገምህ ሁን፡ ከዛሬ-ጀምሮ በልብህ እየተሳብህ ትሄዳለህ። ዕድሜህን-ሙሉ-የመሬት አፈር/ትቢያ እየላስህ ትኖራለህ። ባንተና በሴቲቱም፡ በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነት እንዲኖር አደርጋለሁ፡ አንተ የርስዋን ዘር ሠኮናውን ትነክሳለህ፡ እርሱም የአንተን ራስ-ይቀጠቅጣል"። *(ትርጓሜ ስለ ሰይጣን ዘር የተነገረውን በሚመለከት ፡ከተ3ዳኙ ታሪክና ምሳሌዎች-አንዱ ' ሰይጣን ልጅ አለወይ ?' የሚል ጥያቄ የቀረበላቸው አንዱ የአክሱም ንቡረ እድ የሰጡት መልስ "መቼም ፊታውራሪ እከሌ የበሻር ልጁ ናቸው። የሌሎች ልጆቹ ብዛትማ ስንቱ ተቆጥሮ ያልቃል?" የሚል ነበር። ይህንም ያሉበት ምክንያት ሰይጣን እንደ ሰው ዘር የመውለድና የመዋለድ የተፈጥሮ ባሕርይ ይኖረዋል ማለታቸው ሳይሆን፡ በመጥፎ ግብሩ የሚመስሉት የሰው ዘሮች የርሱ ልጆች ተብለው ይጠራሉ። በ1 ዮሐ 3፡ 10 መልእክት ፍቅር የሌላቸው ሰዎች የሰይጣን ዘሮች ናቸው ። አንትሙሰ እም አቡክሙ ሰይጣን፡ እናንተ የአባታችሁ የሰይጣን ወገኖች ናችሁ እንዲል ዮሐ 8፡ 44 ። በሌላ በኩል ደግሞ ልቡሳነ ሥጋ አጋንንት አሉ። ችግር በመፍጠር መነኮሳትን ያውክ የነበረውን አንድ ሰይጣን ሚልኪ ቁልዝማዊ የተባለ አንድ ቅዱስ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ ዕፀ መሥውሩን አስጥሎ፡ ገንዳ አሸክሞ የነዳው መሆኑ በመጽሐፍ ስንክሣ ተጽፎ ይገኛል።*

*_አንዲት ታማሚ ሴት ሲናገሩ " በሕልም ሳይሆን በቀጥታ ዓይኔ እያየ ዝናሩን ታጥቆ፡ ጠመንጃውን አንግቶ፡ ለላንጋ ይዞ እየወዛወዘ ይመጣና ይጠቅሰኛል። በዚያ ጊዜ ከባለቤቱም ሆነ ከእኔ ጋር አብረውኝ ከነበሩት ሰዎች መሐል ተነሥቼ ወደ እርሱ እሄዳለሁ፡ እንደ ባል ሆኖ ተጫውቶብኝ ይሄዳል" ይሉ ነበር። አዎ፡ በዕፀ መሠውር ተፈጥሮአቸውን ሰውረው ላንኳንስ በሰው፥ በብርሃን መላእክትም መልክ የሚገለጡ መናፍስት መኖራቸው ተጽፏል (2 ቆሮ 11፡ 14 ) ።* .....................................

እግዘአብሔር አምላክ ሴቲቱን እንዲህ አላት፡"ፀንሰሽ በምትወልጅበት-ጊዜ የምጥ ፃዕርሺን አበዛዋለሁ። በምጥ ጻዕር ከወለድሽም-በኋላ የልብሽ ፈቃድ ወደ ባልሽ እንዲመለስ -አደርጋለሁ፡እርሱም ይገዛሻል"።

17 -19 አዳምንም ደግሞ "የሚስትህን ቃል -ሰምተህ እንዳትበላ ካዘዝኩህ ዛፍ ፍሬ በመብላትህ፡ ምድር ስላንተ የተረገመች ትሁን። እሾህና አሜከላ ይብቀልባት፡ አንተ ከመሬት አፈር የተፈጠርህ ስለሆንህ፡ ወደ መሬትነትህ እስክትመለስ ድረስ ፡ ላብህን /ወዝህን አንጠፍጥፈህ ፡ ሠርተህ የምታገኘውን እንጀራ ትበላለህ " አለው።20 ከዚያ በኋላ አዳም ሚስቱ የሕያዋን ሁሉ እናት መሆን ለመግለጥ፡ ሔዋን የሚል ስም -አወጣላት። 21-እግዚአብሔር አምላክ-ለአዳምና-ለሚስቱ-ከቆዳ የተሠራ ቀርበት (ዐጽፍ) አለበሳቸው።

## አዳምና ሚስቱ ተድላና ደስታ ከሞላባት ገነት ተሰደዱ ፡

22 -24፡ እግዚአብሔር አምላክ እንዲህ አለ- " እነሆ አዳም ክፉና ደጉን ለይቶ በማወቅ ከእኛ እንደ እኛ ሆነ ። እንደገናም ከሕይወት ዛፍ ፍሬ ወስዶ የበላ እንደሆነ- ለዘለዓለም ሕያው ሆኖ ሊኖር ነው" ብሎ እግዚአብሔር-አምላክ አዳምን ከገነት- አስወጣውና ፡ከርስዋ የተገኘባትን- ምድር እያረሰ እንዲኖር አደረገው። ወደዚያች ገነትም ተመልሶ እንዳይገባ በዐራቱ ማዕዘን በመገለባበጥ የሚያበራ የነበልባል ሰይፍ የያዙ ኪሩቤልን ከዔደን-በስተምሥራቅ-አኖረ።

*(ትርጓሜ፡* ቊ -5 ሰይጣን በእባብ አድሮ ከተናገራቸው ማታለያ *ቃላት አንዱ- "እንደ አምላክ ትሆናላችሁ" የሚል ነበር። ይሁኑ የጠላት ምስክርነት አንድ ኢትዮጵያዊ መምህር "ሥላሴ" ተብሎ በሚጠራ ቅኔ ሲተረጕሙት እንዲህ አሉ ፡ ----*

*ክራማተ ዕሥራ ፡*

*ሐሰወ ኖኅ ነቢየ ዕድሜ ፡*

*ወትትገፈታዕ በነድ በላኢ ብሔረ ዓመፃ ነነዌ፡*

*ብሂሎተ ጽድቁ ለዮናስ ሕሳዌ።*

*ከመ ትኩኑ አምላከ ባሕቱ ሀለወከም ሀላዌ።*

*ዘይቤ እቤረ ወእረጋዌ*

*እስመ ኮነ ሥጋ አምላከ ማሕየዌ*

*ኢሐሰወ ነቢይና አርዌ፡=*

*ትርጓሜውም በአማርኛ፡ የጥፋት ውኃ /ማየ አይኅ የሚመጣው ከመቶ 20 ዓመት በኋላ ነው" ብሎ የተናገረ የኖኅ-ትንቢት ዕውነት ሆኖ አልተገኘም። የጥፋት ውኃ የመጣ መቶው ዓመት ተፈጽሞ 20-ውን ዓመት በመግደፍ ነበርና። እንዲሁም ነቢዩ ዮናስ ዓመፀኛዪቱ አገራችሁ ነነዌ ከሦስት ቀን በኋላ በእሳት ትገለበጣለች" ብሎ የተናገረውም ትንቢት ሲፈጸም አልታየም። ነገር ግን በኋለኛው ዘመን ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ከቡርክት ቅድስት- ድንግል-ማርያም-የነሣው-ሥጋ ከመለኮት-ጋር-ተዋሕዶ- የባሕርዩ-አምላክ-ሆኗልና-ነቢያችን- እባብ- አዳምንና ሔዋንን- "አምላክ- ትሆናላችሁ"*





www.ethiopianorthodox.org

ሲል የተናገረው ትንቢት- እውነት ሆኖ ተገኘ" ማለት ነው። ይህንም ቅኔ የሰሙት ሌላው የቅኔ መምህር-"ራስህን ችለህ- የኔው- ነቢይ በለው እንጂ እኛን -ሁሉ ወክለህ የጥንተ ጠላታችን የሰይጣን ዲይብሎስ ፈረስ የሆነውን ሳባብ ነቢያችን ብለህ አትጥራብን " አሉ።

ቊ 9 -10 እግዚአብሔር አዳምን "የት ነው ያለኸው?" ብሎ መጠየቁ ያለበትን ቦታ -አጥቶት ሳይሆን፡ በኋለኛው ዘመን መለኮታዊ ባሕርይ የሌለውን አላዋቂ ሥጋ ሰብእ እንደሚዋሐድ በትንቢት መልክ ለመግለጥ ነው እንጂ። ቊ 15 በሴቲቱ ዘርና በእባብ ዘር መካከል ያኖረውን ቅራኔ በሚመለከት የተነገረው መሲሐዊ የትንቢት ቃል በላቲን ቋንቋ የመጀመሪያው ወንጌል ( Prote-Vangelium) ተብሎ ይጠራል።

_የሴቲቱ ዘር የተባለ ከቡርክት ቅ/ት ድንግል ማር-ያም የነሣውን ሥጋ ተዋሕዶ የሚወለድ ክርስቶስ ነው ። የሰይጣን ዲያብሎስን ራስ በመስቀል ላይ የቀጠቀጠ እርሱ ነውና።አንተ የሴቲቱን ዘር ሠኮና ትነክሳለህ ማለት እስከዚያው ድረስ የሰውን ዘር የልብ ሠኮና በኃጢአት መርዝ ስታቈስል ትኖራለህ ለማለት የተነገረ ነው ።

## ፬ /4. የመጀመሪያው ቤተሰባዊ ኑሮ አመሠራረት ታሪክ

1--8 አዳምና-ሔዋን በባልና-ሚስትነት-ሲኖሩ፡-ሔዋን ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች፡ "በእግዚአብሔር-ፈቃድ አገኘሁት" ስትል ስሙን-ቃየል-አለችው-ከዚያ-በመቀጠል-የቃየል-ታናሽ -የሆነውን- አቤልን- ወለደች ። አቤል-በግ-አርቢ-/እረኛ-ሲሆን-ቃየል-እህል-አምራች-ገበሬ-ነበር።_አቤልና ቃየል ሁለቱም ለእግዚአብብሔር-መሥዋዕት-ማቅረብ -ፈልገው ፡ ቃየል- ከእህል-ምርቱ- ያገኘውን-አፍሶ *(ያለምርጫ)*-አመጣ።

_አቤል-ግን- ከበጎቹ በኩራት-መካከል-የሰባውን-የአንድ ዓመት ጠቦት መርጦ-አቀረበ።- ስለዚህም እግዚአብሔርም -ወደ አቤል ተምልክቶ -መሥዋዕቱን ተቀብለለት ።_ወደ ቃይልና-_ወደ መሥዋዕቱ ግን-አልተመለከተም።በዚህም-ምክንያት-ቃየል-ተቈጥቶ-ፊቱን-አጠቆረ። እግዚአብሔር ቃየልን "ለምን- ተቈጣህ ? ፊትህስ ለምን- ጠቆረ? መልካም ነገር አድርገህ ቢሆን ኖሮ-ደስ በተሰኘህ ነበር። ያደረግኸው-ክፉ-ነገር-በመሆኑ-ኃጢአት ልታጠምድህ በደጅህ-ታደባለች፡-አንተም-ንገሥባት"-አለው። ከዚያ-በኋላ ቃየል ወንድሙን አቤልን በማነጋገር-ወደ-ሜዳ--አውጥቶ-ገደለው።



13_እግዚአብሔር-ቃየልን-"ወንድምህ-አቤል-የት-ነው?"-ሲል_ጠየቀው። ቃየልም-"የት-እንዳለ-አላውቅም፡-እኔ-የወንድሜ-ጠባቂ-ነኝን?"-አለ።እግዚ አብሔርም_"ወንድምህ-አቤል-እስኪ-ምን-አደረገህ-?-እነሆ-ያፈሰስኸው የወንድምህ- ደም -ከምድር- ወደ- እኔ-ይጮሃል። የወንድምህን-ደም-በጠጣች-ምድር-ላይ-አንተ-የተረገምህ-ነህ።_ምድርን- በምታርስበት ጊዜ ኃይልዋን ( ብልጽናዋን ) አትሰጥህም። ኮብላይና ተቅበዝባዥ--ሆነህ-ትኖራለህ"-አለው።- 24--15፡-ቃየልም-የፈጸመው-በደል-ታላቅ-መሆኑን-ገልጦ፡-"እንግዲህ--አንተ-እንደዚህ- ካሳደድኸኝማ- ያገኘኝ- ሰው -ሁሉ -ይገድለኛል" ሲል ሥጋቱን ስለገለጠ እግዚአብሔር ያደረገለት ምልክት" ቃየልን የሚገድል ሰው ቢኖር ሰባት- እጥፍ-የሆነ በቀል ይፈጸምበታል" የሚል ነበር።ከዚያ-በኋላ-ቃየል-ከእግዚአብሔር-ፊት ወጥቶ ሄደና መኖሪያውን ከዔደን ምሥራቅ በኖድ ምድር አደረገ ።

## የቃየል ዝርያዎች የጀመሩት የፍልስፍና ጥበብ ፡

16--24 ቃየል አንዲት ከተማ-መሠረተና በልጁ ስም-ሄኖኅ ብሎ ጠራት። ሄኖኅ ጋይዳድን፡ ጋይዳድ ሚኤልን፡ ሚኤል ማቱሳለን፡ ማቱሳላ ላሜህን ወለደ።ላሚህም ዓዳ እና ሴላ የተባሉ ሁለት ሚስቶችን አገባ። *(የመጀመሪያው ድርብ ጋብቻ መሥራች /ፖሊጋሚስት ነበር ማለት ነው።)*-ዓዳ-ከወለደችለት-ሁለት-ልጆቹ-አንዱ-የሆነው-ያባል-ድንኳን እየሠሩ-በዘላንነት የመኖርን የከብት እርብትቶ አደርነትን ሥርዓት አስተማረ። የርሱም ወንድም ዩባል ዋሺንትና- በገና የሚጫወቱ የሙዚቀኞች-አባት-ነበር።ከሴላ-የተወለደ-ቱባልቅይን-የንስሐና--የብረታብረ አንጥረኛነትን_ጥበብ-አስተማረ።

**የአቤል-ምትክ-የሆነ የሴላው-ልጅ-ልደት፡** 25-ሒዋን-እንደገና ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደችና ""እግዚአብሔር-ለአቤል- ምትክ አድርጎ ሰጠኝ" ስትል- "ሴት"-የሚል-መጠሪያ ስም አወጣችለት። ሴት-ሔኖስን ወለደ። በሔኖስ-ዘመን-የነበሩ-ሰዎችም-የእግዚአብሔርን-ስም-መጥራት-ጀመሩ።*(የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል" -ኢዩ-2፡ 32*

***(ትርጓሜ***-፡ *ቊ-10_-እግዚአብሔር- አምላክ -የአቤልን -መሥዋዕት-ሲቀበልለት የቃየልን መሥዋዕት ያልተቀበለበት ምክንያት የቃየል መሥዋዕት የግብር ይውጣ ወይም ጥንቃቄ የጎደለው አቀራረብ ስለነበረ ነው። የአቤል መሥዋዕት አቀራረብ ግን በምርጫ ነበር። ይኸውም አቤል ከበጎቹ በኩራት መካካል በጥንቃቄ መርጦ፡ በነቢዩ*



www.ethiopianorthodox.org

*ኅሪት መዝሙር 69፡ 31 "... ለእግዚአብሔር እምላሕም ላህመ ዘኢያብቈለ ቀርነ ወጽፍረ" ተብሎ እንደተጻፈ= የሰባውንና- ጠጉሩ-ያላረረውን፡-ጥፍሩ-ያልዘረዘረውንና-ቀንዱ ያልከረከረውን የአንድ ዓመት ጠቦት ሲያቀርብ፡ ፡ እግዚአብሔር ንጹሐ ባሕርይ ስለሆነ ንጹሕ ነገር ሊያቀርብለት እንድሚገባ በሥነ ልቡናው ተመራምሮ የተገነዘበ መሆኑን ያሳያል ። እግዚአብሔር አምልክን ደስ የሚያሰኝ ልዩ መሥውዕት ማለት ቅን-ልቡና፡ ትሑት ሰብእና ነውና* (መዝ 50፡ 6- 17 )። '

_*የዋሁ ጻድቅ አቤል መድኃኔ ዓለም ክርስቶስን በሁለት ዋና፡ ዋና ነገሮች ይመስለዋል። ይኸውም ፡ 1ኛ አቤል ምንም ሳይበድል እንደተ ገደለ ክርስቶስም ያን ሁሉ መከራ መስቀል የተቀበለ ምንም በደል ሳይገኝበት ነውና (ኢ.ሳ 53፡ ) -2ኛ የአቤል ደም ነፍሰ ገዳይ ወንድሙን ቃየልን ሲከሥ እንደሚኖር፡ የክርስቶስም ደም ከአቤል ደም ይልቅ የተሻለ የሚናገር /ነባቢ ነውና። "ከአቤል ደም ይልቅ ወደሚ ናገር ደም ደርሳችኋል" (ዕብ 12፡ 24 ። )*

## ፭ /5 <u>የዐሥሩ ጥንታውያን አበው ዘመነ ሕይወት</u> ፡

1 –2 እግዚአብሔር አምላክ እነርሱን በፈጠረበት ዕለት አዳም ብሎ ጠራቸው ። 3 አዳም በ 230 ዓመት ዕድሜው በመልክ የሚመስለውን ልጅ ወልዶ -ሴት የሚል ስም አወጣለት *( ምትክ- ማለት ነው ) ።*
4 -5 _አዳም ሴቶችና ወንዶች ልጆችን ከወለደ በኋላ በ 930 ዓመት ዕድሜው ሞተ ። ሌሎችም አበው እንደዚሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን በመውለድ፡ ያለፉበት ዘመነ ሕይወት ከዚህ እንደሚከለው ነው ፡ ሴት 912፡ ሄኖስ 805፡ ቃይናን 910፡ መላልኤል 905፡ ሄኖክ 365 ፡ማቱሳላ 969፡ ላሜሕ 777 ። ኖኅ 950 ዘመን የኖሩ ሲሆን ከነዚያ አበው መካከል በተለይ ሄኖክ ሴቶችና ወንዶች ልጆችን ከወለደ በኋላ በዚህች ምድር አልተገኘም፡ አካሂዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ እግዚአብሔር-ወስዶታልና" *( ቍ 22፡ 24 ) ።*

*(<u>ትርጓሜ</u> ፡ ሄኖክ አካሂዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ ማለትም በእምነቱ ፅናትና በሥነ ምግባሩ ጥራት፡ ለዘመኑ ትውልድ በሰጠው ትምህርተዊ ምስክርነት እግዚአብሔርን ደስ ስላሰኘው ፡ ሞትን ሳያይ ከነሕይወቱ ወደ መካነ ሕያዋን /ገነት ወስዶታል ወይም እንደ ኤልያስ አሳርጎታል ማለት ነው ( የይሁዳ መልእክት -ቍ 14-15 ይመልከቱ።*



## ፮ /6 <u>በምድር ላይ ገደብ ያጣ የሰው ዘር ክፋት</u>

1--3 ሰዎች በምድር ላይ መብዛት በጀመሩ ጊዜ ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው። የእግዚአብሔር ልጆችም የሴትቶች ልጆችን ውበትና ቁንጅና ተመለከቱ ። ከነርሱ መካከል ለየራሳቸው ሚስቶችን መርጠው ወሰዱ። እግዚአብሔርም እንዲህ አለ ፡ - "ከእንግዲህ ወዲህ መንፈሲ ለዘለዓለም በሰዎች ላይ አድሮ አይኖርም። እነርሱ ሥጋውያን ስልሆኑ ወደፊት የሚኖሩበት ዕድሜ አንድ መቶ ኻያ ( 120 )_ ዓመት ብቻ ይሆናል" ። ከነዚያም ሴቶች ኔፊሊም /ረዓት ተብለው የሚጠሩ ምድር ውለድ ኃያላን ሰዎች ተወለዱላቸው ።

5 –6 እግዚአብሔርም በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ምን ያህል ዓመፀኞችና አሳባቸውም ሁሉ ዘወትር ወደ ክፋት ያዘነበለ መሆኑን ተመለከተ። ሰዎችን በምድር ላይ በመፍጠሩም አዘነ /ተፀፀተ (መክ 9፡ 3 ፡ ኤር 7፡ 9 )። ኖኅ የተባለው ብቻ የእግዚአብሔርን መንገድ የሚከተል ጻድቅ (ደግ ) ሰው ሆኖ ተገኘ። ኖኅም ሴም፡ ካምና ያፌት የተባሉ ሦስት ወንድች ልጆች ነበሩት። 10-18 በኖኅ ዘመን ምድር በእግዚአብሔር ፊት በኃጢአት ረክሳ ነበር። እግዚአብሔር ወደ ምድር ሲመለከት የሚኖርባት የሰው ዘር ሁሉ ወደ ጥፋት ጎዳና ያዘነበለ መሆንን አየ። ስለዚህም እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው፡ "የፈጠርሁትን የሰው ዘር፡ እንስሳትና አራዊትን፡ የሰማይ ወፎችን ጭምር ከገጸ ምድር ላይ የምደመስስበት የፍርድ ቀን ደርሷልና አንተና ቤተሰብህ ከጥፋት ውኃ የምትድኑባትን የእንጨት መርከብ ሥራ "፡፡

*(<u>ትርጓሜ</u>-፡ ከጥፋት ውኃ በፊት የበረው ትውልድ በሁለት ተከፍሎ በእግዚአብሔር የሚያምኑት ሁሉ አንድ ወገን ሆነው የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ሲጠሩ፡ በተለይ በእግዚአብሔር የማያምኑት ግን የሰው ልጆች ተብለው ይጠሩ ነበር። ስለዚህ በዚህ ምዕራፍ 6፡ 1 -2 የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የተጠሩት የአቤል ምትክ ሆኖ ከተወለደውና ሴት ተብሎ ከተጠራው ሰው የተወለዱ ነገደ ሕዝብ አንጂ መላእክት አይደሉም።*

## ፯ /7. <u>ምጽአተ ማየ አይኅ (የጥፋት ውኃ) አመጣጥ</u> :

<u>3- 16</u> እግዚአብሔር ኖኅን እንዲህ አለው፡--"በምድር ላይ ለዘር ያህል እንዲተርፉ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው ከሚኖሩት እንስሳትና አራዊት ፡



www.ethiopianorthodox.org

ከሰማይ ወፎችና ከሌሎችም ፍጥረታት ሁሉ መካከል ከሚበሉት ሰባት፣ ሰባት ጥንድ፣ ከማይበሉት ሁለት፣ ሁለት ተባእትና እንስት ( ሴትና ወንድ ) የሆኑትን ይዘህ ወደ መርከብ ግባ ። ኖኅም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። እርሱና ሚስቱ፣ ሦስቱ ልጆቹና የልጆቹ ሚስቶች ስምንት ነፍሳት ወደ መርከብ ሲገቡ፣ እግዚአብሔር የመርከቡን በር ዘጋበት። 17 -24 ከዚያ በኋላ የታላቁ ውኃ መፍለቂያዎች ተነደሉ ፡ ከሰማይ የሚዘንመው የውኃ መስኮቶች ሁሉ ተከፈቱ፣ የጥፋት ውኃ ( ማየ አይኅ ) በምድር ላይ ዐርባ ቀን ሙሉ ዘነመ። የውኃው ጥልቀት እየጨመረ መጥቶ። ከታላላቅ ተራራዎች በላይ ዐሥራ አምስት ክንድ ከፍ፣ ከፍ አለ።መርከቢቱ በውኃ ላይ መንሣፈፍ ጀመረች። በምድር ላይ የነበሩ ሕይወት ያላቸው ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ሁሉ ተደመሰሱ።

***(ትርጓሜ*** ፡ *( እነሆ አሁንም የንገሩ ሁሉ ፍጻሜ /መጨረሻ ቀርቧል።ስለዚህ እንደ ባለ አእምሮ እያሰባችሁ በመጠን ኑሩ- ( 1 ጴጥ 4፡ 7 ) ቊ 16 እግዚአብሔር የመርከቢቱን በር ዘጋበት ማለት ኖኅንና ከርሱ ጋር ያሉትንን ፍጥረታት ሁሉ እንደ ሊቀ ሐመር= እንደመርከበኞች አለቃ ሆኖ በመከባከብ ከአደጋ ሁሉ የሚጠብቃ ቸው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ያመለክታል ። )*

፰ /8 <u>ፍጥረቱን ሁሉ የማይረሳ የምሕረት አምላክ</u> -

1 –5 እግዚአብሔር ኖኅንና ከርሱ ጋር በመርከብ ውስጥ የነበሩትን ፍጥረታት ሁሉ አሰበ። *( እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ሕዝብህን በምታስብበት ጊዜ እኔንም አስበኝ -ይላል ነቢየ ዳዊት በመዝሙሩ 105፡ 4 )።* ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ነፋስ በምድር ላይ እንዲነፍስ አድርጎ፣ ውኃው በምድር ላይ መጉደል ጀመረ። ከመቶ ሃምሳ ቀንም በኋላ ፈጽሞ ደረቀ። መርከቢቱም በዐራራት ተራራ ላይ ዐረፈች ።

6-16 ኖኅም የውኃውን- መጉደል አይቶ -ይመለስ ዘንድ አንድ ቁራ ላከ። ቁራው ግን ወዲያና-ወዲህ እየበረረ-ወደ-ኖኅ ሳይመለስ ቀረ። ከዚያም-ቀጥሎ-ኖኅ ሁለት ርግቦችን በማከታተል ላከ። የመጀመሪያዋ ርግብ እግሮችዋን ማሳረፊያ አጥታ-ተመለሰች። ሁለተኛዪቱ ርግብ ግን ወደ ማታ ገደማ ስትመለስ፡ውኃው መጉደሉን-የሚያበሥር- ለምለም የወይራ-ዛፍ-ቅጠል_ይዛለት_መጣች።15-ግዚአብሔርም_ኖኅና ቤተሰቡ ከርሱጋር ከነበሩትም ፍጥረታት ጋር ከመርከብ እንዲወጣ አዘዘው።



## <u>የኖኅ መሥዋዕት፡</u>

## <u>የእግዚአብሔር ቃል ኪዳንና በረከት ፡</u>

20—22..ኖኅ-ባቀረበው-የንጹሕ-ጠቦት-መሥዋዕት-ደስ-ስለተሰኘ፣ እግዚአብሔር፣ በአሳቡ እንዲህ አለ-"የሰው ዘር ስለሚፈጽመው በደል ሁሉ ከእንግዲህ ወዲህ- በዚህ ዓይነት- ድምሰሰ ምድርን አልረግም። ምክንያቱም ሰው-ከታናሽነቱ ጀምሮ የልቡ አሳብ ሁሉ እጅግ ክፉ- እንደሆነ- አውቃለሁ"- ( መክ 7፡ 29)።

***(<u>ትርጓሜ</u>***-፡ ***<u>የኖኅ መርከብና ምሳሌነትዋ</u>***፡

*1/. መርከብ በመጀመሪያ የክርስቶስ ምሳሌ ናት ። ይኸውም በጥፋት ውኃ ዘመን_መዳን የፈለገ ሁሉ ወደዚያች መርከብ ለመግባት መቻል ነበረበት። በሐዲስ ኪዳን -ዘመንም ከኀጢአት ባሕር ለመውጣትና የዘለዓለምን ሕይወት ወራሽ ለመሆን፡ ወደ ክርስቶስ ከመቅረብ በቀር ከቶ ሌላ አማራጭ የለም። መዳን በሌላ በማንም የለም። ከሰማይ በታች እንድንበት ዘንድ የሚገባ ለሰው የተሰጠ ሌላ ስም ከቶ የለምና ( የሐዋ ሥ 4፡ 12 ) ።*

*2/_እንድም-ታቦት /መርከብ ጻጋን የተሞላች የቡርክት-ቅድስት- ድንግል ማርያም ምሳሌ ናት። ያችን መርከብ ከሰው ዘር ወገን ለስምንት ነፍሳት መዳን ምክንያት እንዳደረጋት ፡ ጌታችንም በሲኦል ተግዘው የነበሩ የሰው ዘር ነፍሳትን ሁሉ ነጻ ያወጣ በርስዋ አድሮ ፡ የርስዋን ሥጋ ከመለኮቱ ጋር በማዋሐድ ነውና።*

*3/. እንድም መርከብ የቤተ ክርስቲያን ምሳሌ ናት። ይህም ማለት ወደዚያች መርከብ የገቡ ፍጥረታት ሁሉ፡ ክፉውም፡ ደጉም፡ አይጡ፣ ጉርጡ፣ አባቡ፡ ጊንጡ፣ ርግብና ጨልፊት አሞራው ሳይቀር መዳን እንደቻለ፡ ቤተ ክርስቲያን ኃጥእ፡ ጻድቅ፡ ክፉና ደግ፡ ድሃና ባለጸጋ፡ ወይም በቆዳ ቀለም ነጭና ጥቁር በማለት ምንም ዓይነት ልዩነት ባለማድረግ ሁሉንም ተቀብላ በማስተናገድ ከመሥራችዋ ከክርስቶስ በማማለድ የኀጢአትን ስርየት ማግኘት እንዲችሉ ስትጸልይ ትኖራለችና ።*

*4/. እንድም መርከብ የሰው ሕይወት ምሳሌ-ናት። ያች መርከብ በባሕር ላይ ስትንሳፈፍ በዙ ማዕበል ሞገድ እየተጋፋ ያንገላታት እንደነበር፡ የሰውም ልብ እንደዚሁ በልዩ ፡ልዩ የአሳብ ውጣ ፡ውረድ ሲዋልልና*



www.ethiopianorthodox.org

ኃጢአት እንደ ማዕበል ሞገድ ሆኖ ሲያማታው ይኖራል ። ያንንም የእሳብ ውጣ፡ ውረድና የልብን /የአእምሮን ጭንቀት ሁሉ ፀጥ አድርጎ የሚያረጋጋው የሰላም አምላክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ልባችን መርከብ ሲገባ ብቻ ነው ( ማቴ 8 :23 -27 ) ።

5/. በቍ 6 -12 እንደተጻፈ የውኃውን መጉደል አይቶ እንዲመለስ ተልኮ እንደ_ወጣ የቀረው ቍራ ተልእኳቸውን ለመፈጸም ምንም ዓይነት እምነት የማይጣልበቸው ሰዎች ምሳሌ ፡ ስለሆነ የቍራ መልእክትኛ" መባልን አስከትሏል።በአንጻሩ ግን የውኃውን መጉደል ለማብሠር ለምለም የወይራ ቅጠል ይዛ ወደ ኖኅ የተመለሰችው ርግብ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰላም ዓርማ ለመሆን በቅታለች ። የውኃውን መጉደል ያበሠረች ያች ርግብ የኃጢአት ባሕር መጉደሉን ብቻ ሳይሆን ፡ ሥር መሠረቱ መድረቁን ለዓይነ ኅሊናችን አጕልቶ የሚያሳይ የመንፈስ ቅዱስም ምሳሌ ናት።

6/. በሌላም በኩል ርግበ ኖኅ የበ‐ርከት ቅድስት ድንግል ምሳሌ ናት። ከአዳም ሲወራረስ በመጣ በኃጢአት ደዌ የተመረዘ ይህ ዓለም የተፈወሰበት የጽድቅ አጽቅ (A Branch of Righteousness ክርስቶስ ከርስዋ ተወልዶ በሰው መልክ ታ:ː:ልና ነው (ኤር 33፡13)።

## ፱ /9. <u>እግዚአብሔር ለኖኅና ለልጆቹ የሰጣቸው በረከት</u>

1-5 እግዚአብሔር ኖኅንና ልጆቹን እንዲህ ሲል ባረካቸው፡ "ብዙ፡ ተባዙ ድርንም ሙሉአት ፡ የመፈራታችሁ ግርማ በእንስሳትና አራዊት ሁሉ ፡ ላይ፡ በአዕዋፈ ሰማይና በባሕር ዓሣዎች፡ በሌሎችም ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት ሁሉ ላይ ይሁን ። የምድር ሐመልማልና በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ ምግብ - እንዲሆኑላችሁ ሰጥቻችኋለሁ። ነገር ግን ደም ያለብትን ( እርጥብ) ሥጋ እትብሉ ። በደም ውስጥ ሕይወት አለና ( ዘሌ 17፡ 3 ) ። 6 ሰውን የሚገድል ሁሉ ቅጣቱ ሞት ይሆናል ፤ የሰውን ደም የሚያፈስ ፡ የእርሱም ይፈስሳል ፡ እግዚአብሔር ሰውን በራሱ አርአያና አምሳል ፈጥሮታልና ። 8- 17 እነሆ ከእናንተና በደመ-ነፍስ ሕያዋን ሆነው በምድር ላይ ከሚኖሩ ፍጥረታት ሁሉ ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይህ ነው፡ በዚህ ቃል-ኪዳን መሠረት፣ዳግመኛ ምድርን በጥፋት ውሃ እንድትደመሰስ አላደርግም። ለዚህ ቃል-ኪዳን ምልክት ይሆን ዘንድ፣ ሰማይ በደመና በሚሸፈንበት ጊዜ ፣ ቀስተ በደመናው መካከል እንዲታይ አደርጋለሁ›"።



<u>እርግማንና በረከት፡</u> ኖኅ ገበሬ መሆን ጀምሮ ወይን ተከለ። ከወይን ጠጅም ጠጥቶ ሰከረና በድንኳን ውስጥ ዕራቁቱን ተኝቶ ሳለ፡ የከነዓን አባት የሆነው የኖኅ ልጅ ካም ያባቱን ዕራቁትነት አየ። ሄዶም ለሁለቱ ወንድሞቹ ለሴምና ለያፌት ነገራቸው። እነርሱ ግን፣ የአባታቸውን ዕራቁትነት ላለማየት-ፊታቸውን መልሰው ወደ ኋላ በመሄድ ልብስ አለበሱት፡ የአባታቸውን ዕርቃን ማየት አልፈለጉምና። ኖኅ ከወይኑ ስካር በነቃ ጊዜ፣ታናሽ ልጁ ካም ያደረገበትን ነገር አወቀ። ስለዚህ እንዲህ ሲል ረገመው፤‹‹ከነዓን የተረገመ፡ ነው። ለወንድሞቹ አገልጋይ ባሪያ ይሁን። የሴም አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ፤ ከነዓን ለእርሱ አገልጋይ ይሁን፡ እግዚአብሔር ያፌትን ያስፋ፤ በሴም ድንኳ ይደር " ።

(<u>ትርጓሜ-</u> 16 ከእግዚአብሔር የተሰጠው የቀስተ-ደመና ምልክት፣ በቀለም ተሸላልሞ መታየቱ ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተዝጐረጐረውን የቀራንዮ መስቀል ያመለክታል።_የኢትዮጵያም ሰንደቅ-አላማ ምሳሌነቱን የወሰደ ከዚሁ ነው ። የሰንደቅ ዓላማዪቱ አረንጓዴ ቀለም የልምላሜ፡ ቢጫው የተስፋ፡ ምልክት ሲሆን፡ ቀዩ ቀለም ለሀገር ነጻነትና ሉዓላዊነት ክብር የሚከፈለውን መሥዋዕትነት ያሳያል ። <u>በቍጥር 25-27</u> እንደተጻፈ፡ ኖኅ በካም ፈንታ ከነዓንን የረገመበት ምክንያት ፣ ካም ቀድሞ እግዚአብሔር አምላክ የባረከው ስለ ነበርና የእግዚአብሔርን በረከት መለወጥ ስለማይቻል፣ ይህን እርግማኑ በልጅህ አግኘው፡ ዘር አይውጣልህ እንደ ማለት ይመስላል ( ዘኍ 23፥ 20 ) ። <u>ይ-መርገም መቼ ?</u> እንዴትስ ተፈጸመ?" ለሚለው-ጥያቄ እስከ አሁን ድረስ -ትክክለኛ መልስ የተገኘለት አይመስልም ። አንዳንድ መተርጉማን እስራኤል ከግብጽ ወጥተው ሰባቱን ነገደ-ከነዓን ደምስሰው፣ ምድራቸውን በወረሱ ጊዜ ይህ መርገም እንደ ተፈጸመባቸው አድርገው ጽፈዋል።

_እንደዚሁ ደግሞ በአፍሪካ የሚኖሩትን የካምን ነገደ-ሕዝብ የመልክ ጥቍረት በመመልከት፣ይ-መርገም-በእነርሱ-ላይ ብቻ እንደ ተፈጸመ አስመስለው በመተርጐም የባርነትን አገዛዝና ጭቈና የጥቍር ሕዝብ ዕድል፡ ፍንታ አድርገው የሚመለከቱም ነበሩ። ነገር ግን ባርነት የመብት ማጣት፣ የነጻነት ክብር መገፈፍ ያሚያስከትለው የድኽነት ውጤት እንጂ ፣ ከመልክ ጥቍረትና ንጣት ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም። መብት ያጣና፣ ነጻነቱን የተገፈፈ ፡ ነጭም ይሁን



www.ethiopianorthodox.org

ጥቍር ሕዝብ በባርነት መሸጥና መለወጥ ግዴታው ነው። ይህም ቅኝ ገዢዎችና ባሪያ ፈንጋዮች ያመጡበት እዳ መሆኑን ከታሪክ ማኅደር መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ የሴም ዘር የነበረው ዮሴፍ ሰብአዊ መብቱን በገዛ ወንድሞቹ ተገፍፎ ከተሸጠ በኋላ+ ለተወሰነ ጊዜ በባርነት ማገልገሉ ይታወሳል ( ዘፍ 39፡ 2- 12 ) ።

**እንግሊዞች** በሮማውያን ወረራ ድል ሆነው፡ ለዐራት መቶ ዓመታት በተገዙበት ዘመን በሮማ ከተማ ባነስተኛ ዋጋ በባርነት ሲሸጡና ሲለወጡ ነበር። ታዲያ በዚያው ዘመን የነበሩ የሮማው ፓፓ ይህንኑ ተመልክተው ፣ ከየት እንደመጡ ሲጠይቁ፡ ከእንግላንድ የመጡ ናቸው" አሏቸው። ፓፓውም ይህንን ሲሰሙ አዝነው እነዚህ ሰዎች ለእኔ እንደ ኤንጂልስ ማለትም መላእክትን ይመስሉኛል' አሉ። የባርነትን አስከፊነት የተረዱት እኒያ ፖፕ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ አስበውበት አውግስቲን በሚባል ዐቢይ መነኮስ የሚመሩ የወንጌል መልክተኞችን ልከውላቸው የክርስትናን እምነት ከተቀበሉ በኋላ ፣ ነጻነታቸውን ተጐናጽፈው እስካሁን ድረስ ታሪክ ሠሪዎች ለመሆን በቅተዋል። (ይህን ታሪክ 'March of Time" በሚል ርእስ እንግሊዞች የቅኝ አህጉር ዜጎችን ያስተምሩበት በነበረው መጽሐፍ ክፍል ሁለት ይመልከቱ ) ።

_"ልጁ ካም በኖኅ ላይ ፈጸመ የተባለውስ በደል፡ ያን ያህል ከባድ ዓለም አቀፍ መርገም ማስከተል-ይችል-ነበር-ወይ?" ከሚለውም ጥያቄ አንጻር ተፈጻሚነቱ አጠራጣሪ ሆኖ ቀይቷል ለማለትም ያስደፍራል ።

26-_‹‹እግዚአብሔር- በሴም- ድንኳን- ይደር›› የሚለው -መሲሐዊ- ትንቢት፡ ክርስቶስ የሴም-ዘር-ከሆነችው-ከበርከት ቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋና ነፍስን ነሥቶ በመዋሐድ ፣ አምላክ ወሰብእ መሆኑን ያሳያል። የሴም ድንኳን እግዚአብሔር ወልድ ለተዋሕዶተ ሥጋ የመረጣት የበርከት ቅ/ት ድ? ማርያም ምሳሌ ናትና ። """"""""""""""""""""""""

## ፲ /10 ከኖኅ ቀጥሎ የተነሣው-ነገደ-ሕዝብ- የሐረገ ትውልድ-አወራረድ

ታሪክ ፡_የኖኅ ልጆች ማለት የሴም፣ የካምና የያፌት ሐረገ-ትውልድ አወራረድ በዚህ ምዕራፍ ተገልጧል። ስለ ያፌት ትውልድ ከቍ 2--5 ስለ ካም ትውልድ ከቍ 6–20፡ ስለ ሤም ትውልድ ከቍ 21--31 ተጽፎአልና ነው። ቍ 6-12 የካም ልጆች ዐራት ሲሆኑ፡ " ኩሽ፣ ምጽራ ይም፣ ፉጥና ከነዓን ተብለው ይጠራሉ። ኩሽ ናምሩድን ወለደ፡ ናምሩድ



በእግዚአብሔር ፊት የታወቀ ስመ-ጥር አዳኝ * ጦረኛ ) ሆነ ፣ ስለዚህም ሰዎች ሲመርቁ፣ ‹‹ በእግዚአብሔር ፊት እንደ-ታወቀው አዳኝ ( ጦረኛ ) እንደ ናምሩድ ያድርግህ›› ይሉ ነበር። ናምሩድ በሰናኦር ምድር፡-ባቢሎን፣ ኤሬክና አካድ የተባሉትን ከተሞች ከመሠረተ በኋላ፣ ወደ አሶር ዘምቶ ድል በማድረግ ነነዌን፣ ሬሆቦትንና ሌሎችን ከተሞች ቈረቈረ። 14 የፍልስጥማውያን ትውልድ፣ የካም ልጅ ከሆነው ከምፅራይም ሲያያዝ የመጣ ነው።

(ትርጓሜ‹-ኩሽ ናምሩድን ወለደ››ተብሎ የተጻፈውን ስንመለከት፣ መጽሐፍ ቅዱስ ናምሩድን ስመ-ጥር ጦረኛና አገር አቅኚ አድርጎ ከማሳየት ሌላ ፡ አንዳንድ የምዕራብ ዓለም የመጽሐፍ ቅዱስ መተርጒማን የሚያትቱትን ያህል ክፉ የዓመፅ ሰው አያደርገውም። የዓመፅ ሰው ቢሆንማ ኖሮ፣ የዚያ ዘመን ሰዎች የሚወዱትን ልጅ ወይም ሌላ ሰው ሲመርቁ፣ "በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ አዳኝ እንደ ሆነው እንደ ናምሩድ ያድርግህ ››ማለት ባልቻሉም ነበር። ) """"""""""""""""""

## ፲፩ /11. - የባቢሎን ግንብ መፍረስና የሕዝብ ቋንቋ መለያየት :

1 –2 ከአዳም ጀምሮ ፣ የባቢሎን ግንብ እስከተሠራበት ዘመን ድረስ፣ የሰው ዘር ሁሉ የሚናገረው ቋንቋ ወይም ልሳን አንድ ዓይነት ብቻ ነበር ። ሰዎች ሁሉ በሰናዖር ሜዳ ተከማችተው ሲኖሩ ‹‹ኑ ለስማችን መጠሪያ የሚሆን ከተማና ጫፉ እስከ ሰማይ የሚደርስ ታላቅ ግንብ እንሥራ" ተባባሉ ፡ በዚያ ታላቅ ሜዳ ድንጋይ አልነበረም የሠሩበት ጡብ እንደ ድንጋይ ሆነላቸው ፣ የምድሪቱ ዝፍት ( ሬንጅ የሚመስል ማጣበቂያ ቅጥራን ) እንደ ጭቃ ሆነላቸው። 6- 9 ግዚአብሔር አምላክ ‹‹ኑ እንውረድና ቋንቋቸውን እንለዋውጠው›› አለ። ቋንቋቸውም በተለዋወጠ ጊዜ፣በአሳብ መግባባትና መደማመጥ ባለመቻላቸው ምክንያት ስለተበታተኑ፣ የዚያ ቦታ /አገር ስም 'ባቢል (ባቢሎን፡ ዝርወት፡" መበታተን ) ተብሎ ተጠራ።

### የአብራም አባት የታራ ሐረገ- ትውልድ ፡ --

10 –26 ሴም አርፋክስድን፣ አርፋክስድ ቃይንም፣ ቃይንም ሳላን፣ ሳላ ዔቦርን ወለደ፡ ( ዕብራዊ /ዕብራያን የሚለው ሌላው የአብራም ዘርዐ ትውልድ መጠሪያ ስም ከዚሁ ከዔቦር ሲያያዝ የመጣ ነው)። ቀጥሎም ዔቦር ፋሌቅን ወለደ። ፋሌቅ ራግውን፡ ራግው ሴሮህን፡ ሴሮህ ናኮርን፡ ናኮርም ታራን ወለደ። ታራ አብራምን ፡ ናኮርን፡ ሐራንን



www.ethiopianorthodox.org

ወለደ። ሐራን -ሎጥን ከወለደ በኋላ በትውልድ አገሩ ከላውዴዎን ዑር ተብላ በምጠጠራ ከተማው ሞተ ።አብራምና ናኮርም ሚቶችን አገቡ፡ የአብራም ሚስት ስም ሦራ ሲሆን ፡ የናኮር ሚስት ሚልካ ናት ። ታራ ልጁን አብራምን የልጁን የሐራንን ልጅ ሎጥን አስከትሎ፣ በከላውዴዎን አገር ዑር ተብላ ከምትጠራ ከተማው ተነሣ፡ ወደ ከነዓንም ምድር በመጓዝ ካራን ደረሱ ፡ የታራ እድሜ 205 ዓመት ነበር። እርሱም ከነዓን ሳይደርስ በካራን ሞተ። (ትርጓሜ ፡ የባቢሎንን ግንብ በሚመለከት ሰዎች ተጠብበው ከተሞችንና ታላላቅ ሕንጻዎችን መሥራታቸው ኃጢአት አልነበረም ። ነገር ግን እግዚአብብሔር አምላክ ‹‹ብዙ ተባዙ፡" ምድርንም ሙሏት ›› ሲል የሰጠውን ትእዛዝ ሥራ ላይ ለማዋል በዓለም እንዲበተኑ ማድረጉ አስፈላጊ ነበርና ነገሩ ጥበበ እግዚአብሔር ያለበት ይመስላል ፦ የዘመናችንም ትውልድ፣ የገጠሩን የእርሻ ቦታ -እየተወ ወደ ከተማ ፈልሶ በመግባት ተጣቦ መኖሩ፡ ለበሽታና ለኑሮ ችግር የሚያጋልጥ ሆኖ መታየቱ ከዚህ የተለየ አይደለም። ‹‹ኑ እንውረድና ቋንቋቸውን እንለዋውጠው›› የሚለው አነጋገር ዋናው ፍሬ አሳብ የእግዚአብሔርን አንድነትና ሦስትነት የሚገልጥ ምሥጢረ_ሥላሴ ነው። በሌላ በኩል እኛ ብሎ መናገር ዓረብኛንና ጀርመንኛን በመሳሰሉት አንዳንድ ቋንቋዎች የተለመደ ንጉሣዊ ዘይቤ ነው። ይኸውም እርሱን የሚከተሉት እልፍ እእላፋት ቅዱሳን መላእክት አብረውት አሉና ። ከቁ 31-32 ቀጥሎ በጅምር የቀረው የአብራም አባት የታራ ጉዞ ምንን ያስተምረናል? በከላውዴዎን ትውልድ ከተማው ከነበረችው ከዑር ተነሥቶ ወደ ከነዓን ለመድረስ በጉዞ ላይ ሳለ፣ ካራን ተብላ በምትጠራ ቦታ ስለ ሞተ፣ በዚያ ተቀብሯል። ምናልባትም ጣዖት አምላኪ ስለ ነበረ፣ ያችን የተስፋ ምድር የከነዓንን አፈር ለመርገጥ ያልተፈቀደለት ይመስላል። ዛሬም ቢሆን እነሆ፡ በዚሁ ዓይነት የእምነት ጉዞ ጀምረው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመድረስ ጥቂት ሲቀራቸው፡ ጉዟቸው ተሰናክሎ የሚወድቁ እጅግ ብዙ መሆናቸውን ቅዱስ መጽሐፍ ይነግረናል ። የዚህን ተመሳሳይ ሌላ ታሪክ ዘግየት ብለን በመ/ ኊት ምዕ 6–17 በጅምር ከቀረው ከዖርፋ ጉዞ እናያለን ።)

## ፲፪ /12 """"""" የአብራም መጠራትና ጉዞው """""""" ወደ ተስፋይቱ ምድር

1-3 እግዚአብሔር አብራምን እንዲህ አለው፡ ‹‹ከአገርህ ወጥተህ፡ ከአባትህ ቤተሰብ ተለይተህ ፡ እኔ ወደማሳይህ ምድር ሂድ። እኔ አንተን ታላቅ



ሕዝብ አደርግሃለሁ፡ እባርክሃለሁ፡ ስምህን ታላቅ (ገናና) አደርገዋለሁ። የሚረግሙህን እረግማለሁ፡ የሚባርኩህን እባርካለሁ። የምድር ነገዶችም ሁሉ ባንተ ይባረካሉ" አለው። አብራምም በዚያ ለተገለጠ ለት አምላክ መሥዋዕት አቀረበ።

## አብራምና ሦራ ወደ ግብጽ ተሰደዱ፡

10--20 አብራም ከነዓን እንደ ደረሰ ብዙ ሳይቈይ በምድሪቱ ላይ ረኃብ ስለ ሆነ፣ ወደ ግብጽ ወረደ፡ የግብጽ ሰዎች በሚስቱ በሦራ ቁንጅና ምክንያት እንዳይገድሉት ስለፈራ ፡ ‹‹እኅቴ ናት›› አለ። ግብጻውያንም የሦራን ውበት አይተው በመደነቅ "ይህችማ ለንጉሡ ፈሮዖን የምትገባ ናት" ብለው ወደ ቤተ መንግሥት ተወስዳ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በሦራ ምክንያት ተቈጥቶ በግብጽ ንጉሥ ፈርዖንና በባለሟሎቹ ላይ ሁሉ ከባድ መቅሠፍት-አመጣባቸው። ፈርዖንም- ደንግጦ ምንም ችግር ሳይፈጥርባት፣ሦራን ለባልዋ ለአብራም መልሶ አስረከባት። እንደ ካሣ ይሆንለትም ዘንድ ብዙ የበግ ፣ የፍየልና የቀንድ ከብት መንጋ ፣ ብዙ አህዮችና ግመሎችን ከወንዶችና ከሴቶች አገልጋዮች ጋር ለአብራም ሰጠው። በአብራም ላይ ማንም ሰው - የሚያሳዝነውን ክፉ ነገር እንዳያደርግበትና፣ ከግብጽ ሲወጣም በሰላም እንዲሸኙት አዘዘ፡ (ትርጓሜ፡ 'አብራም ሚስቱን እኅቴ ናት " በማለቱ ወደ ንጉሥ ፈርዖን ቤተ መንግሥት የተወሰደችበት ሁኔታ ውስጡ የእግዚአብሔር ጥበብ ያለበት' ነው፡ ይኸውም እግዚአብሔር አብራምን ማበልጸግ ስለፈለገ የርሱ ጥቂ ሳይለያት ወደ ግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ቤተ መንግሥት ተወሰደች ። አብራምም ነቢይ ስለሆነ ይህን ያውቅ ነበር ።)

## ፲፫ /13 በእረኞች ጠብና ክርክር የአብራምና ሎጥ መለያየት ፡

1-2፡ አብራም ከግብጽ ሲመለስ ፡ በብዙ የእንስሳት መንጋ፡ በወርቅና በብር ታላቅ ባለጸጋ ሆኖ ነበር። ሎጥም በበኩሉ የብዙ ከብት መንጋ ባለንብረት ስለነበር ከብቶቻቸውን የሚያሰማሩበት የግር ግጦሽ ቦታ ጠበባቸው ። ከዚህም የተነሣ በአብራምና በሎጥ እረኞች መካከል ጠብና ክርክር መነሣት፡ ጀመረ። ስለዚህ፣ አብራም ሎጥን እንዲህ አለው፡ ‹‹እነሆ እኛ ወንድማማች ነን ። በእኔና በአንተ ፡ በእረኞቻችንም መካከል ጠብና ክርክር ሊኖር አይገባም። እነሆ፣ ምድሪቱ በፊትህ ናት ። ደስ የሚልህን ቦታ መርጠህ አንተ ግራውን ብትይዝ፡ እኔ ወደ ቀኝ እሄዳለሁ፤ አንተ ቀኙን ብትይዝ እኔ ግራውን

www.ethiopianorthodox.org

እይዛለሁ፡ ስለዚህ የከብት መንጋህን ይዘህ ከእኔ እንድትለይ እለምንሃለሁ››። 10-13 ሎጥም ዓይኖቹን አቅንቶ ሲያይ፡ እነሆ በዮርዳኖስ ወንዝ ዙሪያ ያለው አገር ለምለም ፣ እንደ እግዚአብሔር ገነትና እንደ ግብጽም ምድር ውኃ-ገብ መሆኑን አየ። መንጋውን ሁሉ ለይቶ ወደዚያ አመራ። እስከ ሰዶም አስፍቶ ድንኳኑን ተከለ። በዚያች አገር የሚኖሩ የሰዶም ሰዎች ግን፣ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአትን አብዝተው የሚሠሩ ነበሩ። 4-18 ሎጥ ከተለየ በኋላ፣ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና እንዲህ አለው፤ ‹‹ምድሪቱን ዳር እስከ ዳር በዐራቱም ማእዘን ተመልከት። ይህችንም ምድር ለአንተና ለዘሮችህ -የዘላለም ርስት አድርጌ እሰጣለሁ። ዘርህን ሊቈጠር እንደማይችል እንደ ምድር አሸዋ አበዛዋለሁ"።

(ትርጓሜ- በፈተና ውስጥ እንደ ወርቅ ነጥሮ የወጣ

''''''''''' የአብራም እምነት ''''''''''

ምዕ 12፡ 10--20 የአብራም እምነት ፅናትና የሥነ ምግባሩ ጥራት በግልጥ መታየት የጀመረው፣ በልዩ-ልዩ ፈተና ውስጥ በማለፍና እንደ ወርቅ ነጥሮ በመውጣት ነው። ይኸውም፡ 1ኛ የመጀመሪያው ፈተና ከትውልድ አገሩ ወጥቶ ወደማያውቃት አገር እንዲሄድ ሲነገረው "ክየት ወዴት?" ብሎ በመጠየቅ አላመነታም ፡ለእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ታዛዥ ሆኖ ጉዞውን ቀጠለ እንጂ - ዕብ 11፡ 8 )።

2ኛም አብራም እዚያች አገር እንደደረሰ፣ በምድር ላይ ረኃብ በመሆኑ ምክንያት ፡ ምንም ሳይሰቀቅ ፣ ያን ቀውጢ ጊዜ ለማሳለፍ ወደ ግብጽ ቢሰደድም፣ በእምነቱ እንደፀና መገኘቱ፣ ብዙ ሀብትና ብልጽግናን አስገኘለት እንጂ ስደቱ ያጎደለበት ነገር የለም ። በኅር ግጦሽ መጥበብ ምክንያት የተፈጠረውን ያለመግባባት ችግር በቀላሉ ለመፍታት ሲል አብራም-ለምድሪቱ ሳይሳሳ ፡ ሎጥ የሚፈልገውን መርጦ እንዲይዝ መፍቀዱ የሚደነቅ ነው። የፀብና የክርክሩም መነሻ የሀብት ብዛት መሆኑኑን እንመለከታለን።

_የገንዘብ ፍቅር የኃጢአት ሁሉ ምንጭ ( ሥር- መሠረቱ ነውና ( 1 ጢሞ 6፡ 10 ) ። ፍቅረ ነዋይ የሚያሸንፋቸው ሰዎች በከተማ ብቻ ሳይሆን በገጠማትም ይኖራሉ። የአባቶች አባት በነበረው በአብራም ላይ ግን የፍቅረ ነዋይ ተገዢነት አልነበረም። ይህኑ በሚመለከት ለሌሎች ማስተማሪያ ይሆን ዘንድ ብቻ ተከታዩ ተጓዳኝ ታሪክና ምሳሌ እነሆ

"ባለቤት ያጣ ወርቅ " - ሦስት ሰዎች (ጓደኞሞች) መንነው ገዳም ለመግባት ወስነው ጉዞ ይጀምራሉ። ይህን የተረዳ ሰይጣን ገና ሳይጠናከሩ እቅዳቸውን ለማበላሸት የወርቅ ጉልቻ በመንገድ ላይ አስቀምጦ ይጠብቃቸው ነበር።ያን ወርቅ ሲያገኙ ደስ ብሏቸው ከዚያ ወርቅ ትንሽ ቀንሰው ሰጡትና "ወደ ከተማ ተመልሰህ ይህን ወርቅ ወደ ገንዘብ ለውጠህ የከሶ መድኃኒት ገዝተህልን ና " ብለው ከሦስቱ አንዱን ይልኩታል። ያም የምናኔ ጀማሪ ወደ ከተማ ተመልሶ ሲሄድ፡ ሁለት ጓደኞቹን ገድሎ ያን ርቅ ለራሱ ብቻ በማድረግ የንግድ ሥራ ለማቋቋም አሰበ። ስለዚህም ከከሶ መድኃኒቱ ጋር ጓደኞቹን የሚገድልበትን መርዝ ገዝቶ መጣ።

_ሌሎቹም ሁለቱ መናንያን በየበኩላቸው ያን ወርቅ ለየራሳቸው ለማድረግና ወደ ዓለም ሊመለሱ ምኞት ነበራቸው። በማግሥቱ የከሶ መድኃኒቱን ከመርዝ ጋር በጥብጦ ሁለት ጓደኞቹን እንዲጠጡ ጠየቀ። ከሁለቱ አንዱ ጎራዴ ይዞ ራሱን ለማደፋፈር እየፎከረ ከተንጐራደደ በኋላ፡ የሁለቱን ጓደኞቹን አንገት ቆርጦ ይጥልና የተደገሰለትን የከሶ መድኃኒት አንሥቶ ሲጠጣ መርዙ አዙሮ በመጣል ስለገደለው ያ ሁሉ ወርቅ ከሦስቱም ለአንዱ እንኳ ሳይሆን ባለቤት አጥቶ ቀረ" ይልናል የመጽሐፈ . መነኮሳት ታሪክ ) ። የወንጌሉም ቃል -"ለራሱ ሀብትን ማከማችት የሚወድ ፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ድሃ የሆነ ሰው እንደዚሁ ነው ይልላ ( ሉቃ 12 )፡_

የአብራምና የሎጥ እረኞች ዓይነት ጠብና ክርክር ችግር ፈጣሪነት ዛሬም የክርስቶስን መንጋ ጠባቂዎች በሆኑት መንፈሳውያን መሪዎች መካከል፡ አልፎ። አልፎ ይታያል።ያም ዓይነት ችግር ሲኖር በጥሞና ተነጋግሮ ለመፍታት እንደ አብራም ልበ- ሰፊ መሆንን ይጠይቃል።

_በአንጻሩ የሎጥ ምርጫ ግን ስስት የሞላበት ይመስላል። ይህም በጣም ለምለም የሆነውን ውኃ- ገብ ቦታ ሁሉ ለራሱ በመምረጡ ይታወቃል ። የሎጥ መንፈሳዊ ሕይወትም ባጢቃላይ ከአብራም ጋር አብሮ የሚሄድ አይመስልም። አብራም በየደረሰበት መሥዋዕት በማቅረብ ፈጣሪውን ሲያከብር ይታያል። ሎጥ -ግን መሥዋዕት ሲያቀርብ አናይም ።

_በሌላም በኩል፡ ‹‹በሩቅ የሚታይ ተራራ ለምለም ይመስላል›› እንዲሉ ሎጥ በዮርዳኖስ ዙሪያ የነበሩትን የሰዶምና ገሞራ አገሮችን ልምላሜ ብቻ ሲመለከት፣ በውስጣቸው ሥር ሰዶ የነበረውን ኃጢአት አላየም ። ይህም ጥንቃቄ የጎደለው ምርጫ ያስከተለበትን ችግርና ፈተና ሁሉ ዘግየት ብለን በምዕራፍ 14 እና 19 እንመለከተዋለን ።





www.ethiopianorthodox.org

_በዘመናችንም እንደዚሁ አንዳንድ የውጭ አገሮችን ብልጽግና ስንመለከት በውስጣቸው ያለውን ብዙ አስከፊና መጥፎ ልምድ ሁሉ በጥሞና ማጤን ባለመቻል-ብዙ ወገን /ሌጋ በወዶ -ገባ ባርነት ተጎድቷል። የሎጥን ሃይማኖታዊ ሥነ-ምግባር ጐላ አድርጎ የሚያሳይ ሌላው መልካም ታሪክ፡ ምንም እንኳ ሳያውቀው የተፈጸመ ቢሆንም የእግዚአብሔርን መላእክት በቤቱ እንግድነት ለመቀበል መብቃቱ ነው (ዘፍ 19፡ 1- 11 + ዕብ 13፡ 12 ) ። ሎጥ በዓመፀኛ ሕዝብ መካከል ነፍሱ እየተጨነቀች የሚኖር ጻድቅ ሰው ነበር" ይለዋል -2 ጴጥ 2፡ 6-10 )

## ፲፬ /14- የወገን መማረክ ፡ ሰላማዊውን የእግዚአብሔር ሰው አብራምን ለጦርነት አነሣሣ

1-12 አምስቱ የሶዶም፣ የገሞራ፣ የአዳማ ፣ የሰቦይምና የዞዓር /ሴጎር ነገሥታት ለኮሎዶጎሞር ንጉሥ ቅኚ ተገዢዎች ሆነው፣ ዐሥራ ሁለት ዓመት ሙሉ ገብረውለት ነበር። በዐሥራ ሦስተኛው ዓመት ግን፣ "አንገብርም" ብለው ዐመፁ። ስለዚህም ፣ ኮሎዶጎሞር የርሱ ተባባሪዎች የሆኑትን ሌሎች ሦስት -ነገሥታት ጨምሮ ፡ በአምስቱ የሰዶምና የገሞራ ዓመፀኞች ነገሥታት ላይ ዘምቶ ድል ካደረገ በኋላ ፣ የእነዚህን የአምስቱን አገሮችና የአካባቢያቸውን ሕዝብ ሀብት ንብረት ዘርፈው ሲመለሱ ሎጥንም ከነከብቱ ማርከው ወሰዱት።

13- 16 ከጦርነት ሸሽቶ ያመለጠ አንድ ሰው ወደ ዕብራዊዉ ወደ አብራም መጥቶ ይህን ሁሉ ነገረው። አብራም የተማረከብትን የወንድሙን ልጅ ሎጥን ለማስመለስ ፣ ሦስት መቶ ዐሥራ ስምንት የቤት አገልጋዮቹን አስታጥቆ ለመዝመት ተነሣ ። እኩለ ሌሊት ላይ ብላቴኖቹን በቡድን ከፋፍሎ በማሠለፍና ድንገተኛ አደጋ በመጣል ዐራቱን የኮሎዶጎሞር ነገሥታት ድል ነሥቶ ሠራዊታቸውን በመበተን አሳደዳቸው ፡ ሎጥንና ከእርሱ ጋር ከሰዶም ማርከው የወሰዱአቸውን ሴቶችና ሌሎችንም ምርኮኞች አስመለሰ።

_አብራም በታላቅ ድል አድራጊነት ሲመለስ የልዑል እግዚአብሔር ካህን እየተባለ የሚጠራ የሳሌም ንጉሥ መልክጼዴቅ የስንዴ ኅብስትና የወይን ጭማቂ ይዞ መጥቶ ፡ የክብር አቀባበል አደረገለት ። እንዲህ ሲልም ባረከው ‹‹ሰማይንና ምድርን የፈጠረ ልዑል እግዚአብሔር አብራምን ይባርክ። አብራም ሆይ! በጠላቶችህ ላይ ድልን ያቀዳጀህ ልዑል እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን››።



አብራምም ከያዘው ምርኮ ሁሉ ከዐሥር አንዱን እጅ ለመልከ ጼዴቅ ሰጠው ።(ትርጓሜ፡ መልከ ጼዴቅ ለአብራም ያመጣለት ኅብስትና የወይን ጭማቂ የቅዱስ ሥጋውና የክቡር ደሙ-ምሳሌ ነው። መልከ-ጼዴቅ በአንድ እግዚአብሔር ብቻ በማመን ረገድ፣ ከአብራም በፊት የተመረጠና ክህነትን ከመንግሥት ጋር አስተባብሮ ይዞ በመገኘት የወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ለዘላለም የሚኖር ካህን ተብሎ የተነገረለት ታላቅ አባት ነው ( መዝ 110፡ 4 )።
_ከኖኅ ቀጥሎ በረከትን በመስጠት የክህነትን ታላቅነት አጉልቶ የሳየ ይህ መልከ-ጼዴቅ ትውልዱ ከነገደ ካም (አፍሪቃዊ ) እንደ ሆነ፣ ይልቁንም ኢትዮጵያዊ እንደ ነበር ይነገርለታል። ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ‹‹አልቦ ዘዘከረ ሎቱ አበ ወኢእሙ፡ ወአልቦ ጥንት ለመዋዕሊሁ= አባትና እናቱ እነማን እንደ ሆኑና የዘመኑም መነሻ አይታወቅም ›› ብሎ በዕብ 7፡ 3 እንደ ጻፈው፣ የትውልዱን ታሪክ በዝርዝር መግለጥ ያልተፈለገበት ምክንያት፣ ይኸው የካም ዘር ሆኖ መገኘቱ ሳይሆን አይቀርም። እንዴት አንድ አፍሪቃዊ ከአብራም ተቀዳሚነት ያለውና የእውነተኛው እምነት ተከታይ ለመሆን ቢቃ?" የሚል ጥያቄ፣ ዘረኞች የፈጠሩት ሰው- ሠራሽ ግድብ ሳይሆን አልቀረም። ይሁን እንጂ ፣ የአባቶች አባት አብራም ከያዘው ምርኮ ሁሉ አውጣጥቶ፣ ከዐሥር አንዱን እጅ ለመልከ-ጼዴቅ መስጠቱን ስንመለከት ፣ እግዚብሔር አምላክ የክህነትን አገልግሎት ታላቅነት በማጉላት የእጥፍ ድርብ ጸጋና በረከት መገኛ ያደረገው መሆንን ያሳያል። _የወገን መማረክ ሲባል በሎጥ መማረክ ብቻ አላበቃም። ብዙ ወገኖች በሰይጣን ተማርከው ወደ ጥፋት በሚወሰዱበት ጊዜ እነርሱን ለመታደግ "የጸሎት ተጋድሎና ሐዋርያዊ ተልእኮ ለመፈጸም መዘጋጀትን ይጠይቃል" ማለት ነው። ..............................

21-24 ቀድሞ ተሸንፎ የነበረውም የሶዶም ንጉሥ ( ቤራ) አብራምን ሊቀበለው ወጥቶ፤‹‹በምርኮ ያገኘኸውን ሀብት ሁሉ ውሰድ፤ከምርኮኛነት ነጻ ያወጣሃቸውን ሰዎቹን ግን መልስልኝ"፤ አለው። አብራም ግን መልሶ እንዲህ አለው፤‹‹ሰማይንና ምድርን በፈጠረ በልዑል እግዚአብሔር እምላለሁ፤ አብራምን አበለጸግሁት ብለህ እንዳትመካ፤ አንዲት ክር ወይም የጫማ ማሠሪያ (ማዘቢያም) እንኳ፤ ከቶ አልወስድም፤ ከእኔ ጋር የዘመቱ አገልጋዮቼ ከተመገቡትና በጦርነት የተባበሩኝ ወዳጆቼ፤አኔር፣ ኤሽኮልናመምሬ ከሚወስዱት ድርሻ በቀር ሊላውን፤ ቀሪ ሀብትና ንብረትህን ሁሉ ውሰድ››።



www.ethiopianorthodox.org

## ፲፭ /15. """""" የቃል ኪዳን ማጠናከሪያ ራእይ""""""

1-5 እግዚአብሔር ለአብራም በራእይ ተገለጠ፣ ‹‹አብራም ሆይ፣ አይዞህ፣ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ፤ የምሰጥህም ዋጋ እጅግ ታላቅ ነው›› አለው።።አብራምም፤ ‹‹አቤቱ እግዚአብአሔር አምላክ ሆይ፣ ምን ትሰጠኛለህ?! ያለ ልጅ መቅረቴ ነው። እነሆ፣ ኤልዔዘር ተብሎ ከሚጠራና የደማስቆ ሰው ከሆነው ከዚህ ታማኝ አገልጋዩ በቀር፣ ሌላ ወራሽ የለኝም" አለ። የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ አብራም መጣ፤‹‹ከአንተ አብራክ የሚወለድ ልጅ እንጂ፣ሌላ ሰው አይወርስህም››። ወደ ሜዳ (ወደ መስክ) አውጥቶ፤ ‹‹እንግዲህ የሚቻልህ ከሆነ፣የሰማይን ከዋክብት ቍጠር ፤ እነሆ ፣ የዘርህ ብዛት እንደዚሁ ይሆናል›› አለው። 6 አብራምም አመነ፤ ማመኑም ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት።

13-16 እግዚአብሔርም በአብራም ላይ ከባድ እንቅልፍ አመጣበትና፣ ተኝቶ ሳለ *(ከነፍሱ ጋር ለመነጋገር ማለት ነው)* እንዲህ አለው፤ ‹‹ዘርያዎችህ በባዕድ አገር መጻተኞች (ስደተኞች) ሆነው ዐራት መቶ ዓመት በባርነት አስጨንቀው እንደሚገዙአቸው እወቅ፣ በባርነት በሚገዙዋቸው ሕዝብ ላይ ደግሞ እኔ እፈርዳለሁ። ከዚያን በኋላ ግን፣ ብዙ ሀብት ይዘው ይወጣሉ (ዘፀ 12፥35-36 )።

_አንተም በመልካም ሽምግልና ታርፋለህ ። እነርሱም በዐራተኛው ትውልድ ወደዚህች አገር ይመለሳሉ። ያም የሚሆነው የአሞሬዎን ኃጢአት እስኪፈጸም ድረስ ነው››። 18 በዚያች ቀን፤ እግዚአብሔር ‹‹ከግብጽ ወንዝ ጀምሮ እስከ ታላቁ የኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ፣ ይህችን ምድር ለዘሮችህ ሁሉ ርስት አድርጌ እሰጣለሁ›› ሲል ለአብራም የተስፋ ቃል ሰጠው። *(የዚህ አምላካዊ ትንቢት ፍጻሜው በዘፀአት ምዕ 1 እስከ ምዕ 13 ተጽፏል )*

***(ትርጓሜ:*** *ከድል መልስ እግዚአብሔር ለአብራም በራእይ ተገልጦ አዞህ አትፍራ እኔ ላንተ ጋሻህ ነኝ" ማለቱ: "ምናልባት ጠላት እንደገና አንሰራርቶ ይነሣብኝ ይሆን?" እያለ በማሰብና በመጨነቅ ላይ እንደነበር ያመለክታል። በመንፈሳዊዉም ተጋድሎ እንደዚሁ አንድ ጊዜ ብቻ ሰይጣን ዲይብሎስን ድል ነሥቻለሁ ብሎ መዘናጋት አይቻልም። "ሰይጣንና ውሻ ተመላላሽ ነው' እንዲሉ ምን ጊዜም አለመዘናጋትና እንድገና ለሌላ ድል መዘጋጀት ያስፈልጋል ማለት ነው።ሰይጣን ዲያብሎስ ጌታን እንኳ የፈተነው አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሦስት ጊዜ እንደነበር በማቴ 4:1-10 ተጽፏል። )*



## ፲፮ /16. እግዚአብሔር የአጋርን ጭንቀት ተመለከተ :

1-6 የአብራም-ሚስት ሦራ ልጅ ካለመውለዱዋ የተነሣ፣ መኻን እንደ ሆነች የምትቀር መስሏት፣ከግብጽ ካመጣቻት ከአገጋይዋ ከአጋር ልጅ እንዲወልድላት-ፈቅዳ ለአብራም ሰጠችው። አብራም-እንዳለችው አደረገ። ነገር ግን፣ አጋር መፀነስዋን ብወቀች ጊዜ፣ የልብ- ኵራትና-ትዕቢት- አድሮባት እመቤቱዋን ሦራን መናቅ ጀመረች። ሦራ በዚህ ተናዳ ሥቃይ ስላበዛችባት አጋር ወደ በረሃ ኮበለለች።

7-14 የእግዚአብሔር መልአክ አጋርን በአንድ የውሃ ምንጭ አጠገብ አገኛትና እንዲህ ሲል መከራት፤‹‹የሦራ አገልጋይ አጋር ሆይ፣ ከየት መጣሽ? ወዴትስ ትሄጃለሽ? ይልቅስ ወደ እመቤትሽ ወደ ሦራ ተመልሰሽ ሃጂና ታዛዥ መሆንሽን ግለጪላት "።እነሆ፣ አንቺ ፀንሰሻል፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም እስማኤል ብለሽ ትጠሪዋለሽ ። እግዚአብሔር ጭንቀትሽን አይቶአልና። ዘርሽን እጅግ አበዛዋለሁ ፤ ከብዛቱ የተነሣ ሊቈጠር-የማይቻል ይሆናል›› ። 13 አጋርም፣ ‹‹የሚያየኝን እርሱን በእውነት እዚህ ደግሞ አየሁትን?' ለማለት ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ስም፣‹‹ኤልሮኢ›› ብላ ጠራችው። 15-16 ወደ ሦራ ተመልሳም ሄዳ ለአብራም ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ አብራምም አጋር የወለደችለትን ልጅ እስማኤል ብሎ ጠራው። በዚያን ጊዜ አብራም ሰማኒያ ስድስት ዓመት ነበር። ***(ትርጓሜ*** *: የእግዚአብሔር መልአክ አጋርን " የሦራ አገልጋይ አላት" እንጅ ከዚያ የተሻለ የእመቤትነት ደረጃ አልሰጣትም። አገልጋይ ወይም ተገልጋይ ሆኖ በክርስቶስ ለማመን የተጠራም ሁሉ በወንጌል ትምህርት የታነፀ ሕይወት እስኪጀመርና ፡ሁኔታዎች እስኪመቻቹ ድረስ በመቻቻልናበቅን ብማገልገል መቆየት እንጂ ከጌታዬ ከአብራም ፀንሻለሁና በአንድ ጊዜ እመቤት ልሁን ማለት በዚያ ዘመን የተለመደ አልነበረም። ስለዚህ መልአኩ ለአጋር የሰጣት መመሪያ ትዕቢትን አስወግዳ ከሣራ ጋር ቀድሞ በነበረችበት ሁኔታ ታዛዥነትን ባለማጓደል ተግባቢታ መኖር እንድትችል ሲሆን፡ የተሻለ ነጻነትና ክብርን ለማግኘት ደግሞ ከአብራም ወንድ ልጅ በመፅነስዋ የወደፊት ተስፋዋ ብሩህ መሆኑ ተነግሯታል።*

## ፲፯ /17. የግዝረት ሕግ የቃል ኪዳን ምልክት ሆኖ ተሰጠ :

-1-4 አብራም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ፣እግዚአብሔር በራእይ ተገልጦ እንዲህ አለው፤ ‹‹እኔ ኤልሻዳይ ነኝ ፤ ፍጹም ሆነህ በፊቴ ተመላለስ። ከዛሬ ጀምሮ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፤ ነገር ግን፣ ስምህ አብርሃም ይሆናል፤ ለብዙ አሕዛብ አባት አድርጌሃለሁና፤ ደግሞም እጅግ አበዛሃለሁ፣ ነገሥታት ከአንተ ይወጣሉ (ይወለዳሉ)። በእኔና በአንተ



www.ethiopianorthodox.org

መካከል፣ ከአንተም በኋላ፣ በዘርህና በእኔ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳን ይህ ነው፤‹‹በእኔና በአንተ መካከል ምልክት ይሆን ዘንድ፣ ወንድ የሆነ ልጅ ሁሉ በተወለደ በስምንተ-ኛው ቀን ይገዘር።

_ያልተገዘረ ( ቈላፍ የሆነ ) በመካከላችሁ አይኑር።15--24፡-ሚስትህም-ሦራ-ከዛሬ-ጀምሮ-ሣራ-ተብላ-ትጠራለች፤እባርካታለሁ፡ የብዙ ሕዝብና-የአሕዛብ እናት ትሆናለች፡የአሕዛብ ነገሥታት ከእርሱዋ ይወጣሉ›› አብራም ይህን ሁሉ ሲሰማ፣‹‹በእውነት የመቶ ዓመት ሰው፣ልጅ መውለድ ይችላልን ?"ሲል በግንባሩ ወድቆ ሳቀ።እግዚአብሔርም ‹‹በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፤ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ›› አለው። በዚያ ቀን አብርሃም ተገዘረ፡ እስማኤልም ሲገዘር አሥራ ሦስት ዓመቱ ነበር።

*(**ትርጓሜ** ፡ ይህ የግዝረት ሥርዓት ምሳሌነቱ የልብ ሸለፈት የሆነውን ኃጢአት ማስወገድ መሆኑን ሙሴ በዘዳግም 10፡ 16=+ ኤር በምዕ 4፡ 4 ጽፈውታል። በሐዲስ ኪዳን ዘመንም ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ መሆኑን ሐዋርያው ( ሮሜ 10፡ 26 -29 በ + ቆላስይስ 3 11 ።)*

## ፲፰ /18."""""" <u>እግዚአብሔር በሦስት እንግዶች አምሳል</u> """""""

1--8. በቀትር ጊዜ አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ፡ እግዚአብሔር ተገለጠለት፡ ይኸውም አብርሃም ዓይኑን አቅንቶ ሲመለከት፣ እነሆ፣ ሦስት ሰዎች ቆመው አየ። እርሱም ሮጦ ሄደና ወደ ምድር ራሱን ዝቅ አድርጎ ስግዶ እጅ በመንሣት፣ ‹‹እባክህ ጌታዬ አትለፈኝ፡ ጥላ ሥር ዐረፍ በሉ፡ እህልና ውሃ ላምጣላችሁ እግራችሁንም-ታጠቡ፣-ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ፡ እንዳስተናግዳችሁ ፍቀዱልኝ" አላቸው ። እነርሱም መልሰው‹ "እንዳልከው አድርግ›› ሲሉት፡ አብርሃም፡ ሣራ ወዳለችበት ድንኳን ሄዶ፡ ሦስት እንጎቻ እንድታዘጋጅ ነገራት። ወደ ከብቶቹም መንጋ ኼዶ፣ አንድ የሰባ ጥጃ ከመረጠ በኋላ ፡ አርዶ- አውራርዶ ያቀርብ ዘንድ ለአገልጋዩ ሰጠው። አብርሃም ራሱ ያዘጋጀውን እርጎና ወተት አምጥቶ ለእንግዶቹ አቀረበላቸው፡ እነርሱም በሉ። *(**ትርጓሜ** ፡ በመሠረቱ ሥላሴ ምግብ በሉ ማለት እሳት ቅቤን በላ እንደማለት ነው" _ወንዶች ሴቶችን በቤት ሥራ መርዳት /መተጋገዝ በአብርሃም ዘመን በተግባር ታይቷል ። ሚስቱ ሣራ ሦስት ኅብስ (እንጎቻ) ስትጋግር፡ አብርሃም ደግሞ የቤቱን ሥራ ሁሉ ለሚስቱ ለሣራና ለገረዱ ለአጋር ብቻ በመተው*



*ፈንታራሱ ባጭር ታጥቆ፡ እርጎውን፡ ወተቱን ሲያቀራርብና አገልጋዩ ደግሞ አብርሃም ባዘዘው መሠረት ወይፈኑን አርዶ አሣምሮ አወራርዶ ማቅረቡ ተጽፏልና።' ይህን-ታሪክ በአማሪኛ መጽሐፈ ሰዋስው ዘመርሣኤ ሐዘን ወልደ ቂርቆስ አንድ-ባለ-ቅኔ-ከወገናዊ መረዳዳት ጋር አያይዘው በማገናዘብ፡በተናገሩት ኅብር ቅኔ "አንተም ሠርተህ ብላ፡ አንቺም ሠርተሽ ብዪ፡ አላጋር እንጀራ አይበላም ወይ ?" ብለውታል። የአብርሃም እንግዳ አቀባበል የቅርብና የሩቅ ዘመድና ወዳጅ፡ ድኃና ሀብታም በማማረጥና በመለየት አልነበረም። ኃኅላፊ፡ አግዳሚውን ሁሉ ተቀብሎ ማስተናገድ እንጂ ። አድልዎ ያለበት እንግዳ ተቀባይነት ግን ምን እንደሚመስል ከዚህ የሚከተለውን ተጓዳኝ ታሪክና ምሳሌ እንመልከት ፡ --*

## """""" <u>በድሃ መልክ የተገለጠ ጌታ ወዴት ተሰወረ ?</u> """"""

*_በምሥራቅ ሐረርጌ በሚገኘው በአሰቦት ገዳም የሚኖሩ አንዲት መነኩሲት ጥሩ እንግዳ ተቀባይ ሆነው፡ በተለይ ከአዲስ አበባ የሚመጡ ተሳላሚዎችን ሁሉ በጥሩ ክብካቤ እያበሉ፡ እያጠጡ፡ ሽር ጉድ በማለት ያስተናግዱ ነበር። እነርሱም ሱካርም ሆነ ቡና፡ ወይም ፍራፍሬ ካንዳንድ ዓይነት ልብሶች ጋር ይዘውላቸው ስለሚመጡ ጥሩ ቤተሰብነት መሥርተዋል። ታዲያ አንድ ቀን በነዚያ የአዲስ አበባ እንግዶች መካከል ያለቀ ቡትቶ ጨርቅ የለበሰ አንድ ድሃ አይተው ከእንግዶቻቸው መካከል ይለዩትና መንጥቀው ከቤት አስወጥተው " ምን ዓይነቱ ደፋር ነህ እባክህ ? ይህን ቡትቶ ለብሰህ ሰተት ብለህ ትገባለህን ? በል እዚያ ድንጋይ ካብ ላይ ተቀመጥ" ይሉታል። እርሱም በዚያ ብዙ ሰዓት ቆይቶ እንግዶች ከተጋበዙ በኋላ መነክኩሰዩቱ የተራራፈውን ፍርፋፋት በሣህን አድርገው ወስደው " በል እንካ ይህቺን ጉረስ ብለው' ሊሰጡት እጃቸውን ዘርግትውለት ይቀበለኛል ብለው ሲጠብቁ በዓይናቸው እያዩት ከፊታቸው ተሠውሮ ጠፋባቸው። ቢፈልጉትም ሊያገኙት አልቻሉም። ታዲያ በድሃ እምሳል የተገለጠ ያ ሰው ማን ነበር ? ራሱ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ? ወይስ እርሱ የላከው አንድ መንፈስ ? ወይስ መልአክ ይሆን ? እስካሁን ድረስ ይህን ምሥጢር ለማወቅ የቻለ ማንም ሰው አልተገኘም-" ተርቤ አላበላችሁኝም፡ተጠምቼም ነበር፡ አላጠጣችሁኝም፡ እንግዳም ሆኜ አልተቀበላችሁኝም " የሚል ጌታ ራሱ የእኛን እምነት ለመለካት በዚያ ዓይነት መልክ መገለጥ እንደሚችል የሚጠቁሙ ብዙ ታሪካዊ*



www.ethiopianorthodox.org

ማስረጃዎች አሉ። ስለዚህ በጥሩ አጋጣሚ የመጣልንን መልካም ዕድል በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንዳናጣው መጠንቀቅ ይገባል። እኒያ መነኩሲት ከዚያች ዕለት ጀምሮ በብርቱ አዝነው /ተጸጽተው ማንንም ሰው ከማንም ሳያበላልጡ፡ በድሃና በሀብታም መሐል ልዩነት ላለማድረግ ወስነው ያለ ምንም አድልዎ ሰውን ሁሉ እኩል በማየት፡ እንደ አብርሃም ለማስተገድ ጥረት ሲያደርጉ ኖረዋል። ነገር ግን ያን ያጡትን በረከት እንደገና ማግኘት አልተቻላቸውምና በብርቱ ሲያዝኑና ሲጸጸቱ ነበር የኖሩት ። ሐዋርያ ጳውሎስም "ኢትርሥኡ ተቀብሎ ነግድ እንግዳ መቀበልን አትርሱ። እንግዶችን ከመቀበል ልምድ የተነሣ ሳያውቁ የመላእክትን እንግድነት ለመቀበል የታደሉ ሰዎች አሉ" ሲል የተናገረውም ይህኑ የሚገልጥ ነው (ዕብ. 13. 20 )።

_ሌላውም ሐዋርያ-"ወንድሞቼ ሆይ ! ሃይማኖታችሁ ለታይታ አይሁን። ከመ እመ ቦአ ውስተ ማኅበርክሙ ብእሲ ዘሕልቀተ ወርቅ= የወርቅ ቀለበት ያደረገና ጌጠኛ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ማኅበራችሁ ቢገባ፣ በክብር ቦታ ታስቀምቱታላችሁ፡ ያለቀ ጨርቅ የለበሰውን ድሃ ግን "ቁም ከሐከ አንተሰ አው ንበር ታሕተ መከየድየ= አንተስ ወደዚያ ዘወር በል፡ /በሚማዬ ሥር ተቀመጥ ብትሉት ራሳችሁ ማዳላታችሁ አይደለምን ?" ይለናል - ያዕ. 2. 1 -3 ። ):-""""""""""""""""""""

9--12 ከሦስቱም አንዱ አብርሃምን፣ «የዛሬ ዓመት ልክ እንደ አሁኑ ወደ አንተ-ተመልሼ-እመጣለሁ፡ሚስትህ-ሣራ-ወንድ-ልጅ-ትወልዳለች "አለው››ሣራ "ካረጀሁ-በኋላ፣እንዴት-ልጅ-መውለድ-እችላለሁ?››ስትል-በልቡዋ-ሳቀች። እግዚአብሔርም አብርሃምን፣ «ሚስትህ ሣራ "ካረጀሁ በኋላ እንዴት መውለድ-እችላለሁ?" ስትል ስለ ምን ሳቀች ? በእውነት ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር-አለን?›› አለው። 16--ከዚያም በኋላ እንግዶቹ ተነሥተው ለመሄድ ወደ ሰዶም አቀኑ ፤ አብርሃምም ተከትሎ ሊሸኛቸው ወጣ። እግዚአብሔርም፤ «እኔ የማደርገውን ነገር ከአብርሃም አልሰውርም። አብርሃም በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናል። ጽድቅንና ቅን ፍርድን በማድረግም የእግዚአብሔርን መንገድ (ትእዛዝ) ይጠብቁ ዘንድ ከእርሱ በኋላ የሚነሣውን ቤተ-ሰቡን ሁሉ፣ በማስተማር ማዘዝ እንደሚችል አውቃለሁና›› ሲል ተናገረ።
20 ከዚያም አያይዞ እግዚአብሔር "የሰዶምና የገሞራ-ሕዝቦች ጩኸት በዝቶአል፤ ኃጢአታቸው እጅግ ከብዳለች" አለ። 22--33 አብርሃም ወደ እግዚአብሔር ቀርቦ ስለ ሰዶምና ገሞራ ሕዝብ ማማለድ ሲጀምር-" በእውነት ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን /በከተማይቱ ኀምሳ



ጻድቃን ቢገኙ፣ስለ እነርሱ ብለህ ያችን ከተማ አትምርምን?! የምድር ሁሉ-ፈራጅ የሆንህ አንተ፣ቅን ፍርድ-መስጠት የባሕርይ ገንዘብህ አይደ-ለምን?› አለ። እግዚአብሔርም «በሰዶም ከተማ ውስጥ ኀምሳ ጻድቃን ባገኝ፣ ስለ እነርሱ ስል ሁሉን እምራለሁ›› አለ ።

_አብርሃምም እንደ ገና እንዲህ አለ፤« እነሆ፣'እኔ አፈር-ትቢያ ስሆን፣ እንግዲህ አንድ ጊዜ፣ ከጌታዬ ጋር መነጋገር ጀምሬአለሁና ከኀምሳው ጻድቃን አምስት ቢጐድሉና ዐርባ አምስት ቢገኙስ? ወይም ደግሞ ከዚያ አንሰው ዐርባ፤ ሠላሳ፣ ወይም ኻያና ዐሥር ጻድቃን ቢገኙስ ? ለእነርሱ ስትል-አገሪቱን _አትምርምን? ›› እግዚአብሔርም፣ « ዐሥር ጻድቃንም ቢገኙ-እንኳ-ከተማይቱን-አላጠፋም"-ካለው በኋላ ንግግሩን ፈጸመ፤ እግዝአብሔርም ከዚያ ተነሥቶ ሲሄድ_አብርሃም ወደ ቤቱ ተመለሰ።

## ፲፱ /19. የሰዶምና ግሞራ ሕዝቦች ኃጢአት /ዓመፅ ምን ነበር ?

1--11 ሁለቱ መላእክት በእንግዶች ተመስለው ወደ ሰዶም ምድር መጡ። ሎጥ በዚያ ነበርና ሲያያቸው መሬት ላይ ወድቆ እጅ በመንሣት፣ «ጌቶቼ ሆይ፣ ወደ ቤቴ ገብታችሁ እደሩ›› ብሎ ለመናቸው። ወደ ቤቱ በገቡም ጊዜ፣ ምግብ አቀረበላቸው። ተመግበው ገና ሳይተኙ፣ ( ግብረ ሰዶም ፈጻሚዎች የሆኑ-የከተምዪቱ- ዓመፀኞች- ኑዋሪዎቹ- ከውጣተ-እስከ-ሽማግሌ ተጠራርተው መጥተው የሎጥን ቤት ከበቡ፣ ሎጥንም ጠርተው፣«በዚህ ምሽት በቤትህ ለማደር የገቡትን ሁለት ሰዎች አውጥተህ ስጠን፤ ግብረ ሥጋ ልንፈጽምባቸው እንፈልጋለን›› አሉት። ሎጥም በደጃፉ ላይ ቆሞ፣ በሩን ወደ ኋላው በመዝጋት፣ « እባካችሁ፣ እንግድነት ለማደር -ወደ- ቤቴ- በገቡት-ሰዎች-ላይ-ይህን-ክፉ-ነገር-ለማድረግ-ክፉ-አታስቡ፤ብትፈልጉ- ወንድ ያላወቁ የእኔ ሁለት ሴቶች ልጆች አሉ፤እነርሱን ላውጣላችሁና-የምትፈልጉትን ፈጽሙ" ሲላቸው፡ "ዘወር በል ወዲያ ! ደግሞ በእኛ ላይ ፈራጅ ለመሆን ይፈልጋል? የጠየቅንህን ባትፈጽም ፤ በእነርሱ ላይ ከምንፈጽመው የከፋ ነገር እናደርግብሃለን›› ብለው በሩን ሰብረው ለመግባት ተጋፉት። ሁለቱም እንግዶች ሎጥን ወደ ውስጥ ስበው አስገቡትና በዚያ ቤት ዙሪያ የተሰበሰቡ ዓመፀኞች ሰዎች ሁሉ ዓይናቸው እንዲታወር አደረጉ። እነርሱ በዳበሳ እየተደናበሩ፣በሩን ለማግኘት ሲታገሉ አደሩ።12-14 ሁለቱ እንግዶች ሎጥን እንዲህ አሉት "ሴቶች ልጆችም ሆኑ ወይም የእነርሱን እጮኞች፣ በዚህች ከተማ ያሉህን ሰዎች ሁሉ አውጣ፤ እኛ ይህችን አገር ለማጥፋት ከእግዚአብሔር ዘንድ ተልከን መጥተናል››።



www.ethiopianorthodox.org

ሎጥም ወጥቶ፣ልጆቹን ለማግባት ወደ ተዘጋጁት እጮኛዎች ሄደና « እግዚአብሔር ይህችን ከተማ ሊያጠፋት ስለወሰነ፣ከእኔ ጋር ለመውጣት-ተዘጋጁ» አላቸው፤እነርሱ ግን፣ የሚቀልድ መስሏቸው አፌዙበት። 15-17-_ሁለቱም_መላእክት_ሎጥን"ሚስትህንና ያሉህን ልጆችን ይዘህ_በፍጥነት ክዚህች_አገር ለመውጣት ተዘጋጅ» አሉት። በዘገየም ጊዜ፣እግዚአብሔር አዘነለት፤ መላእክቱ ራሳቸው የርሱንና የሚስቱን፣ የሁለቱንም ሴቶች ልጆቹን እጆች ይዘው አወጡአቸውና፤ ‹ራስህን አድን፤ ወደ ኋላ መለስ ብለህ አትይ፤ በዚያ አካባቢ አትቁም፣ ወደ ተራራ ሸሽተህ አምልጥ» አሉት።፡23-28 ሎጥ- ከከተማይቱ ወጥቶ፣ዞዓር /ሴጎር ተብላ ወደምትጠራው ትንሽ ከተማ ሲደርስ፣በምድር ላይ ፀሐይ ወጣች። እግዚአብሔር በሰዶምና በገሞራ ላይ እሳትና ዲን ከሰማይ አዘነመ።፡ የሎጥ ሚስት ወደ ኋላ ዘወር ብላ ስትመለከት፣ ባለችበት ቦታ የጨው ዓምድ /ሐውልት ሆና ቀረች።፡29 እግዚአብሔር የእነዚያን ከተሞች ሕዝብ በደመሰሰ ጊዜ፣ሎጥን ከእነርሱ ጋር እንዳይጠፋ ያዳነው፣ አብርሃምን በማሰቡ ነበር። ***(<u>ትርጓሜ</u> ፡ ሎጥ ሸሽቶ ከጥፋት የዳነባት ዞዓር (ሴጎር ) የቤተ- ክርስቲያን ምሳሌ ናት፡ ስለዚህ፣ ከጥፋት ለማምለጥ የእግዚአብሔር ሰዎች መሸሻ መጠጊያ የዚህችው ቤተ ክርስቲያን መሥራችዋ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን ፡በምድር ላይ የርሱ ተጠሪ-ምስካየ ኅዙናን ይህች ቤተ-ክርስቲያን ብቻ ናት። ሎጥ ወደዚያች ትንሽ ከተማ ሲደርስ ፀሐይ ወጣች ይላል። ይህም አማኞች በሚደርሱበት ቦታ ሁሉ የእግዚአብሔር ብሩህ ተስፋ፡ ጸጋና በረከትም የሚከተላቸው መሆኑን ያስያል። -የሶዶም ሕዝብ ለቅኝ ተገዢነትና ለጠላት ወረራ የተጋለጡበት ምክንያት በዚሁ መጽሐፍ ምዕ 13፡ 13 እንደተጻፈ"ኃጢአትን ሁሉ አብዝተውና አዘውትረው የሚሠሩ ዓመፀኞችና ጣዖት አምላኪዎችም ሆነው በመገኘታቸው ነብር።እኛም ከዚህ ዓይነቱ ርክሶት ሁሉ ነጻ መሆን ይገባናል።)***

<u>የሎጥ-ዘርዐ-ትውልድ</u>-፡30–38-ሁለቱ-የሎጥ-ሴቶች-ልጆች-እርስ በር ሳቸው ሲነጋገሩ፣ታላቂቱ ታናሽ እኅትዋን እንዲህ አለቻት፣ ‹እንደማን ኛውም የሰው ዘር-ልማድ-አሁን-እኛ ወደአለንበት ቦታ-መጥቶ የሚጠይቀን-ማንም ሰው የለም፤ከዚህ የተነሣ፣አባታችን ያለተተኪ ዘር መቅረቱ ነው። ስለዚህ፣ የወይን ጠጅ እናጠጣውና ሰክሮ ሲሸነፍ ከእርሱ ጋር፡ በመተኛት ልጆችን፡ ወልደን፣ዘር እናትርፍለት»። ሁለቱም በዚሁ ተስማምተው የወይን ጠጅ እያጠጡ አስክረው-ሌሊት በየተራ አብረውት በመተኛት ፀነሱ። ታላቂቱ የወለደችውን ልጅ ሞአብ ብላ ጠራችው፤ እርሱም የሞአባውያን አባት ነው። ሁለተኛዪቱ የወለደችውን አሞን አለችው።እርሱ የአሞናውያን አባት ነው።እርሱ የአሞናውያን አባት ነው።

***(<u>ትርጓሜ</u>፡- ከሚያሰክር-መጠጥ የሚመጣ ድክመት፡ አእምሮን የሚነሣ ራስንም የሚያስረሳ እንደ መሆኑ መጠን፣ ሎጥም አእምሮውን መርሣት ብቻ ሳይሆን ራሱም ጭምር በታሪክ የተረሳ ሆኖ እንዲቀር አድርጎታል። ስለዚህም ካሁን በኋላ በተለይ በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ስለ ሎጥ የምናነበው ብዙ ያሪክ አናይም።)*** ''''''''''''''''''''''''''''''

ኛ /20. አብርሃምና የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክ ፡1-7 አብርሃም-ጌራራ ተብላ ወደምትጠራ ምድር በሄደ ጊዜ፣ ሚስቱን ሣራን እኅቴ ናት ብሎ ነበር። ( *ጌራራ በፍልስጥኤም ውስጥ የምትገኝ አገር ናት (ዘፍጥ 26፥ 1)*። የዚያች አገር ንጉሥ አቤሜሌክ ፣ ሣራን የራሱ ሚስት ማድረግ ፈልጎ ወደ ቤተ-መንግሥቱ አስወስዶአት ነበር ፤ ነገር ግን እግዚአብብሔር በሣራ ምክንያት በአገሪቱ ላይ መቅሠፍት አወረደ ፤ በንጉሡ በአቤሜሌክ ቤተ-መንግሥት በምጥ ጻዕር ተይዘው የነበሩ **ሴቶች**-ሁሉ ልጆችን ወልደው እንዳይገላገሉ-ማሕፀናቸውን ዘጋ።ከዚያ **ወዲያውኑ**፣እግዚአብሔር ሌሊት በሕልም ለአቤሜሌክ ተገለጠለትና ፣ **እንዲህ** ሲል በማስጠንቀቅ ገሠሀው፣«ይህች የወሰድካት ሴት የጐልማሳ ሚስት ናት ፤ እርሱዋን በመውሰድህ ምክንያት፣እነሆ፣አሁን-በሞት አፋፍ ላይ ነህ ፤ይህን ነገር ባለማወቅ በንጹሕ-ልቡ-እንዳደረግኸው-አውቄአለሁ።-ስለዚህ፣ ወደ-እርሱዋ እንዳ-ትቀርብና በፊቱ ኃጢአትን እንዳትሠራ ከለከልኩህ። አሁንም ሴቲቱን ለባልዋ መልሰህ አስረክብ፤ እርሱዋን ባትመልስ ግን፣በእርግጥ እንደምትሞት እወቅ፤ ሕዝብህም ጭምር ያልቃል። ሚስቱን ብትመልስለት ግን፣ አብርሃም ይጸልይልሃል፤ እርሱ ነቢይ ነውና»። 8-18 አቤሜሌክ ደንግጦ ብዙ ሀብትና የከብት መንጋ ለአብርሀም ሰጠው። ሚስቱን ሣራንም መልሶ ከአንድ ሺህ ጥሬ ብር ካሣ ጋር አስረከበው፤ አብርሃምም ጸለዮለት፤ ንጉሣዊ ቤተሰቡም ሁሉ ተፈወሰ፤ በምጥ ጣር ተይዘው የነበሩትም ሴቶች ሁሉ፣ ልጆችን ወልደው ከጭንቀት ተገላገሉ።

ኛ፩ /21 ፡ <u>ይስሐቅ ተወለደ</u> ፡1 8 -እግዚአብሔር-አምላክ በሰጠው-የተስፋ ቃል መሠረት፣ ሣራን በረድኤት አሰባት /ጐበኛት ። እነሆ፣ በስተርጅና ዘመንዋ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ስሙም ይስሐቅ ተብሎ ተጠራ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሣራም ‹‹እግዚአብሔር ሳቅ አድርጎኛልና ይህን የሚሰማ ሁሉ በእኔ ምክንያት ይስቃል›› አለች፡፡ በዚያን ጊዜም የአብርሃም ዕድሜ አንድ መቶ ዓመት ነበር፡፡ ሕፃኑ በተወለደ በ8ኛው ቀኑ ተገዘረ፡ ይስሐቅ ጡት መጥባት በተወበትም ቀን፣ አብርሃም ታላቅ የምሳ ግብዣ አደረገ ፡፡

## ሁለቱም ልጆች--እስማኤልና ይስሐቅ) አብረው ሲጫወቱ

-ታዲያ እስማኤል በይስሐቅ ላይ ሲያፌያፌዝበት አይታ፣ ሣራ በቍጣ ተሞልታ፣‹‹ይህችን አገልጋይ ከነልጁዋ ወደዚያ አባርልኝ፤የአገልጋይ ልጅ ከእኔ ልጅ ጋር ወራሽ መሆን አይገባውም›› ስትል በአብርሃም ላይ ጮኸችበት : : አብርሃም በዚህ ነገር ተጨንቆ ሳለ፣ እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡፡ 9-13 "ስለ አገልጋይቱና ከእርሱዋም ስለተወለደው ልጅህ እስማኤልም ማዘንና መጨነቅ አይገባህም፡፡ ሣራ የምትልህን ስማ፡፡ ዘር-የሚወጣልህ በይስሐቅ በኩል ነውና ፡፡ ከአገልጋይህ ከአጋር የተወለደውንም ቢሆን፤ የአንተ ልጅ ስለ ሆነ፣ ታላቅ ሕዝብ እስኪሆን ድረስ እኔ እባርከዋለሁ"፡፡

<u>የአጋርና የእስማኤል ስደት</u>፡ 14-21 ከዚያ በኋላ፣ አብርሃም የዕለት ምግብና ውኃ በአቍማዳ አስይዞ አጋርንና እስማኤልን አሰናበተ፡፡ አጋርም ከዚያ ወጥታ በቤርሳቤሕ በረሃ ስትንከራተት፣ የያዘችው ውኃ አለቀባት፡ ‹‹በውኃ ጥም የተንገበገበ ልጄን "ሲሞት አላይም›› ብላ፣በቍጥቋጦ ሥር አስቀመጠችውና በርቀት ሆና መጨረሻውን ትጠባበቅ ጀመር፡፡ ሕፃኑ ምርር ብሎ- ሲያለቅስ፤ እግዚአብሔር ጩኸቱን ሰማ፡፡ ወዲያውኑም የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ አጋርን በስምዋ ጠርቶ፣ ‹‹አይዞሽ አትጨነቂ ፤ እግዚአብሔር የልጅሽን ጩኸት ሰምቶአል፡፡ ሄደሽ ልጅሽን አንሺው" ብሎ አጽናናት፡፡ ዓይንዋን በከፈተላትም ጊዜ፣ አንድ የውኃ ምንጭ (ጉድጓድ) አየች፡፡ ውሃውንም ቀድታ በአቍማዳ ሞላችና ለልጁዋ አጠጣችው ፡፡ እነሆ፣ በዚህ አይነት ሁኔታ እግዚአብሔር ልጁዋን እስማኤልን ስለ ባረከላት፣ አድጎ በቀስት ውርወራ የሠለጠነ አዳኝ (ጦረኛ) ሆነ አጋርም ከአንዲት ግብጻዊት ልጃገረድ ጋር ጋብቻ-እንዲፈጽም አደረገች፡፡ *(<u>ትርጓሜ</u>፡ቍ 17 ሕፃኑ ምርር ብሎ ሲያለቅስ እግዚአብሔር ሰማው። እናቱ አጋርም እንደዚሁ ምርር ብላ ታለቅስ ነበር፤ ነገር ግን ከእርስዋ ይልቅ፣ የሕፃኑ ለቅሶ በእግዚአብሔር ዘንድ ፈጥኖ ስለ ተሰማ ፣ የሚራዳው- መልአክ- ከእግዚአብብሔር-ታዝዞ-እንዲመጣ- አስደርጓል።-የልጆች ጩኸታቸው ይህን ያህል ተሰሚነትን ካስገኘ፡ በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ማመልከትን ቢለማመዱማ ኖሮ እግዚአብሔር ለነርሱ ምን ያህል ቅርብ እንደሆነ በግልጥ እናያለን።*



*ማገናዘቢያ የሚሆኑ በሁለት አጫጭር ያሪክና ምሳሌዎች እነሆ !*

## *ሀ · <u>አንድ የእግዚአብሔር ሰው</u> <u>በጸሎት ተመስጦ ላይ</u>*

*_ጌታችን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በእንግዳ ሰው አምሳል ተገልጦ ሊያነጋግራቸው ሲመጣ አይተውት "አሁን ጸሎት ላይ ስለሆንሁ ላነጋግርህ አልችልምና ዘግየት ብለህ ብትመለስ ይሻላል" አሉት። እርሱም ወደ ኋላ ተመልሶ ሄደና ዘግየት ብሎ ሲመጣ ራሱ መድኀኔ ዓለም ክርስቶስ መሆኑን ገልጦ -"እስካሁን በትጋት የቆየህበት ፃማ ገድል ይበቃል፡ ካሁን በኋላ በሞት በኩል አልፈህ ወደ እኔ እንድትመጣ ፈቅጀልሃለሁ" አላቸው። እርሳቸውም ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ሰገዱለትና ስለተሰጣቸው የመዳን ተስፋ አመስግነው "ግን አንዲት ጥያቄ ለማቅረብ ፍቀድልኝ። ይኸውም ሳላስቀይምህ በየዋህነት ወደ አንተ መምጣት እንድችል፡ ልጅነቴን መልስልኝ" አሉት። ጌታም ለአንዲት ቀን ብቻ ልጅነታቸውን መልሶላቸው ወደ ማታ ገደማ ከዚህ ዓለም በሞት ተለተው ወደ መካነ ሕይወት ተወሰዱ"።*

***ለ**. """"የ<u>ሕፃናት ነጻነት በአባታቸው እቅፍ ውስጥ</u> """" ያለምንም ፍርሐትና ያለምንም ሥጋት፡ ያለምንም ጥርጥር ተዝናንተው ጣፋጭ እንቅልፍ ይወስዳቸዋል። እኛስ በሰማያዊ አባታችን እግዚአብሔር ላይ ይህን ያህል መተማመን ቢኖረን እንዴት መልካም በሆነ ነበር ! ይህን አባባል አጉልተው ለማሳየት አንድ ሰባኬ ወንጌል ያቀረቡት ተንዳኝ ታሪክና ምሳሌ እንዲህ ይላል፡ አንድ የሀገር ባህላዊ መድኃኒት ቀማሚ ዶክተር አንዲት ዕፅ / በገደል መካከል እንደምትገኝ አውቆ ስለነበር ወደዚያ ቦታ አንድ ሕፃን ልጅ በገመድ አስሮ ለመላክ ፈለገ።*

*_ዶክተሩም ገመዱን ይዞለት አንድ ሕፃን ልጁ ለመውረድ ፈቃደኛ ሆኖ ነበር። " ነገር ግን ሕፃኑ ዶክተሩን ተጠራጥሮት " ገመዱን አንተ ሳትሆን አባቴ እንዲይዘው እፈልጋለሁ። ምክንያቱም አንተ ሰልችተህ ገመዱን ብትለቀው የሞት አደጋ ሊደርስብኝ ይችላል ። አባቴ ግን እስከ መጨረሻው ምንም ሳይሰለች ገመዱን አጥብቆ በመያዝ በፍጹም ጥንቃቄ እንደሚጠብቀኝ ከልብ እተማመንበታለሁ" አለ። "ግድፍ ላዕለ እግዚአብሔር ሕሊናከ ወውእቱ ይሴስየከ=አሳብህን በእግዚአብሔር ላይ አሳርፍ፡ እርሱም ይመግብሃል" (መዝ. 54. 22 ) ተብሎ እንደተጻፈ ሰማያዊ አባታችን እግዚአብሔርም ፍጹም መታመኛችን ነው። ( ሕጻን ኪሩብ ካሣሁን ጥምቀተ ክርስትና በተነሣበት ዕለት በቨርጅንያ ኪ /ምሕረት ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው የነዚህ ሁለት ታሪምክና ምስሌዎች ተናጋሪ መልአከ ምሕረት*



www.ethiopianorthodox.org

ሕይወት ዘውዴ አሁን በአሜሪካ ኗሪ ናቸው) ።እግዚአብሔር የአጋርን ዓይነ ልቡና ከመከፈቱ በፊት ባጠግብዋ የነበረውን የውኃ ጉድጓድ ማየት እንዳልቻለች ሁሉ፡ የእኛንም ዓይነ ልቡና የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ ካልከፈተው በቀር በእጃችን ያለውን የመጽሐፍ-ቅዱስ ቃል-እያነበብነው እንኳ ማስተዋል አንችልም ማለት ነው። አንድ ሰው ብቻውን፣ በማያውቀው ቦታ ከርታታ ሆኖ ግራ-ገብቶት ሳለ፣ አንድ ሌላ ሰው ስሙን እከሌ ብሎ ጠርቶ አይዞህ! ! ችግርህስ ምንድን ነው?››ብሎ ሲያጽናናው-ደስ እንደሚለው-ግልጥ ነው፡-የእግዚአብሔር መልአክ፣ አጋርን በስሟ-ጠርቶ ሲያጽናናት - እንዴት- እንደተደሰተች- መገንዘብ -አያዳግትም ። እንደሁ በችግራችን ጊዜ ፈጥኖ የሚደርስ ፡-መልአኩን ልኮ የሚያጽናና የክብር ባለቤት የሆነ ይአምላካችን ቅዱስ ስም ለዝለዓለም ይመስገን።

## የንጉሥ አቤሜሌክ ቃል ኪዳን ከአብርሃም ጋር

1--8፡ በዚያ ጊዜ፣ የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክ የሠራዊቱን አለቃ ፊኮልን አስከትሎ ወደ-አብርሃም-መጥቶ፣እንዲህ አለው፤‹‹ በምታደርገው ነገር ሁሉ፣እግዚአብሔር-ከአንተ-ጋር-በረድኤት-መኖሩን -በግልጥ- እናያለን ። ስለዚህ፣ እኔንም ሆነ ዝርያዎቼን- ሁሉ የሚያሳዝን በደል እንደማትፈጽም በእግዚአብሔር ስም ቃል -ግባልኝ ። በእንግድነት ለምትኖርባት ለዚህች- ምድር ታማኝነትህን እንደምታሳይ በመሐላ አረጋግጥልኝ""። አብርሃምም፡ ከአቤሜሌክ፡ ጋር በቤርሳቤሕ -ቃል- ኪዳን አደረገ። እነርሱን ሸኝቶ ካሰናበተም በኋላ፣ ይህን ያህል የመከበርን ጸጋና ግርማ-ሞገስ ለሰጠው- አምላክ ሰግዶ ምስጋና አቀረበ። (**ትርጓሜ፡** *አብርሃም እምነቱን የሚገልጥበት የትምህርት መድረክ አልነበረ ውም ። እምነቱ ጉልቶ የሚታየው ለእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ታዛዥ በመሆንና በመልካም ሥራው ብቻ ነበር። የምናኔ ሕይወትም አልነበረውም። በትዳር ላይ እያለ እንደማንኛውም የአዳም ዘር ፈሪሀ እግዚአብሔር በሌለው ማኅበረሰብ መሐል መልካም ሥነ ምግባሩ እንደ አጥቢያ ኮከብ እያበራ (ፊልጵ 2፡ 15 16) ያስገኘለት ጸጋና በረከት ያባቶች አባት፡ የእግዚአብሔር ልዑል መስፍን ለመባል አብቅቶታል ዘፍጥ 23፡1-8 ። ከርሱ በፊትም ሆነ በኋላ የተነሡ ቅዱሳን ጻድቃንና ሰማዕታትም ሁሉ ከርሱ ማዕርግ አልደረሱም። ይህ እንግዲህ በፍጹም የማይመረመር የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታ ነው" ከማለት በቀር ሌላ መደምደሚያ አናገኝለትም ። ይህን ጸጋ ለአብርሃም የሰጠ ሕያው አምላክ እኛንም እንደርሱ በረድኤቱ ያስበን ):''''''''''''''''''''''''''''''''''''''*



## ፳፪ /22፡ አብርሃም የሃይማኖቱን ጥንካሬ ያሳየበት የመጨረሻ ፈተና

1- 8 ከዚህ ሁሉ በኋላ ፣ እግዚአብሔር አብርሃምን፣ ‹‹የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን መሥዕት አድርገህ አቅርብልኝ›› ብሎ አዘዘው። አብርሃምም ለእግዚአብሔር ቃል ፍጹም ታዛዥ በመሆኑ፣ልጁን ይሠዋለት ዘንድ እግዚአብሔር ወዳሳየው ወደ ሞሪያ ተራራ ሲሄድ፣ መሥዋዕቱ የሚቃጠልበትን እንጨት አስሮ ለይስሐቅ አሸከመው። ይስሐቅም"እነሆ፣እንጨትና-እሳት-ይዘናል፣ለመሥዋዕት የሚሆነው በግ የታል?›› ሲል አባቱን አብርሃምን ጠየቀው። አብርሃም‹‹ልጄ ሆይ፣ ለመሥዋዕት ሚሆነውን በግ እግዚአብሔር ያዘጋጃል›› አለው።9-14 አብርሃም እግዚአብሔር ወደ \አመላከተው ተራራ ወደ ሞሪያ ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው-አገልጋዮ-ቹን‹‹ እኔና ልጄ-ሰግደን እስክንመለስ፡ እናንተ ከአህያው ጋር-እዚህ ቆዩ›› አላቸው።

_አብርሃም -መሠዊያ አዘጋጅቶ፣ ይስሐቅን-አሰረው--በመሠዊያ ላይ አጋደመ ውና እጁን ዘርግቶ በቍርጥ ውሳኔ-ሊሠዋው ሲዘጋጅ፣ የእግዚአሔር-መልአክ--ከሰማይ-ጠርቶ እንዲህ-አለው፤‹ ‹በብላቴናው -ላይ ምንም-ክፉ-ነገር-አታድርግበት፤እነሆ፡-የቱን-ያህል-እግዚአብሔርን-እንደምትወ ድና እንደምታከብር- አይቻለሁ፤ አንድ ልጅህን- እንኳ፡ለርሱ- እንዳልነ-ፈግህ-- ተመልክቻለሁ››። አብርሃም -መለስ ብሎ ዙሪያውን- ሲመለከት፣ እነሆ፣ አንድ የበግ ጠቦት ቀንዶቹ በዛፍ ሐረግ ተይዘው አየ፡ ያንም በግ-ወስዶ- በይስሐቅ ፈንታ-ሠዋው። 15-19 እንደገናም የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ጠርቶ አብርሃምን እንዲህ አለው፤ ‹‹ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፣ ‹እነሆ፣በራሴ ማልሁ ፣ለምትወደው ለአንድ ልጅህ እንኳ ሳትሳሳ ፤ ይህን ያህል ታዛዥነትን አሳይተሃልና፤ እኔ- ደግም- አብዝቼ እባርክሃለሁ። የዓለም-ሕዝቦች-ሁሉ-በዘርህ--ይባርካሉ። ዘርህን -እንደ ባሕር ኣሸዋ አበዛዋለሁ፡ ዝርያዎችህ ሁሉ የጠላታቸውን ምድር ይወርሳሉ"።

(**ትርጓሜው፡** *ይህ_ሁሉ-ምሳሌ-ነው፡ አብርሃም የእግዚአብሔር አብ ምሳሌ ፡ ይስሐቅ የእግዚአብሔር ወልድ ምሳሌ ነው ። አብርሃም ሚወደው ለአንድ ልጁ ለይስሐቅ ሳይሳሳ ለመሠዋት ፈቃደኛ ሆኖ እንደ ተገኘ፡ እግዚአብሔር አብም ተቀዳሚ-ተከታይ ለሌለው ለአንድ ልጁ ሳይሳሳ፡ እስከ ቀራንዮ መስቀል ሞት ተላልፎ እንዲሰጥ ፈቅዷል። በሌላም በኩል፣ በዕፀ-ሳቤቅ ሐረግ ተይዞ የተገኘው ነጭ በግ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ያ በግ ለይስሐቅ ምትክ ሆኖ እንደተሠዋ ክርስቶስም*



www.ethiopianorthodox.org

*ለዓለም ቤዛ ሆኖ ተሠውቷልና። ይስሐቅ ተሸክሞት የተጓዘው፣ መሥውዕት የሚቃጠልበት እንጨትና እንዲሁም ለይስሐቅ ምትክ የሆነው በግ ታስሮ የተገኘበት የዛፍ ሐረግ (ዕፀ ሳቤቅ፡ ኃጢአት የሚሰረይበት የዕፀ መስቀል ምሳሌ ነው። "ዕፀ ሳቤቅ ብሂል ዕፀ ስርየት መስቀል" እንዳለ ቅ.ያሬድ በዜማ ድርሰቱ ። )*

- ***<u>በእግዚአብሔር ቃል አሽሙር መናገር ተገቢ አይደለም</u>***

*_ለምሳሌ በእንግሊዝ አገር አንዲት ቤተ ክርስቲያን ተቋቁማ፡ በሁለት ካህናት ትገለገል ነበር ። ምእመናን እየበዙ ሲመጡ ሌላ አንድ ቅርንጫፍ ቤተ ክርስቲያን ያቋቁሙና ከሁለቱ ቀሳውስት አንዱ አዲስ ወደተ-መሠረተችው ቤተ ልርስቲያን እንዲዛወር ሲያደርጉ፡ ለመጨረሻ ጊዜ የአንድ እሑድ የመሰናበቻ ስብከት አሰምቶ እንዲሄድ ተፈቀደለት ። ታዲያ ያ ካህን በመዛወሩ ደስተኛ ካለመሆኑ የተንግ ያደረበትን ቅርታ ለመግለጥ የመረጠው ርእስ በዚሁ ምዕራፍ 22 ቍጥር 5 <u>"አብርሃም አገልጋዮቹን 'እኔና ልጄ ሰግደን እስክንመለስ ድርረ እናንተ ከሀያው ጋር እዚህ ቆዩ' አላቸው"</u> የሚል ነበር ። ይህን አሽሙር ከመናገር ይልቅ ለመዛወር ፈቃደኛ አይደለሁም " ብሎ በሥነ ሥሮዓት መጠየቅ ይገባው እንደነበር ተገልጦለት በማኅበረ ምእመናኑ ተገሥፀበታል ትብኋል ።* ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

*_በዘመናችንም-አንዳንድ-ሊቃውንት-ይሁኑ-የመሰለ-ምሕረት-የለሽ-ያሽሙር ቃል ለመናገር ድፍረቱ አላቸው፡ ግን ተገቢ አይደለም። በብርቱ ሊገሠፁበት ይግባል። የእግዚአብሔር መንግሥት በሚታወጅበት መድረክ ላይ ይህን ዓይነት_አሽሙር-መነገር-የምእመናንን-/የአማኖችን-ልብ-የሚያሳዝንና የእግዚአብሔርንም ቍጣ የሚጋብዝ ነው ። በቃሉ የማይስት ብፁዕ ነው ( ያዕ 3፡ 1-2) ። )* """"""""""""""""""""""""""""""""""""

**፳፫ /23. <u>የሣራ ዕረፍት</u>** ፡1-8 ሣራም አንድ መቶ ኻያ ሰባት ዓመት ከኖረች በኋላ ሞተች፤ አብርሃምም ወደ እርሱዋ ድንኳን ገብቶ አለቀሰላት፡፡ ወዲያውኑ-ከአስከሬኑ አጠገብ ተነሥቶ በመቆም፣ በኬብሮን የሀገር ባላባቶች ከነበሩት ከኬጢያውያን መካከል ፣ በተለይ የዔፍሮን ርስት የሆነችው የማክቤላ ዋሻና በዙሪያዋ ያለው እርሻ፣ የመቃብር ቦታ ይሆንለት ዘንድ መርጦ፣ በዋጋ እንዲሸጥለት ጠየቀ፡፡ እነርሱም ‹‹አንተ እኮ በእኛ-መካከል እንደ አንድ ታላቅ ልዑል መስፍን የምትታይ ነህ፤ ስለዚህ ፣የሚስትህን አስከሬን በምትመርጠው ቦታ ለመቀበር ማንም የሚከለክልህ የለም›› አሉት፡፡ ኤፍሮንም በበኩሉ፣ ‹‹ጌታዬ ሆይ፣ ስማኝ፤ይህን እርሻና በውስጡ ያለውን ዋሻ በወገኖቼ ፊት፣እነርሱን ምስክር አድርጌ ሰጥቸሃለሁ፤አስከሬንህን ቅበር፤ ከዐራት-መቶ ሰቅል ጥሬ ብር በላይ ዋጋ የማያወጣ ምድር በአንተና በእኔ መካከል ምን ቁም ነገር አለው?!›› ሲል መለሰለት፡፡ አብርሃም ግን፣ ቦታው በርስትነት እንዲጸናለት ስለ ፈለገ፣ ዐራት መቶውን ሰቅል ጥሬ ብር መዝኖ ሰጠው፣ ብሩም ለመሸጫና ለመለ-ጫ መተላለፍ የሚችል ገንዘብ ነበር፡፡ 9 ከዚህ በኋላ አብርሃም የሚስቱን ሣራን አስከሬን፣ኬብሮን ውስጥ-በመምሬ ፊት-ለፊአ-በሚገኘው ባለ ድርብ ክፍል በሆነው ዋሻ ውስጥ ቀበረ፡፡ ያም እርሻና በውስጡ ያለው ዋሻ በኬጢ ልጆች ፊት ለአብርሃም የመቃብር ቦታ በዐዕመ ርስትነት ፀናለት፡፡

*(**<u>ትርጓሜ፡</u>** ሣራን ያህል የኑሮ ጓደኛ ማጣት ለአብርሃም ከባድ ሐዘን መሆኑ ግልጽ ነው። አስከሬንዋ ወዳለበት ድንኳን ግብቶ በማልቅስ እርሙን ካወጣ በኋላ ውዲያውኑ ተንሥቶ ስለ መቃብር ቦታ የዝያች ሀገር ባላባቶች · ከነበሩት ከኬጢ ዘሮች ጋር መከራከር ጀመረ። መከራከሩም የመቃብር ዐፅመ ርስትን አስገኘለት።እንደ እኛ አገር ባህል ተቀምጦ ወይም "ያዙኝ፡ ልቀቁኝ" በምለት ሲያለቅስ ቢውል ኖሮ ያን የመቃብር ዐፅመ ርስት ማግኘት ባልቻለም ነበር።*

*_በመሠረቱ አብርሃምና ሣራ በተስፋ ትንሣኤ ሙታን ያምኑ እንደነበር ሐዋርያው ሲጽፍ "በሰማያት ያለችውንና የምትበልጠውን ሀገር ተስፋ ያደርጉ እንደነበር ታወቋል" ይላል (ዕብ 11፡ 16)። ይህም ዓይነቱ ተስፋ ትንሣኤ ያለው ክርስቲያን በሞት አደጋ ጊዜ እምነት የጎደላቸው ሰዎች- በሚፈጽ ሙት- ዓይነት ተስፋ- አስቈራጭ-ለሆነ ሐዘንና- ለለቅሶ ዋይታ የተጋለጠ ተስፋቢስ ሆኖ ዋይ ፡ወይው" ሲል አይኖርም። በፍትሐ ነገሥቱ መመሪያ ሕግ ነፍስ ከሥጋ ስትለይ፡ አስከሬን ከቤት ሲወጣና ግባአተ መሬት ሲፈጽም በመጠኑ ብቻ ማልቀስ ተፈቅዷል ።)*

፳፬ /24. <u>የይስሐቅና የርብቃ ጋብቻ</u> : 1-8 አብርሃም የቤት-ንብረቱ ሁሉ አዛዥ የሆነውን መጋቢውን ኤሊዔዘርን ( ዘፍጥ 15፡2 ) ጠርቶ፣ እንዲህ ሲል አዘዘው፣‹‹እጅህን በጉልበቴ ላይ ጭነህ ማልልኝ፡፡ ለልጄ ለይስሐቅ በዚህች አገር ከሚኖሩ ከከነዓን ሴቶች ልጆች መካከል ሚስት እንዳትመርጥለት አደራ፤የሰማይና የምድር ሁሉ ፈጣሪ በሆነ በእግዚአብሔር ስም አምልሃለሁ፤ ወደ ትውልድ አገሬ ወደ ሶርያ ሄደህ፣ በዚያ ከሚኖሩ ተወላጆቼ መካከል ሚስት ምረጥለት፤ነገር ግን፣በምንም ዓይነት ሁኔታ ልጄን ወደ ቀድሞ ትውልድ አገሬ መልሰህ እንዳትወስደው ተጠንቀቅ፡፡ ከአባቴ ቤትና ከትውልድ አገሬ አውጥቶ ወደዚህች ምድር





www.ethiopianorthodox.org

ያመጣኝ የሰማይ አምላክ የሆነ እግዚአብሔር፣ራሱ መልአኩን በፊትህ ይልካል፣መንገድህንም ያቃናልሃል። ለልጄ ለይስሐቅ የምትሆን-ሚስት-ለማግኘት-እርሱ-ይረዳሃል››።።9-10- አገልጋዩ-የሆነ-መጋቢውም፡ለጌታው ለአብርሃም ማለስትና ከጌታው ቤት ምርጥ ምርጡን የማጫ -ስጦታ ዕቃ-በዐሥር ግመሎች ጭኖ-በሰሜን-ሜሶጰታሚያ (በሁለት ወንዞች መካከል) የአብርሃም ወንድም ናኮር ወደሚኖርባት ከተማ ለመሄድ ጉዞውን ጀመረ።

አስደናቂ ተአምር የተፈጸመበት ጸሎት አቀራረብ

11-14 የአብርሃም አገልጋይ እዚያ አገር የደረሰበት ሰዓት ሴቶች ውኃ ለመቅዳት የሚወጡበት ጊዜ ስለነበር በጉልበቱ ተንበርክኮ ሲጸልይ እንዲህ አለ፡"የጌታዬ የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር ሆይ! እነሆ አሁን የከተማይቱ ሴቶች ልጆች ውኃ ለመቅዳት የሚመጡበት ሰዓት ነው፡ ወደዚህ ቦታ ውኃ ለመቅዳት ከሚመጡት ልጃገረዶች መካከል አንዲቱን ቈንጆ መርጬ ‹እባክሽ ፣ እንስራሽን ዘንበል አድርገሽ ውኃ አጠጪኝ› ስላት፣ ‹እሺ ጠጣ፣ ግማሎችህንም አጠጣልሃለሁ' የምትለኝ፣ እርስዋ ለአገልጋይህ ለይስሐቅ ሚስት እንድትሆን፣ አንተ ራስህ የመረጥህለት መሆንዋን አውቃለሁ፤ በዚህም ዓይነት ሁኔታ ሁሉ ፣ ለጌታዬ ለአብርሃም ያለህን ዘላለማዊ ፍቅር አውቃለሁ››። 15--21 እርሱ ገና ይህን ሁሉ-ተናግሮ ሳይጨርስ፣ የአብርሃም-ወንድም-የናኮር-ልጅ-ባቱኤል-የወለዳት ልጁ ርብቃ፣ ውሃ የምትቀዳበትን እንስራ በጫንቃዋ ተሸክማ በድንገት መጣች።መልክዋ የተዋበ ቈንጆ ነበረች። ውኃ እንድታጠጣው-ሲጠይቃት እንስራዋን ዘንበል አድርጋ ካጠጣችው በኋላ፣ግመሎቹንም አጠጣችለት። ሰውዮውም እግዚአብሔር ተልእኮውን ፈጽሞለት እንደ ሆነ ለማረጋገጥ፣ በመደነቅ ዝም ብሎ ይመለከታት ነበር። ወዲያውኑም፣ ‹‹የማን ልጅ ነሽ?›› ብሎ ሲጠይቃት "ሚልካ ለናኮር-የወለደችለት የባቱኤል ልጅ ነኝ›› አለችው፡26-27 በቀጥታ ተልእኮውን እንዳቃናለት አውቆ ለእግዚአብሔር ሰገደ። እንዲህም አለ ‹‹ቸርነቱንና እውነተኛነቱን ከጌታዬ ከአብርሃም-ያላራቀ፣ የአብርሃም-አምላክ፣እግዚአብሔር ይመስገን፣ጉዞዬን-በማቃናት-ወደ-ጌታዬ-ወንድሞች ቤት መርቶኛልና››። ወዲያው የወርቅ ቀለበትና ጥንድ የእጅ አምባር አሰረላት። _በእንግድነት ለማደር ወደ አባትዋ ወደ ባቱኤል ቤት ሲያመራ፣ ላባ የተባለው የርብቃ ወንድም እየሮጠ መጣ፤ ለርብቃ የተሰጣትን ቀለበትና የወርቅ አምባሮች ባየ ጊዜ፣‹‹አንተ ቡሩክ የእግዚአብሔር ሰው ፣ ለምንስ በውጭ ትቆማለህ? ና ግባ። እነሆ፣እኔ የምታድርበት_ቤትና_ለግመሎችህም_ማደሪያና_የሚመገቡትን_ገፈራ አዘጋጅቻ



ለሁ›› 32-49 ወደ ቤትም በገባ ጊዜ፣በጥሩ ሁኔታ-ተቀብለውት፤እህል፡ ውኃ እንዲቀምስ ጠየቁት፣ እርሱ ግን፣ ‹‹የተላክሁበትን ጉዳይ ሳልፈጽም-መብላት አይገባኝም› አላቸው። ከዚያ በኋላ፣ በውኃው-ጉድጓድ አጠገብ ተንበርኮ በጸለየ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የፈጸመለትን እጹብ-ድንቅ ሥራና ያሳየውን የተልእኮውን መቃናት ምልክት ሁሉ በግልጥ በመተረክ አስረዳቸው።

_እንዲሁም፣እግዚአብሔር-ኣአምላክ ጌታውን- አብርሃምን- እንዴት-እንዳከበረውና እንዳበለጸገው፡ በሽምግልና ዘመኑ ለወለደው ለልጁ ለይስሐቅ ሚስት ለማጨት እንዴት ተልኮ እንደመጣ ተናገረ።ርብቃን-እግዚአብሔር ለይስሐቅ ሚስት ትሆንለት ዘንድ የመረጠበትን ምልክት ሁሉ ገለጠላቸው።-አባትዋም-ባቱኤልና-ወንድምዋ-ላባ-በመገረምና በመደነቅ እንዲህ አሉት፣‹‹እንግዲህ፣ይህ- ጉዳይ ከእግዚአብሔር ፈቃድ-የመጣ ስለሆነ፣ እኛ-መከልከል አንችልም›› እነሆ፣ ርብቃ በፊትህ ናት፣ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለጌታህ ልጅ ለይስሐቅ ሚስት ትሆን ዘንድ እንድትወስዳት ተስማምተናል››።ይህን ሲሰማ አሁንም መጋቢው የአብርሃም ሎሌ፣ለእግዚአብሔር ሰገደ።

ተፈላጊውን የማጫ ስጦታ ሁሉ አቀረበ፤ ለቤተ-ሰብዋም ህሉ ልዩ ፡ልዩ ስጦታ አበረከተ 57-58 በመጨረሻም፣ፈቃደኛነትዋን ለማወቅ ርብቃን ጠርተው፣"እንግዲህ ከዚህ ሰው ጋር-አብረሽ-ለመሄድ-ትፈቅጃለሽን?›› ብለው-ሲጠይቋት፡‹‹አዎ፣ እሄዳለሁ›› አለቻቸው። ከዚያ በኋላ‹‹" እኅታችን ርብቃ-ሆይ! የብዙ እልፍ-አእላፍ ሕዝብ እናት ለመሆን ያብቃሽ፡ ዘሮችሽ ሁሉ የጠላታቸውን ርስት የሚወርሱ ይሁኑ"ብለው-መረቋት። ከምርቃቱ ቀጥሎ፣ ዲቦራ የተባለች ሞግዚትዋን በደንገጡርነት አብራት እንድትሄድ አድርገው በመሸኘት ተሰናበትዋት። 65-66 የመልስ ጉዞ ተፈጽሞ ከነዓን እንደ ደረሱ፣ይስሐቅ ወደ መስክ ወጥቶ፣ ስለ አንዳንድ ሁኔታዎች በልቡ እያሰላሰለ ሲራመድ፣ በርቀት አዩት፤ ርብቃም ‹‹ወደ እኛ የሚመጣ ያ ሰው ማን ነው?›› ስትል አገልጋዩን ጠየቀችው። እርሱም ይስሐቅ መሆኑን ሲነግራት፤ ከግመሏ ላይ ወርዳ፣ ፊትዋን በሻሽ ሸፈነች፤ ወደ ይስሐቅም-ሲቀርቡ፣-አገልጋዩ-በእግዚአብሔር ርዳኤት የተፈጸመውን-አስደናቂ-ተልእኮ -ሁሉ፣ ለይስሐቅ ተረከለት። ይስሐቅም ርብቃን በሚስትነት ተቀብሎ /ተረክቦ ወደ እናቱ ወደ ሣራ ድንኳን ይዞአት ገባ፡ ወደዳትም፤ በሣራ ሞት ከደረሰበት ኀዘን ሁሉ በዚሁ ተፅናና።



www.ethiopianorthodox.org

**ኟ፰ /25. <u>ሌሎች የአብርሃም ልጆች</u>** ፡1-6 አብርሃም ኬጡራ ተብላ ከምትጠራ ቁባቱ ሌሎች ስድስት ወንዶች ልጆችን ወለደ። እነርሱንም ለጊዜያዊ ችግር መቋቋሚያ ስጦታ አስይዞ፣ ራቅ ብለው በምሥራቅ አገር እንዲኖሩ አሰናበታቸው። የነበረውንም ሀብት-ንብረት በሙሉ ለይስሐቅ አወረሰው። (**<u>ትርጓሜ፡</u>** *ከእነዚያ ስድስት ልጆች አንዱ ምድያም ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ አብዛኞቹ የምድያም አገር ሕዝብ፣ የእርሱ ልጆች ዝርያዎች መሆናቸውን በዜና መ. ቀ ምዕ 1፥ 32-33 የተጻፈው ታሪካዊ ቃል ያስረዳል። ይህችም የምድያም ምድር የኢትዮጵያ ግዛት የሆነችበት አንድ- ወቅት እንደ ነበረ፣ ኢትዮጵያዊት ወይም የኩሽ ዘር ተብላ በተጠራችው በሙሴ ሚስት ታሪክ ይታወቃል ( ዘኍል 12፡ 10 ። ከዓለም አቀፍ የታሪክ ማኅደርም ለማስረጃ ያህል ብንጠቅስ "ዱሪሲላ ዱንጂ የተባለች ደራሲት የጻፈችውን ታሪክ በመተርጎም "ፒራሚድ ገንቢዎቹ ጥንታውያን ኢትዮጵያውያን" በሚል ርእስ "አቶ ጌታቸው ተስፋዬ-ጎጂ-በ2002-ዓ /ም ያሳተመው መጽሐፍ የጥንት ኢትዮጵያውያውያን በውስጡ ብዙ አህጉራትን ያካተተ መደበለ መንግሥት (Empire) መሥርተው በምሥራቅ አፍሪቃ እስከ ታንዛኒያ፡ በሰሚን እስከ ምዕራብ አፍሪቃ፡ በመካከለኛው ምሥራቅ የዓረቡን ዓለም ጨምሮ፡ ውቅያኖስን አቋርጦ እስከ ሕንድ የሚዘልቅ ግዛት እንደነበራቸው ይነግረናል። ከግብጽ ፒራሚድ ገንቢዎችም አብዛኞቹ ኃይላን ነግሥታት ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ በተክለ ጻድቅ መኵሪያና በሌሎችም ታሪክ ጸሐፊዎች ጭምር ተዘግቧልና ምድያም የኢትዮጵያ ግዛት እንደነበረች የተነገረው ታሪክ ሁሉ አሳማኝ ነው።*)

<u>**የአብርሃም መሞት**</u> 7-10 አብርሃም በመልካም ሽምግልና አንድ መቶ ሰባ አምስት ዓመት ከኖረ በኋላ ሞተ፤ ሁለቱም ልጆቹ ይስሐቅና እስማኤል ባሉበት፣ የሣራ አስከሬን ባረፈበት በማክቤላ ዋሻ ተቀበረ።

**የ<u>ይስሐቅ በትረ ያሬክነት ዘመን፡</u>** 19-23 ይስሐቅ ርብቃን ባገባ ጊዜ ዐርባ ዓመቱ ነበር፤ ርብቃ ኻያ ዓመት ሙሉ ልጅ ሳትወልድ ስለ ቈየች፣ መኻን ሆና እንዳትቀር በማሰብ፣ ይስሐቅ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ እግዚአብሔርም ጸሎቱን ሰማው፣ ርብቃ ፀነሰች። የተፀነሱት ልጆች መንታ ስለ ነበሩ፣ ገና በማሕፀን ውስጥ እያሉ ትግል ስለ ጀመሩ፣ ጭንቀት በዝቶባት፣እግዚአብርን-መጠየቅ-ወደምትችልበት-አንድ-ቅዱስ-ቦታ-ደች። እግዚአብሔርም‹‹ሁለት ወገኖች (ነገደ- ሕዝብ) በማሕፀንሽ አሉ፤ እርስ-በርስ የማይስማሙ ሁለት ነገዶችን ትወልጃለሽ፤አንዱ-ከሌላው-የበረታ-ይሆናል፤ ታላቁ-ለታናሹ-ይገዛል" አላት።



<u>**የዔሳውና የያዕቆብ ልደት፡**</u> ( ሮሜ 9፡ 10-13፤ ሚልክ 1፥1-3)። ሲወለድ በቅድሞያ መውጣት-የጀመረው-ልጅ-መልኩ-ቀይ ሆኖ፣ሰውነቱ በጠጕር የተሸፈነ ስለ ነበር፣ ዔሳው ተብሎ ተጠራ። ሁለተኛው ልጅ የዔሳውን ተረከዝ ይዞ ወደ ኋላ ጐተተና በማሰናከል ተሽቀዳድሞ ስለ -ወጣ ስሙ ያዕቆብ *(አሰናካይ)* ተብሎ ተጠራ( ሆሴ 12፡4)፡

<u>ዔሳው ብኵርናውን ለያዕቆብ ሸጠ</u> 27-34) ሁለቱ ልጆች አደጉ፤ዔሳው የአደን ሰው ስለነበር፣ ከዕለታት አንድ ቀን፣ በረሃ ውሎ ሲመለስ ተራበ። ያዕቆብን፣ ‹‹ከያዝከው ቀይ ወጥ አብላኝ›› ብሎ ለመነው። ያዕቆብም፣ ‹‹ብኵርናህን ሽጥልኝና እሺ›› አለው። ዔሳውም፣ ‹‹እነሆ፣ እኔ በረሃብ ልሞት ነው፣ ታዲያ ብኵርና ምን ይጠቅመኛል ብለህ ነው ? ከፈለግኽህ ውሰደው›› አለው። ያዕቆብም በእግዚአብሔር ስም አስምሎ ብኵርናውን ከወሰደ በኋላ ከያዘው የምስር ወጥ በእንጀራ አድርጎ ሰጠው

(**<u>ትርጓሜ፡-</u>** *በዚህም ሁኔታ ዔሳው ቸል ብሎ መጀመሪያ ብኵርናውን፡ አቃለላት። ቀጥሎ በረከቱን /ምርቃቱን አጣ። በረከቱ ሊመጣ የሚችለው ከብኵርናው ጋር ነበርና እያለቀሰ እንኳ ቢመኛትም መልሶ ማግኘት አልታቻለውም " ይላል ሐዋርያው ጳውሎስ (ዕብ 12፡ 4) ለእኛም ቢሆን የመዳን ቀን ዛሬ ነው" ተብሎ ተጽፏልና* ከሰማያዊ በረከት ውጭ እንዳንሆን ስንፍናን ለማስወገድ ትጋት ይኑረን።)

**ኟ፰/26.** ይስሐቅ የሚሠራውን ሁሉ እግዚአብሔር ባረከለት

1-4.-ይሰሐቅ በጌራራ ምድር ሲኖር፣እግዚአብሔር ተገለጠለትና እንዲህ የሚል-ተስፋ-ሰጠው፤ "በዚች- ምድር- ተቀመጥ፤ እኔ-ከአንተ-ጋር -እሆናለሁ፤ እባርክሃለሁ፣ ለአብርሃም የሰጠሁትን-ቃል ኪዳን ከአንተ ጋር አፀናለሁ፣ ዘርህን እንደ ሰማይ ኮከብ አበዛዋለሁ››። ከዚያን በኋላ፣ይስሐቅ በዚያች ምድር እህል ዘርቶ፣ መቶ እጥፍ አገኘ። እግዚአብሔር ስለባረከው፣ሀብት-ንብረቱ በዛለት፤ የእንስሳ መንጋና ሌላም ብልጽግና አገኘ። በአባቱ በአብርሃም ዘመን ተቈፍረው የተደፈኑ የውሃ ጉድጓዶችን ሁሉ መልሶ በመክፈት በቀድሞ ስማቸው እንዲጠሩ አደረገ።

26-412 -ከዚህ የተነሣ፣ የጌራራ ንጉሥ አቤሜሌክ አማካሪውን አኮዘትንና የሠራዊቱን አዛዥ-ፊኮልን-አስከትሎ-መጥቶ-ይስሐቅን-እንዲህ-አለው፤ ‹‹እግዚአብሔር- አምላክ በረድኤት -ከአንተ -ጋር- እንዳለ -አውቀናል፣ እንግዲህ፣ በመካከላችን ሰላም ሰፍኖ እንዲኖር ስምምነት ( ውል )



www.ethiopianorthodox.org

እናድርግ››፡ በዚሁ ጥያቄ መሠረት የስምምነቱን ቃል በመሐላ ካፀኑ በኋላ፣ ይስሐቅ ታላቅ ግብዣ አደረገላቸውና፤ አብረው በሉ፤ጠጡ፣ በማግስቱም ጠዋት በሰላም ተሸኝተው ወደ ቤታቸው ሄዱ።

## ፳፯ /27. ይስሐቅ ልጁን ያዕቆብን በእምነት መረቀው፡ ( ዕብ 11፡ 20)

1-4 ይስሐቅ በእርጅና-ምክንያት-አይኖቹ ስለደከሙ፣ አጥርቶ ማየት አይችልም ነበር። የመጀመሪያ ( በኩር) ልጁን ዔሳውን ጠርቶ፣ ‹‹ወደ በረሃ ሄድና አድነህ የአውሬ ሥጋ አምጣልኝ። እኔ እንደምወደውም አድርገህ ጥሩ ምግብ አዘጋጅልኝ። የምሞትበት ጊዜ ስለቀረበ፣ያን ተመግቤ የመጨረሻ-ምርቃቴን ( በረከቴን) እሰጥሃለሁ›› አለው።5-1 ርብቃ ይህን ሁሉ ሰምታ ስለ ነበር፣ የብርቅ ልጇዋን ያዕቆብን ጠርታ፣ ‹‹ሁለት የበግ ግልገሎች አምጣልኝ፤ አባትህ እንደሚወደው ዓይነት አድረጌ ጥሩ ጣዕም ያለው-ማለፊያ-ምግብ እሠራለሁ፤ያንም ይዘህ ገብተህ የአባትህን ምርቃት (በረከት) ትቀበላለህ›› አለችው።ያዕቆብ ፈርቶ፣‹‹አባቴ ያወቀ እንደሆን በመመረቅ ፈንታ ቢረግመኝስ ?›› አላት። እናቱ ርብቃም መልሳ ‹‹ልጄ የአንተ እርግማን በእኔ ላይ ይሁን፣ ያልኩሁን ብቻ አድርግ›› አለችው።

14--17 እርሱ እንደ ታዘዘው አድርጎ ,ምግቡን አዘጋጅታ ስትሰጠው፣ የዔሳውን የክት ልብስ አውጥታ አለበሰችው፤የለሰለሰ-እጆቹንና አንገቱን በጠቦቶቹ ጠጕር ሸፈነች። ያዕቆብ አባቱ ይስሐቅ ወደአለበት ክፍል ሲገባ፣ ‹‹እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ›› አለው። ይስሐቅ ተጠራጥሮ፣ 'እርግጥ ? ድምፅህ ግን የያዕቆብን ይመስላል፣አለ። ቀርቦ እጁንና አንገ-ቱን ሲዳብስ የዔሳው ጠጕር መስሎት፣ እንዲህ ሲል መረቀው፣‹‹እግዚአብሔር-ከሰማይ- የሚያረሰርስ- ጠል- ይስጥህ ።-ምድርህን ያለምልምልህ፣ እህልህንና የወይን ጠጅህን ያብዛልህ፣ መንግሥታትና ሕዝቦች ይገዙልህ ። ሕዝብም -ይስገዱልህ፡ በወንድሞችህ ላይ አለቃ (ገገር) ሁን፤ የሚረግሙህ፣ የተረገሙ፣ የሚመርቁህም የተመረቁ ይሁኑ››። 30--40 ከዚያም በኋላ ዔሳ ዘግይቶ መጣ፣ ካደነውም የአውሬ ሥጋ ጣፋጭ ምግብ አዘጋጅቶ፣ወደ አባቱ ይዞ ገባ።ይስሐቅ‹‹አንተ ማን ነህ?›› አለው። ዔሳውም ‹‹እኔ የበኵር ልጅህ ዔሳው ነኝ›› ሲለው ደነገጠና፤ ‹‹ከአንተ በፊት ያደነውን ሥጋ አጣፍጦ ሠርቶ አምጥቶልኝ በልቼ የመረ-ቅሁት ሰው አለ፤ የሰጠሁትም በረከት የማይለወጥና ፀንቶ የሚኖር ነው›› አለው።ዔሳውም ምርር ብሎ እያለቀሰ፣‹‹አባቴ ሆይ! በረከትህ አንዲት ብቻ ናትን? እኔንም ደግሞ ባርከኝ›› ሲል ለመነ። በመጨረሻም አባቱ ይስሐቅ እንዲህ አለው፣ ‹‹እነሆ፣ መኖሪያህ ከምድር ስብና ከሰማይ



በሚገኝ ጠል ይሆናል። በሰይፍኽ ትኖራለህ፣ ለወንድምህም ተገዢ ትሆናለህ፤ ነገር ግን፣በተቃወምኽው ጊዜ የገዢነቱን ቀንበር ከአንገትህ-ላይ አውርደህ (ሰብረህ ) ትጥላለህ››። 41-45 ከዚህ በኋላ፣ ዔሳው በዚህ ነገር ተናድዶ፣ ‹‹ለአባቴ የሐዘን ቀን ደርሶአል፤ ወንድሜን ያዕቆብን እገድላለሁ›› እያለ መዛት ጀመረ። ርብቃም ይህን በሰማች ጊዜ፣ ልጇዋን ያዕቆብን ስትመክረው፣ ‹‹የወንድምህ የዔሳው ቍጣ እስኪበርድ ድረስ ወደ ትውልድ አገሬ ወደ ሶርያ ሄድና ከወንድሜ ከላባ ጋር ኑር፤ በአንድ ጊዜ ሁለታችሁንም ለምን አጣለሁ?! የወንድምህ ቍጣ ሲበርድ ልኬ አስጠራሃለሁ›› አለችው። 46 ርብቃ ወዲያውኑ ወደ ይስሐቅ ገብታ፤ ‹‹እነሆ ዔሳው እነዚህን የከነዓን ( የአረማውያን ) ሴቶች ልጆችን ማግባቱ እያሳዘነኝ ሳለ፣ ያዕቆብም እነርሱኑ የሚያገባ ከሆነ፣ ሕይወቴን የሚያስጠላ ሊሆንብኝ ነው›› አለችው።

## ፳፰ /28. ያዕቆብ ወደ ሶርያ ተላከ

፡1-4 ይስሐቅ ያዕቆብን ጠርቶ እንዲህ አለው፤‹‹በዚህ አገር ካሉት ከከነዓን ሴቶች-መካከል ሚስት ማግባት አያስፈልግህም፤ ይልቅስ ወደ እናትህ ቤተ-ሰብ ወደ መሶጰጣምያ ሂደህ፣ የእናትህ ወንድም ከሆነው ከላባ ጋር ኑር፤ ሚስትም ከርሱ ሴቶች ልጆች መካከል መርጠህ አግባ፤ ሁሉን የሚችል አምላክ ይባርክህ፣ብዙ ልጆችን ወልደህ፣ የብዙ ሕዝብ አባት ለመሆን ያብቃህ››። _ስለዚህም ዔሳው፣ ያገባቸው የከነዓን ሴቶች ልጆች በአባቱ በይስሐቅ ዘንድ እንዳልተወደዱና ያዕቆብን ባርኮ ከከነዓን ሴቶች ልጆች መካከል ሚስት እንዳያገባ መክሮ ወደ ሶርያ እንደላከው ሰማ። ስለዚህም ዔሳው፡ እስማኤል ወደነበረበት ቦታ ሄዶ፣ የእስማኤል ልጅ የሆነች የነባዮትን እኅት ቤሴሞትን በተጨማሪ አገባ።

### እግዚአብሔር በሕልም ተገልጦ ለያዕቆብ የሰጠው ተስፋ :

10--12 ያዕቆብ ከቤርሳቤህ ተነሥቶ ወደ ሶርያ ሲሄድ ውሎ፣ ሎዛ ተብላ ወደምትጠራው ስፍራ ደረሰና፤ ቀኑ ስለ መሸ በዚያችው ቦታ ደንጊያ ተንተርሶ ተኛ። በሕልሙ፣ ከምድር እስከ ሰማይ የሚደርስ መሰላል ተተክሎ፣የእግዚአብሔር-መላእክት_ሲወጡበትና-ሲወርዱበት፤ በመሰላሉም ራስ ላይ የእግዚአብሔር ዙፋን ተዘርግቶበት አየ።

13-15 በዙፋኑ ላይ እግዚአብሔር ቆሞ ታየውና እንዲህ አለው፤‹‹እነሆ፣ እኔ የአባትህ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅም አምላክ ነኝ፤ ይህቺን የተኛህባትን ምድር ላንተና ለዘሮችህ ርስት አድርጌ እሰጣለሁ፤ ዘርህን እንደ ባሕር እሸዋ አበዛዋለሁ።የምድር አሕዛብ ሁሉ በዘርህ ይባረካሉ፤ እንግዲህ አይዞህ አትፍራ፤ እነሆ፣ እኔ ምን-ጊዜም ከአንተ ጋር ነኝ፣



www.ethiopianorthodox.org

በምትሄድበት መንገድ ሁሉ እጠብቅሃለሁ፤ ወደዚህችም ምድር መልሼ አስገባሃለሁ፤ይህን የገባሁልህን የተስፋ-ቃል ሁሉ-እስከምፈጽምልህ ድረስ ከቶ አልተውህም "(ዕብ 13፡5 )።

16-17 ያዕቆብም ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜ፣ ፍርሃት ተሰምቶት ፣‹‹በእውነት እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ አለ፤ ይህ ስፍራ እንዴት ያስፈራል? ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት፣ የሰማይም ደጅ ነው›› አለ። ከዚያ በኋላ፣ያዕቆብ ማልዶ ተነሣ፤ ተንተርሶት የነበረውንም ደንጊያ ወስዶ ሐውልት አድርጎ አቆመና በላዩ ዘይት አፈሰሰበት። ከዚያ በፊት ሎዛ ይባል የነበረውንም ያን ስፍራ ቤቴል ብሎ ጠራው።ትርጓሜውም የእግዚአብሔር ቤት ማለት ነው። (**ትርጓሜ** ፡ *መሰላሉ የክርስቶስ-ምሳሌ ነው። በመስቀሉ የጥል ን ግድግዳ አፍርሶ በእግዚአብሔርና በሰው-ዘር መካከል ዕርቀ-ሰላም ስለተፈጸመ፡ ሲጠበቅ የነበረው የእግዚአብሔር የምሕረት በር ተከፍቶ፣ መላእክት ከሰማይ ወደ ምድር፣ ከምድር ወደ ሰማይ በመመላለስ አማኞችን ለመርዳት፣ ከማናቸውም አደጋ ለመታደግና ለማዳን መዘጋጀታቸውን ያሳያል ( ዮሐ 1፡ 51 )።*

***አነ ውእቱ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት (እኔ እውነትም መንገድም ሕይወትም ነኝና (ዮሐ 14 ፡6)። ‹‹ፍኖት ለኀበ አቡሁ፡ አንቀጸ ዘመንገለ ወላዲሁ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ ( ወደ አብ የሚያደርስ መንገድና በር እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው›› ( የሌሊት ሰዓታት በአባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ)። በሌላው ገጽታ ደግሞ፣ አምላክን የወለደች ቡርክት ቅድስት ድንግል ማርያም ያችን መሰላል እንደምትመስላት ኤፍሬም ሶርያዊ በውዳሴ ማርያም ድርሰቱ ተናግሮላታል ፡ ( በማክሰኞ ውዳሴ ማርያም ) "አንቲ ውእቱ ሰዋስው ዘርእየ ያዕቆብ" የሚለውን ትርጉም ይመልከቱ ። በመሰላሉ ጫፍ በተዘረጀው ዙፋን ላይ የታየ አምላክ በኋለኛው ዘመን በሥጋ ተገልጦ በርስዋ ዙፋንነት በክንዶችዋ ታቅፋው መታየቱን ያመለክታል። )***

*__በቍ-17__ ፡ ‹‹ይህ ስፍራ የእግዚአብሔር ቤት ነው፣ የሰማይም በር ነው››የሚለውን ቃለ- ትንቢት የተመለከተ ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬም፡ የአምላክ እናት ለመሆን የተመረጠች ቅድስት ድንግል ማርያምን በዚያች በር መስሎ ተናግሮላታል፤ (ስምንተኛውን የረቡዕ ውዳሴ ማርያም ይመለከቱአል)። ይህም በነቢዩ ሕዝቅኤል ምዕራፍ 44፡ 1--4 ስለ ተቈለፈችው የምሥራቅ በር ከተጻፈው ትንቢታዊ ምሳሌ ጋር ተመሳሳይ ነው። በሌላም በኩል በዮሐ ምዕ 10፥ 7 ‹‹አነ ውእቱ አንቀጸ አባግእ "እኔ የበጎች በር ነኝ››ብሎ የተናገረ ጌታም፡ ራሱ በበጎች በር*



*ተመስሏል ። ያዕቆበ ባቆመው የድንጋይ ሐውልት ላይ‹‹ዘይት አፈሰሰበት›› ይላል ። ዘይት ለእግዚአብሔር የተቀደሰ መባ ሆኖ ቦታን ጭምር እንደሚያከብር በግልጥ ያሳያል ማለት ነው። ለምሳሌ ልዑላን መሳፍንት ለመንግሥት ፡ነቢያት ለትንቢት ፡ ቀሳውስት ለክህነት አማኞች ለመንፈስ ቅዱስ ልጅነት ፣ ለቤተ-ክርስቲያን መሪዎች የሚሆኑ አባቶች ለጵጵስናም ሆነ ለፓትርያርክነት ሢመት የሚበቁት፡ በዚሁ በቅብዐ-ዘይት እንዲከብሩ ተደርጎ ነው። ስለዚህም፣ ሕገ እግዚአብሔር በጽሑፍ ጐልቶ ከመታየቱ በፊት፣በዚያ ጨለማ ዘመን፣ ይህ ምስጢር-ተገልጦለት-ያዕቆብ ተግባራዊ ሲያደርገው በመታየቱ፡ የእግዚአብሔርን ጥበብ እናደንቃለን።*

*20--22 ያዕቆብ እንዲህ ብሎ ተሳለ (ብፅዓት አደረገ )፡ ‹‹እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ሆኖ በምሄድበትም ቦታ ሁሉ ቢጠብቀኝና የምበላውን የዕለት እንጀራና የምለብሰውን ልብስ ቢሰጠኝ፡ ወደ አባቴ አገር በደኅና ቢመልሰኝ፣ እግዚአብሔር ለዘለዓለም አምላኬ ይሆንልኛል፣ ሐውልት አድርጌ ያቆምሁት ይህ ደንጊያ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ የሚሠራበት ይሆናል። አምላኬ ሆይ፣ ከምትሰጠኝ ሀብት ሁሉ ከዐሥር አንዱን እጅ ለአንተ እሰጣለሁ››። )* """""""""""""""""""""""""""""""""""

## ፳፱/29. __ያዕቆብ አጎቱ ላባ እሚኖርበት አገር ደረሰ__ ፡

1-28 ያዕቆብ ከዚያ-ተነሥቶ ወደ ምሥራቅ ሰዎች አገር ደረሰ። በሜዳ ላይም አንድ የውኃ ጉድጓድ አየ። በዚያም የከብት መንጋ ጠባቂዎችን (እረኞችን) አገኘ፣ ስለ አጎቱ ስለ ላባ ደኅንነት ጠይቆአቸው ሲነግሩት ሳለ፣ የላባ ልጅ ራሔል የአባትዋን በጎች እየነዳች ውኃ ለማጠጣት በድንገት መጥታ አገኛት። የኀምሳና የስድሳ ሰው ጉልበት የሚጠይቀውን የጉድጓድ ውሃ መክደኛ ደንጊያ ብቻ - ለብቻ አንሥቶ በማስገለል፣ በጎቹዋን አጠጣላት፤ ከዚያም ቀረብ ብሎ፣ ‹‹እኔ የአክስትሽ የርብቃ ልጅ ነኝ›› አላት ከደስታው--ብዛት የተነሣም እያለቀሰ ሳማት። ራሔል የእርሱን-መምጣት ለመንገር ወደ አባቱዋ ፈጥና ሄደች። ላባ የያዕቆብን መምጣት ሲሰማ፣ ደስ ብሎት ሊቀበለው በፍጥነት እየሮጠ መጣ፤ ባየውም ጊዜ አቅፎ ሳመው፡ያዕቆብም ራሔልንና ልያን ለማግባት ዐሥራ ዐራት ዓመት ለማገልገል ከላብ-ጋር ስምምነት አደረገ

26-30 ስለ ራሔል ሰባት ዓመት ካገለገለ በኋላ፣ ላባ የሠርግ ድግሥ አዘጋጅቶ፣ ማታ በምሽት ጊዜ፣ በራሔል ፈንታ ልያን በሚስትነት ሰጠው። ያዕቆብም በማግስቱ ልያ መሆኗን ሲያይ ተቈጣ። ላባ ግን



www.ethiopianorthodox.org

‹‹በሀገራችን፣ ታላቅ ልጅ እያለች ታናሽ ልጅን መዳር ያልተለመደ ሥርዓት ነው። በእርግጥ ራሔልን ደግሞ ከዚህችኛዋ-ሳምንት በኋላ እሰጥሃለሁ፣ ስለ እርሱዋም እንደ ገና ሰባት ዓመት ታገለግለኛለህ" አለው።ያዕቆብም በዚሁ ተስማማ። እንደገናም ራሔልን አግብቶ ሰባት ዓመት አገለገለው።

የእግዚአብሔር ተንቃ የነበረችው ልያን እንድትወደድ አደረገ ፡

31-35 ልያ በያዕቆብ ዘንድ እንደ ራሔል የሚያስወድድ መልክ (ውበት) ስላልነበራት -እግዚአብሔር ችግሯን ተመልክቶ ማሕፀንዋን ስለከፈተላት- ዐራት ወንዶች ልጆችን ለያዕቆብ ወለደችለት። የመጀመሪያውን ሮቤል ብላ ጠራችው። የስሙ ትርጉም፣‹‹እግዚአብሔር መከራዬን አይቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ እኔን ባሌ ይወደኛል›› ማለት ነው። ሁለተኛውን ስምዖን አለችው፤ የስሙም ትርጉም ‹‹መጠላቴንና መናቁን እግዚአብሔር ሰምቶ ይህን ደገመኝ›› ማለት ነው። ‹‹አሁንም ባሌ ወደ እኔ ይቀርባል›› ስትል ሦስተኛውን ልጅ ሌዊ አለችው። ‹‹ስለኔ ይህን ሁሉ መልካም ነገር ያደረገልኝን እግዚአብሔርን አመሰግነዋለሁ›› ስትል 4ኛውን ልጅዋን ይሁዳ አለችው።

ፙ /30. ራሔል በእኅትዋ በልያ አወላለድ ቅናት አደረባት -

1-2 ራሔል መልከ ቀና በመሆንዋ፣ በያዕቆብ ዘንድ በጣም የተወደደች ብትሆንም፣ ልጅ ለመውለድ ባለመቻልዋ፣ በእኅቱዋ በልያ ቀናችባት። ስለዚህ ያዕቆብን፣ ‹‹ልጅ ስጠኝ ፤ አለዚያ እሞታለሁ›› አለችው። 3--8 ለዚህም ለእልህ ስትል፣ ባላ ተብላ ከምትጠራው አገልጋይዋ ልጅ ይወልድላት ዘንድ ለያዕቆብ ፈቅዳለት፣ ‹‹ዳንና ንፍታሌም›› ተብለው የሚጠሩትን ሁለት ወንዶች-ልጆች ወለደችለት። ዳን ማለት እግዚአብሔር ቃሌን ሰምቶ ፈረደልኝ ወይም-ዳኘ"-ማለት ነው። ንፍታሌም ማለት፣ ‹‹ከእኅቴ ጋር ብርቱ ትግል ( ውድድር ) አድርጌ አሸነፍሁ›› ለማለት የወጣለት ስም ነው። 9-13 ልያ ደግሞ በበኩልዋ ልጅ መውለድን እንዳቆመች ባየች ጊዜ፣ዘለፋ ተብላ የምትጠራ አገልጋይዋን ፣ ልጅ ይወልድላት ዘንድ-ለያዕቆብ ሰጠችውና፡ ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደችለት። ይህን ስታይ፣ ልያ ጉድ ብላ ስለ ነበር የመጀ መሪያውን ልጅ ስም ጋድ አለችው። ሁለተኛውንም ልጅ አሴር ብላ ጠራችው። ይኸውም "ደስታ ሆኖልኛልና ሴቶች ሁሉ፣ ‹‹የተባረክሽ ብፅት (ቡርክት) ነሽ›› እያሉ ያመሰግኑኛል ለማለት የወጣለት ስም ነው።

ልያ እንደገና መውልውድዋን በመቀጠል ይሳኮርና ዛብሎን ተብለው የሚጠሩትን ሌሎች ሁለት ወንዶች ልጆችን ለያዕቆብ ወለደችለት።



ይሳኮር የስሙ ትርጉም በእንኮይ ፍሬ የተገዛ (ዐስበ ኮል) ማለት ነው። ይኸውም በስንዴ መከር ወራት የልያ በኩር ልጅ ሮቤል የእንኮይ ፍሬ ይዞ መጥቶ ስለ ነበር፣ ራሔል ልያን፣ ‹ከዚህ የእንኮይ ፍሬ ስጪኝ›› ብላ ብትጠይቃት ‹‹ባሌን መቀማትሽ አንሶ-ደግሞ የልጅን እንኮይ-ተመኘ-ሽን?›› በማለት ስለ ከለከለቻት ‹‹ዛሬ ያዕቆብ ከአንቺ ጋር ይደርልሽ›› ብላ ፈቅዳላት፣በዚያችው ሌሊት ስለ ተፀነሰና በሌላም በኩል፣ ‹‹ገረዶን ለያዕቆብ ስለሰጠሁ፣ እግዚአብሔር አምላክ ጸሎቴን ሰምቶ ዋጋ ሰጠኝ›› ስትል ልያ ያወጣችለት ስም ነው። ከዚያም ቀጥላ ዲና ተብላ የምትጠራ አንዲት ሴት ልጅ ወለደች።22-24 ከዚህ በኋላ፣ እግዚአብሔር ራሔልን በረድኤት ስላሰባት፣ ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች። ስሙንም ‹‹ዓመት ፡ዓመት ድገመኝ›› ለማለት ዮሴፍ ብላ ጠራችው። (ሁለተኛው የራሔል ልጅ ብንያም ተብሎ የሚጠራው-ነው።የርሱን ልደት በዘፍጥ ምዕ 35፡ 16-21 እናየዋለን። እንግዲህ ዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል›› ተብለው የሚጠሩት የያዕቆብ ልጆች እነዚህ ናቸው፡- ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ይሁዳ፣ ይሳኮር፣ ዛብሎን፣ ዳን፣ ጋድ፣ አሴር፣ንፍያሌም፣ ዮሴፍና ብንያም።

*(ትርጓሜ* ፡ ከፍ ብሎ በራሔል ላይ ያየነው መሐንነትና የልያ ወላድነት፡" ልጆች የመውለድንና ያለመውልድን ሁኔታ ብቻ የሚያሳይ ሳይሆን መምህራንንም የሚመለከት ምሥጢራዊ ትርጉም አለው። ይኸውም በትርጓሜ ወንጌል ማቴዎስ 24፡ 19 ወባሕቱ አሌ ሎን ለፅንሳት ወለእለ የሐፅና በውእቱ መዋዕል=በዚያ ወራት ለፀነሱ ነፍሰ ጡሮችና ወልደውም ሕፃናትን ለሚያሳድጉ ሴቶች ወዮላቸው" በሚለው ምንባብ ላይ አባቶች እንደተረጐሙት፡ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ወተት እየጋቱ ደቀ መዛሙርትን በመንፈስ ቅድስ ጸጋ የሚያሳ ድጉ መምህራንንም ይመለከታል። ይኸውም አስተምረው ብዙ ደቀ መዛሙርትን የማውጣት ዕድል በብዙ መልኩ ይለያያል ወይም የደረጃ ልዩነትን ያሳያል። አንዳንድ መምህራን ብዙ በማስተምር ደክመው የበቁ፡ የነቁ ደቀ መዛሙርት አይወጡላቸውም። አንዳንዶቹ መምህራን ደግሞ በቀላሉ አስተምረው ብዙ ደቀ መዝሙርት ይወጡላችዋል። እንድ አሸን ይፈላሉ። ለምሳሌም እንድ ማስረጃ አድርገን ክምንጠቅስቸው እልፍ አእላፍ መምህራን መካከል በጎጃም (ቀራንዮ)፡ በወሎ የልሻማ መድኀኔ ዓለም አለቃ ምሥራቅ፡ በጐንደር መምህር ክፍለ ዮሐንስ፡ የኔታ ክፍሌ የበኣታ አቋቋም ምስክር የነበሩት፡ መምህር አስካል ዘደቡብ ጐንደር፡ አለቃ አየለ፡ ያራቱ ጉባኤ ያት ትርጉም መምህር፡ መምህር ሰይፉ የነበሁዕ አሸን እንድርያስ



www.ethiopianorthodox.org

መምህር የነበሩት፡ በሸዋ አለቃ ጥበቡ ገሜ በሰላሌ አውራጃ ሥሬ መድኃኔ ዓለም፡ በዙዋይ ደሴት ላይ የመምህራን ማሠልጠኛ ከፍተው የነበሩት ብፁዕ አቡነ ጎርጎሬዮስ፡ ወዘተ መልካም መሬት እንዳለው ዕድለኛ ገብሬ-የዘሩት-ሁሉ-የሚበቅልላቸውና ፍሬያማዎች መምህራን ሆነው እንደ አሸን የሚፈሉላቸው ነበሩ። ዛሬ እነርሱን የሚተኩ ብዙ መምህራንን አናይም፡አለመታደል ነው።_ባሁኑ ዘመን በመላዋ ኢትዮጵያ አድባራትና ገዳማት የሚገኙ እልፍ አእላፍ መምህራን መካከል ብዙዎቹ ከእጅ ወደ አፍ በሆን ደመወዝ ተወስነው ከካህናትም ሆነ ከምእመናን መካከል የሚማሩላቸው ደቀ መዛሙርት ማግኘት ተስኗቸው የወላድ መኻኖች ሆነው መቅረታቸው ታሳዝናል። ብዙ ሀብት ባላቸው በአንዳንድ የአዲስ አበባ ገዳምትና አድባራት ሁለትና ሦስት መምህራን ያለደቀ መዛሙርት ተግባረ ፈት ሆነው መገኘታቸው በንፍስም በሥጋም የሚያስፈርድ ነው። ይህን ስሕተት ልለረም ቅዱስ ሲኖዶሱ የግብጽ ክኮፕቲክ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲይንን ኣርአያነቅና ምሳሌነት በመከተል አስገዳጅ መመሪያ ሕግ አውጥቶ ያልተማሩ እንዲማሩ ማድረግ ይቻለዋል።

_ልያ እንደ ራሔል መልከ ቀና አለመሆንዋን የተመለከተ እግዚአብሔር የተጠላችውን ያሀል እንድትወደድ በርከት ያሉትን ልጆች ለመውለድ ማሕፀንዋን ከፈተላት ይላል (ዘፍጥ 29፡ 31-35)። ከመምህራንንም መካከል አንዳንዶቹን እንደ ልያ ወላዶች ሆነው የሚያስተምሩት ቃል ሁሉ በመልካም መሬት ላይ እንደወደቀ ዘር ሠላሳ፡ ስድሳና መቶ ፍሬ የሚሰጥ ሆኖ በመገኘቱ የተወደዱ ሆነዋል። የመልክን ማማርና አለማማር በሚመለከት በአስደናቂሁኔታ ታሪክ የሚጠቀስለት **<u>እስታሎፕሲ</u>** የሚባል አንድ መምህር የፈረንሳይ አገር ዜጋ ነበር። ያም ሰው ሁለንተናው አካለ ስንኩል ሆኖ ዓይነ ሸውራራ፡ አፍንጫው ድፍጥ፡ እግሩ አንካሳ፡ ሰውነቱም ክሳሳ፡ ሆኖ አእምሮው ግን ብሩህ ስለነበር በትምህርት አሰጣጡ ተማሪዎች ሁሉ ከልብ የሚወዱትና የሚያደንቁት ሰው ነበር። ታዲያማ አንድ ጊዜ በፈረንሳይ አገር የቁንጅና ውድድር ለማድረግ በመገናኛ ብዙኃን (በማስ ሚድያ) ታውጆ ነበርና ሕዝቡ በጠቅላላ የሰጠው የምርጫ ድምፅ "በከንቱ አትድከሙ፡ በዓለም ላይ የቆንጆውች ሁሉ ቆንጆ፡ ሸጋ ውብ ዓይናማ ማለት እስታሎፕሲ ብቻ ነው" የሚል ነበር። ታላቁ ኢትዮጵያዊ ምሁር መልአከ ሰላም ሳሙኤል ተረፈ "ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ ራሳችንን አስመስለን በራሳችን አምሳል



ሰዎችን እንፍጠር" ይሉ ነበር። የእኛም የሁላችን ተምኔት ሁሉ ይህን የጥሩ መምህርነት ሙያ በጥራት የተሟላ ለማድረግ ቢሆን የእግዚአብሔር ጸጋና ሞገስ ሁሉ በዝቶልን በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ለማግኘት ከእስታሎብሲ የተሻለ ዕድል ይኖረናልና ነው።

## <u>ያዕቆብ ስለ ደመወዙ ጉዳይ ያደረገው ስምምነት</u>

_27-32 ላባ ያዕቆብን እንዲህ አለው "እግዚአብሔር ባንተ ምክንያት እንደባረከኝ አውቃለሁ፡ አሁንም የደመወዝህን ልክ ንገረኝና አገልግሎትህን ቀጥል፤ እኔም ደመወዝ ልክፈልህ››። ያዕቆብ እንዲህ ሲል መለሰለት፤‹‹ሌላ ደመወዝ እንድታስብልኝ አላስቸግርህም፤ብቻ ሽመልመሌ፤ ዝንጉርጉር፤ ነቍጣና ጥቍር ቀለም ያላቸው በጎችና ፍየሎች የእኔ እንዲሆኑ ብትፈቅድልኝ ይበቃኛል››።ከዚያ በኋላ፤ ያዕቆብ (በዘፍጥ ምዕ 31፡ 1 እንደ ተጻፈው የእግዚአብሔር-መልአክ- በገለጠለት ምልክት-መሠረት) <u>ለውዝና፤ኤርሞን</u> ተብለው ከሚጠሩ እንጨቶች እርጥብ በትሮችን ቈርጦ፤ እየላጠ በውስጥ ያለው ነጭና ጥቍር ሆኖ- እንዲታይ፤ ሽመልመሌ- አድርጎ-አዘጋጀ።መንጋዎቹ-ውኃ-ለመጠጣት በሚመጡበት ጊዜ ሽመልመሊ-የሆኑትን በትሮች ወስዶ በውኃ ማጠጫው ገንዳ አጠገብ ተክሎ ፊት-ለፊት እንዲታዩዋቸው አደረገ፡ እነዚያን በትሮች እያዩ ተባእትና እንስ ጐምጅተው እርስ- በርሳቸው በሚንጠላጠ ሉበት ጊዜየሚወልዱአቸው ግልገሎች ዝንጉርጉር ሽመልመሌ፤ጥቍርና ነቍጣ ያላቸው ሆነው ተገኙ።ስለዚህ፤ያዕቆብ እጅግ ባለጸጋ ሆነ፤ የበግና የፍየል፤ የግመልና የአህያ መንጋዎች ከብዙ

**፴፩ /31.** <u>ያዕቆብ ከአጎቱ ከላባ ቤት በስውር ኮበለለ</u> :

1-3. ያዕቆብ ባለ ጸጋ መሆኑን ባዩ ጊዜ፤ የላባ ልጆች፤ ‹‹ይህን ሁሉ ሀብት ያገኘው የአባታችንን ንብረት ለራሱ በማከማቸት ነው›› እያሉ ሲያሙት ሰማ።ስለዚህ እግዚአብሔር ያዕቆብን፤ ‹‹ወደ አባትህ አገር ተመለስ፤ እኔ ከአንተ ጋር- እሆናለሁ›› አለው።4-13 ከዚህ በኋላ፤ ያዕቆብ-መንጋውን- ወደሚጠብቅበት-ቦታ-እንዲመጡ፤ራሔልንና ልያን አስጠራቸውና ሲመጡ፡ እንዲህ አላቸው፤ ‹‹የአባቴ አምላክ ከእኔ-ጋር-ሆኖ፤ጉልበቴን_ሳልቈጥብ_አባታችሁን- እንዴት እንዳገለገል ሁት ታውቃላችሁ። እርሱ ግን ደምወዜን ዐሥር ጊዜ በመለወጥ አታለለኝ። ግን እኔን እንዲጐዳኝ እግዚአብሔር አልፈቀደለትም። እነሆ፤ በቤቴል በሕልም ያነጋገረኝ አምላክ፤ እንደ-ገና ተገለጠ፤‹‹ወደ-ተወለድህ



www.ethiopianorthodox.org

ሀባት አገርሀ-ተመልሰህ ሂድ' ብሎ አዝዞኛል››፡ 14-16 ራሔልና ልያም በአንድ ድምፅ፤‹‹እኛ በአባታችን ዘንድ እንደ ባዕዳን ተቈጥረናል።እርሱ-እኛን ሸጦ ዋጋችንን በልቶአል፡ አሁንም እግዚአብሔር-የነገረህን ሁሉ አድርግ›› አሉት። ከዚህ በኋላ፤ያዕቆብ ያለውን ሀብት-ንብረት ሁሉ ሰብስቦ፤ ከላባ ተሰውሮ ለመሄድ ተነሣ። ራሔል በአባትዋ በላባ ቤት ውስጥ የነበሩትን ባዕዳን አማልክት / ጣዖታት ሰርቃ ወሰደች' 24 ላባ የያዕቆብን መኮብለል፤የሰማው ከሦስት ቀን በኋላ ነበር። ወዲያውኑ ዘመዶቹን አሠልፎ ይከታተለው ጀመር። ከሰባት ቀን በኋላ፤ በገለዓድ ተራራ ላይ ሊደርስበት ሲቃረብ፤ እግዚአብሔር ለላባ በሕልም ተገልጦ ታየውና፤ ‹‹ያዕቆብን ክፉም ሆነ ደግ እንዳትናገረው ተጠንቀቅ›› ሲል ገሠፀው።

5-32 በተገናኙም ጊዜ፤ ላባ ያዕቆብን፤ ስለ ምን በስውር እንደ ኮበለለ ሲጠይቀው፤ ያዕቆብ በሰጠው መልስ ፤ ‹‹የአባቴ የአብርሃም አምላክ፤ የይስሐቅም ፍርሃት ከእኔ ጋር ባይሆን ኖሮ፤ ባዶ እጄን በሰደድከኝ ነበር። እግዚአብሔር የእኔን መበደልና መገፋት፤ልፋቴንም ሁሉ ስለሚያውቅ፤ ባለፈው ሌሊት በሕልም ገሥፃሃል›› አለው። "መሄዱንስ ሂድ፤ ታዲያ አማልክቶቼን ለምን ሰረቅኸ›› ሲል ላባ ጠየቀ። ያዕቆብ ግን ራሔል ሰርቃ መውሰዱዋን ፈጽሞ አያውቅም ነበርና፡ ‹‹ድንኳኑን ሁሉ ፈትሽህ እነዚያን አማልክት ሰርቆ የወሰደ ቢኖር፤ በሞት ይቀጣ›› ሲል የውሳኔ ቃል ተናገረ። ላባ ድንኳኑን ሁሉ ፈትሾ የተሰረቁበተን አማልክት ማግኘት አልቻለም። ራሔል በግመል ጀርባ ላይ በሚውል ኮርቻ ሥር መደላድል አድርጋ ተቀምጣባቸው ነበርና። አባትዋ ለመፈተሽ ወደ ራሔል ሲመጣ፤"በሴቶች ልማድ (በደመ ትክቶ) ላይ ስልሆንሁ በፊትህ ባለመነሣቴ ይቅርታ አድርግልኝ›› ስትለው፤ በመደንገጥ ተመልሶ ሄደ።

*(<u>ትርጓሜ</u> ፡ እንግዲህ በዚያ ዓይነት ኮርቻ ሥር መቀመጫ የሆኑ ጣዖታት ሀብት ያስገኛሉ ተብሎ መታመኑ ራሱ ታላቅ ሞኝነት ነበር ። ይህ ድርጊት በዘምናችን ከሚታየው የጀበና ባዕድ አምልኮትና ከሌሌ ማንጠልጠል ጋር ተመሳሳይነት አለው። አንዳንድ ሴቶች ቤተ ክርስቲያን ሄደው ሲመለሱ ካዙዋሪ ቸርቻሪዎች ያገኙትን የቁጠማ ዓይነት ሣር ገዝተው ይወስዱና ጎዝጉዘው ፡ ዕጣን አጢሰው፡ ፈንድሻ እየብተኑ የሚለማመኑት የሰይጣን መጥሪያ አምልኮ ነው። ስኒ እየዘቀዘቁ ዕድል እንነግራለን የሚሉትም የውሸት ጥንቈላ በእግዚአብሔር ቃል የተወገዘ ነው። "የሚርትን፡ የሞራ ገላጭነትን፡ ዕድልንም የመንገርና የአስማተኛነትን መተት የሚከተል ሁሉ ከመካከ ላችሁ ተለይቶ ይጥፋ" ይለናል ዘዳግ 18 10፡13-።*



## የጠንቋይ-ቱማታ፡

_አንምዲት ወጣት ቆንጆ ልጅ መውለድ ፈልጋ፡
ሄደች ወደ ጠንቋይ ልትጠይቅ በዋጋ፡
ጠንቋዩም ደስ ብሎት ባለማወላወል
"በሕግ ካጋባሺው ከመጀመሪያ ባል
መውለድሽ አይቀርም፡ አውልያው ታርቈሻል
ተቀባይ ወንድ ልጅ ጀባ ብለንሻል ! "
እያለ ሲያጎራ ሴትዮዋ ገርሟት፡
አይመስለኝም ጌታው፡ ምነው እያወቁት፡
የሕግ ባሌማ ካለፈ ሕይወቱ፡
ከሞተ ቆይቷል ልክ ዐሥር ዓመቱ"
ብላ መልስ ብትሰጥ ጠቋዩ ተቈጣ፡
ነገሩ አሳፍሮት የሚያደርገው ቢያጣ
"ዝም በይ ፍየል ምላስ ምን አስለፈለፈሽ
ቢሞትም ባይሞትም ትወልጃለሽ አልኩሽ
ይህን ካላመንሽ እዚህ ምን አመጣሽ ?"
እያለ አጎራባት በሐፍረት ተውጦ
የጠንቋይ ቱማታ ምኑ ተጨብጦ ?
_ሳይሠሩ ለመክበር በሕዝብ እያሾፉ፡
በሐሰት ጥንቈላ አገር የሚዘርፉ።
ጫት ቅመው በሰው ላይ እያነፈነፉ፡
እንትፍ ትፍ ባመለት ምራቅ የሚተፉ፡
መተት በመተብተብ ክታብ የሚጽፉ
ውሽታቸው ታውቋል፡ ከእንግዲህ አይልፉ።
በዓድዋ ጦርነት አገር ስትወረር፡
ልትወድቅ ታቃርባ ሕዝበ አዳም ሲሸበር፡
ከቶ እውነት መስሏቸው የጥንቈላው ነገር፡
"አስማተኛ ጠንቋይ ባለ መድፍን ፀር፡
ባለ አንደርቢ እሳት የምትፈጥር፡
ጠላት መጥቶብናል፡ ሳትፈሪ፡ ሳታፍር፡
አደባባይ ወጥተህ ሙያህን አስመስክር፡
ተባበር" ተብሎ ተጠይቆ ነበር።
ዳሩ ግን ያን ጊዜ ማንም መልስ አልሰጠም፡



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ውኃ ሽታ ሆኖ ቀርቷል ሁሉም፡
በማይጨውም ጊዜ ጥንቄላ አልጠቀመም።
ስለዚህ ጠንቋይም አስጠንቋም ስማ !
በጥንቄላ አይደለም አገር የምትለማ፡
የጥንቄላ መተት የአስማቱ ጋጋታ፡
ኋላ ቀርነት ነው፡ የመርገም ቱማታ።''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

33--54 ያንም ሁሉ ክትትልና ፍተሻ በሚመለከት ያዕቆብ ላባን በብርቱ ወቀሰ። በመጨረሻ ግን ሁለቱም-ተስማምተው በገለዓድ ተራራ ላይ ምስክር የሚሆን ሐውልት፣ ከድንጋይ ክምር ሠርተው አቆሙ። ድንበር ላይተላለፉና አንዱ በሌላው ላይ ጉዳት ላያደርስ ቃል ኪዳናቸውን በመሐላ አፀኑ። በዚያም ያዕቆብ መሥዋዕት ሠውቶ፣ ወንድሞችን ሁሉ ጋበዘ። አብረው በልተውና ጠጥተው በማግሥቱ በሰላም ተሰነባብተው ወደየአገራቸው ሄዱ።

## ም፲፪ /32. ያዕቆብን በመንገድ ጉዞ ይጠብቁት የነበሩ መላእክት

1-2. ያዕቆብ በጉዞ ላይ ሳለ፣ የእግዚአብሔር መላእክት ተገናኙት። እርሱም ባያቸው-ጊዜ «እነዚህ የእግዚአብሔር ሠራዊት ናቸው» ልማለት ያን ስፍራ መሃናይም ብሎ ጠራው።

<u>የያዕቆብ የምስጋና-ጸሎት</u>፡9-12፣ «የአባቶቼ የአብርሃምና የይስሐቅ አምላክ የሆንህ እግዚአብሔር ሆይ፣ ጸሎቴን ስማ፣ ወደ ትውልድ-አገርህና ወደ ዘመዶችህ ተመለስ ፣ በዚያም መልካም ነገር እንዲሆንልህ አደርጋለሁ» ስትል የሰጠኸኝን ተስፋ አስብ። በእርግጥ እኔ አገልጋይህ ይህን ያህል ቸርነት ልታደርግልኝ የሚገባኝ አልነበርኩም፤ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሬ ስመጣ፣ ከዚህች ከምመረኮዛት በትር በቀር፣ ሌላ ምንም አልነበረኝም። አሁን ግን እነሆ፣ የሁለት ክፍል ሠራዊት ይዤ ለመመለስ ችያለሁ ። እነሆ፣ በእኔ ላይ አደጋ በመጣል ሴቶችንና ሕፃናትን ጭምር ያጠፋል ብዬ ስለፈራሁት፣ ከወንድሜ ከዔሳው እጅ እንድትታደገኝ (እንድታድነኝ)-እለምንሃለሁ። ‹መልካም ነገር አደርግልሃለሁ፤ ዘርህን ሊቈጠር እንደማይቻል እንደ ባሕር አሸዋ አደርገዋለሁ› ስትል የገባህልኝን የተስፋ ቃል አስብ" ። <u>(ትርጓሜ፡</u> ያዕቆብ በሥተኋላ ያሳድደው የነበረውን የአጎቱን የላባን ጉልበት ያብረከረከለት ራሱ እግዚአብሔር እንደ ነበር አይተናል። አሁን ደግሞ ፣ በፊቱ የተጋረጠ ሌላው ተቃዋሚ ፣ ቀድሞ ከትውልድ አገሩ እንዲሰደድ ያደረገው የገዛ



ወንድሙ ዔሳው ነው። በክርስቶስ የሚያምኑ ደጋግ ሰዎችም የሚገጥማቸው ፈተና ከፊትም፡ ከኋላም ስለሆነ ከዚህ የተለየ አይደለም። ስለዚህ በራስ ብቻ በመተማመን ፈንታ፡ መላ ሕይወትን ለእግዚአብሔር በማስረከብ የመጸለይን ጥበብ ከያዕቆብ መማር ይገባናል። ያዕቆብ ከዚያ በፊት የነበረው ታታሪነት፣ ሁሉም ነገር በራሱ ብልሃትና ጥበብ የሚፈጸም መስሎት፡ ብኩርናን በምስር ንፍሮ ገዛ። በረከትን (ምርቃትን) ደግሞ አባቱን በማታለል ወሰደ ። ታዲያ ይህ ሁሉ ተደምሮ ስደትንና በአጎቱ በላባ-ቤት-መታለልን-አስከትሎበታል። በራሔል ፈንታ ልያን-ዳረለት፡ደመወዙን በሥር ጊዜ ሲለውጥበትና ሲያታልለው ቈይቷል። አሁን ግን፡ የእርሱ ታታሪነት ብቻ ምንም ዋጋ የሌለው ከንቱ ድካም መሆኑን የተገነዘበው ያዕቆብ፣ እንደ ገና ሕይወቱን ለእግዚአብሔር በማስረከብ እንዴት እንደ ጸለየ ተመልክተን፡ አርአያና ምሳሌነቱን-መከተል ይገባናል።እነሆ ዛሬም እኛ ሁላችን በራሳችን ጥረት ብቻ ከኃጢአት ሁሉ የምንነጻ መስሎን፡ የእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረቱ እኛ ከምንሠራው በደል ሁሉ በላይ መሆኑን ረስተን እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፡ ለሥጋ ወደሙ አልበቃሁም " በማለት ከዘለዓለም ፍዳ መንጻት ከምንችልበት ከሥጋ ወደሙ ስንሸሽ እንኖራለን። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን ። በጥንት ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ማለትም በግብጽ፡ በሶርያና በአርመን በሕንድ ማላባርና-በአውሮፓ የምሥራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ተብለው በሚጠሩት በግሪክ፡ በራሺያ፡ በሩማኒያንና ቡልጋርያ አብያተ ክርስቲያናት በየዕለተ እሑድ ተሰብስቦ ካስቀደሰ ሕዝበ ክርስቲያን በሙሉ ከልሂቅ ኣስከ ድቂቅ ሥጋ ወደሙ ሳይቀበል ተመልሶ አይውቅም። ታዲያ ያ ሁሉ ሕዝብ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኖች የተሻለ የኃጢአት ንጽሕና ስላለው ይመስላችኋልን? አይደለም። ሥጋ ወደሙ የኃጢአት ሒሳብ ማወራረጅ መሆኑን በማመኑ ብቻ እንጂ። ወደሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ያነጽሐነ እምኵሉ ኃጣውኢነ -የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋውና-ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል ተብሎ ተጽፏልና (1 ዮሐ 1፡7 )።''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

13-21 ያዕቆብ ለወንድሙ ለዔሳው የላከለት ገጸ በረከት፡

_በማግሥቱም ዔሳው ካለው ሀብት ሁሉ ( የእንስሳት መንጋ) መርጦ፣ ሁለት መቶ እንስት ፍየሎችን፡ ኻያ የፍየል አውራዎችን ፣ ሁለት መቶ እንስት በጎችና ኻያ የበግ አውራዎችን ፣ ኻያ የሚያጠቡ ግመሎችን



www.ethiopianorthodox.org

ከነግልገሎቻቸው፣ዐርባ ላሞችና ዐሥር ቦሮችን፣ ኻያ እንስት አህዮችን ከዐሥር ውርንጭላዎች ጋር ለወንድሙ ለዔሳው ገጸ በረከት አድርጎ በማከታተል በአገልጋዮቹ እየተነዱ እንዲሄዱ-አደረገ።

(**ትርጓሜ፡-** እንግዲህ-ያዕቆብ-ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ፡ ከወንድሙ ከዔሳው ያድነው ዘንድ መማፀኑን አይተናል። "ያዲያ ይህ ሁሉ ስጦታ ለምን አስፈለገ?" የሚል ጥያቄ ቢኖር፡ ማንም ሰው የጸሎቱን መልስ መጠበቅ ያለበት የበኩሉን ጥረት እያደረገ ወይም የራሱ አቅም የሚፈቅድለትን የቤት ሥራ (Homework /Assignment እያከናወነ ፡ ጥረቱን እግዚአብርሔር እንዲባርክለት መጠየቅ እንጂ፡ እጁን አጥፎ፡ እግሩን አንጥፎ በመጠበቅ አይደለም። ለዚህ የሚጠቀሱ ብዙ ታሪክና ምሳሌዎች አሉ። ከነርሱም አንዱን ብንጠቅስ በግሪክ አገር በአቴና ከተማ የምትመለክ ዲየና የምትባል የጣዖት ሴት አምላክ ነበረች። ታዲያ አንድ ሰው በውኃ ኀርፍ ተጠርጎ ሲወሰድ "እጁን ዘርግቶ ዲየና፡ አድኚኝ፡ ድረሺልኝ" ሲል ያየውና የሰማው ሌላ ሰው፡ "አንተም በበኩልህ ግር፡ ቅጠሉንና የተገኘውን የዛፍ ሐረግና ሥራሥር ለመያዝ እየሞከርህ የዲየናን እርዳታ መጠየቅ እንጂ አንተ ለመዳን የበኩልህን ጥረት ሳታደግ እንዴት አድርጋ ልትረዳህ ትፈቅዳለች?" አለው ይባላል።

_እንግዲህ ያዕቆብም ለወንድሙ የላከው ገጸ በረከት ዕርቀ ሰላም ለማውረድ የራሱንም ጥረት የሚገልጥ እንጂ በጉቦነት ሊተረጐም የሚገባው አይደለም። ውንድም ለወንድሙ፡ እኅት ለእኅትዋ፡ ልጆች ለወላጆቻቸው /ወላጆች ለልጆቻቸው፡ ፍቅረኛም ለፍቅረኛ ወዘተ የሚያበረክቱት ስጦታ ፍቅርንና መተሳሰብን የሚገልጥ እንጂ ሌላ ትርጕም አይሰጠውም።) ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

## የያዕቆብ ትግል ከእግዚአብሔር ጋር ፡ (ሆሴዕ 12፡4)

22–32 ያዕቆብ ቤተ-ሰቡንና ጓዙን ጠቅልሎ፣የያቦቅን ወንዝ ካሻገረ በኋላ፣ እርሱ ብቻውን ከወንዙ ማዶ ቀረ (የጸሎት ቈይታ ለማድረግ ማለት ነው ) በዚያም፣ ሌሊቱ እስኪነጋ ድረስ እነሆ፣ አንድ ጐልማሳ በሕልም ዘፍጥ- 57 ሲታገለው አደረ። ጐልማሳው ለመሄድ ማልዶ ተነሣ፤ ያዕቆብ ግን፣ ‹‹ካልባረክኸኝ አልለቅህም›› ብሎ ያዘው። ያም ጐልማሳ ያዕቆብን፣ ‹‹ስምህ ማን ይባላል›› ብሎ ጠየቀው። ‹‹ያዕቆብ እባላለሁ›› ሲለው፣ ጐልማሳው መልሶ፤ ‹‹ስምህ ከእንግዲህ ወዲህ እስራኤል ይባል፤ ከእግዚአብሔርና ከሰውም ጋር ታግለህ አሸናፊ ሆነሃልና›› አለው።



## ፴፫ /33 ፡ ያዕቆብ ከዔሳው ጋር በሰላም ተገናኘ 1-7

ያዕቆብ ዓይኑን አቅንቶ ሲመለከት፡ እነሆ ዔሳውን ዐራት መቶ ሰዎችን አስከትሎ ሲመጣ አየው። ያዕቆብ ከቤተሰቡ ፊት ቀደም ብሎ በማለፍ ወደ ዔሳው እስኪደርስ ወደ ምድር ዝቅ ብሎ ሰባት ጊዜ ሰገደ። ዔሳውም ሮጦ አንገቱ ላይ ተጠምጥሞ ሳመው። ሁለቱም በናፍቆት ተላቀሱ። 8-11 ዔሳውም «የላክህልኝ ስጦታ ሁሉ ላንተ ይሁን ÷ እኔ ለራሴ ብዙ ሀብት አለኝ» አለው። ያዕቆብ ግን «በደግነት ተቀብለኸኝ የእግዚአብሔርን ፊት እንደማየት ያህል ፊትህን አይቻለሁና ÷ ያመጣሁትን በረከት ትቀበለኝ ዘንድ ፈቃድህ ይሁን» ብሎ ለመነው። (**ትርጓሚው፡** እነሆ ፡ እንግዲህ ያ ትግል አካላዊ የጕልበት መፈተኛ አልነበረም፡ በጸሎት መትጋትን፣ እግዚአብሔር አምላክ የሰጠው ተስፋ እስከሚፈጸም ያለማቋረጥ በጸሎት በመጠየቅ ፍጹም ተጋድሎ ማድረግን የሚያመለክት እንጂ። ማስረጃውንም በሉቃስ ወንጌል 18፡ 1-7 ከተጻፈው ምሳሌ መገንዘብ ይቻላል። ይኸውም ያች ባልዋ የሞተባት ችግረኛ ሴት እግዚአብሔርን የማይፈራ ፡ ሰውንም የማያፍረውን ዳኛ አላስቆም፡ አላስቀምጥ ብላ በየቀኑ ስለነዘነዘችው፡ ምንም እንኳ እግዚአብሔርን ባልፈራና ሰውንም ባላፍር ፡ ይህች ሴት በየቀኑ ስትነዘንዘኝ- ከምትኖር- ለመጨረሻ- ጊዜ- ፈርጃላ- ልገላገል-ብሎ እንደፈረደላት ጌታንችን ምሳሌ አድርጎ ሲያቀርበው ፡ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር ያላሠለሰ የጸሎት ተጋድሎ ማድረግ እንደሚገባን በግልጥ ተናግሯል። ‹‹አካሂድህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ሆኖ ከተገኘ ፡ ከጠላቶችህ ጋር እንኳ በሰላም አብረህ እንድትኖር ያደርጋል››-ተብሎ የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል የታመነ ነው (ምሳሌ 16፥ 7 )። እግዚአብሔር በተለይ ያዕቆብን በብዙ ፈተና ውስጥ በማሳለፍ፡ ፍጹም ትሑት፣ ጠንካራን አጥብቆ የሚጠላና ጥሩ የሰላም ሰው፣ ብልህ፡ አዋቂና የጸሎትም ሰው ያደረገው መሆኑን ከሃይማኖታዊ ሥነ ምግባሩ እናያለን ( ዘፍጥ 49፡ 5 -7 ።)

12-14 ስለዚህም እነሆ ሁለቱ ወንድማማቾች-የነበራቸውን ቂምና በቀል-ትተው፡ረስተዉት፡ በሰላም ተገናኝተው ናፍቆታቸውን ከተወጡ በኋላ፣ "እፊት -እፊት ሆኖ እየመራ፣ አብረው መንዝ እንዲችሉ፡ ዔሳው ለያዕቆብ ጥያቄ አቀረበ። ያዕቆብ ግን፣ ‹‹ለሚያጠቡ እንስሳትና ለግልገሎቻቸው፣ ለእንቦሶችም (ለእምቦሶች /ጥጆች) ጭምር በመጠንቀቅ በልጆች አቅም ልክ መራመድ ያስፈልገኛል፤ ስለዚህ ጌታዬ ቀድመህ እንድትሄድ እለምንሃለሁ›› አለው። (**ትርጓሜ፡** እንግዲህ ፣ ቤተ-ክርስቲያንም ከዚህ ዓይነቱ ጕዞ በምሳሌነት ልታስተምረው የሚገባ ታሪክ አለ። ይኸው ተተኪ ትውልድ ለማትረፍ፣ ከጐልማሶችና ከሽማግሎች ጋር አዳጊዎች ልጆችንም በእግዚአብሔር ቃል ደረጃ በደረጃ፡ ቀስ- በቀስ ለማነፅ እያስተማረች፣ እንደ ያዕቆብ፣ የትልል



www.ethiopianorthodox.org

*ቆችንና የትንንሾችንም ልጆች ጉዞ አስተባባሪ የሆነ የመንፈሳዊ ዕድገት ጥበብ ያስፈልጋታል ማለት ነው። ) በጣም ይሚገርመው በውጭ አህጉር የሚኖር ሕዝባችን ብዛት በሚሊዮን አሐዝ እያደገ ነው'። ሌሎቹ የግብፅ፡ የግሪክ፡ የአርመን፡ የሶርያ ወዘተ አብያተ ክርስቲያናት አገልጋዮች ካህናት የየሀገሩን ቋንቋ ጭምር በተለይ ከዓለም አቀፍ ቋንቋዎች እንግሊዝኛውን አጥንተው የራሳቸውን ልጆች ብቻ ሳይሆን የፈረንጅ ልጆችን ጭምር እያስተማሩ ቤተ ክርስቲያናቸውን የነጭና የጥቁር ሕዝብ መገኛ አድርገዋታል። የእኛዎቹ ካህናት ግን ዓለም አቀፍ ቋንቋ ማጥናት ነውር መሰሏቸው የፈረንጅ ልጆችን ማስተማር ይቅርና የራሳቸው ምእመናን ልጆችን ማስተማር አቅቷቸው እየጣሏቸው ሲሄዱ ኃላፍነት አይሰማቸውም። ከዚህም ችላ-ባይነት የተነሣ በእኛዪቱ ቤተ ክርስቲያን የፈረንጅ አማኞች መገኘት አልቻሉም። ሥርዓተ እምነታችንን ወደዉት ሳል አስተማሪ በማጣት ማለት ነው። እግዚአብሔር ይቅር ይበለን! )''''''''''*

18-–20 ያዕቆብ ወደ ከነዓን ምድር እንደ ገባ፣ ድንኳን የተከለበትን የእርሻ ቦታ የሴኬም አባት ከሆነው ከኤሞር ልጆች በመቶ በጎች ገዛው። በዚያም መሠዊያውን አቆሞ፣ ኤል-ኤሎሄ እስራኤል ብሎ ጠራው።

## ፴፬ /34፡ የዲና ክብረ-ንጽሕና መደፈር ያስከተለው እልቂት :

1-16_ልያ ለያዕቆብ የወለደችለት ዲና የዚያን አገር ሴቶች ልጆች ለማየት ወጣች።የአገሩ አለቃ /ባለብት የኬጢያዊዉ የኤሞር ልጅ ሴኬም ባያት ጊዜ ወደዳት፣ በማስገደድ ወስዶ ያለ ፍላጎትዋ፣ ክብረ ንጽሕናዋን በመድፈሩ ምክንያት፣ የያዕቆብ ልጆች እንደ ጥቃት ቈጥረውት በብርቱ ተናደዱ።የአገሩ ባላባት ኤሞር ግን ነገሩን በዕርቀ ሰላም ለማብረድ ፈልጎ፣ልጅቱን በሚስትነት ለልጁ ለሴኬም ፈቅደው እንዲሰጡለት አጥብቆ ጠየቀ። እነርሱ ግን፣ «ካልተገዘሩ ሕዝብ ጋር መጋባት አንሻም፣ ከተገዘራችሁ ግን፣ ልንጋባ እንችላለን» ሲሉ ለማዘናጋት ተፈጻሚነት የማይ ኖረው መልስ ሰጡት። 20--24 ኤሞርና ልጁ ሴኬም የግዝረትን ሥርዓት ለመፈጸም ተስማምተው፣ያገሩን ሕዝብ ሁሉ፣ዘመድ ወዳጅ ሳይቀር አስተባብረው፣«ከያዕቆብ ልጆች ጋር የጋብቻ ግንኙነት በማድረግ የሀብታቸው ሁሉ ተካፋዮች ለመሆን እንደ እነርሱ እንገዘር» ብለው በአዋጅ ነግረው አሳመኑ። ሁሉም ተገዘሩ፣ ታዲያ ተኝተው ሳሉ፣ ቍስሉ በሚጠናበት በሦስተኛው ቀን፣ ከያዕቆብ ልጆች ሁለቱ፣ ስምዖንና ሌዊ ሰይፍ-፡ ስይፋቸውን መዝዘው ገብተው የከተማውን ሕዝብ በሙሉ፣ ባላባቱን ኤሞርንና ልጁን ሴኬምን ጭምር አርደው፣ እኅታቸውን ዲናን ከሴኬም ቤት አውጥተው ወሰዱ።ሌሎቹም ወንድሞቻቸው እግር በግር ተከታትለው ገብተው፣ያለውን የሕዝብ ሀብት-ንብረቱን ሁሉ ዘርፈው ወሰዱ። በከተማና በውጭ ያለውን የበግና የፍየል መንጋ ፣



አህዮችንም ጭምር፣ ነድተው ሄዱ። ያዕቆብ ግን ይህን ሁሉ ሲሰማ፣ ደንግጦ ተቈጣ። *(ትርጓሜ፡ ያዕቆብ ከስደት መልስ ፍጹም ሰላማዊ ሆኖ ነበርና ነው።)* እነርሱ ግን፣ "ታድያ፣ድንግል የሆነች-እኅታችንን-እንደ-ጋለሞታ-መድፈር ይገባዋልን ?» አሉ፡

## ፴፭ /35፡ <u>ያዕቆብ ወደ ቤቴል ተመለሰ</u>

2—6 ያዕቆብ ቤተ-ሰቡን ሁሉ፣ «ባዕዳን አማልክትን ከመካከላችሁ አስወግዱ፤ ንጹሐን ሁኑ፤ልብሳችሁን እጠብ /ለውጡ» ብሎ አዘዘ። ያመጡለትንም አማልክት ሁሉ ተቀብሎ በሴኬም የአድባር ዛፍ ሥር ቀበራቸው።*(<u>ትርጓሜ፡ባዕዳን-አማልክት-መኖራቸ</u>ውን -በምን-እንዳወቀ ምሥ-ጢሩ ግልጥ አይደለም። ምናልባት ራሔል ካባቷ ቤት ሰርቃ ስለወሰደቻቸው የቤተሰብ አማልክት ጭምጭምታ ሰምቶ ይሆን?" ያም ሆነ ይህ ፡ ብቻ እንኳንም ቀበራቸው! አምልኮት እንዳይዛባ በቤተሰብ ላይ ዘወትር ቍጥጥር ማድረግ ተገቢ ነው። ለምሳሌ ጻድቅ ኢዮብ "ምናልባት ከልጆቼ አንዱ እግዚአብሔን በድሎ /አሳዝኖ ይሆን?" ብሎ በማሰብ ልጆቹን ከኃጢአት ለማንጻት ስለእያንዳንዳቸው ዕለት፡ ዕለት ለፈጣሪው መሥዋዕት ያቀርብ ነበር (ኢዮብ 1፡ 4_5 ። )*

5-7 ከዚያን ሁሉ ግድያ በኋላ፣ ያዕቆብና ልጆቹ ከሴኬም ተነሥተው ወደ ቤቴል ሲያመሩ፣ እግዚአብሔር በዙሪያው በነበሩ ሕዝብ ላይ ታላቅ ፍርሃትና ድንጋጤ ስለ አሳደረባቸው፣ ምንም ችግር ወይም አደጋ ሳያጋጥማቸው እርጭ ብለው ያለ ምንም ተቃውሞ በሰላም አሳለፉዋቸው። ያዕቆብና ቤተሰቡም ሁሉ ወደ ሎዛ ( ቤቴል) በደኅና መጡ፡ ፡ ያዕቆብ በዚያን ስፍራ መሠዊያ ሠራ፣ የቦታውንም ስም ኤል-ቤቴል ብሎ ጠራው። 8 የርብቃ-ሞግዚት ዲቦራ ስለ ሞተች ፣ በዚያው በቤቴል ፣ ከአድባሩ ዛፍ ሥር ተቀበረች። 9-15-እግዚአብሔር እንደ-ገና--በቤቴል-ተገልጦለት፡ያዕቆብን፣«እስራኤል»ብሎ ጠራውና ሲባርከው፣ «ሁሉን -ቻይ የሆንሁ አምላክ እኔ ነኝ፤ የብዙ ሕዝብና አሕዛብ ቤተሰብ አባት-ሁን፣ነገሥታት-ከአብራክህ_ይወለዳሉ»_አለው_ያዕቆብም እግዚአ ብሔር ከእርሱ ጋር በተነጋገረበት ቦታ የድንጋይ ሐውልት-ተክሎ፣ የመጠጥ-መሥዋዕትና ዘይት በእርሱ ላይ አፈሰሰበት።

**<u>የራሔል ሞት በወሊድ</u>፡** (16-21) ራሔል ባስጨናቂ የምጥ ፃዕር ተይዛ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ለሞት ስትቃረብ የተወለደውን ልጅዋን ቤንያኒ ብላ ጠራችው።አባቱ ያዕቆብ ግን፣ብንያም አለው። ራሔልም በዚያው የምጥ ፃዕር ሞተች፣ ያዕቆብም ወደኤፍራታ በሚወስደው መንገድ አጠገብ



www.ethiopianorthodox.org

ቀበራትና የድንጋይ ቍልል (ሐውልት) አቆሞላት፣ ከዚያ አልፎ ሄደ። **የይስሐቅ መሞትና የቀብሩ አፈጻጸም፡** 29 ይስሐቅ በአንድ መቶ ሰማኒያ ዓመቱ ሞተ ቀብሩም ልጆቹ ዔሳውና ያዕቆብ በተገኙበት ተፈጸመ።

**፴፮ /36 የዔሳው ዝርያዎች** ፡1-43 ይህ ምዕራፍ የያዘው አጠቃላይ ታሪክ፣በዔዶም ዔዶማውያን-ተብለው-የሚጠሩትን-የዔሳውን ዝርያዎች ሐረገ-ትውልድ አወራረድና ከጎሣ አለቅነት እስከ ልዑላን መሣፍንትነት ደረጃ ከፍ- ከፍ ብለው፣ሕዝብ እንኳ፣ንጉሣዊ አስተዳደር ከመመሥረቱ አስቀድሞ፣ሴይር ተብላ በምትጠራ አገራቸው በክብር ነግሠው እንዴት እንደ ኖሩ የሚያስረዳ ነው። ስከዚህም ዔሳው የዔዶማውያን አባት ተባለ።

**፴፯ /37፡ የዮሴፍ ሕልም በወንድሞቹ ላይ ቅናትን አሳደረ ፡**

1-2 ዮሴፍ የዐሥራ ሰባት ዓመት ልጅ በነበረበት ጊዜ፣ ከወንድሞቹ ጋር በጎችን ሲጠብቅ፡ በተለይ ከሁለቱ ገረዶች (ከባላና ከዘለፋ) የተወለዱት የያዕቆብ ልጆች የሚፈጽሙትን ጥፋት፣ለአባቱ ለያዕቆብ እያመጣ ይነግርነበር፤ ያዕቆብ ከሌሎች ልጆቹ ሁሉ አብልጦ ዮሴፍን ይወድደው ነበርና በልዩ ልዩ ቀለማት ያጌጠች እጀ-ጠባብ አሰፋለት። ስለዚህ፣ሌሎች ወንድሞቹ በእርሱ ላይ ብርቱ ጥላቻ አደረባቸው።5-8 ከዕለታት አንድ ቀን፣ ዮሴፍ ሕልም አየ፤ ይኸውም ከወንድሞቹ ጋር አብሮ በስንዴ ማሳ ላይ ተሠማርቶ ነዶ ሲያስሩ ነበር፤ የእርሱ ነዶ ቀጥ ብላ ትቆምና የሌሎቹ -የዐሥራ አንድ ወንድሞቹ ነዶዎች ቀርበው ሲሰግዱላት ያያል። ይህን በነገራቸው ጊዜ ወንድሞቹ «ምናልባት በእኛ ላይ ልትነግሥ ይሆናል» ሲሉ ተሣለቁበት። 9-11 በሌላ ቀን ደግሞ ፣እንደዚሁ ፀሐይ፣ጨረቃና ዐሥራ አንድ ኮከቦች ሲሰግዱለት በሕልሙ ማየቱን በተናገረ ጊዜ ፣አባቱ ያዕቆብ ገርሞት፣«እነሆ፣ እንግዲህ እኔ አባትህና እናትህ፣ ዐሥራ አንዱ ወንድሞችህም ጭምር እጅ በመንሣት እንሰግድልህ ይሆናል፤ለማናቸ-ውም-ይህን ሕልም-ማየትህን አትናገር» ብሎ አዘዘው። ዮሴፍ ግን በየዋህነት ይህን ሕልም ለወንድሞቹ ስለ ነገራቸው ብርቱ የቅናት መንፈስ-አደረባቸው።

**ዮሴፍ ተሸጦ ወደ ግብጽ ወረደ፡** 12-14 የዮሴፍ ወንድሞች የአባታቸውን መንጋዎች እየነዱ በሴኬም ተሠማርተው ነበር ። ወሬያቸውስለ ጠፋ፣ አባታቸው ያዕቆብ፣ «ሂድና እስቲ የወንድሞችህን ደኅንነት፣ የመንጋውን ሁኔታ ጠይቀህልኝ ና» ብሎ ልጁን ዮሴፍን ላከው። 15-17 ዮሴፍም በተላከ ጊዜ፣ ወንድሞቹ የተሠማሩበት ስፍራ ጠፍቶበት በበረሓ



ሲንከራተት አንድ ሰው (መሆኑን ሲነግረው፣ «ከዚህ ተነሥተው፣ ‹ወደ ዶታን እንሂድ› ሲሉ ነበር› አለው። 18-24 ዮሴፍ ወንድሞቹ ወደአሉበት ቦታ እንደ ደረሰ፣ ገና ከሩቅ ሲያዩት፣"እነሆ፣ ያ ሕልም አላሚ መጣ፤ እንግደለውና አባታችን አውሬ በልቶታል ብሎ ማመን እንዲችል፣ የፍየል ግልገል አርደን፣ ልብሱን በደም ነክረን፣ እንልክለታለን» ብለው ተነጋገሩ ። የሁሉ ታላቅ የሆነው ( በኵሩ ) ሮቤል ግን ፤ ዮሴፍን ለማዳንና ወደ አባቱ መልሶ ለመላክ ፈልጎ ስለ ነበር፣«መግደልስ አይገባንም፣ ባይሆን ከነሕይወቱ ጕድጓድ ውስጥ ብንጥለው ይሻላል» አላቸው። 25--28 በዚሁ ተስማምተው ጌጠኛ እጀ ጠባቡን አስወልቀው፣ ዮሴፍን ውኃ በሌለበት ደርቅ ጉድጓድ ውስጥ ጣሉትና ያመጣላቸውን ምሳ መብላት ጀመሩ።_ዓይናቸውን አቅንተው ሲመለከቱ፣ እስማኤላውያን የምድያም ነጋዴዎች ሲመጡ በሩቅ አዩ። በዚያን ጊዜ በተለይ ይሁዳ «ወንድማችንን ገድለን አሟሟቱን ብንሰውር ምን ይጠቅመናል፣ ይልቁንስ ለእነዚህ ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች ብንሸጠው ይሻላል-"የሚል-አሳብ አቀረበ። » ሁሉም በዚህ አሳብ ተስማምተው፣ሴፍን ከጉድጓዱ በማውጣት ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች በኻያ ጥሬ ብር ሸጡት። 20-30 ሮቤል ተመልሶ ሲመጣ፣ ዮሴፍ አለመኖሩን አይቶ በሐዘን ልብሱን ቀዶ፣ «ወይኔ እንግዲህ ምን ይበጀናል» እያለ በመጮኽ አለቀሰ። 31-36 ከዚያ በኋላ አንድ የፍየል ግልገል አረዱ ፤ የዮሴፍንም ዝንጉርጉር እጀ ጠባብ በዚያ ግልገል ደም ነክረው ለአባታቸው ለያዕብ ሲልኩለት፣«እነሆ፣ ይህን በደም የተበከለ ልብስ፣ በመንገድ ር ወድቆ አገኘነው፤ ምናልባት የልጅህ የዮ-ሴፍ ልብስ እንደ ሆነ እስቲ እየው» አሉት። ያዕቆብም የዮሴፍ ልብስ መህኑን ወዲያውኑ አውቆ፣ «ልጄን ክፉ አውሬ አግኝቶ፣ በጫጭቆ በልቶታል» አለ። ወዲያውም፣ልብሱን -ቀደደ፤ማቅ ለበሰ፣ከባድ ሐዘን ላይም ወደቀ። ልጆቹ ሁሉ ሊያጽናኑት አልተቻላቸውም። እስማኤላውያን ነጋዴዎችም ዮሴፍን ወደ ግብፅ አውርደው፣ ጳጢፋር ለሚባለው ለግብፅ ንጉሥ ፈርዖን የዘበኞች አለቃ ( *በሠላሳ ጥሬ ብር* ) ሸጡለት።

**፴፰ /38፡ የይሁዳና የትእማር ፈተና** -1-10 ዮሴፍ ተሸጦ ከሄደ በኋላ ይሁዳም ከወንድሞቹ ተለይቶ ለብቻው ለመኖር፣ ስሙን ኤራስ ብለው ወደሚጠሩ ዓዶሎማዊ ( የከነዓን ) ሰው ፡ዘንድ ሄደ፡ በዚያም ሴዋ ተብሎ የሚጠራ የአንድ ከነዓናዊ ሴት ልጅ አግብቶ ሲኖር፣ ዔር፣ አውና ንና፣ ሴሎም ተብለው የሚጠሩ ሦስት ወንዶች ልጆችን ወለደችለት፡ እነርሱም ባደጉ ጊዜ፣ ትእማር ተብላ የምትጠራ አንዲት ከነዓናዊት ልጃገረድ አጭቶ፣ ለበኵር ልጁ ለዔር አጋባው። ዔር ግን ክፉ ሰው ስለ ነበር



www.ethiopianorthodox.org

*(አረማዊት በመኾንዋ ስለ ተጸየፋት ነው ይባላል)* እግዚአብሔር ቀሥፎት ሞተ። ይሁዳ አውናን የተባለውን ሁለተኛውን ልጁን ጠርቶ፣ ትእማርን አግብቶ ልጅ እንዲወልድላትና ለወንድሙ ስም መጠሪያ የሚሆን ዘር ያቆምለት ዘንድ አዘዘው። አውናን ግን በምቀኝነት ለወንድሙ ዘር ማቆምን ስላልፈለገ፣ አብሯት እየተኛ ፈቃደ ሥጋውን ከፈጸመ በኋላ ዘሩን ወደ ውጪ ያፈስስ ነበር፣ በዚህም ምቀኝነት ምክንያት አምላክ ቀሠፈውና ሞተ። ከዚያም በኋላ ይሁዳ ትእማርን ለሦስተኛው ልጁ ለሴሎም እንዳይሰጣት 'ይሞትብኛል" ብሎ ስለ ፈራ፣ ለጋብቻ ያልደረሰ አስመስሎ፣ ‹ልጁ ሴሎም እስከሚያድግልሽ ድረስ ወደ ቤተ-ሰብሽ ተመልሰሽ ሂጂና በመበለትነት (ባል-አልባ) ሆነሽ ኑሪ» ብሎ አሰናበታት። 12--22 ትእማርም በዚህ አዝና ሳለች፣ ይሁዳ ሚስቱ ሞታበት መዋዕለ ሐዘኑን ሲጨርስ፣ «እነሆ፣ አማትሽ ይሁዳ በጎቹን ለማሸለት ወደ ቴምና ተራራ ሊወጣ ነው» ብለው ነገሩአት። ስለዚህ፣ የመበለትነት ልብስዋን ለውጣ፣ ፊትዋን በሻሽ ሸፍና ሄዳ ወደ ቴምና በሚወስደው መንገድ ዳር ተቀመጠች፡ይሁዳም ባያት ጊዜ፣ አመንዝራ ሴት መስላው ምራቱ መሆንዋን ሳያውቅ፣ ቀርቦ ፈቃዱን እንድትፈጽምለት ጠየቃት፤ እርስዋም «ምን ትሰጠኛለህ ?» ስትል ጠየቀችው። ይሁዳም፣ «አሁን ለጊዜው የያዝኩት ምንም ነገር የለም፤ በኋላ ግን አንድ የፍየል ጠቦት እልክልሻለሁ» አላት። እርስዋ ግን « እስከዚያ ድረስ ቀለበትህን፣አምባርህነ፡ የእጅህን በትር መያዣ አድርገህ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ» አለችው። እርሱም የጠየቀችውን ሁሉ ሰጥቶአት፣ ፈቃዱን ፈጽማለት ሲሄድ፣እርስዋም-ወደ ቤትዋ ተመልሳ ሂዳ፣ልብስዋን ለውጣ፣ፊትዋን-ገልጣ የመበለትነት ልብስዋን ለብሳ እንደ ተቀመጠች፣ ወዳጁ የሆነ አንድ አዶለማዊ ሰው፣ ይሁዳ የላከላትን የፍየል ጠቦት ተሸክሞ መጥቶ፣ « በቴምና መውጫ መንገድ ዳር ተቀምጣ የነበረችው የዚያች ዘማዊት ሴት ቤትዋ የት ነው?» እያለ መጠየቅ ጀመረ። የሰሙት ሰዎች ሁሉ፣«በእኛ መንደር ውስጥ ዘማዊት ሴት የለችም» እያሉ አፌዙበት፤ ወደ ይሁዳም ተመልሶ ሄዶ፣ «ያልካት ሴት አልተገኘችም» አለው። ይሁዳም «ካልተገኘች ተዋት፤ የሰጠሁአትን መያዣ ብቻ ይዛ ትቅር » አለ። 2-430 ከሦስት ወር በኋላ፣ «ምራትኽ ትእማር በዝሙት ፀነሰች እኮ» ብለው ለይሁዳ ነገሩት፤ እርሱም፣ «ከቤት አውጥታችሁ በእሳት አቃጥላችሁ ግደሉአት» ሲል አዘዘ። ሊገድሉዋትም የተላኩ ሰዎች-መጥተው፣ውሳኔውን በነገሯት ጊዜ፣«እኔ የፀነስሁት-ከማን ሆነና? ይህን መያዣ ሁሉ ወስዳችሁ አሳዩት፤ እኔ የፀነስሁት የነዚህ መያዣ ዕቃዎች



ባለቤት ከሆነው ሰው ነው» አለቻቸው። ይሁዳ ያንን ሁሉ አይቶ የሰጠችውን መልስ ሲሰማ «ትእማር ረታችኝ፤ከእኔ ይልቅ እርስዋ-እውነተኛ ሆናለች»አለ። ከዚያ በኋላ ግን አልደረሰባትም። የእርግዝናዋም ወራት ከተፈጸመ በኋላ፣ ፋሬስና ዛራ የተባሉትን መንታ (ሁለት) ወንዶች ልጆችን ወለደችለት። (***ትርግሜው፡*** *ዮሴፍ ተሽጦ ከወንድሞቹ እንዲለይ-አሳብ ያቀረበ ይሁዳ ስለነበር የእግዚአብሔር ጥበብ ደግሞ ይሁዳን ከወንድሞቹ ተለይቶ በእምነት ከማይመስሉት ባዕዳን አረማውያን ሕዝብ ጋር ብቻውን- የመኖር ዕድል እንዲገጥመው አድርጓል ማለት ነው ። በመሠረቱ የትእማርስ ፍላጎት ምን ነበር ? ዝሙት ወይስ የገንዘብ ፍቅር ነበርን ? ሁለቱንም አልፈለገችም። እርስዋን አሳዝኖአት የነበረው ዋና ነገር ታላቁ መሲሕ ( ክርስቶስ ) ከነገደ ይሁዳ ዘር እንደሚወለድ ለአብርሃም፡ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የተነገረውን ተስፋ (ትንቢት) ሰምታ ስለነበር፣«ከዚህ ቤተ-ሰብ ተጋብቼ እንዴት ልጅ ሳልወልድ እቀራለሁ? » የሚል ይመስላል ፡ለዚህም ማስረጃው እነዚያ ሁለት ልጆችዋ በጌታችን፡ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሐረገ -ትውልድ ውስጥ ገብተው መቈተራቸውን በማቴዎስ ወንጌል ምዕ 1-3 የተጻፈው ቃል ያስረዳል። ጌታችን የተወለደ ከቤተ-አይሁድ ብቻ ሳይሆን ከአረማውያንም ጭምር ነውና። ያን ዓይነት ድርጊት ገንዘብ ለማግኘት በማሰብ እንዳልፈጸመችው ዘማዊት ብሎ ከይሁዳ የተላከላትን የፍየል ጠቦት ባለመቀበልዋ ይታወቃል።)* """"""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""

## ፴፱ /39 <u>ዮሴፍ በባርነት አገልግሎት ያሳየው ታማኝነት</u>

2- 6 እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ስለነበረ፣ የሚሠራውን ሁሉ በረድኤቱ ባረከለት ። ከዚህም የተነሣ፣ ግብፃዊ አሳዳሪ- ጌታው እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንዳለና ሥራውንም ሁሉ እንደባረከለት አይቶ፣ዮሴፍን የቤት-ንብረቱ ሁሉ የበላይ ኀላፊ (መጋቢ) አድርጎ ሾመው። እግዚአብሔር የግብፃዊዉን ቤት በዮሴፍ ምክንያት ስለ ባረከለት፣ ሀብቱ በውስጥም በውጭም የተትረፈረፈ ሆነለት ። ከዚህም የተነሣም፣ ያለውን ሀብት-ንብረቱን ሁሉ ለዮሴፍ አስረከበው፤ ከሚበላው እንጀራ በቀር-የሚያውቀው ነገር አልነበረም። (***ትርጓሜ፡*** *እንደዚህ ያለውን በረከት ለማግኘት የሚፈልግ ማንኛውም አማኝ ሰው እንደ=ዮሴፍ-ብርቱ--=የማይናወጥ-ታማኝ--ሆኖ-መገኘት--ይጠበቅበታል።)* """"""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""



www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ ሁሉ የታማኝነት ሥራ ጋር ዮሴፍ ፊቱ የሚያምር መልከ-ቀና ሰው-ነበር። 9 በዚሁ-ምክንያት የግብጻዊ አሳዳሪው ሚስት በዮሴፍ ላይ የዝሙት ዓይንዋን ጣለችበት። ከእርስዋ ጋር ዝሙት እንዲፈጽምም፣ በየቀኑ ትፈታተነው ጀመር። ዮሴፍ ግን፣ «ይህን ዓይነት ክፉ በደል እንዴት አድርጌ በእግዚአብሔር፡ ፊት እፈጽማለሁ፣ጌታዬ በቤት-ንብረቱ ላይ ሾመኝ እንጂ፣ በአንቺ ላይ ሥልጣን አልሰጠኝም» ይላት ነበር። 11-12 ከዕለታት አንድ ቀን፣ ዮሴፍ በቤት ውስጥ የሚሠራውን ሁሉ አከናውኖ ሊወጣ ሲል፣ ከእርስዋ ጋር እንዲተኛ በመጋበዝ ልብሱን ጨምድዳ ብትይዘበት ትቶላት ሸሸ። ( « ከክፉ የጐልማሳነት ምኞት ሸሽ /ራቅ» ( 2 ጢሞ 2፡ 22 ) 19-23 ከዚያን በኋላ ተስፋ ስለቈረጠች ባልዋ ሲመጣ፣ የራስዋን ጥፋት ወደ ዮሴፍ በማዛወር፣ «ያመጣኸው ይህ /አገልጋይ /ባሪያ፣ ደፍሮ መዘባበቻ ሊያደርገኝ ፈልጎ እኔ ወደ አለሁበት ክፍል ገባ፣ እኔ ግን ድምፄን ከፍ አድርጌ ስጮኽበት፣ ልብሱን በእጄ ላይ ጥሎ ወደ ውጭ ሸሸ» አለችው።አሳዳሪውም ዮሴፍን ወስዶ ወህኒ ቤት አስገባው።ዮሴፍ-ግን፣አሁንም እግዚአብሔር-ጸጋና-ሞገስን-ሰጥቶ የሚሠራውን ሁሉ ስለባረከለት፣በወህኒ ቤት ኀላፊውም ዘንድ ባለሟልነትንና፣ልዩ ሞገስና መወደድን ስላስገኘለት፣ በእስረኞቹ ላይና በሚሠራውም ተግባር ላይ ሁሉ ረዳት-ኃላፊ አድርጎ መደበው።

## ፵ /40. <u>የሁለት እስረኞች ሕልምና ትርጓሜው፡</u>

1-8 የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን በወይን ጠጅ አሳላፊዎች አለቃና በእንጀራ ቤት ኀላፊዎች አለቃ ላይ ተቈጥቶ፣ ሁለቱንም ሰዎች ወደ ወህኒ ቤት ልኮአቸው ነበር። የወህኒ ቤቱ አዛዥ እነዚህን ሁለቱን የቤተ- መንግሥት ሰዎች፡ ዮሴፍ ወዳለበት ወህኒ ቤት አስገባቸው። ሁለቱንም ሰዎች፣ ዮሴፍ በመከባከብ እንዲጠብቃቸው አደረገ። በአንድ ሌሊት ሁለቱም ለየራሳቸው ሕልም አዩ፤ ግን የሚተረጉምላቸው አጥተው በማዘንና በመተከዝ ላይ እንዳሉ፣ ዮሴፍ ተመልክቶ፣ «ምን ሆናችኋል ? ፊታችሁ ጠቍሮ እንዲህ የተከዛችሁበትና ያስጨነቃችሁስ ነገር ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፣ «ሕልም አይተን የሚተረጉምልን አጣን» ብለው መለሱለት፤ ዮሴፍም፣ «ሕልምን የሚተረጉም እግዚአብሔር እንጂ መቼ ሰው ነው?! ያያችሁትን ሕልም እስቲ ንገሩኝ» አላቸው። የወይን ጠጅ አሳላፊዎች አለቃም፣ «ሦስት የወይን ዘለላና የንጉሥ ፈርዖንን ጽዋ በእጄ ይዤ ነበር፣ ወይኑንም በጽዋው ውስጥ ጨምቄ ለንጉሡ ስሰጠው አየሁ» በማለት



ሕልሙዘን ነገረው። ዮሴፍም እንዲህ ሲል ተረጐመለት፤ «ሦስት የወይን ዘለላ የተባሉት ሦስት ቀኖች ናቸው፤ ከሦስት ቀኖች በኋላ ንጉሡ ወደ ቀድሞ ሹመትህ ይመልስሃል። እንግዲህ ይህ መልካም ነገር በተፈጸመልህ ጊዜ እኔን አትርሳኝ፣ ለንጉሡ አስታውሰህ ከዚህ ወህኒ ቤት እንድወጣ አድርገኝ፤ የታሰርኩት ያለምንም በደል ነውና» ሲል ተማጥኖት ነበር። 16-17 የእንጀራ ቤት ኀላፊዎች አለቃ፣ የወይን ጠጅ ኀላፊዎች አለቃ ያየውን ሕልም ጥሩ አድርጎ እንደ ተረጐመለት ባየ ጊዜ፣ የራሱን ሕልም ሲነግር እንዲህ አለ፤‹ልዩ፡ ልዩ የምግብ አይነት ያለባቸውን ሦስት ሞሰቦች በራሴ ላይ በማነባበር ተሸክሜ ነበር፤ የሰማይ ወፎች መጥተው ተከፋፍለው በልተው ሲጨርሱት አየሁ»። ዮሴፍም ሲተረጉምለት «ሦስት ሞሰብ ሦስት ቀን ማለት ነው፤ ከሦስት ቀን በኋላ ንጉሥ ፈርዖን በስቅላት ሞት እንድትቀጣ ያደርጋል፤ ሥጋህንም የሰማይ አሞሮች በተሰቀለበት እንጨት ላይ ይበሉታል 'አለው። 20-22 ልክ ዮሴፍ በተረጐመላቸው ዓይነት የሁለቱ ሰዎች ሕልም ተፈጸመ፤ የወይን ጠጅ ኀላፊዎች አለቃ ወደ ሹመቱ ተመለሰ። ነገር ግን ዮሴፍን ሳያስታውሰው ረስቶት ቀረ። የእንጀራ ቤት ኀላፊዎች አለቃም ቅጣቱ በስቅላት ሞት ተፈጸመበት ።*(<u>ትርጓሜው</u>፡ ዮሴፍ የወይን ጠጅ ኀላፊዎችን አለቃ ሕልም ከተረጐመ በኋላ፣ ለንጉሡ ለፈርዖን አስታውሶ ከወህኒ ቤት ያወጣው ዘንድ ተማጥኖት ነበር። የወይን ጠጅ አሳላፊዎች አለቃ ግን፡ ዮሴፍን ረስቶት ስለ መፈታቱ ጉዳይ ሳያስታውስለት ሁለት ዓመት አለፈ። ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት፣ ዮሴፍ አሁንም ፍጹም እምነቱን በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ ፈንታ፣ የሰውን እርዳታ ወደ መተማመን ደረጃ ዝቅ ብሎ በመገኘቱ ነበር። « በሰው የሚታመንና ሥጋ ለባሽን አለኝታው በማድረግ የሚመካ ቢኖር ርጉም ይሁን» ኤር 17፡ 5 ) »። 'ሌላው አስደናቂ ነገር፡ የጥንት ጻድቃን ብሊት በሕገ ልቡናም ሆነ በዘመነ ብሉይ የነበሩ ደጋግ ሰዎች ሁሉ እንደ ማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር ወደ ሲኦል መውረድ አልቀረላቸውም ነበር። ነገር ግን ኢረከቦሙ ሥቃየ ኃጥእ ለግሙራ እስመ እደ እግዚአብሔር ላዕሌሆሙ=በሌሎች ዓመፀኞች ላይ የሚደርስ ሥቃይ እላገኛቸውም ፤ የእግዚአብሔር እጅ በነርሱ ላይ ነበረችና " ተብሎ ተጽፏል። ታዲያ ዮሴፍም እንደማንኛውም ተራ ወንጀለኛ ወህኒ ቤት ወረደ ተባለ እንጂ የእግዚአብሔር ጸጋና ረድኤት ስላልተለየው የወህኒ ቤቱ ረዳት ኃላፊ ሆኖ ተሾሞ ያለምንም ችግር ይኖር ነበር። "ኢኀደረ ዮሴፍ ዘእንበለ ሢመት=ዮሴፍ ያለ ሹመት -ያደረበት-ጊዜ የለም" ተብሎለታልና።)* ""



www.ethiopianorthodox.org

## ዘፍ /41. ፈርዖን ያየው ሕልምና ትርጓሜው :

1-7 ይህ ሁሉ ከተፈጸመ ከሁለት ዓመት በኋላ፣ የግብጽ ንጉሥ ፈርዖን
ሁለት ዓይነት ሕልሞችን አየ። በመጀመሪያ ሕልሙ፣በዓባይ ወንዝ
ዳርቻ ሰባት የወፈሩና የሰቡ ላሞች ከወንዙ ወጥተው ሣር ሲግጡ፣ እንደ
ገና ሌሎች የከሱናአጥንታቸው ያገጠጠ ሰባት ላሞች ከዚያው ወንዝ
ወጥተው እነዚያን የወፈሩና የሰቡ-ሰባት ላሞችን ከዋጡዋቸው በኋላ፣
ምንም የቀመሱ ሳይመስሉ እንደ ከሱ መቅረታቸውን ያያል። እንደ
ገና ተኝቶ ሳለም በሁለተኛው ሕልሙ ደግሞ፣ በአንድ አገዳ ላይ
ሰባት የሚያማምሩ ፍሬያማ የስንዴ እሸት ዛላዎች ያያል፤ ወዲያውኑም
በምሥራቅ ነፋስ የተመቱና የሰለቱ ሌሎች ሰባት የስንዴ እሸት ዛላዎች
ወጥተው፣ እነዚያን እጅግ ያማሩ የስንዴ እሸት ዛላዎች ለቃቅመው
በልተው (ውጠዋቸው) ምንም የቀመሱ ሳይመስሉ እንደ ሰለቱ ሆነው
ሲቀሩ አየ። 8 ከእንቅልፉም ሲነቃ ሕልም መሆኑን አወቀ። ሲነጋም
መንፈሱ ታውኮ፣ ትርጉሙን ለማወቅ ወደ ግብጽ የሕልም መተርጉማንና
ወደ ጠቢባን አስማተኞች ሁሉ ዘንድ ልኮ አስጠራቸውና ሕልሙን
ነገራቸው፤እንነሱ ግን ሊተረጉሙለት አልቻሉም። 9-13 በዚህ ጊዜ፣
በወህኒ ቤት ሳለ ዮሴፍ ሕልሙን የተረጐመለት ያ የወይን ጠጅ
አሳላፊዎች አለቃ ፈርዖንን እንዲህ አለው፤ ‹‹ንጉሥ ሆይ፣ የሠራኂትን
በደል አሁን አስታወስሁ። አንተ በእኔና በእንጀራ ቤት ኀላፊው ላይ
ተቈጥተህ እንድንታሰር ባደረግህ ጊዜ፣ በወህኒ ቤት ሳለን፣ ሁለታችንም
ያየነውን ሕልም የተረጐመልን ዮሴፍ የሚባል አንድ ዕብራዊ እስረኛ እንደ
ነበር ትዝ ይለኛል››። 14--24 ንጉሡም ይህን ሲሰማ ወዲያውኑ ዮሴፍን
ያመጡለት ዘንድ ትእዛዝ ሰጠ። ዮሴፍ ከእስር ቤት ወጥቶ፣ ጠጉሩን
ተላጭቶ፣ ልብሱን ለውጠውለት በቀረበ ጊዜ፣ ፈርዖን ‹‹ እነሆ፣ ሕልምን
አየሁ፤ የሚተረጕመውም አልተገኘም፤ አንተ ግን፣ ሕልምን መተርጐም
እንደምትችል ሰምቻለሁ›› አለው። ዮሴፍ ግን፣ ‹‹ሕልምን የመተርጐም
ጥበብ የሚገኝ ከእግዚአብሔር እንጂ፣ ከእኔ እይደለም፡ እግዚአብሔር
ራሱ ለንጉሡ ለፈርዖን ቀጥተኛውን መልስ ይሰጣል›› አለው።

25-36 ፈርዖንም ያየውን ሕልም ሁሉ ከነገረው በኋላ፣ ዮሴፍ እንዲህ
አለው፤‹‹የሁለቱም ሕልሞች ትርጉም ወይም ፍችው አንድ ዓይነት ነው።
እግዚአብሔር ሊፈጽመው ያቀደውን ሁሉ ለፈርዖን ገልጦለታል። ሰባቱ
የወፈሩና የሰቡ ላሞች እንዲሁም ሰባቱ የሚያምሩ ፍሬያማ የስንዴ እሸት
ዛላዎች በአንድነት ሰባት የጥጋብ ዓመታት ናቸው። ሰባቱ የከሱና



መልካቸው የሚያስቀይም ላሞች ደግሞ ከሰለቱት ከሰባቱ የስንዴ እሸት
ዛላዎች ጋር አንድ ወገን፣ ሰባት የረኃብ ዓመታት ናቸው።ከሰባቱ የጥጋብ
ዓመታት በኋላ፣ ያን ሁሉ የጥጋብ ዘመን የሚያስረሱ ሰባት የረኃብ (የቀጠና)
ዓመታት ይመጣሉ።ሕልሙ ሁለት ጊዜ የተደገመበት ምክንያት ነገሩ መምጣቱ
የማይቀር፣ በእግዚአብሔር ዘንድየተወሰነ፣ በቅርብ ጊዜ በቀጥታ ሊፈጸም
የሚችል መሆኑን ያሳያል። ንጉሥ ሆይ፣ እንግዲህ፣ ከዚያ ሁሉ ችግር ለመዳን
ጥበብና ማስተዋል ያለው ሰው ተመርጦ፣ በሞላ አገሪቱ የበላይ ባለሙሉ
ሥልጣን እንደ ራሴ ሆኖ ይሾም። በሰባቱ የጥጋብ ዓመታት ከሚመረተውም
የእህል ሰብል ሁሉ ከአምስት አንዱን እጅ በመሰብሰብና በየከተማው
ታላላቅ የእህል ማከማቻ ጎተራዎችን በማሠራት ለሰባት ዓመት
የሚተርፍ በቂ መጠባበቂያ ቢዘጋጅ አገሪቱ ከጥፋት፣ ሕዝቡም ከእልቂት
ይድናናሉ"። 37-38 የተነገረውም ቃል ሁሉ በፈርዖንና በመኳንንቱ ፊት
መልካም ሆኖ ታየ፤ ፈርዖንም መኳንንቱን ሁሉ፣ ‹‹በእውነት
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን እንዲህ ያለ አስተዋይ ሰው ማግኘት
ይቻለናልን?›› ሲል ጠየቃቸው።

### ዮሴፍ ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ ሆነ

39-43 ፈርዖን ወደ ዮሴፍ ተመልሶ እንዲህ አለው፣ ‹‹እግዚአብሔር ይህን
ምስጢር ገልጦልሃል፣ ስለዚህ፣ በአገሬ ላይ ባለ-ሙሉ ሥልጣን እንደ ራሴ
( ጠቅላይ ገገር ) አድርጌ ሾሜሃለሁ። ሕዝቤም ሁሉ ለቃልህ ይታዘዛል፤
እኔም የምበልጥህ በዚህ ንጉሣዊ ዙፋኔ ብቻ ነው"። ንጉሡ ፈርዖን
ቀለበቱን ከእጁ አውልቆ በዮሴፍ ጣት ላይ አደረገለት፤ ነጭ ሐር (ከተልባ
እግር የተሠራ) ልብስ አለበሰው፤ በአንገቱ ላይ የወርቅ ማርዳ) ዝርግፍ
ወርቅ አሰረለት፡ በንጉሡም ሁለተኛ ሠረገላ እንዲቀመጥ አድርጎ፣
‹‹እጅ ንሡ፤ ስገዱ›› እያለ እፊት-ፊት የሚሄድ አዋጅ ነጋሪ ዮሴፍ
በበመላዋ የግብጽ ምድር ላይ የተሾመ መሆኑን አበሠረ።
44--45 ፈርዖንም ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ ‹‹እነሆ፣ እኔ ፈርዖን ነኝ፤
በመላዋ የግብጽ ምድር ያለ አንተ ፈቃድ ማንም ሰው እጁንም ሆነ እግሩን
ማንሣት አይችልም›› ።ንጉሥ ፈርዖን ለዮሴፍ፣‹‹ጻፍናት ፐእናህ›› የሚል
የክብር መጠሪያ ስም አወጣለት። የሄልዮቱ ከተማ ካህን የጳጥፌራ ልጅ
የሆነችውን አስኔትንም በሚስትነት እንድ ትዳርለት አደረገ። ዮሴፍ
በፈርዖን ፊት ተሾሞ ማገልገል ሲጀምር፣ ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ነበር።
ከተሾመበት ጊዜ ጀምሮ፣ በግብጽ ምድር ሁሉ እየተዘዋወረ- በሰባቱ-
የጥጋብ ዓመታት ከተመረተው የእህል ሰብል ካምስት አንዱን እጅ
እየሰበሰበ በየከተማው ሊሠፈርና ሊመጠን የማይችል እጅግ ብዙ ሀብት



www.ethiopianorthodox.org

በማከማቸት አደለበ። 50-56 አስኔትም ለዮሴፍ ሁለት ወንዶች ልጆችን ወለደችለት፤ የመጀመሪያ ልጁን ምናሴ ብሎ ጠራው። "በስደት አገር እግዚአብሔር ሐዘኔን እንድረሳ አደረገኝ ሲል። ሁለተኛውንም ኤፍሬም ብሎ ጠራው፣ እግዚአብሔር በመከራዬ አገር ፍሬ ሰጠኝ" ሲል። ዮሴፍ የተረጐመውም ሕልም ተፈጸመ። የረኃብ ዘመን መምጣት ጀመረ። ስለዚህም፣ በየከተማው የተከማቸው የእህል ሰብል ጎተራ ሁሉ ተከፍቶ ለአገሪቱ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን፣ ከዓለም ዙሪያ ለሚመጡ ሕዝቦችም ሁሉ እንዲሸጥላቸው ተደረገ።

## ፵፪ /42 የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብጽ መጡ

1--17 ያዕቆብ በግብጽ እህል መኖሩን ሰማ፤ ታዲያ ብንያምን ብቻ እቤት በማቆየት ዐሥሩን ልጆቹን፣«እህል ሸምታችሁ አምጡልን» ብሎ ላካቸው። ዮሴፍ በዚያች አገር ጠቅላይ ገዢ ሆኖ እህል እያሠፈረ ያሸጥ ነበርና ወንድሞቹ መጥተው፣ ግንባራቸውን መሬት አስነክተው በመስገድ እጅ ነሡት። ዮሴፍም እጅ አነሣሣቸውን በማየት ሕልሙን አስታወሰ። እነርሱ ስለተለወጠባቸው፣ ሊያውቁት አልቻሉም፤ እርሱ ግን ወዲያውኑ ስለአወቃቸው፣ «እናንተ ደግሞ ከየት የመጣችሁ ናችሁ?» ሲል (በቍጣ አነጋገር) ጠየቃቸው። እነርሱም፣ «እኛ አገልጋዮችህ እህል ለመሸመት ከከነዓን አገር የመጣን ነን» አሉት። እርሱም 'እናንተ ሰላዮች ናችሁ፡ የመጣችሁበትም ምክንያት የሀገራችንን ሁኔታ ለማጥናት ነው" ሲላቸው "እኛ አገልጋዮችህ ሰላዮች አይደለንም። የመጣነው ስንዴ ለመሸመት ነው። ሁላችንም በከነዓን የሚኖር የአንድ ሽማግሌ ሰው ልጆች ነን። እንዳውም ዐሥራ ሁለት ነብርን። አንድ ወንድማችን ብቻ በሕይወት የለም። ሌላው የሁላችን ታናሽ የሆነው ከአባታችን ጋር በቤት ይገኛል" አሉት። ዮሴፍም መልሶ "ሁላችንም የአንድ ሰው ልጆች ነን ማለታችሁ ራሱ ውሸት ስለሆነ ሰላዮችመሆናችሁን ይመሰክርባችኋል። እኔ ግን አልለቃችሁም» ብሎ በፈርዖን ስም ማለ። _ቀጥሎም፣ «በቤት አለ የምትሉትን ወንድማችሁን እስከታመጡ ድረስ ከዚህች አገር መውጣት ከቶ አይፈቀድላችሁም፤ ታስራችሁ ትቈያላችሁ» ብሎ ለሦስት ቀን ያህል በግዞት እንዲቈዩ እስር ቤት አስገባቸው። _8-24 በሦስተኛው ቀን ዮሴፍ እንዲህ አላቸው፤ «እነሆ እኔ፣ እግዚአብሔርን የምፈራ ሰው ነኝ፤ በአንድ ውለታ ሕይወታችሁን ለማዳን አቅጃለሁ፤ ይኸውም ታማኞች መሆናችሁ እንዲታወቅ "በቤት አለ»፤ ያላችሁትን ታናሽ ወንድማችሁን እስምታመጡት ድረስ፣ ከእናንተ አንዱ ብቻ፣ በመያዣነት ስም እዚህ ታስሮ ይቈያል፤ ሌሎቻችሁ ግን እህሉን ጭናችሁ ለተራቡ ዘመዶቻችሁ አድርሱላቸው ። በቤት አለ



ያላችሁትን ያን ታናሽ ወንድማችሁን ይዛችሁልኝ ስትመጡ፣ ታማኞች መሆናችሁ ይረጋገጥና ከሞት ትድናላችሁ»። ሁሉም እርስ በርሳቸው ተያይተው፣ «እነሆ፣ በእውነት በወንድማችን በዮሴፍ ላይ ስላደረስንበት ክፉ በደል ተገቢውን ቅጣት እየተቀበልን ነው፤ እኛን በመማጠን ነፍሱ ስትጨነቅ አይተን እንኳ አልራራንለትም ነበርና ይህን ሁሉ መከራ አመጣብን» ተባባሉ። _ሮቤልም መልሶ እንዲህ አላቸው፤«እኔማ በዚያ ልጅ ላይ ክፉ ነገር እናድርግበት ብዬ ተናግሬ ነበር። እናንተ ግን አትሰሙም። ለዚህም እነሆ አሁን፣ የወንድማችን ደም እኛን እንደሚፈላለገን ተመልከቱ» አላቸው፡ ይኸውም ሁሉ ሲሆን፣ ዮሴፍ የሚሰማቸው አልመሰላቸውም፤ በመካከላቸው አስተርጓሚ ነበርና። ከእነርሱም ዘወር ብሎ አለቀሰ፡ እንደ ገና ተመልሶ መጥቶ ከመካከላቸው ስምዖን የተባለውን ነጥሎ ወስዶ አይናቸው እያየ አሰረው።

*(**ትርጓሜ፡** ከመካከላችው አንዱ /ዮሴፍ ብቻ በሕይወት አለመኖሩን ወንድሞቹ የተናገሩትን ታሪክ አንድ ኢትዮጵያዊ ባለ ቅኔ አመሥጥረው ሲናገሩ "ሞተ ዮሴፍ አኀዊሁ ነገርዎ ለዮሴፍ=የዮሴፍ ውንድምች የዮሴፍን መሞት ለራሱ ለዮሴፍ ነግሩት" ብለዋል ። ዮሴፍ ለውንድምቹ የታየበትም ሁኔታ ልክ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ኢማሁስ ጕዞ ጀምረው ለነበሩት ሁለት አርድእት በእንግዳ አምሰል የታየበትን ዓይነት ይመስላል። እርሱ አውቋቸው ሳለ እነርሱ ግን እንዳይውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር" ይላል ሉቃስ 24፡ 13 -33። """""""" ምን ጊዜም ጌታችን ስለ መከራ መስቅቀሉ ከምናስብ አማኞች ጋር ነው። እኛ መከራ መስቀሉን በማሰብና በማሰላሰል ስንጨነቅ ስናስብ እርሱ ባልጠበቅነው መንገድ ከነፍሳችን ጋር ሆኖ ጸሎታችንን ይሰማል፡ አሳባችንንና ለርሱ ያለንን ፍቅር ሁሉ ይመዝናል።*

*_ዮሴፍ ከሌሎቹ ነጥሎ ስምዖንን አስሮ ያቈየበት ምክንያት፣ ረኃብ ፀንቶበት፣ ከሌሎቹ ይልቅ ከስቶ ስላየው፣ እየገገመ እንዲቈይ ለማድረግ ነው። አንድም ደግሞ ዮሴፍ ከወንድሞቹ፣ ተነጥሎ በተሸጠ ጊዜ፣ስምዖን ከሌሎቹ ወንድሞቹ የከፋ ጭካኔ ታይቶበት ስለ ነበር፣ እርምት ለመስጠት ነው ይባላል። በነቢዩ ሆሴዕ መጽሐፍ 5፡15 «በደላቸውን አውቀው ንስሐ እንዲገቡና በመፀፀት እንዲታረሙ፣ ይህ ሁሉ ደረሰባቸው"ተብሎ ተጽፏል።* 25፡ ዮሴፍ መጋቢውን ጠርቶ እንዲህ ሲል አዘዘው፡ «ለእነዚህ ሰዎች በየስልቻቸው ሁሉ ሞልተህ እህል ሸጥላቸው፡ገንዘባቸውን ግን መልሰህ በየስልቻቸው አፍ ላይ ቋጥርላቸው፤ለመንገድ የሚሆን ስንቅ

www.ethiopianorthodox.org

ጨምረህ ስጣቸው››:: 26 እነርሱም አህዮቻቸውን ጭነው የመል:: ጉዞአቸውን ቀጠሉ ::

**ሟ፫ /43. የዮሴፍ ወንድሞች ብንያምን ይዘው ወደ ግብጽ ተመለሱ:-**

1-15 ያዕቆብ፣ "እንደ ዮሴፍ ይጠፋብኛል" ብሎ ስለፈራ፣ የስምዖን መታሰር አሳዝኖት ብንያምን ለመስደድ ፈቃደኛ አልነበረም:: ስለዚህ፣ ሮቤል *(ፈሊጥ በጎደለው አነጋገር)* "ብንያምን በእኔ ኃላፊነት ላከው፣ወደ አንተ መልሼ ማምጣት ባልችል፣ የእኔን ሁለት ወንዶች ልጆች ወስደህ ግደላቸው›› ብሎ ነበር (ምዕራፍ 42 ፥ 37:: ይሁዳ ግን አባቱን እስራኤልን እንዲህ አለው፤ ‹‹እኔ ዋስ እሆናሁ፣ ልጁን ከእኔ ጋር ስደደው፤ እኔ መልሼ ሳላመጣው ብቀር ግን፣በፊትህ በደለኛ ሆኜ ልቅር››:: ያዕቆብም በዚህ አሳብ ተስማምቶ እንዲህ አለ፣ ‹‹ለዚያ አገረ ገዢ እጅ-መንሻ ጥቂት በለሳን፣ ጥቂት ማር፣ ሽቱ፣ ከርቤ፣ ቴምርና ለውዝ ውሰዱለት:: ሁሉን የሚችል አምላክ ስምዖንና ብንያምን በደህና እንዲመለሱ ያድርግ"::

***(ትርጓሜ:*** እዚህ ላይ የሁለት ሰዎችን ንግግር አይተናል። ይኸውም ።1ኛ. ፈሊጥ በጎደለው አነጋገር "ብንያምን መልሼ ማምጣት ባልችል የእኔን ሁለትልጆች ወስደህ ግደል" የሚለው የሮቤል አነጋገር፡ በምሳሌ ነቱ እንደዚሁ ፈሊጥ የጎደላቸው አንዳንድ መምህራን የሚናገሩትን ብላሽ ቃል ያመለክታል። የትምህርተ ወንጌል አቀራራብ ልዩ ጥበበዊ የንግግር ዘዴንና ልዩ ብልሃትን ይጠይቃል። በብኵርናው ብቻ ተቀዳሚነትን ይዞ ንግግር ያሳመረ መስሎት ያንን ብላሽ ቃል የተነገረና በቅርብ ያለውን አባቱን እንኳ ማሳመን ያልቻለ የሮቤል ዓይነት ሰው መድረክ ላይ ቢቀርብ ዜሮ ለዜሮ ከመለያየት በቀር ምንም ዓይነት ማሳመኛ ቃላት ሊያመነጭ አይችልም። አንዳንድ የመድረክ ሰዎች ምዕዳን ወይም ምክር እንኳ መስጠት ተስኗቸው ወንጌሉን በስብከት ወይም በትምህርት መልክ ማቅረብ ትተው ወደ ፖለቲካ ዓይነት ድስኩር ለውጠውታል። ችሎታን መጥኖ አቅምን አለማወቅ-የሚያስትለውን-አሳፋሪ-ትዝብት-የሚገልጡ-ሁለት-ታሪክና ሳሌዎች:-

እነሆ! *ሀ.* ''''''*<u>ይሁዳ እንዴት ሞተ</u> ?* '''''' ሦስት ሰዎች በአእምሮ ሕመም ምክንያት ሆስፒታል ገብተው ነበር። ጥቂት ወራት በሕክምና ላይ ከቆዩ በኋላ "ምንም ዓይነት የአእምሮ ችግር /ሕመም የለብንምና ለመውጣት ይፈቀድልን" ብለው አመለከቱ። ኃላፊውም "ገና ብዙ ሕክምና ያስፈልጋችኋልና ጥቂት [illegible] ዘባተው "[illegible] ጤነኞች ነን:-

”



ለምን በከንቱ ጊዜ እናሳልፋለን ?' በማለት ጥያቂያቸውን አጠናከሩ። ስለዚህ ከነርሱ በፊት ታክሞ ድኗል የተባለውን አንድ የዕብዶች አለቃ ጠርቶ፣ "እባክህ ፈተና አዘጋጅና ስጣቸው፡ ፈተናውን ካለፉ በጠየቁት መሠረት እናሰናብታቸዋለን" ብሎ አዘዘው። እርሱም ፈተናውን ሲያዘጋጅ ከጥያቄዎቹ አንዱ "ይሁዳ እንዴት ሞተ ?" የሚል ነበር። ከተፈታኞቹ አንዱ "ገደል ገብቶ ሞተ" ሲል፡ ሁለተኛው "ውሃ ወስዶት ነው የሞተ" አለ።ሦስተኛው ደግሞ "በመኪና አደጋ ሞተ" ሲል፡ ፈታኙም ገና ያልዳነን ከነርሱ የበሳ ስለነበር መልሱን አላገኛችሁትም፡ ይሁዳ የሞተ በወልድ ነው አለ ይባላል ። የዚሁም ተከታይ ሌላው ታሪክ

***<u>ለ</u>*** '''''''' ***<u>ዮናስ ዓሣ አንበሪውን ዋጠው</u>*** '''''''' የሚል ነው። ይኸውም አንድ ኢትዮጵያዊ ወጣት ወደ አሜሪካ ለመግባት ዕድል ይገጥመውና በወዝ አደርነት ሥራ የሚያገኘው ደመወዝ አልበቃ ብሎት፡ ችግር ሳላስጨነቀው፡ ተጨማሪ ገቢ ለማግኘት "ወደ ቤተ ክርስቲያን ተጠግቼ ወንጌል መስበክ አለብኝ" ብሎ አሰበ። ከዚያ በፊት ዘወር ብሎ አይቶት የማያውቀውን መጽሐፍ ቅዱስ ከጓደኞቹ ተውሶ ለማስተማር ሲያገላብጥ በድንገት የትንቢተ ዮናስን መጽሐፍ አገኘ። ታሪኩን መተንተን ጀመረና በመሳሳት "ዮናስ ዓሣ አንበሪዉን ዋጠው" ሲል። ምእመናኑ፡ ገላጋይነት ገብተው "እንደርሱ አይደለም፡ ዓሣ አንበሪው ነው እኮ ዮናስን የዋጠው " ሲሉት፡ "ካፈርኩ አይመልሰኝ "እንዲሉ፡ በማፈርና በመርበትበት "እንደ እኔም ሆነ እንደ እናንተ አባባል፡ መችም አንዱ ሌላውን ሳይውጠው አልቀረም " ማለቱ ይታዋሳል። በ1ኛው ታሪክ ራሱ ከአእምሮ ሕመም ነጻ ሳይሆን፡ ሌሎችን ለመፈተን በመቅረቡና፡ <u>በ2ኛው ታሪክ</u> ደግሞ መጀመሪያ ራሱ ሳይማር ሌሎችን ለማስተማር የዮናስን ታሪክ አበላሽቶ በመጥቀሱ፡ ፡ሁለቱም ታሪኮች ራሳቸው ሳይማሩ፡ "ሌሎችን እናስተምራለን" ብለው የትምህርትን ክፍልና የስብከተ ወንጌልን መድረክ ለመያዝ በትዕቢትና በድፍረት የሚሽቀዳደሙ ሰዎችን ይመስላሉ። ይህኑ ድፍረት በሚመለከት የእግዚ አብሔር ቃል "ወንድሞቼ ሆይ ! " ከመካከላችሁ ብዙዎች አስተማሪዎች ለመሆን ድፍረት አይኑራችው፡ የባሰውን ፍርድ እንደምንቀበል ታውቃላችሁና" ይላል ያዕ. 3. 1-2 ። አብዛኛውን ጊዜ ትምህርታቸ ውም ሆነ ስብከታቸው እግዚአብሔርን ማዕከል ማድረግ ትቶ "ኢየሱስ ክርስቶስ ብሎ መናገርንም ያፍሩበታል።

_በርግጥ አንዳንድ ትሑታንና አዋቂዎችም የወንጌል መምህራን አሉ። በነርሱ አንጻር ሲታዩ-አንዳንዶችቹ ግን ራሳቸውን ከምሁራን ሁሉ በላይ



www.ethiopianorthodox.org

አድርገው ሊቃውንትን በንቀት ዓይን ይመለከታሉ። ምክርና እርምት የሚሰጧቸውን የምሁራን ሊቃውንትን ስም ለማጥፋትና ከሕዝብ ለማጣላት ይፈልጋሉ። ይህም አላዋቂነታቸውን ይመሰክርባቸዋል።

ያዕቆብ ልጆቹን ሲመርቅ፡ "ልጆቼ ሆይ ! ኑ፡ ወደፊት በምትመሩት ሕይወት የሚገጥማችሁን ክፉውንም፡ ደጉንም (ኃላፊውንና መጪውን ) እንድነግራችሁ ተሰብሰባችሁ ስሙኝ" ማለቱ ተጽፏል (ዘፍ. 49:1)። መምህራኑ ወንጌልም በማስተማርም ሆነ በስብከተ ወንጌል ሥራ ላይ በሚሠለፉበት ጊዜ የሚገጥማቸውን፡ ክፉውንም ሆነ ደግጉን ነገር መድረክ ከመያዛቸው በፊት በራስ -አገዝ ጥናት ጭምር ለይተው ሊታውቁት ይገባል። ሰይጣናዊ ትዕቢትን አስወግዶ በትሕትና 'ምንተ ይብለኒ ሰብእ " ሰው ስለ እኔ ትምህርት አቀራረብ ምን ይላል? ብሎ መጠየቅ ታላቅ ጥበብ ነው።

_አንድ የሐዲስ ኪዳን ትርጉም ደቀ መዝሙር በሚማርበት ዘመን ሁሉ "ጥያቄ የማቅረብ ልምድ አልነረበውም" ይባላል። ነገር ግን በሚመረቅበት ወቅት " ከት/ቤት ከወጣሁ በኋላ የምጠይቀው መምህር አጥቼ እንዳልቸገር" ብሎ በማሰብ እርሙን ያቀረበው አንድ ጥያቄ "ሐዋርያው ጳውሎስ ገላትያ፡ ገላትያ የሚላት ሚስቱ ናት ወይስ ምንድን ናት ?" የሚል ነበር ። "በሞኝ ስሕተት ብልሆች ይማሩበታል" ይባላልና ጠቢባን ሊያጤኑት ይገባል። በተረፈ "ወእመሰ ቦ ዘንጥአ ለጥበብ ለይስአል ኀበ ወሀቢ እግዚአብሔር አብዝቶ የሚሰጥ የጥበብ ባለቤት የሆነ እግዚአብሔርን በጸሎት ይጠይቅ" ( ያዕ 1፡5 ) ።

2ኛ- በሮቤል ብላሽ ንግግር አንጻር ደግሞ ፈሊጥና ጥበብ የሞላበት የይሁዳ ንግግር አባቱን ያዕቆብን አሳምኖ ብንያም በርሱ ኃላፊነት ወደ ግብጽ ለመውሰድ ችሏል። ጥሩ የትምህርተ ወንጌል አቀራረብ ችሎታ /ልዩ ተሰጥዎ ያላቸውመምህራን በጣዕመ ትምህርታቸው እልፍ አእልፍ ሕዝብን መማረክ ይችላሉ።ሕዝበ ክርስቲያኑ ቤተሰቡን ጭምር ያስተምሩለት ዘንድ ለነርሱ አደራ ያስረክባል።ለዚህም የይሁዳ ፈሊጣዊ ንግግር በጣዕመ ትምህርታቸው እልፍ አእላፍ ሕዝብን የሚማርኩ የእውነተኞች መምህራን ምሳሌ ነው ። በአንደበቱ የማይስት ፍጹም ሰው ነው " ተብሎ ተጽፍፉልና ( ያዕ 3፡ 2 ። ) """"""""""""""""""""""""""""""""""""""""

16--34 የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብጽ እንደተመለሱ፣ ዮሴፍ ከሌሎች ወንድሞቹ ጋር ብንያምን ባየ ጊዜ የቤቱን አዛዥ (መጋቢውን) እንዲህ ሲል አዘዘው፤ ‹‹እነዚህን ሰዎች ወደ ቤት ውሰዳቸው፤ ዛሬ ከእኔ ጋር ምሳ ይበላሉ፤ አንድ ከብት አርደህ አዘጋጅ››፡፡ እነርሱ ግን፣ ‹‹እንደ ገና ያስረን ይሆናል››



ብለው በብርቱ ተጨንቀው፣ ‹‹ሳናውቅ በየስልቻችን አፍ ላይ የተገኘውን ገንዘብ መልሰን ይዘን መጥተናል›› አሉት፡፡ መጋቢው ግን፣ ‹‹ቀድሞ እህል የገዛችሁበትን ገንዘብ ተቀብያለሁ፣ምናልባት አምላካችሁ እግዚአብሔር የሰጣችሁ ገንዘብ ሊሆን ይችላል›› ካላቸው በኋላ፣ ስምዖንን አምጥቶ ከእነርሱ ጋር እንዲቀላቀል አደረገ፡፡ ወዲያውኑም የእግር መታጠቢያ ውሃ ሰጣቸው፤ ለአህዮቻቸው ገፈራ አቀረበላቸው፡፡ ዮሴፍም በምሳ ሰዓት መጥቶ ገና ወደ ቤት ሲገባ፣ ከከነዓን ምድር ይዘውለት ያመጡትን እጅ መንሻ አቀረቡለት፤ እርሱም ስለ ራሳቸውና ስለ አባታቸው ደኅንነት ሲጠይቃቸው ተደስተው እጅ ነሡ፡፡ በገበታውም ዙሪያ ወንድሞቹን እንደየዕድሜ ደረጃቸው አስቀመጣቸው፡፡

(ትርጓሜ፦ ዮሴፍ ወንድሞቹን በማዕዱ (በገበታ) ዙሪያ በዕድሜ ደረጃቸው ለማስቀመጥ የተጠቀመበት ልዩ ጥበብ፣ የወይን ጠጅ በሚጠጣባት ዋንጫ የሚጠነቊል መስሎ በመታየት ነበር። ይኸውም ዋንጫይቱን በእጁ ኮርኮም (ገጨት) እያደረገ የምታሰማውን ድምፅ በመከተል፣ ‹‹ይህች ዋንጫ ሮቤል፣ ስምዖን፣ ሌዊ፣ ይሁዳ›› ትላለችሳ? ከእናንተ መካከል ሮቤል፣ ስምዖን የሚባሉ አሉ እንዴ?!›› እያለ የዐሥራ አንዱንም ስም በመጥራት ከበኵሩ ከሮቤል እስከ ታናሹ እስከ ብንያም በደረጃ ሲያስቀምጣቸው አይተው፣ወንድማማቾቹ በመገረም እርስ በርሳቸው ታያዩ." ይላል።

_የሚገርመው ነገር ግን ብዙዎች ታላላቅ የምዕራቡ ዓለም መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች (Bible Commentators ) ይህን ምሥጢር ሳይደርሱበት ቀርተው ዮሴፍ የግብጽን ጥንቈላ ጥበብ በዚያች ዋንጫ አማካይነት ያሳይ እንደነበር በመግለጥ የተሳሳተ ትርጉም ስጥተዋል። ይህን ጥበባዊ ትርጉም የደረሱበት ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ብቻ የሚደነቁ ናቸው። ዮሴፍ የግብጻውይንን የጥንቈላ ጥበብም ሆነ የጣዖት አምልኮትቸውን ፈጽሞ እንዳልተከተለ ሲያስረዳ ነቢየ እግዝIአአብሔር ዳዊት "ወሜጠ ዘባኖ እምሕራምቲሆሙ=ከአምልኮታቸው ሥርዓት ገለል ብሎ ጀርባውን አዞረባቸው" ይለናል ( መዝ 80፡ 6) ። """"""""""""""""""

፵፬ /44 የዋንጫዪቱ መዘዝ፣ 1-2 ዮሴፍ መጋቢውን እንዲህ አለው፣ ‹‹እንግዲህ፣ እነዚህ ሰዎች ለመጫን የሚችሉትን ያኽል እህል በየስልቻ ቸው ሞልተህ፣ ገንዘባቸውን መልሰህ በየስልቻቸው አፍ ላይ ቋጥርላቸው፣ ከዚያ በኋላ እኔ የወይን ጠጅ የምጠጣባትን ዋንጫ ወስደህ በታናሽ ወንድማቸው ስልቻ ውስጥ ጨምራት››፡፡7-13 እነርሱም በማለዳ ተነሥተው ጉዞዋቸውን ቀጠሉ፡፡ ከከተማው ለመውጣት ገና ጥቂት



www.ethiopianorthodox.org

መንገድ ሲቀራቸው ዮሴፍ የቤቱን አዛዥ (መጋቢውን) ጠርቶ፣ "ፈጠን በማለት ተከትለህ ሂድና እነዚያን ሰዎች በማስቆም፣‹‹ጌታዬ የወይን ጠጅ የሚጠጣባትንና የጥንቈላ ጥበብ የሚያውቅባትን ዋንጫ ለምን ሰርቃችሁ ወሰዳችሁ፤ በበጎ ነገር ፋንታስ እንዴት ክፉ ነገር ትመልሳላችሁ? ብለህ ውቀሳቸው" አለው። እርሱም ፈጠን ብሎ በመራመድ ሄዶ አስቆማችውና ይህን ሲነግራቸው፣ ደንግጠው ጭነታቸውን አውርደውለት ሲፈትሽ፣ ዋንጫይቱ በብንያም ስልቻ ውስጥ ተገኘች። ሰዎቹ በብርቱ ደንግጠው በሐዘን ልብሳቸውን ቀደዱ።

18-34 እንደ ገና አህዮቻቸውን ጭነው ወደ ዮሴፍ ተመለሱ፤ በፊቱም መሬት ላይ ወደቁ። እርሱም፣ ‹‹እንዴት እንዲህ ትሠራላችሁ›› ሲል ወቀሳቸው።ከእነርሱም መካከል ይሁዳ ሁሉንም ወክሎ ሲናገር እንዲህ አለ፤ ‹‹እንግዲህ፡ለጌታዬ ምን እንመልሳለን፡ ምንስ መናገር እንችላለን ወይስ ከሠራነው በደል ሁሉ በምን እንነጻለን?

_እግዚአብሔር የእኛን ያገልጋዮችህን ኃጢአት ገለጠው። እነሆ፣ ይህን ልጅ ኃላፊ ( ዋስ ) ሆኜ ያመጣሁት እኔ ራሴ ነኝ። እንግዲህ፣ ከእርሱ ይበልጥ ጉልበት ያለኝ እኔ ስለሆንሁ፣ በእርሱ ፈንታ እኔ የአንተ የጌታዬ አገልጋይ ልሁን፣ ይህ ልጅ ግን ወደ አባቱ እንዲመለስ ፍቀድልን። ምክንያቱም ሽማግሌ አባታችን እርሱን ከመካከላችን ካጣው፣ ወዲያውኑ ከነሽበቱ ወደ መቃብር ከመግባት አይመለስም። የርሱ ሕይወት ከዚህ ልጅ ጋር የተሳሰረች ናት››። ዮሴፍ-ግን፣-‹‹ይህንስ-በምንም-ዐይነት አላደርገውም፤ ዋንጫይቱ የተገኘችበት ሰው ብቻ የእኔ አገልጋይ መሆን አለበት። ሌሎቻችሁ ግን፣ በሰላም ወደ አገራችሁ ሂዱ›› አለ። ይሁዳም መልሶ፣ ‹‹ይህ ልጅ ከእኛ ተለይቶ ቢቀር፣ እንዴት አድርጌ የአባቴን ፊት አያለሁ?! እባክህ እኔ በርሱ ፈንታ እንዳገለግልህ ፍቀድልኝ" አለ።

ፃ፫/45. <u>ዮሴፍ ማንነቱን ለወንድሞቹ ገለጠ፡-</u> በአገልጋዮቹ ፊት ስሜቱን መቈጣጠር ስላቃተው፣ በዚያ ቤት የነበሩት ሰዎች ሁሉ ወደ ውጭ ወጥተው እንዲቈዩ አዘዘ። ከዚያ በኋላ ግብፃውያን ሁሉ እስኪሰሙ ድረስ ድምፁን ከፍ አድርጎ በመጮኽ አለቀሰ፤ የፈርዖንም ንጉሣዊ ቤተ-ሰብ ሁሉ ወሬውን ሰማ። 3 ወደ ወንድሞቹ ቀረብ ብሎም፣ ‹‹እኔ እኮ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ፣ ለመሆኑ አባቴ እስካሁን በሕይወት አለን?›› ብሎ ጠየቃቸው። ወንድሞቹ ግን ደነገጡ፣ መልስ ሊሰጡት አልቻሉም።-15 ዮሴፍ ወደ እርሱ እንዲቀርቡ አድርጎ፣ ‹‹እኔ ወደ ግብፅ የሸጣችሁኝ ወንድማችሁ ዮሴፍ ነኝ። ነገር ግን፣ ይህን ሁሉ በማድረጋችሁ ማዘንና



መፀፀት አይገባችሁም።እግዚአብሔር እኔን አስቀድሞ ወደዚህ አገር የላከኝ የሰዎችን ሕይወት ለማትረፍ ነው። እነሆ፣ በምድር ላይ ረኃብ ከገባ ሁለት ዓመት ሆነው፤ ወደፊት ገና አምስት የረኃብ ዓመታት አሉ። እግዚአብሔር ለፈርዖን እንደ መካሪ አባት አድርጎኛል። ስለዚህ፣ ሳትዘገዩ ተመልሳችሁ ሄዳችሁ አባቴንና ቤተ-ሰቡን፣እንስሶቻችሁን ሁሉ ይዛችሁ ወደ እኔ ኑ›› አላቸው። ከዚያም የወንድሙን የብንያምን አንገት አቅፎ ሳመው፣ ብንያምም አለቀሰ፤ ሌሎቹንም ወንድሞቹን ሲስማቸው ዮሴፍ በብርቱ አለቀሰ። ከዚያን በኋላ፣ወንድሞቹ ከእርሱ ጋር መጫወት ጀመሩ።

16--24 በፈርዖን ቤተ-መንግሥት የዮሴፍ ወንድሞች መምጣታቸው ወሬ ተሰማ። ፈርዖንና አገልጋዮቹም ሁሉ ተደሰቱ። ዮሴፍም በንጉሡ በፈርዖን ፈቃድና ትእዛዝ መሠረት ለጓዝ መጫኛ የሚያገለግሉ ሠረገላዎችንና ለጉዞ የሚሆን ስንቅ፣ ልብስና ገንዘብ ሰጣቸው። ለአባቱም አስፈላጊውን ልብስና ገንዘብ ከልዩ ምግብ ጋር ላከለት። በመንገድ እርስ በርስ እንዳይጣሉም መክሮ አሰናበታቸው።25-28 እነርሱም ተመልሰው ሄደው ከነዓን እንደ ደረሱ፣ የዮሴፍን በሕይወት መኖር ለያዕቆብ ሲነግሩት ለማመን አቃተው። ነገር ግን፣ ከዮሴፍ የተላከለትን ሠረገላ ባየ ጊዜ፣ በሕይወት መኖሩን አውቆ ሕይወቱ በደስታ ታደሰ። ‹‹ከመሞቴ በፊት ሄጄ ልጄን ማየት አለብኝ›› አለ።

*(ትርጓሜ፡ ያዕቆብ የገዛ ልጆቹ የፍየል ግልገል አርደው የልጁን የዮሴፍን ልብስ በደም ነክረው ሲያቀርቡለት፣ ‹‹ልጄን ክፉ አውሬ በጫጭቆ በልቶታል፣ ሞቶአል፣ አለቀለት በቃ!›› ብሎ -ደምድሞ ነበር። መኖርና አለመኖሩን አጣርቶ ለማወቅ ወይም ደግሞ መሥዋዕት ሠውቶ ፈጣሪውን በጸሎት ለመጠየቅ እንኳ አላሰበም። ነገር ግን፣ ‹‹ልጅህ ዮሴፍ በግብፅ ሕያው ሆኖ ተገኝ›› ብለው አሥራ አንድ ልጆቹ ሁሉ በአንድ ድምፅ ሲነግሩት፣ በቀላሉ ለማመን የማይበገር ሆነ።*

*-ይህ ታሪክ ዛሬም በምሳሌነቱ እየተደገመ ነው። ይኸውም ማንም ሰው ከዚህ ዓለም በሞት በተለየ ቍጥር፣ በሚሰጠው ትምህርት፣ ‹‹በክርስቶስ ስም አምነው የሞቱ ሰዎች በሥጋ ወደ መቃብር ቢወርዱም በአካለ ነፍስ በክርስቶስ ዘንድ ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ስለ ሆኑ (ሉቃስ 20፥ 38)፣ ቀቢጸ-ተስፋ የሚታይበት መሪር ሐዘን አያስፈለግም፣ ታገሡ፡ ብዙ አታልቅሱ›› ሲባል ሰሚ ጠፍቶ፣ ሁሉም በሐዘን ጨርቅ ተቈራምዶ፣ ተስፋ-ቢስ መስሎ የመኖር ልማድ ሊታረም የማይችል ሆኖ ቀርቷል ። ‹‹ልማድ ሲሠለጥን ሃይማኖት ይሆናል›› ይባላልና። ያዕቆብ የልጁን*



www.ethiopianorthodox.org

የዮሴፍን በሕይወት መኖር ያሳመነው፡ ዐሥራ አንድ ልጆቹ በአንድ ቃል ከነገሩት ይልቅ፣ ዮሴፍ ራሱ የላከለትን ሠረገላ በማየቱ ነበር ይላል (ቍር 27 )። አዎ፣ አንዳንዱም ሰው እንደዚሁ ከእውነተኛው የቃል ምስክርነት ይልቅ፣ በሚታይ፣ በሚዳሰስ፣ በቊሳቊስ ነገር ያምናል ማለት ነው። ብዙ ሰዎች በክርስትና ትምህርት የሚነገረውን ሁሉ ለመቀበል ዝግጁዎች ናቸው፤ ከሞት በኋላ ሌላ (አዲስ ሕይወት) መኖሩ ሲነገራቸው ግን፣ መጠራጠር ይጀምራሉ። ለምሳሌ፣ ሐዋርያው ጳውሎስ አርዮስፋጎስ ተብሎ በሚጠራው፣ የጥንት ግሪኮች ሸንጎ መካከል ቆሞ የተናገረውን አስደናቂ ትምህርት ሁሉ በደስታ ተቀብለውት ነብር። የትንሣኤ ዘለሕይወት ነገር ሲነሣ ግን፣ አንዳንዶቹ ሲያፌዙበት፣ አንዳንዶቹ ደግሞ 'ይህን ሌላ ጊዜ እንሰማሃለን' በማለት ለማመን መቸገራቸውን ቅዱስ ሉቃስ ጽፎታል (የሐዋ 17፥ 32)። ዛሬም ቢሆን ይህ ችግር የዞረ ድምር ሆኖ ባይቈይ ኖሮ፣ስለ ሞቱ ሰዎች ተስፋ የሚያስቈርጥ ሐዘን ቀርቶ በተስፋ ትንሣኤ መጽናናት በተቻለ ነበር።

## ፵፮ /46. ያዕቆብ ከቤተ-ሰቡ ጋር ወደ ግብጽ ወረደ፤

2--3 እግዚአብሔር ለያዕቆብ በሌሊት ራእይ ተገለጠለትና፤ ‹‹ወደ ግብፅ ለመውረድ-አትፍራ፤ እኔ- ከአንተ-ጋር -አብሬህ-እወርዳለሁ››። 27-30 በምትሞትበት ጊዜ ዮሴፍ በአጠገብህ ይቆማል" አለው። ወደ ግብፅ የወረዱትም የያዕቆብ ዝርያዎች በድምሩ ሰባ አምስት ነበሩ። ዮሴፍም በክብር ሠረገላ ሆኖ አባቱን ለመቀበል ወደ ጌሴም ሄደ ( *ጌሴም በግብፅ ምድር ያዕቆብ ከነቤተ-ሰቡ የኖረባት እጅግ ለም ሆና፣ በተለይ ደግሞ ለከብት ርቢ ምቹ የሆነች ወረዳ ናት* )። በተገናኙም ጊዜ ዮሴፍ በአባቱ አንገት ላይ ተጠምጥሞ ለረጅም ጊዜ አለቀሰ። ያዕቆብም ዮሴፍን፣ ‹‹በሕይወት መኖርህን በዓይኔ አይቻለሁና ከእንግዲህስ ብሞትም ግድ የለኝ›› አለ።

## ፵፯/47. ያዕቆብ በንጉሡ በፈርዖን ፊት ቀረበ፡

7-9 ዮሴፍ አባቱን ያዕቆብን ወደ ግብጽ ቤተ-መንግሥት ወስዶ ከንጉሡ፣ ከፈርዖን ጋር እንዲተዋወቅ አደረገ። የግብጽ-ንጉሥ-ፈርዖንም፣ ‹‹ዕድሜህ-ስንት-ነው?››ሲል-በጠየቀው-ጊዜ-ያዕቆብ_ሲመልስ፣ ‹‹በመንከራተት ያሳለፍኳቸው ዓመታት አንድ መቶ ሠላሳ ብቻ ናቸው፤ እነርሱም አባቶቼ ከኖሩባቸው ዘመናት ያነሱ ናቸው›› አለ። 20-26 ዮሴፍ የግብጽን ምድር ሁሉ ለፈርዖን ገዛ፤ ይኸውም ለአገሪቱ ሕዝብ የሰባት ዓመት ቀለብ፣ ለእርሻቸውም ዘር በመስጠትና ልዋጩን ከርስታቸው ከአምስት አንዱን እጅ ለፈርዖን እንዲሰጡ በመወሰን፣ የካህናት ርስተ-ጉልት ከሆነው ድርሻ በቀር፣ ከሞላው የግብፅ ምድር ከአምስት አንዱ እጅ ለፈርዖን ተሰጥቶ፣ ይዞታው ለዘለቄታ የጸና ሆኖ እንዲኖር አደረገ። በዚያ ሁሉ ዘመነ-ረኃብ የካህናቱ ርስት ሳይሸጥ፡- ሳይለወጥ የቈየበት ምክንያት ከቤተ-መንግሥት ምግብ ስለሚሰጣቸው ነበር።

## ፵፰/48. ያዕቆብ የዮሴፍን ልጆች ባረከ /መረቀ)፤

1-11 ያዕቆብ ዮሴፍን እንዲህ አለው፤ ‹‹እኔ ወደ አንተ ከመምጣቴ በፊት፣ በግብፅ ምድር የተወለዱልህ ሁለቱ ልጆችህ ኤፍሬምና ምናሴ ለእኔ ይሁኑ፤ እነርሱ ለእኔ እንደ ሮቤልና እንደ ስምዖን ናቸው። አንተን ብቻህን እንኳ አይሃለሁ የሚል ተስፋ አልነበረኝም፤ እግዚአብሔር ግን ልጆችህንም ጭምር ለማየት አበቃኝ››። 12-22 ዮሴፍም ልጆቹን እንዲባርክለት በኵሩን ምናሴን, በያዕቆብ ቀኝ፣ ሁለተኛ ልጁን ኤፍሬምን በስተግራው አቆማቸው። ያዕቆብ ግን እጆቹን አመሳቅሎ ቀኝ እጁን በታናሽ ልጁ በኤፍሬም ላይ፣ ግራ እጁን በበኵር ልጁ በምናሴ ላይ አኖረ።

ዮሴፍም ባለማወቅ የተደረገ መስሎት፣ ‹‹ በኵሩ ምናሴ ስለሆነ፣ ቀኝ እጅህን በእርሱ ላይ እንድታኖር-እፈልጋለሁ››-አለው። ያዕቆብ-ግን፣ አውቃለሁ፤ ልጄ-፤ አውቃለሁ የምናሴ ዘር ታላቅ ይሆናል፤ በተለይ እርሱ ታናሽ የሆነው የኤፍሬም ዘር ብዛት ግን ሊቈጠር የማይቻል አሕዛብ መሙላት ይሆናል›› አለው። ከዚህ በኋላ እንዲህ ብሎ መረቃቸው፤ አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በቅንነት ያገለገሉትና እኔንም በሕይወቴ ዘመን ሁሉ እስከ ዛሬ ድረስ የጠበቀኝ (የመገበኝ) እግዚአብሔር፣ ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ የእግዚአብሔር መልአክ እነዚህን ልጆች ይባርክ፤ የእኔ ስም፡-አባቶቼም-የአብርሃምና-የይስሐቅ-ስም-በነዚህ-ልጆች-ሲጠራ ይኑር››።

## ፵፱ /49. ያዕቆብ ልጆቹን ሲመርቅ የተናገረው ትንቢታዊ ቃል፤

፡፡ ያዕቆብ ልጆቹን ሁሉ ጠርቶ፣ ‹‹ወደ ፊት የሚፈጸምላችሁን መልካም ነገርና የሚደርስባችሁን ክፉ ነገር ሁሉ እነግራችሁ ዘንድ ኑ ሰብሰቡ›› አላቸው፡- ሮቤል ሆይ፣ ኃይልና ጉልበት በነበረኝ ጊዜ ወለድኩህ የበኵር ልጄ ነበርህ፣ ነገር ግን፣ እንደ ውሃ የምትዋልል ሆነህ ስ ተገኘህ ብኵርና አይገባህም። ከእኔ ቁባት ጋር በአልጋዬ ላይ ተኝተህ ርክሰኸዋልና›› (ዘፍጥ 35፡ 22)። ስምዖንና ሌዊ ፡ የዓመፅ ተግባር መፈጸም ተባብረው የጦር መሣሪያ በማንሣት የሚያምኑ ወንድማማች ናቸው። እነርሱ በዓመፅና በቊጣቸው ብዛት የብዙ ሕዝብን ሕይወት ያጠፉ በመሆናቸው በምክራቸው፡ አልተባበርም። ጭካኔ የተሞላበት





www.ethiopianorthodox.org

መዓታቸው (ቍጣቸው) የተረገመ ይሁን፡፡ በእስራኤል ሕዝብ መሐል እበትናቸዋለሁ፤ በሕዝብም ውስጥ እከፋፍላቸዋለሁ፡፡

**ይሁዳ**፡ እንደ ደቦል አንበሳ ነው፤ሊቀሰቅሰው የሚደፍር የለም፤ለዘላለም የሚነግሠው (መሢሕ ክርስቶስ) እስከሚመጣበት ዘመን ድረስ በትረ መንግሥት (የገዢነት ሥልጣን) ከእርሱ እጅ አይወጣም፤ ሕዝብም ሁሉ ይታዘዙለታል -5-10 ፡፡ ዛብሎን፡ መኖሪያው በባሕር ዳርቻ ይሆናል፤ ወደቡ የመርከቦች ማረፊያ ነው፡፡ የሚኖርበት ምድር ወሰኑ እስከ ሲዶና ይዘልቃል (13)፡፡ ይሳኮር፡ የግብርናን ሥራ የሚወድ ይሆናል (14-15)፡፡ ‹‹ይሳኮር ፈተዋ ለሠናይት፤ አትሐተ መትከፍቶ ከመ ይትቀነያ ለምድር» (ይሳኮር እርሻና ቁፋሮን ወደደ፤ ምድርን ለማረስ ትከሻውን ዝቅ-ዝቅ አደረገ)፡፡ ተብሎ ተጽፏልና፡፡ ዳን ፡ፈራጅ-ዳኛ ይሆናል፤ እርሱ እንደ መንገድ ዳር እባብ ኾኖ ፈረሰኛውን ከፈረስ ላይ ለመጣል ያደባል፤ የፈረሱን ተረከዝ እንደሚነድፍ እባብ ይሆናል፡፡ ጋድን፡ ቀማኞች ሲያጠቁት ይሞክራሉ፤ እርሱም ዱካቸውን ተከትሎ ያሳድዳቸዋል፡፡

**አሴር**፡ ከምድሩ በማግኘት ለነገሥታት መቅረብ የሚችል የቤተ መንግሥት ምግብ ያዘጋጃል፡፡ ንፍታሌም፡- በየሜዳው--በነጻነት እንደምትቦርቅ-ሚዳቋ-ነው፡መልካም-ድምፅን ይሰጣል፡፡

**ዮሴፍ**፡ በውሃ ፈሳሽ ዳርቻ እንደ ተተከለና ሐረጎቹ በግንብ ላይ እንደሚዘረጉ ዛፍ ነው፡፡ የአባትህ አምላክ ይረዳሃል፤ የአባትህም በረከት በወንድሞችህ መካከል አለቃ በሆንህ በአንተ ራስ ላይ ይውረድ (22-26)፡ ብንያም፡ እንደ ነጣቂ ተኵላ ነው፤ በማለዳ ያደነውን ራሱ ይበላል፤ በምሽት ጊዜ ያደነውን ግን ለሌሎች ያካፍላል (27)፡፡ *( ትርጓሜ፡ የመጀመሪያው ንጉሥ ሳኦል የተቀባው ከነገደ ብንያም ተመርጦ ነበር፤ ዘግየት ብሎ ግን፣ በትረ -መንግሥት ቀደም ሲል ትንቢት ወደተነገረለት ወደ ይሁዳ ነገድ ተመልሶ ከሳኦል በመቀጠል ዳዊት ተቀብቶ መንገሡን ይህ ታሪክ ያመለክታልና ነው፡፡ )*

## ፶/50. የያዕቆብ ሞትና የሥርዓተ-ቀብሩ አፈጻጸም በከነዓን

1-3 ያዕቆብ በሞተ ጊዜ ፣ ልጁ ዮሴፍ በእርሱ ላይ ወድቆ፣ ፊቱን እየሳመ አለቀሰ፡፡ የአባቱንም አስከሬን መልካም መዓዛ ባለው ሽቶ እያሹ ያደርቁለት ዘንድ የግብፅ ባለመድኃኒቶችን አዘዘ፡ እነርሱም በአገሩ ደንብ ( ልማድ) መሠረት አስከሬኑን ለማድረቅ ዐርባ ቀን ወሰደባቸው፡፡ ግብፃውያንም ሰባ ቀን ሙሉ አለቀሱለት፡፡

*(**ትርጓሜ፡** የግብጽ ጠቢባን ያወረሱት ይህ የሰውን አስከሬን እንዳይ ፈርስና እንዳይበላሽ ጥሩ መዓዛ ባለው ሽቱ እያሹ በማድረቅ በክብካቤ የመያዝ ጥበብ ዛሬም በሠለጠነው ዓለም በኬሚካል -ንጥረ ነገሮች ጠብቆ ማኖር የተለመደ ሆኗል። አንዲት ኢትዮጵያዊት እኅት ስትናገር በጣልያን አገር ሮማ ከተማ ስኖር ለሀገር ዜጎች ብቻ እንጂ ለውጭ አገር ዜጎች የማይፈቀድ ሆኖ፡ በሰዓት $ 25 ኻያ አምስት ዶላር /የውሮ የሚታፈስበት ጥሩ ሥራ ነበረኝ" አለች። ምን ዓይነት ሥራ ስትባል እሬሳ /አስከሬን መገነዝ ነበር " አለችን። የሥራን ክቡርነት የማያውቁ አንዳንድ ሰዎች ለመሳቅ ሞከሩ።*

*_በስተኋላ አዙረን ስናየው ግን ለካስ ሥራን መናቅ አይገባም። አገራችንን ካደኸየንበት ምክንያ አንዱ ሥራን መናቅ ነውና። ሕዝባችን በአንዳንድ አጋጣሚ ወደ ሰሜን አሜሪካ ከገባ ግን ሥራ መናቅ ብሎ ነገር የለም። አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ዶክተሩ /ፕሮፌሰሩ ሽንት ቤት ያጸዳል። ሴት፡ ውንዱ ባጭር ታጥቆ ይሠራል። የእጅ ስልክ ሁሉ ድምፁ ይጠፋል። በሀገራችንም እንደዚያ መሥራት ቢቻል ኖሮ የተቀቀለ ሩዝና ስንዴ እርዳታ ተቀባዮች በመሆን ፈንታ አበዳሪዎችና እርዳታ ለጋሾች ለመሆን በታደልን ነበር። "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነውና " (የሐዋ-ሥራ-20.-35 ) ።*

4–6. ከዚህም በኋላ ዮሴፍ ለንጉሡ ለፈርዖን ባለሥልጣኖች እንዲህ አላቸው፤ ‹‹አባቴ ከመሞቱ በፊት በከነዓን ምድር በተዘጋጀ ለት መካነ- መቃብር እንድቀብረው በመሐላ ቃል አስገብቶኛል ፤ ስለዚህም-ሄጄ ቀብሬው እንዲመለስ_ይፈቅድልኝ ዘንድ ለንጉሡ ለፈርዖን ንገሩልኝ››፡፡ ፈርዖንም፣ ‹ በገባህለት ቃል መሠረት አባትህን ቀብረህ ተመለስ›› ብሎ ፈቀደለት፡፡ 7- 12 ስለዚህ ዮሴፍ አባቱን ለመቅበር ሲወጣ፣ የፈርዖን ባለሥልጣኖችና የቤተ መንግሥቱ ታላላቅ መኳንንት ብዙ ሠረገላና ፈረሶችን ይዘው በታላቅ አጀብ ተከትለውት ሄዱ፡፡ ከዮርዳኖስ በስተምሥራቅ አጣድ ተብሎ በሚጠራ አውድማ ላይ ሲደርሱ ፡ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ፡፡ በዚያም የሚኖሩ ከነዓናውያን በመገረም፣ ‹‹ከመዝኑ ላሐ ግብጽ =የግብፆች ለቅሶ እንዴት መሪር ነው? ›› ተባባሉ፡፡ በዚያም የሰባት ቀን የሐዘን ውሎ ተደርጎለት፡ በማክቤላ ዋሻ ሥርዓተ-ቀብሩ ተፈጸመ፡፡ ዮሴፍ ተከትለውት ከመጡት ባለሥልጣኖችና መኳንንት፣ ከወንድሞቹም ጋር ወደ ግብፅ ተመለሰ፡፡ 15--21 ከዚያም የቀብር መልስ በኋላ፣ የዮሴፍ ወንድሞች፣ ‹‹ምናልባት አባታችን ከሞተ በኋላ ይበቀለን ይሆን?›› ብለው ፈርተው፣ ‹‹አባታችን ከመሞቱ በፊት





www.ethiopianorthodox.org

ስለ ፈጸምንብህ በደል ሁሉ ይቅርታ እንድንጠይቅህ አዝዞን ነበርና አሁንም እባክህ ክልብ ማረን፤ ይቅርም በለን›› ብለው-በፊቱ ወደቁ።ዮሴፍ ግን፣ ይህን ሲጠይቁት አዝኖ አለቀሰ። በመጨረሻም ‹‹በርግጥ እናንተ ክፉ ነገር አድርጋችሁብኝ ነበር፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ለበጐ አደረገው (ሮሜ-8፡28)። ስለዚህም አይዞአችሁ ከቶ አትፍሩ›› ብሎ አጽናናቸው)።

## ዮሴፍ የተናገረው ትንቢታዊ የኑዛዜ ቃል

22--25 ዮሴፍ አንድ መቶ አሥር ዓመት ሲሆነው፣ ከመሞቱ በፊት ወንድሞቹን፣ ‹‹እነሆ፣ እንግዴህ እኔ የምሞትበት ጊዜ ደርሶአል፤ እናንተን ግን፣ እግዚአብሔር በረድኤት የሚጐበኝበት ጊዜ ይመጣል፤ከዚህችም አገር አውጥቶ ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ሊያወርሳቸው ቃል ኪዳ ወደገባላቸው (ወደ ተስፋይቱ ምድር) ይመልሳችኋል፤ በዚያ ጊዜ የእኔን ዐፅም ከዚህ አገር ይዛችሁ እንድትወጡ በመሐላ ቃል ግቡልኝ›› አላቸው። እነርሱም ማሉለት። ከዚያም በኋላ ዮሴፍ በአንድ መቶ ዐሥር ዓመት ዕድሜው ሞተ፤ አስከሬኑም ጥሩ መዓዛ ባለው ሽቱ ታሽቶ እንዲደርቅ በማስደረግ በምድረ ግብፅ እስከቈዩበት ጊዜ ድረስ በሣጥን አኖሩት።

## """"""" የአንድምታ ትርጓሜ """""""

### ዮሴፍ-መድኃኔ ዓለም ክርስቶስን በብዙ ነገሮች ይመስለዋል፡

1/ . ዮሴፍ በአባቱ በያዕቆብ ዘንድ ተወዳጅ እንደ ነበር ጌታም በአብ ዘንድ ተወዳጅ ነው "ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር ወሎቱ ስምዕዎ ተብሎ ተጽፏልና (ማቴ 17፡ 5 )

2/. ዮሴፍ በገዛ ወንድሞቹ እንደ ተጠላ ፡ ጌታም፡ ‹‹አስቀድሞ ወደመረጣቸው ወገኖቹ (ወደ ቤተ እስራኤል) መጣ፡ ወገኖቹ ግን አልተቀበሉትም›( ዮሐ. 1፡ 11-12 )

3/. ዮሴፍ በወንድሙ በይሁዳ ምክር እንደተሸጠ ፡ጌታችንም በደቀ መዝሙሩ በአስቆሮታዊዉ ይሁዳ ሤራ ለሠላሳ ብር ተሸጧል ፡ >

4/. ዐሥሩ የዮሴፍ ወንድሞች ወደ ግብጽ በወረዱ ጊዜ፡ ወደ ዮሴፍ ቀርበው ግንባራቸውን መሬት አስነክተው በመስገድ በአክብሮት እጅ ነሥተውታል። ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በሰማይና-በምድር ያሉ ፍጥረታት ሁሉ የሚሰግዱ ለትና-ጒልበትም ሁሉ የሚንበረ ከክለት+ የባሕርይ አምላክ ነውና (ፊል 2፡ 6-10 +ቆላስ ፡ 15 -20 ) >'



5/..ዮሴፍ በከነዓን እንደ ሞተ ያህል ሆኖ ሲቈጠር፡ በምድረ ግብጽ ግን ሕያው እንደነበር-ሁሉ፣ጌታም፡ ‹‹በሥጋ ሞተ፤ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ"- ተብሎለታል- 1 ጴጥ 3፡ 18 ባለመንበርና ዘላለማዊ ሕያው ሆኖ በአብ ቀኝ ይኖራል ( የሐዋ ሥ 54-60 )

6/. ዮሴፍ በዘመነ ረኃብ ለብዙ-ሕዝብና አሕዛብ መዳን ምክንያት እንደሆነ ጌታችንም ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን በመመገብ ለእኛ ለምእመናን መድኅኒት ሆኖልናል፡ በነፍስም በሥጋም መዳን በሌላ በማንም የለም በክርስቶስ እንጂ (የሐዋ. 4፥ 12 )፡

7/ የዮሴፍ ልዕልና-በትንቢታዊ-ሕልም የተገለጠው በተወለደባት አገር በወንድሞቹ መካከል-ሲሆን፡ የተሾመው ግን በአረማውያሕዝብ ላይ እንደ ነበር ‹‹በቤተ-ያዕቆብ ይነግሣል››ተብሎ ትንብት የተነገረለት ጌታም፣ በመጀመሪያ የመጣው ወደ ቤተ እስራኤል ሲሆን፣ ዘግየት ብሎ ግን ከቤተ አይሁድ ብቻ ሳይሆን ከአረማውያንም መካከል በምልአት-አምነው- በተቀበሉት-ምእመናን-ልቡና-ነግሦ የሚኖር ሆኗልና።

8/ ዮሴፍ ብዙ በደል /ግፍ ለፈጸሙበት ወንድሞቹ ፍጹም ይቅርታ በማድረግ ሲረዳቸውና ሲመግባቸው እንደ ኖረ ሁሉ ፡ ጌታም "እንዲሁ በነጻ እወዳቸዋለሁ ፡ የቀደመ በደላቸውንና ፡ ክፉ ሥራቸውን ሁሉ አላስብም›› ሲል በነቢዩ ያናገረውን ተስፋ በመፈጸሙ፡ የታመነ ፡ አበሳ ኃጢአትን ሁሉ ይቅር ባይና ፍጹም መሐሪ ነው ( ሆሴ. 14-4፤ ኤፌ. 1፥7)። ‹‹አባ ስረይ ሎሙ እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና- ይቅር በላቸው)›› ብሎ፣ በመስ ቀል ላይ ለቸነከሩት ጠላቶቹ እንኳ ሳይቀር ጸልዮላቸዋልና (ሉቃስ 23፡

9/. በነቢዩ ሆሴዕ 5 ፡ 15 -እንደተነገረው፡ ዮሴፍ ወንድሞቹ ስለ ፈጸሙበት በደል ሁሉ ንስሐ እስኪገቡ ድረስ -ማንነቱን ሳይገልጥ ሥነ ምግባራቸ ውን -ፈተነ፡ መድኅነ-ዓለም ክርስቶስም የሰዎችን ልብ/ ሕይወት የሚለው ጥበትና ወደ እርሱ የሚያቀር ብበት -የወንጌሉ- ተቀዳሚ- ትምህርት " ነስሑ-እስመ ቀርበት መንግሥተ ሰማያት "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንስሐ ግቡ" የሚል ነው ( ማቴ 4፡ 17 ) ።

''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

... ረታና ቤተሰቡ



www.ethiopianorthodox.org

# ኦሪት ዘፀአት

(መጽሐፈ ሙሴ ካልእት)

***መግቢያ***:ፀአት=ወፅአ ወጣ ከሚለው ከግእዝ የተወረሰ ቃል ነው።

*""""""""""ይኸውም በቀድሞ ጊዜ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የሰጠውን የተስፋ ቃል በማሰብ፣ በግብጽ የባርነት ጭቆና ሥር የነበሩ ሕዝቡን እስራኤላውያንን ነጻ በማውጣት ወደ ተስፋዪቱ ምድር -ከነዓን እንዲመለሱ አድርጎ በሙሴ መሪነት፣ በመልአክ ተራዳኢነት በዓረብ አገር ምድረ በዳ ጉዞ ላይ ሳሉ የፈጸመላቸውን ድንቅ ነገር ሁሉ የሚያስረዳ ነው ። የኦሪትዘፀአት-መጽሐፍ ሦስት ዋና፣ ዋና ክፍሎች የሚከተሉት ናቸው፤ይኸውም :—*

*1._ከግብጽ-ባርነት-ነጻ-ወጥተው-ወደ-ሲና-ተራራ-ያደረጉትን-የበረሃ-ጉዞና እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ቃል ኪዳን በማድረግ ፡ የሞራል መመሪያ ሕጎችን ሁሉ ከማስጠንቀቂያ ከትምህርት ጋር ሰጥቷል።*

*2_በዓለም አቀፍ ደረጃ ማንኛውም ማኀበረሰብ በሚመራበት ሕግ ሁሉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጠቀሱ መሠረታውያን የሆኑ-ዐሥሩ ታላላቅ -/ትእዛዛት መጀመሪያ በጽላተ ሕግ ተቀርጸው ከተሰጡ በኋላ ዘግየት ብሎ-በዚሁ መጽሐፍ-ምዕራፍ- ፳/.20 ተጽፈዋል።*

*3..- እግዚአብሔር ብዙ ድንቅ ነገሮችን ባደረገላቸው መጠን ማመስገን ሲገባ-ሕዝቡ-አልፎ፡-አልፎ፡ እንዴት እንደተፈታተኑትም-ይገልጣ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ታላቅ ታሪክ ያለው የሕዝቡ ነጻ አውጪ ሆኖ የእግዚአብሔርን-ድንቅ ሥራ-ሁሉ አጉልቶ ያሳየ ነቢዩ ሙሴ ወልደ እንበረም ያላቅ የእግዚአብሔር የነበረ ነው ። በዚሁ በዘፀአት መጽሐፍ*

*የእግዚአብሔር አምልኮት የሚፈጸምባት የመጀመሪያዪቱ ቤተ መቅደስ ደብተራ ኦሪት ተብላ የምትጠራው ድንኳን የክህነት አገልግሎት ጭምር በሰማያዊት ቤተ መቅደስ አምሳል እንዲፈጽም ሲገልጥለት ተጠንቅቆ እንዲሠራ ለሙሴ ያሳየው ራሱ እግዚአብሔር ነው ( ዘፀአ 25፡ 22፡ + ዕብ 8፡ 5 )።*





## ፩/1. <u>በእስራኤል ልጆች ላይ የደረሰ የባርነት ጭቆና ፡</u>

8 -12 ከዚያ በኋላ፣ ስለ መልካም ሥራው ሁሉ ዮሴፍን የማያውቅ ሌላ አዲስ ንጉሥ በግብጽ ተነሣ። ያም ንጉሥ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል ተንኰል የሞላበት አሳብ አቀረበ፣ ‹‹እነሆ፣ እነዚህ የእስራኤል ሕዝብ ቍጥር በዝቷል፤ የውጭ ጠላት ቢነሣብን፣ ከዚያ ጋር ተባብረው እኛን ወግተው በማሸነፍ ከአገራችን ወጥተው እንዳይሄዱ፣ ኑ የእነርሱ ዘር እንዳይበዛ መቈጣጠሪያና መቀነሻ ዘዴ እንፍጠር›"፡ከዚያም ጊዜ ጀምሮ፣ ጨካኞች የሆኑ የሥራ ኃላፊዎችን ( አሠሪዎችን ) በእነርሱ ላይ ሾመ፤ እነዚያም የሥራ ኀላፊዎች እስራኤልን በባርነት አገዛዝ በማስጨነቅ ፊቶምና ራምሴ የተባሉትን ከተሞች የግብፅ ንጉሥ ለሆነው ለፈርዖን እንዲሠሩለት አደረጉ። ነገር ግን፣ እነርሱ ጨቍነው ባስጨነቋቸው መጠን፣ የእስራኤል ሕዝብ ቍጥር እየበዛ፣ በምድሪቱ ላይ ተስፋፍተውና ተንሰራፍተው እየበረቱ ሄዱ እንጂ ቍጥራቸው አልቀነሰም።

15-21 ዘግየት ብሎም፣ ንጉሡ ፈርዖን-ሺፕራና-ፉሐ-ተብለው-የሚጠሩ-አዋላጆችን-በመሾም"ከዕብራውያት ሴቶች የሚወለደውን ወንድ-ወንዱን ልጅ ሁሉ ገና ከእናቱ ማሕፀን ሲወጣ፣ ወዲያውኑ እየገደላችሁ ጣሉ›› የሚል ትእዛዝ ሰጠ። አዋላጆቹ ግን እግዚአብሔርን በመፍራ ሕፃናቱን አልገደሉም፣ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ለእነዚያ አዋላጆች የተባረከ ቤተሰብ ሰጥቶ፡ እንዳይቀጣቸውም የንጉሡን ቍጣ በማብረድ ድንቅ ነገርን አደረገላቸው። 22 ንጉሥ ፈርዖን የሰጠው ሦስተኛው ትእዛዝ ደግሞ፣ ሕዝቡ ራሱ ተባብሮ ከዕብራውያን የሚወለደውን ወንድ ልጅ ሁሉ፣ እያነቀ ወደ ባሕር እንዲጥሉ የሚያስገድድ ነበር።

፪ /2. የሙሴ ልደት፤ 15-21 ሙሴ በተወለደ ጊዜ፣ መልኩ የሚያምርና የሚያሳሳ /አሳዛኝ ሕፃን መሆኑን አይታ፣ እናቱ ሦስት ወር ሙሉ ደብቃ አቈየችው። ከሦስት ወር በኋላ ግን፣ ድምፁ እየበረታ ሲሄድ ለዘለቄታ ልትሸሽገው እንደማትችል አውቃ፣ ከጕሽ-መቃ ( ከደንገል ) ተሠርቶ ቅጥራን (ሬንጅ) የተቀባ ሣጥን አዘጋጅታ፣ ሕፃኑን በዚያ ሣጥን ውስጥ አስተኝታ፣ በዓባይ ወንዝ ዳር በሚገኝ ጕሽ-መቃ ውስጥ በማኖር እኅቱ ማርያም ራቅ ብላ ቆማ እንድትጠብቀው አደረገች።5--10 በዚያም ጊዜ እነሆ፣ የግብጽ ንጉሥ የፈርዖን ልጅ ለመታጠብ፣ ለመዋኘትም ብላ እዚያ እንደ ደረሰች፣ያን ሕፃን ገና ስታየው ራራችለት፤ አዘነችለትም። ‹‹ ይህ



www.ethiopianorthodox.org

ልጅ የዕብራውያን ሴቶች እየወለዱ ከሚጥሏቸው ሕፃናት አንዱ መሆን አለበት" አለች። በዚህ ጊዜ፣ የሕፃኑ እኅት ማርያም ወደ ልዕልቲቱ ቀረብ ብላ፣ ‹‹እያጠባች የምታሳድግልሽ ከዕብራውያት ሴቶች አንዲቱን ላምጣልሽን?›› ስትል ጠየቀቻት። ልዕልቲቱም ያን ሕፃን እንደ ራስዋ ልጅ አድርጋ ለማሳደግ ስለፈለገች፣ ‹‹አዎ አሁኑኑ ሄደሽ አምጪልኝ›› አለቻት። ማርያምም ፈጥና ሄዳ የራሱን የሕፃኑን ወላጅ እናት ጠርታ አመጣችላት። ልዕልቲቱም፣ ‹‹ይህን ልጅ ወስደሽ አሳድጊልኝ፤ እኔም ደመወዝ እሰጥሻለሁ›› አለቻት።እርስዋም ሕፃኑን ተቀብላ በክብካካሳደገችው በኋላ፣ወደ ቤተ-መንግሥት ወስዳ ለልዕልቲቱ አስረከበቻት።ልዕልቲቱም ይህ ሕፃን ከውሃ የተገኘ መሆኑን ለመግለጥ " ሙሴ" የሚል ስም አወጣችለት። (ሙሴም በቤተ-መንግሥቱ የግብፃውያንን ጥበብ እየተማረ አደገ፤ ኃያል (ብርቱ ሰውም) ሆነ (የሐዋ 7፡22። ሙሴ ሕዝቡን ( ወገኖቹን ) ለመጐብኘት ወጣ፤ 11-15 ሙሴ ዐርባ ዓመት-ሲሞላው፣ሕዝቡን ሊጐበኝ ወጣ፤ እዚያም አንድ ግብፃዊ አንዱን እስራኤላዊ ሲደበድበው አየ። በዚህም ተናድዶ ግራ ቀኝ ከተመለከተ በኋላ፣ ያን ግብፃዊ በክርን አዳሽቆ ገደለውና አሸዋ ውስጥ ቀብሮት ሄደ። በማግሥቱ፣ ሙሴ እንደ ገና ሌላ ጉብኝት ለማድረግ ሲወጣ፣ሌሎች ሁለት እስራኤላውያን እርስ-በርሳቸው ተጣልተው ሲደባደቡ አገኛቸውና ሊገላግላቸው ቢሞክር፣ በትናንትናው ዕለት ከዚያ ግብፃዊ እጅ ያዳነው እስራኤላዊ ሰው ተቈጥቶ፣ ‹‹አንተን በእኛ ላይ ፈራጅ ዳኛ አድርጎ የሾመህ ማን ነው? ወይስ ትላንት ያንን ግብፃዊ ሰው እንደ ገደልህ እኔንም ለመግደል ትፈልጋለህ ማለት ነውን? ሲል ገላመጠው። ሙሴም የግድያው ወሬ እስከ ግብጽ ቤተ-መንግሥት የተሰማ መሆኑን አውቆ፣ወደ ምድያም ተሰደደ።

ሙሴ በምድያም ምድር፡ 15-25 ሙሴ ምድያም እንደ ደረሰ፣ እረኞች መንጋቸውን ውሃ በሚያጠጡበት ጉድጓድ አጠገብ ዕረፍት አደረገ። ወዲያውም ሰባት ልጃገረዶች ያባታቸውን በጎች እየነዱ ውኃ ለማጠጣት መጡ። እረኞቹ ግን፣ እነዚያን ልጃገረዶች አባረሩዋቸው፤ ስለዚህም፣ ሙሴ ተነሥቶ እነዚያን ልጃገረዶች ከእረኞች እጅ በማዳን የብዙ ሰው-ጉልበት-የሚጠይቀውን የውሃ-ጉድጓድ-መግጠሚያ ድንጋይ፣ ብቻውን ከፍቶ በጎቻቸውን አጠጣላቸው። ልጃገረዶቹም-ተመልሰው ሄደው የሆነውን ነገር ሁሉ ለአባታቸው ለዮቶር (ራጉኤል) ገለጡለት፤ እርሱም፣ ‹‹ያን ሰው ጥሩትና እህል-ውሃ ይቅመስ›› አላቸው።ልጆቹም ሙሴን-ጠርተው አመጡትና ከአባታቸው ጋር ተዋውቆ የምድያም ኑዋሪ ሆነ፡ ዘግየት ብሎም ዮቶር (ራጉኤል) በተለይ ሲፖራ የተባለችውን ልጁን



ለሙሴ በሚስትነት ሰጥቶት የመጀመሪያውን ወንድ ልጅ ወለደችለት፤ እርሱን የባዕድ አገር ስደተኛ ነኝ ለማለት ጌርሳም ብሎ ጠራው።

(ትርጓሜ ከዚሁ ከሙሴ የስደት ታሪክ ጋር—ፍጹም-ተመሳሳይና-አስድናቂ-የሆነ-መንፈሳዊና፡ ማኅበራዊ ትምህርት የምናገኝበት አንድ የሀገራችንም ታሪክ እንደሚከተለው ለትርጉማዊ ግንናዘቢያ በተጓዳኝ ምሳሌነት አቅርበነዋል፡ ርእሱ፡ "*በካፋ በጎጃም ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍት ት/ቤት* ይአሞል ነው።

_አቤቶ በካፋ በአባታቸው በአፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ቤተ መንግሥት መምህር ተቀጥሮላቸው ሲማሩ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብና የጸሎትም ሕይወት ነበራቸው ። በይበልጥም ድግሞ የቅኔና የትርጓሜ መጻሕፍት ትምህርት ለመቅሠም ወደ እናታቸው አገር ጎጃም ተሻግረው፣ ተዋናይ ከተባለው ከታላቁ ምሁር ደቀ መዝሙር ጋር ጓደኞሞች ሆነው በቂ ባህላዊና ብሔራዊ የአብነት ትምህርት ለመማር ጥሩ ዕድል ገጥሚቸዋል። እንደገናም በአባታቸው ባፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ፈቃድ ወደ ጐንደር ተመልሰው ሥርዓተ መንግሥት በማጥናት ላይ ሳሉ ወንድሞቻቸው አቤቶ ተክለ ሃይማኖትና አቤቶ ዳዊት "የአባትችንን መንግሥት ሊወርስ ነው' በሚል ምቀቀኝነት ሊያጠፏቸው ሲዘጋጁ ልክ ሙሴ ወልደ እንበረም ወደ ምድያም አገር እንደተሰደደ፡ ተሰደው ወደ ግብጽ በረሃ ለመሄድ ወሰኑ። በጉዞም ላይ ሳሉ ቋራ በረሃ ሲደርሱ በድንገተኛ የወባ በሽታ ታመው ወደቁ።

_በዚያም እሸቴ ጌታ የተባሉ የሀገር ባላባት አግኝተዋቸው ከወደቁበት በማንሣት ከየት እንደመጡ ሲጠይቋቸው በትምህርት ቤት መጠሪያ ስማቸው "ዐጽመ ጊዮርጊስ እባላለሁ። በጐንደር የአንድ ባላባት ዝሬ ልጅ ነኝ። አባቴ ስለሚወደኝ ወንድሞቼ ተመቅኝተው ሊያጠፉኝ ስለፈለጉ ወደ ግብጽ በረሃ ለመሰደድ ፈልጌ ነው በግዞ ላይ። ያለሁት አሏቸው። እሸቴ ጌታም-አዝነውላቸው-የመጀመሪያ-ትልቋ-ልጃቸው-ምንትዋብ እንድታስታምማቸው አዘዙ።_ከሕመማቸው እንደዳኑም ልክ ዮቶር ካህነ ምድያም ለሙሴ ሲፖራን እንዳደረለት፡ እሸቴ ጌታም ልጃቸውን ምንትዋብን ድረውላቸው በከፋ የቋራ ኑዋሪ መሆን ጀምረው ነበር። እንደገና ዘመዶቹን ጠይቄ ልምጣ በሚል ሰበብ ወደ ጎጃም ተሻግረው የጀመሩትን ትምህርት እንደቀጣሉ ወንድማቸው ዳዊት ሲነግሥ" ይቀናቀኑኛል" በሚል ፍርሐት ከጎጃም አስወስዶ ወህኒ እምባ ላካቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር ያቀደላቸው ዕድል ተሰናክሎ አልቀረም ፡ የሰሜን ጐንደሩ ገዢ ደጃዝማች አምኃ ኢየሱስ ድጋፍ



www.ethiopianorthodox.org

ሰጪ ሆነውላቸው ከውህኒ አምባ አውጥተው በነጭ ፈረስ ላይ ጉብ አድርገው ይዘዋቸው ሲመጡ አይቶ ሕዝቡ በታላቅ ደስታና በእልልታ ተቀብሏቸው፡ አባታቸው ዓፄ ኢያሱ ባሠሩት ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሥርዓተ ንግሥ ተፈጽሞላቸው መሲሕ ሰገድ በሚል ስመ መንግሥት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ለመሆን በቁ።

_የኑሮ ጓደኛን በሚመለከት የክፉ ቀን ታዳጊ የሆነችላቸውን ምንትዋብን ወደ ጐንደር ቤተ መንግሥት ለማምጣት ወሰነው" የቋራውን ገዢ አገርህን ለመጐብኘት ስለምመጣ ሕዝቡን አስተባብረህ ጠብቀኝ" ብለው መልእክተኛ ሰደውለት ስለነበር ዳስ አስጥሎ፡ ድንኳን አስተክሎ ቆያቸው፡ እርሳቸውም ካጀቢዎቻቸው ጋር እዚያ እንደደረሱ ከባለሟላቸው ከጸሐፌ ትእዛዝ አዛዥ ሲኖዳ ጋር ብቻ በምሥጢር ተነጋግረው_እርሳቸውን ይመስላል የሚባል አንድ ሰው ዙፋን ጠባቂ አድርገው፡ ቀድሞ በት/ቤት ይጠቀሙበት የነበረውን የተራ ሰዎች ልብስ ለብሰው ከሁለት ጋሻ ጃግሬዎቻቸው ጋር በቀጥታ ወደ ባላባቱ እሸቴ ጌታ ቤት አመሩ። እሸቴ ጌታም ንጉሠ ነገሥት መሆናቸውን ሳያውቁ በዚያ ቀድሞ በሚያውቁት የት/ቤት መጠሪያ ስማቸው "ዐጽመ ጊዮርጊስ ! እንኳን ደህና መጣህ፡ ሁላችንም ተጨንቀን። ሚስትህ ምንትዋብም በብርቱ እያዘነች ስንጠብቅህ ነበር። እንግዲህ እናንተ እዚህ ዕረፍት አድርጋችሁ ፡ ተጫወቱ። እኔ ግን ታላቁ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ በካፋ አገሬን ሊጐበኙ ስለመጡ ለማስተናገድ ወደርሳቸው መሄድ አለብኝ" አሉ።

_ዐጽመ ጊዮርጊስም "ታዲያ ምን አለ እኛስ ከርስዎ ጋር አብረን ሄደን አቀባበል ብናደርግላቸው ?" አሉ። እሸቴ ጌታም ደስ ብሏቸው "እኔማ እንዳይደክምህ ብዬ ነው እንጂ አብረን ብንሄድማ ደስታውን አልችለውም። እንዳውም ለንጉሠ ነገሥቱ ለዓፄ በካፋ ቅኔ ታበረክትላቸዋለህ " አሉ። ከዚህ በኋላ ምንትዋብ ለንጉሠ ነገሥቱ የሚቀርብ ማለፊያ ልዩ ምግብ በመሶብ ወርቅ ተሸክማ እፊት፡ እፊት ቀድማ እየመራች፡ ተከታትለው ንጉሡ ወዳረፉበት ድንኳን ሄዱ። አዛዥ ሲኖዳ በካፋንና ምንትዋብን ለይተው ወደ እልፍኝ አስገቧቸው። እሸቴ ጌታም ወደ ድንኳኑ አዳራሽ ገብተው ከመኳንንቱ ጋር እንዲቀመጡ ተደረገ።_ወደ እልፍኙም እንደገቡ በካፋ የተራ ሰው ልብሳቸውን ለውጠው ልብሰ መንግሥት መልበስ ጀመሩ። የምንትዋብንም እጅ ይዘው "ደስ ብሎኛል፡ ደስ ይበልሽ ! አይዞሽ እንግዲህ አትፍሪ፡ አትደንግጪ፡ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዓፄ በካፋ



ማለት እኔ ነኝ። ካሁን በኃላ እንቺም ንግሥት ነሽ፡ ይህን ልብሰ መንግሥት ልበሺና ሕዝቡ ወዳለበት አዳራሽ እንገባለን " ሲሏት ደንግጣ ሰመመን ወሰዳት። አልባሾች በማበረታታት እያፅናኑ አልብሰዋት በዓፄ በካፋ ቀኝ ጎን-ሆና-ብሙሽርነት ወደ ድንኳኑ አዳራሽ ሲገቡ እልልታው ቀለጠ። ጭብጨባው አስተጋባ። ወዲያውኑ በሥርዓተ ተክሊል ጋብቻቸው ተፈጸመ ! በታላቅ ተድላ ደስታ አድረው፡ በማግሥቱ በታላቅ ክብር ታጅበው፡ ግርማ ለብሰው፡ ግርማ ተጐናጽፈው በሆታና በእልልታ ታጅበው ወደ ጐንደር ቤተ መንግሥታቸው ተመለሱ። የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ ያለበት ይህ ሁሉ ታሪካዊ ድንቅ ሥራ እኛና ልጆቻችንም ሁሉ ልንማርበትና ልንመከርበት የተጻፈ ስለሆነ ፡ የዚህ ድንቅ ሥራ ባለቤት የሆነ የሕያው አምላካችን ቅዱስ ስም የተመሰገነ ይሁን ፡ አሜን! """"""""""""""""""""""""""""""""

23-25፡-ክዚያ-በኋላ፣የግብጽ-ንጉሥ-ፈርዖን-መሞቱ-ተነገረ። የእስራ ኤል-ሕዝብ- ግን፣ አሁንም በከባድ የባርነት አገዛዝ ቀንበር-ሥር ነበሩ። እግዚአብሔር ጩኸታቸውን ሰማ፡ ጭንቀታቸውን አየ፤ከአብርሃም፣ ከይስሐቅና ከያእቆብ-ጋር የገባውንም-ቃል-ኪዳን አሰበ።

፫ /3. <u>የመሴ መጠራት</u>፣ 12-25 እነሆ፣ ሙሴ የምድያም ካህን የሆነውን የዮቶርን በጎች ይጠብቅ ነበር። መንጋውንም እየነዳ የእግዚአብሔር ተራራ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ኮሬብ ( ሲና ) ጥግ ደረሰ።እዚያም፣የእግዚአብሔር-መልአክ በእሳት ነበልባል በተቀጣጠለ የቍጥቋጦ ሐመልማ ውስጥ ህኖ ታየው። ቍጥቋጦው በእሳት ተያይዞ ሳለ፣ ነበልባል ሐመልማሉን-ሳያቃጥለው፣ ሐመልማሉም- ነበልባሉን- ሳያጠፋው-በመቅረቱ-ተገረመ። እግዚአብሔርም ሙሴን፣‹‹የቆምክባት ምድር የተቀደሰች ናትና፣ ጫማህን አውልቅ›› አለው።

(<u>ትርጓሜ፡</u> ነበልባሉ ከሐመልማሉ ጋር ተዋሕዶ ፣ ተቀጣጥሎ እያለ ቅጠሉ ሳይቃጠል መታየቱ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑ እስራኤል በግብጽ የባርነት አገዛዝ ሥር ሳሉ፣ መከራው ዝግዛቸው እንጂ፣ እስከ መጨረሻው ድረስ ያላጠፋቸው መሆኑን ያሳያል። አንድም፣ ነበልባል የመለኮት፣ ሐመልማል ወይም እፀ-ጳጦስ የቡርክት የቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋ ምሳሌ ነው። ሐመልማል ከነበልባል ተዋሕዶ ሳይቃጠል መታየቱ የድንግል ማርያም ሥጋ በመለኮት እሳት አለመቃጠሉን ያመለክታል ማለት ነው። አንድም ደብረ ሲና የቤተ ክርስትያን ምሳሌ ናት። የቆምክባት ምድር የተቀደሰች ስለሆነች፡ ጫማህን አውልቅ " ተብሎ እንደተጻፈ በተለይ ወደ እኛ ኦርቶዶክሳዊት



www.ethiopianorthodox.org

*ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጫማን አውልቆ መግባት የተለምደውም ይህን ቃል መመሪያ በማድረግ ነው። አንድም በዚሁ በጫማ አንጻር ቂም-ብቀልን፣ ቅናት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነትን ከልብ ሡኮና አውልቆ መጣል ይገባል ተብሎ ተተርጕሟል።)* ----------

6_ከዚያም በመቀጠል እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፣ ‹‹እነሆ፣ እኔ የአባትህ-የአብርሃም-አምላክ፣ የይስሐቅ-አምላክ፣ የያዕቆብም-አምላክ-ነኝ፤ በግብጽ የሚኖሩ የሕዝቤን የእስራኤልን-ጩኸት-ሁሉ-በእውነት-ሰምቻለሁ፤8-ስለዚህም ላድናቸው ወርጃለሁ፣ ግብፃውያን በእነርሱ ላይ ያደረሱባቸውን ግፍና ጭቈና ተመልክቻለሁ፤ ስለዚህም፣ ልታደግቸውና ከዚያች አገር ላወጣቸው ስለ ወሰንኩ፣ እነርሱን ነጻ ታወጣ ዘንድ አንተን ወደ ግብፅ ንጉሥ ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ፡፡ ለአባቶቻቸው ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያእቆብ የሰጠኋቸውን የተስፋ ቃል (ኪዳን) በማሰብ ከዚያ የባርነት አገዛዝ ነጻ አውጥቼ ማርና ወተት የሚፈስባትን ለምለም ምድር (ከነዓንን ) አወርሳቸዋለሁ ››፡፡

13-14 ሙሴ ወደ ግብፅ ሄዶ ያን ሕዝብ ነጻ ማውጣት ከእርሱ አቅም በላይ መሆኑን ገለጠ፤ እግዚአብሔር ግን፣ እርሱኑ ለመላክ ስለ ወሰነ፣‹‹ ታዲያ ማን ላከኝ ብዬ ልንገራቸው?›› ሲል ሙሴ ጠየቀ፡፡እግዚአብሔርም ‹‹ዘሀሎ ወይሄሉ የነበረ፡ ያለና የሚኖር ተብሎ የሚጠራ አምላክ ልኮኛል ብለህ_ትነግራቸዋለህ››አለው፡፡*(ትርጋሜ፡ሙሴስ የዋህ እምኵሎሙ ደቂቀ እስራኤል= ሙሴ ከእስራኤል ልጆች ሁሉ የተለየ የዋህና ትሑት ሰው ነበር" ተብሎ እንደተጻፈ (ዘኍልቍ 12፡3፡ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ለዚህ ታላቅ የነጻ አውጪነት ተግባር እንዲመረጥ ያደረገው ይኸው የዋህነቱና ትሕትናው ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ትሑታንና የዋሆች ሰዎችን ይወዳል፡፡_ለምሳሌ በእስራኤል ሕዝብ መካከል ከነበሩት የዋሃን /ትሑትን ሰዎች መካከል አንዱ ነቢዩ ዮናስ ነበር፡፡ ውደ ነነዌ ሂድና ያች አግር እንዳትጠፋ ሕዝቡ በንስሐ ወደ እኔ እንድመለሱ አስተምራቸው " ብሎ አዘዘው፡፡ የዋሁ ዮናስ ግን ወደ ዚያች አግር መሄድ ስላልፈለገ እግዚአብሔር የማያየው መስሎት በሸልክታ ወደ ጠርሴስ /ሕስፔይን ለመኮብለል ውስኖ፡ ገንዘብ በመክፈል መርከብ ላይ ተሣፈረ፡፡ እግዚአብሔር ግን ያንኑ የዋህ ሰው መላክ ስለፈለገ ሳይወድ በግዱ በዓሣ አንበሪ ተውጦ ነነዌ እንዲደርስ አድርጎታል፡፡ ሙሴም እንደዚሁ አንደበተ ርቱዕ "ባለመሆኑ ወደ ግብጽ ፈርዖን መሄድ አልፈለገም ነበርና ብዙ ምክንያት ቢያቀርብም እግዘአብሔር አልተቀበለለትም፡፡ ያለው ምርጫ*



*ታዛዥ ሆኖ መገኘትና ጕዞውን ለመቀጠል መዘጋጀት ብቻ ነበር፡፡ ሌላውን ነገር ሁሉ ባለቤቱ እግአብሔር አቃንቶለት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ማውጣት ችሏል፡፡ የዘፀአት መጽሐፍ ይህኑ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ሁሉ የምናይበት ነው፡፡ ብፁዓን የዋሀን ልብ =ልበ የዋሆች ብፁዓን ናችው ብሎ የተናገረ አምልክትን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ እንደ የዋሃኑ ነቢያት እንደ ሙሴና እንድ ዮናስ ንጹሕ ልብ ፈጥሮልን የማስተዋልን ጥበብ እንዲሰጠን ቅዱስ ፈቃድ ይሁንልን፡ አሜን ! )*

## ፬ -/4. እግዚአብሐር ለሙሴ የሰጠው ሁለት ምልክቶች፤

1-–7 እግዚአብሐር ባዘዘው መሠረት፣ ሙሴ በእጁ የያዛትን በትር መሬት ላይ ሲጥላት ተለውጣ እባብ ሆነች፤ ጅራትዋን ይዞ ሲያነሣትም ደግሞ ወደ በትርነትዋ ተመለሰች፡፡ ቀጥሎም፤ "እጅህን በብብትህ ውስጥ አድርግ" አለውና መልሶ ሲያወጣው በለምጽ እንደ በረዶ ነጭ ሆኖ ታየው፡፡ እንደ ገና አስገብቶ ሲያወጣው ደግሞ ተመልሶ እንደ ቀድሞው ጤናማ) ሆነለት፡፡ እነዚህን ሁለት ምልክቶች በግብፅ ንጉሥ በፈርዖን ፊትማሳየት እንደሚችል እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው፡፡

*(ትርጓሜ፡ በምስጢረ ሥጋዌ ትምህርት እግዚአብሔር ወልድ የሰውን ሥጋ በመዋሐድ፣ ፍጹም ሰው ፍጹም አምላክ ሆነ ስንል፣ እንደ ሙሴ በትር የመለወጥ ጉዳይ ስላልሆነ ያለመለወጥ (እንበለ-ውላጤ)-መሆኑን--የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት-ታስተምራሉ።*

17 ሙሴም፡ ‹‹ጌታ ሆይ፤ እነሆ አሁን ስናገር አንተ ራስህ እንደምትሰማኝ፣ አንደበቴ የቀና ሰው አይደለሁም፣ ድዳ ነኝ፣ ታዲያ እንዴት አድርጌ ማሳመን እችላለሁ?›› ሲል ጠየቀ፡፡ እግዚአብሔር ግን፣ ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹ለሰው ሁሉ፣ አንደበትን የፈጠረ ማን ነው? ድዳነትስ የሚመጣ ከየት ነው?! ከእኔ ዘንድ አይደለምን? ካስፈለገ ወንድምህ አሮን አስተርጓሚ ይሁንልህ›› አለው፡፡27፡ከዚያም በኋላ፣ አሮን ከግብፅ መጥቶ ሁለቱም ወንድማማቾች የእግዚአብሔር ተራራ ተብሎ በሚጠራው በኮሬብ ተገናኝተው ስለ ተልእኮዋቸው አፈጻጸም መነጋገር ጀመሩ፡፡*(አሮን ከራምሴ ከምድያም ሙሴ-ተራክቡ በደብረ ሥላሴ "እንዲሉ) ፡፡*

## ፭ /5. ሙሴና አሮን በግብጽ ንጉሥ ፊት ቀረቡ፡

1-2 ሙሴና አሮን ወደ ግብጽ ንጉሥ ፈርዖን ፊት ቀርበው፣ ‹‹የእስራኤል አምላክ የሆነ እግዚ.ዚአብሔር፣ ሕዝቤን እስራኤልን ልቀቅ! ብሎሃል›› አሉት፡፡



www.ethiopianorthodox.org

ፈርዖን ግን፣ በቍጣ መንፈስ ተሞልቶ እግዚአብሔርን አላውቅም፣ ባሪያዬን እስራኤልንም አልለቅም። እናንተ ሙሴና አሮን ይህን ሕዝብ ለምን በከንቱ ሥራ ታስፍፊቱታላችሁ?" አለ።

፮ /6. እግዝአብሔርም ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፡-"."የግብጽ ንግሥ ፈርዖን እንዲህ እንዳመፀ አይቀርም፡ ሕዝቤን እንዲለቅ በኃይል አስገድደዋለሁ። "አገሬን ለቃችሁ ውጡልኝ" ብሎ እንዲወተውት አደርገዋለሁ፡ እኔ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ መሆኔን አሳውቀዋለሁ። እንዲሁም ከዚህ በፊት ለአብርሃም፡ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ፡ እግዚአብሔር ( ኤሎሂም-ሁሉን ቻይ) ተብሎ በሚጠራው ስሜ-ተገልጬላዋለሁ።-ያህዌ በተሰኘው ቅዱስ ስሜ ግን አልተገላጥሁላቸውም፡ የሙሴና የአሮን ትውልድ 14 -21 የሙሴና አሮን ትውልዳቸው ከነገደ ሌዊ ሲሆን-አባታቸው እንበረም፡እታቸው-ኢዮካብድ-(ዮኬቤድ)-ይባላ (ዘኁል 26፡ 9) ። 23 የአሮን ሚስት ኤልሳቤጥ ወለተ አሚናዳብ ናዳብን፡ አዩድን፡ አልዓዛርንና ኢታምርን ወለደችለት።

፯ /7. ሙሴ የመናገር ችሎታው ያልተሟላ መሆኑን ደጋግሞ በመግለጡ ምክንያት እግዚአብሔር እንዲህ አለው፡ "እነሆ እኔ አንተን ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፡ ወንድምህ አሮንም ነቢይ ይሁንልሀ"። በፈርዖን ፊት ቀርበው መነጋገር በጀመሩ ግዜ ሙሴ የሰማኒያ፡ አሮን ድግም የሰማኒያ ሦስት ዓምት ሰዎች ነበሩ። ከታዩት ሁለት ምልክቶች አንዱ. የአሮን በትር ወደ እባብነት ተለወጠች፡-13 አሮን በትሩን መሬት ላይ ሲጥላት ተለውጣ እባብ ሆነች። የግብጽ መተተኞችና አስማተኞች ጠቢባንም በትሮቻቸውን መሬት ላይ ጥለው በአስማት ወደ እባብነት እንዲለወጡ አደረጉ።ነገር ግን ወደ እባብነት የተለወጠች የአሮን በትር አስማተኞች በመተት ወደ እባብነት የለወጧቸውን በትሮች ሁሉ ለቃቅማ ዋጠቻቸው።ንጉሥ አርያንም አስማተኞቹም ተመሳሳይ ድርጊት በመፈጸማቸው በነርሱ ጥበብ ተማምኖ ልቡን በማደንደን እንደገና እምቢተኛነትን ገለጠ። ሁለተኛ ሙሴ እጁን ወደ ብብቱ አስገብቶ ሲያወጠው ወደ ለምጽነት ተለወጠ ነበር፡ እንደግና አስገብቶ ሲያወጣው ደህና ሆነ። (***ትርጓሜው፡*** *ሙሴ እጁን ወደ ብብቱ ሲያስገባው ለምጽ የወረሰው መሆኑ የእስራኤል ልጆች ግብጽ ገብተው ሲኖሩ መከራ ላይ መውደቃቸውን ያሳይና እጁን ከብብቱ ሲያወጣው ጤነማ መሆኑ ከግብጽ ባርነት ነጻ ሲወጡ ያገኙትን ደህንነት*



*የመለክታል። ሙሴንና አሮንን ከተፈታተኗቸው ዋና፡ ዋናዎቹ አስማተኞች መሐል በተለይ ኢያኔስና ኢያንበሬስ የሚባሉ እንደነበሩ ተጽፏል ( 2 ምጢሞ 3፡ 8)። ካሁን በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር በግብጽ ላይ ሊያማጣው ያቀደው ዘጠኝ መቅሠፍት" ዐሥረኛ ሞተ በኩር፡ ዐሥራ አንደኛ ስጥመት አፈጻጸሙ እንደሚከተለው ነበር። )* """""""""

14፡ 15 የዓባይ ወንዝ ውኃ ወደ ደምነት ተለወጠ (1ኛ መቅሠፍት) ፡.

፰/8፡የግብጽ ምድር በእንቊራሪት/ጓጕንቸር ተወረረች (2ኛ መቅሠፍት).

1-7. አሮን በትሩን በዘረጋ ጊዜ የጓጕንቸር፡( የእንቊራሪት) መንጋ ወጥቶ የፈርዖን ቤተ መንግሥትና የመኳንንቱም ቤቶች ሁሉ፡ ምድጃዎችና የቡሆ ዕቃዎች ሁሉ በእንቊራሪት ተሞሉ። አሮን እጁን ዘርግቶ የምድሩን ትቢያ በበትሩ በመታ ጊዜ እንደ ተርብ የሚናደፍ ቅማል በምድሪቱ ላይ እንደ አሸን ፈላ ( 3ኛ መቅሠፍት ). ። ሰውንና እንስሳቱን ሁሉ የሚያሳክክ ተባይ ተነሣባቸው። የግብጽ ጠቢባንም ሁሉ በቅማል ተበልተው ከሕዝሁ ጋር አብረው በማከክ ስለተሸነፉ "ዝሰ አጽባዕተ እግዚአብሔር=ይህስ የእግዚአብሔር ጣት ነው" አሉ። 20፡24 የተቈናጣጭ ዝንብ መንጋ አካግሥ፡እጅግ አስፈሪ ሆኖ ታይቶ ነበር ።

፱ /9. አሰቃቂ የከብት በሽታ ( 4ኛ መቅሠፍት ) ፤ 1-7 በአገሪቱ እንስሳት ላይ የደረሰው የከብት እልቂት እጅግ የሚያሰቅቅ ሆነ። ( 5ኛ መቅሠፍት.). በጕንጅ የሚመስል አሰቃቂ ቊስል ሕዝቡን አሠቃየ። ( 6ኛ መቅሠፍት)። 8-12 እሳት ከበረዶ ጋር ተቀላቅሎ ዘነመ፤ 13-15 ምድሪቱ በመብረቅ ታረሰች፤ በነጐድጓድ ድምፅ ተናወጠች፤ ሰውም እንስሳም በበረዶ አለቀ፤ ሰብሉም ሁሉ ወደመ። 7ኛ መቅሠፍት / ሻህኝ ፡ በጉንጅ የሚባል ቊስል በእንስሳት ላይ ወጣ።

1 /10. ከእግዚአብሔር ታዝዞ የመጣ የአንበጣ መንጋ

(8ኛ መቅሠፍት) ፡21-28 ማር- ቅጠሉንና-ሰብሉን፣አዝርዕትና አትክልቱን ሁሉ፣የደኑንም ዛፍ ጭምር መድምዶ ጋጠው (አጠፋው)። ( 9ኛ መቅሠፍት ): ድቅድቅ ጨለማ፤ በግብፅ ምድር ለሦስት ቀን ያህል ሕዝብ እርስ በርሱ መተያየት ያልቻለበት፣ በእጅ የሚዳሰስ የሚመስል ድቅድቅ ጨለማ ከእግዚአብሔር ታዝዞ ሸፈናቸው። እስራኤላውያን በሚኖሩባት ምድር ግን ብርሃን ነበር። ያም ጥቅጥቅ ያለ አስፈሪ ጽልመት ( ጨለማ ) ፍርሃትንና ሽብርን ያስከተለ ቢሆንም፣ የፈርዖን ልብ ግን ገና እንደ ደነደነ ነበር፤ ስለዚህም ሙሴን፣ «ከፊቱ ውጣ፣ከአሁን በኋላ ዳግመኛ ፊቱን



www.ethiopianorthodox.org

ለማየት አይፈቀድልህም› አለው።ሙሴም፣ ‹‹አዎን፤ በእውነት አንተን የማላይበት ጊዜ ይመጣል›› ሲል መለሰለት። *(አነጋገሩም ውስጡ ወይራ ሆኖ፣ ከነጭርሱ ለመጥፋት ተቃርበሃል ማለቱ ነበር ) ።*

፲፩ /11፡ 10ኛ ሞት በኵር ወይም የመጀመሪያ ሆነው የተወለዱ ልጆች እልቂት ታወጀ፤ የዘጠኙ መቅሠፍት አመጣጥ እዚህ ላይ ከተፈጸመ በኋላ፣ በግብፅ ምድር ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳና አዕዋፍም ጭምር፣ በኵር ወይም የመጀመሪያ ሆኖ የተወለደው ሁሉ እንደሚሞት ሙሴ አስጠነቀቀ።

፲፪ /12 ሞተ በኵር ።43-47 ሞተ በኵር የተባለው እልቂት የእግዚአብሔር ሕዝብ ተብለው ወደሚጠሩት ወደ እስራኤል ልጆች ቤት ሳይገባ፣ አልፎ መሄዱ ፋሲካ (Passover )ተብሎ ተጠራ።ያም የሞተ በኵር አደጋ አልፎ እንዲሄድ ለማድረግ፡ እያንዳንዱ ቤተ-ሰብ አንድ ዓመት የሆነውን የበግ ወይም የፍየል ጠቦት (ቀንዱ ያልከረከረውን፣ ጥፍሩ ያልዘረዘረውን፣ ጠጉሩ ያላረረውን ) መርጦ ማረድና ደሙን ተቀብሎ በየቤቱ ደጃፍ መቃንና ጉበን ላ-መቀባትና እንዳለበት ታወጀ /ተነገረ።ያም ዕለት እስራኤል ከግብጽ ባርነት ነጻ የወጡበት ታላቅ የተድላ የደስታ ቀን በመሆኑ፣ ፋሲካ ተብሎ ተጠራ። ሕዝቡ ሰባት ቀን ሙሉ እርሾ ያልነካውና ያልቦካ ቂጣ እንዲበሉ ትእዛዝ ተሰጠ። 46 ።የፋሲካውን ጠቦት ሥጋውን ጠብሰው፣ ጫማቸውን ሳያወልቁ በትራቸውን እንደ ያዙ፣ በችኮላ እንዲመገቡት ታዝዘዋል። ይኸውም ከግብጽ ምድር የወጡበትን አጣዳፊ ጊዜ ለማስታወስ ሥርዓት ሆኖ እንዲታሰብ ታወጀ። "ኢትስብሩ ዐፅሞ-ለበግዕ= የጠቦቱንም-አጥንቱን አትስበሩት" ተብሎ ተነገራቸው በመጨረሻም ከንጉሡ አልጋ ወራሽ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድሃ የሰው እሬሳ የሌለበት ቤት ከቶ አልነበረም።*(ትርጓሜ፡የበግ-ጠቦት የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ የተባለ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። (ዮሐ. 1፡ 54 ) ለቤዛ ዓለም ዘፀ ቀራንዮ በተባለው ቦታ በመስቀል ላይ ከመሰቀሉ ሳምንት ያህል ቀደም ብሎ፣ወደ ይሁዳ ምድር መሄድን ትቶ ኤፍሬም ተብላ ወደምትጠራ ትንሽ ከተማ ሄዶ መቄየቱ፣ የፋሲካው ጠቦት ለእርድ በመዘጋጀት ተጠብቆ ይኖር እንደ ነበር፣ እርሱም ለሞት መዘጋጀቱን ያሳያል ( ዮሐ 11፥54 ) ።አጥንቱን አትስበሩት የተባለበት -ምክንያት -ጌታ -ከከፉ- አድራጊዎች-ጋር- በተሰቀለ ጊዜ የሌሎችን ወንበዴዎች- ጭን፡-ጭናቸውን -ሰብረው-*

*〃*



*አስከሬናቸውን_ሲያወርዱ-የርሱን-ዐፅም_አለመስበራቸውን-ያመለክታል- (ዮሐ,19፡ 33)። በመሠረቱ የእስራኤል ሕዝብ በግብጽ ምድር የኖሩበት ዘመን ሁለት መቶ አሥራ አምስት ዓመት ብቻ ሲሆን፣ እዚህ ላይ (ዘፀ 12፡ 40 ) ዐራት መቶ ሠላሳ ዓመት ተብሎ የተጻፈበት ምክንያት አብርሃም ከተጠራበት ጊዜ ጀምሮ ያለውን ዘመን በመቍጠር ነው። ይህንንም ሐዋርያው ቅ/ ጳውሎስ ለገላትያ ምእመናን በጻፈው መልእክቱ እንደ ገለጠው፣ ‹‹የተስፋው ቃል ከተነገረ በራት መቶ ሠላሳ ዓመት በኋላ የተሰጠው ሕግ፣ አስቀድሞ በእግዚአብሔር የተረጋገጠውን የተስፋ ቃል መሻር አይችልም›› ይላል (ገላ 3፡ 15-17)። _እዚህ ላይ ግእዙም ወነድረቶሙ ለደቂቀ እስራኤል ዘነበሩ ምድረ ግብጽ ወምድረ ከነዓን እሙንቱ ወአበዊሆም ዐርባዕቱ ምዕት ወሠላሳ ዓመት "የሚል ገጸ ንባብ ስላለው ለዚህ ትርጕማዊ አባባል አስተዋፅኦ አለው። )* ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

የእግዚአብሔር ሕዝብ የግብጽን ምድር ለቀው ወጡ (1 6 )

ልክ በምዕ 6፡ 2 እግዚአብሔር እንደ ተናገረ፣ እነሆ፣ ንጉሡ ፈርዖንና የግብጽ- ሕዝብ- እስራኤላውያኑን፣ "እባካችሁ-አገራችንን-ለቃችሁ- ውጡልን፡ አታስፈጁን፣ የፈለጋችሁትን ሀብት- ንብረት ሁሉ ውሰዱ›› እያሉ መወትወት ጀመሩ። እስራኤላውያን የወርቅና የብር ጌጣጌጥ፤ እንዲሁም ልብስና ገንዘብም ጭምር፣ የፈለጉትን ሁሉ በጠየቁ ጊዜ፣ ግብጻውያን የጆሮ ጉትቻና የአንገት ሐብል፣የጣት ቀለበት ሳይቀር እያወለቁ ይሰጧቸው ዘንድ እግዚአብሔር የሕዝቡን ልብ ሁሉ አራርቶላቸው ነበር። 36- 37 ፡ያም ሁሉ ስጦታ፣ በባርነት ላገለገሉበት ዋጋ እንደ ካሣ ሆኖ የሚቈጠር ነበር። ሴቶችና ልጆች ሳይቈጠሩ፣ ተመዝግበው ጕዞ የጀመሩት ድምር 600,000 ስድስት መቶ ሺህ ነበር።

፲፫ /13. በኵር የሆነ ሁሉ ለእግዚአብሔር የተለየ እንዲሆን ታዘዘ፡

1-2 በግብጻውያን ላይ የደረሰውን የበኵር ልጆች እልቂት ለማስታወስ፣ ከእስራኤል ሕዝብም ሆነ ከእንስሳ፣ በኵር ሆኖ የሚወለድ ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር ተለይቶ የተቀደሰ እንዲሆን ታወጀ።

የሕዝቡ የበረሃ ጕዞ አመራር፤ 17-19 እግዚአብሔር ሕዝቡን ከግብጽ የባርነት አገዛዝ ነጻ ካወጣ በኋላ፣ ቅርብ ከሆነው ጥግ-ጥጉንብን በፍልስጥ ኤም የባሕር ጠረፍ በኩል ሳይሆን፣ ዙሪያ ጥምጥም በሆነው በዋናው



www.ethiopianorthodox.org

የበረሃ መንገድ፣ ወደ ቀይ ባሕር አቅጣጫ መራቸው። ጉዞአቸውም ልክ ለጦርነት እንደ ተዘጋጁ (እንደ ተሠለፉ) ዓይነት ሆነው ነበር። በኑዛዜውና በገቡለት ቃለ-መሐላም መሠረት፣ የዮሴፍን ዐፅም (አስከሬን) ይዘው ተጓዙ። እግዚአብሔር ራሱ ከቀን ሐሩር ለመጠበቅ ቀን እንደ ደመና፣ ጨለማንም ለማስወገድ ሌሊት እንደ ብርሃን ምሰሶ (ዓምድ) ሆኖ ይመራቸው ነበር እግዚአብሔር አምላክ ሕዝቡን ቅርብ በሆነው በባብ ኤል-መንደብ ማሳለፍ ሲችል፣ዙሪያ-ጥምጥም-በሆነ-የበረሃ-መንገድ-ወደ-ባሕረ-ኤርትራ-( ቀይ-ባሕር ) በማምራቱ ብዙ ደክሙ።

**(<u>ትርጓሜ</u>:** *ይህም በክርስቶስ የሚያምኑ እስራኤል-ዘነፍስ ተብለው የሚጠሩ ምእመናን ) ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት የሚችሉት በብዙ ገድልና ትሩፋት።በፈተናም-ውስጥ-በማለፍ-መሆኑን-ያመለክታል (የሐዋ-ሥ 14፡-22፡)*

፲፬ /14 <u>እስራኤላውያን ቀይ ባሕር ተከፍሎላቸው ተሻገሩ፡</u>

21--22 እግዝዚአብሔር እንዳዘዘው ሙሴ በትሩን በኤርትራ በባሕሩ ላይ ሲዘረጋ ባሕሩ ከሁለት ተከፍሎላቸው ውኃው ወደ ኋላ ተመለሰና በግራና በቀኝ እንደ ግድግዳ- ቆመ።-የእስራኤልም-ሕዝብ-በደረቅ ምድር ተሻገሩ። በዚያም ጊዜ፣ የግብጽ **ንጉሥ** ፈርዖን፣ እስራኤል አገሩን ለቀው መውጣታቸውን ሲያይ፣ እንደ ገና ቈጭቶት ሠራዊቱን በማስከተት፣ በስድስት መቶ ሠረገላና በብዙ ፈረሰኞች ታጅቦ፣ ወደ ቀይ ባሕር አመራ። የእግዚአብሔር ሕዝብ ከተሻገሩ በኋላ ፈርዖንና ሠራዊቱ ከሁለት ተከፍሎ እንደ ግድግዳ በቆመውም ውሃ መካከል ለማለፍ ተዘጋጁ።

**<u>በግብጻውያን ላይ የደረሰ ስጥመት:</u>** እግዚአብሔር ሙሴን፣ ‹‹በትርህን በባሕሩ ላይ ዘርጋ›› አለው። ሙሴም በትሩን ሲዘረጋ፣ በቀኝና በግራ እንደ ግድግዳ ቆሞ የነበረው ውኃ፣ በግብጽ ንጉሥ ፈርዖንና በሠራዊቱ ላይ ተከነበለ፤ ያም ሁሉ ሠራዊት ከነሠረገላውና ከፈረሰኞቹ ጋር ሰጠመ። የእስራኤል ሕዝብ ሁሉ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ አይተው ያዳናቸውን እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

፲፭ /15፡ <u>**የሙሴ መዝሙር፣**</u> የነቢዪቱም ማርያም ማኅሌት (ዘፈን)፣ በክብር ከፍ ብሏልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ።ሕዝብህን ርስትህ በሆነው ተራራ ላይ ትከላቸው፤ ይህ ተራራ ማደሪያህ ይሆን ዘንድ አንተ የመረጥኸው ቤተ-መቅደስህ ነውና፡ 9፡-21 የሙሴና የአሮን እኅት የሆነችው ነቢዪቱ ማርያም ከበሮዋን አነሣች፤ ሌሎችም ሴቶች አታሞ እየመቱ፣ ማርያም በዝማሬ-አውራጅ ሆናላቸው እንዲህ አለች፤‹‹ፈረሱንና ፈረሰኛውን



አሽቀንጥሮ ለጣለውና መለኮታዊ ግርማን በተሞላ ሁኔታ ድልን ለተጐናፀፈ አምላካችን ለእግዚአብሔር ዘምሩ››።ሌሎችም ሴቶች ከእርስዋ ጋር አሸበሸቡ።

**<u>እግዚአብሔር መራራውን ውሃ አጣፈጠ</u>፡**

22-26 እግዚአብሔር ለሙሴ አንድ እንጨት አሳየው። እርሱንም ወስዶ በመራራው ውሃ ላይ ጣለው፤ መራራ የነበረውም ውኃ ወደ ጣፋጭነት ተለወጠ። እግዚአብሔርም፣ ‹‹ትእዛዜን ብትፈጽሙ፣ እንደዚህ ውኃ **ፈዋሻችሁ እኔ ነኝ›› አለ**። 27 የእስራኤል ሕዝብ ከዚያ አልፈው፣ አሥራ ኹለት የውሃ ምንጮችና ሰባ ኹለት የቴምር ዛፎች ወዳሉበት ቦታ ደረሱ።'

**(<u>ትርጓሜ</u>:** *እነዚያ ዐሥራ ሁለት የውሃ ምንጮች በብሉይ ኪዳን ዘመን የ12ቱ ነገደ እስራኤል፡ 72ቱ የቴምር ዛፎችም የሰባው ሊቃናት ምሳሌውች ነበሩ፡ በዘመነ ሐዲስ ኪዳን ግን 12ቱ የውኃ ምንጮች የ12ቱ ሐዋርያት፡ 72ት የቴምር ዛፎች የሰባ ሁለቱ አርዳእት ምሳሌዎች ናቸው (ማቴ 10፡ 1 4+ ሉቃ 10፡ 1 ) ።*

፲፮_/16፡- እግዚአብሔር-<u>ከደመና-ያዘነመው_መና፡</u>

13--20 ሥጋ እንዳያምራቸው በምሽት ጊዜ የድርጭት መንጋ መጥቶ ሠፈሩን ሸፈነው።በማለዳም ደግሞ፣ በሠፈሩ ጤዛ ነበር። ጤዛው ከረገፈ በኋላም፣ ደቃቅ የሆነ ነገር ታየ።አመዳይ ይመስል ነበር። ሕዝቡም፣ ‹‹መና›› አሉት። በዕብራይስጥ፣ ‹‹ይህ ምንድን ነው?›› ማለት ነው። ሙሴም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤ ‹‹ይህ እንድትመገቡት-ከእግዚአብሔር-የተሰጣችሁ-ሲሳይ-ነው።እግዚአብሔርም እንዲህ ብሎ አዞአል ‹እያንዳንዱ ሰው በቤተ-ሰቡ ልክ ይሰብስብ፤ አንድ ሰው አንድ **ጎሞር** (መሥፈሪያ) ይውሰድ›። ነገር ግን፣ እያንዳንዱ አብዝቶ፣ ሌላው አሳንሶ ሰብስቦ ነበር፤ ሲሠፈር ግን፣ ጥቂት የሰበሰበ አልጎደለበትም፤ ብዙም የሰበሰበ አልተረፈውም። እንዲሁም ሙሴ የሰጣቸውን ትእዛዝ ባለመከተል፣ ከዚያው መና ለነገ ይሆናል ብለው አስተርፈው ያሳደሩ ነበሩ፤ በማግሥቱ ሲታይ ግን፣ ተልቶ-ተበላሽቶ ተገኘ። ለሰንበት ቀን አትርፈው ያሳደሩት ግን አልተበላሸባቸውም። አንዳንድ ሰዎች በሰንበት ቀን ለመሰብሰብ ወጡ፤ ነገር ግን መና አልተገኘም። ያ መና መልኩ ነጭ ሆኖ የድንብላል ፍሬ የሚመስል ሲሆን፣ እንጀራና ዳቦ አድርገው ቢጋግሩት፣ቅንጬ አድርገው ቢመገቡት እንደ ፈለጉት መሆን የሚችልና፣ ጣእሙም እንደ ማር ኬክ (ቂጣ) አይነት ጣፋጭ ነበር።

፲፯ /17፡ **እግዚአብሔር ለሕዝቡ ውኃ ከዐለት <u>አፈለቀላቸው</u>**

1--6 እግዚአብሔር ሙሴን፣ ‹‹በተቀደሰው ተራራ በኮሬብ በሚገኘው ዐለት (ድንጋይ) ፊት ለፊት እቆማለሁ፤ አንተ ዐለቱን በበትርህ ምታው፤



www.ethiopianorthodox.org

እኔም ለሕዝቡ የሚጠጡትን ውኃ አፈልቅላቸዋለሁ›› አለው፤እንዳለውም ሆነ፡፡ *(ትርጓሜ ፡እነሆ ፡ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤ ይከተላቸው ከነበረው ከዚያ ዐለት /ድንጋይ የፈለቀላቸውን ውኃ ጠጥተዋልና፡ ያም ዐለት ክርስቶስ ነበር (1 ቆሮ 10፡4--5 ፡፡)*

**ሙሴ በጸሎት ፡ኢያሱ በቀስት** ፡ 8--18 እስራኤል ረፊዲም በተባለው ቦታ ሠፍረው ሳሉ፣ አማሌቃውያን ወጥተው አደጋ ሊጥሉባቸው መጡ፡ ፡ ሙሴም ኢያሱን ተርቶ ‹‹ ጕልማሶችን ምረጥና ወጥተህ ተዋጋ፤ እኔ በነገው ቀን የእግዚአብሔርን በትር ይዤ በኮረብታው ራስ ላይ እቆማለሁ›› ብሎ አዘዘው፡፡ ሙሴ በተራራው ራስ ላይ እጆቹን ወደ እግዚአብሔር ዘረጋ (ለጸሎት ማለት ነው)፡፡ በድካም እንዳይዝልም አሮንና ሆር በግራና በቀኝ ሆነው ክንዱን ደገፉለት፡፡ ሙሴ በርትቶ እጁን በዘረጋ መጠን ፤ እስራኤል ድል ሲያደርጉ፣ እጁ ዝሎመዘርጋት ሲያቅተው ደግሞ፤ አማሌቃውያን ለማሸነፍ ይሞክሩ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ የሙሴ እጆች ፀሐይ እስክትጠ ልቅ ስለ ጠነከሩ፣ኢያሱ በሰይፍ ስለት አማሌቃውያንን ድል ነሣ፡ 15 ከዚያ ድል በኋላ፣ሙሴ መሠዊያ ሠርቶ፣ ‹‹ያሕዌህ ንሲ (እግዚአብሔር የድል ሰንደቅ አላማዬ )›› ብሎ ጠራው፡፡

*(**ትርጓሜ**፡ ምን ጊዜም ቢሆን፣ እንደ ሙሴ እጁን ዘርግቶ በትጋት ወደ እግዚአብሔር የሚጸልይ መንፈሳዊ አባት (መሪ ) ሲኖር፣ እንደ አሮንና እንደ ሆር መተባበርና በብርቱ መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ‹‹የዛሉ እጆችን አንሡ፥ የደከሙ ጕልበቶችንም አበርቱ›› (ዕብ 12፡ 12--13 ፡፡ )*

## ፲፰ /18፡ የሙሴ አማት የዮቶር ጉብኝትና የሰጠው ምክር፡

1-12 የሙሴ አማት ዮቶርም፣ እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤልን ከግብጽ መርቶ ባወጣቸው ጊዜ፣ ያደረገላቸውን ድንቅ ሥራ (ታምራት) ሁሉ ሰምቶ ስለ ነበር፣ የሙሴን ሚስት ሲፓራንና ሁለቱን ወንዶች ልጆቹን ይዞለት መጣ፡፡ ከደስታው ብዛት የተነሣ ሲናገርም፤‹‹ከግብፃውያን የባርነት ቀንበር ሕዝቡን ነጻ ያወጣ እግዚአብሔር ይክበር - ይመስገን፤ እርሱ ባደረገው ድንቅ ነገር፣ ከአማልክት ኹሉ እንደሚበልጥ አሁን አወቅሁ›› አለ፡፡ ለእግዚአብሔርም የሚቃጠል መሥዋዕት አቀረበ፡፡ አሮንና የሕዝቡም አለቆች ሁሉ፣ ወደ እርሱ መጥተው አብረው እንጀራ በሉ፡፡13-27 በዚያን ጊዜ ሙሴ የዳኝነት ሥራ በዝቶበት ብቻውን ሲደክም አይቶ፣ ዮቶር እንዲህ ሲል መከረው፤ ‹‹ይህ ሁሉ የዳኝነት ሥራ በአንተ ብቻ የሚከናወን ከሆነ ይከብድብሃል፤ ይልቅስ፣ ከሕዝቡ መካከል በተለይ



እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፣ የሚያከብሩትንና ከግፍ ሥራ የራቁትን፣ በጉቦ የማይደለሉትን መርጠህ፣ በአንተ ሥር ሆነው ያገለግሉ ዘንድ የሺህ አለቆች፣ የመቶ አለቆች፣ የኀምሳ አለቆችና የዐሥር አለቆች አድርገህ ሹማቸው፡፡ በአንዳንድ አነስተኛ ጕዳዮች ላይ እነርሱ ይፍረዱ፤ ከባድ የሆነውን ግን፣ ወደ አንተ ያቅርቡ፡፡ ይህን ብታደርግ እግዚአብሔር የሚያዝህን ነገር ለማስተማር በቂ ጊዜ ይኖርህና ፀንተህ መቆም ይቻልሃል››፡፡

## ፲፱ /19፡ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ በሲና ተራራ ግርጌ፡

3--6 እግዚአብሔርም **ሙሴን** ጠርቶ እንዲህ አለው፤ ‹‹ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፤‹‹ቃሌን ብትሰሙና በቃል ኪዳኔም ፀንታችሁ ብትኖሩ፣ ምድር በመላዋ የእኔ ናትና ከአሕዛብ ሁሉ ተለይታችሁ ለእኔ የተቀደሰ ሕዝብ ፣ የክህነት መንግሥት ተብላችሁ ትጠራላችሁ›› ፡፡ 14-15 ሙሴም እግዚአብ ብሔር እንዳዘዘው ሕዝቡ ንጽሕናቸውን ጠብቀው ፣ ልብሳቸውን አጥበው፣ ከሩካቤ ሥጋ ርቀው እስከ ሦስት ቀን ድረስ እንዲቈዩ ነገራቸው (1ሳሙ 21፡ 4-5) ፡፡16-19 በሦስተኛውም ቀን፣ እግዚአብሔር በእሳት አምሳል በወረደ ጊዜ፣ የሲና **ተራራ ተናወጠ**፣ **የነጐድጓድ** ድምፅ አስተጋባ፣ የመብረቅ ብልጭልጭታና ፡የተንጣለለ ድቅድቅ ጨለማም **ታየ** (ዕብ 12፡ 22)፡፡

## ፳/20፡ እግዚአብሔር የተናገራቸው ዐሠርቱ ትእዛዛት፡

1-17 ‹‹እኔ እግዚአብሔር አምላክሀ **ነኝ**፤ **ከእኔ** በቀር ሌሎችን አማልክት **አትከተል**፡፡ በማናቸውም ዓይነት ቅርጽ የተሠሩ ሥዕሎችንና ምስሎችን **አታምልክ**፤ አትስገድላቸውም፡፡ የእኔን የአምላክህን ስም በከንቱ **አታንሣ**፡፡ እግዚአብሔር-ስሙን-በከንቱ-የሚያነሥውን-ሰው-ሳይቀሥፍ **አይተወውምና**፡፡ የሰንበትን ቀን የተቀደሰ አድርገህ ጠብቀው፡፡ በምድር **ላይ** ዕድሜህ ይረዝም ዘንድ አባትህንና እናትህን አክብር፡፡

*(**ትርጓሜ፡** አንተ ለአባትህ ያላደረግህለትን መልካም ነገር ክልጅህ መጠበቅ አትችልም፡፡ ለዚህም ተጓዳኝ የሚሆን እጅግ አስድናቂ የሆነ እውነተኛ ታሪክና ምሳሌ እንዲህ ይላል፡ ቦታው በአቃቂ ወረዳ በሚገኘው የአባ ሳሙኤል ባሕር አካባቢ የሚኖሩ አቶ አብሴ የተባሉ አንድ ታላቅ አዛውንት የነበራቸውን ርስት ጕልትና ሌላውንም ሀብት ንብረት ሁሉ ለበኵር ልጃቸው ለአቶ ብራ አውርሰው እርሳቸው ተጠዋሪ ሆኑ፡፡ ሀብታቸውን ሁሉ የወረሱ ልጃቸው አቶ ብራ ግን አባታቸውን በሥነ ሥርዓት እየመገቡ ተከባክበው መጦር ሲገባቸው፡*



www.ethiopianorthodox.org

ለቁመተ ሥጋ ያህል የባቄላ እሸት እየተሰጣት፣ ጥጆች እየረገጧቸውና ውሻ እየፈለሰሰባቸው ባንሰዲት ትንሽ ጎጆ ውስጥ የመከራ ኑሮ ይገፉ ነበር። የዚያም ሀብት ወራሽ የነበሩት ሰው ደግሞ ብዙ ጊዜ በመሐንነት ከኖሩ በኋላ በመከለኛ ዘመናቸው ወንድ ልጅ ወለዱ። ስሙንም ዱዲ አሉት። ያም ልጅ ከአባቱ ጋር ከብት እየጠበቀም" እያረሰና በመጠኑም እየተማረ በማደግ ላይ ሳለ፣ አንድ ቀን አባቱ "ዮ ኸው እንግዲህ እኔ አንተን በወግ በማዕርግ ተከባክቤ እያሳደግሁህ እዚህ ደርሰሃል።ታዲያ እኔ ሳረጅ አንተ እንዴት አድርገህ ነው የምትጠረኝ ?" ብለው ጠየቁት። ያም ልጅ እጁን አንሥቶ እያቱ ወደሚኖሩባት ጎጆ በጣቱ እየመለከተ፡ "የእንተ አባት፡ ለእኔ ደግሞ አያት ለሆነው ሽማግሌ በምታደርገለት ዓይነት እዚያች ጎጆ ውስጥ ትገባለህ።ያው አሁን እንደምታየው አባትህ /እያቱ በሚኖረው ዓይነት የባቄላና የሽንብራ እሸት ይቀርብልሃል። እስከ ሕይወትህ ፍጻሜ ፣በዚያች ትኖራለህ። ከዚህ ሌላ ከእኔ ምን ትጠብቃለህ ?' አላቸው። """""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""

_አባትዮውም ኡቶ ብራ ይህን ሲሰሙ ደነገጡ። በአባታቸው ላይ ያደረሱት በደል ተሰምቷቸው በመፀፀት አዝነው ወዲያውኑ አባታቸውን ከዚያች ጎጆ ውስጥ አውጥተው በእልፍኝ ድንክ አልጋ አስዘርግተው፣ ጥሩ ምግብና ልብስ ተሰጥቷቸው፣ በወግ፣ በማዕርግ እንደ ገና አዲስ ሕይወት እንዲጀምሩ አደረጉ። ሽማግሌውም አያት፣ ይህን መልካም ዕድል ያስገኘላቸው የልጅ ልጃቸው መሆኑ አውቀው ስለነበር፣ ለልጃቸው ካውረሷቸው ርስት ጉልት ላይ አንድ ጋሻ መሬት ወስደው ለልጅ ልጃቸው ለዱዲ ሰጡት። ያም ልጅ አድጎ በወግ በማእርግ ተድሮ፣ አያቱና አባቱም ሲሞቱ የርስት ጉልታቸው ሁሉ ወራሽ ሆኖ በተድላ በደስታ ሲኖር እንደነበር የሚመሰክሩ አሉ። ) """

_አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በማንም ላይ በሐሰት አትመስክር፥ የሌላው ሰው ንብረት፣ሚስቱንም ሆነ አገልጋዮቹን-ለመውሰ አትመኝ፥ ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ" (ዘሌ 19፥18)፡፡ 2 ሕዝቡም እነዚህን ትእዛዛት በሰሙ ጊዜ፣ ፈርተው በርቀት ቆሙ፡፡ ሙሴንም፣ "አንተ ብቻ ተናገረን፤ እንሰማለን፡፡ እግዚአብሔር-ቢናገረን-ግን፣ እንዳንሞት እንፈ_ራለን" አሉት፡፡

ሿ፭/21፡ የአገልጋዮች /የባሮች ሕጋዊ -አያያዝ፤ 2--6 አንድ ዕብራዊ አገልጋይ ቢኖርህ ስድስት ዓመት ብቻ ካገለገለህ በኋላ፣ በሰባተኛው ዓመት ነጻ እንዲወጣ አድርግ፤ ነገር ግን አገልጋዩ፣ "የጌታዬ ባሕርይ



(ጠባዩ) ተስማምቶኛል፤ ኑሮ ተመችቶኛል፤ ነጻ መውጣት አልፈልግም" ቢል፣ የእግዚአብሔር-አገልጋዮች-ወደ-ሆኑት-ዳኞች-ወስደህ-በፊታቸው አቅርበው፡ በነርሱ አስፈርደህ እዚያው በቤት መቃኖች መካከል፣ በጉበን ላይ አጋድመህ ጆሮውን ተልትለህ፣ በወስፌ በመብሳት ለዘላለም ባሪያ አድርገህ ግዛው፡፡ **(ትርጓሜ** ፡ ይህ ባርነት በሥጋ ብቻ ሳይሆን በጣም የከፋ የሚሆነው የመፈስ ባርነት ሲታከልበት /ሲጨመርበት ነው። ብዙ ሰዎች በልዩ፡ ልዩ መልኩ የመንፈስ ባርነትን ይገባሉ። አንዳንዱ ለዛር አንጋሽ ቃልቻና ጠንቋይ ቡና አፍሊ፣ ካዳሚ ሆነው መኖርን ይመርጣሉ። የጥንቁላ መተት ተብታቢዎች ሥነ ልቡናውን ሰልበው ዓይን በዓይን እያታለሉ ገንዘቡን እየመነተፉ ሲያደጁሉት ይኖራሉ። በቅርብ ጊዜ የተፈጸመ አንድ ተጓዳኝ ታሪክና ምሳሌ እንጥቀስ፡ -ሴትዮዋ በቂ ሀብት ነብረት አላት። ነገር ግን ሳይቸግራት ለሐሰተኛ ጠንቋይ ማሽርገድና ማደግደግ፡ ትወዳለች። ታዲያ አንድ ጊዜ ወደ አንድ ጠንቃይ ትሄድና" "ጥሩ ገቢ ያለው ቡና ቤት አለኝ። ከጥቂት ጊዜ ወዲህ ቀዝቀዝ እያለብኝ መምጣት ጀምሯልና፡ እንዴት ትረዳኛለህ?' ስትለው " ይህ ቀላል ነው፡ በአንድ ሳምንት ውስጥ ታምር ታያለሽ፡ ኃምሳ ሺህ ብር ክፈይ" ይላትና ወዲያውኑ ቼክ ጽፋ ትሰጠዋለች።

_ዐርባውን ሺህ ብር ወደ ባንክ ይልክና ዐሥሩን ሺህ ብር ቀንሶ የጎዳና ተዳዳሪዎችና ሥራ ፈቶች የሆኑ ችግረኞችን ጥሩልኝ ይልና ሰብስቦ " በሉ እንግዲህ ይህን ዐሥር ሺህ ብር ውሰዱና እወይዘሮ እከሊት ቡና ቤት ገብታችሁ፡ ብሉበት፣ ጠጡበት ። በዚያ ቡና ቤት ለሚገኘው ደንበኛ ሁሉ ከበር በመለስ ስጡ ብላችሁ ማዘዝ ትችላላችሁ፡ ካለቀ እጨምራልሁ። በሉ አሁን ሂዱችሁ ተጋበዙ" ብሎ ያዛል። ሄደው ቡና ቤቱን በአንድ ጊዜ ይሞሉትና አንዱ ክትፎ ሲያዝ፡ ሌላው ቁርጥ ሥጋ፡ አንዱ ጎረድ ጎረድ፡ አንዱ ቅቅል፡ ሌላው ምንቸት አብሽ፡ አንዱ ቢራ፡ ሌላው ዊስኪ ወዘተ በማዘዝ ሠራተኞቹን ሁሉ ዕረፍት ነሥተው ትንፋሽ ሲያሳጧቸው ሴትዮዋም ራስዋ ሥራ ማገዝ ጀምራ ስትባክን ቆየችና። ራስዋን ይዛ በገዛ ገንዘብዋ ትያትር ሠርቶ ለተጫወተባት ለዚያ ጠንቃይ ውዳሴ ስታቀርብ "ጠንቋዩ እከሌ እኮ አምላክ እንጂ ሰው አይደለም " አለች። እንደዚህ ያለውን የማጭበርበር ሥራ በብዙ ሺህ እሐዝ መጥቀስ ይቻላል። ግን ማን ቢሰማ? ብዙ ሕዝብ ይህን ዓይነቱን የመንፈስ ባርነት በራሱ ፈቃድ ነትቶ የመጣው ስለሆነ ነጻ መውጣትን ስላልፈለገ፡ ሲመክሩትና ሲያስተምሩትም የዘሆን ጆሮ



www.ethiopianorthodox.org

ይሰጠኝ" ብሏል። ሰይጣን ዲያብሎስ ወደ ገባ አገልጋይ ባሪያ አድርጎ እየተጫወተበት ነው። እንግዲህ በገዛ ገንዘቡ ይህን ያህል የሚታለለውን እልፍ አእላፍ ወይም በብዙ ሚሊዮን የሚቈጠር ይህን ሁሉ የዋህ ሕዝብ ማን ሊታደገው ይችላል ? )
በከንቱ ነው እንጂ የምትሰግዱለት ፡ ትቢያ የምትልሱ፡
ጠንቋይ እንኳን ለሰው አያውቅም ለራሱ።

<u>ሌሎች ልዩ፡ ልዩ ሕግጋት፡</u> 14-16 ባለማወቅ ድንገት ሰውን መትቶ ቢሞትበት ገዳዩ_የሚማፀንበትን ቦታ እኔ አዘጋጃለሁ ፤ነገር ግን ሆን-ብሎ በማወቅ፣አድፍጦ ሰውን የገደለ ከሆነ፣ለጊዜው በደም ፍላት ሊበቀለው ከሚፈልግ ሰው ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ወደመማፀኛ ቦታዬ ቢሄድም፣መግደሉ ከተመሰከረበት ከመማፀኛ ቦታዬ ተወስዶ በሞት ይቀጣ ( 1ነገ 2፡ 29—3 )፡ 15--17 አባቱን ወይም እናቱን ደፍሮ የሰደበ ( የመታ ) በሞት ይቀጣ። 18-19 ሰውን ሰብሮ ወይም ፈንክቶ ያቈሰለ ቢኖር፤ ተደብዳቢው እስከሚድን ድረስ፣ ደብዳቢው ተገቢውን ክብካቤ ያድርግለት። 20 አገልጋዩን መትቶ የገደለ ሰው፣ ተገቢውን ቅጣት ይቀበል።22-25-ነፍሰ-ጡር-የሆነችውን-ሴት-መትቶ-ቢያስወርዳት ባልዋ የሚጠይቀውን ካሣ ይክፈል። የባሰ ጉዳት ቢያገኛት ግን፣ ሕይወት በሕይወት ይለወጥ። ዓይን ያጠፋ ሰው ዓይኑ ይጥፋ፤ጥርስ ይሰበር፣ ጥርሱ ይርገፍ /ይሰሰር፡ እጅና እግርን የቈረጠም የርሱ እጅና እግሩ ይቈረጥ።-ቃጠሎ-በቃጠሎ፣ ቍስል በቍስል፣ ግርፋት በግርፋት ይክፈል።26-27 የአገልጋዩን ዓይን ያጠፋ ሰው ካሣ ይክፈል፣ አገልጋዩንም ነጻ ያውጣ። 28-32 የተዋጊነት ጠባይ ያለውን በሬ ስደ በመልቀቅ ጉዳት-ያደረሰ-ሰው፣ በፈጸመው ጥፋት መጠን ተገቢውን ቅጣት ይቀበል። ጕድጓድ የከፈተም ሰው ወድቆ ለተሰበረበትም ሆነ ለሞተው እንስሳ ዋጋ የሚሆን ለባለቤቱ ይክፈል።35-36 ተዋጊ በሬውን ለቅቆ የሌላውን ሰው በሬ እስኪሞት ድረስ ወግቶ ጉዳት ቢያደርስበት፣ በሬውን በበሬው ፈንታ ይተካ።(**ትርጓሜ።** ይህም እንዲሁ በደፈና-ሳይሆን የድርጊቱ አፈጻጸም ትክክለኛ ፍትሕ ታይቶ ማለት ነው።

**፳፪** /22፡ የቤት ንብረት አጠባበቅ ሕግ፤ 1-3 በሬ የሰረቀ እጥፍ፣ በግ የሰረቀ ግን ዐራት እጥፍ አድርጎ ይክፈል።ሌባ የሆነ ሰው አጥር ሲጥስ፣ ግንብ ሲያፈርስ ተገኝቶ ቢገደል፤በደሙ ተጠያቂ-አይኖርም (ደሙ-ደመ-ከልብ ሆኖ-ይቀራል ማለት ነው)። ፀሐይ ከወጣ በኋላ ቢመታ ግን ደብዳቢው በደሙ ይጠየቅበታል።ስለዚህ ማጕሊያ የሆነ ተግዳኝ



ታሪክና ምሳሌ እነሆ ! <u>"""""ሌባዬን እኔ ራሴ አውቀዋለሁ"""""</u>

**አ**ንድ ግለሰብ በሌሊት ቤቱ ተቆፍሮ፡ አንድ ሣጥን ሙሉ ንብረት ከወርቅና ብር ጋር ስለተወሰደበት ለአካባቢ ባለሥልጣኖች ያመለከትና በአፈርሳታ /በአውጫጪኝ እንዲጣራለት ትእዛዝ ተሰጥቶለት ሕዝብ ተሰበሰበ። ግን ሌባውን ለማጋለጥ የሚያስችል ፍንጭ አልተገኘም ነበርና፡ የንብረቱ ባቤት ቀርቦ-"ሌባዬን እኔ ራሴ በግልጥ አውቀዋለሁ፡ የምፈልገው የናንተን ፈቃድ ብቻ ነው። በፊታችሁ በሰይፍ አንገቱን ቆርጬ ራሱን እንደ ኳስ ለማሽከርከር ይፈቀድልኝ" አለ ።ሕዝቡም "_ካወቅኸውማ ምን ችግር አለ ? ፈቅደንልሃልና ራሱን በመቀላት ገላግለን " የሚል ድምፅ አስተጋባ። ስለዚህ ሰውዮው ሰይፉን መዝዞ እያብለጨለጨ ወደ ሕዝቡ መሐል ለመግባት መንደርደር ሲጀምር ለካስ ሌባው በዚያ ስብሰባ ላይ ነበርና "በሕዝብ መሐል ከመታረድ ላምልጥ" ብሎ ፈትለክ ለማለት ሞከረ። "ያዘው፡ ያዘው ተባለና ተይዞ ሲመረመር ሌባው ራሱ መሆኑን አምኖ የሰረቀውን ንብረት አምጥቶ በሕዝቡ ፊት በቀጥታ ለባለቤቱ አስረከበ ተባለ ።

_በመንፈሳዊዉ ትርጉም ሰይፍ የተባለ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ያም የእግዚአብሔር ቃል ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው። ወየሐሥሥ ኅሊና ወፍትወተ ወምክረ ልብ = ልብ ያሰበውን አእምሮም ያመላለሰውን የሰውን አሳብ ሁሉ መግለጥ የሚችል ነው (ዕብ. 4፡ 12 13)። በሌላ በኩል ደግሞ የሰውን ሕይወት የሚሰርቅ ሌባ፡ ነፍስ ገዳይ ሰይጣን ዲያብሎስ ነው። ምንም ጥፋት ያልፈጸመ መስሎ በሕዝብ መካከል ይሸምቃል። አንድ ጊዜማ በሸማግሌ ተመስሎ ገዳም በመግባት ብጥብጥ መፍጠሩ በታምረ ማርያም ተጽፏል። መናፍስትን የመለየት ጸጋ /ተሰጥዎ ያላቸው ( 1 ቆሮ. 12፡ 10 የመንፈስ ዐርበኞች ከጸሎት ጋር የመንፈስ ሰይፍ በተባለው በእግዚአብሔር ቃል ያጋልጡታል ( ኤፌ. 6፡ 10 -18 )። መናፍስትን የመለየት ሀብተ መንፈስ ቅዱስ ያላቸው እንደነ ቅዱስ ሚልኪ ቍልዝማዊ ያሉት ቅዱሳን አበው የእግዚአብሔር ሰይፍ በተባለው በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ሰይጣን የሚሸምቅበትን ዕፀ መሥውር አስጥለው ገንዳ በማሸከም በሕዝብ ጉባኤ ፊት ነድተውታል"" ይላል መጽሐፈ-ስንክሣር።)

**5** ከብት ለቆ የሰው ሰብል ያስበላ፣ ያስጠፋውን ሰብል፣ አፈላማ ከራሱ እርሻ ይተካ። 6 የእሳት ቃጠሎ አስነሥቶ ንብረት የሚያስጠፋ ሰው፣ የመካስ ግዴታ-ይኖርበታል።(ትርጓሜ ተጓዳኝ ታሪክና ምሳሌ ፡



www.ethiopianorthodox.org

''''''ከአንድ ቤት ሌላ አላቃጠልሁም'''''''' አንድ ሰው "መቶ ቤት ኢቃጥለሃል" ተብሎ ክሥ ቀርቦበት ሲጠየቅ "እኔ ያቀጠልሁት የባሊጋራዬ አንዲት ጎጆ ብቻ ናት" አለ። "ታዲያ ሌላውን ዘጠና ዘጠኝ ቤት በሙሉ ማን ኢቃጠለ ? " ቢሉት "ሌላው ቤትማ በሙሉ እርስበርሱ ቢግበዘው እሳት ተያይዞ ነደደ /ተቃጠለ" በማለት ደመደመ። "ሰደድ እሳት አስነሥቶ ንብረት ያቃጠለ ሰው የመካሥ ግዴታ አለበት" ይላል ( ዘፀ. 22. 6 )። ብዙ ሰው እንደዚሁ ከባድ ኃጢአት ሠርቶ ሲናዘዝ በደሉን አሳንሶና አቅልሎ ማሳየት ይፈልጋል። በእግዚአብሔር ፊት በደልን ለመናዘዝ ግን የውሸት መከላከያ ( defense Mechanism ) አያስፈልግም። " ነጻ የሚያወጣህ እውነት ክርስቶስ ብቻ ነው" ይላል (ዮሐ. 8. 32 )። ብዙ በደል መሥራትህን እግዚአብሔር ያውቃልና አንተ ለማሳነስ ብትሞክር የሠራኸውን በደል ከማክበድ በቀር ማቅለል አትችልም ። ንጉሥ ዳዊት ከሌላው ሰው ሁሉ የበለጠ ኃጢአት አልሠራም። በደሉን ሲናዘዝ ግን" በዝን እምሃርተ ርእስየ =የሠራሁት በደል ቍጥሩ ከራስ ጠጉሬ የበዛ ነው " አለ ። ) ''''''''''''''

ንብረት ጠብቅልኝ ተብሎ በአደራ ተሰጥቶት እምነቱን በማጉደል ቢክድ፣
ከተፈረደበት በኋላ እጥፍ ይክፈል፤ ምስክር ባይኖር ግን፣ በእግዚአብሔር
ስም ይማል። የባልንጀራህን ጋቢ መያዣ አድርገህ ብትወስድበት፣ ፀሐይ
ከመጥለቅዋ በፊት መልስለት።የሞራልና የእምነት መመሪያ ሕግጋት፣
16-17 የልጃገረድን ንጽሕና የደፈረ ሰው፣ ተገቢውን ማጫ ሰጥቶ ያግባት።
አባትዋ ሊድርለት ፈቃደኛ ባይሆን ግን፣ ለአንዲት ድንግል መታጫ ዘዐ
የሚበቃ ገንዘብ ይክፈል። 18 የጥንቈላ መተት የተገኘባት አስማተኛ
በሞት ትቀጣ (ትርጓሜ፡ በመላ ምት ጭምር እንጠነቍላለን የሚሉ ሴቶችም ወንዶችም ቍጥራቸው ብዙ ነው፡ ለዓይነት ያህል አንዱን ብንጠቅስ የምንጃር ሴት የሰጠች የመላ ምት ጥንቈላ ከዚህ የሚከተለው ነው፦''''ዘንድሮ የጤፍ ዘመን ይሆን ወይ?'''''' ይኸውም "ወለቱ ዘንድሮ ጤፍ የሚሆን ይመስልሻልን ? ምን ይታይሻል" የሚል ጥያቄ ቀርብላት የሰጠችው መልስ "ማን ያውቃል? ምናልባት ሊሆንም ላይሆንም ይችላል። ካልሆነ ግን ገልብጦ ሽንብራ መዝራት ነው" የሚል ነበር። እንግዲህ አንዳንዱ የዋህ ገበሬ ይህን አባባል እንኳ እውነት መስሎት አምኖበት ቢገኝ ማፈሪያ ነው።

„ 19 በእንስሳ ላይ የሚያመነዝር ይገደል። 20-24 በስደተኛ ላይ በደል
አትፈጽሙ፤እናንተም በግብፅ ምድር ስደተኞች ነበራችሁና ። ባልዋ
የሞተባትን መበለትና ወላጆች የሞቱባቸውን ድሃ- አደግ - ልጆችን
ብትበድሉና ወደ እኔ ቢጮኹ፣ እኔ እግዚአብሔር በፍጥነት ጩኸታቸውን
ሰምቼ እናንተን በሰይፍ እንድትገደሉ አደርጋለሁ። 25 ለድኻ ብታበድር
ወለድ አትብላ (አትቀበል)። (ትርጓሜው፡ እንግዲህ ችግሩ ያለው አበዳሪው ላይ ብቻ አይደለም። በተለይ በቂ ሀብት እያለው አንዳንድ ተብዳሪም የተበደረውን ባለመክፈል የባሰ በደል ስለሚፈጽም ሁለቱንም ወገን- በዳኝነት-መልክ ማየት ይጠይቃል። ይህኑ በሚመለከት-ነቢዩ ንጉሥ ዳዊትም "ይትሌቃሕ ኃጥእ ወኢይፈዲ= ክፉ ሰው የተበደረውን መልሶ አይከፍልም" ይላል (መዝ -36፡ 21 ) ። ከዚህም ጋር የተጠሰ አንድ ተጓዳኝ ቅኔያዊ ታሪክና ምሳሌ እነሆ !

'''''''' በዱቤ ላይ ዱቤ ''''''''''

_በየዓመት በዓሉ አንዳንድ ጊዜም በወር
የሰባ ፍሪዳ በታረደ ቍጥር
ቅርጫ እየገባ ለሚበላው ሥጋ፡
በወቅቱ የማይከፍል ተገቢውን ዋጋ፡
በሕግ ተከሥሦ ዋሱን ያሳሰረ
ዱቤ እማይሰለቸው አንድ ሰው ነበረ።
ያም ሰው በአስገዳጅ በፖሊስ ተይዞ
ወደ ፖሊስ ጣቢያ ተጀመረ ጉዞ።
ታዲያ በሚያልፍበት በአንድ አውራ መንገድ ዳር፡
አንድ የሰባ ሠንጋ የመጣ ከሐረር፡
ፍሪዳ ተጥሎ ከጨጓራው ጋራ ምላስና ሠንበር
ጉበቱም ለቅምሻ ሲቆረጥ ሲመተር
የማለዳ ፀሐይ ፈንጥዎበት ጮራ፡
ሲቅለጠለጥ አየው ጮማውን ሲያበራ።
በዚያም የሚያውቀን ጓደኛውን አይቶ
ድምፁን ከፍ አድርጎ በጥቅሽአ ተጣርቶ
"አቶ እኼሌ እባክህ እኔንም አትርሳኝ
አደራ ወንሜ ከሰው አትለየኝ።
ነገ እከፍልሃለሁ አንድ ዕጣ ያዝልኝ"
ብሎ ትእዛዝ ሰጠይላንዳች ይሉኝታ





www.ethiopianorthodox.org

በልቶ እንደሚከፍል ለባለ ውልውታ።
ዱቤስ መልካም ነበር ብድር ለሚከፍሉ፡
ዳሩ ግን ታማኞች፡ ሐቀኞች ስንት አሉ?
ከቶ የሕዝብን ሀብት ያለምንም ፈቃድ
የመርፌ ክር እንኳ ያለ ዋጋ አትውሰድ
(የቻይናዎች አባባል)
ለምትገዛው ዕቃ ዋጋ አለመክፈል፡
አያንስም ከቅሚያ ከለየለት ወጀል።
በወለድ ዋስ ጠርቶ ዕዳ በመነከር
በዱቤ ላይ ዱቤ ብድር ማነባበር፡
አንዱን ዋስ አድርጎ ሌላውን ምስክር
መሥሪያ ቤትንና ጐረቤትን ማክሠር
የተወገዘ ነው አስነዋሪ ተግባር ።

*_ይህም በዱቤ ላይ ዱቤ፡ ነቢዩ ሆሴዕ 13፡ 12 13 የኤፍሬም በደል በዝቷል፡ ኃጢአቱም ተከመችቷል" ብሎ ከተናገረው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው።*

28 ዳኞችንና የሕዝብህን አለቃ አትስደብ (አትርገም)፡ 31 አውሬ የገደለውን የእንስሳ ሥጋ አትብላ፡ (የሐዋ ሥ 15፡ 29 ) ።

ጽ፫/23፡ <u>ለሁሉም የወል/የጋርዮሽ ተፈጻሚነት ያለው ፍትሐዊ አሠራር</u>፡

1-2 ሐሰተኛ ወሬ አትቀበል (አታሠራጭ)። ክፉ ሰዎች በጅምላ ሁከት ሰማሥተው በሚጮኹበት ጊዜ ተባባሪ አትሁን።

***(ትርጓሜ:*** *ጌታ በጲላጦስ አደባባይ በቀረበ ጊዜ፣ የነገሩን መነሻና መድረሻ ሳያውቁ፣ ‹‹ስቀለው! ስቀለው!›› እያሉ ይጮኹ በነበረው ዓይነት ወይም በሐዋ 19፡ 21-41 እንደተጻፈው፣ በማታውቀው ነገር ገብተህ ያዘው ፡ ትለፈው በማለት አሽባሪና ሁከት-ፈጣሪ አትሁን ማለት ነው።)*

12 <u>በሳምንት ስድስት ቀን ሥራህን ሥራ፣</u> በሰባተኛው ቀን ግን ዕረፍት አድርግ፣እንስሳትህና አገልጋዮችህም ሁሉ ዕረፍት ያድርጉ።

***ትርጓሜ፡*** *የሰንበት ቀን ዕረፍት ሲባል፡ እጅን አጥፎ፡ እግርን አንጥፎ ተቀምጦ መዋል ሳይሆን በአንድ በኩል ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሄዶ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማ ጊዜ የማግኝት ዕድል አለው ( ኢሳ 66፡ 23 )። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቶያን ተከታይ የሆነ ሕዝባችን*



*ቀዳሚት ሰንበትን የሚያከብሩት እንደ አይሁድ በመጠናቀቅ "ቀበቶን እንኳ ጠበቅ አድርግ መታጠቅ አይግብም" በሚለው የአይሁድ ጸሐፍት ፈሪስውያን ባህልዊ ተፅዕኖ በማድርግ ሳይሆን፡ እንደ ፍትሐ ነግሥቱ ሥርዓት ስለሆን ከቤተ እግዚአብሔር መልስ በሬ ጠምዶ አያርስም እንጂ ቅዳሜ በሀገር ቤት የጦፈ ንግድ የሚካሂያድባት የገበያ ቀን ናት። ሣር ማጨድ፡ የቆመውን እንጨት መቁረጥ፡ የወደቀውን መፍለጥ፡ ዓውድማ መለቅለቅ፡ ሞፈርና ቀንበር፡ ድግር ቆርጦ ለብልቦ ማረቅ፡ ነዶ ማጋዝና መከመር፡ ወዘተ ይከንወንብታል። የሰንበት ጌታዋ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ኢይሱስ በሰንብት ቀን መልክም መሥራት ይገባል በማለት ድዊ ይፈውስባት እንደንበርም በወንግል ተጽፏልና (ማቴ 12፡ 1-8)*

14-15 <u>ሦስቱ ዐበይት በዓላት</u>፤ 14-15 የመጀመሪያው ታላቅ በዓል፣ ከሞተ-በኵር ድናችሁ ከግብፅ የጭቆና አገዛዝ ነጻ የወጣችሁበትን ጊዜ ለማስታወስ፣ ሰባት ቀን ሙሉ፣ ያልቦካ ቂጣ የምትበሉበት የፋሲካ በዓል ( በዓለ መጸለት) ነው።ሁለተኛው፣ መከር መሰብሰብ ሲጀመር፣ ከፋሲካ ሰባት ሳምንት በኋላ የሚከበር የእሸት በዓል ሲሆን፣ እርሱም በዓለ ኀምሳ (ጰንጠቆስጤ) ተብሎ የሚጠራው ነው።ሦስተኛው፣ የመከር ክታች የሚታሰብበት የዳስ በዓል ነው (ዘዳግ 16፥1-17)። እነዚህንም በዓላት ለማክበር ወንዶች ልጆች ሁሉ በዓመት ሦስት ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት እንዲታዩ አድርግ። በፊቴ ለመስገድ ስትመጡም መባ ሳትይዙ ባዶ **እጃችሁን አትቁሙ።**

<u>ለመልአክ የተሰጠ ሥልጣን</u>፤ 20-23 እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤ ‹‹ከአደጋ የሚጠብቅህንና ወደ አዘጋጀሁአት ምድር ያስገባህ ዘንድ፣ መንገድ የሚመራህን መልአክ እነሆ በፊትህ እልካለሁ፤ እርሱ የሚነግርህን ሁሉ ለመፈጸም ለቃሉ ታዘዝ። በእርሱም ላይ እንዳታምፅ ተጠንቀቅ፤ ስሜ በእርሱ አለና። ስለዚህም፣ የምትፈጽመውን በደል አይቶ ምሕረት አያደርግልህም። ለእርሱ ብትታዘዙና እኔም የምነግራችሁን ቃል ብትሰሙ ግን፣ ጠላቶቻችሁን ሁሉ እዋጋላችሁአለሁ››።

***( ትርጓሜ፡*** *በኋለኛው ዘመን እስራኤል ዘነፍስ የተባሉ ክርስቲያን አማኞችን (ምእመናንን) ከግብርናተ ዲያብሎስ ነጻ ያወጣ ቤዛ ዓለም ክርስቲስ ግን ሕዝቡን ራሱ መሪ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የሚያስገባ መሆኑን ሲገልጥ ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ "አኮ በተንባል ወአኮ በመልአክ፡=በመልእክተኛ ወይም በመልአክ አይደለም ። እርሱ ራሱ ስለሚወዳቸው ለዘለዓለም አከበራቸው ይላል። ( ምዕ 63፡ 9 ) ። በዚህ አባባል ግን መላእክት ተልእኳቸውን ያቋርጣሉ ማለት*



www.ethiopianorthodox.org

*አይደለም። ከትንግሌው በኋላ ነፍሳትን ከሲኦል ሲያወጣ የመላእክት አገልግሎት አላስፈለገውም ማለት ነው እንጂ። እኔ ከእናንተ ጋር አብሬያችሁ አልሄድም። መልአኬን ብቻ በፊታችሁ እልካለሁ" ሲል የተናገረ በወቅቱ ላመፁበት ሕዝብ ብቻ ነበር እንጂ ከዚያ ወዲህ በተነሣው ትውልድ ዘመን ሁሉ፡ በሐዲስ ኪዳንም ዘመን የመላእክት አገልግሎት ተቋርጦ አያውም ( የዚህንም ማስረጃ መልአኩን ልኮ ሠለስቱ ደቂቅን ከባቢሎን የደመራ እሳት፡ ዳንኤልን ከአንበሳ ጉድጓድ፡ ወዘተ ማዳኑን እናያለን (ዳን ሞ 3 እና 6 ይመልከቱ። በሐዲስ ኪዳንም ዘመን የእግዚአብሔር መልአክ ወደ ወህኒ ቤት የወረዱትን ሐዋርያት ከእስር ቤት አውጥቶ "ወደ ቤተ መቅደስ ገብታችሁ ይህን የሕይወት ቃል ለሕዝቡ ንገሩ ብሎ ሲያሠማራቸው እናያለን፡ ( የሐዋ ሥ 5፡ 19 -- 20 )። እንዲሁም ሐዋርያ ጴጥሮስን ከፅኑ እስራት የፈታና ያዳነው የእግዚአብሔር መልአክ መሆኑን ራሱ ጴጥሮስ መስክሯል ( የሐዋ ሥ 12፡ 6 -12 )። ነገር ግን የዘመናችን ብዙ ምእመናንም ሆኑ ያልተማሩ አንዳንድ ካህናት እንደ ጴጥሮስ "እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ አዳነኝ። መልአኩ ከእግዚአብሔር በማግለድ ከጎኔ ቆሞ ረዳኝ" በማለት ፈንታ የእግዚአብሔርን ስም ስይጨምሩ የሁሉ ነገር አድራጊ፡ ፈጣሪ ራሱ መልአኩ ብቻ መስሎ እንዳይታያቸው፡ እንደ ጴጥሮስ "እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ አዳነኝ" የማለት ልምድ እንዲኖራቸው ማስተማር ይገባል። )*

25-28 እኔን አምላካችሁን እግዚአብሔርን ብቻ በማምለክ ፀንታችሁ ትኖራላችሁ። እኔም የምትበሉትን እህልና የምትጠጡትን ውሃ እባርካለሁ። ዕድሜአችሁንም አረዝማለሁ፤የበሽታ ዘሮችን ሁሉ ከመካከላችሁ በማራቅ አስወግዳለሁ። መፈራቴን በፊትህ-እኖራለሁ፤ የምትዘምቱባቸውን ሕዝብ አስደነግጣቸዋለሁ። በፊትህ ተናዳፊ ተርብን እሰዳለሁ። 9 ምድሪቱ ባድማ እንዳትሆን፣ የሚኖሩባትን ሕዝብ ሁሉ በአንድ ጊዜ ሳይሆን፣ ጥቂት-በጥቂት ከፊታችሁ ጠራርጌ አባርርላችሁአለሁ። የምድራችሁን ወሰን ከኤርትራ ባሕር እስከ ፍልስጥኤም የባሕር ጠረፍ ድረስ አሰፋለሁ።

**ኛ፬/24፡** <u>በደም የታተመ ቃል ኪዳን፤</u> 4--7 ከዚህ በኋላ፣ ሙሴ የእግዚአብሔርን-ትእዛዝ-ሁሉ-በመጽሐፍ-ጻፈ።የእግዚአብሔር-ትእዛዛት የተጻፉበትንም የቃል ኪዳኑን መጽሐፍ ባነበበላቸው ጊዜ፣ ሕዝቡ፣ ‹‹ለእግዚአብሔር እንታዘዛለን፤ ቃሉንም እንፈጽማለን›› አሉ። ሙሴ ለደኅንነት መሥዋዕት ከቀረበው የእንስሳ ደም በገበቴ ወስዶ በሕዝቡ ላይ ረጨ፤ እንዲህም አለ፤ ‹‹ይህ እንግዲህ እግዚአብሔር እነዚህን ትእዛዛት



በሰጣችሁ ጊዜ፣ ከእናንተ ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያጸናበት ደም ነው››፡

<u>ሙሴ በሲና ተራራ ላይ</u> ፤ 12-18 እግዚአብሔር ሙሴን፣‹‹እኔ ወዳለሁበት ተራራ ወጥተህ በዚያ ቈይ፤እኔ ዐሥሩን ትእዛዛት የጻፍሁባቸውን ሁለት የድንጋይ ጽላቶች እሰጥሃለሁ›› ሲል አዘዘው። ሙሴ የእርሱ ረዳት የሆነውን ኢያሱን አስከትሎ፤ አሮንና ሆርን ሠፈር ጠባቂዎች-አድርጎ ወደ ሲና ተራራ ወጣ፤ በዚያም ዐርባ ቀንና ዐርባ ሌሊት ቈየ።

**ኛ፭ /25፡** <u>እግዚአብሔር የሚመሰገንበት መቅደስ አስፈላጊነት፡</u>

8 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ሲል አዘዘው፤ ‹‹በመካከላቸው እኖር ዘንድ ሕዝቡ መቅደስ እንዲሠሩልኝ ንገራቸው፤ የመቅደሱን ድንኳንና በውስጡ የሚኖሩትን ዕቃዎች (ንዋያተ ቅድሳት) እኔ በማሳይህ ዓይነት እንዲሠሩ ታደርጋለህ።16 እኔ የምሰጥህ ዐሥሩ ትእዛዛት የሚጻፉባቸውን ሁለት ጽላቶች በታቦት ውስጥ ታኖራለህ። 22 እኔም፣ በዚያ የቃል ኪዳን ታቦት የሥርየት መክደኛ ላይ በተሣሉት በሁለቱ ኪሩቤል መካከል ሆኜ፣ ለእስራኤል ሕዝብ የምታስተምራቸውን ሕግና ሥርዓት እሰጥሃለሁ››። 22 በተራራው ላይ ባሳየሁህም ዓይነት ለመሥራት፣ ጥንቃቄ አድርግ።

<u>የመብራት መቅረዝ</u>፤ 32 የመብራትም ማኖሪያ (መቅረዝ) (ተቅዋመ ወርቅ) **ንጹሕ ወርቅ ሥራ**፤ የመቅረዙም መሠረቱና ዘንጉ ከተቀጠቀጠ ወርቅ የተሠራ ይሁን፡ *(**ትርጓሜ፡** ተቅዋም የቡርክት ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ፡ ( ማኅቶት ) መብራት የጌታችን ምሳሌ ሲሆን፣ ወርቅ የመለኮታዊ ባሕርዩን ንጽሕና ያመለክታል። መቅረዙ ከተቀጠቀጠ ወርቅ መሠራቱ፣ ክርስቶስ ለቤዛ ዓለም በቀራንዮ መስቀል ላይ መቀጥቀጡን ያመለክታል። አንድም የወርቅ-መቅረዝ የቤተ - ክርስቲያን ምሳሌ መሆንዋን ወንጌላዊ ዮሐንስ ባየው የጌታችን ራእይ ምእ 1፡ 20 ሲገልጥ፡‹‹ሰባቱ መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው›› በማለት ጽፎአል። እንዲትን ቤተ ክርስቲያን መቅረዝ የሚያሰኛት እግዚአብሔርን ማዕከል የሚያደርግና የሰውን አእምሮ የሚያበራ ትምህርተ ወንጌል የሚነገርባት ሆና ስትገኝ ብቻ ነው።)* ——

**ኛ፮/26፡** ይህ ምዕራፍ በሙሉ ለእግዚአብሔር መቅደስ እንድትሆን፣ ስለምትሠራዋ ድንኳንና ስለ መገልገያ ንዋተ ቅድሳት፥ በለተልይም ስለመጋረጃዎች አሠራር ሁሉ ይነገራል።

**ኛ፯ /27፡** <u>ስለ መብራት የሚደረግ ጥንቃቄ፡</u> 20-21 ለቤተ-እግዚአብሔር መብራት፣ ተወቅጦ የጠለለ የወይራ ዘይት ያመጡ ዘንድ፣ ለእስራኤል



www.ethiopianorthodox.org

ልጆች ነገር፡፡ መብራቱም በየምሽቱ ሲበራ ይደር፣ አሮንና ልጆቹ ያዘጋጁት፣ ከምሽት እስከ ነጋት እንዲበራ ከቃል ኪዳኑ ታቦት ፊት-ለፊት፣ ከመጋረጃው ውጭ ያኑሩት፡፡ **(ትርጓሜ፡** *የዚህ መብራት ሥርዓት ምሳሌነቱ፣ አማናዊ ብርሃን የሆነ የክርስቶስ ቃል እንደ አጥቢያ ኮከብ በምእመናን ሕይወት ለዘለዓለም ሲያበራ መድኖር እንዳለበት ያሳያል። እስከይሠርቅ ለከም ቤዝ ውስተ ልብክሙ= በልባችሁ ውስጥ የአጥቢያ ኮከብ (ክርስቶስ) እስከሚያበራላችሁ ድረስ ቃሉን ተማሩ ለማለት የተሰጠ ምሳሌ ነው (2 ጴጥ 1፡ 19፤)።*

ኛ፰ /28፡ <u>የልብሰ-ተክህኖ አሠራር፣</u> 2 ለውበትና ለክብር ይሆንለት ዘንድ፣ ለወንድምህ ለአሮን የክህነት ልብስ አሠራለት፡፡31-35 በኤፉድ ላይ የሚደረበው ቀሚስ፣ ከታች በኩል ባለው ዘርፍ ዙሪያ፣ ከወርቅ የተሠሩ ትንንሽ ቃጭሎች እንዲኖሩት አድርግ፡፡ ካህኑም ወደ ተቀደሰው ስፍራ በሚገባበት ጊዜ ድምፃቸው ስለሚሰማ፣ ከሞት ይድናል፡፡

**(ትርጓሜ፡** *የእነዚያ የወርቅ ቃጭሎች ትርጉም፣ የሐዲስ ኪዳን ካህን ሁል-ጊዜ የወንጌልን ቃል ከማስተማርና አሰምቶ ከመናገር መዘናጋት እንደሌለበት የሚያሳዩ--ምሳሌዎች- ናቸው። አንበሳ-በደኑ፡-ነብር-በዱሩ፡-መኖሩ-የሚታወቅ የጕርምር-ምታ ድምፅ ማሰማት ሲችል ነው። ካህንም በደብሩ መኖሩ የሚታወቀው በሚያስተምረው የወንጌል ድምፅ ነው ። ድምፁን ካጠፋ ግን ራሱም ጠፍቷል ማለት ነው ። )* ..........................................................

40-41 ለአሮን ልጆች ውበትና ክብር ይሆንላቸው ዘንድ ሸሚዝ፣ መታጠቂያና ቆብም ጭምር እንዲሠራላቸው አድርግ፡፡41 እነርሱንም የወይራ ዘይት በመቀባት የክህነትን ማዕረግ ትሰጣቸዋለህ፡፡ 15-22 የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚጠየቅበትን የደረት ኪስ ለሊቀ ካህናቱ ለአሮን እንዲሰፋለት አድርግ፡፡ ዐራት ረድፍ ያለው የዕንቍ ፈርጥ አድርግበት፡፡ በመጀመሪያውም ረድፍ ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮንና የሚያብረቀርቅ ዕንቍ፡፡ በሁለተኛው ረድፍ ባሉር፤ ሰንፔርና አልማዝ፡፡ በሦስተኛው ረድፍ ደግሞ ያክንት፣ ኬልቄዶንና አሜቴስጢኖስ፡፡ በዐራተኛው ረድፍ ከቢረሌ፣ ከመረግድና ከኢያስጲድ የተሠራ የወርቅ ፈርጥ ይኑርበት፡፡ በእነዚህ ዐሥራ ሁለት የዕንቍ ድንጋዮች ላይ የእያንዳንዱ ነገደ እስራኤል ስም ይቀረጽባቸው፡፡29 ካህኑ አሮን ወደ ተቀደሰው ስፍራ በሚገባበት ጊዜ ሁሉ፣ የእስራኤል ነገዶች ስሞች የተቀረጹበትን ይህን የደረት ኪስ ይለብሳል፡፡ በዚህም ሁኔታ እኔ እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሕዝቤን እስራኤልን አስታውሳለሁ፡፡ 30 ኡሪምና ቱሚም የተባሉትንም ነገሮች በደረት ኪሱ ውስጥ አስገባቸውና አሮን በደረት ኪሱ ይሸከማቸው፤ የእኔን ፈቃድ ለእስራኤል ሕዝብ ማስታወቅ ይችል ዘንድ በደረት ኪሱ ያኑራቸው፡



ኛ፱ /29፡ <u>ስለ ክህነት ሥልጣን የተሰጠ መመሪያ፡</u> 33 የክህነት ሥልጣን በሚቀበሉበት ጊዜ፣ ስለ ኃጢአት ይቅርታ የተሠዋውን ካህናት ይብሉት፤ ከሥጋውም ብሆነ ከኅብስቱ ተርፎ የሚያድር በእሳት ይቃጠል እንጂ የተቀደሰ ስለ ሆነ ውሎ፣ አድሮ አይበላ፡፡

፴ /30፡ <u>የዕጣን አዘገጃጀት፡</u> 34-37 የእያንዳንዳቸው ሚዛን እኩል የሆነ ጣፋጭ ቅመሞችን፣ ይኸውም የሚንጠባጠብ ጣፋጭነት ያለው ሙጫ፤ በዛጎል ውስጥ የሚገኝ ሽቶ፣ ጠፍጣፋ ኾኖ ሽታ ያለው እጣን አዘጋጅ፤ ንጹሕና ቅዱስም ይሆን ዘንድ ጨው ጨምርበት፡፡ በዚህም ዓይነት ዘዴ ለግል ጥቅማችሁ የሚውል ዕጣን ከመሥራት ተጠንቀቁ፡፡

<u>፴፩/31፡ የእግዚአብሔር መንፈስ የእጅ ሥራ ጥበብን የገለጠላቸው ሰዎች፡</u>

1-6 ማንኛውንም የእጅ ጥበብ ሥራ መሥራት እንዲችል፣ ልዩ ማስተዋልና ብልኀት ይኖረው ዘንድ በመንፈሴ እንዲሞላ፣ ከይሁዳ ነገድ የሆር የልጅ-ልጅ የሆነውን ባስልኤልን መርጬዋለሁ፡፡ከእርሱም ጋር፣ ለፈርጥ የሚሆነውን የዕንቍ ድንጋይ ለመቅረጽና፣እንጨትንም በመጥረብ፣ በመፈልፈል ልዩ መልክ መስጠት ይችል ዘንድ፣ ከዳን ወገን የኾነውን ኤልያብን መርጬዋለሁ፡፡

፴፪ /32፡ <u>የወርቅ ጥጃ ምስልን ማምለክ ያስከተለው ቅጣት፤</u>

1-10 ሙሴ ወደ ተራራ ወጥቶ ዐርባ ቀንና ሌሊት ስለ ቈየ፣ የእስራኤል ሕዝብ በዓመፅ አነሣሽነት ተመርተው ወደ አሮን በመቅረብ፣ ‹‹ያ ከግብፅ ምድር መርቶ ያወጣን ሙሴ፣ ከቶ ምን እንደ ሆነ-አናውቅም፡፡ስለዚህ፣ በፊታችን እየሄዱ የሚመሩን አማልክት ሥራልን›› አሉት፡፡ አሮንም፣ ‹‹ሚስቶቻችሁ፣ ሴቶችና ወንዶች ልጆቻችሁ የሚያ ጌጡበትን ወርቅ ኹሉ ሰብስባችሁ አምጡልኝ›› አላቸው፡፡ እነርሱም ያላቸውን ወርቅ ሁሉ፣ የጆሮ ጉትቻ ሳይቀር እያወለቁ ሰብስበው አመጡለት፡፡ አሮን ጉድጓድ አስቈፍሮ አስገባውና በእሳት ቢያቃጥለው፣ የወርቅ ጥጃ ዓይነት ቅርጽ ያለው ምስል ሆኖ ወጣ፡፡ ሕዝቡም በጅምላ እየጮሁ፣ ‹‹ከግብፅ ምድር መርቶ ያወጣህ አምላክ ይህ ነው›› የሚል አዋጅ አስነገሩ፡፡ ለዚያ የወርቅ ምስል መሥዋእት ለማቅረብ ርብርብ ተጀመረ፡፡ ከበሉና ከጠጡም በኋላ፣ ሕዝቡ ኹሉ ሊዘፍኑ ተነሡ፡፡ እግዚአብሔር ሙሴን፣ ‹‹ከግብፅ ምድር መርተህ ያወጣሃቸው ሕዝብኽ ኃጢአት በመሥራት ራሳቸውን አርክሰዋልና እነዚህን እልኸኞች ሕዝብ አጥፍቼ አንተን ከእነርሱ በሚበልጥ ሌላ ታላቅ ሕዝብ ላይ ልሾምህ›› አለው፡፡ 13 ሙሴ ግን፣ ‹‹አገልጋዮችህን



www.ethiopianorthodox.org

አብርሃምን፣ ይስሐቅና ያዕቆብን በማሰብ ወደ ገባህላቸው ቃል ኪዳን ተመልከተህ በደላቸውን ሁሉ ይቅር በል›› ሲል ተማፀነ። 15-19 ከዚያን በኋላ፣ ሙሴ በሁለቱም በኩል ዐሥሩ ትእዛዛት የተጻፉባቸውን ሁለቱን የድንጋይ ጽላቶች ይዞ ከተራራው ወረደ ። ኢያሱ የሕዝቡን ጫጫታ ሰምቶ፣ ‹‹በሠፈሩ የጸብ ግርግታ ድምፅ ይሰማል›› ሲል፣ ሙሴ፣‹‹የወይን ጠጅ ስካር እንጂ፣ የጠብ ድምፅ አይደለም›› አለ። ሙሴም ወደ ሠፈሩ ቀርቦ የወርቅ ጥጃውንና የሕዝቡን ጭፈራ ባየ ጊዜ እጅግ ተቈጣ። ያመጣቸውንም ጽላቶች በወርቅ ጥጃው ላይ ወርውሮ ምስሉንም ጽላቶቹንም ሰባበሮ ጣለ። ያን የወርቅ ጥጃ በማቅለጥ እንደ ዱቄት እስኪልም ድረስ ካስፈጨው በኋላ፣ ከውሃ ጋር በመደባለቅ በጥብጦ፣ሕዝቡ እንዲጠጡት አደረገ።

***(ትርጓሜ** : ያንም የጣዖት ድቃቂ /ፓውደር ብጥብጥ ከጠጡት ሰዎች መሐልየጣዖቱ ፍቅር ያደረባቸው ሁሉ፣ በግንባራቸው ላይ የለምጽ ምልክት ተቀርጸባቸው ስለ ታየ፣ ሙሴ በዚህ ምልክት እየተ መራ፡ ሴረኞቹን ለይቶ ለማወቅ ችሏል።)* ----------------------------

26-28 ከዚያ በኋላ ሙሴ፣‹‹እንግዲህ ከእግዚአብሔር ጋር የሚቆም (የሚሠለፍ ማነው?" ብሎ ሲጠይቅ፣ ሌዋውያን ወደ ሙሴ ቀረቡ። ሙሴም ሌዋውያኑን ከጐኑ አሠልፎ፣ ‹‹ወንድም ወንድሙን አይማር፤ አባትም እንኳ ቢሆን ለልጁ ሳይራራ አጥፊዎቹን ይቅጣ›› ሲል ትእዛዝ ሰጠ ፤ በዚህም ጊዜ፣ ሦስት ሺህ ሰዎች በሰይፍ ተጠረጉ/ተገደሉ። ሙሴም እንድገና ወደ እግዚአብሔርም ተመልሶ፣ ‹‹እባክህ፣ የሕዝብኽን ኃጢአት ይቅር በላቸው፤ የማትምራቸው ከሆነ ግን፣ የእኔን ስም ከመጽሐፍህ ደምስስ›› አለ። 29-35 የወርቅ ምስል እንዲሠራ አሮንን በማስገደዳቸው ምክንያት፣እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ከባድ በሽታ ላከባቸው።

**ፃ፫ /33፡** በመልአክ-መሪነት የእግዚአብሔር ሕዝብ ጉዞ፣1-6፡ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹በፊታችሁ እየሄደ የሚመራችሁን መልአክ እልካለሁ፤እኔ ግን እልኸኞች ናችሁና፣ እናንተን በመንገድ ተቈጥቼ እንዳላጠፋችሁ፣ አብሬአችሁ አልሄድም፡ ላንድ አፍታ እንኳ፣ አብሬአችሁ ብሄድ አጠፋችሁአለሁ››። ሕዝቡ ይህን ቃል ሲሰሙ አዘኑ፤ አለቀሱም። 11 እነሆ፣ በዚህ ዓይነት ሁኔታ፣ ሰው ከባልንጀራው ጋር እንደሚነጋገር፣ እግዚአብሔር ሙሴን ፊት-ለፊት ያነጋግረው ነበር።

**<u>ሙሴ እግዚአብሔርን በአካል ማየት ፈለገ-</u>** 19-22 እግዚአብሔርም ለሙሴእንዲህ ሲል መለሰለት፤ ‹‹እኔ ክብሬን የምገልጥበት ግርማ ሞገስ በፊትህ እንዲያልፍ አደርጋለሁ፣ ቅዱስ ስሜንም በፊትኽ አውጃለሁ፣



ፊቴን በአካል እንድታይ ግን አልፈቅድልህም፣ እኔን በአካል አይቶ በሕይወት መኖር የሚቻለው የለምና፣ ይሁን እንጂ በተሰነጠቀው አለት መካከል እስካልፍ በእጄ እጋርድህና ፊቴን ሳይሆን፣ ጀርባዬን እንድታይ አደርጋለሁ››።*(**<u>ትርጓሜ፡</u>** በጥንቱ የእንግሊዝኛ ምሳሌያዊ ዘይቤ (አነጋገር) ‹‹ጀርባ›› ልጅ ማለት ነው። ይኸውም ልጅ ወልደሃል ወይ?›› ለማለት ‹‹Have you soon your back?›› ማለት የተለመደ አነጋገር እንደ ነበር ይታወሳል። ስለዚህም፣ በኋለኛው ዘመን-የሰውን ሥጋ በመዋሐድ የተገለጠ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስን ቢታቦር ተራራ ላይ ከኤልያስ ጋር ቆሞ ባየው ጊዜ ትንቢቱ ተፈጸሞለታል ማለት ነው (ሉቃ 9፥30-31)። የሚከተለውን የዚህ <u>ተጓዳኝ ትርጉማዊ ታሪክና</u> ምሳሌ ይመልከቱ ፡-* ***"እግዚአብሔርን በአካል የማየት ዕድል <u>ያመለጣቸው ሰዎች ፀፀት</u>"***

*_የአንድ ቤተ ክርስቲያን ምእመናን-"እግዚአብሔርን በዓይናችን ማየት እንፈልጋለን" ብለው የሚያገለግላቸውን ካህን ማስቸገር ጀመሩ። ካህኑም ሱባኤ ገብተው ሲጸልዩ- "በመጭው ሳምንት እሑድ ከቀትር በኋላ ከቤተ ክርስቲያኑ በላይ በሚገኘው ታላቅ ተራራ ራስ ላይ እንዲወጡ ንገራቸው፡ እኔ በዚያ እገለጥላቸዋለሁ" የሚል ድምፅ መጣላቸው ። ካህኑም ይህኑ መልእክት እሑድ ጠዋት ከቅዳሴ በኋላ ለምእመናኑ ጉባኤ ነግረው፡ አንድም ሰው ሳይቀር ያን ተራራ መውጣቱን ተያያዘው። እያንዳንዱ ሰው ባጭር ታጥቆ ሴት፡ ወንዱ፡ ወጣቱም ሳይቀር ተራራውን ሲወጣ ከነጭ ሽበት ጋር አስደሳች መልክ ያለው አንድ መልከ-ቀና ሽማግሌ ከዘራ ይዞ እየተውተረተረ፡ "እባካችሁ እጄን ይዛችሁ ደግፉኝ፡ እኔም ከናንተ ጋር አብሬ ወጥቼ እግዚአብሔርን በዓይኔ ማየት ስለምፈልግ ተባበሩኝ" ብሎ ሲለምን የሚተባበረው አንድም ሰው አልነበረም። "ጊዜ ታሳልፍብናለህ" ብለው ሁሉም ትተውት ወጥተው፡ ተራራው ላይ ተሠልፈው ሲጠብቁ ቆዩ። ነገር ግን እግዚአብሔር ወደነርሱ ሳይመጣ ዘገየባቸው። ጀምበር ከመጥለቅዋ በፊት አንድ ዓይነት ድምፅ ወደ ካህኑ መጣ። ይኸውም "በተራራው ግርጌ የአንድ መልከ መልካም ሽማግሌ ፊት አይታችኋል። እርሱ ከናንተ ጋር ወደዚህ ተራራ መምጣት ፈልጎ እጁን ይዛችሁ በመደገፍ ከናንተ ጋር መምጣት እንዲችል ትብብር ቢጠይቃችሁ እምቢ ብላችሁት መጥታችኋል። እነሆ ያ ሽማግሌ ራሱ እግዚአብሔር ነበር። ነገር ግን እርዳታ ሲጠይቅ ትብብር ሳታደርጉለት*



www.ethiopianorthodox.org

*በመቅረታችሁ ፡ የመጣላችሁን መልካም ዕድል አጥታችሁታልና እንግዲህ ሳይመሽባችሁ በጊዜ ወደየቤታችሁ ሂዱ (ተመለሱ) ' ብለህ ንገራቸው" የሚል ነበር "እውነት እላችኋለሁ ከሁሉ ከሚያንሱት ከነዚህ መካከል ለአንዱ ያላደረጋችሁት ለእኔ እንዳላደረጋችሁት ይቈጠራል፤ (ማቴ. 25.45)።እኛንስ ይህ ዓይነቱ ዕድል ስንት ጊዜ አምልጦን ይሆን ?)*

ፙ፬ /34፡ <u>እንደ ገና የተሠሩ ሌሎች ሁለት ጽላቶች</u>

1-7 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹የፊተኞቹን የሚመስሉ ሁለት የድንጋይ ጽላቶችን ቅረጽና ይዘህ ና፤እኔ በቀድሞዎቹ ጽላቶች ላይ የነበሩትን ትእዛዛት እጽፍባቸዋለሁ። ዘላለማዊ ፍቅሬን እስከ ሺህ ዘፀ ትውልድ እጠብቃለሁ፤ ነገር ግን፣ እስከ ሦስትና እስከ ዐራት ትውልድ ስለ ወላጆች ኃጢአት ከመቅጣት አልወሰንም። 20 መባ ሳይዝ ማንም ሰው ባዶ እጁን በፊቴ አይታይ››። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ቈይቶ በወረደ ጊዜ፣ በፊቱ ላይ ፀዳለ ብርሃን (የብርሃን ነፀብራቅ) ተሥሎበት ታየ፤ ካህኑ አሮንና ሕዝቡ የእርሱን ፊት ማየት ፈሩ፣ ሙሴ ፊቱን በሻሽ መሸፈን ጀመረ (2ቆሮ 3፥13-)። <u>በምዕ 35፡-እና 36</u>፡ የሚታየው አብዛኛው ታሪክ እግዚአብሔር የሚመለክበትን ድንኳን ለመሥራት ሕዝቡ ልዩ፡ልዩ ስጦታ ማበርከት እንዲችል ተጠይቆ፤ ሁሉም ተባብሮ (ርብርብ በማድረግ) በየቀኑ ከማለዳ ጀምሮ ያጐረፈው ስጦታ ከሚጠበቀው በላይ ሆኖ በመገኘቱ፣ የስጦታው ብዛት እንዲገታ በአዋጅ መነገሩን የሚገልጥ ነው ። ፴፯ /37 እና-፴፰/38፡ በዝርዝር የተጻፈው ታሪክ ስለ ቃል ኪዳኑ ታቦት፡ ስለ-ንዋያተ-ቅድሳትና-ስለተቀደሰ-የክህነት-አልባሳት-አሠራር ያሳያል።

፵/40፡ የድንኳኑ መተከልና የአገልግሎት አጀማመር፤ 9-11 ከዚያ በኋላ፣ እግዚአሐር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹ድንኳኑንና ንዋያተ ቅድሳቱን ቀጥሎም መሠዊያውንና የመታጠቢያውን ሰን (ሳህን) ከነማስቀመጫው የተቀደሰውን ዘይት በመቀባት፣ ለእግዚአብሔር የተለየ አድርገው፤ ይህም ሁሉ የተቀደሰ ይሆናል›› ። 17 ከግብጽ በወጡ በሁለተኛው ዓመት እግዚአብሔር የሚመለክባት ድንኳን ተተከለች፡ 22-29 ሙሴም ሁሉን ነገር እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ። ለእግዚአብሔር መባ የሚሆነው የተቀደሰ ኅብስት የሚቀርብበትን ገበታ ከመጋረጃው ውጭ በሰሜን በኩል፣ ከወርቅ የተሠራውንም መሠዊያ ከመጋረጃው ፊት ለፊት፣ የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበትን መሠዊያ ደግሞ፣ ከድንኳኑ መግቢያ ፊት-ለፊት-አኖረ።-34-48-ከዚህ-ሁሉ-በኋላ፣ድንኳኑ-በደመና-ተሸፈነ፤-የእግዚ



አብሔርን- ክብር የሚገልጠው አንጸባራቂ ብርሃን ድንኳኑን ሞላው፡ የእስራኤል ሕዝብ የሠፈሩበትን ቦታ ለቀው በመንቀሳቀስ ጕዞ የሚጀምሩትም ፣ ደመናው ከድንኳኑ ላይ በሚነሣበት ጊዜ ነበር ። በበረሃም በሚጓዙበት ጊዜ ሁሉ፣ በቀን የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጠው ደመና ድንኳኑን ሸፍን፣ሌሊት ደግሞ በድንኳኑ ላይ እሳት እየነደደ ሲያበራ ይታይ ነበር።*(ትርጓሜ፡ እግዚአብሔር በሚመለክበት ድንኳን ላይ የረበበው ደመና የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ምሳሌ ነው። እውነተኛውን አምልኮተ እግዚአብሔር የምትከተል ቤተ-ክርስቲያንም የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የሚያርፍባትና የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጥባት ናት፡ ማለት ነው።*

# ኦሪት ዘሌዋውያን

( መጽሐፈ ሙሴ ሣልሲት )

***መግቢያ፡*** *ሌዋዊ ካህን ማለት ነው ። ሥርወ ቃሉ በግእዝ ቋንቋ ሌወወ ጠመጠመ ከሚል ግሥ የተወረሰ ነው። ሌወወ ማለትም ቀጸላ /አክሊል ወይም ጥምጥም በራስ ላይ ማድረግን ያመለክታል። እግዚአብሔር አምላክ ለመጀመሪያ ጊዜ የራሱ አገልጋዮች አድርጎ የመረጠ ከሕዝቡ ልጆች መካከል በተለይ በኵር ሆነው የተወለዱትን ነበር ( ዝፀ 13፡ 1 )። ዘግየት ብሎ ግን በዘኁልቍ 11 -13 እንደተጻፈ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፡ "የእናቱን ማሕፀን በሚከፍት በኵር ልጅ ሁሉ ፈንታ ከእስራኤል ነገደ ሕዝብ መካከል በተለይ የነግደ ሌዊ ልጆችን መርጫለሁ። እነርሱ ለእኔ የተለዩ አገልጋዮች ይሆናሉ።ይህን የተናገርሁ እኔ እግዚኣአብሔር ነኝ"።*

*_ሌዊና ስምዖን የተባሉት የነገድ አባቶች ቀድሞ የሚታወቁት ሰይፍ በማንሣትና በጦረኛነት ጠባይ ነበር። የእኅታቸው የዲና ክብረ ንጽሕና በመደፈሩ ምክንያት ተቆጭተው የምድረ ሴኬም ባላባት የነበረውን ኤሞርንና ልጁን ሴኬምን ከብዙ ሕዝብ ጋር በግዝረት ቍስል ላይ ሳሉ ሰይፍ፡ ሰይፋቸውን መዘው ገብተው በጭካኔ ጠራርገው ማጥፋታቸው ተጽፏልና ( ዘፍጥ 34፡ 1 -16 + ዝፍት 49፡ 49፡ 5 -7 ) ። ሕዝቡም ዐምፀው የወርቅ ጥጃ ጣዖት አቁመው በመስገድ እግዚአብሔርን ባሳዘኑም ጌዜ የዓድማው አነሣሾች ተለይተው ከታወቁ በኋላ "እነዚህን*



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ በሰይፍ ለመጥረግ ከእግዚአብሔር ጋር የሚሠለፍ /የሚቆም ማን ነው?" ብሎ ሙሴ በጠየቀ ጊዜ፡ 'እኛ አለን ብለው ከሕዝቡ መካከል አፈፍ ብለው ተነሥተው ሦስት ሺህ ዐመፀኞችን በሰይፍ አጭደው ደምስሰዋል ( ዘፀ 32፡ 26 -28 ) ። ዘማየት ብሎ ግን ያ ሁሉ የኃይል አሠራር ተለውጦ፡ ሌዋውያን ለክህነት አገልግሎት ሲመረጡ ደግሞ =የመንፈስ ሰይፍ ተብሎ የሚጠራውን የእግዚአብሔርን ቃል አፅንተው ይዘው በጸሎት ኃይል በመትጋት የሰይጣን ዲያብሎስን ምሽግ ለማፈራረስ የሚያስችል ልዩ መንፈሳዊ ኃይልና ሥልጣን ተሰጥቷቸዋል። "የካህን አፉ፡ የአህያ ዕውሩ ለምንም አይበጅም " እንዲሉ በሕዝቡ መሐል ቆመው በማስተማር ረገድ ፊት አይተው ሳያዳሉ መምህራን ወመገሥፃን ይሆኑ-ዘንድ-ሥልጣናቸው የማይዳሰስ፡ ቃላቸው የማይገሠሥ-ሆኖ ተሾመዋል :: ) """""""""""""""""""""""""""""""""""

በዘሌዋውያን መጽሐፍ-- ከ1-7- ያሉት- ምዕራፎች -በሙሉ--ስለ መሥዋዕትና መባ አቀራረብ የሚያስረዱ ናቸው፡፡‹‹የሚቀርበው፣ የሚቃጠል መሥዋዕት የበግና የፍየል ከሆነ፣ ነውር የሌለበት ተባእት ይሁን›› (1፡10)፡፡ ለእግዚአብሔር የሚቀርበው ቊርባን (መሥዋዕት) ከወፎች ወገን ከሆነ ግን፣ ዋኖስ ወይም ርግብ ሲያመጡለት ካህኑ ራሱን ይቈለምምና በመሠዊያው ላይ እንዲቃጠል ያድርገው (1፡14-15)፡፡ የምታቀርበውን የእህል መሥዋዕት ሁሉ በጨው ታጣፍጠዋለህ፤ ምክንያቱም ጨው ከአምላክህ ጋር ለምታደርገው ቃል ኪዳን መታወቂያ ነው፡፡ **(ትርጓሜ፡** የጨው ባሕርይ ሁሉ፣ ምግብን ከመበላሸት እንደሚጠብቅ፣ ቃል ኪዳንንም ጠብቆ ለመኖር በምሳሌነቱ የተጠቀሰ መሆኑን ዜና መዋዕል ካልእ 13፡ 5 ላይ የዳዊት ዘር መንግሥት ለዘላለም ሳይቋረጥ እንደሚቀጥል እግዚአብሔር የሰጠው ተስፋ፣ ‹‹የጨው ቃል ኪዳን›› ተብሎ ይጠራል። በሐዲስ ኪዳን ትምህርትም ጨው_የፍቅር ምልክት መሆኑ ተነግሮአል (ማር_9፥49-50)። ‹‹ንግግራችሁ ሁል-ጊዜ በጨው እንደ ተቀመመ ይሁን (ይጣፍጥ)››። ተብሎ በቆላ 4፥ 6 እንደ ተጻፈ፣ ጨው የመልካም ንግግር ጥበብ ምሳሌ መሆኑም ተገልጦአል (ቆላ 4፥6)። በትምህርትና በመልካም ሥነ ምግባር የታነፀ የኅብረተ-ሰብ ሥርዓተ ኑሮ፣ ሰላማዊ ጣዕመ ጸጋ የሞላበት እንዲሆን የሚያደርጉ የወንጌል መምህራንም በምድር ጨው ተመስለዋል (ማቴ 5፥13)፡፡ ። በመጽሐፈ ሰዓታትም እንኳ አባ ጊዮርጊስ ዘጋሥጫ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በጨው መስሎ ሲናገር "ጼው ዘአጥዓሞ-ለልሱሕ'-ይለዋል።አልጫውን-ዓለም-ያጠፈጠው-ጨው-ማለትነው ።ጨው የእግዚአብሔርም ቊጣ የሚገለጥበት የጥፋት ምልክት ይሆናል። ለምሳሌ በመዝሙረ ዳዊት 116፡ 34 ወረስያ



ለምድር ጼወ እንተ ትፈሪ በእንተ እከዮሙ ለእለ ይነብርዋ' =በሚኖሩባት ሕዝብ ክፋት ምክንያት ምድሪቱ ጨውን እንድታፈራ አደረጋት" ይላል። አቤሜሌክ የተባለውም እስራኤላዊ የዓመፅ ንጉሥ ያመፁበትን የሴኬም ኑዋሪዎች /ሕዝብ የዘለዓለም ጥፋት የተፈረደባቸው መሆኑን ለመግለጥ ሕዝቡን ከደመሰሰ በኋላ ምድሪቱን ጨው ዘራባት ተብሏል ( መሳ 9፡ 50 -56 ) ። ይህም ሁሉ ድርጊት እግዚአብሔርን ከሚያስቈጣና ከሚያሳዝን ተግባር ሁሉ ተዐቅቦ በማድረግ፡ የመልካም ጨውነትን ባሕርይ ሳይለውጡ፡ በጥሩ ሥነ-ምግባር-ታንፆ፡ ከዓመፅ-ተግባር ሁሉ ርቆ በወንድማማችነትና በእኅትማማችነት ፍቅርና ሰላም ፀንቶ በመቻቻል መኖር እንደሚገባ ምሳሌያዊ ትምህርት ሆኖ ተጽፏል። ·

"""""""""""""""""""""""""""""""""""'''"""""""""""""""""""""""""""""""""""

## ስለ ደኅንነትና ስለሰላም የሚቀርብ የኅብረት መሥዋዕት፤

_ማንኛውም ሰው ከቀንድ ከብት፡ ከበግነ ከፍየል መንጋ መካከል ነውር የሌለበትን መርጦ ሲያቀርብ፡ እግዚአብሔር በሚመለክበት ድንኳን ደጃፍ እጁን በእንስሳው ራስ ላይ ጭኖ ይረደው (ምዕ 3፡1 17)፡፡

_ባለማወቅ ስለ ተፈጸመ በደል የሚቀርብ መሥዋዕት 4፡1--15፡፡

ልዩ ::ልዩ ሕግና ሥርዓት ስለ መተላለፍ የሚቀርብ መሥዋዕት 5፥1-19፡፡

=ስለ ኃጢአት ስርዩት የሚቀርብ መሥዋዕት 6፥24-30፡፡

=ስለ በደል ዕዳና ስለ ደኅንነት የሚቀርብ የኅብረት መሥዋዕት 7፥1-38፡፡

=የአሮንና የልጆቹ የክህነት ሹመት አሰጣጥ ሥርዓት 8፥1-14፡፡

=አሮን ለእግዚአብሔር ያቀረበው መሥዋዕት --9፥1-24፡፡

## ፲ /10፡ ከውጭ እሳት ጭረው ወደ ያመጡ ካህናት በሞት ተቀጡ፤

1--7 ናዳብና አብዩድ ተብለው የሚጠሩት 2ቱ የካህኑ የአሮን ልጆች የየራሳቸውን ጥና ይዘው፣ ከቤተ-እግዚአብሔር ውጭ እሳት ጭረው አመጡ፡፡ በዚያም እሳት ላይ ፡ዕጣን ጨምረው ወደ እግዚአብሔር አቀረቡ፤ እግዚአብሔርም ተቈጥቶ ከሰማይ የተላከ እሳት ስለበላቸው በእግዚአብሔር ፊት ሞቱ፡፡ **(ትርጓሜ** ፡ዛሬም እንደዚሁ፡ ከውጭ አገሮች እየተጫረ የሚመጣ አጉል ልማድ፣ ባህልና ባዕድ ርእዮተ-ዓለም ሁሉ፣ ልክ በዚሁ ዓይነት መዘዙ ብዙ ነው። በአሁኑ ዘመን ብዙ ያልተለመዱ ባህሎች ከባዕዳን አህጉር ተጭረው የመጡ ናቸው፡ ከነዚያ ሁሉ መጥፎ ልምዶች ሕይወትን ጠብቆ በሥነ ሥርዓት ለመኖር



www.ethiopianorthodox.org

መቻል የጥሩ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ያላቅ ጥበብ ነው። """""""""""""""""

<u>የካህናት መመሪያ ሕግ፡</u> 8-9 የወይን ጠጅና ሌላም የሚያሰክር ነገር ጠጥታችሁ እኔ ወደምመለክበት-ድንኳን-(ቤተ-እግዚአብሔር) ከመግባት ተጠንቀቁ፡ይህን-ብታደርጉ-የሚደርስባችሁ-አደጋ-የሞት-ቅጣት ነው።

## ፲፩ /11፡ <u>የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትና አዕዋፍ ዓይነት፡</u>

2--12 የማይበሉት "ከእንስሳ ወገን ዘንፉቅ ሠኮናሁ ወዘያማስክዕ ኪያሁ ብልዑ= ሠኮናው የተሰነጠቀውንና የሚያመሰኳውን እንስሳ ትበላላችሁ። ነገር ግን ግመልን፣ ሽኮኮንና ጥንቸልን የመሳሰሉት የሚያመሰኩ ቢሆኑም፣ ሠኮናቸው ስንጥቅ ባለ መሆኑ ርኩሳን ናቸው።

_አሳማዎችም እንደዚሁ።ከዓሣ ዓይነቶችም ክንፍና ቅርፊት ያላቸውን ሁሉ እንዲበሉ። ነገር ግን በውሃ ውስጥ ከሚገኙት ሁሉ ክንፍና ቅርፊት የሌለው ሁሉ እንዳይበላ ተከልክሏል። 3-20 ከአዕዋፍም ወገን፤ ንሥር፣ ገዴ፣ ዓሣ-አውጭ፣ ጥንብ-አንሣ፣ ጭላትና ጭልፊት፣ በያይይነቱ፣ ቁራ በየወገኑ፣ ጉጉትና ሰገኖ፣ ወይም ሰጐን፣ እርኩምና ጋጋኖ፣ የውኃ ዶሮ፣ ይብራ፣ ጠላቋ በቋል፣ ስደተኛ አሞራ፣ ሽመላ፣ ሳቢሳ፣ ጅንጂላቴ፣ የሌሊት ወፍና እንዲሁም ክንፍ ያላቸው ሆነው በዐራት እግር የሚንቀሳቀሱ ፍጥረታት ሁሉ በእናንተ ዘንድ የረከሱ ናቸው" ተብሎ ተጽፏል።

20-22 ነገር ግን፣ ክንፍ እያላቸው ተስፈንጣሪዎች የኾኑት ሁሉ የሚበሉ ናቸው፡*(**ትርጓሜ** ፡ይህ እንግዲህ የኦሪቱ ትእዛዝ ሲሆን በሐዲስ ኪዳን ግን መባልዕትን በሚመለከት የተሰጠው ትምህርተ ወንጌል ከዚህ ሁሉ የተለየ ነው። ይህንም ብፁዕ አቡነ ጎርጎሬዎስ በጻፉት የኢ. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደገለጡት ይህን ሁሉ ማንንም ሰው በየሚኖርበት አካባቢ ያለው ባህልና አስተዳደግ እንጂ ሃይማኖቱ ይከለክለዋል ማለት አልመሆኑን በመግለጥ በዓፄ ገላውዴዊስ ዘመነ መንግሥት በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ቀርቦ የነበረውን ክሥና የተጠውን መልስ ጠቅሰዋል።*

*_በቤተ ክርስቲያኒቱ ላይ ቀርቦባት የነበረው ክሥና ወቀሳ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በብዙ ነገር ኦሪታዊት እንጂ ወንጌላዊት አይደለችም"' "የሚል ነበር። ይህንም ከሚያስረዱት ነገሮች መካከል 1ኛ "የአመጋገብን ሥርዓት የምታስተምረው፡ በዚሁ በዘሌዋውይን ምዕራፍ 11 የተጻፈውን መሠረት በመድረግ ብቻ ነው የሀዲስ ኪዳኑን ትምህርት ግን ትታዋለች የሚል ነበር ።*



**2ኛ**. *ግዝረትን ትፈጽማለች" የሚል ነበር። ስለዚህም ዓፄ ገለውዴዎስ ጉባኤ ሊቃውንት ጠርተው በማወያየት ተከራክረውበት የሚከተለው መልስ ተሰጥቶበታል ፡- 1ኛ. ግዝረት ማንም ሰው በራሱ ፈቃድ በየቤቱ ለጽዳት ሲባል የሚፈጽመው እንጂ በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን በጸሎት የሚፈጸም አይደለም። ቤተ ክርስቲያናችን -"ያልተገዘረ አይጠመቅ" የሚል_ብይን /ውሳኔ የላትም ። 2ኛ, የሚበሉና የማይበሉ እንስሳትና አዕዋፈ ሰማይን ወዘተ በሚመለከትም ማንንም ሰው የሚከለክለው ያደገበት ባህሉና የራሱ ልምድ እንጂ ሃይማኖቱ አይደለም " ሲሉ በዐራት ነጥብ ዘግተውታል።*

*_መባልዕትን በሚመለከት በሐዲስ ኪዳን የተሰጠውን ትምህርተ ወንጌል ሁሉ ከቅዱሳት መጻሕፍት ባጭሩ፡ ሮሜ ምዕራፍ 14= የሐዋ ሥ ምዕ 10 በሙሉ፡ ጢሞ 4፡ 1 -5 በግልጽ ማየት ይቻላል። በፍትሐ ነገሥት አንቀጽ 23፡ ቍ 804 - 6 የተጻፈውም የቅ/ ዮሐንስ አፈወርቅ ትርጉምና ትምህርት ከዚህ በላይ በሡፈሩት ምዕራፍና ቍጥሮች ከተጻፈው ቀዋሚ መመሪያ ጋር ሙቶ በሙቶ ይተባበራል። )* """"""""""""""

## ፲፪ /12፡ <u>ሴቶች ከወለዱ በኋላ የሚጠብቁት የመንጻት ሥርዓት፡</u>

1--5 ሴት ፀንሳ ስትወልድ በወር አበባዋ እንደሚሆነው ሁሉ፣ እስከ ሰባት ቀን ድረስ ያልነጻች ትሆናለች። ከስምንት ቀን በኋላ፣ ሕፃኑ ይገዘር። ከዚያን በኋላ፣ በተጨማሪ የደምዋ ፈሳሽ እስከሚደርቅ፣ እስከ ሠላሳ ሦስት ቀን ድረስ፣ ማናቸውንም የተቀደሰ ነገር ሁሉ ከመንካት ትቈጠባለች። ሴት ልጅ ብትወልድ ግን፣ እስከ ዐሥራ አራት ቀን ድረስ የመንጻት ጊዜ ያስፈልጋታል። ከዚያን በኋላ ደምዋ እስኪደርቅና የመንጻትዋም ወራት እስኪፈጸም ድረስ፣ ወደ ቤተ-መቅደስ ሳትገባ፤ እንደ ገና ስድሳ ስድስት ቀን ትቈያለች።*(**ትርጓሜ፡** ወንድ ልጅ ሲወለድ ለመንጻት ጊዜ የተወሰነው ሰባትና ሠላሳ ሦስት ቀን ሲደመር አርባ ቀን ይሆናል፤ ሴት ልጅ ስትወለድ ዐሥራ አራትና ስድሳ ስድስት ቀን ሲደመር ሰማኒያ ቀን ስለ ነው። ወንድ ልጅ በተወለደ በአርባ ቀኑ ፣ ሴት ልጅም በተወለደች በሰማኒያ ቀንዋ እንዲጠመቁ በሥርዓተ ቤተ -ክርስቲያን የተወሰነው ከዚህ በመነሣት ነው። = ከ13-14 ያሉት ምእራፎች በሙሉ ከለምጽ በሽታ ስለ መንጻት ሥርዓት የተሰጠውን መመሪያ ሁሉ በዝርዝር የሚያስረዱ ናቸው። ለምጽ የኃጢአት ምሳሌ ሲሆን፣በካህኑ ምርመራ መንጻትና አለመንጻቱ ይረጋገጥ እንደ ነበር፣ በንስሐ ከኃጢአት*



www.ethiopianorthodox.org

*የመንጻት የሐዲስ ኪዳን ሥርዓትም በካህን አማካይነት ይከናወናል (ማቴ 8፥4)። )*

፲፭ /15፡ ከሰውነት የሚወጣ ፈሳሽ ነገር ያለው ሰው ከዚያ በሽታ ነጻ እስኪሆን ድረስ ርኩስ መሆኑን ይገልጣል። ከታወቀው የወር አበባ የተለየ ፈሳሽ የሚኖራትም ሴት ደምዋ እስከሚቆም ድረስ የረከሰች ናት። ለምጽ ያለበት ሰው ሁሉ ካህኑ መርምሮት ነጻ ሆኖ ሲገኝ፣ የመንጻት ሥርዓት የሚፈጸምበትን መሥዋዕት ያቀርባል።

፲፮/16፡ <u>የኃጢአት ስርየት ቀን</u>፤ 4 ካህኑ አሮን ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ከመግባቱ በፊት ሰውነቱን ታጥቦ የክህነት ልብሱን ይልበስ። 11-12 አሮን ስለ ራሱና ስለ ቤተ-ሰቡ ኃጢአት ማስተሥረያ አንድ ኮርማ ወስዶ መሥዋ ዕት አድርጎ ይረደው።

## የሕዝቡን በደል ተሸክሞ ወደ በረሃ <u>ለአዛዜል</u> <u>የሚለቀቅ የፍየል ጠቦት</u>

5-10 የእስራኤል ማኅበር ስለ ኃጢአት ማስተስረያ መሥዋዕት፣ተባእት የሁኑ ሁለት-የፍየል-ጠቦቶችን-ለካህኑ-ለአሮን-ያምጡለት።-ካህኑ-አሮን-አንዱ‹ ለእግ ዚአብሔር››፣ሁለተኛው- ‹‹ለአዛዜል›› -የሚል-ምልክት_ያለባቸውን ጠቦቶች ወስዶ፣ ዕጣ ያውጣና ለእግዚአብሔር የተመረጠውን የፍየል ጠቦት የኃጢአት ማስተሥረያ መሥዋዕት አድርጎ ያቀርበዋል። 20-22 ለአዛዜል ድርሻ ሆኖ የተመረጠውንም የፍየል ጠቦት ወስዶ ሁለት እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ ጭኖ፣ የሕዝቡን ኃጢአት በርሱ ላይ በመናዘዝ፣ በፍየሉ ራስ ላይ ያሸክመውና ለዚሁ አገልግሎት በተመደበው ሰው እጅ ተወስዶ ወደ በረሃ-እንዲለቀቅ ይደረጋል።ይህም ሥርዓት ሕዝቡን ከኃጢአት ለማንጻት በዓመት አንድ ጊዜ የሚፈጸም ነው። ***(ትርጓሜ፡** የሕዝቡን ኃጢአት (ጠስ ) ተሸክሞ ወደ በረሃ የሚለቀቀው የፍየል ጠቦት ስለ ሕዝቡ ኃጢአትና በደል ቤዛ ሆኖ ከከተማ በር ውጭ ሊገደል መስቀሉን ተሸክሞ ወደ ቀራንዮ የወጣ /የተጓዘ የመድኃኔ ዓለም ክርስቶስ ምሳሌ ነው።*

፲7 /17፡ ደም ያለበትን ሥጋ መብላትን የሚከለክል መመሪያ፡

13-16 ማንም ሰው በሥርዓቱ ንጹሕ የሆነ እንስሳ ወይም ቆቅና ጅግራ (ሶረኔ) አድኖም ሆነ አጥምዶ ቢይዝ ደሙን በመሬት ላይ በማፍሰስ አፈር ያልብሰው፣ 3 የእያንዳንዱ ሕያው ፍጥረት ሕይወቱ የሚገኘው በደሙ ውስጥ ስለሆነ፣ ሥጋን ከነደሙ (እርጥቡን) የሚበላውን ማንኛውንም



ሰው ከሕዝቡ መሐል አስወግዱ። ማንም ሰው ቢሆን ሞቶ የተገኘና አውሬም የገደለው የእንስሳ ሥጋ ቢበላ ወይም ቢነካ ልብሱን አጥቦ፣ ሰውነቱን ታጥቦ እስኪነጻ ድረስ እስከ ሥርክ /ምሽት ድረስ፣ ከሠፈር ውጭ ተገልሎ ይቈይ፡

፲፰ /18፡ <u>በሕግ የተከለከለ የግብረ ሥጋ ግንኙነት</u>፤

2-3 የወር አበባ ካለባት ሴት ጋር አትተኛ፤ ራስህንም አታርክስ። ይህ ሁሉ ድርጊት በእግዚአብሔር ዘንድ የተጠላ፣ አስጸያፊም ው። ይህም ከቀድሞ ጀምሮ በግብጽና በከነዓን ምድር የሚኖሩ አረማውያን ሕዝብ ሁሉ ሲፈጽሙት የነበረ ነው።6-18 ከእናንተ ማንም ሰው፣ ከሥጋ ዘመዱ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አያድርግ። በተለይም ከእያትህ፣ ከእኅትህ፣ ከእንጀራ እናትህ፣ ከእንጀራ አባትህ ልጅ ጋር፣ ከእናትህ፣ ከአጎትህ ሚስት፣ ከልጅህ ሚስት (ከምራት)፣ ከወንድም ሚስት፣ እንዲሁም በግብረ ሥጋ ከምታውቃት ሴት፣ ልጅ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከማድረግ ተጠንቀቅ።ሚስትህ በሕይወት እያለች-የገዛ እኅትዋን አግብተህማስቀናት አይገባህም።28-29 ማንም ሰው ወይም ሴት ከእንስሳት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት-አያድርግ።እንደዚህ ያለው አስነዋሪ ተግባር በሥርዓቱ የረከስህ ያደርግሃልና።

፲፱ /19፡ <u>የቅድስና አኗኗር ሕግ</u> ፡ 2 እኔ አምላካችሁ እግዚአብሔር ቅዱስ ነኝና እናንተም እንዲሁ ቅዱሳን ሁኑ (1 ጴጥ 1፥15-16) ። ከእናንተ እያንዳንዱ እናትና አባቱን ያክብር። 9-10 የእርሻችሁን ሰብል ወይም መከር በምትሰበስቡበት ጊዜ፣ በእርሻችሁ ዳርቻ ያለውን እህል አትጨዱ፤ ስታስሩ የፈሳችሁት ነዶ ቢኖር፣ እርሱን ለማንሣት ወደ ኋላ አትመለሱ፣ ቃርሚያውን ሁሉ አጥርታችሁ አትሰብስቡ። በወይንህ ሐረግ የቀረውን ዘለላ ወይም መሬት ላይ የረገፈውን ፍሬ ሁሉ በምድሪቱ ለሚገኙ ድሆችና ስደተኞች ተውላቸው። ይህን ብታደርግ አምላክህ እግዚአብሔር ይባርክሃል። 11-13 ሰውንም ከማታለል ተጠበቅ፤ ውሸት አትናገሩ። በስሜ በሐሰት አትማሉ።ባልንጀራህን-ማታለል-አይገባህም።-ቀጥረህ-ለምታሠራው-ሰው የምትከፍለውን ዋጋ አውለህ ሳታ ሳድር በዕለቱ ስጠው።15 በዓይነ-ስውሩ ፊት እንቅፋት አታኑር። በፍርድ አሰጣጥ ጠንቃቃና ታማኝ ሁን። 16-18 በሕዝብህ መካከል ወጣ ወረድ እያልክ ስም ለማጥፋት ሐሜትና የስም ማጥፋ አሉባልታ አታዛምት ።

***(ትርጓሜ፡** ባለቅኔዎች ሐሜተኛነትንና የስም አጥፊነትን አሉባልታ የሰውን ሥጋ ከመብላት (ከካኒባሊዝም) ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው* **አድርገው ሲያቀርቡት እንዲህ ይሉታል፡ "ቡናስ መልካም ነበር ለሱስ**



www.ethiopianorthodox.org

የሚበድ፡ቍርሱ የሰው ሥጋ መሆኑ ነው እንጂ (መዝ 33፡ 13+ ያዕ 3፡ 2- 10)።
አልሰማችሁም ወይ ወንድሟን በማማት፡
ማርያም እኅተ ሙሴ ለምጽ እንደወጣባት? ( ዘኍልቍ 12፡ 1 -8 ) ።
በጠለፋ ወሬ የሰው ስም በማጥፋት
ቀልሎ ሰውን ማቅለል ኀረቤትን ማማት።
ጓደኛን ማሳዘን ሁሉን ማበሳጨት
ይህ ነው ሌላው ክፍል ግድፈተ ጾም ማለት።
ሰውን ለመበደል ተንኮ ለመሥራት፡
አፍ ይጹም፡ ዓይን ይጹም ይጠበቅ ሥርዓት፡
ጆሮም እንኳ ይጹም ክፉ ከመስማት
መላው ሐዋስ ይጹም ከክፉ ትዕቢት (ከምግብ ጾም ጋር )
አምላክ የመረጠው ይህን ነው ጾም ማለት ( ኢሳ 58 ፡ 1 9 ) ።
መሠረት በሌለው መናኛ አሉባልታ፡
የስንት ባለትዳር ቤት ንብረት ተፈታ ?
ሐሜት ወረርሺን ነው ብርቱ ተላላፊ፡
አሉባልታ እባብ ነው ሥውር ተናዳፊ
በሐሜት ወረርሺኝ እንዳትለከፉ።
ተንኮልን ክፋትን ከውስጣችሁ አጥፉ !
ጾም ማለት ይኸው ነው ይለናል መጽሐፉ።
(ከምግብ ጾም ቀጥሎ ማለት ነው። )

*_አውግስጢን የተባለ ታላቅ አፍሪቃዊ የቤተክርስቲያን ሊቅ ሐሜትን የሚጠላ ሰው ስለነበር፡ "ሐሜተና ሰው ከእኔ ጋር አብሮኝ እንዲበላ አልፈቅድም" የሚል ቃል በጕሉኅ ተጽፎ በምግብ ጠረጴዛው ላይ ይታይ ነበር። ( " ከእንጨት ክፉ ጠማማ፡ ከሰው ክፉ የሚያማ "የሚለውን ተጓዳኝ ታሪክና ምሳሌ በዚህ መጽሐፍ መቸረሻ /Appendix ይመልከቱ )። ‐*

_ሰውን ለክፉ አደጋ የሚዳርግ ምንም ዓይነት ክፉ ነገር አታድርግ፡፡ ቂም- በቀል አትያዝ፡፡ ከማንም ጋር ያለህን አለመግባባት ሁሉ በስምምነት ( በዕርቅ ) ጨርስ፡፡ ባልንጀራህን እንደ ራስህ አድርገህ ውደድ (ሮሜ 13፥8፤ ማቴ 22፡ 36-40)፡፡ 26-28 ***(ትርጓሜ፡*** ይህ ሁሉ ትምህርታዊ መመሪያ በሌላው መጽሐፈ ኦሪት ዘፀ 21፡ 24 በተለየ መልኩ ዓይን ፍዳ ዓይን።



*ዓይን ያጠፋ ዓይኑ ይጥፋ፡ ጥርስ ያወለቀ ጥርሱ ይርገፍ በማለት ፈንታ ጠላትን እንኳ ሳይቀር መውደድ እንደሚገባ የተነገረ ይህ ዓይነቱ ትምህርት ክልደተ ክርስቶስ በፊት የነበረ የክርስትና ትምህርት ዓይነት ነው"ለማለት ይቻላል። )*

_የአስማተኛን ምክር አትከተሉ፡፡ የራስ ጠጕራችሁን ዙሪያውን አትከርክሙ፡ጢማችሁን-አሳጥራችሁ-አትቍረጡ፡፡በሰውነታችሁ-ላይ-ንቅሳት(ውቅራት) እንዲኖር አታድርጉ፡፡ ለሙታን በማዘን ጠጕርን በመንጨት ሰውነታችሁን አታጕሳቍሉ፡፡ 31 ከሙታን ጠሪዎች ምክር አትጠይቁ፡፡ 32-34 ሽማግሎችን ስታይ ከተቀመጥህበት በመነሣት ክብር ስጣቸው፡፡ በምድራችሁ የሚኖሩ ስደተኞችን-አታጉላሉ፡፡ይልቁንም እንደ ራሳችሁ አድርጋችሁ ውደዱአቸው፡፡ እናንተ ራሳችሁ በግብፅ ስደኞች ነበራችሁና፡፡35 በሚዛን /በመለኪያና በመስፈሪያ ከማታለል ተጠንቀቁ፡፡

**፳ /20፡** ቀደም ሲል በምዕራፍ 18ና 19 የተጻፉትንና እስካሁን ያየናቸውን ሕግጋት በተጨማሪ የሚያብራራ ሲሆን፣ ምእራፍ 21ም እንደዚሁ ስለ ካህናት ቅድስና፣ ምዕራፍ 22 ደግሞ ስለ መባ (ስጦታ) ቅድስና እንዲሁም ምእራፍ 23 በዘፀአት ምእራፍ 23፡ ስላየናቸው ስለ- ሃይማኖ-ዐበይት በዓላት አከባበር የሚናገር ነው፡፡ በዚሁ በምዕ 20 የተጻፈው ሌላ አዲስ ቃል-ግን፣- ከዚህ የሚከተለው ነው፡መከር በምትሰበስብበት ጊዜ የመጀመሪያውን ነዶ አምጥተህ-ለካህኑ ስጠው፤ እግዚአብሔር ወዶ፣ ፈቅዶ ይቀበልላችሁ ዘንድ፣ ካህኑ ነዶውን ወደ ላይና ወደ ታች በመወዝወዝ ልዩ መባ አድርጎ ያቀርበዋል፡፡

**፳፬ /24፡**በእግዚአብሔር ስም ላይ የተሰነዘረ ስድብ ያስከተለው ቅጣት፤

10--16 አባቱ ግብፃዊ ኾኖ፣ ሰሎሚ ተብላ ከምትጠራ እብራዊት የተወለደ አንድ ሰው፣ ከአንድ ዕብራዊ ጋር ተጣልቶ፣ ‹‹የእግዚአብሔርን ስም የሚያስነቅፍ የስድብ ቃል መናገሩ ስለ ተመሰከረበት የእስራኤል ማኅበር በድንጋይ ወግረው (ደብድበው) እንዲገድሉት ተፈረደበት፡፡

*<u>(ትርጓሜ፡</u> የዚህን ሰው በደል በግልጥ የተናገረ ገጸ ንባብ አላየንም። ሊቃውንት እንደተረጐሙት ግን" ትውልዱ ባንድ በኩል ግብጻዊ ስለነበር ተጣልቶት የነበረውን ዕብራዊ "አንተ ቀድሞ ባገሬ በግብጽ ባሪያ ነበርህ፡ አሁን ነጻ ወጣህ ብለህ ትኮራለህ" ብሎ በመሳደቡ ምክንያት ፡ በአርአያ ሥላሴ የተፈጠረውን ሰው ባሪያ ብሎ መሳደብ ፈጣሪውን መስደብ ነው ፡ ሸክላውን መንቀፍ ሸክላ ሠሪውን እንደ መንቀፍ የሚያስቈጥር ( Blaspheme ) ነው " ተብሎ ተፈረደበት ።)*



www.ethiopianorthodox.org

## ኗ5 /25፡ የጠቅላላ ምሕረት ዓመተ ኅድገት (ኢዮቤልዩ) ዓዋጅ

8-10 ሰባት ጊዜ ሰባት ዓመት ቍጠር፤ ጠቅላላ ድምሩ አርባ ዘጠኝ ዓመት ሲሆን ኃምሳኛው ዓመት አንድ ኢዮብልዩ ተብሎ ይጠራል ማለት ነው። ሰባተኛው ወር በገባ በዐሥረኛው ቀን፣ በኃጢአት ስርየት ዕለት፣ በምድሪቱ ሁሉ የመለከት ድምፅ (መጥቅዕ) ወይም ነጋሪት እየመታ የሚያውጅ ሰው ትልካላችሁ። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ኀምሳኛውን ዓመት ለይታችሁ፣ በምድሪቱ ለሚኖሩ ሁሉ ነጻነትን ታውጃላችሁ። ከዚያ ዓመት በፊት የተሸጠና የተለወጠ ማናቸውም መሬትና ሌላውም ቤት ንብረት

_ሁሉ፣ ለባለቤቱ ወይም ለወራሽ ቤተ-ሰቡ እንዲመለስለት ታደርጋላችሁ፡ ፡ባሪያ ሆኖ ለማገልገል የተሸጠ ሰውም ሁሉ፣ ነጻ ሆኖ ወደ ቤተ-ሰቡ ይመለሳል። 23 ፡ ምድሪቱ ለዘለቄታ የምትሸጥ መሆን አይኖርባትም፤ ምድሪቱ የእኔ እንጂ የእናንተ አይደለችም፤ እናንተ እንደ ገባሮች (ጢሰኞች) ሆናችሁ እንድትጠቀሙባት ብቻ ፈቅጃለሁ። 24 መሬት በሚሸጥበት ጊዜ፣ የቀድሞ ባለይዞታው አቅሙ የሚፈቅድለት ከሆነ ፣ መልሶ ለመዋጀት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል። 39-40 እስራኤላዊ የሆነ ወንድምህ ራሱን ለባርነት ቢሸጥልህ፣ እንደ ተቀጣሪ ሆኖ ያገልግልህ እንጂ፣ እንደ ባሪያ አድርገህ አትግዛው።-*(<u>**ትርጓሜ**</u> :-ይህ የጠቅላላ ምሕረት ዓዋጅ ጌታችን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በቀራንዮ መስቀል ላይ ለቤዛ ዓለም በተቸነከረ ጊዜ "አባ ስረይ ሎሙ እስመ በዘኢየምሩ ይገብሩ= አባት ሆይ የሚያድርጉትን አያዉምና ማራቸው /ይቅር በላቸው" ሲል ለተናገረው ጠቅላላ የኃጢአት ምሕረትና የይቅርታ ዓዋጅ ታላቅ ምሳሌ ሆኖ የተነገረ ነው። ይህም አጠቃላይ ዓለም አቀፍ የምሕረት ዓዋጅ በዓለም ዙሪያ የሚኖሩ አማኞች ሁሉ ከሚሠሩት በደል ሁሉ በላይ ነው። ይህን የየናምን እኛ ምናችን ሞኝ ነው ?*

*.ማንም ሰው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ የሚሠራው በደል ተደምሮ እንኳ ከእግዚአብሔር የጸጋ ምሕረት ጋር ቢነጻጸር በውቅያኖስ ባሕር ውስጥ እንደ አንዲት ጠብታ ያህል ሆኖ የሚታይ ነው። በክርስትስ አምኖ የተጠመቀ ክርስቲያን ሁሉ በዚህ አጠቃላይ የምሕረት ዓዋጅ ሥር ነው።ያዲያ ለምንድን ነው ብዙ ስዎች ለዘዓለም ራሳቸውን ኃጢአተኛ አድርገው በመኰነን ከቅዱስ ሥጋ ወደሙ አስገልለው፡ ይሙት በቃ ሲፈርዱበት የሚኖሩ? እኔ ኃጢአተኛ ነኝ፡ ለሥጋ ወደሙ አልበቃሁም" ከማለት ይልቅ እኔ ኀጢአተኛ ስለሆንሁ በቅዱስ ሥጋህና በክቡር ደምህ የኃጢአት ስርየትን ሰጥተህ በቸርነትህ ማረኝ፡ ይቅር በለኝ" በሚል ቃል መተካት ይገባዋል። ምክንያቱም ማንም ሰው በራሱ ጥረት ብቻ ከኃጢአት የመንጻት ተስፋ አልተሰጠውም። ያ ቢሆንማ ኖሮ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ እስከ ቀራንዮ መስቀል መንገዘ ባላስፈለገውም ነበር። በዓለም መንግሥታት ማኅበር የታወጀ ጠቅላላ ምሕረት (Amnesty International ) በዓለም ዙርያበሚካሄደው ጦርነት ሁሉ እልፍ አእላፍ ሕዝብ የደመሰሱ የስንት ሚሊዮን ሕዝብ ደም ያፈሰሱ የጦር መኰንኖችና የሠራዊት አባላት ሁሉ እጅ ሰጥተው ከተማረኩ በኋላ ሰብአዊ ርኅራኄ ያልተለየው ጥበቃ እንዲደረረላቸ ውና ጉዳያቸው ትክክለኛ ፍትሕ እንዲሰጥበት ይጠይቃል።*

*_በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ የተሰጠው የጠቅላላ ምሕረት ዓዋጅ ስዎች ከሚፈጽሙት በደል ሁሉ በላይ ነው ። ስዎች በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ የሚፈጽሙት በደል ተደምሮ ከእግዚአብሔር የምሕረት ዓዋጅ ጋር ሲነጻጸር በውቅያኖስ ውስጥ እንደ. አንዲት ጠብታ ያህል ሆኖ የሚታይ ነው። በክርስቶስ ደም ታትሞ የተሰጠን የአምላካችን የጸጋ ምሕረት ዓዋጅ ግን እንደ ውቅያኖስ ባሕር ነው። ታዲያ በዚህ የምሕረት ዓዋጅ የማንጠቀም እኛ ምናችን ሞኝ ነው ?*

*_አንድ ጊዜ ከበረሃ ወጥቶ የመጣ ባሕታዊ በአንድ ቤተ ክርስቲያን ቆሞ በሚያስቀድስበት ጊዜ ካህኑ እጆቹን ዘርግቶ አሐዱ አብ ቅዱስ፡ አሐዱ ወልድ ቅዱስ፡ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ " ሲል ሰምቶ "ይህማ ድፍረት ነው፡ ትዕቢትም ነው። እንዲህ ብሎ ማመስገንና መቀደስ ለመላእክት እንጂ ለሰው አልተሰጠም "በማለት ተቈጣ። ዘግየት ብሎ ደግሞ "በከመ ምሕረትክ አምላክነ ወእኮ በከመ አበሳነ= አምላካችን ሆይ ! እንደ ምሕረትህ ፡ እንደ ቸርነትህም ነው እንጂ እንደ በደላችን አይሁን" ሲሉ በሰማ ጊዜ ደግሞ 'አሁን ገና ቅዳሴዋ ልክ መጣች፡ ለሰው የተሰጠች ቅዳሴ ይህች ናት" አለ።*

*_ቀጥሎም እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ =ክርስቶስ ሆይ ! ማረን። ይቅር በለን " ሲባልለት ጊዜማ በጣም ደስ አለው ። ከሁላችንም የሚፈለገ ታላቅ ቁም ነገር ይኸው ነው ። ማንም ሰው ከእግዚአብሔር ጠቅላላ የምሕረት ዓዋጅ ውጪ በራሱ መፍጨርጨር ብቻ ከኃጢአት እነጻለሁ የሚለው ተምኔት ሁሉ መሠረት የሌለው አጉል ግብዝነት ነው። እንኳስ ሕዝባዊዉ ካህኑም ቢሆን በራሱ ጥረት ብቻ ከበደል የመንጻት ሥልጣን አልተሰጠውና። )*

## ኗ፮ /26፡ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ የሚገኝ በረከት፤

3-10 በሕጌና በሥርዓቴ ብትመሩና ትእዛዛቴን ብትጠብቁ፤ ምድራችሁ በእህል ሰብል፣ዛፎቻችሁም-ሁሉ-በፍሬ-የተሞሉ- እንዲሆኑ- ዝናምን--





www.ethiopianorthodox.org

በወቅቱ እሰጣችኋ-ለሁ። ሰብላችሁም ከመብዛቱ የተነሣ፣ የእህል መከር ሰብስባችሁ ሳትጨርሱ፣ የወይን ዘለላ የምትቈርጡበት ጊዜ ይደርሳል። ተወይኑም ዘለላ ተሰብስቦ ሳያልቅ-እህል የምትዘሩበት ጊዜ ይደር-ሳል_። ክፉዎችን አራዊት ከምድራችሁ አስወግዳለሁ።ሰይፍ-በምድራችሁ-አያልፍም፡-የሚያስፈራችሁና የሚያስደነጣችሁ ሳይኖር ያለምንም ሥጋት ትኖራላችሁ።ለምግብ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ እያገኛችሁ፣ በምድራችሁ ለዘላለም በሰላም-ትኖራላችሁ፡-(አሞፅ9፡13)። እባርካችኋ ለሁ፤ ብዙ ልጆችን እሰጣችኋለሁ።፡ከዓመት እስከ ዓመት የሚቈይ ሰብል ሰብስባችሁ ለማኖር ባለፈው የመከር ስብሰባ የተትረፈረፈውን አውጥታችሁ ለመጣል ትገደዳላችሁ ።

## ለእግዚአብሔር ቃል አለመታዘዝ የሚያስከትለው መዘዝ፤

18-33 ቃሌን መስማት እምቢ ብትሉ፣ ኃጢአታችሁ በሚያስከትልባችሁ ቅጣት ላይ ሰባት እጥፍ እጨምራለሁ። ከራሳችሁ በላይ ያለውን ሰማይ እንደ ብረት፣ ምድራችሁንም እንደ ነሐስ የጠጠረች አደርጋለሁ። ተግታችሁ የምትደክሙበት ሥራ ሁሉ ከንቱ ልፋት ብቻ ይሆንባችኋል። ምድራችሁ ሰብልን አታስገኝም፣ ዛፎቻችሁም አያፈሩም፤ ስለዚህ ከረሃብ ፅናት የተነሣ፣ የገዛ ልጆቻችሁን ሥጋ ለመብላት ትገደዳላችሁ (ነገ ካልእ-6፡ 26--29)። ዐሥር ሴቶች በአንድ ምጣድ ላይ የሚጋግሩበት ጊዜ ይመጣል፤ምግባችሁን በሚዛን ለክተው ያቀርቡላችኋል፤ በልታችሁም አትጠግቡም። በየኰረብታዎች ላይ የምትሠሯቸውን መስገጃዎች እደመስሳለሁ፤የዕጣን መሠዊያዎችንም ሁሉ አፈርሳለሁ። እሬሳችሁንም በወደቁ-ምስሎቻችሁ -ላይ እጥላለሁ፣ በፍጹም- እጸየፋችሁአለሁ። ከተሞቻችሁን ሁሉ ወደ ፍርስራሽነት እለውጣለሁ። በእናንተ-ላይ-ጦርነትን አምጥቼ በአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ።ምድራችሁም ሰው አልባ ሆና ትቀራለች።

36--39 ከእናንተ ተለይተው በሚቀሩት ላይ በልባቸው ድንጋጤን አሳድርባቸዋለሁ፤ በነፋስም የምትንቀሳቀስ የቅጠል ኮሽታ ታስደነግጣቸዋለች ።40-44 ነገር ግን፣ ሕዝቤ በደላቸውን ቢናዘዙና በትሕትና ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ቢገኙ፣ ለያዕቆብ-የገባሁትን-ቃል ኪዳን እንደገና አስባለሁ።እስከ መጨረሻ ይጠፋ ዘንድ አልተዋቸውም።

## ፳፯/27፡ ለእግዚአብሔር ስለሚቀርቡ ስጦታዎች የሚያስረዳ ሕግ፤

26-27 በኵር ሆኖ-የሚወለድ እንስሳ ሁሉ፣-ቀድሞውኑ የእግዚአብሔር ስለ ሆነ፣ ማንም ሰው የበጎ ፈቃድ ስጦታ አድርጎ ሊያቀርበው አይችልም፤



እንቦሳም ሆነ የበግና የፍየል ግልገሎች አስቀድመው ለእግዚአብሔር የተለዩ ናቸውና። 30--32፡ ምድሪቱ የምታስገኘው እህልም ሆነ ፍራፍሬ ከዐሥር አንዱ እጅ ለእግዚአብሔር የተለየ ነው። ማናቸውንም ነገር መልሶ መዋጀት ወይም መግዛት የሚፈልግ ሰው ቢኖር፣ በደፉ በታወቀው ዋጋ ላይ በመቶ ኻያ እጅ ጨምሮ ይውሰድ። ከቤት እንስሳም ቢሆን ከዐሥር አንዱ እጅ የእግዚአብሔር ድርሻ ነው።

# ኦሪት ዘኍልቍ

(መጽሐደ ሙሴ ሣልሲት)

**መግቢያ**፡ በመሠረቱ-ኍልቍ-ቍጥር-ማለት-ነው።ሥርወ ቃሉም ኖለቈ= ቈጠረ ከሚለው የግእዝ ግሥ የተገኘ ነው። *ይህ ስያሜ ለዚህ መጽሐፍ የተሰጠበትም ምክንያት የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤል በበደላቸው ምክንያት የሚጓዙበት መንገድ ተዘግቶባቸው ጫን፡ ተብትብ በማለት የቆዩበት ዐርባ ዓመት ተፈጽሞ በሲና ጥግ በሚገኘው የከነአንን ደቡባዊ ወሰን በነበረው ቢቃዴስ በየኖሩበትን ሠፈር ለቀው የተስፋይቱ ምድር ምሥራቅ ወደሆነው ወደ ዮርዳኖስ ማዶ ሲደርሱ በሞአብ ሜዳ ሙሴ ያደረገውን የሕዝብ ቈጠራ የሚገልጥ በመሆኑ ነበር።መጽሐፉ ግን ከሕዝቡ ቍጥር በላይ ብዙ ትምህርት ሰጭ የሆነ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ሁሉ የተገለጠበት ትምህርታዊ ታሪክ የሞላበት ነው። የሕዝቡ በጕርምርምታ ብዛት የሕዝቡ በደል እግዚአብሔትን የተፈታተኑበትና መሪ ሆኖ የተመረጠላቸውን ሙሴን ማሳዘን የዘወትር ተግባራቸው ቢሆኖም በዚያው መጠን የእግዚአብሔር መሐሪነትና ይቅር ባይነት ታክሎበት በጠላቶቻቸው ላይ የተገናፀፉት ድል ታሪክ ሁሉ ምን ጊዜም የማይረሳ ነው።*

*ዘኍልቍ ተብሎ የተሰየመበት ምክንያት በበረሃ የኖሩበትን ሠፈር ለቀው የተስፋይቱ ምድር ምሥራቅ ወደሆነው ወደ ዮርዳኖስ ማዶ ሲደርሱ በሞአብ ሜዳ ሙሴ ያደረገውን የሕዝብ ቈጠራ የሚገልጥ በመሆኑ ነበር። መጽሐፉ ግን ከሕዝቡ ቍጥር በላይ ብዙ ትምህርት ሰጭ የሆነ የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ሁሉ የተገለጠበት ትምህርታዊ ታሪክ የሞላበት ነው። የሕዝቡ በጕርምርምታ ብዛት*



www.ethiopianorthodox.org

የሕዝቡ በደል እግዚአብሔትን የተፈታተኑበትና መሪ ሆኖ የተመረጠላቸውን ሙሴን ማሳዘን የዘወትር ተግባራቸው ቢሆንም በዚያው መጠን የእግዚአብሔር መሐሪነትና ይቅር ባይነት ታከሎበት በጠላቶቻቸው ላይ የተገናፀፉት ድል ታሪክ ሁሉ ምን ጊዜም የማይረሳ ነው።

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

<u>ከ1- 4</u> ባሉት ምዕራፎች የተጻፈው ታሪክ የመጀመሪያውን የእስራኤል ሕዝብ- ቈጠራ፤ ውጤት- የሚገልጥ -ነው። ይህም-የሕዝብ-ቈጠራ ዕድሜያቸው ከኻያ ዓመት በላይ ሆኖ፣ በወታደርነት ለማገልገል የሚችሉ የእስራኤል ኃያላን ድምር ስድስት መቶ ሦስት ሺህ አምስት መቶ ኀምሳ ( 603,550 ) መሆኑን ያስረዳል። ይኸውም ሴቶችንና ከኻያ ዓመት በታች ዕድሜ ያላቸውን ልጆች ሳይጨምር ማለት ነው።_

፫ /3 ፡3-39 <u>የሌዋውያን ቍጥር፡</u> **ዕድሜያቸው አንድ ወርና ከዚያም በላይ ሆኖ የተመዘገቡ /የተቈጠሩ** ሌዋውያን ድምር ኻያ ሁለት ሺህ ነበር።11-13 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹የእናቱን ማኅፀን በሚከፍት በኵር ልጅ ሁሉ ፈንታ፣ ከእስራኤል ሕዝብ መካከል የነገደ ሌዊን ልጆች መርጫለሁ፤ እነርሱ ለእኔ የተለዩ አገልጋዮች ይሆናሉ፣ ይህን የተናገርሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ››።

<u>፬ /4</u> ፡ 41-43 ዕድሜያቸው ከሠላሳ እስከ ሃምሳ ዓመት ሆኖ፣ በክህነት ማገልገል የሚችሉ ሌዋውያን ድምር ስምንት ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ (8,580) መሆኑን ይሚገልጥ ነበር።

፭ /5፡ <u>ባሎቻቸውን የሚያስቀኑ ሴቶች ተለይተው የሚታወቁበት ምልክት ፡</u> ከሌላ ወንድ ጋር በማመንዘር ባልዋን ያስቀናች ሴት ከተገኘች፣ ካህኑ እርግማን የሚፈጸምበትን ማየ ዘለፋ-(መራራ-የእርግማን ውሃ) ከማጠጣቱ በፊት፣እንዲህ ሲል ያስምላት፤‹‹ይህን የተጠረጠርሽበትን ነገር ፈጽመሽ ባልሺን አስቀንተሺው ከሆነ፣ እግዚአብሔር የስምሽን መታሰቢያ ከሕዝብሽ መካከል ለይቶ ያጥፋው። ይህ ማየ ዘለፋ ገብቶ-ሰውነትሽን-ያሳብጠው፤ ማኅፀንሽንም- ያኮማትረው፤ የተጠረጠርሽበትን የዝሙት ተግባር ያልፈጸምሽ ከሆንሽ ግን እግዚአብሔር ከማናቸውም ጉዳት ሁሉ ይጠብቅሽ፤ በወንድ ልጅ ተበከሪ (የመጀመሪያ ወንድ ልጅ ይስጥሽ)››። እርሱዋም ፈጽማው ከሆነ እርግማኑ ፡ያልፈጸመችው ከሆነ በረከቱ እንዲደርሳት፣'አሜን"ትላለች ።

፮ /6፡ የናዝራውያን መመሪያ ሕግ ፤ 1-9 ናዝራዊ (ናዝራዊት) ለመሆንና ራስን ለእግዚአብሔር የተለየ አድርገው ማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መመሪያ /ትእዛዝ "ከሚያሰክር መጠጥ ተቈጥበው ይቈዩ፤ ጠጕራቸውን አይላጩ፤ የሞተ ሰው ወይም የእንስሳ በድን አይንኩ›› የሚል ነው።

<u>የካህናት-ቃለ በረከት፡</u> 24-27 ሕዝቡን ስትባርኩ እንዲህ በሉ፤ ‹‹እግዚአብሔር ይጠብቅህ፤ የፊቱንም ብርሃን በአንተ ላይ ያብራ፤ ይራራልህ፣ ሰላምንም ይስጥህ››። እግዚአብሔርም እንዲህ አለ፣ ‹‹በዚህ ዓይነት ሁኔታ ስሜን ጠርተው ሕዝቡን ሲባርኩ፣ እኔም እነርሱን እባርካቸዋለሁ››፡

ምዕራፍ ፮ /6፡ ራስን ለእግዚአብሔር የተለየ አድርገው ማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ፣ ከእግዚአብሔር የተሰጠ መመሪያ /ትእዛዝ "ከሚያሰክር መጠጥ ተቈጥበው ይቈዩ፤ ጠጕራቸውን አይላጩ፤ የሞተ ሰው ወይም የእንስሳ በድን አይንኩ›› የሚል ነው። ምዕራፍ ፯ /7፡በሙሉ የ0ሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል አለቆች መሠዊያው ለሚቀደስበት ክብረ በዓል ያቀረቡትን መባ የሚያስረዳ ነው። <u>ምዕራፍ 8</u> ፡1-4 ሰባቱን መብራቶች በመቅረዝ ላይ ስለ ማኖር ሥርዓት ይናገራል። ከቍ 5-26 ሌዋውያን ካህናት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ተለይተው የመንጻት ሥርዓት እንዲፈጸምላቸው ከእግዚአብሔር የተሰጠውን ትእዛዝ ያስረዳል። <u>ምዕራፍ 9</u> ፡እስራኤል ከግብፅ ከወጡ በኋላ፣ ለሁለተኛ ጊዜ የፋሲካን በዓል እንዴት እንዳከበሩ ይገልጣል። በ<u>ምዕራፍ 10</u>፡ ከብር የተሠሩት ሁለት መለከቶች ለሕዝቡ ስብሰባ መጥሪያና ለጕዞ አሠላለፍ ሥርዓት፣ ለጦርነትና ለበዓላት አዋጅ መንገሪያ የሚሰጡትን አገልግሎት በመግለጥ ከእግዚአብሔር የተሰጠው መመሪያ ተጽፎአል።

## <u>በቅደም ተከተል የሕዝቡ ጕዞ አሠላለፍ ሥርዓት በ4 ረድፍ</u>

11--36 በይሁዳ ነገድ የሠፈር አርማ ሥር የይሳኮርና የዛብሎን ሠራዊት በየነገድ አለቆቻቸው መሪነት ግንባር ቀደም ሆነው ሲጓዙ፣ የመቅደሱን ድንኳን የተሸከሙ የጌርሾንና የሜራሪ ጕሣዎች ተከተሉ። በሮቤል ነገድ የሠፈር ዓርማ ሥር የስምዖንና የጋድ ሠራዊት ተራቸውን ጠብቀው ሲጓዙ ፤ ከነገደ ሌዊ የቀሐት ጕሣ የሆኑት ሰዎች ንዋየ ቅድሳትን ተሸክመው ጕዞ ቀጠሉ። በኤፍሬም የነገድ አርማ ሥር የምናሴና የብንያም ሠራዊት በነገድ አለቆቻቸው መሪነት ተሰልፈው ሲጓዙ የኋላ ደጀን በሆነው በዳን ነገድ የሠፈር ዓርማ ሥር የተሠለፉት የአሴርና የንፍታሌም



www.ethiopianorthodox.org

ሠራዊት ተከተሉ።ሙሴወደትውልድ አገሩ ሊሄድ-ዝግጁ የነበረውን የአማቱን የዮቶር ( የራጉኤል) ወንድም የሆነ- ሆባብን «እባክህ፣ አንተ ከእኛ ጋር አብረኸን ተጓዝ፤ እግዚአብሔር ለእኛ ከሚያወርሰን በረከት ሁሉ ተካፋይ ትሆናለህ ፡የምድረ በዳውን መንገድ ስለምታውቅ ዓይን ሆነህ ትመራናለህ» ሲል ለመነው

፲፩ /11፡ <u>የሕዝቡ ጩኸትና ጉርምርምታ በረታ</u>፡

4-6 ሕዝቡ-በእግዚአብሔር-ላይ አምፀው-በማጉረምረም እንዲህ አሉ፤ «እንግዲህ የምንበላውን ሥጋ ከየት-አግኝተን እናምጣ በግብፅ ምድር በነበርን ጊዜ፣ ዋጋ ሳንከፍልበት እንበላው የነበረ ዓሣ፤ ዱባውና በጢህ ተብሎ የሚጠራው ውሃ የሞላበት የዱባ ዓይነት ፍሬ፣ ቀይና ነጭ ሽንኩርቱ፣ ድንቹም ትዝ አለን። አሁን ግን፣ ይህን መና ብቻ በመብላት፣ ሰውነታችን ደርቆ ኀይላችን ደከመ። 10-15 ሙሴም ይህን ሁሉ ሲሰማ በብርቱ አዝኖ፣ «እነዚህን ሁሉ ሕዝብ በብብትህ እቀፋቸ የምትለኝ፣ እኔ ፀንሼ ወልጃቸዋለሁን?» ሲል ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመረ ።

15-27 እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል አዘዘው፤ «ይህን በአመራር ሥራ የሚያግዙና ሸክም እንዲቀልልህ የሚያደርጉትን ሰዎች፣ ከያንዳንዱ ነገድ ስድስት-ስድስት ሰው በመምረጥ፣ ሰባ ሊቃናት (አለቆችን) ይዘህ ወደ መገናኛው ድንኳን ና፤ እኔም በአንተ ላይ አድሮ ከሚኖረው መንፈስ ወስጄ፣ በእነርሱ ላይ አሳድርባቸዋለሁ»። ሙሴም ከዐሥራ ሁለቱ ነገድ መካከል ስድስት፡ ስድስት ሰው ሲመርጥ ድምሩ 72 ስለሆነበት ይዘህ ና ያለኝ ሰባ ሰዎችን ብቻ ስለሆነ እግዚአብሔር ያዝንብኛል" ብሎ በመፍራት ተመርጠው በትርፍነት የተመዘገቡትን ሁለት ሰዎች በመቀነስ በሠፈር ትተቻቸው ሰባውን ሊቃናት ብቻ ይዞ ሄደ። እግዚአብሔርም በደመና ወረደ፤ ለሙሴ ከሰጠው መንፈስ ወስዶም በሰባው ሊቃናት ላይ ባሳደረባቸው ጊዜ፣ ትንቢት መናገር ሲጀምሩ፣ በሠፈር ቀርተው የነበሩትም ሁለቱ ኤልዳድና ሙልዳድም እንደ እነርሱ ትንቢት ተናገሩ። በዚህ ጊዜ፣ ረዳቱ የሆነው የነዌ ልጅ ኢያሱ ወደ ሙሴ ቀርቦ፣ እነዚያ ሁለት ሰዎች ትንቢት እንዳይናገሩ ይገሥጻቸው ዘንድ ነገረው። ሙሴ ግን፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ በሕዝቡ ላይ አድሮ፣ ሁሉም ትንቢት መናገር ቢችሉ እንዴት ደስ ባለኝ ነበር?!» አለው።

<u>ሕዝቡ የተመኙት ሥጋ ተትረፍርፎ ቀረበ</u> ፡ 23 እግዚአብሔር ድርጭቶችን እየነዳ የሚያመጣ ነፋስ ላከ ፣ ድርጭቶች በጅምላ መጥተው በአፈሩ ውስጥና በዙሪያው ሁሉ የተከማቹበት ስፍራ የአንድ ቀን ውሎ



መንገድ ያህል ነበር፤ ነገር ግን እግዚአብሔር በሕዝቡ ማጉረምረም ተቈጥቶ ስለ ነበር፣ የሚበሉት ሥጋ ገና ከጉሮሮአቸው ሳይወርድ፣ ብርቱ መቅሠፍት አምጥቶባቸው ብዙዎቹ ሞቱ። ያም ቦታ የምኞት መቃብር ተብሎ ተጠራ።

፲፪ /12፡ <u>የሐሜት ቃል የተናገረች ከንፈር በለምጽ ነደደች</u> ፡

1-16 ሙሴ ከኵሽ ነገድ የሆነች ኢትዮጵያዊት ሴት በማግባቱ ምክንያት፣ የገዛ እኅቱ ማርያምና ወንድሙ አሮን በሐሜት እንዲህ ሲሉ ነቀፉት፤ «እግዚአብሔር የተናገረ በሙሴ አማካይነት ብቻ ነውን? በእኛስ አማካይነት ተናግሮ የለምን?!» ሙሴ ግን በምድር ከሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ይልቅ፣ የዋህና ትሑት ሰው ነበር። እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ተቈጥቶ፤ «በአገልጋዬ በሙሴ ላይ የሐሜት ቃል ለመናገር እንዴት ደፈራችሁ?!» አላቸው። ከዚያን በኋላ ፣ ማርያም በለምጽ በሽታ ተመታች። እርሱዋም ቀሳ ወጥታ ቈይታ በሙሴ አማላጅነት ከለምጽ በሽታዋ እስክትነጻ ድረስ የሕዝቡ ጕዞ ተቋርጦ አንድ ሳምንት ቈየ።

*(<u>**ትርጓሜ**</u> ፡ የዘረኛነት ሐሜትና ከንቱ አሉባልታ ጥንትም ሆነ ዛሬ እንደዚሁ የሕዝብን ሥልጣኔ፣ የቤተ ክርስቲያንንና የሀገርን የዕድገት ርምጃ ሁሉ ወደ ኋላ የሚጐትት የማኅበረ-ሰብ ተውሳክ /ደዌ ነው።*

፲፫ /13፡ ሕዝብን <u>ተስፋ የሚያስቈርጥ ሪፖርት</u> ፡

1--33 ሙሴ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት፣ ከዐሥራ ሁለቱ ነገደ እስራኤል ዐሥራ ሁለት ተወካዮችን መርጦ ወደ ከነዓን ምድር፣ ዘልቀው-ገብተው-የአገሪቱን-ሁኔታ- አጥንተው- (ሰልለው) እንዲመጡ ከፋራን ምድረ-በዳ ላካቸው። የተላኩት ተወካዮች ለዐርባ ቀናት ያህል እየተዘዋወሩ ሲያጠኑ ቈይተው፣ ለዓይነት የሚታይ የስንዴ ዛላ፣ የወይን ዘለላ ተሸክመው መጡ። ከዐሥራ ሁለቱ ተካዮች መካከል በተለይ ዐሥሩ የምድሪቱን ለምነት፣ ይኸውም በርግጥም ማርና ወተት የሚፈስስባት መሆንዋን ከገለጡ በኋላ፣ «ከተሞቻቸው በጠንካራ ሁኔታ የተመሸጉ ስለ ሆኑ፣ ወደዚያች አገር ለመግባት የማይቻል ነው» ሲሉ ተናገሩ። በመቀጠልም፣ «በተለይ የዔናቅ ዝርያዎች የሚባሉትን ረጃጅሞች ምድር-ወለድ ኀያላን አየናቸው። እኛ ከእነርሱ ጋር በቁመት ስንታይ፣ በፊታቸው እንደ ኩብኩባ ( የትንኝኛ የዘሆን ያህል ) ሆነን ተገኘን። አማሌቃውያን በምድሪቱ ደቡባዊ ክፍል ፣ ሒታውያን ፣ ኢያቡሳውያንና አሞራውያን ደግሞ በዮርዳኖስ ወንዝ ዳርና በሜዲትራኒያን ባሕር ጠረፍ ይኖራሉ»



www.ethiopianorthodox.org

በማለት አጋንነው-አሸባሪ ቃል ተናገሩ። በዚያን ጊዜ፣ የሕዝቡ ወኔ (ሞራሉ) ተሰበረ። በፍጹም ተስፋ ቈርጠው እየጮኹ ማልቀስና ማጕረምረም ጀመሩ። ነገር ግን፣ የነገደ ይሁዳ ተወካይ ሆኖ ከእነርሱ ጋር የተላከው ካሌብ፣ የሚያጕረመርሙትን ሕዝብ ሁሉ በማረጋጋት ጸጥ አድርጎ፣ ‹‹በምድሪቱ ላይ አደጋ መጣል ከፈለግን፣ አሁኑኑ ለመዝመትና ለመውረር የሚያስችል በቂ ኀይል አለን›› አለ።

**፲፬/14፡ የሕዝቡ ጕርምርምታ በረታ**፤1-10 ሕዝቡ በሙሉ የዐሥሩን መላክተኞች ንግግር ከሰሙ በኋላ፣ ሌሊቱን ሁሉ በመጨነቅ ሲጮሁ አደሩ፤‹‹ሴቶቻችንና ልጆቻችን ምርኮኞች ከሚሆኑ፣ አለቃ ሹመን ወደ ግብፅ እንመለስ›› ተባባሉም። የነዌ ልጅ ኢያሱና የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ግን፣ ‹‹እግዚአብሔር እንዲወደን ሆነን ከተገኘን ማርና ወተት ወደሚፈስባት ወደዚያች አገር ያስገባናል። የምድሪቱን ሰዎች አትፍሩ፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር መሆኑን አውቀው፣ በመፍራት ደንግጠው ጥላቸው ተገፎ፣ የጀግንነት ወኔ ተለይቷቸዋል›› አሏቸው። ሕዝቡ ተናድደው ስለ ነበር፣ ሙሴንና አሮንንም መላው የእስራኤል ማኅበር በድንጋይ ደብድበው ለመግደል በብርቱ ተነሣሡባቸው፤ ነገር ግን፣ የሚያንጸባርቅ ብርሃን ያለው የእግዚአብሔር ክብር በድንኳኑ ላይ በመታየቱ ፈርተው፣ ያሰቡትን ክፉ ነገር ለመፈጸም አልቻሉም።

11-25 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹እነዚህ ሕዝብ እኔን የሚንቁኝ እስከ መቼ ነው?! በመካከላቸው ያደረግሁትን ድንቅ ሥራ ሁሉ አይተው የማያምኑብኝስ እስከ መቼ ነው? በአባር በቸነፈር ላጠፋቸው ወስኛለሁ፤አንተንም ከእነርሱ በሚበልጥ ሕዝብ ላይ እሾምሃለሁ››።ሙሴ ግን፣እግዚአብሔር-የሕዝቡን-ኃጢአትና-በደል-ይቅር-ብሎ-ይምራቸው ዘንድ-አጥብቆ-/ለመነ። እግዚአብሔር-አጕረምራሚዎች-የሆኑትን ሕዝብ በሞት ቀጣ 26-38 እግዚአብሔር የሙሴን ምልጃ ተቀብሎ እንዲህ አለ፤ ‹‹እነሆ፣ ያን ሁሉ ድንቅ ሥራ በፊታቸው አሳይቻቸው፣ የትእግሥቴን ብዛት በመፈታተን ለእኔ መታዘዝን እምቢ ብለዋል ። ስለዚህ ፣ ያችን ምድር አጥንተው ከመጡት ተወካዮች መካከል ከካሌብና ከኢያሱ በቀር፣ ወደዚያች ምድረ- ርስት የሚገባ አይኖርም።ለሕዝቡ እንዲህ-ብለህ ንገራቸው፣ ‹‹እነሆ፣ እኔ እስከ ዐርባ ቀን ላስገባችሁ ወስኜ ነበር፣ እናንተ ግን፣ ዐርባ ቀን የሚለን ዐርባ ዓመት ማለቱ ነው ብላችሁ ተናግራችኋል፤ ስለዚህ፣ አሐቲ ዕለት ትኩንክሙ ዓመ =አንዲቱ ዕለት እንደ አንድ ዓመት ትሁንባችሁ። እነሆ፣ ዐርባ ዓመት ሙሉ በዚህ ምድረ-በዳ



እንድትንከራተቱ አደርጋለሁ። ዕድሜአችሁ ከኻያ ዓመት በላይ የሆነ ሁሉ ወደ ምድረ-ርስት ሳትገቡ እሬሳችሁ በዚሁ በረሃ ወድቆ ይቀራል። ምርኮኞች ሊታደርግብን ነው ያላችኋቸውን ልጆቻችሁን ግን አስገባቸዋለሁ ።በእኔ-ላይ-ያመፃችሁብኝ-እናንተ- በተለይ- ትሞታላችሁ ፤እኔ-እግዚአብሔር-ይህን ተናግሬአለሁ››።እነዚያ አሸባሪ ቃል የተናገሩት ዐሥሩ መልክተኞች፡ ከእግዚአብሔር የአባር ቸነፈር መቅሠፍት ታዝዞባቸው ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ፊት ሞቱ። 39-45 አንዳንዶቹ ደግሞ፣ ‹‹አሁኑኑ እንዝመትና አገሪቱን በቍጥጥራችን ሥር እናድርግ›› ብለው ለመዝመት ተነሡ። ሙሴም እንዲህ አላቸው፤ ‹‹ለእግዚአብሔር የማትታዘዙ ስለ ምንድን ነው?! እነሆ፣ በአሁኑ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር አይደለም። ስለዚህ፣ በጠላቶቻችሁ እጅ ትወድቃላችሁ›› አላቸው። እነርሱ ግን፣ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ታቦትና ሙሴም ከሰፈር ሳይነሡ ብቻቸውን ተለይተው፣ ወደ ተራራማው አገር ለመዝመት መገሥገሥ ጀመሩ።እነርሱንም በዚያ የሚኖሩ አማሌቃውያንና ከነዓናውያን ድል አድርገው አሳደዷቸው።

**፲፭ /15፡ የሰንበትን ቀን መሻር ያስከተለው የሞት አደጋ**፤ 32-36 ሰለጸዓድ ተብሎ የሚጠራ አንድ ሰው፣ በሰንበት ቀን የማገዶ እንጨት ሲለቅም ተገኝቶ ስለ ተያዘ፣ ወዲያውኑ በመላው የእስራኤል ማኅበር በደንጊያ ተደብድቦ እንዲገደል ተፈረደበት።

**በልብስ ዘርፍ ላይ ሰማያዊ ጥለት -ሲኖር እንደሚገባ መመሪያ ተሰጠ**። 37-41 ሕዝቡ መልብሳቸው ጠርዝ ላይ ሰማያዊ ጥለት ያሠሩ ዘንድ እንዲነግር፣ እግዚአብሔር-ሙሴን አዘዘው።

**፲፮ /16፡ ቆሬ፡ ዳታንና አቤሮን የፈጸሙት ዓመፅ፡**

1-3 ቆሬ ትውልዱ ከነገደ ሌዊ ነው፡በድፍረት ተነሣስቶ፣ ከሮቤል ነገድ የሆኑት ዳታንና አቤሮን ተባብረው፣ማኅበሩ መርጦዋቸው በአመራር ሥራ የታወቁ ሌሎችም ሁለት መቶ ኀምሳ ሰዎች ደግፈዋቸው፣ ሙሴንና አሮንን እንዲህ አሏቸው፤ ‹‹እናንተ እኮ በሥልጣናችሁ ከልክ አልፋችሁአል፣ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ብቻ ሳይሆን ከእኛም ጋር ነው። በእግዚአብሔር ጉባኤ ላይ ራሳችሁን ከፍ ፡ከፍ አድርጋችሁ የምትኖሩት እስከ መቼ ነው?!›› ሙሴ ሲመልስላቸው ‹‹የእኔና የአሮን ሹመት በእግዚአብሔር ምርጫ እንጂ፣ በራሳችን ምኞት አይደለም›› በማለት አስረዳ። 16-34 ቆሬና ተከታዮቹ ሁለት መቶ ኀምሳ ሰዎች ዕጣን የሚያጥኑባቸውን፣ከነሐስ የተሠሩ ጥናዎች አዘጋጁ፤ ፍምና እጣን ይዘው



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔር ወደሚመለክበት ድንኳን መጥተው ከሙሴና ከአሮን ጋር ቆሙ። በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር በቆሬ፣ በዳታንና በአቤሮን ላይ ተቈጣ፤ ምድሪቱም ተከፍታ ከነቤተ-ሰቦቻቸውና ከነድንኳኖቻቸው ዋጠቻቸው። ከዚያን በኋላ፣ እግዚአብሔር እሳት ልኮ ፣ ያጥኑ የነበሩትን ሁለት መቶ ኃምሳውን ሰዎች አቃጠለ። 41-50 በማግስቱ ደግሞ፣ የእስራኤል ልጆች ማኅበር ሁሉ፣ «እናንተ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ገድላችኋል» በማለት በሙሴና በአሮን ላይ -አጕረመረሙ። ወደ መገናኛ ድንኳን ሲመለከቱም የእግዚአብሔር ክብር መገለጡን አዩ፡እግዚአብሔር ተቈጥቶ በቅጽበት ሊደመስሳቸው ተቃርቦ ነበርና ሙሴ፣ አሮንን ጥናህን ይዘህ፣ ከመሠዊያው ላይ እሳት ወስደህ ዕጣን አድርግበት። «ፈጥነህምወደ ሕዝቡ በመሄድ አስተስርይላቸው፤ የእግዚአብሔር ቍጣ መጥቶባቸዋልና» አለው። አሮን በሙታንና በሕያዋኑ መካከል ቆሞ ሲያስተሠርይላቸው፣ ቀደም ሲል፣ ዐሥራ ዐራት ሺህ ሰባት መቶ ሕዝብ ደምስሶ የነበረው መቅሠፍት ቆመ።

፲7/17፡ <u>የአሮን በትር-ልምላሜና ፍሬ፤</u> 1-11 እግዚአብሔርም ሙሴን፣ «ከእያንዳንዱ ነገደ እስራኤል አንዳንድ በትር ተቀብለኽ አሥራ ሁለት በትሮችን ወደ መገናኛው ድንኳን አምጥተህ፣ አንተን በማነጋግርበት ስፍራ በታቦቱ ፊት-ለፊት አኑራቸው» አለው። ሙሴም እንደ ታዘዘው አደረገ። እነሆ፣ ከነገደ ሌዊ የአሮን ስም የተጻፈባት በትር በማግስቱ ስትታይ፣ ለምልማ-አብባ የበሰለ የለውዝ ፍሬ አፍርታ ተገኘች። *(**ትርጓሜ፡** የዚያች በትር ፍሬ፣ የአሮን ክህነት ሥልጣን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተገኘ መሆኑን የሚያሳይ ነው። በሌላም በኩል፣ በትረ አሮን የምልእተ ጸጋ ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ ስትሆን፣ ፍሬዋ ደግሞ የጌታ ምሳሌ ነው። ያች በትር ማንም ሰው ሳይደክምባት በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ አፍርታ እንደ ተገኘች፣ ቡርክት ቅድስት ድንግል ማርያምም ያለ ዘርዐ ብእሲ በግብረ መንፈስ ቅዱስ ጌታን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና መውለድዋን ያመለክታል። የእውነተኞች -አማኞችም-ሕይወት-የእግዚአብሔር-መንፈስ ሲያድ ርበት እንደዚያች በትር ለምልሞ ፍሬ ምግባር ወሃይማኖት የሚገኝበት- መሆን-ይችላል። "ያዕቆብ-ሥር-ይሰዳል እስራኤልም ለምልሞ አበባ ይሰጣል" የሚለው ትንቢት በክርስቶስ አምነው በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ልዩ የሕይወት ልምላሜ የሚያገኙ ምእመናን ምሳሌ ነውና ( ኢሳ 27፡ 6 ።)*

፲፰/18፡ የካህናት ርስት እግዚአብሔር ነው፤ 20 እግዚአብሔር ካህኑን



አሮንን እንዲህ አለው፤ «ለትውልድ የሚተላለፍ ርስት መካፈል አያስፈልግህም፤ እኔ ራሴ ለአንተ ርስትህ ነኝ»። 5-26 እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ለካህናት የሰጠው የመመሪያ ትእዛዝ ይህ ነው፡- "እግዚአብሔር እንደ ርስት አድርጎ የሚሰጣችሁን ዐሥራት ከሕዝቡ-ስትቀበሉ-፣እናንተ-ከድርሻችሁ -ሁሉ፣ ዐሥራት-በማውጣት ለእግዚአብሔር መባ ትሰጣላችሁ› (ነህምያ 10፥38 ) ።

፲9 /19፡ የሚቃጠል መሥዋዕት ሆና የምትቀርብ ጊደር፡ አመድዋ ከሠፈር ውጭ በንጹሕ ስፍራ ይፍሰስ' ተብሎ ታዘዘ ። *<u>(**ትርጓሜ፡**</u> ይህም በገዛ ደሙ ሕዝቡን ለመዋጀት ቅዱስ ፈቃዱ የሆነ ክርስቶስ፡ አምላካችን ከከተማ በር ውጭ መከራ የሚቀበል መሆኑን የሚያመለክት ምሳሌ ነበር* <u>(-ዕብ 13፡ 12 ፡፡ )</u> """"""""""""""""""""""

<u>በድን የመንካት ርኵሰት፡</u> 11-22 በድን የሚነካ ሰው እስከ ሳምንት፣ የመንጻት ሥርዓት የሚፈጸምበትንም ውሃ የሚነካ እስከ ምሽት ርኵስ ነው። ሰው የሞተበት ድንኳንና በውስጡ የሚገኘው ዕቃ ሁሉ፣ እስከ ሰባት ቀን ርኵስ ይሆናል። ርኵሰትንም ለማንጻት ለኃጢአት ማስተስረያ ከተቃጠለችው ጊደር ጥቂት አመድ ተወስዶ ከተበጠበጠ በኋላ በሂሶፕ ይረጭ።

፳ /20 ፡ <u>በቃዴስ የተፈጸሙ ድርጊቶችና የሙሴ ስሕተት ፡</u>

1 በዚያን ጊዜ ማርያም (የሙሴና የአሮን እኅት) ስለ ሞተች በቃዴስ በረሃ ተቀበረች። 3-12 በውሃ እጦት ምክንያት፣ ሕዝቡ እንደ ገና ማጕረምረም ጀመሩ። ሙሴና አሮንም በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሠረት ሕዝቡን ሰብስበው፣ ሙሴ፣ «እናንተ ዓመፀኞች ከዚህ የዐለት ድንጋይ ውሃ እንድናፈልቅላችሁ ትፈልጋላችሁን?» አላቸውና ፡ድንጋዩን በበትሩ ሁለት ጊዜ ሲመታው ውኃ ፈለቀላቸው፤ ሕዝቡና እንስሳዎቻቸውም ከዚያ ጠጡ። እግዚአብሔርም በሙሴና በአሮን ላይ ተቈጥቶ፣ «ይህን ውኃ ባፈለቀሁላቸው-በእስራኤል-ማኅበር-ፊት-ለእኔ-ክብር-ባለመስጠታችሁና ባለማመስገናችሁ ምክንያት የዚህ ሕዝብ መሪዎች ሆናችሁ ወደዚያች ምድረ-ርስት አትገቡም» ሲል በብርቱ ገሠጻቸው።

*(**ትርጓሜ** ፡ እዚህ ላይ የተጸመው ስሕተት ምን ነበር? እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያፈለቀላቸውን ውኃ ሙሴና አሮን ራሳቸው እንዳፈለቁላቸው አድርገው ለእግዚአብሔር ምስጋና ሳያቀርቡ መቅረታቸው እግዚአብሔርን አስቈጥቷል። ምን ጊዜን ቢሆን ምግብም ሆነ*



www.ethiopianorthodox.org

የምንጠጣው ውኃ ሲቀርብልን እግዚአብሔር የሚመሰገንበትን የማዕድ ጸሎት ማድረግን መርሳት አይገባንም። ማንም ሰው እግዚአብሔርን በጸሎት ማመስገን ያለበት ምግብ ሲቀርብለት ብቻ ሳይሆን፡ ተመግቦ ሲያበቃም ያን ምግብ የሰጠውን ፈጣሪውን ማመስገን እንደሚገባው በዘዳግም መጽሐፍ መዕራፍ 8፡ 10 እንዲህ ይላል፡ በልተህ ስትጠግብና ጠጥተህ ስትረካ፤ ይህችን ለም ምድር የሰጠህን አምላክህን እግዚአብሔርን አመስግን። ጥሩ ቤቶች ሠርተህ የከብቶችህና የበጎችህ መንጋ ርቢ ሲበዛልህ፤ ወርቅና ብር እንዲሁም ሌላው ሀብት ሁሉ ሲሞላልህ አይተህ፤ ልብህ እንዳይታብይና አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ ( መዝ 61፡ 10+ ጢሞ 6፡ 10 ) ።ለዚህም ተጓዳኝ ትርጉም ሰጪ ሆኖ የቀረበ አንድ ታሪክና ምሳሌ ከዚህ የሚከተለው ነው፡"""""" <u>የቡቺ አባት መጡ</u> ! """"""""" አንድ የዋድላ ደላንታ አባት ገበሬ ልጁን "ምግብ በሚቀርብልህ ጊዜ እንዲሁ እንዳገኘህ መዘንጠል ሳይሆን። እየጸለህ የፍጥረት ሁሉ መጋቢ የሆነ ፈጣሪህን እግዚአብሔርን በጸሎት አመስግነህ ብላ " ብሎ መክሮት ነበር። በአባቱ ምክር እየተመራ በጸሎት ባርኮ ሲመገብ የተረፈውን ለውሻው ይሰጣል ። ውሻው (ቡቺ ) ግን ዝም ብሎ ያገኘውን ይበላ ነበርና ወደ አባቱ ሄዶ 'አባዬ አንተ በመከርኸኝ መሠረት እኔ እየጸለይሁና እግዚአአብሔርን እያመሰገንሁ እበላለሁ። ቡቺ ግን አይጸልይም "አለ። አባትዮውም "ቡቺ መካሪ አባት የለውም። አንተን ግን እኔ አባትህ ስለመከርሁህ እንዳልኩት ፈጣሪህን እያማሰገንህ መመገብህ መልካም ነው" አለው። ዛዲያማ አንድ ቀን አንድ የጎረቤት ሰው ወደዚያ ቤት ይመጣና ምግብ ቀርቦለት፡ ምንም ቃል ሳይጸልይና እግዚአብሔርን ስያመሰግን ዝም ብሎ ሲበላ አይቶት፡ ያ ሕፃን ልጅ ወደ አባቱ እየሮጠ መጥቶ" አባዬ የቡቺ አባት መጡ' አለው። በምን አወቅህ-?'_ቢለው፡ ልክ እንደቡቺ ሳይጸልዩ ይበላሉ፡ መጥተህ ማየት ትችላለህ " አለው ይባላል። እንግዲህ የዚህ ታሪክና ምሳሌ ዋና መልእክት "የሰው ልጅ ከእንስሳ ማነስ አይገባውም። ምግብ ከመቍረስ በፊትም ሆነ ከምግብ በኋላ ፈጣሪውን ማመስገን ለምን ይረሳል ?" የሚል ነው። " ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ /የተባረከ ይሆናል" ተብሎ ተጽፏልና ነው ( 1 ጢሞ. 4. 5 )። _ሌላውም አንድ ሕፃን ልጅ በችኮላ ቍርሱን በልቶ ስሲጨርስ ሳይጸ ልይ መብላቱ ትዝ ባለው ጊዜ። ተጽጽቶ " ሰማያዊ አባት እግዚአብሔር „ ሆይ ! በሆዴ ውስጥ ያለውን ምግብ ባርክልኝ' ማለቱ ይታወሳል።



<u>የዔዶም ንጉሥ እስራኤላውያን በአገሩ እንዳያልፉ ከለከለ ፡</u>
14-21 ሙሴም ወደ ዔዶም ንጉሥ መልክተኞቹን ልኮ፣ ‹‹እነሆ፣ ይህ መልእክት ዘመዶችህ ከሆኑት ከእስራኤል ነገዶች የተላከ ነው፡፡ ከዋናው መንገድ ሳንወጣ በአገራችሁ መካከል ማለፍ ፍቀዱልን፤ እኛና እንስሶቻችን ውኃ ብንጠጣ እንኳ ዋጋ እንከፍላለን›› ብለው ቢለምኑት እምቢ በማለቱ፣ በሌላ መንገድ ዞረው አለፉ፡፡

<u>የአሮን መሞት፡</u> 22-29 ሕዝቡ ተጉዘው ወደ ሆር ተራራ ሲደርሱ፣ በዚያው ካህኑ አሮን ሞተ፡፡ ሙሴ የአሮንን የክህነት ልብስ አውልቆ ለልጁ ለአልዓዛር አለበሰው፡፡መላውም የእስራኤል ማኅበር ለአሮን ሠላሳ ቀን አለቀሱለት፡፡

**ኍ፩/21፡ ከዮርዳኖስ ማዶ የተገኘ ድል፤** 1-3 በደቡብ በኩል አራድ የተባለው አገር ገገር የነበረው የከነዓናውያን ንጉሥ፣ እስራኤል በጉዞ ላይ ሳሉ አደጋ ጥሎባቸው ጥቂቶቹን ማረከ፡፡ እስራኤላውያንም ለእግዚአብሔር ብፅአት አድርገው ጦርነት ገጠሙት፤ ድልም አደረጉት፤ ከተማው በፍጹም የተደመሰሰ መሆኑን ለመግለጥም ሆርማ አሉት፡፡

<u>በእባብ አምሳል የተሠራው የነሐስ በትር፤</u> 4-9 ሕዝቡ ስለ ምግብና ውሃ እጦት እያጉረመረሙ በእግዚአብሔር ላይ ክፉ ቃል በመናገር ስላስቈጡት ነዘር (መርዘኛ) እባብ አስነሥቶባቸው፣ ብዙዎች ተነድፈው ሞቱ፡፡ ሙሴም ወደ እግዚአብሔር በጸለየ ጊዜ፣ ‹‹እባቡን አስመስለህ አንድ በትር ከነሐስ ሥራና በዛፍ ላይ ስቀለው፤ በእባብ የተነደፈውም ሰው ሁሉ እርሱን-አይቶ-ይዳን››ሲል-አዘዘው፡፡ *(<u>ትርጓሜ፡</u> እባብ_የሰይጣን ዲያብሎስ ምሳሌ ነው። በእባብ መርዝ እንዳለበት በዲያብሎስም ኃጢአትና ፅኑ ፍዳ አለበትና ነው።በእባብ አምሳል ከነሐስ የተሠራ በትር የጌታችን የአምላካችን፣ መድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው ። በዚያ በትር መርዝ እንደ ሌለበት ሁሉ፣ ክርስቶስም በባሕርዩ ንጹሕ ነው። ያ የእባብ ብትር በአባብ አምሳል እንዲሰቀል መሆኑ ፣ ክርስቶስ በአርአያ እኩያን ማለት በክፉ አድራጊዎች አምሳል የሚሰቀል መሆኑን ያሳያል። "ተኖለቈ ምስለ ጊጉያን =ከኃጢአተኞች ጋር ተቈጠረ" ተብሎ ተጽፎአልና ( ኢሳ 53፡ 9) _ይህንንም ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ_፡ ‹‹ከጻድቃን ጋር ይደምረን ዘንድ ፈቅዶ፣ ሠምሮ ከአመፀኞች ጋር ተሰቀለ›› ብሎ ርጉሞታል። በእባብ አምሳል ተሠርቶ፣ የተሰቀለውን እባብ አይተውና ድምፁን ሰምተው የዳኑ ሰዎች ጌታ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ በሰው አርአያና መልክ በተገለጠ ጊዜ ፣*



www.ethiopianorthodox.org

በዓይነ ሥጋ አይተውት፣ የወንጌሉን ትምህርት ሰምተው ያመኑና የዳኑ ሰዎች ምሳሌ ሲሆኑ፣ ድምፁን ብቻ ሰምተው የዳኑት ደግሞ ጌታ ካረገ በኋላ ከተነሡ ተከታዮቹ ሐዋርያትና ከሌሎችም መምህራን የተሰበከላቸውን የወንጌሉን ቃል ሰምተው ያመኑ ሰዎች ምሳሌዎች ናቸው›› ይላል የኢ.ት ሊቃውንት ትርጓሜ ።) ''''''''''''''''''''''''''

21--35 የባሳን ንጉሥ ዖግና የሐሴቦን ንጉሥ ሴዎን ፡በአገሮቻችን መካከል አናሳልፍም ብለው መንገድ ስለ ዘጉባቸው፣ እስራኤላውያን ተዋግተው በእግዚአብሔር ኀይል ድል አድርገው ምድራቸውን ሁሉ ወረሱት። (**ትርጓሜ** ፡ ወደ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚደረገውም ጉዞ እንደዚሁ መሰናክል-የበዛበት-ስለሆነ-እንደ-ኬላ ቈራጭ፣ በየመንገዱ የተሠራውን_ የሰይጣን ዲያብሎስን ምሽግ ለማፈራረስ በሃይማኖት ፀንቶ በጸሎት የመትጋትን መንፈሳዊ ተጋድሎ /ዐርበኝነት ይጠይቃል።)

## የሞአብ ንጉሥ ባላቅ-ተራጋሚውን በለዓምን አስጠራ፡

1--6 እስራኤልም ጉዟቸውን በመቀጠል፣ ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ በስተምሥራቅና በኢያሪኮ ትይዩ በሞዓብ ሜዳ ላይ ሠፈሩ። ቀደም ሲል ስላስቈጡት ነዘር (መርዘኛ) እባብ አስነሥቶባቸው፣ ብዙዎች ተነድፈው ስላስቈጡት ነዘር (መርዘኛ) እባብ አስነሥቶባቸው፣ ብዙዎች ቀዳጁትን ድል የሰማው የሞዓብ ንጉሥ ባላቅም፣ ከጦርነት ይልቅ እነርሱን በእርግማን ለማጥፋት ፈልጎ፣ በለዓም የተባለውን ጠንቋይ አስጠራ። 12-30 እግዚአብሔር ግን በለዓምን፣ ‹‹እግዚአብሔር የባረከውን ሕዝብ አንተ መርገም አትችልምና እንዳትሄድ›› ብሎ ከለከለው። እንደ ገናም ዘግየት ብሎ የእግዚአብሔር መልአክ በለዓምን፣ ‹‹መሄዱን ሂድ፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የእርግማን ቃል ሳይሆን፣ እኔ የምነግርህን ቃል ብቻ እንድትናገር›› ብሎ አዘዘው። ስለዚህም፣ በለዓም አህያውን ጭኖ፣ ለመሄድ ተነሣ። በጉዞ ላይ ሳለም፣ የእግዚአብሔር መልአክ ሰይፉን መዝዞ በአህያዪቱ ፊት ቆመ። አህያዪቱ መንቀሳቀስ ባለመቻልዋም፣ በለዓም ደበደባት። እግዚአብሔርም የአህያዪቱን አንደበት ከፍቶላት በለዓምን እንዲህ አለችው፡ ‹‹ሦስት ጊዜ የመታኸኝ ምን በድየህ ነው?›› በለዓምም ‹‹ሰይፍ በእጄ ቢኖር በገደልኩሽ ነበር›› ሲላት፣ ‹‹ከብዙ ዘመን ጀምር እስከ ዛሬ ድረስ፣ ያገለገልኩህ አህያህ አይደለሁምን?! እንዲህ እንዲህስ አደርግ ዘንድ ልማዴ ነበርን?!›› አለችው። 31-35 እግዚአብሔር የበለዓምን ዓይኖች ከፈተ። የእግዚአብሔርም መልአክ በመንገዱ ላይ ቆሞ፣ የተመዘዘም ሰይፍ በእጁ ይዞ በታየው ጊዜ፣ በግንባሩ መሬት ላይ



ወድቆ ሰገደ። የእግዚአብሔርም መልአክ፣ ‹‹እነሆ፣ በመንገድህ ይልብህ አሳብ በፊቴ ጠማማ ነውና ልገሥፅህ መጥቻለሁ፤ አሁንም፣ መሄዱን ሂድ፤ ነገር ግን እኔ የምነግርህን ቃል ብቻ እንድትናገር›› ይሁን" አለው። (**ትርጓሜ**፡ በአንድ በኩል የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመድፈጸም ደቃደኛ መሆኑን እየገለጠ፡ በሌላ በኩል ደግሞ ንጉሥ ባላቅን ለማስደሰት በጕዞው ላይ የእርግማን ቃል ማሰላሰል ጀምሮ ስለነበር፡ የልቡን የሚያውቅ /ማእምረ ኅቡአት እግዚአብሔሔር የሚገሥፀውን መልአክ ሰድዶ በገዛ አህያውም ጭምር እንዲዘለድፍ አድርጓል ይላል 2 ጴጥ 2፡ 16 )። ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

36-41 የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ፣ በለዓምን በአክብሮት ተቀብሎ ሲያነጋግረው፣‹‹መምጣቴን ብቻ አይተህ መደሰት አይገባህም፤ መናገር የምችለው እግዚአብሔር የሚሰጠኝን ቃል ብቻ ነውና›› ሲል መለሰለት። ባላቅ ግን፣በአሳቡ ፀንቶ ምኞቱን ለማስድፈጸም በነበረው እቅድ መሠረት የከብቶችን ፍሪዳና በጎችን አሳርዶ ለመሥዋዕት አቀረበ።

፳፫ /23 ፡ <u>የበለዓም መጀመሪያ ትንቢት</u>፡ 8-10 እግዚአብሔር ወደ በለዓም መጥቶ ቃሉን በአንደበቱ አኖረ። ስለዚህ፣ በለዓም እንዲህ አለ፤ ‹‹እግዚአብሔር ያልረገመውን ሕዝብ እኔ እንዴት አድርጌ እረግማለሁ?! እግዚአብሔር እንዲጠፋ ያላደረገውንስ ሕዝብ ይጥፋ ብዬ የምፈርድ እኔ ማን ነኝ? እነርሱ ራሳቸውን ችለው የሚኖሩና ከሌሎች ሕዝቦችም ይልቅ የተለዩ መሆናቸውን ያውቃሉ። ብዛታቸው እንደ ምድር አሸዋ ነው። የዘመኔ መጨረሻ ከእነዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ አንዱ ቢሆንልኝ እወዳለሁ፤ እንደነዚህ ጻድቃን (እንደነዚህ ደጋግ ሰዎች) ሆኜ በሰላም-ልሙት››።

<u>የበለዓም ሁለተኛ ትንቢት</u> ፥- 18-24 እግዚአብሔር እንደ ሰው የሚዋሽና የሚጸጸት አይደለም።እንደ ሰውም አሳቡን አይለውጥም። የርሱን በረከት እኔ መለወጥ አይቻለኝም። የእስራኤል ሕዝብ እንደ ብርቱ አንበሳ አድኖ የያዘውን ቦጫጭቆ እስኪበላ ድረስ ዕረፍት የለውም።

፳፬ /24 ፡ የበለዓም ሦስተኛ ትንቢት፥ 4-9 የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ፤ የአምላኩንም ራእይ የሚያይና ዓይኖቹም የተከፈቱለት (በለዓም) እንዲህ ይላል፤ ‹‹ያዕቆብ ሆይ፣ ድንኳኖችህ ምንኛ ያምራሉ?



www.ethiopianorthodox.org

ንጉሡ ከአጋግ ይልቅ ከፍ:: ከፍ ይላል:: እግዚአብሔር-ሕዝቡን-ከግብጽ-መርቶ-አወጣቸው፤ስለዚህ፣እርሱ-ራሱኢ-ይዋጋላቸዋል፤ጠላቶቻቸውን እንደ አንበሳ ይቦጫጭቃሉ፤አጥንቶቻቸውን ያደቅቃሉ፤ቀስቶቻቸውንም-ይሰብራሉ:::-እስራኤልን--የሚመር-ሁሉ--የተባረከ--ነው፤-የሚረግማቸ ውም የተረገመ ይሆናል::

<u>በለዓም የተናገረው 4ኛው የመጨረሻ ትንቢት፡</u> 15-25 የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰማ የቢኦር ልጅ ባላቅ እንዲህ ይላል፤ «አየዋለሁ፤ ግን አሁን በቅርብ ቀን አይደለም:: ከያዕቆብ-ኮከብ ይወጣል፤ከእስራኤልም በትር ይነሣል፤ የሞዓብን ማዕዘኖች *(መሪዎችን)* ይመታል፤ ሕዝቡንም ይዳምጣል፤ እስራኤል አሸናፊ (ድል አድራጊ ) እንደሆነ ይኖራል:: ኤዶምያስና ሴይር ርስቱ ይሆናሉ:: ከያዕቆብ የሚነሣ የሕዝብ ገዢ ይሆናል፡ አማሌቅ የሕዝብ አለቃ ነበር፤ ፍጻሜው ግን ወደ ጥፋት ይመጣል:: እግዚአብሔር ይህን ሲያደርግ፣ አወይ ማን በሕይወት ይኖር ይሆን? <u>**(ትርጓሜ**</u>: *በለዓም አስፈርቶና አስገርሞ የተናገረው ይህ ትንቢት ከ400 መቶ ዓመት በኋላ በሞአብ ላይ ተፈጽሟል::*
*ይኸውም ለመጀመሪያ ጊዜ በእስራኤል ላይ ነግሦ ለነበረው ለንጉሥ ሳኦል በነቢዩ ሳሙኤል አማካይነት የተላለፈለት መልእክት "እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ አዞሃል :"ሕዝቤ-ከግብጽ-ከወጡ-በኋላ መንገድ አናሳልፍም ብለው አማሌቃውያን የሠሩትን በደል አሁን እበቀላለሁ : ሄደህ አማሌቅን ምታ ሕዝቡንም ደምስስ፡ የሚል ነበር:: ንጉሥ ሳኦልም በአትእዛዙ መሠረት የፈጸመው ድምስሴ ልክ በለዓም አስፈርቶና አስገርሞ በተናገረው ዓይነት ነበር መፅሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊ 15):: 2 -3 ::)* ከዚህ-በኋላ፡ በለዓም ስለ ቄናውያን ዘሮች-መጥፋት-ትንቢት ተናግሮ እንደ ፈጸመ፣ ወደ አገሩ ለመሄድ ተነሣ::

## ፳፭ /25 <u>የበለዓም ክፉ ምክር ያስከተለው አደገኛ</u> መቅሠፍት :-

1 -2 እስራኤልም በሰጢን ሠፈሩ:: ከሞአብ-ልጆች-ጋር አመነዘሩ:: የጣዖት ለጣዖት-አማልክቶቻችው- የቀረበውን- ተረፈ- መሥዋዕት በመብላትም ረከሱ:: <u>**(ትርጓሜ**</u> : *በለዓም ከንጉሡ ከባላቅ እጅ ልዩ፡ ልዩ የወርቅና የብር ስጦታ ተቀብሎ ፤ እስራኤልን ለመርገም ባይችልም፤ የመከረባቸው ደባና ተንኰል ነበር፡ ይኸውም «እግዚአብሔር ይህን ሕዝብ አትርገም አለኝ እንጂ፣በእነርሱ ላይ ክፉ አትምከር ብሎ አላዘዘኝም:: አንተ የምትፈልገው የእስራኤልን ሕዝብ መጥፋት ስለ ሆነ፣ ዘዴውን ልምከርህ:: በሞዓብ ምድር ከሚገኙት ሴቶች መካከል ውበትና ቍንጅና ያላቸውን ወጣት ልጃገረዶች ምረጥ፤ ለጣዖት የተሠዋውን ተረፈ-መሥዋዕት አስይዘህ፣ በጥሩ ልብስ አጊጠው ወደ እስራኤል ሠፈር እንዲገቡ አድርግ:: ይህ በበረሃ ጉዞ ላይ መና እየተመገበ በፍትወተ-ሥጋ ሲቃጠል የቈየ ሕዝብ፣ሴት አይቶ አያልፍምና ፈቃደ ሥጋ ለመፈጸም በሚጠይቃቸው ጊዜ፣ መጀመሪያ ለጣዖት ከቀረበው መሥዋዕት ትራፊውን ብሉልን ይበሉአቸው:: ከዚያ በኋላ፡ ተረፈ-መሥዋዕቱን በልተው ዝሙት ሲፈጽሙ፣ ራሱ እግዚአብሔር ተቈጥቶ የገዛ ሕዝቡን እስራኤልን ያጠፋልሃል›› ብሎ መከረው (ራእ 2፡ 14 ) የሞዓብ ንጉሥ ባላቅ ይህን ምክር ተቀብሎ፣ የእስራኤል ሕዝብ ከሞዓብ ሴቶችጋር ዝሙት እንዲፈጽሙ አደረገ:: በዚህም ምክንያት እግዚአብ*
*ሔርን ስላስቈጡት፣ ተሰቅ ለው እንዲሞቱ ተፈረደባቸው፣ኻያ ዐራት ሺህ ሰዎች በእሳት ተቃጥለው ሞቱ (አለቁ):: የካህኑ የአሮን ልጅ ፊንሐስ ከነገደ ስምዖን ዘምሪ ተብሎ የሚጠራ አንድ እስራኤላዊ ፡ ከስቢ ተብላ ከምትጠራ አንዲት ሞአባዊት ጋር በድንኳን ውስጥ ተኝተው ዝሙት ሲፈጽሙ፡ ወደ ድንኳኑ ገብቶ፣ ሆዳቸውን በጦር ወግቶ ከመሬት ጋር በሠፋቸው ጊዜ የእግዚአብሔር ቍጣ በረደ።*

## ፳፮ /26 : ለሁለተኛ ጊዜ የተካሄደው የሕዝብ ቈጠራ፤

1-51 ከእያንዳንዱ ነገደ ሕዝብ ዕድሜያቸው ኻያ ዓመትና-ከዚያም በላይ ሆኖ በወታደርነት ማገልገል የሚችሉት ወንዶች እንዲቈጠሩ፣ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት፣ቈጠራ ተካሂዶ የተገኘው ውጤት፣ስድስት መቶ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሠላሳ ( 601, 730 ) ነበር ::

## ፳፯/27፡ <u>የሰለጰአድ ሴቶች ልጆች የርስት አወራረስ መብት ጥያቄ፡</u>

1-11 ማሕላ፣ ኖዓ፣ ሐግላ፣ ሚልካና ቲርጻ ተብለው የሚጠሩ የሰለጰአድ ሴቶች ልጆች፣ስለ አባታቸው ርስት አወራረስ የመብት ጥያቄ አቀረቡ:: በእግዚአብሔርዘንድ ፊተቀባይነትን አግኝቶ ::«ሠናየ ይቤላ አዋልደ ሰለጰአድ =የሰለጰአድ ልጆች ይህን ጥያቄ ማቅረባቸው እውነትን ተከትለው ስለሆነ አሳባቸውን ተቀብለህ (አስተዋስቦን ምስለ ቅሩቦን =ከቅርብ ዘመዶቻቸው ጋር እንዲገቡ አድርገህ ርስት ያግኙ›› ሲል ለሙሴ ነገረው::በእነርሱ-ጥያቄ-መነሻነት-በሞላው-እስራኤል፣በተለይም-አባቶቻቸው የሞቱባቸው ሴቶች ልጆች ሁሉ፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው





www.ethiopianorthodox.org

ጋር እየተጋቡ ርስት የመውረስ መብት እንዲሰጣቸው ተፈቀደ። (ስለጸአድ ትውልዱ ከነገደ ምናሴ ሲሆን፣ በሰንበት እንጨት ሲለቅም ተገኝቶ በድንጋይ ተደብድቦ የሞተ ነው ዘኁል 15። 32 -35 )።

*(**ትርጓሜ:** በቅዱስ መጽሐፍ" ሠነየ ይቤላ አዋልደ ሰለጸአድ"= የሰለጸአድ ሴቶች ልጆች የተናገሩት ቃል /ያቀረቡት አሳብ መልካም-ነው"-ተቀበለሀ-ተግባራዊ-አድርግላቸው"-ተብሎ-በራሱ በእግዚአብሔር አምላክ ቃል የተመሰከረላቸውና ልሙሴ የነገረላቸው እነዚያ ልጆች-የመጀመሪያዎቹ የሴቶች-መብት ተከራካሪዎች (Activists) ነበሩ።*

_ሴቶች የምድራዊ ርስት፡ ጉልት ወራሾች ብቻ አይደሉም። የሰማያዊት መንግሥትም ወራሾች እንጂ።ይህንም ሐዋርያው ሲገልጥ "አንትሙሀ: ዕደው አፍቅሩ አንሲያክሙ። ኣስመ ይወርሳ እማንቱኒ ክብረ ወሕይወተ ምስሌክሙ፡ ከመ ኢትትዐቀፍ ጸሎትክሙ =ጉልማሶች ሆይ ! *ጸሎታችሁ ተሰናክሎ እንዳይቀር ሚስቶቻችሁን ውደዱ፡ እነርሱም ከናንተ ጋር አብረው ዘለዓለማዊ ክብርን ወራሾች ናቸውና ይላል -1 ጴጥ 3፡ 7 ።በተለይም እግዚአብሔር ለተዋሕዶተ ሥጋ መርጦ ከሴቶች ሁሉ ለይቶ ላከበራት ለቡርክት ቅድስት ድንግል ማሪያም የሰጣትን ልዩ ጸጋና በረከት ተከትሎ የመጣላቸው የዕኩልነት መብት ለተቀደሱ ሴቶች ሁሉ የፍጹም ነጻነታቸው ማረጋገጫ ሆኗል። ከሴቶች የሚጠበቅ ዋና ነገር በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የሚመራ ሕይወት እንዲኖራቸው ብቻ ነው። ወከማሁ አንስትኒ ይትረስያ ለጸሎት በፈርሐ እግዚአብሔር =ሴቶችም እንደዚሁ እግዚአብሔርን በመፍራት ለጸሎት የሚተጉ ይሁኑ ተብሎ ተጽፏልና ( 1 ጢሞ 2፡ 9 )። ይህንም ሁሉ ያደርጉ ከነበሩት ቅዱሳት አንስት መካከል አንዳንዶቹ የእግዚአብሔር ቅዱስ መንፈስ አድሮባቸው እንደ ሐዋርያት ታምራት የማድረግ ሥልጣን የተሰጣቸው ነበሩ፡ አሉ፡ ወደፊትም ይኖራሉ። ለዚህም ማስረጃ ሆኖ የተጻፈ የቅድስት /ልስልት ሒላሪን ታሪክ መመልከቱ ይበቃል፡ ----*

*<u>በመ /ቅዱስ ቃል ልብዋ የተመሰጠ የልዕልት ሒላሪ ምናኔ</u>*

*_የቍስጥንጥንያ ንጉሠ ነገሥት ዜኖ ሁለት ሴቶች ልጆች ነበሩት።. ከሁለቱ አንደኛዪቱ ለወራሲተ መንግሥትነት ተመርጣ ነበር። ታዲያ ያ ዘመን የክርስትና ሃይማኖት ማደግና መስፋፋት የጀመረበት ጊዜ ስለነበር በወንጌል ትምህርት የታነፀ ሕይወት ያላት ታላቅዋ ልጅ ልዕልት ሒላሪ ልቡናዋ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የተማረከ ስለነበር፡*



*የልዕልት ሒላከቤተ መንግሥት በድንገት ወጥታ ሳትመለስ እንደውጣች በመቅረትዋ ብዙ አሳዛኝ ችግር ተፈጠረ። በየሀገሩ መልእክተኖች ተልከው ፍለጋው ቀጠለ። ነገር ግን ልዕልቲቱን ማግኘት አልተቻለም። ልዕልት ሂላሪ በቀጥታ ወደ እስክንድርያ በሚያመራ መርከብ ተሣፍራ የተጓዘችው ወደ ግብጽ በረሃ ነበርና። እዚያ እንደደረሰች ምሥጢርዋን አበ መነኮሳት ለነበረው ቅዱስ መቃሪ ብቻ ገልጣ በወንድ ስም አባ ሂላሪያ ተብላ ተሰይማ መነኮነ ጸሎት ተሰጣት። ለምን ጽሕም አላወጣችም እንዳይባል ጃንደረባ ነው ተባለች። ቅዱሳት መጻሕፍትን በማንበብ የጸሎት ተጋድሎዋን ቀጠለች። ያም ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ ፍቅር ከእግዚኣአብሔር ዘንድ ማናቸቸንም ሕመም የመፈወስን ልዩ ስጦታ አስገኘላት። በምንም ዓይነት ደዌ የተያዘ ሰውም ሆነ እንስሳ እንኳ ሳይቀር እጅዋን ጭና ስትጸልይለት ይድን ነበር ይባላል ።ንጉሥ ዜኖ በታላቂቱ ልጁ መጥፋት አዝኖ ሁለተኛዪቱን ልጁን አልጋ ወራሽ አድርጎ ሲኖር፡ እርስዋም ባደገኛ ሁኔታ ታማበት ውጪ ነፍስ፡ ግቢ ነፍስ ሆነ። በሀገሪቱ የሚገኝ ሐኪሙም ወጌሻውም ሊያድናት ባለ መቻሉ ልትሞትበት ስቃረብ የተገለጠለት መልካም አሳብ ያችን ልጅ ወደ ግብጽ በረሃ አባቶች ዘንድ ልኮ በጸሎት እንዲፈውሱለት መማፀን ነበር። በክብር ዘብ ታጅባ ተላከች። እንደደረሰችም ማኅበረ መነኮሳቱ ተሰብስበው ከጸለዩላት በኋላ ማረፊያ ቦታ ለማግኘት ወደ ጃንደረባው አባ ሂላሪያ ተላከች። አባ ሂላሪያም እጁን በራስዋ ላይ ችኖ ሲጸልይላት ወዲያውኑ ዳነች። ከሕመምዋ ተፈውሳ የዮሴፍ ወንድሞች "የዮሴፍን መሞት ለዮሴፍ ነገሩት' እንደተባለው፡ ስለእኅትዋ መጥፋት ለአባ ሂላርያ እየገለጠችለት ጥቂት ጊዜ አብራ ቆይታ ወደ ቍስጥንጥንያ ስትመለስ ንጉሠ ነገሥት ዜኖ ከደስታው ብዛት የተነሣ ወዲያውኑ ደብዳቤ ልኮ አባ ሂላሪያ ቤተ መንግሥቱን እንዲጐበኙለትና ቡራኬ እንዲሰጡት ጠየቀ። አበምኔቱም ደብዳቤውን ተቀብሎ አባ ሒላሪያ ወደ ቍስጥንጥንያ እንዲሄድ ፈቃደኛ መሆንና አለመሆኑ ሲጠየቅ "እዚያ ከሄድሁ በኋላ በዚያው እንድቀር ላለማድረግ ንጉሡ ቃል ይግባልንና እሄዳለሁ" አለ። _በዚህ ጉዳይ ላይ ስምምነት አድርገው አባ ሂላሪያ ወደ ቍስጥንጥንያ ተጓዘ። በቤተ መንግሥቱ የክብር እንግዳ ሆኖ ከ2- 3 ወር ከቆየ በኋላ ለመመለስ በሚዘጋጅበት ዋዜማ ንጉሡንና፡ ንግሥቲቱን ፡ ታማ ከተፈወሰችው ልጅ ጋር በግል ወደ ማረፊያ ክፍሉ ጠርቶ፡ "መንግሥታችሁ ዕንዕ ፡ ሰላም እንዲሆን በጸሎት እያሰብሁ አንድ ምሥጢር ልገልጥላችሁ እወዳለሁ። ምሥጢሩን ስገልትላችሁ ደግሞ*



www.ethiopianorthodox.org

*መደንገጥና ማዘን አይገባችሁም። ይኸውም በእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ የተፈጸመ ስለሆነ በሰብአዊ ፍላጎት የሚለወጥ አይደለም። እነሆ እኔ ቀድሞ አልጋ ወራሽ የነበርኩት የመጀመሪያ ልጃችሁ ልዕልት ሂላሪ ነኝ" ። ነገር ግን ከአሁን በኋላ የሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ አገልጋይ ስለሆንሁ እኔን እዚህ ለማስቀረት ማሰብ የለባችሁም። በውለታችን መሠረት እኔ ወደ ግብጽ በረሃ እመለሳለሁ። ስለመንግሥታችሁ ፅናት፡ ስለ ሀገሪቱ ሰላም በጸሎት ከማሰብ አልቆጠብም " ስትላቸው ሦስቱም በብርቱ ደንግጠው መሬት ላይ ወደቁ፡ የሚሉትን አጥተው ለረጅም ጊዜ በአርምሞ ቆዩ። በመጨረሻም በምክር አፅናንታቸው በፍቅርና በሰላም ተሰናብታቸው ስትሄድ "የእግዚአብሔር ፈቃድ ይሁን፡ እንኳንም ልጃችንን በሕይወት አገኘናት፡ ለሰማያዊ ንጉሥ ክርስቶስ አገልጋይ መሆንዋም ድንቅ ነው ፡ ብለው" የክብር አሸኛኘት አድርገውላት ተመለሱ። እነሆ ዛሬ በግብጽ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ቅድስት ሒላሪ ተብላ ትጠራለች። የቅዱስ ቃሉ ወዳጅ የነበረችውን ልዕልት ሒላሪን ባርኮ ጸጋውን አብዝቶላት ይህን ድንቅ ነገር ለመሥራት ያበበቃት የሕያው <u>አምላካችን ስሙ ለዘለዓለሙ የተመሰገነ ይሁን !</u>*

*_እነሆ በዚህ ዓይነት የሰማዕትነትን አክሊል ለመቀዳጀት ነገደተ ሮሜ የተባለላት ቅድስት ሶፍያን፡ አርሴማን፡ በሀገራችንም ክርስቶስ ሠምራና፡ ፀበለ ማርያምን የመሳሰሉ ሌሎችም ብዙ ቅዱሳት አንስት መኖራቸው ተጽፏል። )* """"""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""""

18-22 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹መንፈስ ያለበትን የነዌን ልጅ ኢያሱን በአንተ እግር ተተክቶ የሕዝቡ መሪ ይሆን ዘንድ እጅህን ጫንበትና በካህኑ በአልዓዛርና በማኅበሩም ፊት አቁመው››።

<u>፳፰ /28</u> ፡ <u>ስለ ዘወትር መሥዋዕት አቀራረብ</u> ይናገራል ፡ ይኸውም 1-8 በየቀኑ ሆለት ጠቦቶች፣ አንዱ በማለዳ፣ ሌላው በምሽት (በሠርክ) የሚቀርብ ይሁን። 9-10 ለሰንበት መሥዋዕት፣ አንድ ዓመት ያልሞላ ቸው ሁለት የበግ ጠቦቶች አቅርቡ። 11-15 በየወሩ መባቻ (መጀመሪያ ቀን) ነውር የሌለባቸውን ሁለት ወይፈኖችና አንድ አውራ በግ፣ አንድ ዓመት ያልሞላቸው ሁለት የበግ ጠቦቶች ታቀርባላችሁ። 16-25 በበዓለ-መጸለት( በፋሲካ-በዓል )፣ሰባት ቀን ሙሉ-እርሾ ያልነካውና ያልቦካ ቂጣ ትበላላችሁ።26-31 ለመከር በዓል፣ መጀመሪያ አዲስ እኽል ለእግዚአብሔር መባ አድርጋችሁ ታቀርባላችሁ። ቀጥሎ ሁለት ወይፈኖች፣ አንድ አውራ በግ አንዳንድ ዓመት የሆናቸው ሁለት ተባእት የበግ ጠቦቶች ታቀርባላችሁ።



<u>፳፱ /29</u> ፡ 1-6 <u>በኃጢአት ማስተሥረያ (Day of atonement) ቀን</u>፣ 12-40 የዳስ በዓል በሚከበርበት ጊዜ ስለሚቀርቡ ልዩ፡ ልዩ የመሥዋዕት ዓይነቶች ይናገራል። <u>*(ትርጓሜ*</u> *፡ በሐዲስ ኪዳን ዘመን ግን ፡ ይህ ሁሉ ተጠቃልሎ በክርስቶስ መሥዋዕትነት ተተክቷል። የእንስሳትና የእህል መሥዋዕት ሁሉ ቀርቷል ( ዳን 9፡ 27 ።*

<u>፴ /30</u> ፡1-16 <u>ስለ ስእለትና ብፅዓት አፈጻጸም</u> ፡ 6--8 አንዲት ወጣት ልጃገረድ ስእለትና ብፅዓት ስታደርግ፣ አባቱዋ ወይም ባሉዋ፣ ሰምቶ ሳይከለክል ዝም ካለ ይፀናል፤ ከተቃወመ ግን አይፀናም።

<u>፴፩ /31</u> ፡25-27 ለጦርነት የተሠለፈው ሠራዊት ምድያማውያንን ድል አድርጎ ሲመለስ የተደረገለትን አቀባበል ያስረዳል።ይኸውም 1-24 ሙሴ ዐሥራ ሁለት ሺህ ሰዎችን መርጦ፣የአልዓዛርን ልጅ ካህኑን ፊንሐስን መሪ አድርጎ አዘመተ። ክፉ የመከረባቸውን በለዓምንም እዚያው አግኝተው በሰይፍ ገደሉት። ከድል መልስ ከተካፈሉትም ምርኮ ከአምስት አንዱን እጅ ለእግዚአብሔር ሰጡ ።

<u>፴፪ /32</u>፡ <u>ከዮርዳኖስ ማዶ ያለውን ምሥራቃዊ ግዛት አወራረስ</u>፡ 1-38 ያን ግዛት እንዲወርሱ የተፈቀደላቸው የሮቤል፡ የጋድና የሮቤልና የጋድ ነገደ ሕዝብ እጅግ ብዙ የሆነ የከብት መንጋ ነበራቸው። ከዮርዳኖስ ማዶ ከጠላት በተወረሰው የገለዓድ ምድር የእነርሱ የርስት ድርሻ ሆኖ እዲሰጣቸው ሙሴን ጠየቁት። ሙሴም ይህን ርስት ከወረሱ በኋላ፣ በተለይም ዕድሜያቸው ከኻያ ዓመት በላይ የሆነ ወጣቶችና ጉልማሶቻቸው ከሌሎቹ የእስራኤል ነገዶች ጋር የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው፣ ሁሉም የርስት ድርሻቸውን ማግኘት እስከሚችሉ ድረስ አብረው መዋጋት እንዳለባቸው ቃል አስገብቶ ፈቀደላቸው። 39-42 እኩሌታው የምናሴ ነገድም፣ በሰሜን ገለዓድ የባሳንን ምድር ወረሰ፡ ጉዞ የሚገልጥ ሲሆን፣ ከቍ 50—56 የተጻፈው እስራኤል የዮርዳኖስን ወንዝ ከመሻገራቸው በፊት፣ ሙሴ የሰጣቸውን ትምህርታዊ መመሪያ ያስረዳል፡ ምዕራፍ 34፡ 1--29 የምድሪቱን ስፋትና ወሰን በመዘርዘር ይናገራል።

<u>፴፭</u> /35፡ 1-8 ሌዋውያን ካህናት ርስት የመካፈልና የመውረስ መብት ባይኖራቸው እንኳ፣ የቤት መሥሪያ ከተሞችና የከብት ማሰማሪያ መስኮች ተከልለው እንዲሰጡዋቸው የተፈቀደላቸው መሆኑን ያሳያል።

**የግድያ ወንጀል የፈጸሙ ሰዎች**፤ 9-34 ጉዳዩ በሕጉ መሠረት



www.ethiopianorthodox.org

ሞዕራፍ 33 ፡ 1-49 ከግብጽ እስከ ሞዓብ የተደረገውን በዳኝነት እስከ ወሰንላቸው ድረስ፣ ማንም ሰው በደም ፍላት በመግደል እንዳይበቀላቸው፣ ለጊዜው መጠለያ (መጠጊያ /መማፀኛ /የሚሆኑላቸው፣ ስድስት ከተሞች እንዲከለሉላቸው ተደረገ። የከተሞቹም ስም ዝርዝር በመጽሐፈ ኢያሱ 20፡ 1-9 ይገኛል። (**ትርጓሜ** ፡ በእነዚያ ስድስት ከተሞች የሚጠለሉ ነፍሰ-ገዳዮች ከቅጣት የሚድኑት ጉዳዩ በዳኝነት ሲታይ፣ ከወንጀል ሥራ ነጻ ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው። ውንጀለኞ ሂነው ከተገኑ ግን ከቅጣት ነጻ መሆን አይችሉም። ከመማፀኛው ቦታ ትወስደው እንደፈጸሙት ወንጀል መጠንን ትገቤ ው ቅጣት ሊፈጸምባቸው ይችላል። ልምሳሌ ኢዮአብ የተባለው የንጉሥ ዳዊት ሠራዊት አዛዥ ሁለት ታላላቅ ይቶር መኰንኖችን በግፍ ገድሎ ስለነበር በንጉሥ ዳዊት ኑዛዜ መሠረት ለፍርድ እየተፈለገ ሳለ ወደ መማፅእና ቦታ ሄዶ ምህረት ጠይቆ ነበር። ለፍርድ እንዲቀርብ ና ' ተብሎ ሲጠየቅ ከዚህ መማፀኛ ቦታ አልወታም ቦል ነበር። ነገር ግን የፈጸመው ወንጀል ምህረት ማስገኘት የማይችል ስለነበር በዚያው በመማፀናው ቦታ በሞት እንዲቀጣ ንጉሥ ሰሎሞን ትእዛዝ መስጠቱ ተጽፏል (1 ነገ 2። 26 -27 )።

<u>ወይከውን ምስማከ ለኵሉ ምድር</u>= ለምድር ሰዎች ሁሉ መጠጊያ /መማፀኛ ይሆናል-ተብሎ የተነገረለት"-ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስም ለሚያምኑበት ሁሉ መጠጊያና መጠለያ (ምስካየ ኅዙናን) ነው። ታዲያ ከኦሪታዊዉ መመሪያ በተለየ መልኩ በሃይማኖት ወደ ክርስቶስ የምትጠጋ ነፍስ በንስሐ ታድሳ ለዘለዓለም የርሱ መንግሥት ወራሽ ትሆናለች እንጂ፣ እንደ ኦሪታዊው ሕግ እንደገና ተመርምራ ወንጀለኛ /ኃጢተኛ ሆና ተገኘች ተብሎ ዳግም ሞት አይኖርባትም። የክርስቶስን ወንጌል ቃል የምትሰማ ነፍስ ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገረች ስለ ሆነች ከማናቸውም ክሥና ወቀሳ ነጻ ናት (ዮሐ 5፡ 24-29 + ሮሜ 8፡ 33 ።) ይህም በሀገራችን ባህልና ሥርዓት አንድ ሰው የነፍስ ግድያም ሆነ ወይም ሌላ ከባድ ወንጀል (Notorious crime ) ከፈጸመ በኋላ ወደ አንድ ገዳም ወይም ታላቅ ደብር ሄዶ ደወል ይመታና ምሕረት ሲጠይቅ ቢያንስ የቅጣት ቅናሽ ወይም እንደ ሁኔታው ጠቅላላ ምሕረትም ማግኘት ይችላል። ይህም ልምድ የተወሰደ ከዚሁ ታሪክ ነው።



# ኦሪት ዘዳግም

(መጽሐፈ ሙሴ ኃምሲት)

**መግቢያ** ፡ዘዳግም በድጋሚ የተጻፈና የተነገረ ማለት ነው።

ይኸውም ሙሴ በዘፀአት፡በዘሌዋውያንና በዘኁልቍ ከተጻፍፈው የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራና ከትእዛዛቱም አንዳንዱን እንደገና እያብራራ ለአፅኖዖተ ነገር- ለሕዝቡ ማጠናከሪያ ትምህርት የሰጠበት ስለሆነ ዘዳግም ተብሎ ተሰይሟል ማለት ነው። በዚህ መጽሐፍ የሚገኘው ወርቃዊ ቃል ሁሉ ተነብቦ የማይጠገብ ፡ የማይሰለች ፍጹም ታሪካዊና ትምህርታዊ ( Didactic ) ነው። ትርጉም ሰጪም ነው። ለምሳሌ ግዝረት የሚለውን ቃል በዚሁ መጽሐፍ 10፡ 16 የልባችሁን ሸለፈት ግዘሩ" ብሎ ተርጕሞታል። ነቢዩ ሙሴ በዚህ መጽሐፍ ሞዕራፍ 28 ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ የሚያስገኘውን በረከትና የሀገር ብልጽግና በሚያስደንቅ ሁኔታ ከገለጠ በኋላ፡ እንደገና ለእግዚአብሔር ቃል አለመታዘዝ በሚያስከትለው አደገኛ መዘዝ ሕዝቡ የሚደርስባቸውን ስደትና ውርደት፡ የሀገሪቱንም ጥፋት እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ በሆነ ትንቢታዊ ቃል ገልጦታል።

የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ በኑዛዜ ቃሉ ወደፊት የሚሆነውን ሁሉ ለሕዝቡ ሲገልጥ "እናንተ ክፉዎች ስልሆናችሁ ያስተማርኳችሁን የእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ረስታችህ እግዚአብሔርን ለባሰ ቍጣ ታነሣሡትና እኔ ከሞትሁ በኋላ ብርቱ መቅሠፍት እንደሚመጣባችሁ አውቃለሁ" ካለ በኋላ፡ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ተመልሳችሁ-ለቃሉ-ታዛዦች-ሆናችሁ-ብትገኙ -እግዚአብሔር- ክቶ አይጨክንባ_ችሁም፡ ምሕረት ያደርግላችሁና እስከ ምድር ዳርቻ ከተበተናችሁበት አገር ሁሉ ሰብስቦ በማምጣት በምድሪቱ እንደገና ያበለጽጋችኋል' የሚል የተስፋ ቃልም በትንቢት መልክ ተናግሯል። በዚሁ መጽሐፍ 34፡ 9- 12 እንደተጻፈ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ያወቀና በግብጽ ምድር በንጉሥ ፈሮዖንና በመኳንንቱም ፊት በምድሪቱ ላይ ምልክትና ልዩ፡ ልዩ ድንቅ ሥራዎችን ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ከልዩ ኃይል ጋር እንደላካውና በፀናች ክንድ በእስራኤል ፊት ሁሉን ነገር በሚያስደነግጥና በሚያስፈራ ግርማዊ ቃል እየተነጋረ ማሳመን የቻለ እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ በእስራኤል ከቶ ተነሥቶ አያውቅም ' በማለት ይደመድማል። ከሊቅ እስከ ደቂቅ ፡ ወጣት ሽማግሌና ጐልማሳ፡ ሴት ወንድ ተብሎ ሳይለይ-ሁሉም-ይህን-መጽሐፍ-በማንበብና-በማጥናት-ሊባረክበት ተጻፈ።



www.ethiopianorthodox.org

፩ /1 ፡ **ከሲና ተራራ ጥግ በመነሣት የተጀመረ ጉዞ**

6--8 ሙሴ ለሕዝቡ እንዲህ አለ፣ ‹‹በሲና ተራራ (ኮሬብ) ላይ በነበርንበት ጊዜ እግዚአብሔር ያዘዘን ቃል ይህ ነው፤ 'እነሆ፣ በዚህ ተራራ ላይ ለረጅም ጊዜ ቈይታችሁአል፤ ከአሁን በኋላ ግን፣ ሠፈራችሁን ነቅላችሁ ጉዞ ቀጥሉ፤ ወደ ከነዓን ምድር ሂዱ፣ ወደ ዮርዳኖስ ሸለቆ፣ ወደ ደጋውና ቆላ ወደ ሆነው ደቡባዊ አገር፣ወደ ሜድቴራኒያን ባሕር ጠረፍ እለፉ፣የሊባኖስን ተራሮች አቋርጣችሁ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ፣ ይህን ሁሉ ምድር እንድትወርሱ ለቀድሞ አባቶቻችሁ የተስፋ ቃል ሰጥቻለሁ››፡ ሴ ፍርድ የሚሰጡ ዳኞችን ሲሾም የሰጠው ትምህርታዊ መመሪያ፡

9--18 ‹‹በምትሰጡት የፍርድ ውሳኔ አድልዎ አታድርጉ፤ለድሃም ሆነ ለሀብታም፣ለትልቅም ሆነ ለትንሽ ዕኩል ፍረዱ፤ ፍርድ የእግዚአብሔር ነውና (2 ዜና መ 19፡ 5—7 ) ፡፡ 36 የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ለእኔ ፍጹም ታማኝ ሆኖ ስለ ተገኘና በሙሉ ልብ ስለ ተከተለኝ፣ ለጐበኘት በተላከ ጊዜ የረገጣትን ምድር ለእርሱ አወርሰዋለሁ›› ሲል እግዚአብሔር ተናግሮለታል፡፡

፪ /2 ፡ 5--6 እግዚአብሔር እንዲህ አለ፤‹‹ለዔሳውና ለዘርያዎቹ ርስት አድርጌ-በሰጠሁት-በሴይር ( በዔዶም) ስታልፉ፣ እነርሱን ለጦርነት አታነሣሡ፤ ከእነርሱ ቦታ የአንዲት ጫማ መርገጫ ያህል እንኳ መሬት አልሰጣችሁም፤ የምትፈልጉትን እህልና ውሃም ቢሆን በገንዘብ ግዙ››፡ 9 የሎጥ ዝርያዎች የሆኑትንም ሞአባውያንን አታስቸግሩዋቸው፤ የሴይርን ተራራ /ከተማ ለእነርሱ ርስት አድርጌ ሰጥቻለሁ (2 ዜና መ 20፡ 10-11) ፡፡ 36 እግዚአብሔር ልንወርሳቸው ፈቅዶልን እኛን ገድቦ ለመያዝ የሚችል ቅጽር ያላቸው ከተሞች አልተገኙም፡፡ ፫ /3 ፡11 ከአረፋውያን ወገን የሆነው ንጉሡ ኦግ፣ ከብረት የተሠራ ሆኖ ቁመቱ ዘጠኝ ክንድ የጎኑም ስፋት አራት ክንድ የሆነ አልጋ ነበረው፡ 23-28 እኔም፣ ‹‹ዮርዳኖስን ተሻግሬ እጅግ ለም የሆነችውን ምድረ ርስትና የሊባኖስን ተራሮች ለማየት ፍቀድልኝ›› ብዬ ጸለይሁ፡፡ እግዚአብሔር ግን፣ በእናንተ ምክንያት ተቈጥቶ ልመናዬን ማዳመጥ አልፈቀደም ፡፡

፬ /4 ፡ 3 በምሰጣችሁ ሕግ ላይ ምንም ነገር አትጨምሩ፤ ከእርሱ ምንም ነገር አታጉድሉ (ራእ 22፡18-19 )፡፡ 7--8 ወደ እርሱ ስንጸልይ አምላካችን እግዚአብሔር ወደ እኛ በሚቀርበን ዓይነት፣ በችግሩ ጊዜ ሲጠራው የሚቀርበው አምላክ ያለውሕዝብ፣ ከእኛ በቀር ማን ነው?



**ከባዕድ-አምልኮ ስለ መራቅ የተሰጠ ትእዛዝና ማስጠንቀቂያ ፡**

5-7 አምላኬ እግዚአብሔር እንዳዘዘኝ ሥርዓቱንና ፍርዱን ትጠብቁ ዘንድ አስተማርኋችሁ፤ ይህችን ሥርዓት ሰምተው፣ ‹‹በእውነት ይህ ታላቅ ሕዝብ ጠቢብና አስተዋይ ነው›› ብለው በሚያደንቁ አሕዛብ ፊት አስተዋዮች መሆናችሁ ተለክቶ የሚታወቅበት ምልክት ይህ ነውና፡፡ 15-16 እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በእሳት ነበልባል ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ፣ ምንም ዓይነት ቅርጽ (መልክ) አላያችሁም፡፡ ስለዚህም፣ ምንም ዓይነት ምስል (ቅርጽ) ሠርታችሁ እንዳታመልኩ ተጠንቀቁ፡፡ 20 እግዚአብሔር እናንተን ከአሕዛብ ሁሉ መካከል መርጦ በመለየት፣ የርስቱ ወራሾችና ልዩ ሕዝብ ትሆኑለት ዘንድ፣ ከግብጽ የጭቈና አገዛዝ ቀንበርና ከእሳት አውጥቷችኋልና፡፡ ምዕርፍ 5 ፡ 1-9 በተለይ ስለ ዐሥሩ ትእዛዛት በድጋሚ ማጠናከሪያ ትምህርት የሚሰጥ ነው፡፡ 10 ‹‹ለሚወዱኝና ትእዛዛቴን ለሚጠብቁ ሁሉ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ዘላለማዊ ፍቅሬን አሳያቸዋለሁ›› ይላል እግዚአብሔር፡፡

፮ /6 ፡ የመታዘዝን ጥቅም የሚያስረዳ ማስጠንቀቂያ ፤ 1-4 ‹‹እናንተና ልጆቻችሁ በምትወርሱአትና፣ ማርና ወተት በሚፈስባት ምድር ለረጅም ዘመን መኖር ትችሉ ዘንድ፣ አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ፣ በፍጹም ነፍሳችሁ፣ በፍጹም ኀይላችሁ፣ ውደዱ፣ ለቃሉም ታዛዦች ሁኑ››፡፡ ይህንም ብታደርጉ፣ ሁሉ ነገር ለመልካም ይሆንላችሁአል፡7--8 እነዚህንም ትእዛዛት -ለልጆቻችሁ -አስተምሩ ፡፡ በቤት-ትቀመጥም ሆነ፣ በመንገድ ስታልፍና ስታገድም ወይም በምታርፍበት ጊዜ ሁሉ፣ እነዚህን ትእዛዛት በማሰላሰል ዘወትር አስታውስ፡፡ማስታወሻ ይሆኑልህ ዘንድ፣በክንድህና በቤትህ ደጃፍ፣ በመቃኖችና በቅጽርበሮችህ ላይ ጻፋቸው፡፡አምላክህን እግዚአብሔርን አትፈታተን (ማቴ4፡7)፡፡13 አምላካችሁን እግዚአብሔርብቻ አምልኩ፤ መሐላችሁም በርሱ ስም ብቻ ይሁን፡፡

፯/7 ፡ **የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝብ፡** 7 እግዚአብሔር እናንተን መርጦ የወደደበት ምክንያት፣ በቍጥር ብዙዎች በመሆናችሁ አይደለም፤ እናንተ በምድር ላይ ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ በቍጥር ያነሣችሁ ናችሁና (ኢሳ 10፡ 22 ) ፡፡

፰ /8፡ **ያለፈውን ታሪክ የማስታወስ ትምህርት፡** ምላክህ እግዚአብሔር ዐርባ ዓመት ሙሉ በመከራ ውስጥ እንዳሳለፈህ አስታውስ ፡፡



www.ethiopianorthodox.org

በረኃብ እንድትፈተን ያደረገበትም ምክንያት፣ ሰው ከእግዚአብሔር አንደበት በሚወጣው ቃል እንጂ፣በእንጀራ-ብቻ መኖር እንደማይችል ሊያስተምርህ ፈልጎ ነው (ማቴ 4፡ 4 ) ።10 በልተህ ስትጠግብና ጠጥተህ ስትረካ፣ ይህችን ለም ምድር የሰጠህን አምላክህን እግዚአብሔርን አመስግን። ጥሩ ቤቶች ሠርተህ የከብቶችህና የበጎችህ መንጋ ርቢ ሲበዛልህ፣ ወርቅና ብር እንዲሁም ሌላው ሀብት ሁሉ ሲሞላልህ አይተህ፣ ልብህ እንዳይታበይና አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ ( መዝ 61፡ 10+ ጢሞ 6፡ 10 )

**፱ /9 ፡ ሁሉም ነገር በእግዚአብሔር ቸርነት የተፈጸመ ስለመሆኑ**

2--3 የዔናቅ ዘሮች ቁመተ-ረዳጅሞችና በማንም የማይደፈሩ መሆናቸውን ሰምታችኋል፤ ነገር ግን፣ እንደሚባላ እሳት የሆነ አምላካችሁ እግዚአብሔር በፊታችሁ ስለሚሄድ፣ እነርሱን ነቃቅሎ በማባረር በፍጥነት ለማጥፋት የሚያስችል ኀይል ይኖራችኋል። እግዚአብሔር ያችን ምድር የሚያወርሳችሁ እርሱዋን ለመውረስ የተገባችሁ ሆናችሁ አይደለም፣ እናንተ ገና ልባችሁ የደነደነ እልኸኛ ሕዝብ ናችሁና።

**፲ /10፡** 1-11 እንደ ገና ስለተሠሩት ጽላቶችና የነገደ ሌዊ ዝርያዎች ብቻ ለክህነት ስለ መመረጣቸው፣ ሙሴም በሲና ተራራ ላይ ስለ አቀረበው ጸሎት በዚህ ምዕራፍ በድጋሚ ተጽፎ ይገኛል።

**፲፩ /11፡** 1-15 እንደዚሁ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፣ የተስፋይቱን ምድር በረከትና የትእዛዛቱን ፍጹምነት የሚያስረዳ ሆኖ በምዕራ 6 ከተጻው ጋር ተቀራራቢነት ያለው ነው። 16 የልባችሁን ሸለፈት ግዘሩ፤ ከእንግዲህ ወዲህ፣ ልበ ደንዳኖችና እልኸኞች አትሁኑ ይላል ( ኤር 4፡ 4+ ቆላ 2፡ 11-12 ) ።21 ትእዛዛቱን ብትጠብቁ፣ እናንተና ልጆቻችሁ ለረጅም ዘመን ከምድር በላይ ያለው ሰማይ የሚኖረውን ያኸል መኖር ትችላላችሁ። 26-30 እነሆ እኔ ዛሬ፣ከበረከትና-ከመርገም-አንዱን-እንድትወርሱ-ምርጫ እሰጣችኋለሁ፤ በረከቱን በገሪዛን ተራራ ላይ፣ መርገሙን በጌባል ተራራ ላይ ታውጃላችሁ። እነዚህም ተራሮች ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተምእራብ በከነዓናውያን ግዛት የሚገኙ ናቸው።

**፲፪ /12፡ እግዚአብሔር የሚመለክበት ብቸኛ- ማእከላዊ ስፍራ፤**

5 በየነገዳችሁ ከምትኖሩበት ስፍራ ሁሉ መጥታችሁ ተሰብስባችሁ፣ በፊቱ የምትሰግዱበትን ቦታ ራሱ እግዚአብሔር ይመርጣል። 11 እኔ



ያዘዝሁአችሁንም መባ ሁሉ ወደዚያ ስፍራ ታመጣላችሁ።
21 እግዚአብሔር የመረጠው ያ ማእከላዊ ስፍራ ሩቅ ቢሆን ግን፣ በሚያስፈልጋችሁ ጊዜ ሁሉ፣እግዚአብሔር ከሰጣችሁ የከብትም ሆነ የበግ መንጋ መርጣችሁ፣እኔ ባዘዝኋችሁ መሠረት አርዳችሁ፣ሚዳቋና ዋሊያ እንደሚበሉ እንዲሁ ሥጋውን በቤት ትበሉታላችሁ። እናንተ ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር መስገድ የሚገባችሁ አሕዛብ ለባዕዳን አማልክቶቻቸው በሚሰግዱት ዓይነት መሆን አይገባውም። እነእርሱ ሲፈልጉ የገዛ ልጆቻቸውንም እንኳ፣ በመሠዊያ ላይ በእሳት ያሳልድፋሉ /ያቃጥላሉና።

**፲፫/13** ፡1-4 በመካከላችሁ ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ተነሥቶ፣ «ምልክት ወይም ታምራት አሳያለሁ» ቢልህና እንደ ነገረህ ምልክቱም ሆነ ታምራቱ ሲፈጸም ብታይ እንኳ፣ የዚያን ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቃል አትስማ፤ አምላካችሁን እግዚአብሔርን ብቻ በፍጹም ልባችሁ ተከተሉ፤ ቃሉን ስሙ። በዚህ ነገር፣ የእናትህ ልጅ ወንድምህ ወይም ልጆችህና ሚስትህም ብትሆን፣ የሚያስትህን ማንንም ሰው አትከተል።

**፲፬/14 ፡ በሞት አደጋ ጊዜ የተከለከለ አጉል የለቅሶ ልማድ፤**

1--2 እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ፤ ስለዚህ፣ ለሞተ ሰው በምታዝኑበት ጊዜ፣ ሌሎች አረማውያን ሕዝቦች በሚያደርጉት ዓይነት ፊታችሁን አትንጩ፤ ጠጉራችሁን አትላጩ። እናንተ ከሌሎች ሕዝቦች መካከል ለአምላካችሁ ለእግዚአብሔር የተመረጣችሁ ልዩ ሕዝብ ናችሁ። 3-21፡በዚህ ክፍል ያለው ቃል በዘሌ ምዕራፍ 11 ስለሚበሉና ስለማይበሉ እንስሳት፣አራዊትና አዕዋፈ-ሰማይ የተጻፈውን በድጋሚ የሚያሳይ ነው።

**፲፭ /15** ፡ 3 ለውጭ አገር ባዕዳን (ሰዎች)-ያበደራችሁትን-ገንዘብ-መልሳችሁ መውሰድ ትችላላችሁ፤ እስራኤላውያን ለሆኑት ወገኖቻችሁ ያበደራችሁትን ግን፣ መልሳችሁ አትውሰዱ። ይህን ብታደርጉ አምላካችሁ እግዚአብሔር በሚሰጣችሁ ምድር ስትኖሩ ይባርካችኋል፤ ከእናንተ ወገን ድኽ ሆኖ የሚኖር አይገኝም። እናንተ በብዙ አሕዛብ ላይ የበላይነት ይኖራችኋል፤በእናንተ ላይ የሚሠለጥንባችሁ አይኖርም።

**፲፮ /16** ፡ ይህ በጠቅላላ፣ በተለይ ስለ አሪታዊው ፋሲካ፣ የእሸትና የመከር ክታች በዓላት አከባበር በዘሌ 23፥15-43 የተጻፈውን በድጋሚ የሚያሳይ ነው።



www.ethiopianorthodox.org

፲7/17፡ 1 ነውር ያለበትን እንስሳ መሥዋዕት አድርጋችሁ አታቅርቡ። 12 ለዳኛው ወይም በአገልግሎት ላይ ለሚገኘው ካህን ባለመታዘዝ፣ የድፍረት ቃል የሚናገር ቢኖር በሞት ይቀጣ።

## ስለ ንጉሥ አመራረጥ የተሰጠ ትምህርታዊ መመሪያ፡

15-19 ንጉሥ ለማንገሥ ስትፈልጉ፣ ከእግዚአብሔር የተመረጠላችሁ መሆኑን አረጋግጡ። መመረጥ ያለበት ከራሳችሁ ተወላጆች ብቻ ነው። እርሱም ለሠራዊቱ ብዙ ፈረሶች የሚኖሩት መሆን የለበትም። ብዙ ሚስቶች እንዲኖሩትም አያስፈልግም። የሚስቶች ብዛት እግዚአብሔርን ከመከተል እንዲገታ ያደርገዋልና ( 1 ነገ 11 ፡1-4፤ ነህምያ 13፡ 26 ) ። 17 የወርቅና የብር ብዛት አያስፈልገውም። ይልቅስ በሚነግሥበት ጊዜ፣ የዚህ የሕግ መጽሐፍ ቅጂ እንዲኖረው አድርጎ፣ በዘመኑ ሁሉ ያንብበው።

፲፰ /18፡ ከአረማውያን አስጸያፊ ልማድ ተጠብቆ መኖር እንደሚገባ፤ ያስረዳል።10-13 ልጆቻችሁን የሚቃጠል መሥዋዕት አድርጋችሁ አታቅርቡ። የሟርትን፤ የሞራ ገላጭነትን፤ እድልን የመናገርና የሚከተል ከመካከላችሁ ተለይቶ ይጥፋ። መናፍስትን የሚጠራ ጠንቋይ፣ ሙታንንም ጠሪ በእናንተ ዘንድ አይኑር። እግዚአብሔር ከእናንተ በፊት፣ በዚህች ምድር ሲኖሩ፣ ይህን ሁሉ ርኩሰት እንድትሞላ ያደረጓትን አረማውያን ሕዝብ ነቃቅሎ ለማጥፋት የወሰነበትም ምክንያት ይኸው ነውና፤ በእግዚአብሔር ፊት ከዚህ-አስነዋሪ-ተግባር-የነጻችሁ-ሁኑ።17-19፡-ከዚህም-በኋላ፣ሙሴ-ለሕዝቡ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ ‹‹**አምላካችሁ እግዚአብሔር ከወገኖቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ሌላ ነቢይ ያስነሣላችኋል።** እግዚአብሔር ስለዚያ ነቢይ አነሣሥ እንዲህ ብሏል፤ ‹እርሱ የሚናገረውን ቃል እኔ እሰጠዋለሁ፡ቃሉን የማትሰማ ነፍስ ከሕዝቡዋ ተለይታ ትጥፋ.... ( የሐዋ ሥ 3:23) ።

፲፱ /19 ፡ 14 ከቀድሞ ጀምሮ ጸንቶ የኖረውን ድንበር አታፍርስ" ይላል **(ዘዳግ 27፡17+ ምሳ 22፡ 28+ ሆሴ 5፡ 10 ) ።**

### ስለሐሰት መስካሪዎች የተሰጠ ትምህርታዊ ማስጠንቀቂያ፤

15 አንድ ሰው ወንጀለኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ቢያንስ ሁለት ምስክሮች ያስፈልጋሉ። 16 አንድ ሰው እስራኤላዊ በሆነ ወንድሙ ላይ የሐሰት ክሥ መሥርቶ ቢገኝ፣ለተከሳሹ የሚገባውን ቅጣት እርሱ ራሱ ይቀበል።



## ፳ /20 ፡ ስለጦርነት-የተሰጠ-መመሪያ፡

1-4 ጠላቶቻችሁን ለመውጋት በምትዘምቱበት ጊዜ፣ የሠረገላዎችን፣ የፈረሶችንና የሠራዊትን ብዛት አይታችሁ አትፍሩ፤ እግዚአብሔር ራሱ ስለ እናንተ ይዋጋልና። ጦርነት ከመጀመራችሁ በፊት፣ ካህኑ ወደ ሠራዊቱ ቀርቦ እንዲህ ይበል፤ ‹‹የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ ስሙ፤ ከጠላቶቻችሁ የተነሣ አትፍሩ፤ ወኔአችሁ አይቀዝቅዝ አትሸበሩ፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሄዳል፤ ድልንም ይሰጣችኋልና›› ። 10-12 በአንዲት ከተማ ላይ አደጋ ለመጣል በምትዘጋጁበት ጊዜ፣ በመጀመሪያ ሕዝቡዋ በሰላም እጃቸውን እንዲሰጡ ጠይቁ፣እምቢ ካሉ ግን፣ ከተማይቱን ክበቡ፡19 ለረጅም ጊዜ ከበባ ስታደርጉ ፍሬ የሚሰጡ ዛፎችን አትቍረጡ፤ ዛፍ የሰው ዘር ሁሉ ምግብ ነውና።

፳፩/21፡ 22 የተጻፈው አንድ ሰው በፈጸመው ወንጀል በእንጨት ላይ ተሰቅሎ ቢሞት፣ በተሰቀለበት እንጨት ላይ-እንዳያድር በዕለቱ አውርደህ ቅበረው። ‹‹በእንጨት ላይ ተሰቅሎ የሞተ ርጉም ነውና›› ( ገላ 3፡ 13 )።

፳፪ /22 ፡ ልዩ፡ ልዩ ሕግጋት (ትእዛዛት) ፤ 1 የወገንህ ንብረት የሆነ ከብት ባዝኖ ብታገኝ፣ ለባለቤቱ መልስ። 4 በሬ ወይም አህያ መንገድ ላይ ደክሞ (ወድቆ) ብታገኝ፣ እንዲሄድ እርዳው፡6 እንቍላሉዋን ታቅፋ የተገኘችውን ወፍ ነጥለህ አትውሰድ። እናቲቱን ትተህ እንቍላሉዋን ውሰድ። 24 አንዲት ድንግል (ልጃገረድ) ሰው ሊሰማ በሚችልበት ከተማ ውስጥ እያለች በማስገደድ ክብረ ንጽሕናዋ ቢደፈር፣ እርዳታ ለማግኘት ድምፅዋን ካሰማች፣ ከደፈራት ሰው ጋር በሞት ከመቀጣት ነጻ ትሆናለች ( 2 ሳሙ 13፡ 5- 18 ) ።

፳፫/23፡ አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ሕዝብ የሚለይበት ሁኔታ፤

1 ብልቱ ተቀጥቅጦ ጃንደረባ የሆነ፣ ወይም ዲቃላ ሆኖ የተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ማኅበር (ጉባኤ) ገብቶ አይቈጠር። 3-10 አሞናዊና ሞዓባዊ የዐነ ሰው ሁሉ፣ እስከ ዐሥር ትውልድ ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ አይግባ። ኤዶማውያንና ግብጻውያን ግን፣ ከሦስት ትውልድ በኋላ፣ ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ ገብተው ይቈጠሩ። 12-13 የምትጸዳዱበትን ስፍራ ከመኖሪያ ሠፈር ውጭ አዘጋጁ፤ ከሰውነትህ የሚወጣውን ዓይነ-ምድር በተቈፈረ ጉድጓድ ውስጥ አፈር አልብሰው። 17--18 የሴት ወይም የወንድ ጋለሞታ በምድርህ



www.ethiopianorthodox.org

እንዲኖሩ አታድርግ። በግልሙትና የተገኘ ገንዘብ፣ መባ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ቤት አይግባ። 19-20 ወለድ ( አራጣ ) መቀብል የሚቻልህ ከውጭ አገር ተወላጅ-እንጂ፣ ከእስራኤላዊ ወገንህ መሆን አይገባውም። 21-23 ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስእለት ወይም ብፅዓት በምታደርግበት ጊዜ፣ ለመስጠት ቃል የገባህበትን ስእለት አታስቀር፤ እግዚአብሔር ከአንደበትህ የወጣውን ቃል እንድትፈጽም ይፈልጋል፤ ባትፈጽመው ደግሞ ኃጢአት ይሆንብሃል፤ ቀድሞውኑ ባትሳል ግን ግዴታ አይኖርብህም (መክ 5 :4 -3 ) ። 24--25 በባልንጀራህ ሰብል መካከል ስታልፍ፣ በእጅህ ቀጥፈህ (ቈርጠህ) እሸት መብላት ትችላለህ፤ ነገር ግን ሰብሉን በማጭድ አጭደህ አትውሰድ።

## ፳፬ /24 : ስለ መፋታትና ስለ ዳግም ጋብቻ የተሰጠ ትምህርት

1-4 አንድ ሰው፣ ያገባትን ሚስት የሚፈታበት በቂ ምክንያት-ሲገኝ፣ የተፈታችበትን ምክንያት የሚገልጥ የፍቺ ደብዳቤ ሰጥቶ ያሰናብታት። 5 አዲስ ሚስት ያገባ ሰው እስከ አንድ ዓመት ድረስ፣ ከውትድርና አገልግሎት ነጻ ይሁን። 15 የሀገር ተወላጅ የሆነ ድኻ፣ በየቀኑ የሠራበትን ዋጋ ፀሐይ ከመጥለቅዋ በፊት ስጠው፤ ሳትከፍለው-ቀርተህ ወደ እግዚአብሔር ቢጮኽ ግን በደል ይሆንብሃል (ያዕ 5፡ 4 ) ። 16 ልጆች በሠሩት- በደል ወላጆች ወይም ወላጆች በፈጸሙት ጥፋ ልጆች አይጠየ_ ቁበትም (ሕዝ 18፡ 20) ።

፳፭ /25 : 1-3 በደል የፈጸመ ሰው በግርፋት በሚቀጣበት ጊዜ፣ ግርፋቱ ከአርባ ጅራፍ መብለጥ የለበትም። 4 እህልህን በምታበራይበት ጊዜ፣ የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር (1ቆሮ 9፡ 9 ) ። የዋርሳ ሕግ፤ 5-10 በአንድ ርስት ላይ ከሚኖሩ ሁለት ወንድማማች መካከል አንዱ ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፣ የእርሱ ተከታይ የሆነው ወንድሙ ሚስቱን በዋርሳነት ይረከብ። በመጀመሪያ የሚወለደውም ልጅ በሟች ወንድሙ ስም ይጠራ። በሕይወት ያለው ወንድሙ፣ ይህን ለማድረግ ፈቃደኛ ኾኖ ባይገኝ፣ የሟቹ ሚስት ወደ ከተማይቱ ፈራጆች ቀርባ ታመልክት። እምቢ ማለቱ ሲታወቅም፣ ከእግሩ ጫማዎች አንዱን ታውልቅ፤ ምራቁአን በፊቱ ላይ-ትትፋ፤ ‹‹ለወንድሙ ዘር ማቆምን እምቢ ለሚል አይነት አሳፋሪ ነገር ሊፈጸሙበት ይገባል›› ትበል። የዚያ ሰው ቤተሰብ በእስራኤል፣ ‹‹ጫማው የተፈታበት ሰው ቤተሰብ›› እየተባለ በመነቀፍ ሲጠራ ይኑር (ሩት 4 ) ። 16 እውነተኛና ታማኝ የሆነ ሚዛንና መስፈሪያ ይኑርህ፤ (ዘሌ



25፡ 35+ ምሳሌ 11 :1-20 + 10፡ 23 ) ። 17-19 አማሌቃውያንን ከገጸ-ምድር ደምስስ መተላለፊያ መንገድ\ ከልክለው እስራኤላውያንን ገድለዋልና ›› (1 ሳሙ 15፡ 1-3 ) ፡

ምዕራፍ 26፡ 12 በየሦስተኛው ዓመት ከምትሰበስበው መከር ከሀሥር አንዱን እጅ (ዐሥራት) ለመጻተኞች (ለስደተኞች)፣ ለሙት ልጆችና፣ ለመበለቶች (ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች) ትሰጣለህ። 18 እግዚአብሔር የሰጠህን ሕግ ለመጠበቅና ትእዛዛቱንም ለመፈጸም ቃል መግባትህን አትርሳ፤ ይህን ብታደርግ እግዚአብሔር ከምድር አሕዛብ ሁሉ በላይ ከፍ፡ ከፍ ያደርግሃል።

## ፳፯ /27 : መርገመ-ጌባልና በረከተ-ገሪዛን፤

11-26 ገሪዛንና ጌባል ተብለው በሚጠሩት ተራሮች ላይ ሕዝቡ በቡድን ተከፍለው፣ማዶ-ለማዶ በመቆምና በመቀባበል ከሚያሰሙት በረከትና መርገምም ለዓይነት (ብንጠቅስ) እንዲህ-ይላል፡በጌባል ተራራ ላይ የቆመው ቡድን፣ ‹አባቱን ወይም እናቱን በመናቅ የሚያዋርድ ርጉም ይሁን›› ሲል፣ በገሪዛን ተራራ ላይ የቆመው ሕዝብ፣ ‹‹አሜን›› በማለት ይመልሳል። በገሪዛን ተራራ ላይም የቈመው ሕዝብ፣ የምርቃት ቃል ሲናገር፣ ፀጌባል ተራራ ላይ ያለው ቡድን ‹‹አሜን›› ይላል። በዚሁ ዓይነት ባዕዳን-አማልክትን የሚከተል፣ የጐረቤቱን ድንበር የሚያፈርስ፤ ዓይነ ስውሩን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ የሚመራ፣ ስደተኛውን የሚያንገላታ ፣ ‹‹ርጉም ይሁን›› ሲባል መልሱ ‹‹አሜን›› ።

## ፳፰ /28 : ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ የሚገኝ በረከት፡

14 ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ብትታዘዝና እኔ የምሰጥህን ሕግጋት ሁሉ በፍጹም ታማኝነት ብትጠብቅ፣ በገጸ-ምድር ከሚኖሩ አሕዛብ ሁሉ በላይ ከፍ- ከፍ አደርግሃልትሁ ከዚህ- ለሚከተሉትም-በረከቶች ሁሉ ባለቤት ትሆናለህ፤ የምድርህ ፍሬ፣ የላምሆና የበሆ ዕቃህ ቡሩክ ይሆናል። አንተ በመግባትህና በመውጣትህ (ባወጣጥህና ባገባብህ) ሁሩክ ትሆናለህ። እግዚአብሔር በአንተ ላይ የሚነሡትን፣ ጠላቶችህን ሁሉ በፊትህ የተመቱና የተዋረዱ ያደርጋቸዋል፤ በአንድ መንገድ ተሦ ልፈው ይመጡብሃል፤ ነገር ግን፣ በሰባት መንገድ ተበታትነው ከፊትህ ይሸሻሉ። ለቃሉ ታዛኘር ብትሆን ብዙ ልጆችን፣ ብዙ የቀንድ ከብትና የተትረፈረፈ የእርሻ ሰብል ይሰጥሃል።

_በረከቱን በአንተ ላይ፣በጐተራህና በእጅህ ሥራ ላይ ሁሉ እንዲወርድ ያዝዛል።እግዚአብሔር ለራሱ የተቀደሰ ቡሩክ ሕዝብ አድርጎ ያቆምሃል፡



www.ethiopianorthodox.org

የምድር አሕዛብም ሁሉ የእግዚአብሔር ስም በአንተ ላይ እንደ ተጠራ ሲያዩ ይፈሩሃል። እግዚአብሔር በጎነቱን ሁሉ ያበዛልሃል። ለምድሪቱ በወቅቱ ዝናምን ይሰጣል። ለብዙ አሕዛብ ታበድራለህ እንጂ፣ አንተ ከማንም ተበዳሪ አትሆንም። እግኢብሔር የሁሉ ራስ (መሪ) ያደርግሃል፤ የማንም ጅራት አትሆንም፤ ሁል ጊዜ የበላይ እንጂ የበታች አትሆንም።

## ለእግዚአብሔር ቃል አለመታዘዝ የሚያስከትለው መዘዝ ፡

15--19 ነገር ግን፣ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝን እምቢ ብትልና ብታምፅ፣ሕጉንና ሥርዓቱንም ሁሉ ለመጠበቅ ታማኝ ሆነህ ባትገኝ፣ግን በምትኖርበት ከተማና በእርሻህ ቦታ ሁሉ፣ ርጉም ትሆናለህ፣ እንቅብህና የቡሆ ዕቃህ ሁሉ ባዶ ሆናል። የምድርህ ፍሬ፣ የላምህና የበግህ ርቢ መቅኖ-ቢስ ይሆናል። በመውጣትህና በመግባትህ ርጉም ትሆናለህ። 20-24 እግዚአብሔር በቸነፈርና በክሳት፣ በንዳድና በጥብሳት፣ በትኩሳትና በድርቅ፣ በዋግና በአረማሞ ይመታሃል። ከራስህ በላይ ሰማይ እንደ ነሐስ፣ ከእግርህም በታች ምድሪቱ እንደ ብረት ትሆንብሃለች። 25-26 እግዚአብሔር በጠላቶችህ ፊት የተመታህ ያደርግሃል፤ በአንድ መንገድ ተሠልፈህ ትዘምትባቸዋለህ፤ በሰባት መንገድ ተበታትነህ ከፊታቸው ትሸሻለህ፡የምድር መንግሥታትም ሁሉ የሚደርስብህን ጥፋት ሁሉ አይተው ይሸበራሉ። ሥጋህን የሰማይ ወፎችና አራዊት ይበሉታል 26-29-እግዚአብሔር በግብፃውያን ላይ እንዳደረገው፣ የእባጭ በሽታ ይልክብሃል፤ ሰውነትህን ሁሉ፣ በማይፈወስ ቍስል እንዲበላሽ ያደርገዋል፤ በሚያሳክክ ቋቍቻና በችፌ ይመታሃል። አእምሮህን በሚያስት እብደት፣ በእውርነትም የተመታህ ትሆናለህ። ዘወትር ምዝበራና ጭቈና ይደርስብሃል።

30--31 ሚስት አጭተህ ታገባለህ፤ ሌላ ሰው ይወስዳታል። ቤት ትሠራለህ አንተ አትኖርበትም። ወይን ትተክላለህ ፍሬውን ግን አትበላም። የቀንበር በሬህ በፊትህ ይታረዳል፤ ሥጋውን አትበላም። አህያህ በግድ ተነጥቆ ይወሰዳል፤ ወደ አንተም አይመለስም። ያሳብኸው በግ ለጠላት ይሰጣል፤ ከዚህ ሁሉ መከራ የሚያድንህ አይኖርም።32-50 ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ትወልዳለህ፤ ነገር ግን ተማርከው ሲሄዱ ታያለህ። ዛፍህንና የምድርህ ፍሬ ሁሉ ኩብኩባ ይበላዋል።ለምድር አሕዛብ ሁሉ መገረሚያ ትሆናለህ። መጻተኞች በአንተ ላይ ይሠለጥናሉ፤ እነርሱም ለአንተ አበዳሪዎች ይሆናሉ፤ ራስ የነበርከው ጅራት ትሆናለህ። ጠላቶችህ በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር ይጭናሉ፤ ለአዳኒ ወጣቶች ልጆችህ የማይራሩ ጨካኞች



ናቸው፤ እነርሱም በዐራቱ ማእዘን ከበው ያስጨንቁሃል። 54-55 ሁል ጊዜ በቅምጥልነት በመለሳለስ ይኖር የነበረ ክቡር ሰው፣ በዚያች የከበባ ጊዜ፣ የገዛ ልጆቹን ሥጋ ለመብላት ይገደዳል። ከዚያ ሥጋ ለልጆቹና ለሚስቱ እንኳ አያቀምስም። 56-57 በተድላ በደስታ ተለሳልሳ የምትኖር ከመሆንዋ የተነሣ፣ ምድርን ለመርገጥ እንኳ ትጸየፍ የነበረች እመቤት፣ የወለደችውን ልጅና የእንግዴ ልጅዋን ጭምር ተደብቃ ስትበላ፣ ለምትወደው ባልዋና ለልጆችዋም አታቀምስም። 63 እግዚአብሔር እናንተን ለማበልጸግና ቍጥራችሁን ለማብዛት የወደዳችሁን ያህል፣ እንደገና እናንተን በማጥፋት ደስ ይለዋል፡ 64-68 ስለዚህ፣ በመላው ዓለም ጽንፍ እስከ ጽንፍ በሚኖሩ አሕዛብ መካከል ይበትናችኋል፤ በዚያ ከእንጨትና ከድንጋይ ለተሠሩ ባዕዳን-አማልክት ለመስገድት ገደዳላችሁ፤ በጭንቀት የተሞላ አእምሮ፣በናፍቆት የደከመ ዓይን፣ በተስፋ መቍረጥ የተሞላ ልብ ይኖራችኋል። ሕይወታችሁ ሁል-ጊዜ ለአደጋ የተጋለጠ ይሆናል። ከዚህም የተነሣ፣ራሳችሁን ለጠላት ባሪያ አድርጋችሁ፡ለመሸጥ ትመኛላችሁ፤ ነገር ግን፣ ለመግዛት የሚፈልጋችሁ ታጣላችሁ።

**፳፱ /29 ፡ ማጠናከሪያ ትእዛዝ** ፡ -4--5 ብዙ ድንቅ ሥራዎችን ሁሉ-አይታችኋል፤-ነገር-ግን፣-እግዚአብሔር-እስከዚህ-ቀን-ድረስ ያለፋችሁ በትን ሁኔታ ሁሉ የምታዩበትን ዓይነ -ልቡና፣ የምትሰሙበትን ጆሮ፣ የምታስተውሉበትን ብሩህ አእምሮ ገና አልሰጣችሁም። ዐርባ ዓመት ሙሉ በምድረ በዳ መራኋችሁ፤ ልብሳችሁ አላለቀም፤ ጫማችሁም አልቆ አልወደቀም።

19-23 ዛሬ በእናንተ መካከል ሆኖ ይህን ጥብቅ ትእዛዝ የሚሰማ ሰው ሁሉ፣ ልቡን በማደንደን ራሱ በመረጠው መንገድ የሚሄድ ከሆነ፣ ‹‹ሁሉም ነገር ለመልካም ይሆንልኛል›› ብሎ በከንቱ ራሱን አያታል። በዚህ ነገር ተጠንቀቁ፤ እንደዚህ ያለው ሰው ለራሱ ብቻ ሳይሆን ደጋጎችም፣ ክፉዎችም ለሆናችሁት ሁሉ፣ የጥፋት ምክንያት መሆን ይችላል። በዚህ መጽሐፍ የተጻፉት መቅሠፍቶች ሁሉ እንዴት እንደሚፈጸሙ ተተኪው ትውልድ በዓይኑ ያያል ። የእርሻ መሬቶች በዲንና በጨው ተሸፍነው፣ ምንም ጥቅም የማይሰጡ ፍጹም ጠፍ መሆናቸውን ይመለከታል። በእነርሱ ላይ አትክልትና አዝርዕት ይቅርና አረም እንኳ አይበቅልባቸውም። ምድራችሁ፣ በብርቱ-ቍጣው-እግዚአብሔር እንደመሰላቸው እንደ ሰዶምና እንደ ገሞራ፣ እንደ



www.ethiopianorthodox.org

አድማህና እንደ ሰቦይም ሆና ትቀራለች። 29 ምስጢር የሆነው ነገር ሁሉ፥ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፥ የተገለጠውና በዚህ ሕግ የተጻፉት ቃሎች ሁሉ ግን፣ እንፈጽማቸው ዘንድ ለእኛና ለልጆቻችን የተሰጡና ለዘለዓለም ጸንተው የሚኖሩ ናቸው።

፴ /30 : <u>የሞትና የሕይወት ምርጫ</u> 1-3 እናንተና ዘሮቻችሁ ወደ እግዚአብሔር ብትመለሱና ለእግዚአብሔር ሕግ ታዛገሮች ሆናችሁ ብትገኙ፣ እግዚአብሔር ምሕረት ያደርግላችኂል፤በአሕዛብ መካከል እናንተን ከበተነበት ስፍራ ሁሉ ሰብስቦ በማምጣት፣ እንደገና በምድሪቱ ያበለጽጋችሁአል። 6 አምላካችሁ እግዚአብሔር ለእናንተና ለልጆቻችሁ ታዛዥ ልብ ይሰጣል። 14 ቃሉ ለእናንተ ቅርብ ስለ ሆነ፣ እናንተ በልባችሁ የምታውቁትና በምትፈልጉ ጊዜ በአንደበታችሁ የምትናገሩት ነው። ስለዚህ፣ ልትፈጽሙት ይቻላችኂል። 15-16 እነሆ፣ ዛሬ በመልካምና በክፉ ነገር እንዲሁም በሕይወትና በሞት መካከል ምርጫ እሰጣችሁአለሁ።የእግዚአብሔርን_ትእዛዝ_ብትፈጽሙ ትበለጽጋላችሁ፡ የብዙም ሕዝብ መንግሥት ትሆናላችሁ። 19-20 እነሆ፣ በሕይወትና በሞት መካከል ምርጫ እሰጣችሁአለሁ፤ ስለ ምታደርጉት ምርጫ ሰማይንና ምድርን በእናንተ ላይ ምስክር አድርጌ እቈጥራለሁ። ስለዚህ፣ እናንተና ዝርያዎቻችሁ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጡ። አምላካችሁን እግዚአብሔርን ውደዱ፤ ለእርም ታማኞችና ታዛገሮች ሁኑ፡

፴፩ /31 : <u>በኋለኛው ዘመን የሚመጣ ጥፋት፡</u> 24 ሙሴ ምንም ሳያስቀር፣ በጥንቃቄ የእግዚአብሔርን ቃል በመጽሐፍ ጽፎ ከፈጸመ በኋላ፣ የእግዚአብሔርን የቃል-ኪዳን ታቦት ለማገልገል ለተሾሙት ሌዋውያን ካህናት እንዲህ አላቸው፤ ‹‹በእናንተ ላይ ምስክር እንዲሆን ይህን መጽሐፍ ወስዳችሁ በቃል-ኪዳኑ ታቦት አጠገብ አኑሩት፣ በሕዝቡ ላይ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ በዚያ ይኖራል። እኔ ከሞትሁ በኋላ፣ እናንተ ክፉዎች- ስለ -ሆናችሁ፣ ያስተማርኂችሁን -ቃል-ሁሉ- እንደምትተዉና- እግዚአብሔርን- ለቍጣ- አነሣስታችሁ፣ ያልጠበቃችሁት- ክፉ--ነገር- /ብርቱ- መቅሠፍ እንደሚመባችሁ አውቃለሁ››።

፴፪ /32 : <u>የሙሴ መዝሙር፡</u> 1--2 ሰማያትና ምድርም ሆይ፣ ቃሌን አድምጡ። የዝናም ጠብታ ከሰማይ ወርዶ ከመስክ እንደሚስማማ፣ የእኔም ትምህርትና ቃሌ እንደዚሁ፣ በአዲስ ተክል ላይ እንደሚዘንም (ካፊያ)፣ ዝግ ብሎም በለምለም ሣር ላይ እንደሚወርድ ዝናም ነው።13 እግዚአብሔር በድንጋያማ መሬት ( በጨንጫ ) ላይ የወይራ ዛፎች



ፍሬ ማፍራት እንዲችሉ አደረገላቸው)። 5 ዩሹሩን ( የእግዚአብሔር ሕዝብ ) እጅግ ባለ- ጸጋ ሆነ፤ በዚያው መጠን ግን ዓመፀኞች ሆኑብኝ። 47 ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ትእዛዝ ሁሉ ለሕዝቡ አስተምሮ ሲጨርስ፣ እንዲህ አለ፤ ‹‹ዛሬ የሰጠኂችሁን ትእዛዝ ሁሉ ለመፈጸም የተዘጋጃችሁ ሁኑ፤ ለልጆቻችሁ- አስተምሩ። ይህ-ትምህርት-የሕይወታችሁ-መሠረት ነው››፡

፴፫ /33፡ ሙሴ የእስራኤልን ነገድ ሁሉ የባረከበት ቅኔዊ ትንቢት 2- 7 እግዚአብሔር ከሲና ተራራ መጣ፤ በዔዶም ላይ እንደ ፀሐይ ወጣ። ከፋራንም ተራራ ለሕዝቡ አበራ። አእላፍ መላእክት ከእርሱ ጋር ናቸው። ሙሴ የሰጠንን ሕግ እንጠብቃለን፤ ይህ ሕግ ለሕዝባችን እጅግ የከበረ ታላቅ ውርስ ነውና። 6 ሙሴ በተለይ ስለ ሮቤል እንዲህ አለ፣ ‹‹ሮቤል በሕይወት ይኑር፣ አይሙት። የሕዝቡ ቍጥር አነስተኛ አይሁን፡

8 እግዚአብሔር ሆይ ! ለሌዋውያን በኡሪምና በቱሚም አማካይነት ፈቃድህን ግለጥላቸው። የእስራኤል ሕዝብ ሆይ፣ በግርማ ተሞልቶ፣ ሰማይን ሰንጥቆ በማለፍ፣ በደመና ተቀምጦ አንተን ለመርዳት የሚመጣ፣ እግዚአብሔርን የሚመስል አምላክ ማን ነው?! በእግዚአብሔር የተወደደ ሰው በርሱ ተማምኖ ይኖራል፤ ቀኑን ሁሉ ይጋርደዋል፤ በትከሻው መካከል ያርፋል።

፴፬ /34 : <u>የሙሴ መሞት፤</u> 1-8 ሙሴም ከሞአብ ሜዳ በኢያሪኮ ፊት-ለፊት ወደ ናባው ( ኔቦ ) ተራራ ወደ ፊስጋ ራስ ወጣ፡ እግዚአብሔር በሰጣቸው የተስፋ--ቃል መሠረት፣ ለሕዝቡ የሚያወርሳትን ምድር ዳር እስከ ዳር አሻግሮ እንዲመለከት ካደረገው በኋላ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ በሞዓብ ምድር ሳለ፣ እግዚአብሔር በተናገረው መሠረት እዚያው ሞተ። -ዕድሜው ገና አንድ መቶ ኻያ ዓመት ነበር፤ ነገር ግን ዓይኑ አልፈዘዘም፤ ጉልበቱ አልደነገዘም። የእስራኤል ልጆች በሞአብ ሜዳ ሠላሳ ቀን አለቀሱለት። 9-12 እግዚአብሔርን ፊት-ለፊት ያወቀ፣ በግብጽ ምድር በፈርዖንና በመኳንንቱም ፊት፣ በምድሪቱ ላይ ምልክትና ልዩ፡ ልዩ ድንቅ ሥራዎችን ያሳይ ዘንድ፣ እግዚአብሔር የላከው፣ በእስራኤል ፊት በጸናች ክንድ ሁሉን ነገር በሚያስደነግጥና በሚያስፈራ ቃል የፈጸመ በእስራኤል ኩቶ ተነሥቶ አያውቅም። <u>*(ትርጓሜ፡*</u> *ከእግዚአብሔር ጋር አምስት መቶ ሰባ ጊዜ ቃል በቃል የተነጋገረ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ፣ እንደ ማንኛውም ሰው ሞተ፣ ተቀበረ፣ ነገር ግን፣ ‹‹ዮት ያደረገ፣ እንደ ሙሴ*



www.ethiopianorthodox.org

ያለ ነቢይ በእስራኤል ከቶ ተነሥቶ አያውቅም። _እንደ ተቀበረ እንኳን ዛሬ ቦታውን ለይቶ የሚያውቅ የለም›› ይለናል የእግዚአብሔር ቃል። አሁንም ቢሆን ዋናው ቁም ነገር ያለው፣ የሙሴን መቃብር ቦታ ከማወቁ ላይ አይደለም፤ ዋናው ተግባር እርሱ ከእግዚአብሔር ተቀብሎ የጻፈውንና ለትውልደ-ትውልድ ያስተላለፈውን ዘላለማዊ ሕያው ቃል ማወቅ መቻል ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሙሴን መቃብር ቦታ ከማወቃቸው ይልቅ አለማወቃቸው የተሻለ ሆኖአል።

_የተቀበረበትን ቦታ አውቀውት ቢሆንማ ኖሮ፣ ምናልባትም የእርሱን ዐፅም (ሥጋ) እንደ አምላክ አድርገው ቢሰግዱለት በነፍስም በሥጋም የሚጐዱበት-ክንያት ሊሆን-ይችል ነበር።ይኸውም በይሁዳ መልእክት _ቊ 9 ላይ ተጽፎ እንደሚገኝ፡ የእስራኤል ሕዝብ የሙሴን ዐፅም ማግኘትና ማምለክ እንደሚፈልጉ አውቆ፣ ሰይጣን ዲያብሎስ ወደ ሙሴ መቃብር እየመራ ሲወስዳቸው፡የመላእክት አለቃ የሆነው-ሚካኤል አይቶት፣ የስድብ ቃል ሊናገረው- ባይፈልግም ‹‹እግዚአብ ሔር ይገሥጽህ››ብሎ የተንኰል እቅዱን እንዳከሸፈበት እናያለን። እንኳንስ የሙሴን ዐፅም ወይም ሥጋውን አግኝተው ይቅርና በእባብ አምሳል የሠራውን በትር እንኳ፣ ለመታሰቢያ በቤተ እግዚአብሔር አኑሮት በመገኘቱ ፣ ሕዝቡ-እንደ አምላክ- ቈጥረውት ዕጣን እያጠኑ ሲሰግዱለት እንደ ነበር በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 18፡ 4 የተጻፈው ያስረዳል። ‹‹ነሑሽታን››እያሉ በመጥራት ስለአመለኩት፣ ንጉሡ ሕዝቅያስ ያንን በትር ሰባብሮ ለመጣል የወሰነበትም ምክንያት ይኸው ነበር። እግዚአብሔር-አምላክ አገልጋዮቹን ሁሉ በሞት ደመና እንዲጋረዱ ያደርጋል። መልካም ሥራቸው ግን፣ ሕያው ሆኖ ትውልድን ሁሉ ሲያስተምር ይኖራል። ሙሴ የተስፋይቱን ምድር አሻግሮ ያየት፣ ናባው በሚባል በአንድ ረጅም ተራራ ጫፍ ላይ ሆኖ ነበር፤ ነገር ግን፣ ከአንድ ሺህ አምስት መቶ ዓመት በኋላ፣ ጌታችን አምላካችን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በታቦር ተራራ ላይ ግርማ መለኮቱን በገለጠባት ዕለት ከነቢዩ ኤልያስ ጋር በአካለ ነፍስ ተገልጦ፣ ስለ ጌታችን መከራ መስቀል ሲነጋገር መታየቱን መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል ( ሉቃ 9፥30-31 )_በዚያች ቀን በአካለ ነፍስ የሙሴ መገለጥና ከጌታ ጋር ሲነጋገር መታየቱ፣ በተስፋ ትንሣኤ ሙታን ለሚያምኑ ክርስቲያኖች ሁሉ፣ ዋና ማስረጃ ነው። "እስመ እሙንቱ ሕያዋን በኀቤሁ = ቅዱሳን በእግዚአብሔር ዘንድ ሕያዋን ናቸው (ሉቃስ 20፡ 38 ) ተብሎ የተጻፈውንም የወንጌል ቃል ከዚሁ ጋር



አብረን ማጤን ይገባል። ይህም ብቻ አይደለም ; ሙሴ በዚሁ በዘዳግም 33፡ 6 በተለይ ስለ ሮቤል ሲጸልይ እንዲህ አለ፣ ‹‹ሮቤል በሕይወት ይኑር፣ አይሙት። የሕዝቡ ቍጥር አነስተኛ አይሁን " ሲል የተናገረው ቃል ስለሞቱ ሰዎች መታሰቢያና በሕይወት የሚኖሩ ልጆቻቸውን ማረጋገያ ትምህርት ለመስጠት የሚያስችል ነው ።

_እንግዲህ ሮቤል ሞቶ ከተቀበረ ከአንድ መቶ ሃምሳ ዓመት የሚያንስ አይመስልም። ታዲያ ሙሴ " ሮቤል በሕይወት ይኑር፡ አይሙት" በሚልበት ጊዜ ተስፋ ትንሣኤ እንዳለውና ዳግም የነፍስ ሞት (ራእይ 21፡ 8 ) ማለትም ርደተ ገሃነም እንዳይደርስበት ተማፅኗል።መ

""""""""""""""""""""""""""""""

# መጽሐፈ ኢያሱ

## ወልደ ነዌ

**መግቢያ**፡ ኢያሱ የስሙ ትርጉም እግዚአብሔር አዳኝ ማለት ነው።በዘኍልቍ-13፡-8 አውሴ በሚል ተለዋጭ ስም ሲጠራ እናያለን።ኢያሱ፡ ኢሳይያስ የተባሉት ስሞች ከእግዚአብሔር አዳኝነት-ጋር ግንኙነት ስላላቸው ኢየሱስ ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይነት ወይም ተዛማጅነት አላቸው። የእግዚአብሔር ሕዝብ እስራኤል ከግብጽ በወጡ ጊዜ ኢያሱ ገና ወጣት /ብላቴና ነበር። በዐርባው ዓመት ን" ተብሎ ከሚጠራው በረሃ አልፈው በረፊድም በሠፍሩ ጊዜ አማሌቃውያን አደጋ ሊጥሉባቸው ሲመጡ በሙሴ ትእዛዝ ኢያሱ የጦር አዝማች ሆኖ ድል አድርጓል (ዘፀ 17፡ 8 -13)። በዘኍልቍ 27፡ 18--22 እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ ‹‹መንፈስ ያለበትን የነዌን ልጅ ኢያሱን በአንተ እግር ተተክቶ የሕዝቡ መሪ ይሆን ዘንድ እጅህን ጫንበትና በካህኑ በአልዓዛርና በማኅበሩም ፊት አቁመው››። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለው መንፈሳዊ መሪ ያስፈልገናል።

_በመጨረሻም ሙሴ ሲሞት ኢያሱ በርሱ እግር ተተክቶ በመስፍንነት ሕዝቡን እየመራ በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሮ፡ ጠንካራ ምሽጎን በመደርመስ ኢያሪኮን የድል መጀመሪያ /መቋደሻ ካደረገ በኋላ ሌሎቹንም ሰባት ነግደ ከነዓን ከነገሥታቶቻቸው ጋር ድል ነሥቶ ነቀትሎ በማጥፋት ምድረ ርስትን ለማውረስ ችሏል። ኢያሱ ይህን ድል ለመቀዳጀት የበቃው "ይህ



www.ethiopianorthodox.org

የሕግ መጽሐፍ ካንደበትህ አይለይ ዘወትር በማንበብ በልብህ አሰላስለው። ይህን ብታደርግ እኔ ካንተ ጋር እሆናለሁ በየደረስክበት ድል አድራጊ ትሆናለህ፡ ሁሉ ነገር ይከናወንልሃል" ሲል እግዚአብሔር ያባዘዘውን ቃል ሁሉ ተግባራዊ በማድረጉ ነው (መጽ/ ኢያሱ 1፡ 8)። ዛሬም ቢሆን አማኞች በነቢዩ ንጉሥ ዳዊት መዝሙር 1፡ 2- 3 ወዘሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ ይከውን ከመ ዕፅ እንተ ትክልት ኀበ ሙኃዘ ማይ =የእግዚአብሔርን ሕግ /ቃሉን በመዓልትና በሌሊት የሚያነበውና የሚያሰላስለው ሰው ብፁዕ ነው። እርሱም በፈሳሽ ውኃ ዳር ተተክላ በየጊዜው ፍሬዋን እንደምትሰጥና ቅጠልዋም እንደማይጠወልግ ዛፍ ይሆናል። ወኵሎ ዘገብር ይፌጽም =የሚሠራውም ነግር ሁሉ ይከናወንለታል" ተብሎ እንደተጻፈ የመስፍኑን ኢያሱን አርአያና ምሳሌነት መከተል ቢፈቅዱ በሰይጣን ዲያብሎስ ሠራዊት ላይ ድል አድራጊዎች ሆነው የመኖር መብታቸው የተጠበቀ ነው። በመጽሐፈ ኢያሱ ዋና ማዕከል ሆኖ ሁልጊዝ ሲታወስ የሚኖር ታላቅ የውሳኔ ቃል "የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፡ እኔና ቤቴ ( ቤተሰቤ ) ግን እግዚአብሔርን በማምለክ ፀንተን እንኖራለን" የሚለው ነው ( ኢያሱ 24፡ 15) ። የሁላችንም ምርጫ ይኸው ቢሆን በሕያው አምላካችን ጸጋ ለዘለዓለም እንባረክበታለን ።

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

## ፩/1፡ እግዚአብሔር ለኢያሱ የሰጠው ልዩ ትእዛዝና መመርያ ፡

5--9 እግዚአብሔር፣ የነዌን ልጅ ኢያሱን እንዲህ ሲል አዘዘው፤ ‹‹እነሆ፣ እኔ ከሙሴ ጋር እንደ ነበርሁ፣ ከአንተም ጋር እሆናለሁ፤ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፣ አንተን ተቋቁሞ ድል መንሣት የሚችል አይኖርም፤ ከቶም አልተውህም፤ ፅናትና ብርታት ይኑርህ፤ በአገልጋዬ በሙሴ አማካይነት ለተሰጠህ ሕግ ሁሉ፣ታዛዥ ሁን፣ በምትሄድ_በት ስፍራ ሁሉ፣ ማናቸውም ነገር እንዲከናወንልህ ከዚህ ሕግ ወደ ቀኝም ወደ ግራም አትበል። የዚህ ሕግ መጽሐፍ ቃሉ ከአንደበትህ አይለይ፤ ትእዛዙን መፈጸም እንድትችል ዘወትር ቀንና ሌሊት አሰላስለው፤ ይህን ማድረግ ብትችል፣ ሁሉ ነገር ይከናወንልሃል፤ በምትሄድበትም ስፍራ ሁሉ፣ እኔ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር እሆናለሁ››።



(**ትርጋሜ፡** በዚህ ቅዱስ ትእዛዝ ጥላ ሥር ቢነገሩ ተስማሚ የሆነ ተጓዳኝነት ያላቸው ታሪክና ምሳሊዎችንም መቃኘት ሲያስፈልግ፡ ሦስት ያህሉን እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡ -

## 1ኛ. $ 50 ሺህ ዶላር ተንተርሶ በድህነት መኖር ?

አንድ ወጣት እናቱ በልጅነት ሞታበት ተሰፋ ቆርጦ ሲያለቅስ አክስቱ ከወደቀበት መከራ አፅናንተው -“አይዞህ፡ የእኅት ልጅ ባይወልዱትም ልጅ" ይባላልና እኔ በእናትህ ምትክ ሆኜ አሳድግሃለሁ፡ ከልጆቼ እኩል ወራሽ፡ ቆራሽ ትሆናለህ” ብለው ወደ ቤታቸው ወሰድውት” ከአክስቱ ልጆች ጋር በሥነ ሥርዓት ካደገ በኋላ "ዕድለቢስ ነጋዴ ጧፍ ልነግድ ብሎ ቢነሣ፡ ሌሊቱ ተለውቶ ቀን ይሆንበታል" እንዳሉ አክስቱ ደግሞ በድንገተኛ ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። በዚህም ምክንያት ከአክስቱ ልጆች ጋር በሥርዓት ካደገ በኋላ እንዳጋጣሚ አክስቱ ደግሞ በድንገተኛ ሕመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ። በዚህም ምክንያት ከአክስቱ ልጆች ጋር በመሪር ሐዘን ላይ ከቆየ በኋላ በዐርባቸው ድግሥ ማግሥት ንስሐ አባትየው ለቤተሰቡ የኑዛዜ ቃል ሲያፈሱ /ሲያነቡ “ደጃፍ የመለሰውን፡ ማጀት የጎረሰውን ሀብት ንብረት በሙሉ ለልጆቻቸው አከፋፍለው፡ ላሳደጉት ለእኅታቸው ልጅ ግን አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ የተናዘዙለት መሆኑ ተነግሮት ወዲያውኑ መጽሐፉን አስረከቡት። ወጣቱ ይህን ሲሰማ ለቅሶውን አቁሞ፡ እንባውን አብሶ እየተናደደ ወደ መኖሪያ ክፍሉ ሄደ። ያን መጽሐፍ ቅዱስ በፕላስቲክ ጠቅሎ በትራስጌው ፍራሽ ሥር ያስቀምጠውና አንድም ቀን ገልጦ ሳያየው፡ በኩሊነት ሥራ የዕለት ጉርስ ያመት ልብስ ብቻ እያገኘ ኻያ ዓመት ሙሉ ኖረ ። ከኻያ ዓመት በኋላ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ እያዞሩ በየቤቱ በቅናሽ ዋጋ ያድሉ ነበርና “አቶ እከሌ መጽሐፍ ቅዱስ ትገዛለህ ወይ?” ብለው ጠየቁት። እርሱም - “የእኔ ችግር የገንዘብ ማጣት እንጂ መጽሐፍ ቅዱስማ አክስቴ የሰጠችኝ አለ።ብትፈልጉ ልሸጥላችሁ” አለ። እስኪ አምጣውና እንየው ሲሉት ከትራስጌው መዝዞ አምጥቶ ገና አዲስ መሆኑን ለማሳየት ከፈት ሲያደርግ በመጀመሪያው ገጽ አንድ መቶ ዶላር፡ በሁለተኛውም ገጽ አንድ መቶ ዶላር አገኘ። እየተደነቀ ገጹን ሁሉ ሲከፍት አንዳንድ መቶ ዶላር ተሰግሥጎበት አገኘና ድምር ኃምሳ ሺህ ዶላር ሆንለት የኻያ ዓመት ድህነት በዚህ አከተመለት ማለት ነው። የብዙዎች ክርስቲያኖችና ካህናትም ሕይወት ልክ እንደዚሁ ነው።መጽሐፍ ቅዱስን እንደዚያ ሰነፍ ሰው ትራስ አድርገው ተኝተውበት ይኖራሉ።



www.ethiopianorthodox.org

"ንሥአ ለዛቲ መጽሐፍ ወብልዓ == ይህችን መጽሐፍ ወስደህ ብላት ፡ -ሕዝ. 3፡ 1። ወዘልፈ ሁሉ ባቲ -አዘውትረህ አንብባት"ተባለ እንጂ እንዳያቃሥያችሁ "መጽሐፍ ቅዱስን ተንተርሳችሁ ተኙ" የሚል መመሪያ ፈጽሞ የለም። ዘወትር እያነበቡ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን በማደስና በፈሳሽ ውሃ ዳር ተተክላ ቅጠልዋ እንደማይረግፍ፡ በየወቅቱ ፍሬ እንደምትሰጥ ዛፍ በነፍስም በሥጋም ለምልመው፡ በመኖር ፈንታ (መዝ. 1. 2 -3 ) በነፍሳቸውም በሥጋቸውም የእውቀት ድሆች ሆነው የሚኖሩ ሁሉ ያልታደሉ ናቸው። 2ኛ. ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሌላው ታሪክና ምሳሌ ርእሱ፡ """""" <u>የወርቅ ቍልፍ የነበራት አዲስ መኪና</u>"""""" ይላል

_አንድ-ወጣት የዩኒቨርሲቲ ተማሪ አባቱ የታወቁ ሀብታም /ሚሊዮነር ናቸው። አንዲት የወርቅ ቍልፍ ያላት አዲስ መኪና ገዝተው ቈልፈው፡ ሽራ አልብሰው አስቀምጠዋታል።ወጣቱ ልጃቸው እኔ የዩኒቨርሲቲ ትምህርቴን ጨርሼ ስመረቅ አባቴ ይህችን መኪና ሽልሞ ቍልፍዋን ያስረክበኛል" ብሎ ጠብቆ ነበር። ነገር ግን በተመረቀበት ቀን አባቱ ስለ መኪና ምንም ቃል ሳይናገሩ" በከፈይ ቀለም ባጌጠ ካርቱን አሽገው አንድ መጽሐፍ ቅዱስ ሸለሙት። ተመራቂው ወጣት ምሥጢሩን ሳያውቅ የአባቱን ሽልማት በማቃለልና በምናቅ ወስዶ አንድ ሣጥን ውስጥ ወርውሮት አኩርፎ ከብተሰቡም ሁሉ ተለይቶ ወደ ሌላ እስቴት| ሄደ። እዚያም በተራ አስተማሪነት ተቀጥሮ ኻያ ዓመት ያህል ቆየ። በመካከል ቤት አባቱም እናቱም ሞተው መርዶ ሲነገረው "ሰው ምን ይለኛል?' በሚል ይሉኝታ ወደ አባቱ ቤት ይመጣና ጥቂት ቀናት ቆይቶ ያን ካርቱን ከፍቶ በሚመለከትበት ጊዜ ያች የመኪናዩቱ የወርቅ ቍልፍ ከአንድ ሚልዮን ድዶላ ቼክና ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር አብራ አገኛት። መኪናዋ ግን አልነበረችም። ቼኩም ዘመን አልፎበት ነበርና እንዲህ ከሥሮ ቀረ። ቅዱሳት መጻሕፍትን ለማንበብና ለማጥናት ፈቃደኛ ያልሆነ ካህንም ሆነ ምእመን ሁሉ እንደዚሁ የከሠረ ነው።

ቤተ ክርስቲያናችን በካህናት ቍጥር ብዛት ከዓለም አንደኛ ናት። የካህናቱ ቍጥር ከግማሽ ሚሊዮን በላይ ነው። ከዚህ ቍጥር ውስጥ ቢያንስ ኃምሳው ሺህ ያህል ካህናት እንኳ መጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ቢሆኑ ኖሮ በትምህራታቸው ዓለምን ለመለወጥ በቻሉ ነበር። በሐዋርያዊ ተልእኮ ወደ ልይ፡ ልዩ የአፍሪቃ አህጉር እንኳ



በመሠማራት የስብከተ ወንጌል ድርጅት በማቋቋም ከችግር ተላቀው ኑሮአቸውንም ጭምር አመቻችተው የተድላ ደስታ ሕይወት መምራት በተቻላቸው በነበር። _በእርግጥ በልዩ ፡ ልዩ የአገልግሎት ዘርፍ ሙያ ብዙ እውቀት አላቸው። መዝሙረ ዳዊት አዛውትረው ይጸልያሉ። በብዙ ነገር ጆሮ ጠገብ ስለሆኑ ዓይነ ልቡናቸው /አእምሮዋቸው ተከፍቶላቸ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መመልከት ቢፈቅዱ ኖሮ እነርሱን በማሠልጠን የትምህርተ ወንጌል መድረክ ባለቤቶች ለማድረግ የአንድ ዓመት ጊዜ እንኳ አይፈጅም ነበር። ለዚህም አንድ ተጓዳኝ ታሪክና ምሳሌ እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፡ ፡-

## 3ኛ ' <u>ስንት ሌሊት እንዲሆን ይፈልጋሉ ?</u>

_ራስ ጉግሳ ወሌ የተባሉ የእቴጌ ጠይቱ ብጡል የወንድማቸው ልጅ ቀድሞ የንግሥት ዘውዲቱ ባል የነበሩ ሲሆኑ ዘውዲቱ ንግሥተ ነገሥታት ለመሆን ሲመረጡ ራስ ጉግሳ ከንግሥቲቱ ጋር አብረው እንዲኖሩ አልተፈቀደም ነበርና የየጁና ደቡብ ጐንደር ገዢ ሆነው በሹመት ሲኖሩ ከመሐል አገሩ ማዕከላዊ መንግሥት ጋር መግባባት አልነበራቸውም። ዛዲያማ ራስ ጉግሳ ወሌ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያንን የሚወዱ ከመሆናቸው የተነሣ ሐዲስ ተክሌና ብሉይ ተልክሉ የተበሉት ታላላቅ ሊቃውንት ባጠገባቸው ነበሩ። የራስ ጉግሳ ንስሐ አባታቸው ግን ብዙም የቤተ ክህነት ትምህርት ሳይኖራቸው በግብረ ገብነት፡ በታማኝነትና በትሕትናቸው ብቻ የሚደነቁ ሰው ነበሩ። ሌሎች ካህናት በቅንዓት መንፈስ ተነሣሥተው ለራስ ጉግሳ ያቀረቡላቸው ጥያቄ "እርስዎን የመሰለ ርእሰ መኳንንት ከሊቃውንት መካከል መምረጥ ሲገባዎት እንዴት እንደዚህ ያለውን ያልተማረ ካህን ንስሐ አባት ያደርጋሉ። አሁንም ያስቡበት" የሚል ነበር።

_ራስ ጉግሳም "እኒህ አባት ታማኝና ፍጹም ትሑት በመሆናቸው እንወዳቸዋለን። ጉድለታቸው ምንድን ነው?" ብለው ሲጠይቁ "እረ እንዳው ያልተማሩ ጨዋ ናቸው፡ የባሕረ ሐሳብ ቀመር ስለማያውቁ ማሥረቅ እንኳ ስለማይችሉ "ዛሬ ስንት ሌሊት አደረ?" ብለው ቢጠይቋቸው መልስ አይኖራቸውም ብለው ይወነጅሏቸዋል። ራስ ጉግሳም ለጊዜ ጉዳዩን ብዙም ሳያስቡበትና ትኩረት ሳይሰጡት ይቆዩና በመካከል ቤት ከማዕከላዊዉ መንግሥት ጋር በነበራቸው ቅራኔ መሠረት ጦርነት ሊጀመር ተቃርቦ ከመሐል አገር በደጃች ክፈተው



www.ethiopianorthodox.org

የሚመራ ሠራዊት ወደ ወሎ ሲሻገር፡ የሰሜን ጐንደር ገገር የነበሩትን ደጃች አያሌውን ደግሞ "ከእኛ ጋር ተበብረው አብረን ተዋግተን ራስ ጉግሳን ብናሸንፍ ደቡብ ጐንደርን ጭምር ደርበው እንዲገዙ እንፈቅድልዎታለን" የሚል መልእክት ደረሳቸውና የእንታቸውን ልጅ ራስ ጉግሳን ትተው ከመሐል አገር ጦር ጋር ተባብረው አንቺም ተብላ በምትጠራውና (ከጐንደርና ጋር በምትዋሰን ቦታ) ጦርነቱ ሲካሂያድ ተወሰነ።በዚህም ጊዜ የራስ ጉግሳ ንስሐ አባት የጁ ነበሩና የንስሐ ልጃቸው እዚህ ጦርነት አፋፍ ላይ እያሉ ዝም ብለው መቆየቱ አላስችል ብሏቸው፡ ከየጁ ገሥግሠው ራስ ጉግሳ ወዳሉበት ጦር ሠፈር ይመጣሉ። በክብር ተቀብለዋቸው ሲያተናግዱዋቸው፡ አምሽተው ሌሊቱን በጸሎት ወደሚያሳልፉባት ማረፊያ ክፍል አመሩ።

_በማግሥቱም ጦርነት የሚገጥሙበት ዕለት በምሆኑ ጸሎተ ንስሐ ተቀብለው መሄድ ስለፈለጉ፡ ራስ ጉግሳ ንስሐ አባታቸው ወዳአደሩበት ክፍል መጥተው ጸሎተ ማርያምና ጸሎተ ንስሐ አድርሰውላቸው ወደዘመቻው ቦታ ለመሄድ ተነሡ። ወዲያው ግን እንደገና ወደ ኋላ መለስ ብለው "አባቴ ይገርምዎታል ! ብዙ ጊዜ እጠይቅዎታለሁ ስል እየረሳሁት የቆየ አንድ ጥያቄ አለኝ፡ ለመሆኑ ዛሬ ስንት ሌሊት አደረ?" ሲሏቸው ንስሐ አባትዮው ተገርመው፡ "አዬ ጌታዬ ! እኛ ለራሳችን ስለጦርነቱ በማሰብ- እንዱ-ሌሊት-አልነጋ- ብሎን- ስንጨነቅ አድረናል። እርስዎ ደግሞ ስንት ሌሊት እንዲሆን ይፈልጋሉ?" አሏቸው። ራስ ጉግሳም በዚያ መልስ ተደንቀው "ወሴ ይሙት። እኒህን ካህን አልተማሩም 'የሚል ሁሉ ራሱ ያልተማረ ነው" ብለው ትተዋቸው ሄዱ ተባለ።

_እነሆ በዚህ ዓይነት ብሩህ አእምሮ ያላቸው ካህናት አሉን። ዛዳማ ከዚህ ጋሮ ጠንብ እውቀት ጋር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ተጨምሮበት ቢሆንማ ኖሮ የእኛን ካህናት ሁሉ ማን ይወደደራቸው-ነበር? አሁንም እግዚአብሔር አምላክ የተዘጋውን በር /መንግዱን ይክፈትላቸው" ብልን መጸለይ ይገባል።)

## ፪ /2 : ኢያሱ የኢያሪኮን ሁኔታ የሚያጠኑ ሁለት ሰላዮችን ላከ፡

1--7 ከእስራኤላውያን ወገን የተላኩ ሁለት ሰዎች አገሪቱን ሲሰልሉ መምጣታቸውንና በምሽት ጊዜ ረዓብ ( ራኬብ ) ተብላ ወደምትጠራ ሴትኛ-አዳሪ ቤት ለማደር መግባታቸውን የኢያሪኮ ንጉሥ ሰማ። መልክተኞቹንም ልኮ፣ እነዚያን ሰዎች አውጥታ እንድትሰጥ ስትጠየቅ፣ እርስዋም እንዲህ አለች፤ ‹‹በእርግጥ ከወዴት እንደ መጡ አላወቅሁም እንጂ፣ ሁለት ሰዎች ወደ ቤቱ ገብተው ነበር፤ ነገር ግን ጀንበር ስትጠልቅ፤ የከተማው ቅጽር በር ከመዘጋቱ በፊት ወጥተው ሄደዋል፤ ወዴት እንደ ሄዱ ግን አላወቅሁም፤ ፈጥናችሁ እግር-በእግር ብትከታተሏቸው ትደርሱባቸዋላችሁ››። ኢያሱ የላካቸውን ሰላዮች ግን፣ ደብቃ ከሞት ለማዳን ወደ ቤቱዋ ጣሪያ አውጥታ፤ በላያቸው ላይ የተልባ እግር ረብርባ ሸሽጋቸው ነበር። 8-13 እነርሱም ከመተኛታቸው በፊት፣ ወደ ተሸሸጉበት ወደ ቤትዋ ጣሪያ ወጥታ እንዲህ አለቻቸው፤ ‹‹እግዚአብሔር ይህችን ምድር ለእናንተ አሳልፎ እንደሰጣችሁ አውቃለሁ፤ እናንተን ከመፍራት የተነሣ፣ የአገሪቱ ነዋሪ ሁሉ ተሸብሮአል፤ እናንተን በመፍራት ልባችን ቀልጦ ወኔ ተለይቶናል፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር የሰማይና የምድርም ንግሥ ነው። አሁን እኔ እናንተን ከሞት ለማዳን ይህን መልካም ነገር እንዳደረግሁላችሁ፣ እናንተ ደግሞ፣ ይህችን አገር ድል አድርጋችሁ በምትገቡበት ጊዜ፣ እኔንና ቤተ-ሰቤን ከጥፋት ለማትረፍ ማሉልኝና ዋስትና የሚሆን ምልክት ስጡኝ››።

14--16 መልክተኞቹም እርሱዋንና ቤተ-ሰብዋን ሁሉ ከጥፋት እንደሚያድኑ ቃል ገቡላት። ረዓብ የምትኖርበትም ቤት ከኢያሪኮ ከተማ ቅጽር ተጠግቶ የተሠራ ስለ ነበር፣ በመስኮቱ በኩል በገመድ ተንጠላጥለው ወደ ታች እንዲወርዱ ረዳቻቸው፤ እንዲህ ስትልም መከረቻቸው፤ ‹‹የንጉሡ መልክተኞች እንዳይደርሱባችሁ ወደ ኮረብታማው አገር ሂዱና በዚያ ሦስት ቀን ተደብቃችሁ ቆዩ፤ ከዚያን በኋላም ጉዞአችሁን መቀጠል ትችላላችሁ››። 18-19 መልክተኞቹ እንዲህ ሲሉ ምልክት ሰጡዋት፤ ‹‹እኛ ምድራችሁን በምንወርበት ጊዜ፣ ይህን ከቀይ ፈትል የተገመደ ክር፣እኛን ባወረድሽበት መስኮት ላይ አስረሽ እንዲታይ አድርጊ፤ አባትሽና እናትሽ፣ ወንድሞችሽና ቤተ-ሰብሽ በሙሉ በአንድነት ተሰብስበው በቤትሽ እንዲቀመጡ አድርጊ››። መልክተኞቹም-ወደ-ኢያሱ-ተመልሰው-መጥተው፣በኢያሪኮ-ከተማ የሚኖሩት ሁሉ፣ እስራኤላውያንን ፈርተው በመሸበር ላይ መሆናቸውን አስረዱ።

## ፫/3 : የእስራኤል ሕዝብ የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻገሩ :

1--6 ኢያሱና የእስራኤል ሕዝብ የሰጢምን ሠፈር ለቀው ወደ ዮርዳኖስ ሄዱ። እግዚአብሔር-በሙሴ ማካይነት ቀይ ባሕርን ከፍሎ እንዳሻገራቸው፤ በኃይል ሞልቶ የነበረውን የዮርዳኖስን ወንዝ ውሃ መውረዱን አቁሞ፣ በሌላ አቅጣጫ በመፍሰስ እንዲከማች አድርጎላቸው፣ በኢያሪኮ ፊት-ለፊት





www.ethiopianorthodox.org

በደረቅ ምድር ተሻገሩ። ከመሻገራቸው በፊት ግን፣ ከነገድ አለቆች በተሰጠው መመሪያ መሠረት፣ የቃል ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ሌዋውያን ሕዝቡ በሁለት ሺህ ክንድ ርቀት እንዲከተሉ ሆኖ፣ ሕዝቡ በሙሉ እስኪሻገሩ ድረስ፣ ካህናቱ የቃል ኪዳኑን ታቦት እንደ ተሸከሙ በወንዙ መካከል ቆመው ቈዩ።

፬ /4 ፡ 5-10 ለኢያሱ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት፣ የቃል ኪዳኑ ታቦት ከቆመበት ቦታ በዐሥራ ሁለቱ ነገዶ እስራኤል ስም ዐሥራ ሁለት ድንጋዮች ከወንዙ ይዘው ወጥተው፣ በዚያኑ ዕለት ማታ በሠፈሩበት ቦታ፣ ለእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ መታሰቢያ የሚሆን ሐውልት አድርገው አቆሙ። ኢያሱም እንደ ገና ሌሎች ዐሥራ ሁለት ድንጋዮችን ከደረቅ ምድር ወደ ወንዙ አስገብቶ፣ ታቦተ- ሕጉን ተሸክመው በቆሙት ካህናት ፊት የመታሰቢያ ሐውልት አድርጎ አቆመ።

፭/5 ፡1 ከዮርዳኖስ ወንዝ ማዶ በስተምዕራብ ያሉ የአሞራውያ ነገሥታትና በሜዲቴራኒያን ባሕር ዳርቻ ጠረፉን ተከትለው የሚኖሩ የከነዓን ነገሥታት፣ ይህን ሁሉ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ሲሰሙ፣ በመደንገጥ ወኔ ተለያቸው። 2--7 ከዚህ በኋላ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን፣ ‹‹ከባልጭት (ከድንጋይ ስባሪ -ሱፋጭ) የተሠራ መቍረጫ አዘጋጅተህ ወንዶች የሆኑ እስራኤላውያን እንዲገዘሩ አድርግ›› ሲል አዘዘው። ኢያሱም እንደ ታዘዘው አደረገ። ከዚያን በኋላ፣ ኢያሪኮ አጠገብ ባለው ሜዳ በጌልጌላ ሠፈሩ፤ የፋሲካንም በዓል በዚያው አከበሩ። በፋሲካ ማግሥት በከነዓን የበቀለውን እህል መብላት ሲጀመሩ መና መገኘነሙ ተገታ።

<u>ኢያሱና የተመዘዘ ሰይፍ የያዘው ጐልማሳ</u> ፡ 13-15 ኢያሱ በኢያሪኮ አጠገብ ሳለ፣ ቀና ብሎ ሲመለከት፣ እነሆ፣ የተመዘዘ ሰይፍ በእጁ የያዘ ሰው በፊቱ ቆሞ አየ። ኢያሱም ወደ እርሱ ቀርቦ፣ ‹‹አንተ ከየትኛው ወገን ነህ? ከጠላቶቻችን ወይስ ከእኛ ወገን?›› አለው፤ ያም ሰው፣ ‹‹እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አዛዥ ሆኜ መጥቻለሁ›› አለው። ኢያሱም በግንባሩ ወደ ምድር ተደፍቶ ሰገደ። ወዲያውም የእግዚአብሔር ሠራዊት አዛዥም ኢያሱን፣ ‹‹የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ ነውና ጫማህን ከእግርኽ አውልቅ›› አለው።*(<u>ትርጓሜ</u>፡ እዚህ ላይ፣ የኢያሱ ስግደት ለመልአኩ የጸጋና የአክብሮት ስግደት ሲሆን ፡ ለእግዚአብሔር ግን የባሕርይ አምላክነት ስግደት መስገዱን እናያለን። መልአክ ባለበት ቦታ ምንጊዜም እግዚአብሔር አለና። ይኸውም ፡‹‹የቆምህበት ስፍራ የተቀደሰ በመሆኑ ጫማህን አውልቅ›› የተባለበት ምክንያት ራሱ እግዚአብሔር ባዚያ ቦታ ስለነበረ ነውና።*



*ለምሳሌ በዘፀአት 3፡ 12 -25 በእሳት በተቀጣጠለው ቍጥቋጦ መካከል በመጀመሪያ ለሙሴ የታየው የእግዚአብሔር መልአክ ሲሆን ፡‹‹ጫማህን አውልቅ ብሎ ያዘዘው ግን ራሱ እግዚአብሔር ነበር። )*

፮ /6፡ ከፍተኛ ሥጋትና ድንጋጤ ያደረባት የኢያሪኮ ከተማ

_የኢያሪኮ ከተማ ቅጽር በሮች ሁሉ፣ ተዘግተው በዘብ ይጠበቁ ነበር፤ ወደ ከተማይቱ የሚገባም ሆነ የሚወጣ አልነበረም። 11-21 የቃል-ኪዳኑን ታቦት የተሸከሙ ካህናትና ቀንደ-መለከት የሚነፉ ሰባት ካህናት በመካከል ሆነው፣ ሠልፈኛው ሠራዊት ከተማዪቱን ስድስት ቀን ዞረ። በሰባተኛው ቀን ደግሞ፣ ማልደው በመነሣት ሰባት ጊዜ ዞሩአት። በዚህ ጊዜ፣ ኢያሱ እንዲህ ሲል አዘዘ፤ ‹‹ከብርና ከወርቅ፤ ከነሐስና ከብረት የተሠራ ማናቸውም ነገር እንደ በኵራት (የድል መጀመሪያ) ሆኖ፣ ለእግዚአብሔር የተለየ ይሁን››። በሰባተኛው ዙር ጊዜ፣ ካህናቱ የቃል-ኪዳኑን ታቦት ተሸክመው፣ ሰባቱ ካህናት ቀንደ-መለከት ሲነፉ፣ ሰልፈኞቹ ወታደሮችም ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ደነፉ፡ ፡ በዚያን ጊዜም፣ የኢያሪኮ ግንብ ዳር እስከ ዳር ተናደ፤ እንዳልነበርም ሆኖ ከተማይቱን ማረኩ። ኢያሱም ኢያሪኮን ሰልለው እንዲመለሱ የላካቸውን ሁለት መልክተኞች ሸሽጋ ከሞት ያዳነቻቸውን ያቺን ጋለሞታ፣ ረዓብን፣ ቤተ-ሰብዋንና ዘመዶችዋን ሁሉ መልክተኞቹ በሰጡዋት ዋስትና መሠረት፣ ከጥፋት እንድትድን አደረገ። 26 ቀጥሎም ኢያሱ እንዲህ ሲል ተናገረ፣ ‹‹ይህችን የኢያሪኮ ከተማ መልሶ የሚሠራ ሰው ቢኖር፤ የእግዚአብሔር መርገም በእርሱ ላይ ይሆናል፤ የመሠረቱን ድንጋይ በሚያኖርበት ጊዜ፣ የመጀመሪያ ልጁን ያጣል፤ የቅጽር በሮችዋን ሲያቆም ሁለተኛው ልጁ ይሞታል››። (የዚህን ትንቢት አፈጻም 1 ነገ. 16፡34 መመልከት ይቻላል)፡

፯/7፡<u>አካን የፈጸመው የስርቆት በደል በጠላት ፊት መሸነፍን አስከተለ</u> ፡

1--26 አካን ከነገደ ይሁዳ የዛራህ ጐሣ የነበረ ነው።እርሱም ለእግዚአብሔር ከተለየው፣-ከኢያሪኮ ከተማ-ምርኮ ውስጥ አንድ የባቢሎን ካባ ሁለት ኪሎ ግራም የሚመዝን ብርና ግማሽ ኪሎ ግራም የሚመዝን ምዝምዝ ወርቅ ሰርቆ ወሰደ። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በረድኤት ስለ ተለያቸው፣ ዓይ ተብላ የምትጠራውን ከተማ ወግተው ለመያዝ ተልከው ከነበሩት ሦስት ሺህ ሰዎች መካከል፣ ሠላሳ ስድስት ያህል ሰዎች ተገድለውባቸው ሌሎቹ ለመሸሽ ተገደዱ። ኢያሱ-ወደ እግዚአብሔር ጮኸ በጸሎት በጠየቀ ጊዜ፣ለመሸነፍ ምክንያት የሆነው የአካን ስርቆት መሆኑ



www.ethiopianorthodox.org

ታወቀ። አካንም ተይዞ ስርቆቱ ከተረጋገጠ በኋላ፣ በድንጋይ ተደብድቦ እንዲሞት ተፈረደበት፤ ቤት-ንብረቱም ከቤተ-ሰቡ ጋር አብሮ በእሳት ተቃጠለ፣ የመከራ ጉድጓድ ተብሎ በተጠራው ሸለቆም ውስጥ ተጣለ።

፰ /8 ፡ <u>የዓይ ከተማ-ተደመሰሰች፤</u> 18-27 ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር እያሱን፣«ጦርህን ወደ ዓይ-(ጋይ) ከተማ-በመቃጣት ዘርጋ፤ እኔ እርስዋን ለአንተ አሳልፌ እሰጣለሁ» አለው። ኢያሱም እንደ ታዘዘው አድርጎ ሠራዊቱን በማዝመት፣ ጦሩን ወደ ዓይ ከተማ ቃጣ፣ ከተማይቱ ተማርካ ዐሥራ ሁለት ሺህ ነዋሪዎቿዋ አለቁ፤ ከነሕይወቱ ተማርኮ ወደ ኢያሱ ቀረበ ንጉሥዋ ብቻ ነበር። ኢያሱ የጠላት ጦር እስኪደመሰስ ድረስ ወደ ዓይ ከተማ የቃጣውን ጦር ሳይመልስ ቈየ። እግዚአብሔርም ለኢያሱ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት፣ የዓይ ከተማ ምርኮ ሁሉ ለድል አድራጊው ሠራዊት እንዲከፋፈል ተደረገ፡ ሙሴ የጻፈው የእግዚአብሔር ሕግ በጌባል ተራራ ላይ ተነበበ። 30-32 ኢያሱም በጌባል ተራራ ላይ ለእስራኤል አምላክ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሠራ፤ አሠራሩም፣ «መሠዊያን ከድንጋይ በምትሠሩበት ጊዜ በብረት መሣሪያ የተጠረበ እንዳይሆን»ሲል፣ እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ነው (ዘፀ 20፥25። ኢያሱም እስራኤላውያን እያዩ፣ ሙሴ ከጻፈው ሕግ አንዱን ቅጂ እዚያ ቦታ በሚገኝ ድንጋይ ላይ ቀረጸው። 35-ሴቶች፣ሕፃናት-ልጆችና-የውጭ-አገር ስደተኞች በተገኙበት በእስራኤል ጉባኤ ፊት፣ እያንዳንዱን የሙሴ ሕግ ትእዛዝ ኢያሱ አነበበ።

፱ /9 ፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይጠየቅ <u>የተደረገ ስምምነት፤</u>

1-7 ሌሎች ነገሥታት ሁሉ ኀይላቸውን አስተባብረው በኢያሱና በእስራኤል ላይ አደጋ ለመጣል ተዘጋጁ። የሒታውያን ወገኖች የሆኑ የገባዖን ሰዎች ግን፣ከሩቅ አገር የመጡለመምሰል ስንቅ አዘጋጅተው፣ አሮጌ-ስልቻና-ተቀዶ-የተጣጣፈ የወይን ጠጅ አቁማዳ በአህዮች ጭነው፣ ያለቀ አሮጌ ልብስ ለብሰው፣ የተጠጋገነ አሮጌ ጫማ አድርገው፣ ኢያሱ ወደ አለበት ሠፈር መጡ፣ እንዲህም አሉት፤ «እኛ ከሩቅ አገር የመጣን ሰዎች ነን፤ ከእናንተም ጋር የሰላም ውል (ስምምነት) ማድረግ እንፈልጋለን»። 14-15 የእስራኤል ሰዎች ከመንገደኞቹ ስንቅ ጥቂት ምግብ ወስደው አዩ፤ ስለ ሁኔታው ግን፣ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሳይጠይቁ ከገባዖናውያን ጋር የሰላምና የወዳጅነት ስምምነት አደረጉ። የእስራኤል ሕዝብ መሪዎችም ስምምነቱን ለመጠበቅ ቃል ገቡላቸው።



16 ነገር ግን፣ ስምምነቱ በተደረገ በሦስተኛው ቀን፣ ሰዎቹ በቅርብ የሚኖሩ የገባኦን ሰዎች መኾናቸውን እስራኤላውያን አወቁ። የእስራኤል መሪዎች፣ «ቃል-ኪዳኑ እንደ ተጠበቀ ኾኖ፣ እነዚህ ሰዎች በመካከላችን ይኑሩ፤ እንጨት እየቈረጡና ውሃ እየቀዱ አገልጋዮቻችን ይኹኑ» የሚል መመሪያ ሰጡ።

፲ /10 ፡ <u>አሞራውያን ተሸነፉ፤</u> 1-11 ኢያሱ የዓይን /ጋይን ከተማ ደምስሶ፣ ንጉሥዋን መግደሉንና የገባዖን ሰዎችም ከኢያሱ ጋር የሰላም ስምምነት- ማድረጋቸውን የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒቤዜቅ ሰማ። ከዚህ የተነሣም፣የኢየሩሳሌም ኗሪ ሕዝብ ብርቱ ድንጋጤና ፍርሃት አደረባቸው፡ ስለዚህም አዶኒቤዜቅ፡- የኬብሮን ንጉሥ ሆሃማን፣ የያርሙት ንጉሥ ፒራምን፣ የለኪሶን (የላኪሽ) ንጉሥ ያፊዓን፣ የዔግሎን ንጉሥ ደርቢን፣ አስተባብሮ የጦር ግንባር በመፍጠር፣ መጀመሪያ በገባዖን ላይ አደጋ ጣሉባት። የገባዖን ሰዎችም በተገባላቸው ቃል መሠረት፣ የኢያሱን ርዳታ ጠየቁ፤ ኢያሱና ሠራዊቱም ሌሊቱን ሙሉ ከጌልጌላ ወደ ገባዖን ሲገሠግሡ አድረው፣ በአሞራውያን ላይ ድንገተኛ አደጋ ጣሉባቸው። እግዚአብሔርም በእስራኤል ሠራዊት ፊት፣ አሞራውያን እንዲሸበሩ አደረገ። አሞራውያን በመተላለፊያው ቍልቍለት በሚሸሹበትም ጊዜ፣ እግዚአብሔር ታላላቅ የበረዶ ናዳ ከሰማይ በማውረድ፣ እስከ አዜቃ ድረስ አሳደዳቸው። ስለዚህ፣ እስራኤላውያን በሰይፍ ስለት ከገደሉዋቸው ይልቅ፣ በበረዶ ናዳ የሞቱት ሰዎች ቍጥር-እጅግ ብዙ ሆነ። እግዚአብሔር በአሞራውያን ላይ ለእስራኤል ድልን በሰጠበት ቀን፣ ኢያሱ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር፣ «በገባዖን ላይ ፀሐይ ሳትጠልቅ ትቈይ፤ ጨረቃም በአያሎን ሸለቆ ቆማ ትቈይ» አለ። እንዳለውም ሆነለት። እግዚአብሔር የሰውን ቃል የሰማበት፣ እንደዚያ ያለ ቀን ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ ታይቶ አይታወቅም። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጎን ሆኖ ይዋጋላቸው ነበርና። 16 ይህም ሁሉ ሲሆን፣ አምስቱ አሞራውያን ነገሥታት ለጊዜው አምልጠው በማቄድ ዋሻ ውስጥ ተደብቀው፣ መውጫው በር በትልቅ ድንጋይ ተገጥሞበት ነበር። ከዚያን በኋላ፣ ኢያሱ አምስቱንም ነገሥታት አስመጥቶ ገደላቸውና በአምስት እንጨት ላይ ሰቀላቸው፤ ሬሳቸውም እስከ ምሽት ድረስ ዋለ።

፲፩ /11 ፡ <u>የሐፆር ንጉሥ ያቢን ከጦር ተባባሪዎቹ ጋር ተደመሰሰ፡</u>

1--6 ያቢን ያስተባበራቸው ነገሥታት የሠራዊታቸው ብዛት እንደ ባሕር አሸዋ ሲሆን፣ ከዚያ ሁሉ ሠራዊት ጋር እጅግ ብዙ ፈረሶችና ሠረገላ



www.ethiopianorthodox.org

ዎችም ነበሩዋቸው። እግዚአብሔር ግን፣ ኢያሱን እንዲህ አለው፣ ‹‹ይህን የምታየውን የሠራዊት ብዛት ከምንም አትቍጠረው፤ እኔ ራሴ ስለ ሕዝቤ ስለ እስራኤል እዋጋለሁ፤ ነገ ይህን ጊዜ ሁሉንም እደመስሳቸዋለሁ። አንተም የፈረሶቻቸውን ቋንጃ ቈራርጠህ ትጥላለህ፤ ሠረገላዎቻቸውንም በእሳት ታጋያለህ (ታቃጥላለህ)'፡ ( የዚህ ምዕራፍ ቀሪው ክፍል የእስራኤል ነገዶች ተዋግተው ያስለቀቁትን አገር እንዴት ተከፋፍለው እንደያዙ የሚያስረዳ ነው 23 ) ። 19 ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፣ ስምምነት አድርጋ በሰላም የኖረች አገር፣ ከሒታውያን ወገን ጥቂቶቹ የሚኖሩባት የገባዖን ምድር ብቻ ስትሆን፣ ሌሎቹ በሙሉ
በጦርነት ድል ኾነው የተያዙ ነበሩ። 22 ከዓናቅ (ረአይት)ዝርያዎች በእስራኤል ምድር የተረፈ አልነበረም፤ ነገር ግን፣ ጥቂቶች ብቻ በጋዛ፣ በጋትና በአስቀሎና ይኖሩ ነበር።

## ፲፪ /12፡ ኢያሱ የደመሰሳቸው ነገሥታት በሙሉ ሠላሳ እንደ ነበሩ፡

ቍጥር 24፡ ( የዚህ ምዕራፍ 12 ቀሪው ክፍል ቀደም ሲል ሙሴ ከዮርዳኖስ ማዶ (በገለዓድ) የደመሰሳቸው ነገሥታት አወዳደቅ ተጠቅሶ፣ አሁን ደግሞ በመሐል አገር ገብቶ ኢያሱ ድል የነሣቸው የሠላሳ አንዱ ነገሥታት ስም ዝርዝር ተጽፎ ይገኛል።)

## ፲፫ /13፡ መወረስ የነበረበት፣ ሆኖ ገና ያልተያዘው ምድር፤

1–7-እግዚአብሔር -ኢያሱን ‹‹ሊያዝ የሚገባው ገና ብዙ ምድር ቀርቶአል፤ አንተ ግን ሸምግለሃል።አምስት የፍልስጥኤም ነገሥታት በጋዛ፣ በአሽዶድ፣ በአስቀሎና፣ በጋትና በዔቅሮን ይኖራሉ›› አለው።(ቀሪው የዚህ ምዕ. ታሪክ በድል የተያዘው አገር ለዘጠኙ ነገድ ተኩል እንዴት እንደ ተከፈለ ያሳያል") ።(*ትርጓሜ፡ ገና ሳይያዝ ተቀረው ብዙ ግዛት እስከ ዛሬ ድረስ በመላው ዓለም ዙሪያ ወንጌል ሳይሰበክለት ተቋርጦ የቆየውን ሀገርና ማኅበረሰብ ሁሉ ያመለክያል። ስለዚህም የእግዚአብሔር መንፈስ ዛሬም "ወደ ዚያ ሕዝብ ማንን ልላክ" እያለ ነው (ኢሳ 6፡ 8 )።*

## ፲፬ /14፡ ኬብሮን ለታላቁ አርበኛ ለካሌብ የተሰጠችበት ሁኔታ፡

6--15 ትውልዱ ከነገደ ይሁዳ የሆነ፣ የዮፎኒ ልጅ ካሌብ ወደ ኢያሱ ቀርቦ እንዲህ አለው፤ ‹‹እግዚአብሔር በአገልጋዩ በሙሴ አማካይነት ስለ አንተና ስለ እኔ የተናገረውን ታስታውሳለህ፤ በቃዴስ በርኔ በነበርንበት



ጊዜ፣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሙሴ የዚያችን ምድር ኹኔታ ለማጥናት ሲልከኝ እኔ የአርባ ዓመት ጕልማሳ ነበርኹ፡ ለአምላኪ ለእግዚአብሔር ታማኝ (ታዛኘር) ኾኜ በማገልገሌ፤ በእግሬ የረገጥሁአት ምድር ለእኔና ለልጆቼ ለዘለዓለም ርስት እንድትኾን ሙሴ ቃል ገብቶልኛል፣ እግዚአብሔርም ይህን ቃል በሙሴ አማካይነት ከተናገረ እነሆ፣ አርባ አምስት ዓመት አልፎአል። እግዚአብሔር በሰጠኝ የተስፋ ቃል መሠረት እነሆ፣ በሕይወት ጠብቆኝ እስከ አሁን አቈይቶኛል። እስኪ ተመልከተኝ፤ እንግዲህ አሁን የሰማኒያ ዓመት ሰው እመስላለሁን ? ይሁን እንጂ፣ አህንም ያለኝ ብርታትና የጕልበት ጽናት፣ ሙሴ እኔን በላከበት ዘመን እንደነበረው ዓይነት ነው፤ አሁንም ገና ለመዋጋትም ሆነ ማናቸውንም ተግባር ለማከናወን የሚያስችል ብርቱ ጕልበት አለኝ። እንግዲህ፣ በዚያች እለት እግዚአብሔር በሰጠኝ ተስፋ መሠረት፣ ይህችን ኮረብታማ አገር (ኬብሮንን) ለእኔ ስጠኝ። አሁንም ቢኾን፣ እግዚአብሔር ከእኔ ጋር መሆን ስለሚችል፣ ዓናቃውያን (ዔናቃውያን ረአይት) ተብለው የሚጠሩትን ቁመተ-ረጃጅም ኀያላን ነቃቅዬ አባርራቸውአለሁ›› (ዘዳግ 1፥36)። ኢያሱም የዮፎኒ ልጅ ካሌብን ባረከው (መረቀው)፤ ኬብሮንንም ርስት አድርጎ ሰጠው። ኬብሮን ከዚያ በፊት ቂርያት አርባቅ ተብላ ትጠራ ነበር። ይህም አርባቅ በአናቅ ሰዎች መካከል ከኹሉ የሚበልጥ ነበር፤ከዚህ በኋላ፣ ምድሪቱ የተረጋጋችና ሰላም የሰፈነባት ሆነች፡

**፲፭/15፡** ከቍ 1—12 ያለው ክፍል ለይሁዳ ነገድ ስለ ተመደበው የርስት ይዞታ የሚናገር ነው። ካሌብ ኬብሮንና ደቢርን ድል አድርጎ የያዘበት ሁኔታ 13-19 ኬብሮን ተብላ የምትጠራው የዓናቅ (ዔናቅ) አባት አርባቅ የነበረባት ከተማ ናት። ደቢር ደግሞ ቂርያት-ሴፌር ትባል የነበረች ከተማ ናት። ካሌብ፣ ‹‹ቂርያት ሴፌርን ወግቶ ለሚይዝ ሰው፣ ልጄን አክሳን በሚስትነት እድርለታለሁ›› ብሎ ተናገረ። ወዲያውኑ የካሌብ ወንድም የሆነው ከቄኔዝ የተወለደው ጎቶንያል ከተማይቱን ወግቶ ያዘ፣ ካሌብም ልጁን አክሳን ዳረለትና ምድሪቱን አወረሰው። አክሳም ባሉዋን ጎቶንያልን ‹‹አባቴ የውሃ ጕድጓድ እንዲሰጠን ጠይቅ›› ብላ መከረችው። እርሱ ለመጠየቅ ሲዘጋጅ እርሱዋው ቀደም ብላ ከበቅሎ ወርዳ፣ ‹‹አባቴ ሆይ፣ የሰጠኸኝ ምድር ደረቅ ስለ ሆነ፤ የውሃ ጕድጓድ እንድትሰጠኝ እፈልጋለሁ›› አለችው። ካሌብም ከላይና ከታች በኩል ያለውን ሁለት የውኃ ጕጓድ ሰ/ጣት። <u>ከ16 እስከ 19 ያሉት ዐራት ምዕራፎች</u> በሙሉ ስለየነገዱ ርስት አከፋፈልና ይዞታ የሚናገሩ ናቸው። ምዕራፍ \፲፰ /18 ፡ 1-2 ድል ነሥተው ምድሪቱን ከያዙ



www.ethiopianorthodox.org

በኋላ፣ መላው የእስራኤል ሕዝብ በሴሎ ተሰብስበው እግዚአብሔር የሚመለክባትን ድንኳን ተከሉ። ምዕራፍ 19 በሙሉ ለቀሩት ሰባት ነገዶች የተመደበውን የርስት ድርሻና ይዞታ ይገልጣል።

፳/20 ፡ **የመማፀኛ ከተሞች ምርጫ** ፡1-9 ከዚህ በኋላ፣ እግዚአብሔር ኢያሱን እንዲህ አለው፤«ማንም ሰው ሳያውቅ ( ሳያስበው ) በድንገት፣ ሲበቀለው ከሚፈልገው ባለ ደም ለማምለጥና ጉዳዩ በፍርድ እስኪወሰን ድረስ የሚማፀንባቸውን ከተሞች ከልሉ። በደል የሠራ ሰው፣በሸንጎ ቀርቦ ፍርድ እስከሚቀበልና በዘመኑ ያለው ሊቀ ካህናት እስከሚሞትበት ጊዜ ድረስ፣ በመማፀኛ ከተማ መቈየት ይችላል»። በዚሁ ትእዛዝ መሠረት፣ከመ ከመኻል አገር 1 ከገሊላ ቃዴስ፤2 ከተራራማው የኤፍሬም አገር ሴኬም፤ 3 ከይሁዳ ምድር ኬብሮን፤ 4 ከገለዓድ፣ ከሮቤል ግዛት ቤጼ /ቦሶር፤ 5 ከጋድ ነገድ ርስት ራሞት፤6 ከምናሴ ነገድ ይዞታ ባሳን ተመረጡ።

፳፩/21 ፡ ለሌዋውያን ካህናት የተመደቡ ከተሞች፤ 4-7 የካህኑ የአሮን ዝርያዎች የሆኑ ቤተ-ሰቦች ከይሁዳ፣ከስምዖንና ብንያም ነገዶች ግዛት ዐሥራ ሦስት ከተሞች ተከልለው ተሰጡአቸው።ለቀአት ጐሣ ከኤፍሬ፣ ከዳንና ከምዕራብ ምናሴ ዐሥር ከተሞች ተመደቡለት፡ለጌርሶን ጐሣ ከይሳኮር፣ ከአሴር፣ ከንፍታሌምና ከምሥራቅ ምናሴ ዐሥራ ሁለት ከተሞች ተሰጡ። ለመራሪ ጐሣ ቤተ-ሰቦችም ከሮቤል፣ከጋድና ከዛብሎን ግዛቶች ተከፍለው ዐሥራ ሁለት ከተሞች-ተመደቡላቸው። 41 የእስራ ኤል ሕዝብ ርስት አድርገው ከወረሱት ምድር፡ ዐርባ ስምንት ከተሞች ከነግጦሽ ምድራቸው ለሌዋውያን ተሰጡ።

፳፪ /22 ፡ ኢያሱ ከዮርዳኖስ ማዶ መጥተው ሌሎች ወንድሞቻቸው የርስት ድርሻቸውን ማግኘት እስኪችሉ ድረስ፤አብረው ሲዋጉ የነበሩትን የሮቤል፣የጋድና የምናሴን እኩሌታ ነገዶች ሲያሰናብት «አምላካችሁን እግዚአብሔርን ውደዱ፤ ፈቃዱን ድፈጽሙ። ትእዛዙን ጠብቁ፤ ለእርሱም ታማኞ ሆናችሁ በሙሉ ልባችሁ፣ በፍጹም ነፍሳችሁ አገልግሉት»፡ አላቸው። ከቍ-20—63-ያለው፣ ስለ ይሁዳ ከተሞች አመዳደብ ይገልጣል።

አስደናቂ የሆነው የመሠዊያ አሠራር ፡ 10-34 እነዚህ ነገደ-ሕዝብ፣ ከዮርዳኖስ ማዶ ወደሚኖሩበት ርስት እንደ ተመለሱ፣ በወንዙ አጠገብ ገሊሎት ተብሎ በሚጠራው ቦታ አስደናቂ የሆነ መሠዊያ ሠሩ። የእስራኤል ሕዝብ ይህን በሰሙ ጊዜ፣ ከሌሎቹ ነገዶች ተለይተው ዓመፅ ለማድረግ የተነሣሡ መስሎአቸው፣ በእነርሱ ላይ ጦር ለማዝመት እስከ



ማሰብ ደርሰው ነበር። በኋላ ግን፣ በቅድሚያ የካህኑን የአልዓዛርን ልጅ ፊንሐስን ልከው ሲያስጠይቁ እንዲህ ብለው መልስ ሰጡ፤ «ይህ መሠዊያ ለዓመፅ ተግባር የሚያገለግል አይደለም።እኛ-እርሱን-የሠራነው-በእኛና ከዮርዳኖስ-ወንዝ-ማዶ በመሐል አገር በምትኖሩት መካከል ምልክት ሆኖ እንዲኖር ነው። የእናንተ ዝርያዎች የእኛን ዝርያዎች «ከእግዚአብሔር ጋር ምን ግንኙነት አላችሁ?' እንዳይሉአቸው ለማድረግ ይጠቅማል»። ካህኑ ፊንሐስና ከእርሱ ጋር አብረው የተላኩት የነገድ አለቆች፤ ከዮርዳኖስ ማዶ የነበሩት የሁለቱ ተኩል ነገዶች ተወካዮች የሆኑ ታላላቅ ሰዎች፣ የሰጡትን መልስ ሰምተው በመደሰት እግዚአብሔርን አመሰገኑ። የሮቤልና የጋድ ነገዶች የሚኖሩበትን ምድር ለመደምሰስ-ጦርነት ስለ ማንሣት የታቀደውን ሁሉ፣ መናገር አልፈለጉም።የሮቤልና የጋድ ሕዝብም፣«ይህ መሠዊያ እግዚአብሔር ብቻ አምላክ ስለ መሆኑ ለሁላችንም ምስክር ነው» አሉ፡ ያን መሠዊያ «ምስክር» ብለው ጠሩት።

፳3 /23 ፡ ኢያሱ የተናገረው ታሪካዊ ምስክርነት፤ 10 ከእናንተ አንዱ ብቻውን ህኖ አንዱን ሺህ ጠላት ማባረር ይችላል፤ ይኸውም አምላካችሁ እግዚአብሔር ስለ እናንተ እየተዋጋላችሁ ነው። እግዚአብሔር ከሰጣችሁ የተስፋ-ቃል ሁሉ አንድም ሳይቀር እነሆ ተፈጽሞአል " ( 1 ነገ ፡፡

፳፬/24) ፡ ኢያሱ በሴኬም ያደረገው ንግግር፤ 1-2 ኢያሱ የእስራኤልን ነገዶች በሙሉ በሴኬም ሰበሰበ፤ ሽማግሌዎችን፣ የሕዝብ መሪዎችን፣ ዳኞችንና የጦር አዛገሮችን ሁሉ ጠርቶ እንዲህ አላቸው፤ «የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው፤ 13 «ከብዙ ዘመናት በፊት፣ የቀድሞ አባቶቻችሁ ከኤፍራጥስ ወንዝ ማዶ ባእዳን-አማልክትን በማምለክ ይኖሩ ነበር፤ከእነዚያ አባቶች አንዱ የአብርሃምና የናኮር አባት ታራ ነበር፤ይህ ሁሉ ድል የተገኘው በእናንተ ሰይፍና ቀስት አይደለም፤ እናንተ-በማረስ-ያልደከማችሁበትን-ለምለም-ምድርና-ያልሠራችኋቸውንም ከተሞች-መኖሪያ-አድርጌ- ሰጠሁኋችሁ። እነሆ፣ አሁን-ያልተከላች ሁትን- የወይን- ተክልና ያልደከማችሁበትን የወይራ ዛፍ ፍሬ እየተመገባችሁ ትኖራላችሁ»። 15 እንደገናም ኢያሱም ለሕዝቡ እንዲህ አለ፤«የምታመልኩት-ዛሬ-ምረጡ፤እኔና-ቤቴ-( ቤተ-ሰቤ)-ግን እግዚ. አብሔርን እናመልካለን» ። 19 እግዚአብሔር ቅዱስና ቀናተኛ አምላክ ስለሆነ፣ እናንተ እርሱን ማገልገል አትችሉም» *( እግዚአ ብሔር አንዳች ነገር እንደሚጎድለው ሆኖ በሰው እጅ አይገለገልም፡ የሐዋ ሥ 17፡ 25፡፡)*



www.ethiopianorthodox.org

የኢያሱና የካህኑ የአልዓዛር መሞት፡ -29 ከዚህ በኋላ የእግዚአብሔር አገልጋይ ኢያሱ፣ በአንድ መቶ አሥር ዓመት ዕድሜው ሞተ።የራሱ ርስት በሆነችው በተምና-ሴራሕም ተቀበረ። 31 ኢያሱ በሕይወት በነበረበት ዘመን ሁሉ፣ ሕዝቡ እግዚአብሔርን አመለኩ። ከኢያሱም ሞት በኋላ፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን ድንቅ ነገር በዓይናቸው ያዩት መሪዎች እስካሉበት ጊዜ ድረስ እርሱን በማምለክ ኖሩ። 33 የአሮን ልጅ ካህኑ አልዓዛርም ሞተ፤ በኮረብታማው በኤፍሬም አገር በምትገኘው በጊብዓ ተቀረ። **(ትርጓሜ፡** ***መስፍኑ ኢያሱ መድኅኔ ዓለም ክርስቶስ ኢየሱሱን በብዙ ንገር ይመስለዋል-።*** ***ኢያሱ (አውሴ) የስሙ ትርጉም ‹‹እግዚአብሔር አዳኝ››ማለት ሲሆን፡ ትውልዱ ከነገደ ኤፍሬም ነው ( 1 ዜና 7፡ 26–27 ) ። በአገልግሎቱ /በተልእኮውም የሙሴ የቅርብ ረዳትና ተቈርቋሪ ባለሟል የነበረ ሰው ነው ( ዘኁል 11+ 26- 27 ) ። በዚህም ታማኝነቱ የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቀራቢና ልዩ ባለሟል የነበረውን ወንጌላዊው ዮሐንስን ይመስላል*** *( ዮሐ 13። 23 -25 + ማር 9፡ 38 -41 )።*

***1ኛ ኢያሱ በአማሌቃውያን ላይ የተቀዳጀው ድል (ዘፀአ 17፡ 8-13 )***

***2ኛ ሙሴ ከሞተ በኋላ፣ በእርሱ እግር ተተክቶ የእስራኤል ዘሥጋ መሪ በመሆን የሰባቱን ነገደ-ከነዓን ነገሥታት ድል መንሣቱና ምድረ- ርስትን ማውረሱ፣ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መከራ መስቀልን ሁሉ በማሸነፍ ሠራዊተ-አጋንንትን ድል ነሥቶ፣እስራኤል ዘነፍስ ተብለው የሚጠሩ ምእመናንን ፣ የአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የመንግሥተ ሰማያት) ወራሾች እንዲሆኑ ማብቃቱን ያሳያል። ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ እየመራ ሲጓዝ፣ በኃይል ሞልቶ የነበረውን የዮርዳኖስን ወንዝ ውሃ፣ በእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ እንዲገታ አድርጎ ለማሻገር መቻሉ፣ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከአዳም ጀምሮ በዘር ሲወራረስ የመጣውን የኃጢአት ጕርፍ እንዲቋረጥ አድርጎ፣ ምእመናንን ከሞተ-ሥጋ-ወነፍስ ወደ ዘላለማዊ ሕይወት የማሸጋገሩ ምሳሌ ነው።_ኢያሱ እስከ ዕድሜው ፍጻሜ ድረስ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ እንደተገኘ ጌታችን መድኅኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በእግዚአብሔር ቤት የታመነ ሆኖ፣ እስራኤል\ ዘነፍስ የተባሉ (ምእመናን ) በእርሱ መሠረትነት ላይ የእግዚአብሔር ቤት ሆነው በቃሉ እንዲታነፁ አድርጎአል ( ኤፌ 2፡19-22 ፤ 1ቆሮ 3፡9 ። )***

''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''' ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''



# መጽሐፈ መሳፍንት

***መግቢያ*:**ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከግብጽ ባርነት ነጻ ''''''''''''''''''''''''''ወጥተው፡ዐርባ ዘመን በዓረብ ምድረ በዳ ቆይተው፡ በእግዚአብሔር ኃይለ ረድኤት፡ በኢያሱ መሪነት ወደ ተስፋይቱ ምድረ ርስት ግብተው፡ ኢያሱ ከሞተ በኋላ እስከ ሊቃነ ካህናቱ ዔሊና ሳሙኤል ዘመን 300 ዓመት ሙሉ የእግዚአብሔር ሕዝብ የተባሉ ሕስራኤልን ያስተዳድሩ ዘንድ መሳፍንትን አስነሥቶላቸዋል። ስለዚህም መሳፍንት በየተራ በተነሡበት ዘመን ሁሉ የተፈጸመውን የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ ጭምር የሚገልጥ የታሪክ መጽሐፍ ነው።ከተነሁትም መሥፍንት መካከል አንዳንዶች ኃያላን ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደካሞች ቢሆኑም ዋናው የሕዝቡ መሪ ግን ራሱ እግዚአብሔር ስለሆነ ሁሉም ኃላፊነታቸውን በአሸናፊነት ለመወጣት ችለዋል። ይህን የተመለከተ ሐዋርያ ጳውሎስ ለዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ 11፡ 32 ከኃያላኑ መስፍንት መካከል ጥቂቶቹን በመጥቀስ ሲገልጥ "እንግዲህ ምን እላለሁ ? ስለ ጌዴዎን፡ ስለ ባርቅ፡ ስለ ዮፍታሔና ሶምሶን መናገር እንዳልችል ጊዜ ያጥርብኛል በማለት ባጭሩ ደምድሞታል። _ከኢያሱ ሞት በመቀጠል ያን ሁሉ የእግዚአብሔርን ድንቅ ሥራ ያየው ትውልድ ጭምር ካለፈ በኋላ በዘመነ መሳፍንት የነበረው የእስራኤል ሕዝብ አምልኮት ቀደም ሲል ከነበሩት አረማውያን እምነት ጋር እየተቀየጠ፡ ፈጣሪያቸውን ባሳዘኑት ቁጥር ለአንዳንድ ጠላት አሳልፎ በመስጠት በጭካኔ እንዲገዙዋቸው ቢያደርግም እንደገና ንስሐ ገብተው እንዲታደጋቸው ሲለምኑት በቸርነቱ ምሕረት ከማድረግ የተቆጠበበት ጊዜ አልነበረም ።በዘመነ መሳፍንት ለነበሩ እስራኤላውያን ደንቃራ፡ ወጥመድና ብርቱ መሰናክል ሆኖባቸው የኖረ ችግር፡ በጦርነቱ ከተደመሰሱት አረማውያን ሕዝብ መካከል ከሞት ተርፈው የተማረኩትን አሽከርና ገረድ ወይም ጎረቤት አድርገው ሲኖሩ ቀስ በቀስ በተቀራረቡ መጠን በባዕድ አምልኮ እየተመረዙ በኣልና አሽረ ወይም ሞሎክ የተባሉትን የጣዖት አማልክት ለመከተል መሞከራቸው ነበር።

_አንድ ጊዜ የእግዚአብሔር መልአክ ከጌልጌላ ወደቦኪም መጥቶ ለሕዝቡ ያቀረበው ወቀሳ እንዲህ የሚል ነበር ፡-በዚህች ምድር ከነበሩ ጣዖት አምላኪዎች አረማውያን ጋር መተባበር ይቅርባችሁ፡ መሠዊያቸውን ሁሉ አፍርሱ፡ ከነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አታድርጉ' ብ



www.ethiopianorthodox.org

*አስጠንቅቂያችሁ ነበር። እኔ ከናንተ ጋር ያደረግሁትን ቃል ኪዳ አላፈረስኩም፡ እናንተ ግን ቃል ኪዳን አፍራሾች ሆናችኋል።" መልአኩ ይህን ወቀሳ ተናግሮ ሲጨርስ ሕዝቡ በመላቀስ እንባ በእንባ ተራጩ። በዚህም ምክንያት ያ ቦታ ቦኪም ተብሎ ተጠራ። መካና ወይሌ /የለቅሶ ቦታ ማለት ነው" ይላል መሳ 2፡ 1 -5 )። ከቃል ኪዳን አፍራሽነትና ከዚህ ዓይነቱ ክሥና ወቀሳ እግዚአብሔር ይሠውረን !*

,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,,

## ፩/1፡ ተማራኪው የኢየሩሳሌም ንጉሥ አዶኒ-ቤዜቅ የደረሰበት ፍዳ፡

1--7 ኢያሱ ከሞተ በኋላ፣ የእስራኤል ሕዝብ፣ ‹‹በከነዓናውያን ላይ አደጋ ስመጣል፣ ከነገዶቻችን መካከል ተቀዳሚ_ሆኖ ዘመቻውን ማን ይምራ?›› ብለው ጠየቁ። እግዚአብሔርም፣ ‹‹የይሁዳ ነገድ ተቀዳሚ ሆኖ ይዝመት፤ እኔ ምድሪቱን ለእነርሱ አሳልፌ እሰጣለሁ›› አለ። የይሁዳ ሕዝብ ከስምዖን ነገድ ጋር ዘምተው፣ እግዚአብሔር በሰጣቸው ድል ዐሥር ሺህ ሰራዊት ደምስሰው፣ የከነዓናውያንን ንጉሥ አዶኒ-ቤዜቅን ከማረኩት በኋላ፣ የእጆቹንና የእግሮቹን አውራ ጣቶች ቈረጡ። በዚህ ጊዜ አዶኒ-ቤዜቅ እንዲህ አለ፣ ‹‹እኔ ከማረክሁአቸው በኋላ የእጆቻቸውንና የእግሮቻቸውን አውራ ጣት ቈርጬ፣ ሳጕላላቸው የነበሩ ሰባ ነገሥታት ከእኔ ገበታ ሥር የወደቀ ፍርፋሪ እየለቀሙ ይመገቡ ነበር። ስለዚህም፣ እግዚአብሔር እኔ በእነርሱ ላይ የፈጸምኩትን ግፍ ቈጥሮ፣ ይህን ፍዳ በእኔ ላይ አመጣ››። -
21 ከዚያን በኋላ፣ አዶኒቤዜቅ ወደ ኢየሩሳሌም ተወስዶ እዚያው ሞተ።

***(ትርጓሜ፡*** *እንግድህ ብንየማውያን የሩካቤ ሥጋን ሥርዓት ለዋጭነት የተማሩት ከነዚሁ ከኢያቡሳውያን ዘሮች ነበር ማለት ነው። አዎ፡ በመጥፎ ልምድ ተከትበው በመኖር፡ ዘግየት ብሎ በዚሁ በመጽሐፉ መሳፍንት ከ19 እስከ 21 ባሉት 3 ምዕራፎች እንደተነገረ በሥርዓት ለዋጭነት ትውልድን የሚያስረግም ርኩሰትና ጭካኔ በተሞላበት አረማዊነት ነፍሰ ግድያ በሴት ልጅ ላይ በመፈጸማቸው ምክንያት ነበር ዘርማንዝራቸው ተጠራርጎ እስከ መጨረሻ እንዲደመሰሱ የተፈረደባቸው። )* ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

*ከብዙ መቶ ሺህ ሕዝባቸው መካከል ዘጠና ዘጠኝ በመቶው ተደምስሶ ባቸው ስድስት መቶ ሰዎች ብቻ በበረሃ ዋሻ ውስጥ ተደብቀው ተገኝተው ነበር፡ ለዘር ያህል እንዲተርፉ የሆነው። በዘመናችንም ቢሆን*



***እንደዚሁ ባህሉን፡ እምነቱን፡ ክቡር ሰብእናውን፡ ባጠቃላይ ፈሪሐ እግዚአብሔርን ካጣ ሕዝብ ጋር መጐዳኘት ለውርደትና ለቅሌት መዳረግን ማስከተሉ በሰው ዘር ታሪክ ውስጥ ትናንትም ዛሬም ሲደገም የኖረና የሚኖር ነው። መጥፎ ጓደኝነት "ግዕዘ ሠናየ የማስን " መልካሙን ጠባይና ነጻነትን ያጠፋል ተብሎ ተጽፏልና -1 ቆሮ 15፡ 33።) ከዓመፀኛ ትውልድ ጋር ተጎዳኝቶ መኖር ምን ጊዜም ቢሆን ለእልቂት፡ ለሚያሳፍር ውርደትና ለቅሌት የሚዳርግ ንው። )*** ''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

2--23 የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች ቤት-ኤልን ከመያዛቸው በፊት፣ አንድ ሰው ከከተማይቱ ሲወጣ አግኝተውት፣ ‹‹ወደዚህች ከተማ እንዴት መግባት እንደሚቻል ብትነግረን፣ ጉዳት አናደርስብህም›› ስላሉት ተባብሮአቸው ከተማይቱን ያዙ። ያም ሰው፣ ኋላ ወደ ሒታውያን ሄዶ ሲኖር፣ የሠራትን ከተማ ሎዛ ብሎ ጠራት።

### እስራኤላውያን ያልደመሰሱዋቸው ሕዝብ እንደገና ማንሰራራት፤

27-33 የምናሴ፣የኤፍሬም፣ የዛብሎን፣ የአሴርና የንፍታሌም ነገዶች በየርስታቸው የነበሩትን ከነዓናውያን ጨርሰው ሳያጠፉ፣ ከቀሪዎቹ ጋር ተባብረው መኖርን ቀጠሉ። 14 ከዚህም የተነሣ፣ አሞራውያን አንሰራር ተው የዳንን ነገድ ሕዝብ ወደ ኮረብታማው አገር አባረሩአቸው።

2--23 የኤፍሬምና የምናሴ ነገዶች ቤት-ኤልን ከመያዛቸው በፊት፣ አንድ ሰው ከከተማይቱ ሲወጣ አግኝተውት፣ ‹‹ወደዚህች ከተማ እንዴት መግባት እንደሚቻል ብትነግረን፣ ጉዳት አናደርስብህም›› ስላሉት ተባብሮአቸው ከተማይቱን ያዙ። ያም ሰው፣ ኋላ ወደ ሒታውያን ሄዶ ሲኖር፣ የሠራትን ከተማ ሎዛ ብሎ ጠራት።

### እስራኤላውያን ያልደመሰሱዋቸው ሕዝብ እንደገና ማንሰራራት፤

27-33 የምናሴ፣የኤፍሬም፣ የዛብሎን፣ የአሴርና የንፍታሌም ነገዶች በየርስታቸው የነበሩትን ከነዓናውያን ጨርሰው ሳያጠፉ፣ ከቀሪዎቹ ጋር ተባብረው መኖርን ቀጠሉ። 14 ከዚህም የተነሣ፣ አሞራውያን አንሰራርተው የዳንን ነገድ ሕዝብ ወደ ኮረብታማው አገር አባረሩአቸው።

**፪/2፡** <u>የእግዚአብሔር መልአክ ወቀሳ በቦኪም፡</u> 1-5 የእግዚአብሔር መልአክ ከጌልጌላ ወደ ቦኪም መጥቶ ሕዝቡን ሲወቅስ እንዲህ አለ፣ ‹‹እነሆ፣ እኔ ከግብጽ ምድር- አውጥቼ ለቀድሞ አባቶቻችሁ ልሰጣቸው ወደ ማልሁላቸው ምድር አመጣኋችሁ፣‹‹ከእናንተ ጋር የገባሁትን ቃል ኪዳ አላፈርስሁም፤ እናንተ በዚህች ምድር ከሚኖሩ ሕዝብ ጋር ምንም ዓይነት ስምምነት አታድርጉ፤ መሠዊያቸውን ሁሉ አፍርሱ እንጂ›› አልሁ። እናንተ ግን ቃሌን መስማትን እምቢ አላችሁ ፡ እንግዲህ፣ እነዚህን



www.ethiopianorthodox.org

ሕዝብ ሁሉ ልደመስስላችሁ አልፈቅድም። ስለዚህ፣ እነርሱ ለእናንተ ብርቱ ጠላቶች ሲሆኑ፣ ባዕዳን አማልክቶቻቸውም ወጥመድ ይሆኑባችኋል››።መልአኩ ይህን ሁሉ የወቀሳ ቃል ተናግሮ ሲጨርስ፣ ሕዝቡ ምርር ብለው አለቀሱ። የዚያ ቦታ ስም ቦኪም (ማልቀሻ) ተባለ። በዚያም ለእግዚብሔር መሥዋዕት አቀረቡ። 10 እነሆ፡ የእግዚብሔርን ድንቅ ሥራ ህሉ አይቶ የነበረ ያ ሁሉ ትውልድ ሞተ። ከዚያ ቀጥሎ፣ እግዚብሔር ለቀድሞ አባቶቹ ያደረገላቸውን ድንቅ ሥራ ሁሉ የማያውቅ ሌላ አዲስ ትውልድ ተነሣ። እስራኤል እግዚአብሔርን ማምለክ ትተው፣ በኣልና አስታሮት ተብለው-የሚጠሩትን-ሌሎች-ባዕዳን-አማልክትን-ማገልገል-ሲጀምሩ ግዚአብሔር በረድኤት ተለያቸው። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ራሱ የደመሰሰላ ቸው የጠላት ርዝራዦች ሁሉ፣ እንደ ገና በማንሰራራት ከየአቅጣጫው ተነሡባቸው። ወደ ጦርነት በዘመቱ ቍጥር፣ግንባራቸው መታጠፍ ጀመረ፤ አምላካቸው እግዚአብሔር በእነርሱ በደል ተቈጥቶ፣ ጠላቶቻቸው እንዲበረቱባቸው አደረገ።

፫/3፡ ምንም ቢበድሉት እግዚአብሔር ሕዝቡን አልረሳም፤

1-6 እግዚአብሔር አምላክ የአረማውያን ተረፈ-ሕዝብ ( ርዝራዥ) እንዲኖር የፈቀደበት አንዱ ምክንያት፣ የጦርነት ስልት ያልተማሩ እስራኤላውያን ከእነርሱ ጦርነትን መማር- እንዲችሉ- ሲሆን፣ ሁለተኛው- ምክንያት፣ ሕዝበ-እስራኤል የተሰጧቸውን ትእዛዛት ማክበርና አለማክበራቸውን መፈተኛ እንዲህኑ ፈቅዶ ነው።

*(**ትርጓሜ፡** የሰይጣን ዲያብሎስ ኃይል፣ በቀራንዮ መስቀል ላይ ተመትቶ ድል ሆኗል። ነገር ግን፣ በክርስቶስ አምነን፣ በወንጌሉ ቃል ፀንተን ለመኖር መቻልና አለመቻላችንን መለኪያ የሚሆን ፈተና ለማምጣት የተዘጋጁ፣ የርኩሳን መናፍስት ርዝራዦች የሚያካሂዱት የደፈጣ ጦርነት እንጂ፣ ቀዋሚና ሕጋዊ ሆኖ የታወጀ ጦርነት (Conventional war ) ዛሬ በእኛ በክርስቲያኖች ላይ የለም ።)*

የዖትንዔል አነሣሥ፡ 7-11 የእስራኤል ሕዝብ በኣልና አሸራ ለተባሉት አማልክት በመስገዳቸው-ምክንያት፣እግዚአብሔር-ተቈጥቶ-የመሶጶጣሚያ-ንጉሥ-በሆነው በኵሰር ሰቴም እጅ እንዲወድቁ በማድረግ፣ ስምንት ዓመት ገዛቸው። የእስራኤል ልጆች እንደ ገና ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመሩ። የእግዚብሔርም መንፈስ የካሌብ ታናሽ ወንድም ልጅ በሆነው፣በቄኔዝ ልጅ በዖትንኤል ላይ ወረደ፤ እርሱም ኵሻን ወይም ኵሰርሰቴም ሸዓታይም



እንዲኖር የፈቀደበት አንዱ ምክንያት፣ የጦርነት ስልት ያልተማሩ እስራኤላውያን ከእነርሱ ጦርነትን መማር- እንዲችሉ-ሲሆን፣ ሁለተኛው- ምክንያት፣ ሕዝበ-እስራኤል የተሰጧቸውን ትእዛዛት ማክበርና አለማክበራቸውን መፈተኛ እንዲህኑ ፈቅዶ ነው።

(ትርጓሜ፡ የሰይጣን ዲያብሎስ ኃይል፣ በቀራንዮ መስቀል ላይ ተመትቶ ድል ሆኗል። ነገር ግን፣ በክርስቶስ አምነን፣ በወንጌሉ ቃል ፀንተን ለመኖር መቻልና አለመቻላችንን መለኪያ የሚሆን ፈተና ለማምጣት የተዘጋጁ፣ የርኩሳን መናፍስት ርዝራዦች የሚያካሂዱት የደፈጣ ጦርነት እንጂ፣ ቀዋሚና ሕጋዊ ሆኖ የታወጀ ጦርነት (Conventional war ) ዛሬ በእኛ በክርስቲያኖች ላይ የለም ።)

የዖትንዔል አነሣሥ፡ 7-11 የእስራኤል ሕዝብ በኣልና አሸራ ለተባሉት አማልክት በመስገዳቸው-ምክንያት፣እግዚአብሔር-ተቈጥቶ-የመሶጶጣሚያ-ንጉሥ-በሆነው በኵሰር ሰቴም እጅ እንዲወድቁ በማድረግ፣ ስምንት ዓመት ገዛቸው። የእስራኤል ልጆች እንደ ገና ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመሩ። የእግዚብሔርም መንፈስ የካሌብ ታናሽ ወንድም ልጅ በሆነው፣በቄኔዝ ልጅ በዖትንኤል ላይ ወረደ፤ እርሱም ኵሻን ወይም ኵሰርሰቴም ሸዓታይም
የተባለውን ንጉሥ ድል ነሥቶ ዐርባ ዓመት መራቸው።...

የኤሑድ ምሥፍና፤ 15--30 እንደ ገናም፣ ከሞዓባውያን ንጉሥ ከዔግሎን እጅ የሚያድናቸውን ኤሑድን ከነገደ ብንያም አስነሣላቸው፤ እርሱም ግራኝ ነበር። የእስራኤል ሕዝብ ኤሑድን ግብር አስይዘው ወደ ሞዓብ ንጉሥ ወደ ዔግሎን ላኩት። ኤሑድም ከሁለት ወገን ስለት ያላት ጩቤ በቀኝ ጐኑ በኩል ታጥቆ ነበር። ለንጉሡ ያመጣውንም ግብር ካስረከበ በኋላ፣ ‹‹ለንጉሥ በግል የማቀርበው ምሥጢራዊ ጉዳይ አለኝ›› አለ። ዘብ ጠባቂዎችና አገልጋዮች እንዲወጡ ከተደረገ በኋላ፣ ወደ ንጉሡ ቀርቦ ጩቤውን አውጥቶ በሆዱ ላይ ሲሸጥበት፣ እስከ እጀታው ወደ ሆድ-እቃው ዘልቆ የገባውን ጩቤ ሳይነቅል፣ የፊት-ለፊቱን ዋና በር ዘግቶ፣ በኋላ በር ተሾልኮ ሄደ። ከዚያ ወደ ተራራማው የኤፍሬም አገርገብቶ መለከት በመንፋት ሕዝቡን ለጦርነት የሻምጋር ምሥፍና ፡ 31 ከኤሑድ ቀጥሎ የተነሣው መሪ የዓናት ልጅ ሻምጋር ነው። እርሱ 600 ፍልስጥኤማውያንን በበሬ መንጃ በመግደል፣የእስራኤን ሕዝብ የታደገ ጀግና ሰው ነበር።

4/4፡ ነቢዩቱ ዲቦራና የባርቅ ድል፡ 1-3 ኤሑድ ከሞተ በኋላ፣ የእስራኤል ሕዝብ እንደ ገና በሠሩት በደል-ምክንያት እግዚአብሔር ተቈጥቶ፣ በሐጾር ከተማ ለከነዓናውያን ንጉሥ ለያቢን-አሳልፎ ሰጣቸው፤የርሱም



www.ethiopianorthodox.org

ሠራዊት አዛገ፣ ሲሣራ ተብሎ የሚጠራው የሐሮሼት ከተማ ነዋሪ ነበር። ዘጠኝ መቶ ሠረገላ የነበረው ንጉሥ ያቢን፣ እስራኤልን በጭካኔና በዓመፅ ለኻያ ዓመት ገዛቸው። 4-1 የላጲደት ሚስት የነበረችው ነቢዪት ዲቦራ፣ በዘንባባ ዛፍ ሥር ተቀምጣ ፍርድ በመስጠት፣ የእስራኤልን ሕዝብ ትመራ ነበር። እርሱዋም ከንፍታሌም ወገን ወደ ሆነው ወደ ባርቅ ልካ አስጠራችውና፣ ‹‹ዐሥር ሺህ ሠራዊት መርጠህ፡ /መልምለህ፡ ውሰድና በታቦር ተራራ ላይ ዐሥፍር› ብሎ እግዚአብሔር አዝዞሃል››አለችው። ባርቅ፣ ‹‹አንቺ አብረሽኝ የምትዘምቺ ከሆነ እሺ እዘምታለሁ፤ አንቺ ከእኔ ጋር ካልዘመትሽ ግን አልሄድም›› ሲል መለሰላት። ዲቦራም፣ ‹‹በእርግጥ እኔ ከአንተ ጋር እዘምታለሁ፤ ነገር ግን፣ የምትመራው ዘመቻ ለአንተ ብዙ ክብር አይጨምርልህም። ምክንያቱም፣ እግዚአብሔር የጠላታችን ሠራዊት መሪ የሆነውን ሲሣራን በሴት እጅ እንዲሞት ያደርገዋል›› አለችው። ከዚህ በኋላ፣ ባርቅ ከንፍታሌምና ከዛብሎን ነገዶች የተመረጠ ዐሥር ሺህ ሠራዊት አስከትሎ፣ ዲቦራም አብራው ዘመተች።

11-16 በዚያኑ ወቅት፣ ቄናዊው ሔቤር፣ የሙሴ አማት፣ የሆባብ ዝርያዎች ከሆኑት ከቄናውያን ነጠል ብሎ በቀዴሽ አጠገብ በጻዕናይም በሚገኘው ዋርካ ዛፍ አጠገብ ድንኳኑን ተክሎ ይኖር ነበር።የአቢኒሔም ልጅ ባርቅ ወደ ታቦር መውረዱን ሲሰማ፣ ሲሣራ ዘጠኝ መቶ ሠረገላውንና ሠራዊቱን ወደ ቂሶን ወንዝ አዘመተ። ዲቦራም ባርቅን፣‹‹እግዚብሔር ሲሣራን_በእጅህ አሳልፎ የሚሰጥበት ቀን ዛሬ ነው። ስለዚህ ተነሥ። እነሆ እግዚአብሔር በፊትህ ወጥቷል" አለችው። ባርቅም ሠራዊቱን አስከትሎ ከታቦር ተራራ ወርዶ፡ አደጋ መጣል ሲጀምር፡ እግዚአብሔር ሲሣራን ከሠረገላዎቹና ከሠራዊቱ ጋር በአሸባሪ አደጋ ሁከት ላይ እንዲወድቁ አደረገ። ባርቅ ያን ሁሉ የብረት ሠረገላ አንከተከቶ ጣለ።

_የሐፆር ንጉሥ ያቢንም ከሔቤር ቤተሰብ ጋር ቤተሰባዊ ሰላም መሥርቶ ይኖር ስልነበር፡ ሲሣራ ሸሽቶ የሄቤር ሚስት ወደሆነችው ወደ ያኤል ድንኳን መጣ። ያኤልም ሲሣራን ልትቀበለው ወጥታ "ጌታዬ ! ና ወደ ድንኳኑ ግባ። ከቶ አትፍራ" አለችውና ሲገባ ከድንኳኑ መጋረጃ በኋላ ደበቀችው። "የምጠጣው ውኃ ስጪኝ ፡ በጣም ጠምቶኛል" ሲላት፡ ከአቁማዳ የተሠራ የወተት ዕቃዋን ከፍታ አጠጣችውና ተደብቆ ተኛ።በጣም ደክሞት ስለነበር በከባድ እንቅልፍ ላይ ሳለ፡ ያኤል የድንኳን ካስማ ይዛ፡ ኮቴ ሳታሰማ በቀስታ ወደ እርሱ ቀረበችና በጆሮ ግንዱ አስገብታ ካስማውን በመዶሻ ስትመታው ራሱ ከመሬት ጋር ተሰፋ። በዚያም ተንሣቀሎ ሞተ። ባርቅ ሲሣራን እየፈለገ ሲመጣ፡ "የምትፈልገው ሰው እዚህ አለልህ" አለችውና ሄዶ ሲመለ



ከት የድንካነኑ ካስማ በጆሮ ግንዱ እንደተቸነከረ ፡ እሬሳው ተጋድሞ አየው።

## ፭ /5፡ ነቢዪት ዲቦራና ባርቅ የተናገሩት የድል መዝሙር፡

12 የአቢናሐም ልጅ ባርቅ ሆይ ! ተነሥ፡ ምርኮህን እየመራህ ወደፊት ገሥግሥ ። 28 -30 የሲሣራ እናት በመስኮት-በኩል በዓይነ ርግብ አትኩራ-ተመለከተች።-"የልጄ ሠረገላ ምነው ዘገየ? ፈረሶችስ ለምን ፈጥነው አልመጡም? እነርሱ እኮ የሚካፈሉትን ምርኮ አግኝተው ይሆናል። ለያንዳንዱ ወታደር ሁለት ቆነጃጅት ይሰጡ ይሆናል። ለእኔም የአንገት ሐብልና በጥልፍ ሥራ ያጌጡ ልብሶችን ያመጡላኛል" አለች። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ! ጠላቶችህ ሁሉ በዚህም ዓይነት ሞት ይጥፉ። ከዚያም በኋላ ምድሪቱ ለዐርባ ዓመት ይህል ዕረፍት አገኘች።

## ፮ /6፡- ከከተማ ወደ ዋሻ፤

1-10 -የእስራኤል ሕዝብ አሁንም-እንደገና በእግዚአብሔር ፊት በደል ሠሩ። እርሱ ተቈጥቶ ለምድያማውያን አሳልፎ ሰጣቸውና ሰባት ዓመት ገዙአቸው።ከዚህ የተነሣ፣የእስራኤል ሕዝብ ከከተማ እየሸሹ በዋሻ ውስጥ መጠለልና በየኰረብታው ተጠግተው መኖር ግድ ሆነባቸው። የእህል ዘር በሚዘሩበት ጊዜ፣ ምድያማውያንና አማሌቃውያን አደጋ እየጣሉ፣ በሰብላቸውም ላይ የከብት መንጋ እየለቀቁ ያስበሉባቸው ነበር። የከብትና የአህያ መንጎቻቸውን እየነዱ ከድንኳኖቻቸው ጋር በጅምላ ተግበስብሰው ሲመጡ የአንበጣ መንጋ ይመስሉ ነበር። የግመሎቻቸው መንጋ ብዛት ሊቈጠር የማይቻል ነበር። በመጨረሻ የእስራኤል ሕዝብ ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመሩ። እርሱም በመጀመሪያ አንድ ነቢይ ልኮ ስለሠሩት በደል ሁሉ እንዲገሥፃቸው አደረገ።

የጌዴዎን አነሣሥና-ዘመነ-ምሥፍና ፤ 11-16 የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን፣ ምድያማውያን እንዳያዩት ተደብቆ፣ በወይን መጭመቂያው ቦታ ስንዴ ይወቃ ነበር። የእግዚብሔር መልአክ ተገለጠለትና፣ ‹‹አንተ ኃያልና ብርቱ- ሰው፣እግዚአብሔር- ከአንተ-ጋር-ነው› አለው፡ ጌዴዎንም፣"ጌታዬ ሆይ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ቢሆንማ ኖሮ፣ ይህ ሁሉ ችግር ( ፈተና ) እንዴት ሊደርስብን ይችል ነበር? ! አባቶቻችን እንደ ነገሩን፣ ያ ሁሉ ድንቅ ሥራው ዛሬ የታለ ?›› አለው። ከዚያን በኋላ፣ እግዚአብሔር ጌዴዎንን ‹‹ሂድ እንግዲህ ባለህ ብርቱ ኃይል እስራኤልን ከምድያማውያን እጅ መታደግ እንድትችል እነሆ፣ እኔ ራሴ ልኬሃለሁ›› አለው።



www.ethiopianorthodox.org

ጌዴዎንም መልሶ፣ «ቤተሰቤ እጅግ ደካማ ከሆነው ከምናሴ ነገድ መካከል ነው፤ እኔም በቤተሰቤ መካከል እጅግ የተናቅሁ ሰው ነኝ፤ ታዲያ፣ እንዴት አድርጌ ነው እስራኤልን መታደግ የምችል?» አለው። እግዚአብሔርም «እኔ ራሴ ስለምረዳህ ይህን ሁሉ ማድረግ ትችላለህ፤ ምድያማውያንን እንደ አንድ ሰው ያህል አድርገህ ታደቃቸዋለህ» አለው። 17-24 ጌዴዎንም፣ ይህ ትእዛዝ ከእግዚአብሔር የመጣ መሆኑን ለማረጋገጥ ምልክት ይሰጠው ዘንድ ፈልጎ፣ መሥዋዕት ለማቅረብ እንዲፈቀድለት ለመነ።

_ጌ ዴዎን በዐለት ድንጋይ ላይ ያቀረበውን የፍየል ጠቦት መሥዋዕት፣ የእግዚአብሔር መልአክ ቀረብ ብሎ በያዘው በትር ጫፍ ሲነካው፣ እሳት ከዐለቱ ድንጋይ ወጥቶ ሥጋውንም ኅብስቱንም በላ። ጌዴዎን-መሠዊያውን፣«ሻሎም -እግዚአብሔር የሰላም አምላክ» ብሎ ጠራው፡ 25--27 በዚያችው ሌሊት እግዚአብሔር ጌዴዎንን እንዲህ አለው፣ «አባትህ ለባኣል የሠራውን መሠዊያ አፍርሰው፤ በአጠገቡ ያለውን፣ የአሼራን ምስል ሰባብረህ ጣል፤ በዚያም ቦታ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አግምረህ መሠዊያ ሥራ» ብሎ አዘዘው። ጌዴዎንም የከተማውን ነዋሪዎች በመፍራት ቀኑን ሙሉ ገዥም-ብሎ ውሎ፣ የቀኑን ክፍለ ጊዜ አሳልፎ፣ በሌሊት ጨለማ ለብሶ የታዘዘውን ሁሉ ፈጸመ። ሕዝቡም ይህን ሁሉ ባዩ ጊዜ፣ በቍጣ ተሞልተው ወደ ጌዴዎን አባት ወደ ኢዮአስ መጡ፤ «ይህን ያደረገ የአንተው ልጅ ጌዴዎን ስለሆነ፣አውጥተህ ስጠንና እንገደለው» ብለው ጠየቁት፤ ኢዮአስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፣ «እንግዲህ፣ የእናንተ ጠባቂነትና ተከላካይነት ካስፈለገው፣ የበኣል አምላክነት እምነት ላይ ነው? አምላክ ነኝ የሚል ከሆነ፣ እነሆ፣ መሠዊያው ፈርሶአል፤ ምስሉም ተሰባብሮአልና፣ ጠላቱን ለይቶ ማወቅና ራሱን ለማዳን መቻል አለበት»። _ስለዚህ፣ ኢዮአስ በዚያን ቀን፣ «በኣል የሚቻለው ከሆነ ከእርሱ ጋር ይሟገት» ለማለት ልጁን ጌዴዎንን ይሩባባል" ብሎ ጠራው።

33--40 ከዚያን በኋላ፣ ምድያማውያንና አማሌቃውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው በኢይዝራኤል ሸለቆ ሠፈሩ። የእግዚአብሔር መንፈስ በጌዴዎን ላይ ስለወረደ፣ ቀንደ-መለከቱን ነፋ፤ የአቢዔዝርም ጐሣዎች ተከተሉት። ወደ ምናሴና ወደ አሴር ወደ ዛብሎንና ወደ ንፍታሌም ምድር ሁሉ መልእክተኞችን ሰደደ፤ እነርሱም ሊገናኙት ወጡ። 36–40 ጌዴዎንም እንዲህ አለ፤ «እግዚብሔር ሆይ፣ አንተ እንደተናገርህ፣ የእስራኤልን ልጆች በእኔ እጅ ለማዳን ፈቃድህ መሆኑን ለማወቅ አንድ ምልክት ስጠኝ፤ ይኸውም፣ በአውድማው ላይ የበግ ጠጉር ባዘቶ (ፀምር) እዘረጋለሁ፤ መሬቱን



ሳይነካ የዝናም ጠል በባዘቶው (በፀምሩ) ላይ ብቻ ይውረድ» እግዚአብሔርም እንዳለው አደረገለት። ጌዴዎን እንደ ገና፣ «የዝናሙ ጠል ባዘቶውን ሳይነካ በመሬቱ ላይ ብቻ እንዲወርድ አድርግልኝ» ሲል ጠየቀ፤ አሁንም እግዚአብሔር ጥያቄውን ፈጸመለት።

*(**ትርጓሜ**፡- ጌዴዎን ያቀረበውን መሥዋዕት፣ መልአኩ በያዘው በትር ጫፍ ሲነካው፣ እሳት ወጥቶ መሥዋዕቱን እንዲቃጠል አደርጎአል። እሳት የእግዚአብሔር መቅሠፍት ምሳሌ ሲሆን ፣ የመሥዋዕቱ ሥጋ የአረማውያኑ የምድያማውያንና የአማሌቃውያን ምሳሌ ነው፡ የመልአኩ በትር እነርሱን የቀጡበት የጌዴዎን ጦር ምሳሌ ነው።*

2- *ባዘቶ (ፀምር) የእስራኤል ምሳሌ ሲሆን፣ የዝናም ጠል የእግዚአብሔር ረድኤት ምሳሌ ነው። የዝናሙ ጠል በባዘቶ ላይ እንጂ፣በመሬቱ ላይ እንዳልወረደ፣-እግዚአብሔር-የሚረዳ እስራኤልን-እንጂ፣ ምድያማ-ውያንን አለመሆኑን ያሳያል፡ እንድም ባዘቶ (ፀምር) የእስራኤል ምሳሌ ሲሆን፣ የዝናም ጠል የእግዚብሔር መቅሠፍት ምሳሌ ነው። ይኸውም በሁለተኛው ጥያቄ ጠል በመሬት ላይ እንጂ፣ በባዘቶው-(በፀምሩ)-ላይ-እንዳልወረደ፡ የእግዚአብሔር መቅሠፍት በአረማውያኑ በምድያማውያን ላይ እንጂ፣* በእስራኤል ላይ አለመውረዱን ያመለክታል።

3- *በዘመነ ሐዲስ ትርጓሜ ግን፣ ባዘቶ (ፀምር) ጸጋን የተመላች የቡርክት ቅድስት ድንግል ማርያም ምሳሌ፣ የዝናም ጠል የጌታ ምሳሌ። ጠል በፀምር ላይ መውረዱ ጌታ በቅድስት ድንግል ማርያም የማደሩ ምሳሌ ነው። አንድም ባዘቶ የምእመናን፣ የዝናም ጠል የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ምሳሌ። )*

፺ /7፡ ጌዴዎን በእግዚአብሔር ኃይል የተቀዳጀው ታላቅ ድል፤

1--8 ጌዴዎን ሠላሳ ሺህ ወታደር ሰብስቦ በማሠልጠን ላይ ነበር። እግዚአብሔር ግን፣ «ድልን የማቀዳጅህ እኔ ራሴ እንጂ፣ የአንተ ሠራዊት ብዛት አይደለምና "እኛ በኀይላችን ድል አደረግን» ብለው እንዲመኩ አያስፈልግም። በመካከላችሁ ፈሪ ሰው ካለ፣ ‹ያለይ› ብለህ ንገራቸው» ሲል አዘዘው። ይህንንም ሲነግራቸው፣ ኻያ ሁለቱ ሺህ ሰዎች ወደየመኖሪያ ቦታቸው ተመልሰው ሄዱ። እግዚአብሔር፣ «አሁንም ሠራዊትህ ብዙ ስለ ሆነ፣ ወደ ሐሮድ ወንዝ አውርደህ በጉልበቱ ተንበርክኮ የሚጠጣውን ሁሉ ትተህ በአንድ እጁ መዳፉውን እንዳስገበ፣ በሌላ እጁ ውኃውን እየዘገነ የሚጠጣውን ብቻ መርጠህ አሠልፍ» አለው። በዚህም ዓይነት፣ ፈተና አልፈው የተመረጡት ሦስት መቶ ሰዎች ብቻ ነበሩ።



www.ethiopianorthodox.org

እግዚአብሔርም፣ «እንግዲህ እነዚህን ብቻ ይዘህ ዝመት፣ በእነርሱ አማካይነት እታደጋችኋለሁ››አለው። ጌዴዎንም ሌሎቹን በሙሉ አሰናብቶ፣ሦስት መቶውን ብቻ ይዞ-ለመዝመት-ተዘጋጀ። 9–18- በዚያችም ሌሊት፣ እግዚአብሔር- ጌዴዎንን፣ «ፑል ተብሎ ከሚጠራው አገልጋይህ ጋር ሆነህ፣ ወደ ምድያማውያን ሠፈር ውረድና እነርሱ የሚሉትን ስትሰማ፣ ክንድህ ትበረታለች›› አለው። ጌዴዎን እዚያ በደረሰ ጊዜ፣ አንድ ምድያማዊ ወታደር ያየውን ሕልም እንዲህ ሲል ለጓደኛው ነገረው፣ «በሕልሜ አንዲት የገብስ ቂጣ ከላይ ተንከባላ ወርዳ፣ የሠፈራችንን ድንኳን ስትመታው፤ ድንኳኑም ተገልብጦ በምድር ላይ ሲዘረጋ አየሁ››። ጓደኛውም፣ «ይህማ የእስራኤላውያን ሰይፍ የሆነው የኢዮአስ ልጅ ጌዴዎን ነው፤ ቢቃ እንግዲህ! እግዚአብሔር ለጌዴዎን በምድያም ሠራዊት ላይ ድልን ሰጥቶታል ማለት ነው›› ሲል ተረጐመለት። ጌዴዎንም ይህን እንደሰማ፣ በመጀመሪያ ለእግዚብሔር ሰገደ።ወዲያውኑም ወደ ጦር ሠፈሩ ተመልሶ፣ «እነሆ፣ እግዚአብሔር አምላክ የምድያማውያ ንን ሠራዊት ሁሉ በእጃችሁ ጥሎላችኋልና ተዘጋጁ›› ሲል ወታደሮቹን በሚያበረታታ- ን ግ ግ ር የጦር ትእዛዝ ሰጠ። ሦስት መቶውን ሠራዊት ከፍሎ፣ በሦስት ቡድን አሠለፋቸው። ለእያንዳንዱም አንዳንድ ቀንደ-መለከት ና ችቦ ያለበት የሸክላ ማሰሮ አድሎ፣ እንዲህ አላቸው፤ «እኔ ወደ ሠፈሩ ዳርቻ ስደርስ የማደርገውን በጥንቃቄ ተመልከታችሁ፣ እኔና ከእኔ ጋር የተመደቡት ሰዎች ቀንደ-መለከት ስናሰማ፣ እናንተም የያዛችሁትን የቀንደ-መለከት ድምፅ በሠፈሩ ዙሪያ እያሰማችሁ፣ «ለእግዚብሔርና ለጌዴዎን እንዋጋለን (ኃይል ዘእግዚአብሔር፡ ኵይናት ዘጌዴዎን' ብላችሁ በፉከራ (በመደንፋት) ጩኹ››፡

_19--22 እኩለ- ሌሊት ሲሆን፣ ዘብ ጠባቂዎች ከተቀያየሩ በኋላ፣ ጌዴዎንና ሠራዊቱ ወደ ጠላት ጦር ሠፈር ዳርቻ ቀርበው ቀንደ-መለከት ነፉ፣ የያዙትንም ማሰሮ ሁሉ ጥለው ሰባበሩ። በሌላውም ረድፍ የተሠለፉት፣ በእሳት የተቀጣጠሉትን ችቦዎች በግራ እጃቸው፣ ቀንደ-መለከታቸውን በቀኝ እጃቸው ይዘው፣ «የእግዚብሔር ኀይልና የጌዴዎን ሰይፍ"›› እያሉ በፉከራ (በመደንፋት) እያንዳንዱ ሰው በተመደበለት ቦታ ቆመ። በዚያች ቅጽበት፣ የጠላት ሠራዊት የዐ-ዑታ ድምፅ እያሰማ መሸሽ ጀመረ። እግዚአብሔር የጠላትን ወታደር እርስ- በርሱ በማዋጋት፣ጓደኛን በጓደኛው ላይ በጠላትነት በማነሣሣት በገዛ



ሰይፉ እንዲተላለቅ አደረገው። የተረፉትም ሁሉ ጀርባቸውን በማዞር ሸሽተው ሄዱ። 23--25. ከዚያ በኋላ፣የንፍታሌም፣የአሴርና ሁለቱ የምናሴ ነገዶች ተጠርተው ወጥተው፣ምድያማውያንን ማሳደድ ጀመሩ።የኤፍሬም ሰዎች ሔሬብና ዜብ የተባሉትን ሁለት ምድያማውያንን ባለሥልጣኖችን ማርከው፡ ራሳቸውን ቆርጠው ወደ ጌዴዎን አመጡለት።

ቋ/8 : ለደከሙ ወታደሮች፣ «እህልና ውሃ አናቀምስም›› ያሉ ሰዎች ተቀጡ፡ 4--9 ጌዴዎን፣ «ጠላትን በማሳደድ ለደከሙ ወታደሮቼ እባካችሁ እህልና-ውሃ ስጡልኝ" ሲል የስኮት ከተማ ነዋሪዎችንና የጵኒኤልን ሰዎች ቢጠይቅ፣«ለመሆኑ የምድያም መሪዎች የሆኑትን ዛብሄልና ስልማናን ማርከህ በእጅኽ አስገብተሃልን?›› ሲሉ በማፌዝ እምቢታቸውን ገለጡ። 10-12 ከበረሃ ነገዶች ከተውጣጣ አንድ መቶ ሀያ አምስት ሺህ የምድያማውያን ሠራዊት፣ አንድ መቶ ኻያው ሺህ ተደምስሶ ያመለጠው ዐሥራ አምስት ሺህ ብቻ ነበር። ጌዴዎን ዱካቸውን ተከትሎ በመገሥገሥ፣ አምልጦ በነበረው ሠራዊት ላይ አደጋ ጣለ። ከዚያም ጌዴዎን ሁለቱንም የምድያም ነገሥታት ዛብሄልና ስልማናን አሳድዶ ማረካቸው። 13-17 ጌዴዎን ከዘመቻ ሲመለስ፣ አንድ ብላቴና ከስኮት- ከተማ- ወጥቶ- ሲሄድ አገኘውና-በከተማይቱ=ስለሚኖሩት-ሰዎች ሁኔታ በመጠየቅ መረመረው፤ብላቴናውም_የሰባ ታላላቅ ሰዎችን ስም ዝርዝር ሰጠው። ጌዴዎን እነዚያን ሰዎች ሁሉ ጠርቶ- እንዲህ አላቸው፣ «ለደከሙ- ወታደሮቼ- እህል-ውሃ- ስጡልኝ- ብዬ- ብጠይቃችሁ፣ ዛብሄልንና ስልማናን ማርከህ በእጅ አስገብተሃልን ?››ብላችሁ አፌዛችሁብኝ ነበር፤እነሆ አሁን፣ዛብሄልና ስልማና በእኔ እጅ ናቸው›› አለ። ከዚያም በኋላ፣ ከበረሀ በተገኘ ኵርንችትና በአጣጥ እሾህ ገረፋቸው።ከዚያም የከተማዪቱን ሰዎች ገድሎ፤ የጵንኤልንም መጠበቂያ ግንብ አፈረሰባቸው።

_18--21 ጌዴዎን፣ ዛብሄልና ስልማናን አቅርቦ፣ «ለመሆኑ፣ በታቦር የገደላችሁአቸው ሰዎች ምን ዓይነት ነበሩ?››ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፣«ልክ እንደ አንተ የነገሥታት ልጆች ይመስሉ ነበር›› አሉት። ጌዴዎንም መልሶ፣ «እነርሱ የእናቴ ልጆች የሆኑ ወንድሞቼ ነበሩ፤ ታድያ፣ እነርሱን ማርካችሁ በሕይወት አቈይታችኋቸው ቢሆን ኖሮ፣ እኔም ዛሬ ለእናንተ ምሕረት ባደረግሁላችሁ ነበር›› አላቸው። ወዲያውም የበኵር ልጁን ዬቴርን፤ «ግደላቸው›› ሲል አዘዘው፤ ብላቴናው ግን ፈርቶ፣ ሰይፉን መምዘዝ አቃተው።ዛብሄልና ስልማና፣«የሰው ኃይሉ እንደ ሰውነቱ ነውና አንተ ራስህ ተነሥተህ ግደለን›› አሉት፤ ጌዴዎንም እነርሱን ገድሎ፣ በግመሎቻቸው አንገት ላይ የነበረውን ጨረቃ የመሰለ የወርቅ ማርዳ ሁሉ ወሰደ።



www.ethiopianorthodox.org

22--27 ከዚያም በኋላ፣ የእስራኤል ሕዝብ ጌዴዎንን፣‹‹ከምድያማውያን እጅ አድነኸናልና አንተና ልጆችህ፣ የልጅ ልጅህም ለዘለቄታ ገገርዎቻችን ሁኑ›› አሉት። ጌዴዎን ግን፣ "እኔም ሆንሁ ልጆቼ የእናንተ ገገርዎች አንሆንም፤ ገገርአችሁ እግዚአብሔር ይሆናል››።ከዚህስ ይልቅ፣ የማረካችሁትን የወርቅ ጕትቻ ስጡኝ›› አላቸው። ምድያማውያን የእስማኤል ዘሮች ስለ ነበሩ፣ በጆሮአቸው ላይ የወርቅ ጕትቻ የማንጠልጠል ልምድ ነበራቸውና። ወዲያውኑ ጋቢ ዘርግተው ኻያ ኪሎ ግራም ያህል የሚመዝን የወርቅ ጕትቻ ሰብስበው አስረከቡት። ጌዴዎንም ያንን ወርቅ ኤፉድ አድርጎ አሠራውና በትውልድ ከተማው በኦፍራ አኖረው። እስራኤላውያንም ያንን ከወርቅ የተሠራ ኤፉድ እንደባዕድ-አምላክ አድርገው በመከተል አመነዘሩበት፣ ይህም ለጌዴዎንና ለቤተ-ሰቡም ሁሉ መጥፋት መሰናከያ ወጥመድ ሆኖባቸው ቀረ።

## ፱/9፡ ከጌዴዎን ሞት በኋላ በባዕድ-አምልኮት መስፋፋት የሕዝቡ እልቂት፡

1--6 ከጌዴዎን ልጆች አንዱ አቤሜሌክ፣ ወደ ሴኬም ሄደ፣ ለእናቱ ቤተ-ሰቦችና ለሌሎቹም ነዋሪዎች-እንዲህ-አላቸው፤‹‹ሰባ-የሆኑት-የጌዴዎን-ልጆች-ሁሉ ቢገዙአችሁ? ወይስ አንድ ሰው ብቻ ቢገዛችሁ ይሻላችኋል? እኔ ደግሞ የሥጋ ዘመዳችሁ መሆኔን አትርሱ››። ይህንም ብሎ በማሳደም ዘመዶቹን ሁሉ አስተባበረ። እነርሱም አቤሜሌክን ደገፈው፣ በኣል-ብሪት ተብሎ የሚጠራውን ጣዖት ከሚያመልኩበት ቤት አውጥተው ሰባ ጥሬ ብር ሰጡት፤ እርሱም በዚያ ገንዘብ ጥቂት ነፍሰ-በላዎችን /ገዳዮችን ቀጥሮ ተከታዮቹ አደረጋቸው። ከእነርሱም ጋር አብሮ ወደ አባቱ ወደ ጌዴዎን ከተማ ወደ ኦፍራ ሄደ፤ ከዚያም ሰባውን ወንድሞቹን በአንድ ድንጋይ ላይ አጋድሞ አረዳቸው። ከእነርሱ መካከል ተደብቆ ለማምለጥ የቻለ ኢዮአታም የተባለው የጌዴዎን የመጨረሻ ታናሽ ልጁ ብቻ ነበር። ይህንም ሁሉ ካደረገ በኋላ፣ የሴኬምና የቤት-ሚሎ ሰዎች ሁሉ በአንድነት ተሰብስበው፣ በአንድ የአድባር ዛፍ ሥር አቤሜሌክን አነገሡት።

7-21 ከዚያም፣ ከጌዴዎን ልጆች መካከል ከሞት ያመለጠው ታናሽ ልጁ ኢዮአታም፣ የበረከት ቃል በሚነገርበት በገሪዛን ተራራ ላይ ቆሞ በምሳሌ እንዲህ አለ፤ ‹‹የሴኬም ሰዎች ሆይ! እግዚአብሔር እንዲሰማችሁ ስሙኝ፣እነሆ፣አንድ ጊዜ ዛፎች ተሰብስበው ወይራን፣ ‹‹በእኛ ላይ ንገሥና አስተዳድረን›› አሉት። ወይራ ግን፣ ‹ሰዎች የሚከብሩበትን ዘይቴን ትቼ በእናንተ ላይ መንገሥ አልፈልግም› አላቸው። በለስን ‹ንገሥልን›



ቢሉት፣ ‹ጣፋጭ ፍሬዬን ትቼ መንገሥ አልፈልግም› አላቸው፤ ወይንም ተጠይቆ፣ ‹ደስ የሚያሰኝ የወይን ጠጄን ትቼ፣ በእናንተ ላይ መንገሥ አልፈልግም" አላቸው።በመጨረሻም ወደ አጣጥ እሾህ ሄደው፣ ‹‹ንገሥልን››ብለው_ጠየቁት።እርሱም-‹‹እንግዲህ_በርግጥ-ልታነግሡኝ ከፈለ ጋችሁ፣ መጥታችሁ በጥላዬ ሥር መጠለያ አግኙ፣ ይህን ባታደርጉ ግን፣ ከእሾኻማ ቅርንጫፎቼ እሳት ወጥቶ የሊባኖስን ዝግባዎች ያቃጥላል›› ሲል አስጠነቀቃቸው። እናንተም የሴኬም ሰዎች እንደዚሁ፣ አቤሜሌክን አንግሣችኋል። አባቴ ጌዴዎን ስለ እናንተ ተጋዳይ ዐርበኛ ሆኖ ከምድያማውያን እጅ እንዴት እንደታደጋችሁ ታውቁ ነበር። አሁን ግን ያን ሁሉ ውለታ ረስታችሁ፣ ሰባውን ልጆቹን በአንድ ድጋይ ላይ አሳርዳችኋል፤ ወንድማችሁ ስለ ሆነ፤ ከቁባት ዲቃላ ሆኖ የተወለደውን አቤሜሌክን አንግሣችኋል። እንግዲህ-ከአቤሜሌክ እሳት ይውጣ፤ የሴኬምን ሰዎችና ቤት-ሚሎን ይብላ›› በማለት ምሳሌያዊና ትንቢታዊ የመርገም ቃል ተናግሮ ተሰወረ፡50-56 እነሆ፣ በዚህ ዓይነት ዓመፅ አቤሜሌክ በእስራኤል ላይ ነግሦ፣ ሦስት ዓመት ከገዛ በኋላ፣ ራሳቸው የሴኬም ሰዎች ዐመፁበት፤ ስለዚህ፣ ሕዝቡን በጭካኔ ጨፍጭፎ አጥፍቶ፣ የሴኬምን ምድር ጨው ዘራባት። ከሞት የተረፉት የከተማይቱ ሽማግሎች በኣል-ብሪት-በሚባለው ቤተ-ጣኦት ውስጥ ተሸሽገው ( መሸ ገው) ነበር። አቤሜሌክም ይህን ሲሰማ፣ የማገዶ እንጨት አከማችቶ፣ የደመራ እሳት በማንደድ አጋያቸው። እንደ ገናም፣ በከተማይቱ የነበረውን የመጠበቂያ ግንብ፣ በእሳት ለማቃጠል ጠንክሮ ሲዋጋ ሳለ፣ አንዲት ሴት የወፍጮ ስባሪ ወርውራ መሐል አናቱን ጨፈለቀችው። አቤሜሌክም፣ ‹‹ሴት ገደለችው›› ተብሎ መዘባበቻ እንዳይሆን በማሰብ፣ ከጋሻ-ጃግሬዎቹ አንዱን ጠርቶ፣ ‹‹ሰይፍህን ምዘዝና ግደለኝ›› ብሎ አዘዘው፤ ጋሻ-ጃግሬውም ሕይወቱን ጨረሰለት። እነሆ፣ በዚህ አይነት ሁኔታ፣ አቤሜሌክ የገዛ ወንድሞቹን በመግደል፣ በአባቱ ቤተ-ሰብ ላይ ስለ ፈጸመው ግፍ፣ እግዚአብሔር ይህን ውርደት አመጣበት።57 የሴኬም ሕዝብም፣ በዘረኛነት ስለ ፈጸሙት ደባ፣ የጌዴዎን የመጨረሻ ልጁ ኢዮአታም የተናገረው መርገም በእነርሱ ላይ ተፈጸመ። ራሱ እግዚአብሔር ያን ሁሉ ፍዳ በእነርሱ አናት ላይ እንዲከነበል አድርጎታልና። ፲ /10 ፡1-2 አቤሜሌክ ከሞተ በኋላ፣ ከይሳኮር ነገድ የሆነው፤ ቶላ የሚባል መስፍን ተነሥቶ፣ እስራኤልን ኻያ ሦስት ዓመት ገዛ። 3-5 ከቶላ ቀጥሎ ደግሞ፣ በሠላሳ አህያ ተቀምጠው የሚጋልቡ ሠላሳ ወንዶች ልጆች የነበሩት፣ የገለዓድ ተወላጅ የሆነው ኢያእር፣ ኻያ ሁለት



www.ethiopianorthodox.org

ዓመት አስተዳደራቸው። አሁንም ከነጻነት ወደ ባርነት፤ ተመልሰው፡ 6--9 በኣልና አስታሮት የተባሉትን ባዕዳን-አማልክት ከመከተል አልፈው፤ የሶርያንና የሲዶናን፣ የሞዓብንና የአሞንን፣ የፍልስጥኤምንም አማልክት መከተል ቀጠሉ። በዚህም ሁሉ እግዚአብሔር ተቈጥቶ ፍልስጥኤማውያንና አሞናውያን የእስራኤልን ልጆች ድል ነሥተው እንዲገዙዋቸው አደረገ። እነርሱም-በገለዓድ-የሚኖሩ እስራኤላውያንን ዐሥራ-ስምንት ዓመት ሙሉ ጨቍነው በመግዛት ብዙ ግፍ ፈጸሙባቸው። 10-16 ከዚህ በኋላ የእስራኤል ሕዝብ፣ «አንተን አምላካችንን ትተን፣ እነዚህን ሁሉ ባእዳን-አማልክት በመከተል በደል ሠርተናል፤ ይቅር በለን» ብለው ወደ እግዚአብሔር ጮኹ። እግዚብሔር ግን፣ «ከአሁን በኋላ የእናንተን ጩኸት አልሰማም፤ ወደ መረጣችኋቸው አማልክት-ሂዱ፤እነርሱ ያድኗችሁ» ሲል-ፊቱን አዙሮባቸው ቈይቶ ነበር። ነገር ግን፣ ባዕዳን-አማልክትን አስወግደው እግዚአብሔር ራሱ ያድናቸው ዘንድ በብርቱ ተማጠኑ። የደረሰባቸውን ግፍና ውርደት፣ የመከራቸውንም ብዛት አይቶ፣ እግዚአብሔር እንደ ገና በመራራት አዘነላቸው።

፲፩ /11 :<u>የመስፍኑ የዮፍታሔ አነሣሥ፡</u> 1--6 የዮፍታሔ አባቱ ገለዓድ የሚባል ኤፍሬማዊ ነው። ከቁባት የተወለደ ዲቃላ በመሆኑ፣ የገዛ ወንድሞቹ፣ «ከእኛ ጋር ርስት መውረስ አይገባህም» ብለው አሳዝነውት ካባቱ ቤት ተባርሮ ወጥቶ ነበር። ከወንድሞቹ ሸሽቶ፣ ጦብ ተብላ በምትጠራ ምድር ኑሮውን መሠረተ። በዚያም ጥቂት ነፍሰገዳዮችን ሰብስቦ፣ የእነርሱ አለቃ በመሆን በሽፍትነት ኖረ። ከጥቂት ጊዜም በኋላ፣ አሞናውያን እስራኤልን ለመውጋት ዘመቱ።ስለዚህ፣ከወንድሞቹ ከኤፍሬማውያን ጋር-በገለዓድ-ምድር የነበሩ የሕዝብ ሽማግ-ሎች፣ዮፍታሔን ከጦብ ለማስመጣት ሄደው፣ «አሞናውያንን ለመውጋት እንድንችል መጥተህ የእኛ መሪ እንድትሆን እንፈልጋለን» ብለው ማለዱት። 11 ዮፍታሔ ግን፣ «እናንተ እኔን ጠልታችሁ ከአባቴ ቤት እንድባረር አድርጋችኋል፤ ታዲያ አሁን፣ ችግር ሲገጥማችሁ መምጣታችሁ ስለ ምንድነው?» አላቸው። እነርሱም፣ «አሞናውያንን አብረን ወግተን ድል ብናደርግ የእኛ መሪ ትሆናለህ» ብለው በእግዚአብሔር ስም ስለማሉለት፣ ከእነርሱ ጋር ወደ ምጽባ መጣ፤ መስማማቱንም በእግዚአብሔር ፊት-ገለጠ። 12-28 ከዚህ በኋላ፣ ዮፍታሔ ወደ አሞን ንጉሥ መልክተኞች ልኮ እንዲህ አለው፣ «በዚህ አንተ የእኔ ነው በምትለው አገር የነበሩ አሞራውያንን ያስወጣና ለእስራኤል ያወረሰ፣ የእስራኤል አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ነው። አንተ አምላክህ ኮሞሽ የሚያወርስህን አገር-ፈልግ፤ እኛም አምላካችን የሰጠንን



አገር ወርሰን እንኖራለን። እስራኤላውያን ይህን አገር ከያዙ ሦስት መቶ ዓመት አልፎአል፤ ታዲያ አንተ፣ አገሬን ወሰዱ የምትለው እውነት ከሆነ፣ ለምን እስከ ዛሬ ማስመለስ አልቻልክም? እንግዲህ እኔ ሳልበድልህ በእኔ ላይ ጦርነት ለመክፈት የተነሣሣህ አንተ ራስህ ነህ፤ስለዚህም ፈራጅ እግዚአብሔር ነው። እርሱ ዛሬ በእስራኤልና በአሞን ሕዝቦች መካከል ፍርድ ይሰጣል»። አሞን ንጉሥ ግን፣ይህን-መልእክት በማቃለል እምቢተኛነቱን ገለጠ። 29-32 በዚያን ጊዜ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ በዮፍታሔ ላይ ልዩ ኀይል አሳደረበት። ዮፍታሔም በገለዓድና በምናሴ መካከል አለፈ፤ ወደ ምጽባም ተመልሶ፣ ወደ አሞን ጕዞውን ሲቀጥል፤ ለእግዚአብሔር እንዲህ ሲል ተሳለ፤ «በአሞናውያን ላይ ድልን ብታቀዳጀኝ፣ ከዘመቻ ስመለስ፣ በመጀመሪያ_ሲቀበለኝ-የሚወጣውን፣ለአንተ-መሥዋዕት-አድርጌ አቀርበዋለሁ»። ዮፍታሔም ጦርነት በገጠመ ጊዜ፣እግዚአብሔር አሞናውያንን በእጁ-ጥሎለት ድል አደረገ። በጠቅላላ ኻያ ከተሞችን አስለቅቆ ያዘ። ድል አድርጎ ሲመለስም፣ ለአባትና ለእናትዋ አንዲት ብቻ የሆነች ሴት ልጁ፣ ከበሮ ይዛ እየጨፈረች ልትቀበለው ወጣች። ዮፍታሔም ደንግጦ፣ «ዛሬ ገና ተዋረድሁ፤ መጀመሪያ ወጥቶ የሚቀበለኝን ለእርሱ መሥዋዕት አድርጌ ላቀርብ ወስኛለሁ፤ ስለዚህም፣ መሥዋዕት ሆነሽ መቅረብሽ የማይቀር ነው» አላት። እርሱዋም፣ «‹እግዚአብሔር በአሞናውያን ላይ ድልን ያቀዳጀህ ስለ ሆነ፣ ለእኔ በመራራት ወደ ኋላ ሳትል፣ ስእለትህን ፈጽም፤ ወደ ተራራ ወጥቼ ስለ ድንግልናዬ የማለቅስበት የሁለት ወር ጊዜ ብቻ ስጠኝ» አለችው። እርሱዋም ገና ድንግል እንደ ሆነች ሞተች።ከዚያን ጊዜ ወዲህ፣ የእስራኤል ወጣት ልጃገረዶች ለዐራት ቀን ያህል ወደ ሩቅ -ስፍራ እየሄዱ፣ ለዮፍታሔ ልጅ ሐዘናቸውን መግለጥ የተለመደ ሆነ። <u>*(ትርጓሜ፡*</u> *እንደ ዮፍታሔ ግብታዊ ስእለትና ብፅዓት ማድረግ፣ እንደ ንጉሥ ሄሮድስ ቸኩሎ መሐላ መፈጸም አደጋ ላይ የሚጥል አሳዛኝ ድርጊት መሆኑን ያልተገነዘቡ አንዳንድ ምእመናን፣ አሁንም ይህንኑ ታሪክ ሲደግሙት ይገኛሉ። ስእለትና ብፅዓት እንደ ቃየል መሥዋዕት በችኮላ የግብር ይውጣ እንዳይሆን መጠንቀቅ ይገባል፤ ግብታዊ ስእለት ከማድረግና የማይወጡትን መሐላ ከመፈጸም ይልቅ፡ አለመፈጸሙ የተሻለ መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ይነግረና ( ዘዳግ 23፡ 22 )።* """"""

፲፪/12 <u>ሁለተኛ በደል፡</u> የገዛ ወንድሞቹ ኤፍሬማውያን ዮፍታሔን ለመውጋት ተነሣሥተው ከበቡት፤1--6 የጦርነቱ መነሻ፣ «አሞናውያንን ለመውጋት ስትዘምት እኛን ያልጠራኸን፣ ምር2 እንዳንካፈልህ ፈልገህ ነው»



www.ethiopianorthodox.org

የሚል ነበር። ዮፍታሔ የገለዓድን ሰዎች አስተባብሮ፣ ኤፍሬማውያንን ጦርነት በገጠማቸው ጊዜ ተበታትነው ሲሸሹ ከገለዓዳውያን ጋር ስለ ተደባለቁ፣ ለይቶ ለመምታት አስቸገረ። ስለዚህም፣ ገለዓዳውያን የዮርዳኖስን መሻገሪያ (መልካ) ዘግተው እንዲይዙባቸው አደረገ። አንድ ሰው ለማምለጥ ፈልጎ ይመጣና ልሻገር ሲላቸው፣ «ኤፍሬማዊ ነኽ ወይስ ገለዓዳዊ?» ብለው ይጠይቁታል፤ ኤፍሬማዊ ነኝ ያለ እንደ ሆን እስኪ፣ «ሺቦሌት» በል ይሉታል፤ እርሱም (የሸ ፊደል ዘሩ በእብራይስጥ ቋንቋ ካለመኖሩ የተነሣ) ሺቦሌት ማለት ስለማይችል ሲቦሌት ይላል። በዚህም አነጋገሩ ኤፍሬማዊነቱ ታውቆ ይገድሉታል። እነሆ፣ በዚህ አይነት ሁኔታ ባጠቃላይ ዐርባ ሁለት ሺህ ኤፍሬማውያን በሰይፍ ተገደሉ።7 ዮፍታሔም ስድስት ዓመት ሙሉ የእስራኤል መሪ ሆኖ ከኖረ በኋላ ሞተ።

<u>የኢብጻን፡የኤሎንና የአብዶን ምስፍና</u>፡ 8-9 ከዮፍታሔ በኋላ፣ የቤተ-ልሔም ተወላጅ የሆነው ኢብጻን የእስራኤል መሪ ሆነ። እርሱም ሠላሳ ሴቶች ልጆች ስለ ነበሩት፣ እነርሱን ከገሣ ውጭ ከሆኑ ሰዎች ጋር እንዲጋቡ በማድረግ የሕዝብን ኅብረት አሳይቶአል። ከኢብጻንም ቀጥሎ፣ የዛብሎን-ተወላጅ-የሆነው-ኤሎን፣ እስራኤልን ዐሥር ዓመት መርቶአል። እርሱም ሲሞት፣ የሂሌሌ ልጅ አብዶን መሪ ሆነ። በሰባ አህዮች ላይ ተቀምጠው የሚጋልቡ ዐርባ ወንዶች ልጆችና ሠላሳ የልጅ-ልጆች ነበሩት። እርሱም ስምንት ዓመት ገዝቶ ሞተ።

፲፫ /13፡ <u>የሶምሶን ልደት በብሥራተ መልአክ</u> ፡ 1-5 አሁንም፣ እስራኤል እንደ ገና በደል ስለሠሩ፣ እግዚአብሔር ለፍልስጥኤማውያን የጭቈና አገዛዝ አሳልፎ ሰጣቸው። ትውልዱ ከዳን ነገድ የሆነ ማኑሄ የሚባል አንድ ሰው ነበር፤ ሚስቱ መኻን ሆና ልጅ ሳትወልድ ቈይታ ነበር፡ የእግዚአብሔርም መልአክ ተገልጦላት እንዲህ አላት፤ «በቅርብ ጊዜ ፀንሰሽ ወንድ ልጅ ትወልጃለሽ፤ የወይን ጠጅም ሆነ፣ ማንኛውንም የሚያሰክር መጠጥና የተከለከለ ምግብ ከመብላት ተጠበቂ፤ ልጁም ከተወለ በኋላ፣ጠጕሩን እንዳልትላጪው። እርሱ ከሚወለድበት ጊዜ ጀምሮ ለእግዚአብሔር_የተለየ-ናዝራዊ-ይሆናል_እስራኤልንም ከፍልስጥኤማው ያን እጅ መታደግ ይጀምራል»፡

፲፬-14፡ <u>የሶምሶን ጋብቻ ከፍልስጥኤማዊት ልጃገረድ ጋር</u>፡

1-11 ሶምሶን ካደገ በኋላ፣ አንድ ቀን ወደ ቲምና ወርዶ አንዲት ፍልስጥኤማዊት ልጃገረድ አየ። ወደ ቤቱም ተመልሶ ሲመጣ ለአባቱና



ለእናቱ፣ «በቲምና አንዲት ፍልስጥኤማዊት ልጃገረድ አይቼ ወድጃታለሁና እርሱዋን አጭታችሁ አጋቡኝ» አላቸው። ሶምሶን ይህን ያደርግ ዘንድ የሚመራውና የሚያበረታታው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ሳያውቁ፣ "ከአገርኽ ልጆች መርጠህ አግባ" በማለት ለማከላከል ቢሞክሩም እርሱ፣ «ያችን-ልጅ ማግባት አለብኝ» ብሎ ወሰነ። በዚያን-ጊዜ፣ ፍልስጥኤማውያን እስራኤልን ይገዙ ስለ ነበር፤ እግዚአብሔር እነርሱን ለመቅጣት ምክንያት ይፈልግ ነበር። ከዚያን በኋላ፣ ሶምሶን ከአባቱና ከእናቱ ጋር ወደ ቲምና ወረደ። እዚያም ለመድረስ በወይን ተክል መካከል አልፈው ሲሄዱ፣ ሶምሶን ነጠል ብሎ ወደ ጫካ ገብቶ ስለ ነበር፣ አንድ የአንበሳ ደቦል እያገሳ መጣበት። በድንገትም፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ልዩ ኀይል አሳደረበት። ስለዚህ፣ ያንን ደቦል አንበሳ እንደ አንድ የፍየል ጠቦት ያህል በመቊጠር፣ ያለ ምንም መሣሪያ በባዶ እጁ አንሥቶ አፈረጠውና ገድሎት ሄደ። እንደ ትልቅ ነገር አድርጎም ስላልቈጠረው፣ ለወላጆቹ ይህን-አደረግሁ ብሎ አልነገራቸውም። ከዚያም-በኋላ፣ እንደ ገና ልጂቱን ለማግባት ሲሄድ፣ ያንን የገደለውን አንበሳ ሁኔታ ለማየት ከመንገዱ ዘወር ብሎ በተመለከተ ጊዜ፣ በድኑን ንቦች ገብተው ሠፍረውበት ማር ሞልቶበት አገኘ፤ ከማሩ ቈርጦ እየበላ ሲመለስ ለወላጆቹ ሰጣቸውና በሉ፤ ነገር ግን ከየት እንዳመጣው አልነገራቸውም ነበር። ሶምሶን ከዚያ ወደ ልጅቱ አባት ቤት ሲገባ፣ ትልቅ ግብዣ ተዘጋጅቶ ጠበቀው። ፍልስጥኤማውያን እርሱን ባዩት ጊዜ፣ ፈርተዉት ሠላሳ ወጣቶች ሚዜዎችን መርጠው ያጫውቱት ዘንድ ላኩ፣ በሚጫወቱበት ጊዜም፣ ሶምሶን እንቆቅልሽ ሲነግራቸው እንዲህ አለ፣ «በሰባቱ የሠርግ በዓል ቀኖች ውስጥ ይህን እንቆቅልሽ ተርጕማችሁ ፍችውን ብትነግሩኝ፣ ሠላሳ የበፍታ ቀሚስና ሠላሳ መቀየሪያ ልብስ እሰጣችሁአለሁ፤ ፍቺውን-መንገር-ባትችሉ ግን፣ ይህንኑ ዓይነት ልብስ ለእኔ ትሰጡኛላችሁ። እንቆቅልሹም፣ «ከበላተኛው አፍ መብል ተገኘ፤ ከብርቱውም ጣፋጭ ነገር ወጣ» የሚል ነው። እነርሱም እስከ ሦስት ቀን ድረስ፣ እንቆቅልሹን መፍታት ባለመቻላቸው፤ ሙሽራይቱን፣ «ይህንን እንቆቅልሽ ከሶምሶን ጠይቀሽ ንገሪን፤ ይህን ባታደርጊ ግን፣ የአባትሽን ቤትና አንቺንም ጭምር በእሳት አቃጥለን እንሄዳለን። ለካስ የሠርግ ግብዣ ብላችሁ የጠራችሁን ልታዘርፉን ነበርን?!» ብለው አስጨነቋት። እርሱዋም ሌት-ከቀን ሶምሶንን በማግባባት-እያለቀሰች አስልችታው



www.ethiopianorthodox.org

ነበርና በመጨረሻን ነገራት፡እርስዋም ምስጢሩን ገለጠችላቸው። «እንግዲህ ከአንበሳ የበረታ፤ ከማር የጣፈጠስ ምን አለ? ከአንበሳ አፍ ማር አግኝተህ በልተህ ይሆናል» አሉት። ሶምሶንም፣ «በእኔ ጊደር ባታርሱ ኖሮ፣ይህን የእንቆቅልሽ ፍቺ ማግኘት ባልቻላችሁም ነበር» አለ። የእግዚአብሔር መንፈስ ኃይልን ስለ ሰጠው፣ ወደ ገዛ አገራቸው አስቀሎና ወርዶ፣ ከገዛ ሕዝባቸው-መካከል ሠላሳ-ሰዎችን ገድሎ ልብሳቸውን ገፈፈና ወስዶ የእንቆቅልሹን ፍቺ ለነገሩት ሚዜዎች አስረከባቸው። በዚሁ ምክንያት በመቈጣት፣ አኵርፎ ወደ ቤቱ- ተመልሶ-ሄደ። አማቶቹ - በዚያው- የሚቀር- መስሏቸው፡ሚስቱን--ሚዜዋ-ዳሩበት።

፲5 /15፡ <u>ሶምሶን የወሰደው የበቀል እርምጃ</u>፡ 1--6 ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ በስንዴ መከር ወራት ሶምሶን ለሚስቱ አንድ የፍየል ጠቦት ይዞላት ወደ ቲምና መጥቶ "ልግባ" ሲል፣ የሚስቱ አባት፣ «ልጂቱን ጠልተህ የተውካት ስለ መሰለኝ፣ ሚዜህ ለነበረው ሰው ዳርኩአት፡ ሆኖም ፈቃደኛ ከሆንህ የእርሱዋ ታናሽ የሆነች ቈንጆ ልጅ አለችና እርሱዋን ልዳርልህ» አለው።ሶምሶን_ግን_ቍጣው-በረታና፣«ከእንግዲህ-ወዲህ፣በፍልስጥኤ ማያን ላይ-ስለምወስደው እርምጃ በኀላፊነት አልጠየቅበትም» ብሎ ማለ።

_ከዚያም ሄዶ ሦስት መቶ ቀበሮዎችን በማደን ያዘ፤ ጥንድ-ጥንዱን ጭራቸውን በማያያዝ አቈላልፎ፣ ችቦዎችን አብሮ አሰረና በእሳት አቀጣጥሎ፣ በማሳ ላይ ወዳለውና ገና ወዳልታጨደ የስንዴ መከር ውስጥ ለቀቃቸው፤ ታጭዶ የተከመረውንና ያልታጨደውን ስንዴም ሆነ የወይራና የወይን ተክሉንም ጭምር አቃጠለ። የፍልስጥኤም ገበሬዎች፣ «ይህን ያደረገ ማን ነው» ብለው ጠየቁ። ያ ሁሉ ጥፋት ሲደርስ የቻለው፣ የሶምሶን ሚስት ለሌላ በመሰጠቱዋ ምክንያት መሆኑን ሲረዱ፣ የዚያችን ልጅ እናትና አባት በእሳት አቃጠሏቸው። (***<u>ትርጓሜ፡</u>*** *ሶምሶን ሦስት መቶ ቀበሮዎችን አባርሮ ለመያዝ ያስቻለው፣ በእርሱ አድሮ ድንቅ ሥራ የሚያሠራው የግዚብሔር መንፈስ ኀይል ነው እንጂ፣ በራሱ ጥበብና ኀይል ወይም በሩጫው ፍጥነት አልነበረም።)*

*6*-ሶምሶንም ደግሞ፣ «እንግዲህ እናንተ ይባስ ብላችሁ ይህን ካደረጋችሁ፣ እናንተን ሳልበቀል አልተዋችሁም» ብሎ ማለ። ወዲያውም አደጋ ጥሎባቸው ብዙዎችን ከገደለ በኋላ፣ ሄዶ ኤጣም ተብላ በምትጠራ ዋሻ ውስጥ ተቀመጠ። 9-16 ፍልስጥኤማውያን ደግሞ በይሁዳ ላይ ዘምተው፣ ሌሒ ተብላ በምትጠራ ከተማ ላይ አደጋ ጣሉ። የይሁዳ ሰዎችም፣ «በእኛ ላይ አደጋ መጣል የፈለጋችሁበት ምክንያት ምንድን



ነው?» ብለው ቢጠይቁዋቸው፣ «ሶምሶንን አስረን መውሰድ ፈልገን ነው» ሲሉ መለሱላቸው። ስለዚህ፣ ሦስት ሺህ የሚሆኑ የየሁዳ ሰዎች ወደ ኦጣም ዋሻ መጥተው ሶምሶንን፣ «ፍልስጥኤማውያን የእኛ ገዢዎች መሆናቸውን እያወቅህ፣ ይህ ያደረግህብን ነገር ምንድን ነው?» ሲሉ ጠየቁት በኋላ፣ «እኛ አሁን የመጣነው አንተን አስረን ለእነርሱ አሳልፈን ልንሰጥህ ነው» አሉት። ሶምሶንም፣ «ብቻ፣ እናንተ ሳትገድሉኝ ቃል ገቡልኝና አሳልፋችሁ ስጡኝ» አላቸው። እነርሱም ራሳቸው ላይገድሉት ቃል ገቡለትና እርሱን ይዘው በሁለት አዳዲስ ገመድ ጠፍረው በማሰር ወስደው ለፍልስጥኤማውያን አለቆች ሲያስረክቡዋቸው፣ ፍልስጥኤ ማውያን እየተራራጡ መጥተው እየፎከሩ (እየደነፉ) ዙሪያውን ከበቡት። በድንገትም የእግዚአብሔር መንፈስ ልዩ ኀይል አሳደረበት፤ እጆቹ-ተጠፍረው የታሰረባቸውን ገመዶች እሳት እንደ ነካው ፈትል በጣጣሶ ጣለ፣ የአንድ አህያ መንገጭሌ አንሥቶም በመወርወር አንድ ሺህ ሰው ገድሎ፣ እሬሳ -በሬሳ ላይ አነባበረ። 17-20 በዚያም ጊዜ፣ ሶምሶን እጅግ ስለ ተጠማ፣ «እነሆ፣ ይህን የመሰለ ድል ከሰጠኸኝ-በኋላ፣ በውሃ ጥም ምክንያት በእነዚህ ባልተገረዙ ፍልስጥኤማው_ያን እጅ ልማረክ ነውን?!» ሲል የእግዚአብሔርን ስም ጠራ። እግዚአብሔርም በሌሂ የነበረውን አንድ የውሃ ምንጭ ከፈተለትና ጠጥቶ ስለ ረካ ብርታት አገኘ። በዚህም ሁኔታ ፍልስጥኤማውያን የአገሪቱ ገገርዎች በነበሩበት ዘመን ሶምሶን የእስራኤልን ሕዝብ ለኻያ ዓመት መራ።

፲፮/16 ፡ <u>ሶምሶን እንደ ገና በጋዛ ተከበበ</u> ፡ 1-3 በአንዲት ሴት ቤት ለማደር ስለ ገባ ፍልስጥኤማውያን፣ «ሲነጋ እንገድለዋለን» ብለው ከበውት አደሩ፡ ሶምሶን ግን፣ ከዕኩለ ሌሊት በኋላ ከመኝታው ሲነሣ፣ የተከበበ መሆኑን ስለ አወቀ፣ የጋዛ ሰዎች እርሱን ለመያዝ የሠፈሩበትን የከተማይቱን ቅጽር (ግንብ አጥር) በር ፈነቃቅሎት፣ የበሩን መቃን ከነቍልፉ ተሸክሞ-ወስዶ፣ በኬብሮን ፊት-ለፊት ባለው ኰረብታ ላይ አራግፎ ጣላቸው።

የሶምሶን ምስጢራዊ ኃይል በጋለሞታዩቱ በደሊላ ስለላ ፤

_22 ሶምሶን በሶሬቅ ሸለቆ የምትኖር-ደሊላ የምትባል-ሌላ ሴት-ወደደ።- አምስቱ የፍልስጥኤም ነገሥታትም ሄደው ደሊላን እንዲህ አሉአት፤ «ሶምሶንን በማግባባት ይህን ብርታት ያገኘው ከምን እንደ ሆነና እንዴትስ አስረን በቍጥጥራችን ሥር ልናውለው እንደምንችል ጠይቂው፣ እያንዳንዳችን አንድ ሺህ አንድ መቶ ጥሬ ብር እንሰጥሻለን»። እርሱዋም በየዕለቱ በማግባባትና በመነዝነዝ፣ይህንኑ የእርሱን ኃይል መገኛ ምስጢር እንዲነግራት በመነዝ



www.ethiopianorthodox.org

በመነዝነዝ፣ ይህንኑ የእርሱን ኃይል መገኛ ምስጢር እንዲነግራት ደጋግማ ጠየቀችው፤ ሶምሶንም ‹‹በሰባት አዳዲስ ጠፍሮች ቢያስሩኝ ኀይሌ ይደክማል›› ሲል ምስጢሩን ገለጠላት፡፡ መሳፍንቱም ሰባት አዳዲስ የጠፍር ማሰሪያዎችን አምጥተውላት፣ ‹በዚህ እሰሪልን›› ብለው ሰጧት፡፡ እርሱም የታሰረበትን ጠፍር ሁሉ በታትኖ-ተነሣ፡፡ ደሊላም ‹‹አታለልከኝ እኮ፣ እውነቱን አልነገርከኝም›› አለችው፡፡ ሌላም ጊዜ የራሱን ቈንዳላዎች ጕንጕና መሬት ላይ ብትቸክል ሳይኾንላት ቀረ፡፡ በመጨረሻም፣ ከብዙ ጕትጐታ በኋላ፣ ሲሰለቸው አንድ ቀን፣ የኀይሉ ብርታት ያለው በጠጕሩ ላይ መሆኑን ገልጦ፣ ‹‹ጠጕሬ ቢላጭ እንደማንኛውም ሰው ደካማ እሆናለሁ›› ብሎ እውነቱን ነገራት፡፡ ከዚያም-በኋላ፣ ደሊላ-ራሱን-እየደባበሰች_እንቅልፍ_እንዲወስደው_አድርጋ፣ከሚጠባበቁት ፍልስጥኤማውያን አንዱን ጠርታ፣ ሰባቱን የሶምሶንን ቆንዳላዎች አስቈረጠች፡፡ ኀይል እንደተለየው አውቃ፣ ከክብር በማዋረድ ታስጨንቀው ጀመር፡፡ ወዲያውም፣ ‹‹ሶምሶን ፍልስጥኤማውያን_መጡብህ››-አለችው፡እርሱ-ከእንቅልፉ-ነቅቶ-እንደ-ወትሮው-ተነሥቶ-ለመሄድ-ሲጀምር፡ እግዚአብ ሔር-እንደ-ተለየው-አላወቀም-ነበር ፍልስጥኤማውያን- መጥተው-ማረኩትና ሁለት ዓይኖቹን አውልቀው በነሐስ ሰንሰለት አስረው፣ ወስደው በታሰረበት ቤት እህል እንዲፈጭ አደረጉት፡፡ በዚያን ጊዜ ውስጥ ጠጕሩ እንደ ገና ማቀምቀም ጀመረ፡፡

23-30 በመጨረሻም ታላቅ የድልና የደስታ በዓል ማዘጋጀት ፈልገው፣ ዳጎን ተብሎ በሚጠ-በአምላካቸው ቤተ-ጣኦት-ውስጥ፣-ሦስት ሺህ የሚሆኑ መኳንንትና ሴት ወይዘሮዎችን ሰበሰቡ፡፡ከዚያም ሶምሶንን በመካከላቸው- በማቆም እየዘፈኑ ያዝናናቸው ዘንድ ጠየቁ፡፡ በዚያን ጊዜ፣ ጠጕሩ አቀምቅሞ ማደግ ጀምሮ ነበር፤ በአዳራሹ የመሐል ምሰሶዎችን ተደግፎ ቆሞ፤ እንዲህ ሲል ጸለየ፣ ‹‹ልዑል እግዚአብሔር ሆይ፣ እንደ ገና እንድታስበኝ እለምንሃለሁ፤ የነበረኝን ኃይል መልስልኝና እርዳኝ፤ ሁለት ዓይኖቼን ያሳወሩ ፍልስጥኤማውያንን አጥፍቼ ልጥፋ!››፤ ይህን የጸሎት ቃል ተናግሮ ሲጨርስ፣ ያንን ግዙፍ ሕንጻ የተሸከሙትን ሁለቱን የመሐል ምሰሶዎች በቀኝና በግራ እጆቹ ይዞ፣ ባለው ሙሉ ኀይል ሲገፋቸው፣ ሕንፃው በሙሉ ተደረመሰ፡፡ ሦስት ሺህ መሳፍንት፣ መኳንንትና ሴት ወይዘሮዎችም እንዳሉ አለቁ /ሞቱ ፡፡

***(ትርጓሜ፡*** *<u>የሶምሶን ምሳሌነት፣</u> ሶምሶን በብሥራተ መልአክ መፀነሱና ናዝራዊ በመሆኑም ጭምር እንዲሁም በነበረው አስደናቂ ኀይል ሁሉ፣ የጌታችን የአምላካችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ*



*ክርስቶስ ምሳሌ ነው ፡፡ ሶምሶን በሕይወተ- ሥጋ በነበረበት ጊዜ ካጠፋቸው ጠላቶቹ ይልቅ ፣ በሞቱ ጊዜ የደመሰሳቸው እንደሚበዙ ሁሉ፣ ጌታም በዚህች ምድር በአካለ ሥጋ ይመላለስ በነበረበት ጊዜ፣ በታምራት ካሳደዳቸው ይልቅ፣ በመስቀል ላይ ሳለ በሞቱ የደመሰሳቸው አጋንንት ቍጥር ይበልጣል ማለት ነው፡፡ በሌላም በኩል፣ ሶምሶን መላውን ማኅበረ ምእመናን የሚወክልበት ምሳሌነት አለው፡፡ ይኸውም እያንዳንዱ ምእመን ኀይልንና በአጋንንት ሠራዊት ላይ ድል አድራጊነትን መቀዳጀት የሚችለው፣ በክርስቶስ መንፈስ ሲመራ ብቻ መሆኑን በግልጥ ያስገነዝባል። ከውድቀት መዳን የሚችለውም፣ በክርስቶስ ቸርነትና በምሕረቱ እንጂ፣ በራስ ጽድቅ፣ ‹‹እቆማለሁ›› ቢል በቀላሉ ይወድቃል። ሶምሶንን ለውድቀት የጋበዘ ታላቅ ኃጢአት በጠጕሩ ላይ የነበረውን የእግዚአብሔር ምሥጢር ለጋለሞታ መንገሩ ነው። ታዲያ ከዚህ የሚበልጠው ታላቅ ኃጢአት ደግሞ፣ ከወደቁ በኋላ እንደ ዳዊት በንስሐ መነሣት ሲቻል፣ ራስን እንደ ርኵስ ቈጥሮ፣ በዚያው እንደወደቁ መቅረት ነው፡፡ ከዚህም ጋር ሶምሶን ያን ሁሉ የዝሙት ኃጢአት፡ ያውም ከአረማውያት ሴቶች ጋር እየፈጸመ፣ በችግሩ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት መጮኹን አላቋረጠም። እግዚአብሔርም፣ ‹‹ኃጢአተኛ ስለ ሆንህ፣ ጸሎትህን አልሰማም ብሎ የምሕረት በሩን አልዘጋበትም፡ በቅዱስ ወንጌል የተጻፈውም መመሪያ ይኸው ነው። ‹‹ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፣ ‹እውነት እላችሁአለሁ፣ ቀራጮችና ጋለሞቶች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሟችኋል፤ ዮሐንስ በጽድቅ መንገድ መጥቶላችሁ ነበር፣ እናንተ ግን አላመናችሁበትም፤ ቀራጮችና ጋለሞቶች ግን አመኑበት። ሌላው ቀርቶ ይህን ሁሉ አይታችሁና ሰምታችሁ እንኳ ንስሐ አልገባችሁም›››* *ብሏቸዋል ( ማቴ .21፡ 31–32 ፡ )*

## ፲፯ /17፡ <u>ሚካ ያሠራው የጣዖት ባዕድ አምልኮት መዛመት፡</u>

1-6 ሚካ የተባለ እስራኤላዊ በኰረብታማው የኤፍሬም አገር ይኖር ነበር፤ ከእናቱ በሰረቀው ገንዘብ በወርቅ የተለበጠ ጣዖት አሠርቶ፣ ከልጆቹ አንዱን በክህነት ያገለግል ዘንድ መደበው፡፡ ከቤተ-ልሔም ተሰዶ የመጣ አንድ ሌዋዊ ካህን በማግኘቱ ደስ ብሎት፣ ‹‹ለእኔ ካህን ሁንልኝ›› ሲል ጠየቀው፣ሌዋዊውም እሺ ብሎ እንደ ልጁ ሆኖ አገልግሎቱን ቀጠለ፡፡

## ፲፰ /18 <u>፡ አገር ለመሰለል የመጡ አምስት የዳን ነገድ መልእክተኞች፡</u>

1-13 ሚካ ወደሚኖርበት ቦታ እንደ ደረሰ፣ ያንን ካህን ብቻውን አገኘት፤



www.ethiopianorthodox.org

እርሱን መርምረው ሁኔታውን ሁሉ ስለ ተረዱና ከእርሱም ዘንድ ኤፉድ መኖሩን ስላወቁ፣ ‹‹ጉዞአችን እንዲሳካልን ጸልይልን››-አሉት። ካህኑም-‹‹አይዞአችሁ፤ምንም-ችግር አይገጥማችሁም ፤ እግዚአብሔር ይጠብቃችኋል›› አላቸው*(በውሸት ትንቢት ማለት ነው)።* አምስቱ ሰዎች ከዚያ ተነሥተው ወደ ሌሳም መጡ፤ በዚያች አገር የሚኖሩ ሕዝብ ከማንም ጋር ሳይጋጩ፣ ፀጥ ባለ መንፈስ የሚኖሩ ሰላም ወዳዶች መሆናቸውን ተመለከቱ። ተመልሰውም ይህን ሁሉ ለዳን ነገደ-ሕዝብ አስረዱ። 14-26 ስለዚህ፣ ከዳን ነገድ ስድስት መቶ ሰዎች ለጦርነት ተዘጋጅተው ከጾርዓና ከኤሽታኦል ተነሡ። ሚካ ወደሚኖርበት ቦታ እንደ-ደረሱም፣እነዚያ-ቀድሞ ተልከው የነበሩት አምስት ሰላዮች፣ በሚካ ቤት የሚመለክ ጣዖትና አንድ ሌዋዊ ካህን መኖሩንና በኤፉድ ጭምር የሚያገለግል መሆኑን ጠቈሙ። የዘመቻውም መሪዎች ሌዋዊውን ካህን፣ ‹‹ለአንድ ሰው ከማገልገል ይልቅ ለነገደ-ሕዝብ አገልጋይ መሆን ይሻልሃልና፣ከእኛ ጋር ና አብረኸን እንሂድ››ብለው በማግባባት አባብለው አስኰብልለው ወሰዱት። ሚካ በዚህ ዘረፋ ተናዶ፣ ጣዖቱንና ካህኑን እንዲመልሱለት አቤቱታ ቢያቀርብም የሚሰማው ዳኛ አጥቶ፣ ወደ መኖሪያ ቤቱ ተመለሰ። 27-30 ያም ዘማች ሠራዊት ወደ ሌሳም መጥቶ፣ እነዚያን ሰላም ወዳድ ሕዝብ ገደለ፤ ከተማይቱንም አቃጠለ። የዳን ሰዎች ያችኑ ከተማ እንደ ገና ሠርተው የራሳቸው መኖሪያ አደረጉአት። ያንንም የሚካን ጣዖት በዚያ አኖሩ። ከሙሴ ልጅ ከጌርሳም ጕሣ የተወለደ፣ ዮናታን ተብሎ የሚጠራ ካህንም በዚያ ቤተ-ጣዖት ለዳን ነገድ ማገልገል ጀመረ። የርሱም ዘሮች ሁሉ፣ *( በዚሁ አምልኮ ባዕድ ኣየተመሩ)* ሕዝቡ ተማርከው እስከ ተወሰዱበት ዘመን ድረስ ቈይተዋል።

፲9 /19፥ <u>ቁባት የነበረችው አንድ ሌዋዊ ካህን</u> ፤ 1-8 በእስራኤል፣ ንጉሥ ባልነበረበትና ማንም ሰው በፊቱ ደስ የሚለውን ተግባር ይፈጽም በነበረበት በዚያ ዘመን፣ በኰረብታማው በኤፍሬም አገር፣ ራቅ ብሎ በሚገኝ ስፍራ የሚኖር፣ አንድ ሌዋዊ ካህን፣ በይሁዳ ግዛት ከምትገኘው ከቤተ-ልሔም የወሰዳት አንዲት ልጃገረድ ቁባት ነበረችው። ነገር ግን፣ ልጅቱ ከርሱ ጋር ተጣልታ በመኰብለል፣ በቤተ ልሔም ወደሚገኘው ወደ አባቱዋ ቤት ሄዳ ዐራት ወር ተቀመጠች፤ ሌዋዊውም ካህን ሊማልዳትና ወደ ቤቱ ሊመልሳት ቢሄድ፣ አማቱ በደስታ ተቀብሎ ለሦስት ን አስተናገደው፤ በአራተኛው ቀን



ለመሄድ-ሲነሣም፣"ብርታት-እንድታገኝ፣ዋል"፣-እደር-በማለት-አዘገየው፡ ፡ በአምስተኛውም ቀን ጥዋት ለመሄድ ሲነሣ፣ እህል-ውሃ ቀምሰህ ትሄዳለህ" በማለት አዋለው። ዘግየት ብሎም ሌዋዊዉና፣ አገልጋዩቁባቱና እንደ ገና ጕዞ ለመጀመር ሲነሡ፣ የልጅቱ አባት፣ ‹‹ቀኑ ስለ መሸ የዛሬን እደሩ›› ቢላቸው፤ ሌዋዊዉ፣ ‹‹ዛሬስ ማደር የለብንም›› ብሎ አህያውን ጭኖ ጕዞውን ጀመረ። ፀሐይ ለመጥለቅ ስትቃረብ የነገደ ብንያም ግዛት ወደሆነች ጊብዓ ደርሰው ሌሊቱን በዚያ ለማሳለፍ ውደ አንድን ሽማግሌ ገበሬ ቤት ገቡ። በራት መስተንግዶ ላይ እንዳሉ የግብረ-ሥጋ ሥርዓት ለዋጮች (ሰዶማውያን) የአስተናጋጁን ሽማግሌ ቤት ከብበው፣ ‹‹ወደ ቤትህ ለማደር የገባውን ሰው አውጥተህ ስጠን፤ ግብረ-ሥጋ ልንፈጽምበት እንፈልጋለን›› ብለው ክፉኛ አስጨነቁት። እንግዳ ተቀባዩም ሽማግሌ ወደ ውጭ ወጥቶ፣ ‹‹እባካችሁ ይህን ክፉ ነገር በዚህ እንግዳ ሰው ላይ ለመፈጸም አታስቡ፣ እነሆ፣ የሰውዮው ቁባትና ገና ድንግል የሆነች የእኔም ልጅ አለችላችሁ፤ እነርሱን ላውጣላችሁና ወስዳችሁ የምትፈልጉትን አድርጉ›› ብሎ ቢማጠናቸውም እምቢ አሉት።

በመጨረሻ ግን፣የካህኑን ቁባት ወስደው በማመንዘር ( በአስጨናቅቂ ሩካቤ ሥጋ ሲጫወቱባት አደሩ። ሲነጋ ግን፣ እንድትሄድ ፈቀዱላት። ጥዋት ጎሕ ሲቀድ፣ ያች ሴት መጥታ ባሉዋ ባደረበት ሽማግሌ ቤት በበሩ አጠገብ ወድቃ ፀሐይ እስክትወጣ ቈየች።

_ሌዋዊዉ ጕዞውን ለመቀጠል በሩን ሲከፍት፣ ቁባቱ እጁዋን ወደ በሩ እንደ ዘረጋች ወድቃ አገኛት። በሕይወት ያለች ስለመሰለችም፣ ‹‹ተነሺ እንሂድ›› አላት። ነገር ግን፣ መልስ ልትሰጠው አልቻለችም።ከዚያ በኋላ አስከሬኑዋን- በአህያው ጭኖ ሄዶ ወደ ቤቱ እንደ ደረሰ፣ ሥጋዋን በቢላዋ ቈራርጦ፣ ዐሥራ ሁለት ቦታ ከፍሎ፣ ወደ ዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች ላከው። ያንንም አሳፋሪና አስከፊ ድርጊት የሰሙ ሁሉ፣ ‹‹ይህን የመሰለ ነገር በእስራኤል ከቶ ሰምተን አናውቅም፤ ስለዚህ ጕዳይ አንድ ውሳኔ ላይ መድረስ አለብን›› አሉ። *(ትርጓሜ፡ በመሠረቱ ሌዋዊ ካህን ማለት ነው። ታዲያ እንዴት ቊባት ማስቀመጥ ቻለ? የድርጊቱ አፈጻጸም ማዕከላዊ አምራር ስጪና ሕጋዊ አካል ባለመኖሩ ነው ብንልም በተለይ ካህን የሆነ ሰው የእግዘእሔርን ሕግ እያወቀ ቊባት እስከ ማስቀመጥ መድረሱ ለዚህ ውርደት ጋብዞታል። ሴትዩዋም ብትሆን ቊባት አድርጎ ባስቀመጣት ካህን ብቻ ተወስና መርጋት የቻለች አትመስልም። መኰብለል ጀምራ ነበርና*



www.ethiopianorthodox.org

*የፈለገችውን ዝሙት ትጥገበው በማለት በገፍና በግፍ ለቅጣት የታዘዘባት ይመስላል። ይህ ዓይነቱ አደጋ በዘመናችን የከፋ ስለሆነ አዲሱን ትውልድ እግዚአብሔር ይጠብቅ ! !*

## ፳ /20: የተፈጥሮ ሥርዓት ለዋጮችን ለመቅጣት

1--11 ከዳን እስከ ቤርሳቤህ (ከሰሜን እስከ ደቡብ) ያሉትና እንዲሁም በስተ ምሥራቅ፣ በገለዓድ ምድር የሚኖሩ፣ መላው የእስራኤል ሕዝብ፣ ለጦርነት መዘጋጀት ግዴታ ሆነባቸው፣ በምጽባም በእግዚአብሔር ፊት በአንድነት ተሰበሰቡ፤ በእስራኤል የነገድ አለቆች አስተባባሪነት የተመረጠ የእግረኛ ወታደራቸው ብዛት ዐራት መቶ ሺህ ነበር። የእስራኤል ሕዝብ ያንን ሌዋዊ አስቀርበው፣የድርጊቱን አፈጻጸም እንዲተርክላቸው-አደረጉ። ድርጊቱን በዝርዝር ካጠኑም በኋላ፣ ሕዝቡ እንዲህ አሉ፤ ‹‹እንግዲህ ከእኛ መካከል፣ ማንኛውም ሰው ወደ ቤቱ መመለስ የለበትም፤ በጊብዓ ላይ አደጋ የሚጥሉ ሰዎችን በዕጣ መምረጥ አለብን፤ ከእስራኤል ሕዝብ አንድ ዐሥረኛው እጅ፣ ለሚዘምተው ሥራዊት ሥንቅ ያዘጋጅ፤ የቀሩት ግን ዘምተው ይህን አሳፋሪና አስነዋሪ ድርጊት የፈጸሙትን የተፈጥሮ ሥርዓት ለዋጮችን መቅጣት አለባቸው››።

12-16 የእስራኤል ነገዶች በአንድ ድምፅ ተባበሩ፤ በብንያም ግዛት ተዘዋውረውም፣ እንዲህ የሚል ቃል የሚናገሩ መልክተኞችን ላኩ፤ ‹‹ይህ የፈጸማችሁት ወንጀል ምንድን ነው? እነርሱን ገድለን ይህን ክፉ ነገር ከእስራኤል ማስወገድ እንድንችል በጊብዓ የሚገኙትን እነዚያን የተፈጥሮ ሥርዓት ለዋጮችን (ግብረ-ሰዶማውያን) አውጥታችሁ ስጡን››። የብንያም ሕዝብ ግን "እምቢ፤አሻፈረን "አሉ። _እንዲያውም ሌሎቹን ዐሥራ አንድ የእስራኤል ሕዝብ ነገዶችን ለመውጋት ከብንያም ከተሞች ተጠራርተው፣ ወደ ጊብዓ መጥተው ተሰበሰቡ። በዚያኑ ቀን፣ ኻያ ስድስት ሺህ ወታደሮችን መርጠው አሠለፉ። ከነዚህም ጋር፣ ድንጋይ አወንጭፈው፣ ጠጉር እንኳ የማይስቱ ሰባት መቶ ግራኞች ነበሯቸው።

18--28 እግዚአብሔርም የይሁዳ ነገድ ተቀዳሚ ሆኖ እንዲዘምት ነገራቸው። በጦርነቱ የመጀመሪያ ቀን፣ የብንያም ሠራዊት ከምሽት በፊት፣ ኻያ ሁለት ሺህ የእሥራኤልን ዘማቾች ገደለ፤ በሁለተኛው ቀን በተደረገው ጦርነት ደግሞ ዐሥራ ስምንት ሺህ፣ በድምሩ ዐርባ ሺህ ዘማች ገደሉባቸው። የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት አዝነው፣ አልቅሰው እንደ ገና ጠየቁ፤ እግዚአብሔርም፣ በማግሥቱ ድልን እንደሚያቀዳጃቸው ነገራቸው። 29-36 ፡ የእሥራኤል ልጆች ሦስተኛ ጊዜ ለጦርነት ወጡ።

አሁንም ብንያማውያን እንደ ገና ከእስራኤል ሠላሳ ያህል ወታደሮችን



ገደሉባቸው፤ እስራኤላውያንም ለመሸሽ ያሰቡ መስለው፣ ወደ ኋላ ማፈግፈግ ጀመሩ። ብንያማውያን እነርሱን ለማሳደድ ከከተማዪቱ ወጥተው ሲዋጉ፣ የእስራኤል ጦር በእግዚአብሔር ኀይለ- ረድኤት ተነሣሥቶ ከተማዪቱን በእሳት አነደዳት (አጋያት)። የቃጠሎውም ጢስ ወደ ሰማይ ተትጐልጒሎ ወጣ። ብንያማውያንም ያን ሲያዩ በርግገው ወደ ምድረ-በዳ ለመሸሽ ተገደዱ፤ ነገር ግን ማምለጥ አልቻሉም፤ ስለዚህም፣ ኻያ አምስት ሺህ አንድ መቶ ወታደሮች ሲገዱሉባቸው፣ የተረፉት ወደ በረሃ ለመሸሽ ግድ ሆነባቸው። 44-48 እንደ ገናም፣ ከብንያም ምርጥ ወታደሮች ዐሥራ ስምንት ሺህ ሲገደሉ፣ የተረፉት አምስት ሺህ ወታደሮች-ደግሞ ፣የሪሞን-ዐለት ወደሚባለው ስፍራ መጥተው ሲያልቁ፣ሌሎች-ሁለት ሺህ- ወታደሮችም ተገደሉባቸው።የሪሞን ዐለት ወደሚባለው ስፍራ ሄደው ለዘር ያህል ከሞት የተረፉት ብንያማውያን ወንዶች ስድስት መቶ ብቻ ነበሩ።

<u>እንደ ገና ከነገደ ብንያም ዘር ለማትረፍ የተደረገ ስብሰባ</u> ፡ 1-7 የእስራኤል ሕዝብ በምጽባ በተሰበሰቡ ጊዜ፣ ‹‹ከእኛ ወገን ማንም ሰው ሴት ልጁን ለብንያም ተወላጅ በሚስትነት እንዳይሰጥ›› ሲሉ በእግዚአብሔር ስም ተማምለው ነበር። አሁን ደግሞ፣ የዚህ ነገድ ስም-አጠራርና ዝርያውም ሁሉ ተደምስሶ መቅረቱ አሳዝኖአቸው፣ እንደ ገና በእግዚአብሔር ፊት አለቀሱ። 8-24 ከእስራኤል ነገዶች መካከል በምጽባ በተደረገው ስብሰባ ላይ ያልተገኘ ወገን ማን እንደሆነ ሲመረምሩ፣ በገለዓድ ከሚኖሩት መካከል፣ በተለይ የኢያቢስ ዘገለዓድ ሰዎች አለመኖራቸው ስለ ታወቀ፣ እንዲደመሰሱ ሲፈረድባቸው፣ ከሞት የተረፉት፣ ወንድ ያላወቁ ዐራት መቶ ልጃገረዶች ብቻ ነበሩ። ከሞት የተረፉት ስድስት መቶ ብንያማውያን ተመልሰው እጃቸውን ስለ ሰጡ፡ እነዚያን ከኢያቢስ ዘገለዓድ ተማርከው የመጡትን ልጃገረዶች፣ለዐራቱ መቶ ብንያማውያን በሚስትነት ሰጧቸው። ለቀሪዎቹ ሁለት መቶ ብንያማውያን ደግሞ፣ እንዲህ የሚል መመሪያ ተሰጠ፤ ‹‹እስራኤላውያን በሴሎ ተሰብስበው በዓል በሚያከብሩበት ቀን፣ ብዙ ልጃገረዶች ለዘፈንና ለጨዋታ ወጥተው ስለሚሰበሰቡ፣ በወይን ተክል ውስጥ ደፈጣ አድርጋችሁ፣ለእናንተ-ሚስቶች-እንዲሆኑላችሁ-የምትፈልጓቸውን-ደናግል_መርጣችሁውሰዱ፡ ወንድሞቻቸው 'ስለ ምን እንዲህ ተደረገብን?'›› ብለው ቢጠይቁንና-እናንተን-ሲጣሏችሁ-ቢያስቡ፡-ለእኛ-ስትሉ--ተባበሯቸው'ብለን እንማልድ ላችኋለን››። 25 እነሆ በዚያ ዘመን፣ በእስራኤል ሕግና ሥርዓትን የሚያስከብር ንጉሥ ስላልነበረ፣ ማንም ሰው ለራሱ ደስ የሚለውን ነገር



www.ethiopianorthodox.org

እንደ ፈለገ ያደርግ ነበር። (ትርጓሜ፡ ከዚህም ሁሉ የሚገርመው በዚያ ዘመን ባለቀባት ካህን ጭምር መኖሩ ነው። ነቢዩ "ወካህንኒ ከመ ሕዝብ=ካህኑም እንደ ሕዝብ ሆነ" ማለትም ከሚሰክረው ጋር ይሰክራል፡ ከሚያመነዝረው ጋር ያመ ነዝራል" ሲል እንደተናገረ፡ (ሆሴዕ 4፡ 6 ) በዘመናችንም ይህ ዓይነቱ ዓይን ያወጣ ድርጊት እንዳይደገምና ወደ ሌላ ደረጃ አድጎ የኅብረተሰብ ጠንቅ ከመፈጠሩ ፊት በሕግ መታረም ይኖርበታል።

''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''

# መጽሐፈ ሩት

***መግቢያ*** ፡ *መጽሐፈ ሩት 'እግዚአብሔርን ከማያውቅ ከሞአባው _ '''''''''''''''''''''' ማኅበረሰብ የለይታ ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ በመግባት እንደ አንዲት እስራኤላዊት ዜጋ ለመሆን የበቃችና ፍቅርን፡ ሰላምን ትሕትናን ከፍጹም ተታዛዥነትና ሰብአዊነት ጋር ማስተማር የሚያስችል ጥሩ ሕይወት የነበራት የአንዲት ሴት ታማንነት መዘክር ነው። ይህንም ለማድረግ ያባቃት ኖኀሚን የተባለችውን እስራኤላዊት ተከትላ ወደ ምድረ እስራኤል ለመግባት ስታስብ ከምንም ጥቅም ጋር ባልተያያዘ መልኩ " ከሁን ባኋላ ካንቺ አልለይም፡ ሕዝብሽ ሕዝቤ፡ አምላክሽ አምላኬ ፡ አገርሽ፡ አገሬ ፡ መቃብ_ርሽ መቃብሬ ይሆናል" በማለት የተናገረችው የውሳኔ ቃል ነው።*

*_ይህንም ቍርጥ ውሳኔዋን የተመለከተ አምላክ እስራኤ ለሩት እጅግ ብዙ አስደናቂ ነገር ፈጽምላታል። ይህም ዓይነቱ ውሳኔ ክርስቶስን የመከተል ፍላጎት ልክ ሞአባዊትዋ ሩት እንዳደረገቻው ከምንም ዓይነት ሥጋዊ ጥቅም ጋር የተያያዘ መሆን እንደሌለበት ያስተምራል። ያም ዓይንቱ ውሳኔ ውሎ አድሮ እኛ ሳንጠይቀው የሚያስፈልገንን ሁሉ የሚያውቅ አምላክ ለሩት እንዳደረገው ያልጠበቅነውን በረከት በጸጋው እንደሚሰጠን የታመነ ነው። ሩት-"አንቺን በመከተል አብሬስሬሽ ወደ ሀገርሽ ብሄድ ምን ታደርጊልኛለሽ?' የሚል ጥያቄ ለኖኃሚንን አላቀረበችም። ከሐዋርያቱ ዋና ተናጋሪ የነበረው ሐዋርያ ጴጥሮስ ግን ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ከመቀበሉ በፊት የነበረው ጥይቄ "ናሁ ኮሎ ኀደግነ ወተሎነከ ምንተ እንከ ንረክብ/" እነሆ ኑሉን ነገር ትተን ተከተልንህ፡ ምን እናገኝ ይሆን? የሚል ነበር (ማቴ 19፡ 270 ።) ''''''''''''*

''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''''



**፩ /1 ፡** <u>ኖኃሚንና አቢሚሌክ ከልጆቻቸው ጋር ወደ ሞዓብ ተሰደዱ</u>

1--5 በዘመነ-መሳፍንት ( መሳፍንት በሚገዙበት ዘመን ) በአንድ ወቅት፣ በምድር ላይ ብርቱ ረኀብ ሆኖ ነበር። ከዚህ የተነሣ፣ ኖኃሚን ተብላ የምትጠራ አንዲት እስራኤላዊት ፣ አቤሜሌክ- ተብሎ ከሚጠራው ባሉዋ ጋር፣ ምሐሎንና ኬሌዎን የሚባሉትን ሁለት ወንዶች ልጆችዋን ይዛ ወደ ሞዓብ አገር ተሰደደች። በዚያም ሁለቱ ወንዶች ልጆቹዋ ምሐሎንና ኬሌዎን ከሞዓብ አገር ተወላጆች መካከል ዖርፋና ሩት የተባሉ ሚስቶችን አገቡ። ዘግየት ብሎ ግን፣ ባሉዋ አቤሜሌክና ሁለቱ ልጆቹዋም ስለ ሞቱባት፣ ኖኃሚን ብቻዋን ቀረች።

## <u>ኖኃሚን ወደ አገሩዋ ለመመለስ ያደረገችው ውሳኔ፡</u>

6--17 ኖኃሚን በሞዓብ አገር ሳለች፣ እግዚአብሔር በረድኤት ሕዝቡን እንደ ጐበኛቸውና ብዙ የእህል መከር / ሰብል መሰብሰብ መቻላቸውን ሰምታ፣ ወደ አገሩዋ ለመመለስ ወሰነች። ጕዞዋንም ስትጀምር፣ ሁለቱ ምራቶችዋ ዖርፋና ሩት፣ ‹‹ከአንቺ አንለይም፤ አብረንሽ ወደ አንቺው አገር እንሄዳለን›› ብለው ተነሡ። ኖኃሚን ግን፣ እንዲህ አለቻቸው፤ "ከአሁን በኋላስ፣ ተመልሳችሁ ከቤተ-ሰባችሁ ጋር ኑሩ፤ ለእኔና ለሞቱት ባሎቻችሁ መልካም ነገር እንዳደረጋችሁ፣ እግዚአብሔር ለእናንተም እንዲሁ መልካም ነገር ያድርግላችሁ››። ከዚያን በኋላ፣ ኖኃሚን ለመሰናበት ስትስማቸው፣ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ተላቀሱ። ኖኃሚን እንደ ገና እንዲህ አለቻቸው፣ ‹‹ከእኔ ጋር የምትሄዱ ለምንድን ነው?!›› አሁንም እንደ ገና ከተላቀሱ በኋላ፣ በተለይ ዖርፋ የተባለችው፣ ኖኃሚንን ስማ በመሰናበት ወደ ኋላ ተመልሳ ሄደች። ሩት ግን፣ ኖኃሚንን እንዲህ አለቻት፤ ‹‹በፍጹም አታከላክይኝ፤ እኔ ከአንቺ ጋር አብሬሽ እንድሄድ ብቻ ፍቀጂልኝ፤ ሕዝብሽ ሕዝቤ፣ አምላክሽ አምላኬ፣ አገርሽ አገሬ፣ መቃብርሽ መቃብሬ ይሆናል። ከሞት በቀር ከአንቺ የሚለየኝ የለም፤ ብለይሽ እግዚአብሔር ይጣለኝ››። ከዚህ በኋላ፣ ሁለቱም ጕዞዋቸውን ቀጥለው ወደ እስራኤል ምድር ገቡ። እዚያም እንደ ደረሱ፣ ኖኃሚንን የሚያውቋት ሰዎች ሁሉ ተገርመው፣ ‹‹በእውነት ይህቺ ኖኃሚን ናትን?!›› አሉ። እርሱዋም መልሳ፣ ‹‹ሁሉን የሚችል አምላክ ሕይወቴን መራራ ስላደረገው፣ ‹‹ማራ በሉኝ እንጂ ኖኃሚን አትበሉኝ፤ ከአገሬ ስወጣ ብዙ ነገር ነበረኝ፤ እግዚአብሔር ግን ባዶ እጄን እንድመለስ አድርጎኛልና›› አለቻቸው። ኖኃሚንና ሩት ወደ እስራኤል ምድር የመጡበት ወራት የገብስ መከር እየተሰበሰበ የሚገባበት ወቅት የተጀመረበት ጊዜ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

**፪/2 : ሩት በቦኤዝ እርሻ ለቃርሞሽ ተሠማራች** ፡-7 ሩት በቦኤዝ እርሻ ቃርሞሽ ስትቃርም ውላ፣ ያገኘችውን እህልና ከቀን ምሳ የተረፋትን ምግብ ማታ ወስዳ ለኖኃሚን በመስጠት ትረዳት ነበር። ሩት፣ እህል የምትቃርምበትን ምክንያት፣ አገልጋዮቹ ለቦኤዝ ነገሩት። ቦኤዝም እንደ ልብዋ እንድትቃርም፣ ከነዶው የሚዝረከረከውን ሁሉ ሠራተኞቹ ለእርሱዋ እንዲተውላት፣ ወደ ሌላ እርሻ ሳትሄድ፣ ከእርሱ እርሻ-ብቻ እንድትቃርም ነገራት። በምሳም-ጊዜ በአጠገቡ ተቀምጣ ከወጭቱ ወጥ አብራ እያጠቀሰች እንድትበላ ያደፋፍራት ነበር።

**፫/3 : ኖኃሚን ከራሱዋ ይልቅ ለሩት ያደረገችው ወሮታ፡**

1-4 ፡ ቦኤዝ በዋርሳነት ከሩት ይልቅ ለኖኃሚን ይቀርብ ነበር። ነገር ግን፣ ኖኃሚን ሁኔታውን ለሩት አመቻችታ፣ የዋርሳነቱ ባለ መብት እንድትሆን፣ እንዲህ ስትል መከረቻት፣ ‹‹ቦኤዝ የቅርብ ዘመዳችን እንደ ሆነ ነግሬሽ ነበር፣ ዛሬ ማታ ገብስ ይወቃል። ስለዚህም ሰውነትሽን ታጠቢ፤ ሽቶ ተቀቢ፤ የክት ልብስሽን ልበሺ፤ እርሱ ገብስ ወደሚወቃበት አኣውድማ ሄደሽ፤ እራቱን እስከሚበላና እስከሚጠጣ ድረስ በፊቱ ቀርበሽ አትታዪ። የት እንደሚተኛ ካወቅሽ በኋላ፣ እንቅልፍ ሲወስደው፣ ቀረብ ብለሽ ከግርጌው በኩል ልብሱን ገልጠሽ በእግሩ አጠገብ ተኚ፤ ስለ ጋብቻ ጉዳይ መደረግ የሚገባውን ሁሉ እርሱ ራሱ ይነግርሻል››።

5-18 ሩትም እንደ ተመከረችው አድርጋ፣ በእግሩ ሥር ተኝታ ሲያገኛት፣ ‹‹አንቺ ማነሽ?›› አላት። እርሱዋም "ጌታዬ ሆይ፣ እኔ አገልጋይህ ሩት ነኝ፣ አንተ ለሞተው ባሌ የቅርብ ዘመዱ ስለ ሆንህ በዋርሳነት-ልትቀበለኝ ይገባሃልና የኑሮ ጓደኛ እንድትኾነኝ እፈልጋለሁ›› አለችው።ቦኤዝም እንዲህ አላት፤ ‹‹እግዚአብሔር ይባርክሽ፤ ከዚህ በፊት ለአማትሽ ካደረግሽው የሚበልጥ ቤተ-ሰባዊ ታማኝነትን አሳይተሻል፤ ከእንግዲህ ወዲህ በምንም ነገር አታስቢ፤የከተማው ሰው ሁሉ የአንቺን መልካምነት ያውቃል፤ የምትፈልጊውን ሁሉ አደርግልሻለሁ፤ እኔ ለአንቺ የቅርብ ዘመድ መሆኔ እውነት ነውና። ነገር ግን፣ ከእኔ ይልቅ በጣም ቅርብ የሆነ ሌላ ዘመዳችን አለ፤ እስኪነጋ እዚሁ ቆዪ፤ ሲነጋ ያ ሰው ስለ አንቺ ኀላፊነትን እንዲወስድ በሽማግሎች አስጠይቀዋለሁ። 'እምቢ፡ አይሆንልኝም' የሚል ከሆነ እኔ ኀላፊነቱን እወስዳለሁ፤ ይህንንም በሕያው እግዚአብሔር ስም እምልልሻለሁ››። ከመንጋቱ በፊት፣ ስድስት መስፈሪያ ገብስ በነጠላዋ አስይዞ አሰናበታት። ተመልሳ ሄዳ ለኖኃሚን ስትነግራት፣ ‹‹ ይህ ሁሉ ወደ



ምን እንደሚያመራ ታያለሽ፤ በትዕግሥት ጠብቂ፤ ቦኤዝ ይህን ጉዳይ፣ ዛሬውኑ ወደ ፍጻሜ ሳያደርስልሽ ከቶ አያርፍም›› አለቻት።

**፬ /4 : ቦኤዝ ሩትን ለማግባት ኀላፊነቱን ተረከበ** ፡-

_12 ሩትን በዋርሳነት እንዲረከብ ቅድሚያ ተሰጥቶት የነበረው የቅርብ ዘመድ፣ርስቱን እንደሚቤዥ ከገለጠ በኋላ ሩትን በዋርሳነት ማግባት ከአቅሜ በላይ ስለሚሆንብኝ፣ ኀላፊነቱን አንተው ውሰድ" ብሎ በከተማው ሽማግሎች ፊት ተናገረ፤ ቦኤዝም በሕጉ መሠረት፣ ሩትን በዋርሳነት ለማግባት ፈቃደኛ መሆኑን ገለጠ። በአደባባይ ተቀምጠው የነበሩት የከተማውም ሽማግሎች፣ እንዲህ ሲሉ መረቁት፤ ‹‹እንግዲህ እነሆ፣ እኛ ለዚህ ጉዳይ ምስክሮች ነን፤ እግዚአብሔር ይህችን ሚስትህን ለያዕቆብ ብዙ ልጆች እንደወለዱለት፣ እንደ ልያና እንደ ራሔል ያድርግልህ፤ እግዚአብሔር በኤፍራታ ያበልጽግህ፤በቤተ-ልሔም ዝነኛ ያድርግህ፤ከዚህች ውብ ወጣት የሚሰጥህን ልጆች ይባርክልህ፤ ቤተ-ሰብህን ከይሁዳና ከትእማር እንደ ተወለደው እንደ ፋሬስ ቤተ-ሰብ ያድርግልህ››።

23 ቦኤዝም በዚህ ሁኔታ ሩትን አግብቶ፣ ወደ ቤቱ ወሰዳት። እርሱዋም ወዲያውኑ ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደችለት። 14--15 የጎረቤት ሴቶችም ኖኃሚንን እንዲህ አሏት፤ ‹‹የሚጦርሽ የልጅ-ልጅ ስለ ሰጠሽ እግዚአብሔር ይህን ልጅ በእስራኤል ዝነኛ ያድርገው፤ምራትሽ-በጣም-ትወድሻለች፤ሰባት-ልጆች-ከሚያደርጉልሽ-የበለጠ-አድርጋልሻለች፤አሁን ደግሞ፣ ሕይወትሽን የሚያድስልሽና በእርጅናሽ ወራት የሚጦርሽን ወንድ ልጅ ወልዳልሻለችና››። 16--17 ኖኃሚንም፣ ያን ሕፃን ልጁዋ አድርጋ አቀፈችው፣ ተከባክባም አሳደገችው። የጎረቤት ሴቶች፣ ልጁን፣ ‹‹ኢዮቤድ›› ብለው ስም አወጡለት። የንጉሥ ዳዊት አባት የኾነውን እሴይን የወለደ ይኸው ኢዮቤድ ነው።

***( ትርጓሜ፡*** *ሩት የስምዋ ትርጒም ውቢት (ቈንጂት) ማለት ነው። እንግዲህ፣ ሩት ለአማቱዋ ለኖኃሚን ፍጽምት ታማኝ ሆና በመገኘት፣ ‹‹ሕዝብሽ ሕዝቤ፣ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል›› ስትል የተናገረችው ቊርጥ ውሳኔ፣ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ ተስፋ- ትንቢት ለተነገረለት መሲሕ (ክርስቶስ) የዘር ግንድ ስሙ መነሻ ለሆነው ለዳዊት ቅድመ አያት የሆነ ልጅ ለመውለድ አብቅቶአታል (ማቴ.1፡ 5 ) ።*

*_ባል ሞቶባት፣ ከርስት-ጉልት ተነቅላ፣ ከቤተ-ሰብነት ወጥታ*



www.ethiopianorthodox.org

ተስፋ-ቢስ ከርታታ የኾነችውን ሴት በዋርሳነት ሕግ መዋጀት ወይም ቤዛ፣ ጥላና ከለላ ሆኖ ወደ ቤተ-ሰብነት መልሶ ማቋቋም ራሱ፣ ከማኅበረ መላእክት ተለይቶ ከርስቱ ከገነት ወጥቶ የተሰደደ አዳምን የዋጀውንና ወደ ቀደመ ክብሩ የመለሰውን የመሲሑን (የክርስቶስን) ቤዛነት የሚያመለክት ምሳሌ ነው። ሩት ከሀገሩዋ ወጥታ፡ ከቤተ-ሰብ ተለይታ፣ አማቱዋን ኖኃሚንን ተከትላ ወደማታውቀው አገርና ወደማታውቀውም ሕዝብ ስትጓዝ፣ ከምንም ዓይነት ጥቅም ጋራ በተያያዘ መልኩ አልነበረም። የተከተለቻት ኖኃሚንም ምንም ዓይነት ተስፋ ያልነበራት፤ ባልዋንና ሁለት ወንዶች ልጆችዋን ለሰው አገር አፈር በመገበር፣ ያላትን ንብረት ሁሉ አጥታ፣ ባዶ እጅዋን ስትመለስ የምትገባበት ቤት፣ የምታዝበት ሀብት-ንብረት እንዳልነበራት ታውቅ ነበር። ከዚህ አንጻር ሲታይ፣ ክርስቶስንም የመከተል ሁኔታ፡ እንደ ሩት ከምንም ዓይነት ምድራዊና ዓለማዊ የቍሳቁስ ወይም የገንዘብ ጥቅም ጋር ያልተያያዘ፣ ቍርጥ ውሳኔ ማድረግን ይጠይቃል ማለት ነው (ሉቃስ 9፥ 52–62 ) ።

_ሩት የምታውቀው አንድ ዋና ነገር፣ አብራት ለመሄድ የተማጠነቻት እስራኤላዊት ሴት፣ ምንም እንኳ ለጊዜው ሆድ የባሳት ከርታታ ድኻ ብትሆንም፣ በኋለኛው ዘመን፣ የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ፣ ዓለምን ለማዳን ይመጣ ዘንድ ተስፋ-ትንቢት የተነገረለት፣ ታላቁ-መሲሕ (ክርስቶስ) በረድኤት የሚጐበኘው፣ የአንድ ታላቅ ሕዝብ ዜጋ መሆንዋ ብቻ ነበር። ስለዚህም፡ ‹‹አምላክሽ አምላኬ ይሆናል›› በሚል ቍርጥ ውሳኔ፣ የጀመረችው ጕዞ መጨረሻው ያማረና የሠመረ ሆኖላት፣ ያልጠበቀችውን ታላቅ ጸጋና በረከት እንዳስገኘላት፣ ከተጻፈላት ታሪክ መገንዘብ ይቻላል። በዚህም ዓይነት ሁኔታ፣ ቍርጥ ውሳኔ አድርገው፣ ሩት እንዳደረገችው፣ ሁሉን ነገር ትተው፣ ክርስቶስን የሚከተሉ ሰዎች ሁሉ፤ በዚህ ዓለመ-ሥጋም ሆነ ወይም በሚመጣው በአዲሱ ዓለመ -ነፍስ-የሚያገኙት-እንጂ፡ የሚያጡት አንዳች ነገር የለም ማለት ነው ( ማቴ.19፡ 27--=30 ) ።'

## ልዩ ማስታወሻ

_ከዚህ የሚከተለው ትምህርታዊ የትርጕም ትንታኔ፣ የመጽሐፈ ሩትን ታሪክ ከሐዲስ ኪዳን ትምህርት ጋራ በማቀናጀት፣ ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት ሊቁ ቅዱስ ባስልዮስ ዘቂሣርያ (330-79) ጽፎ ያስተማረው ቃለ-ስብከት



(Homily) ሲሆን፣ ይህንኑ የተሟላ ትርጕምና ልዩ መልእክት ያለውን ትምህርት-ሰጭ ትንታኔ፣ ማኅበረ ቅዱሳን ‹‹ሐመር›› በተሰኘ መጽሔቱ ከአሰራጨው ከመጋቢት- ሚያዚያ 1993 ወር እትሙ በመጥቀስ ተጨማሪ ማስረጃ አድርገን እንደሚከተለው አቅርበነዋል።--

_ሩት ሥራን ባለመናቅ፣ የባልዋ የቅርብ ዘመድ ወደ ሆነው ወደ ባለጸጋው ቦኤዝ እርሻ ተሰማራች። ቦኤዝ የመድኀኔ-ዓለም ምሳሌ ነው። የስሙ ትርጕም፣ ‹‹ብርታት፣ መስማማት፣ ኀያል፡ ባለ-ጸጋ ማለት ነው። ቦኤዝ በእርሻው ሠራተኞችን አሰማርቶአል። ምእመናንን እንደ ሠራተኞ፡ የወንጌል መምህራንን ደግሞ ሥራ ኃላፊዎች አድርጎ ዓለም ተብላ በምትጠራ እርሻው ያሰማራ ጌታችንም ድንቅ፣ መካር፡ 'ኃያል አምላክ›› ነው (ኢሳ 9፡ 6 ) ፡ ሩት ሁሉን ነገር ትታ መጣች ፡ ሁሉ ነገር ካለው አምላክ እርሻ ውስጥ ተሰማራች፤ የራስዋን ተወች፡ የእግዚአብሔርን ብልጽግና ፍለጋ ተሰማራች። የተሰማራችበት ሥራ አድካሚ፣ አሰልቺና አስቸጋሪም ነበር፤ እርሱም የቃርሞሽ ሥራ ነበር። መቃረም ማለት ገበሬዎች እህል ሲያጭዱ እያዝረከረኩ ያለፉት ቅንጥብጣቢ የእህል ቅሪት መልቀም ማለት ነው።

_በኦሪቱ ሕግ፣‹‹ቃርሚያ(ቃርሞሽ)-ለስደተኞች፣ለድሃ-አደጎችና-ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ( ለመበለቶች ) ይሁን›› (ዘዳግ 24፥19-22) ተብሎ ስለ ታዘዘ፣ ገበሬዎች ቃርሚያውን ይተውላቸው ነበር። እንግዲህ በቃርሞሽ ቦታ፣ ከላይ ዋእየ-ፀሐይ፣ ከታችም ረሞጫ አለ። ሩት ወደ ቤተ ልሔም ስትገባ፣ ሁሉ በእጅዋ፣ ሁሉ በደጅዋ ተመቻችቶ አልጠበቃትም፤ ብርቱ ትግልና ድካም ነው የጠበቃት። ነገር ግን፣ ሁሉን ነገር ያለምሬትና ያለመሰልቸት ተወጣችው። የአጫጆቹ አዛዥም ሳይቀር፣‹‹ከማለዳ ጀምሮ እስካሁን ስትሠራ ጥቂት ጊዜ እንኳ አላረፈችም›› ሲል ነው የመሰከረላት። _አንዳንድ ሰዎች፣ ወደ መንፈሳዊ ሕይወት ሲመጡ፣በአንድ ቀን የሚለወጡ ይመስላቸዋል፤ ከአሁን በኋላም፣ ምንም አይነት ፈተና ወይም ችግር የማይገጥማቸው፣ ሁሉም ነገር ባሰቡት መልክ የሚቃናላቸው፣ መንገዱም ሁሉ አልጋ-በአልጋ-ሆኖ የተመቻቸ መስሎ ይታያቸዋል፣ ሌሎች ደግሞ፣ በማመናቸው ብቻ፣ በጸሎት፣ በጾም በማስቀደስ፣ ራስን በመግዛት፣ ገድል-ትሩፋት መፈጸም የቀረላቸው ይመስላቸዋል። እውነቱ ግን ይህ አይደለም። የእስራኤል-ዘነፍስ ምሳሌ የሆኑት እስራኤል-ዘሥጋ ወደ ከነዓን የገቡት በተጋድሎ ነው። በዘመነ-ዕዝራና ነህምያ ሕዝበ-እስራኤል ከፋርስ (ባቢሎን) የተመለሱት በተጋድሎ ነው። ለዚህ ነው፣ ቅዱስ ጳውሎስ፣ ‹‹ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልጋል›› በማለት ያስተማረው (የሐዋ ሥ 14፡ 22 ) ። ወደ እግዚአብሔር መጣን ማለት፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን ቀረብን ማለት፣ መማርና ማስቀደስ፣ መጾምና መጸለይ ማለት ዓለምን ድል አድርገን አክሊል ተዘጋጀልን ማለት አይደለም፤ ተጋድሎ ገና ጀመርን ማለት ነው እንጂ። ዓለምን ለማሸነፍ ኀይል ያስፈልጋል፤ ያም ኀይል የሚገኘው ደግሞ፣ በድካም ነው ‹‹ስደክም ያን ጊዜ ኀይለኛ እሆናለሁ›› እንዳለ



www.ethiopianorthodox.org

ሐዋርያው ( 2 ቆሮ 12፡10 ) ። ሩት ያለ እረፍት ተጋች፣ እኛም የምንሻውን ሁሉ ለማግኘት ያለ ዕረፍት እንትጋ፣ ጥቂት ድል አገኘን ብለን አንዝናና፤ ጥቂት ሠራን ብለንም አንሰልች፤ የዕረፍት ጊዜ እስኪሰጠን- ድረስ እንጋደል። ቅዱሳን_አበውም፣ እግዚአብሔር-ዕረፍት እስኪሰጣቸው ሳያርፉና ሳይሰለቹ ደከሙ፤ ኃይልና ጸጋ ያለ ድካም እንደማይገኝ አውቀዋልና።

_ቦኤዝ ምስክርነትን ከአዛገሮች አለቃ ተቀበለ፤ እግዚአብሔርም ስለ እኛ የቅዱሳንን ምስክርነት ይሰማል፣ የጠባቂ መልአክን ምስክርነት ያዳምጣል (ኢዮብ 33፡ 23 -25)። ሩት ወደ ሥራዋ ስትሰማራ ቃርሚያ ለመልቀም እንጂ፣ ስለ ራስዋ ለማንም አልተናገረችም፤ ማንነትዋን ሥራዋ መሰከረላት፤ በአጠገብዋ ያልነበረው ቦኤዝ እንኳ፣ ‹‹ባልሽ ከሞተ በኋላ፣ አባትሽንና እናትሽን፣ የተወለድሽበትንም አገር ትተሽ፣ ቀድሞ ወደማታውቂው ሕዝብ መጥተሽ፣ ለአማትሽ ያደረግሽውን መልካም ነገር ሁሉ ሰምቻለሁ›› ነበር ያላት (ሎ 2። 11 ) ።

_ከፍሬዋ ታወቀች፤ ሥራዋ መሰከረላት፤ ብርሃንዋ በሰው ፊት በራ፤ እርስዋ አልተናገረችም፤ የሠራተኞች አለቃና ቦኤዝ መሰከሩላት እንጂ። እንደዚሁም ሁሉ፣ ቅዱሳን ስለ ራሳቸው ክብርና ዝና ተናግረው አያውቁም፤ ሌሎች ቅዱሳንና እግዚአብሔር ራሱ ግን ይመሰክሩላቸዋል። ሩትማ፣ ስለ ራስዋ፣ ‹‹እኔ እንግዳ ነኝ›› ነበር ያለችው ( ምዕ 2፡10። የቅዱሳንም ጸሎት፣ ‹‹ወነግድ ከመ ኵሉ አበውየ - እኔ እንደ ቀድሞ አባቶቼ እንግዳና አልፎ-ሂያጅ መንገደኛ ነኝ›› የሚል ነው።‹‹ከአገልጋዮችህ እ ንደ አንዱ ልታደርገኝ ፈቀድህን?›› ብላ ነበር የተደሰተችው፤‹‹ለምን ባለሟልህ አላደረግሽኝም?!›› ብላ ቅር አልተሰኘችም። ሩት የእምነት፣ የተስፋና የፍቅር መገኛ ብቻ አይደለችም፤ እነዚህን ሁሉ አስተባብሮ የያዘ ሰው የሚያገኛቸው ታዛዥነትና ትሕትናም ነበሯት እንጂ። በማታውቀው አገር ለአማትዋ ቃርሚያ ለመልቀም ተሠማርታ፣ የምታገኘውን ጸጋ ሁሉ በትሕትና፣ እጅ በመንሣት ትቀበለው ነበር። በቦኤዝ ፊት በግንባርዋ ተደፍታ፣ ‹‹እኔን በደግነት ለመቀበል በምን ነገር በፊትህ ሞገስን አገኘሁ?›› ነበር ያለችው ( ምዕ 2፡ 10)። ይገባኛል አላለችም፤ አይበቃኝም ብላም አልተከራከረችም። ላገኘችው መልካም ነገር ሁሉ በትሕትና ታመሰግን ነበር።

_ጕበዛዝቱ አጫጆች ሩትን ከቀዱት ውሃ፤ ‹‹ጠጪ›› አሏት። አዎ፣ ከዓለም ስንመለስ ነፍሳችን ተጠምታ ነው የምትገኝ እርካታን ትሻለች፣ ነፍሳችን ትረካ ዘንድ፣ የሕይወትውኃ ምንጭ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል ያስፈልጋታል (ዮሐ-4፥ 14) ። ሩት ወንዝ ወርዳ አልቀዳችም፤ ጕበዛዝቱ ቀዱ፤ እርስዋ ግን ጠጣች። ገበሬዎች ዘሩ፤ አጫጆች አጨዱ፤ ሩት ደግሞ ሰበሰበች። አልዘራችም፤ አላጨደችምም፤ ነገር ግን ሰበሰበች። ወንጌል እንዲህ ይል፣ ‹‹አንዱ ይዘራል፤ ሌላው ያጭዳል፤ እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኳችሁ፤ ሌሎች ደከሙ፤ እናንተ በድካማቸው ገባችሁ ( ዮሐ 4፡ 38 ) ።



_ጕበዛዝቱ አበው እጅግ ደከሙ፤ የእምነትን እርሻ አርሰው የጥበብና የጸጋ መከር አፈሩ፤ ዛሬ እኛ በድካማቸው ገብተን፣ እነርሱ የጻፉዋቸውን መጻሕፍት እናነባለን፤ ለመዳን፣ እኛም የምንፈጽመው የሥራ ድርሻ አለ፤ ለምሳሌ በነጻ የሚዘንምልንን ዝናም ለመቀበል ምድሩን አለስልሰን፣ አርሰን መጠበቅ ይኖርብናል። በየቀኑ የሚወጣውን የፀሐይ ብርሃንም ሆነ ሙቀቱን ለመቀበል ወደ ውጭ ወጥተን ፀሐይ በሚደርስበት ቦታ መገኘት ያስፈልጋል። "ገንፎ ከሰማይ ቢዘንምላቸው እንኳ ሳህን ይዘው መቀበል የማይችሉ ሰነፎች አሉ" እንደሚባል የተዘረጋውን የእግዚአብሔር የጸጋ ስጦታ መቀበል አለመቻል ታላቅ ድክመት ነው። ሩት በማረስና በመዝራት ያልደከመችበትን ቃርሞሽ ለማግኘት ወደ እርሻው መሄድና ለመልቀም መቻል ነበረባት። ነገር ግን፣ የቱንም ያህል ተጋድሎ ብናደርግ፣ ክርስቶስ ለእኛ ከከፈለው መሥዋዕትነት ጋር ሲነጻጸር፣ በውቅያኖስ ውስጥ እንደ አንዲት ጠብታ የሚታይ ነው። እዚህ ላይ ጣልቃ በማስገባት የአንድ ትምክሕተኛውን ባሕታዊ አጭር ታሪክ እንጥቀስ፡

"ከትምክሕተኛው ባሐታዊዉ ይልቅ የደጉ አገልጋይ ቅንነት"

በአንድ ገዳም ውስጥ ለሚኖሩ አበው መነኮሳት ተላላኪ፡ የጽዳት ሠራተኛ፣ ምግብ አብሳይ፡ ንፍሮ ቀቃይ፡ እግሪ አጣቢ፡ ኵንታል እህል ተሸካሚ፡ ፈረስ ለጓሚ፣ ልብስ ሰፊ፡ ሆኖ ለገዳሙ መነኮሳት በሚያስፈልጋቸው ነገር ሁሉ ፡ "በመላላክ የሚያገለግልም ቢሆን በአገልግሎቱ ይፅና" ተብሎ በሮሜ 12.. 7፡ እንደተጻፈ ባጭር ታጥቆ የሚሠራ ትሑት አገልጋያቸው ነበር። የስሙ አጠራር በሐዋርያው ጴጥሮስ መጀመሪያ መልእክት 4. 10 “ተለአኩ ከመ ላእክ ኄር=እንደ ደግ አገልጋይ ሁኑ” ተብሎ ከተጻፈው ቃል ተወስዶ “ደጉ አገልጋይ” የሚል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በዚያ ገዳም ዐርባ (40 ) ዓመት ሙሉ ዘግቶ በጾምና በጸሎት ጥሬ ሽንብራ እየቆረጠመ በብሕትውና የኖረ፡ አንድ ተመጻዳቂ ዝጉኃዊ፡ ባሕታዊ፡ ከብቃት ደረጃ የደረሰ ቅዱስ አባት ነው” ተብሎ ይታሰብ ነበር።

_ገዳሙ በታላቅ ደረጃ የሚያከብረው አንድ ዓመታዊ በዓል ደርሶ ስለነበር የገዳሙ አስተዳዳሪ ይህን ባሕታዊና ደጉን አገልጋይ ጠርቶ “ለምናከብረው ዓመታዊ በዓል የምንግጕዘጕዘው ቂጠማ ቆርጣችሁ አምጡልን” ብሎ ያዛል። ሁለቱም ተነሥተው ቄጠማ ወደሚገኝበት ስፍራ አብረው ሲሄዱ ባሕታዊዉ በሐዘን በትካዜ ላይ ነበር። ያዘነበትም ምክንያት “እኔ ዐርባ ዓመት ሙሉ በዋሻ / ጎጆ ውስጥ ዘግቼ ስጸልይ የኖርሁ ንጹሕ ድንግል ባሕታዊ ነኝ። ይህ ከእኔ ጋር የሚሄደው ሰው ደግሞ ስለ ጾምና ጸሎት፡ ስለብሕትውና ሕይወት፡ ስለምንኩስና ሥርዓት ባጠቃላይ ስለ ገዳማዊ ሕይወት ምንም ነገር ሳያውቅ የገዳሙን መነኮሳት እግር እያጠበ ፡ ልብሳቸውን እያፀዳ፡ ምግባቸውን እያሰናዳ፡ ሲጠሩት አቤት፡ ሲልኩት ወዴት ?' በማለት ሲባክን የሚኖር ሥጋዊ ሰው ነው። ታዲያ አርባ ዘመን ዘግቼ የኖርሁ እኔን ያህል ሰው እንዴት ከዚህ ተራ መሐይምን ጋር ይልኩኛል?” እያለ በማዘንና በማማረር ላይ ነበር ።



www.ethiopianorthodox.org

_ቄጠማ ከሚቆረጥበት ቦታ ሲደርሱ የከባድ ዝናም ወራት ስለነበረ በጎርፍ ተጥለቅልቆ ጥልቅ ባሕር ሆኖ አገኙት። ደጉ አገልጋይ ግን ሰተት ብሎ ወደ ባሕሩ በመግባት ልክ ጌታችን አምላካችን መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ በጥብርያዶስ ( በገሊላ ባህር ) እንዳደረገው በደረቅ ምድር እንደሚራመድ ሰው በባሕሩ ላይ እየተረማመደ ቄጠማውን ማጨድ ጀመረ። ተመጻዳቂው ባሕታዊ ግን ወደ ባሕሩ ለመግባት ሲጀምር ሰማይና ምድር ስለዞረበት ደንግጦ በባሕሩ ዳርቻ ቆመ። ደጉ አጋልጋይ "አባቴ ና እንጂ ለምን ትፈራለህ ? እምነት ያለው ሰው እኮ መፍራት የለበትም" በማለት በትሕትና እያነጋገረው፡ ለገዳሙ በዓል የሚያስፈልገውን ቄጠማ ቆርጦ ሁለት ሸክም አምጥቶ በባሕሩ ዳር ከመረ። ባሕታዊዉም እጅግ ተገርሞ በመደነቅ፡ በደጉ አገልጋይ ጫማ ላይ ወድቆ "ወዳጄ ይቅር በለኝ፡ እኔ የእግዚአብሔርን ጸጋ ሳላውቅ አንተን እንደ ተራ ሰው በመቍጠር እንቅህ ነበር። ለካስ ከእኔ ይልቅ አንተ ተባርከህ ከዚህ የብቃት ደረጃ መድረስህን አላወቅሁም ነበር" አለ። "ናሁኬ ኢኮነ ለዘሮፀ ወለዘበደረ፡ አላ ለዘ እግዚአብሄር ምህሮ =ለሮጠና ለቀደም አይደለም፡ እግዚአብሔር የምሕረት ጸጋውን ላበዛለት ነው እንጂ" ( ሮሜ 9 ፡ 15 -16 ) ። ( ከሐመር መጽሔት ትምህርታዊ ትንታኔ እዚህ ላይ ቀጥሏል)

_ሌሎች ዘርተው ያበቀሉትን ከመቃረም፣ ቀድተውም ያስቀመጡትን ውሃ ከመጠጣት ያለፈ አይደለም፡፡ ነገር ግን፣ ይኸው እንኳ አድክሞን የቀረን ስንቶች ነን? _ትጋት ያላት ሩት፣ በምሳ ሰዓት ደግሞ፣ ታላቁን ስጦታ አገኘችው፡፡ ከጌታዋ ማዕድ ትበላ ዘንድ ተፈቀደላት፡፡ የሰማያዊ አባታችን ማዕድ የጌታችን ሥጋውና ደሙ፣ የእግዚአብሔር ጸጋና በረከቱም ነው፡፡ ይህ የማዕከላዊነት ደረጃ ነው፡፡ በልታም ጠገበች፤ አተረፈችም፤ በረኀብ ለደከመች ለአማትዋ አተረፈችላት፡፡ አዎ፣ ወደ እግዚአብሔር ማዕድ ስንቀርብ እናተርፋለን፤ ለእኛ ብቻ አይደለም፣ "በመላላክ የሚያገለግልም ቢሆን በአገልግሎቱ ይፅና" ተብሎ በሮሜ 12.. 7፡ ተጽፏል፡፡ ለሌሎችምና ለልጆቻችን፣ ለጓደኞቻችን፣ ለወገኖቻ ችን፣ ለተማሪዎቻችን ማትረፍ ይጠበቅብናል፡፡ ከማዕዱ በኋላ፣ ቦኤዝ ጐበዛዝቱን አጫጆች፣ ‹‹በነዶው መካከል ትቃርም፤ አታሳፍሯት፤ ከነዶው ተውላት፤ እርስዋም ትቃርም›› (ምዕ 2፡ ቍ 16) ብሎ አዘዘላት፡፡

_ሩት በመጀመሪያ እንድትቃርም ብቻ ነበር የተፈቀደላት፤ አሁን ግን፣ ያፈሱላት ዘንድ አዘዘላት፤ ከበፊቱ ይልቅ፣ የአሁኑ ድካምዋ ቀነሰ፤ ጸጋው በዛላት፡ ፡ ወገኖች ሆይ ተመልከቱ፤ ወደ እግዚአብሔር በቀረብን ቍጥር፣ እንደዚህ ጸጋው እየበዛልን ይሄዳል ማለት ነው፡፡ የክርስትና ጉዞ እንደዚሁ በየዕለቱ፣ ከድል ወደ ድል፡ ከኃይል፣ ወደ ኃይል፡-ከጸጋ ወደ ጸጋ፣ከክብር ወደ ክብር-መሸጋገሪያ ነው፡፡ ለዚህም ነው-በቅዱሳን ታሪክ-መካከል አናብስት የታዘዙላቸው(ዳን 6፡18) ፡፡ _ቍራዎች ምግብ ያመላልሱላቸው ዘንድ የታዘዙላቸውም ነበሩ -1 ነገ 17፡`2 )፡፡ ዳሩ ግን፣ ይህ ሁሉ ጸጋ እያላቸው ጸሎትና ተጋድሎ አልቀረላቸውም፡፡ እነሆ፣ ሩት ድካም ተቀንሶላታል እንጂ፣ መሥራት አልቀረላትም፤ ጸጋ በዝቶላታል፣



ስለዚህም፣ ብዙ መቃረም ቻለች፤ የቃረመችውንም አማትዋ ኖኃሚን አየች ( ምዕ 2፡ 18)፡፡ በክርስትና ጉዞ፣ ትልቁ ቁም ነገር መቃረሙ ብቻ አይደለም፤‹‹የት ነው የቃረምነው? ›› የሚል ነው፤ ስለዚህም ነበር ኖኃሚን፣ ‹‹ዛሬ ወዴት ቃረምሽ?›› ስትል ሩትን የጠየቀቻት፡፡ ብዙ ሰዎች ቃለ- እግዚአብሔርን እየተማሩ መሆኑን፣ እየጸለዩና እያገለገሉ መሆናቸውን ገንዘባቸውንም ለመንፈሳዊ አገልግሎት እየሰጡ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ግን ከየት ቦታ? ከማንስ እርሻ?" እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል ከሚነገርባት ከእውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን፡ ታላቁ ሊቅ ቅዱስ ባስልዮስ በደረሰው፣ ‹‹ውዳሴ አምላክ ዘዘወትር›› በተሰኘ የጸሎት መጽሐፉ፣ ነፍሱን እንዲህ ሲል ይጠይቃታል፣ ‹‹ነፍሴ ሆይ፣ በማን እርሻ ሊያውሉሽ ተቃጠሩሽ? ሠላሳ፣ ወይስ ስልሳና መቶ ፍሬ በሚሰጥ በመልካም እርሻ? ወይስ በመንገድ ዳር፣ በጨንጫ ላይ፣ በእሾህና በአሜከላ መካከል ተዘርቶ ያለ ፍሬ በቀረው መከር ? ›› ( (ማቴ 13፡ 18—23 ) ፡፡

_ኖኃሚን ለሩት የነገረቻት ይኸንኑ ነው፡፡ ‹‹ልጄ ሆይ፣ ከገረዶቹ ጋር ስትወጪ በሌላ እርሻ ባያገኙሽ መልካም ነው›› (ምዕ 2፡ 22)፡፡ ኖኃሚን በወለደቻቸው ልጆችዋ ያላገኘችውን ዕረፍት፣ እግዚአብሔር እንደ ልጅ አድርጎ በሰጣት ምራትዋ በኩል አገኘችው ፡፡ አብርሃም እንደ ሥጋ በወለደው በእስማኤል ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር ስጦታ በሆነው በይስሐቅ በኩል በረከትን አገኘ፡፡ወደ እግዚአብሔር ስንመለስ ያጣነውን ነገር ሁሉ ከእርሱ እናገኘዋለን፡፡ምዕ ‹‹ልጄ ሆይ፣ መልካም እንዲሆንልሽ ዕረፍትን አልፈልግሽም›› በቤተ ክርስቲያ መከር የተሰማራን ሁሉ፣ መልካም ይሆንልን ዘንድ፣ ዕረፍትን እናብዛ፤ ደከመን፣ ሰለቸን፣ ታከተን አንበል፡፡ ያለዚያ፣ ጊዜውን ጠብቆ እግዚአብሔር የሚሰጠንን በረከት እናጣዋለን፡፡ ‹‹ኢንትሐከይ ገቢረ ሠናይ እስመ በዕድሜሁ ነአርሮ - ጊዜው ሲደርስ እናጭደዋለንና መልካም ነገር ከመሥራት ቸል አንበል›› እንዳለ ሐዋርያ (ገላ 6፡ 9)፡፡

_ሩት ብትሰለችና ታክተኝ ብላ ሥራዋን ብታቋርጥ ኖሮ፣ ታጣው የነበረውን ታላቅ ጸጋ እንመልከት፡፡ ምዕ 3 ፡‹‹እነሆ፤ ቦኤዝ ዛሬ የወቃውን ገብስ በመንሽ (በላይዳ) የሚያዘራበት ቀን ነው፤ ሰውነትሽን ታጠቢ፤ ሽቱ ተቀቢ፤ የክት ልብስሽን ለብሰሽ ሂጂና ሌሊት እንቅልፍ ሲወስደው፣ ልብሱን ገልጠሽ በእግሩ ሥር ተኚ››፡፡ ይህ የኖኃሚን ትእዛዝ ነው፡፡ ኖኅሚን ለርስዋ የሚገባውን ዋርሳነት ለምራትዋ አሳልፋ መስጠትዋ ያልተጠበቀ ልግሥና ነው፡፡ ቅን ታዛገርቱ ሩትም፣ ‹‹የነገርሽኝን ሁሉ አደርጋለሁ›› አለች ( 3፡ 2--5)፡፡ አዎን፣ እስከ አሁን ድረስ፣ ሩት በተሰጣት ትእዛዝ ስትከራከርና ስታንጐራጕር አልተሰማችም፤ መታዘዝ ከመሥዋዕት እንደሚበልጥ አውቃለች (1ሳሙ 15፡ 22) ፡፡

_ተስፋ ያደረገችው አምላክ የታመነ መሆኑን አውቃለች፡፡ ቦኤዝ ሌሊት ሲነቃ፣ ሩትን እግሩ ሥር ተኝታ ማግኘቱ፣ ጌታ ከትንሣኤው በኋላ፣ እግሩ ላይ ተጠምጥማ ስትሰግድለት የታየችውን ማርያም መግደላዊትን ያሳስበናል፡፡ ቦኤዝ፣ በመንፈቀ- ሌሊት ሲነቃ ሩትን እግሩ ሥር ተኝታ ማግኘቱ፡ ጌታ ከትንሣኤው በኋላ እግሩ ላይ ተጠማጥማ ስትሰግድለት የታየችውን ማርያም መግደላዊትን ያሳስበናል፡፡

ቦኤዝ ለሩት ሦስት ነገሮችን ሰጥቷ`ታል፡ ይኸውም 1. ቡራኬ፡ ልጄ ሆይ ! በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ፡፡‹‹ልጄ ሆይ፣ በእግዚአብሔር የተባረክሽ ሁኚ››



www.ethiopianorthodox.org

2 ቃል ኪዳን፡ ያልሺውን ሁሉ እፈጽምልሻለሁ። 3. የእህል ስጦታ፡ ስድስት መሥፈሪያ ገብስ ሰጥቷል። ይህ የፍጹምነት ደረጃ ነው። ቦኤዝ ስለ ሩት በጎ ምግባር ሲመሰክር፣ «ባለጸጋም ድሃም ብለሽ_የሌላ_እርሻ ጉበዛዝትን አልተከተልሽም፣ጊዜ፣ ለሩት ሦስት ነገሮችን ሰጣት፤ 1. ቡራኬ፣ የሀገሬ ሕዝብ ሁሉ ምግባሬ- መልካም ሴት መሆንሽን አውቀዋል» ሲል ጽናትዋንና ለሥጋዋ ምኞት አለመንበርከኳን ሲገልጥላት፣ ብርሃንዋ በሰው ሁሉ ፊት መብራቱን አሳይቶላታል። ይህንንም ራስዋ አልተናገረችውም፣ ቦኤዝ እንጂ። _«ከፊተኛው ይልቅ፣ በመጨረሻው ጊዜ ቸርነትን አድርገሻል» ( 3፡ 10) ተብሎ ለሩት እንደ ተነገረላት መሆን ሲገባው፣ በመልካም ጀምረን በክፉ፣ በጽድቅ ጀምረን በኃጢአት፣ በእምነት ጀምረን በክሕደት፤ በአገልግሎት ጀምረን በንዝህላልነት፣ በመንፈስ ጀምረን በሥጋ ልንፈጽም አይገባንም (ገላ 3+3)። ከፊተኛው ይልቅ፡ እንደ ሩት የመጨረሻው እንዲሠምርልን ያስፈልጋል። ይህ ደረጃ ቃል-ኪዳን ያለበት መሆኑን፣ «ያልሽውን ሁሉ አደርግልሻለሁ» ከሚለው ቃል መረዳት ይቻላል።ሩት በመትጋትዋና ፍጽምት ታዛዥ ሆና በመገኘትዋ፣ «ሁሉን ነገር አደርግልሻለሁ» ተባለች። በመልካም እርሻ ውስጥ በሥራችን ጸንተን ብንገኝ፣ ሁሉም ነገር ይደረግልናል። ቅዱሳን ያሉት ሁሉ ተደርጎላቸዋል፤ የለመኑትን አግኝተዋል። ሩት እንደ ሌላይቱ እኅትዋ እንደ ዖርፋ፣ በሥጋ መንገድ ተጉዛ ቢሆን ኖሮ፣ ባል አታጣም ነበር፤ ነገር ግን፣ ያ ባል በረከትን አያመጣላትም፤ ዘግየት ብለን የምናየውን ጸጋ አያስገኝላትም ነበር። እርስዋ ግን፣ እንደ መንፈሳዊ ፈቃድ በመታዘዝ ተጓዘች። እግዚአብሔርም የሚበልጠውን ጸጋ ሊሰጣት ቃል ገባላት።

_በወጣኒነትዋ ትቃርም ነበር።_በማእከላዊነት አጫጆች ያፈሱላት ዘንድ ሲታዘዙ ድካም ተቀነሰላት፤ አሁንሳ ? አሁንማ፣ «የያዝሽውን ኩታ አምጥተሽ ዘርጊው» ብሎ ስድስት መስፈሪያ (ቍና ወይም ላዳን) ገብስ ሠፈረላት» (ቍ 15)። ሳትቃርምና ሳትደክም ያገኘችው በረከት ነው። ቀኑን ሁሉ ቃርማ ያን ያህል ያገኘችበት ጊዜ አልነበረም። ስድስት እጥፍ ማግኘት ታላቅ ጸጋ ነው። የእግዚአብሔር ቸርነት ከሰው ሥራ ይበልጣል። በክርስትና ኑሮ ፀንተው እስከ መጨረሻው የተጋደሉ ሁሉ፣ በድካማቸው ከሰበሰቡት ይልቅ፣ እግዚአብሔር በቸርነቱ የሚሰጣቸው ይበልጣል። ስጦታውም በአንድ ቀን ጀምበር የሚገኝ አይደለም። ሩት ያገኘችው፡ እስራኤል እንኳ ያላገኙት በረከት ነው። _በቍርጥ ውሳኔ ተግታ በመሥራት፣ በፍጹም ታዛዥነትም ተስፋ ያደረገችው አምላክ ከቶ አላሳፈራትም። ግን፣ ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ አልሰጣትም። እግዚአብሔር የታመነና ምንም ነገር የማይሳነው መሆኑን አምኖ፣ ለተከተለው ለወዳጁ ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ አፈጻጸም ስንመለከት፣ ለሩትም የተፈጸመላት መልካም ነገር ሁሉ፣ ከእርሱ ጋራ ተመሳሳይነት አለው። ኖኅሚንስ ምን ነበር ያለቻት? «ልጄ ሆይ ! ሰውዮው ይህን ነገር ዛሬ እስኪጨርስ ድረስ አያርፍምና ፍጻሜው እስኪታወቅ ዝም በይ»። ሐዋርያትም፣ እስከ ጌታ ትንሣኤ



«ዝም በሉ ለማንም አትናገሩ» የተባሉበት ጊዜ ነበር ( ማቴ 17፡ 9 ) ።ሂዱና ለአሕዛብ ጅብ ሉ ንገሩ የተባሉበት ጊዜ እስኪደርስ፣ የተወሰነ የዝምታ ጊዜ ነበር ማለት ነው።ምዕ 4፡ (ዘዳግም 25፡ 5) በተጻፈው መሠረት፣ቦኤዝ ከእርሱ ይልቅ፣ ለአቤሜሌክ የሚቀርበውን የቅርብ ዘመድ ፈልጎና አግኝቶ፣ «የወንድማችንን የአቤሜሌክን እርሻ ዋጀው» ሲል ጠየቀው። እርሱም፣ «እሺ፣ እዋጀዋለሁ» አለው። ቦኤዝም፣«ርስቱን ከኑኃሚን በምትዋጅበት ቀን፣ ለሞተው፣ በርስቱ ስሙን እንድታስነሣለት፣ ከምዋቹ ሚስት ከሞዓባዊትዋ ከሩት ዳግሞ ትገዛለህ አለው» ሩትንም አብረህ ማግባት አለብህ» ማለቱ ነው። ሰውዮው ግን፣ «እርስዋን ማግባትስ ከአቅሜ በላይ ስለሚሆን፣ ነላፊነቱን (መቤገርቱን) አንተ ውሰድ» አለው (1-4)። መሬቱን እንጂ ሩትን አልፈለጋትም ማለት ነው። እንግዲህ ዓለም እንደዚሁ ናት፤ የእኛ የሆነውን እንጂ፣ እኛን አትፈልገንም። ውበታችንን፣ ገንዘባችንን፣ ጉልበታችንን፣ እውቀታችንን ትጠቀምበታለች። ከዚያ በኋላ ግን፣ እንደ አሮጌ ቍና ትወረውረናለች። ስለ እኛ የሚያስብ፣ የእኛ ቤዛ-ዓለም፣ ክርስቶስ ብቻ ነው።

## ቦኤዝ የአቤሜሌክን ርስት ዋጅቶ ሩትን አገባት፡

_እንግዲህ ሩት፣ «ሕዝብሽ ሕዝቤ ይሆናል» ብላ መጣች። «ሞዓባዊ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ» (ዘዳ 23፡ 3) የሚለው ሕግ አላገዳትም። ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ገባች። ከአሁን በኋላ ግን፣ የሩት ሞአባዊነት በትውልድ ዘር ብቻ እንጂ፣ በምግባርና በእምነት አለመሆኑ ታወቀ፣ በዚህም ከእስራኤል በልጣ ተገኘች። እኛንም ክርስቲያን የሚያሰኘን፣ በሚያስተምሩን ቃለ እግዚአብሔር፡ በእምነታችንና በሥነ ምግባር፡ትሩፋታችን መጠን እንጂ፣ እግዚአብሔርን ማወቅ የምንችልበትን የቅዱስ መጽሐፍ ቃል ሳያስተምሩን፡ በስም ብቻ ክርስቲያኖች ተብለው ከሚጠሩ ቤተሰቦች በመወለዳችን ብቻ አይደለም።

_ከቅዱሳት መጻሕፍት ተለይተው ራሳቸው ሳይማሩና ልጆቻቸውንም ሳያስተምሩ ከአባይ ጠንቋይና ከቃልቻ ጋር እያጨበጨቡ፡ ጀበና አምላኪዎች ሆነው ከልጆቻቸው ጋር አብረው የሚጠፉ ወላጆች ብዙ ናቸውና ነው ። ይልቅስ እንደ ሩት ከሩቅ የሚመጡ ብዙ ወገኖች አሉ። እኛ ባናውቅበት፣ ከእኛ አስቀድመው የመንግሥት-ሰማያት ወራሾች መሆን የሚችሉ አሉ፤«ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፡ ከአብርሃም፡ ከይስሐቅና ከያእቆብ ጋር በመንግሥተ ሰማይ ይቀመጣሉ፡ የመንግሥት ልጆች ግን፣በውጭ ወዳለው ጨለማ ይጣላሉ' -ማቴ-8+11)።

_ሽማግሎች ቦኤዝን እንዲህ ብለው መረቁት፣ «እግዚአብሔር ይህችን ወደ ቤትኽ የምትገባውን ሴት ባርኮ፣ የእስራኤልን ቤት እንደ ሠሩት፤ እንደ ሁለቱ እንደ ራሔልና እንደ ልያ ያድርጋት (11)፤ «አንተም በኤፍራታ ባለ-ጸጋ ሁን፤ ስምህም በቤተ-ልሔም ይጠራ፣ቤትህም እግዚአብሔር ከዚህች ቈንጆ ከሚሰ **ጥህ ዘር** ትእማር ለይሁዳ እንደ ወለደችለት እንደ ፋሬስ ይሁን»።



www.ethiopianorthodox.org

በመሠረቱ ራሔልና ልያ የዐሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገዶች እናቶች ናቸው። በእምነት ተስባ የመጣች ሞአባዊት ሩትም ከነዚሁ የእስራኤል መሠረት ከሆኑት እናቶች ጋር አብራ ተጠራች። እግዚአብሔር ከሰመነችውና ተስፋ ካደረገችውም በላይ ያልጠበቀችውን እንደ ሰጣት ተመልከቱ።

_ቤተ-ልሔም፣ ዳዊት የነገሠባት ከተማ ናት፤ ኋላም ጌታ ራሱ ተወልዶባታል። የዳዊትም ጥንተ-አያት ቦኤዝ ነው።በኤፍራታ የተጠራ ቦኤዝ በሥጋ የጌታ ጥንተ-አያት ነው። ትእማር የተናቀችና ከአረማውያን ወገኖች የተወለደች ሴት ነበረች፤ ነገር ግን፣ እግዚአብሔር እንደ ሩት አከበራት፤ የጌታችን የዘር ሐረግ የተጠራ በትን ፋሬስን ወለደች (ዘፍጥ 38)። ኖኃሚን ቤተ-ሰብዋን አጥታ፣ ተስፋ የቈረጠች ከርታታ ነበረች ብለናል። አዎ. በረኃብ ምክንያት ቤትዋ ቦዶ ሆኖ ቀርቶ ነበር። በመጀመሪያ ወደ ሞአብ የተሰደደችበት ምክንያት፣ ዘር እንዳታጣ ነበር፤ ነገር ግን፣ የፈራችው አልቀረም፤ የባዕድ አገር፣ ሞአብ ብቻዋን-ከመቅረት አላዳናትም። በገዛ ጥበብዋ ያደረገችው ሁሉ፣ከተስፋ መቍረጥ በቀር ያተረፈላት ነገር የለም። ልክ በዚሁ ዓይነት፣ ሥራና ትምህርት ፍለጋ፣ ባል ወይም ሚስት ለማግባት፣ ልጅ ለመውለድ፣ ሥልጣን ለመያዝ፣ ሀብት ለማግኘት፣ ታዋቂ ለመሆን ሲሉ፣ የዚህን ዓለም መንገድ የሚመርጡ አሉ። ነገር ግን፣ የማግኘት ተስፋቸው ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ የመነመነ ይኾናል፣ አስቀድመው ጽድቅንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ቢሹ ግን፣ የቀረውም ነገር ሁሉ በተጨመረላቸው ነበር (ማቴ 6፡ 33)። ሩት ትታው ከመጣችው በላይ አተረፈች፤ ለእግዚአብሔር ሲሉ ማጣት እጥፍ-ድርብ በረከትን ያስገኛልና። ኢዮብ ስለ እውነት ተፈትኖ ሁሉን አጣ፤ ኋላ ግን በእጥፍ ተቀበለው (ኢዮብ 42፡ 12 )።

_‹‹እግዚአብሔርም ለሩት፡ ልጅ የመፅነስን ዕድል ሰጣት›› ተባለ (4፡ 13 )። የመታዘዝዋ ፍሬ ስለ ሆነ፣ የእግዚአብሔር ስጦታ ነውና። ቦኤዝ ኢዮቤድን ወለደ፡ የኖኃሚን ሐዘን ወደ-ደስታ ተለወጠ።እግዚአብሔር፣ከበለስ እስራኤል ያጣውን ፍሬ ማለት ምግባር -ወሃይማኖት፣ በሩት በኩል ከአረማውያን አገኘ፣ ኖኃሚን ሕፃኑን አቀፈችው፣ ሞግዚትም ሆነችው (4፡ 16)። ጐረቤቶች ኖኃሚንን፣ ‹‹ከሰባት ወንዶች ልጆች ይልቅ ለአንቺ፣ ከምትሻል፣ ከምትወድሽ ምራትሽ ተወልዶልሻልና ሰውነትሽን ያድሰዋል፤ በእርጅናሽም ይመግብሻል›› አሏት (14)። በእርግጥም፣ ከሥጋ-ፍሬ ይልቅ፣ የመንፈስ ፍሬ ሰባት እጥፍ ይበልጣል። እንግዲህ ሩት፣ ‹‹ሕዝብሽ ሕዝቤ፣ አምላክሽ አምላኬ ይሆናል››ያለችው የቍርጥ ውሳኔ-ቃል-ተፈጽሞላት፣ከዘርዐ- እስራኤል ሐረገ ትውልድ-ገብታ-ተቈጠረች፤ ይልቁንም-የነገሥታት-እናት-ሆነች። ቃርሚያ በመቃረም ጀመረች፤የእርሻው ባለቤት የሆነውን ራሱን ባለ-ጸጋውን ቦኤዝን አገባች ። ባዶ ቤትተቀበላት፣ ባለ-ጸጋ ሆነች። በድካም ጀመረች፤ በዕረፍት ፈጸመች። በመታዘዝ ጀመረች፤ በእመቤትነት፡ፈጸመች። በስደተኛነት-ጀመረች፤ በባለርስትነት-ፈጸመች። በእንግ ድነት_ጀመረች፤በባለ-ቤትነት-ደመደመች ‹‹በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ያጭዳሉ /ይሰበስባሉ"_(መዝ 125፡ 5)።



www.ethiopianorthodox.org